አ ዳ ም ረ ታ

# አፍ



# አፍ

(ሥግር ልብወለድ)

አዳም ረታ

© አዳም ረታ - 2010
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የሽፋን ሥዕል - ዮናስ ሚሊዮን

የመጀመሪያ ሕትመት - 2010
አሳታሚና አከፋፋይ፡ ሀሳብ አሳታሚ
ስልክ ቁ. 0936959644/0923797954

(በራሱ ውስጥ ተፃራሪ ወይም 'ተቀናቃኝ መጽሐፍ' ያልያዘ መጽሐፍ እንዳላለቀ ይቆጠራል:: *ሆርግ ሉዊ ቦርገስ* *Tlon, Uqbar Tertius,* from "The Garden of Forking Paths," *1948*)

# መልካ መልክ

፩

●○○○○

## ጌርሳሞት

ቡናማ ፀጉሯን የምትቆረጠው አሳጥራ ነው:: ሁልጊዜም እንደ ረጠበ ጥቁር ብልቃጥ ያብለጨልጫል:: ኩልኩልቷ በመስቀል ጌጥ የፈካ ነው:: ደሞ አንገተ ረዥምም ናት:: ተረከዝ የሌላቸው ጫማዎች ስለምታደርግ ከዕድሜዋ ልጅ ትመስላለች:: ፈርጠክ ያሉ እግሮች አሉዋት:: የሰርክ ጫማዋ ስኒከር፣ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደሞ የምትለብሰው ታይት ሱሪና ቀላል የበጋ ትሬንች ኮት ነው:: ከአንዱ (ከቀሚስ) ወደ አንደኛው (ሱሪ) ለምን እንደተዛወረች የሚገባው ጥቂት ነው:: ከዘነጠች ደሞ የምትለውጠው የጫማዋን ስታይል ብቻ ነው: ጫማዋ ባለአጭር ተረከዝ ኪትን ሂል ይሆናል:: በወንዶች አጠገብ ስታልፍ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሴት ጠረን አልነበራትም:: ምድር የምትሸተው ካፊያ ሲወርድ አይደለም? ጌርሳሞት ላይ ገና ጎረምሳ አልዘነበም፤ አውሎ ሲነፍስባት አይደለም? ጌርሳሞት ላይ ገና ብላቴና አልነፈሰም:: ቅልብጭ ያለች 'ምንም አትል' የሚሏት አይነት ልጅ ናት::

ከሁሉ ልጃገረዶች ጌርሳሞትን የተለየ የሚያደርጋት ቢያንስ በየወሩ አስገራሚ በሆነ መልክ የከንፈሮቿ ማማር ነው: ልክ እንደ ሃር የለሰለሱ፣ ልክ እንደ ቀለማም ኩሬ የሚንተገተጉ፣ ልክ ሊፈነዱ እንደደረሱ የፅጌ እምቡጦች የሚያባቡ ይሆናሉ:: በዚህ ውብ ክስተት ስንቶቹ ተማርከዋል? ቾኩን በቀኝ እጁ ይዞ ፊቱ ከቀረ የሲቪክ አስተማሪ ጀምሮ (ሽፍቱን ጨርሶ ወደ ቤቱ ከመሄዱ በፊት ይህችን ያማረች የእንስት ትዕይንት በዐይኑ ውሃ ለማስገባት) ክፍሏ በር ላይ በሚጠብቃት ሐይለኛ ተማሪ በኩል አድርጎ፣ ለገነት መግቢያ ያዘጋጀው የብፁዕነት ማርኩ ብትቀንስ ግድ እስከሌለው ሌላ ክፍል የሚማር የሆነ የአክራሪ ሃይማኖተኛ ድርጅት አባል ድረስ:: እሷን ያየች 'ከእኔ በላይ ቆንጆ ለአሳር' የምትል የአየር ጤና ፕሬፓራቶሪ ኮረዳ በተዛባ ውድድር አንደኛ የወጣ ፊቷን በቅናት ጋርዳ፣

ድምፅዋንም ዝቅ አድርጋ 'ው-ይ ይይይይ ታድላ' ብላለች፡፡ እና ይሄን ሁሉ አይቶ ወደ ጌርሳሞት አፍ ተጠግቼ ላንቧቧ የሚለው (መፅሐፉ 'አንኳኩ ይከፈትላችኋል' እንዳለው) ደፋሩ ማነው? ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምኗን መንከባከብ እንዳለባት ስለገባት ቦርሳዋ ውስጥ የማይጠፋው በብራዚል ካርናውባ የተቀመመ ላቤላ የከንፈር ሰም ነው፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አፏ ለራሷም ባዕድ ነበር፡ ልክ እንደምትበላው ተልባ ፍትፍት፣ እንደምትጠጣው ጠላ፣ እንደምታደርገው ጫማ፣ እንደ ወረቀቱ፣ እንደ ትምህርት ቤቷ፣ እንደ አውቶቡሱ፣ አባቷ እንደሚነዳው መኪና፡ ከንፈሮቿን የሰጧት ሌሎች ነበሩ፡ እግዚአብሄር፣ ወላጆቿና አድናቂ፡፡ አሁን አሁን ካማሩላት በሁዋላ እየተንከባከበች ልኩራባቸው ትላለች፡፡ ትበል እንጂ ትንሽ ቢመረመሩ የምር ከንፈሮቿ የእሷ አይደሉም (መሰላት እንጂ)፡ ምናልባት የሴት ቅድመ አያቷ ነው፡ በወራሪ ጦረኛ በሆነ አንጋች ተደፍራ ከደፋሪው ደፋር በተደፋሪዋ በኩል የወረሰችው የውርደት ዘረመል ነው፡፡ ምናልባት በባሪያ ፈንጋይ ዘመን አጎንብሳ ከምትፈጭ ኮረዳ ጌታዋ ከጀርባዋ ከደፈራት ልጃገረድ ያገኘችው ድፍር ለምቦጭ ነው፡፡ ምናልባት ተወልዳ ከተጣለች እናቷን ለገዳም ገብራ በጉዲፈቻ ከበለፀገች ሶስተኛ ሚስት የወረሰችው ቅራሪ ለንጨጭ ነው፡፡ አባ ጅፋር ከጋምቤላ ፈንግለው የሸጧት የጆንጆሮ ፍናጅ ቅናጅ መልከመልካም እድለቢስ አረብ ያሙን ከፈታባት ዘይላ ደርዝ አሸዋ ላይ ባሪያ ብሎ የተፋባት ከትራፊው የተቀመመች የሰልቫጅ ደም ቅራሪ ናት፡፡ ምናልባት የአንድ እናርያ ወይዘሮ እንጁላት ሌላውን ትታ አፏን ብቻ ወራሽ ናት፡፡ ምናልባት የአንዲት መለኮ የልጅ ልጅ ልጅ ልጅ ልጅ ልጅ ናት፡፡ ዕጣ ክፍል ትዕቢት ቢያመጣ ዝርዝር ገብተን ጉረኛውን ሁሉ እናሳፍርምና የጌራ ብቻ ሳይሆን የአለም ባህል ነውና ጆለስ ሆይ በአራዳ ደንብ በቸልታ እንተላለፍ፡፡

በነፋስ እንደሚገፋ ሰንበሌጥ እያዘመመች እንደ ኮሸሽላ እየሸተተች ከቤቷ ስትወጣ የምታውቃቸው የታቦት ማደሪያ ጎረምሶች የሚደረደሩበት ላይ ተደርድረው ዐይኖቻቸውን በልጥጠው ይጠብቋታል፡፡

---

## ○ ዘሪሁን

ዘሪሁንን የማያውቅ ማነው? ሰላምተኛ፣ አላፊ አግዳሚውን ስለዘመድ አዝማድ ደህንነት የሚጠይቅ፣ ታቦት ማደሪያ ተፀንሶ የተወለደ 'ተግባቢ' የተባለ ልጅ ነው:: በዚህ ፀባዩ *ዘርሽ* በተባለ ቁልምጫ ተሰይሚል:: ተክለቁመናው ከላይ ሰፋ ከታች ጠበብ ብሎ እንደ ቃርያ የተሰራ ነው:: ዝም ሲል ወይም ሲተክዝ የተቆጣች ሙሽራ ይመስላል:: ፀጉሩ እንደ ጥቁር የጋሸበ ኩታት ነው: ዙሪያውን ይላጭና መሃል አናቱ ላይ የተቆጣጠረ የረዥም ፀጉር መረባ ይተዋል:: ትንሽ ቢስተካከል ሴት የሚያስመስለው መልከመልካም ረቂቅ ፊት አለው:: ሁልጊዜ ከላይ የሚለብሰው ቲሸርት በሰደርያ ነው:: ሰደርያው ጥለት አያጣም:: ተረበኛው ራሚሱ *ታዲያስ አገር ፍቅር* ይለዋል:: ይሄን አለባበሱን የራሚሱ አሽሙር ይሁን የአየር ፀባይ መቀያየር አያስጥለውም:: ሲራመድ ከሩቅ ይታወቃል: *ኤ! አ! ዘርሽ ያቻት!* የሚያደርገው ጫማ *ባላንስ እስኒከር* ይሁን ሱዌዲ ከአረማመዱ ነጠር ነጠር ይላል:: ዘርሽ ወሬ ይወዳልና ሁልጊዜ እንዳወራ ነው:: እንደበቱ ሰው፣ ታሪክና ዛሬን የሚሸረሽር ከገደል እንደሚወርድ ጣፋጭ ማይ ነው:: በትምህርቱ አማሃይ፣ በእሱ አባባል ማርኩ ነጋ ጠባ *ንፁህ ሲ* ወይም *ንፁህ ሰባ* ምናምን ነው:: ጠንቃቃ ፋሽን ተከታይ ነውና ከተማዋ ውስጥ መወደድ የጀመረ አለባበስ ሲያይ ያኔውኑ ይቀዳል:: ይሄ ጉልዝንነቱ ወይም *ጆሊነቱ* ግን ወሬ በመውደዱ ይበላሽበታል:: አብሮአቸው የመቆየት ተስፋ (እንዲህ ያለውን ግንኙነት 'ስቴዲ'2 ይሉታል በሰፈር) የሰጣቸውን ልጃገረዶች ወር ሳይሞላ በማያቋርጥ ወሬው ያደክማቸዋል:: ወሬው ሲያልቅበት የሚተካው አሉባልታው ወይዛዝርቶቹን ከአጠገቡ ያሸሻቸዋል:: ማራኪው ልጅ በዝግመተ ለውጥ እንደ እትዬ አስካለ ቀዳጅ ይሆናል (*አስካለ* እናቱ ናቸው):: ይሄ ገብቶት የራሱን ምላስ ስለሚፈራ በወሬ ምትክ *ይፎጫል*:: የአፎጫጨት ስልቱን እንዳሻው መለዋወጥ ይችላል:: ለንጨጨን ወይም ለምቦጨን ከመሃል በጣቶቹ አጥፎ እንደ ገበሬዎች ያጮሃል:: አፉን በትንሹ ከፍቶ እንደ አውስትራሊያ አቦርጂኒስ ዲጂሪዱ ያስገመግማል::

---

1 ------------

ልራቀቅ ሲል ደሞ የጥላሁን ገሡሡን ምናሊዞ፣ የሚኒሊክ ወስናቸውን እሽት እሽት ልቅም አድርጎ ያፏጫል። የአለማየሁ ፈንቴን ክራር ይደረድራል፣ የአስፋ አባተን ማሲንቆ ይገዘግዛል። በጣም የሚያምር ፉጨት አፏጪ ነው። ወደ ቋንቋ ሊለወጥ ትንሽ የሚቀረው ድምፅ በስስ ከንፈሮቹና በጥርሶቹ ይሰራል። ከካናሪ ደሴት ጎሜሮ እረኞች ኤል ሲልቦ ይበልጣል። የፉጨት አምላክ የተባለው ሮጀር ዊትአከር ምን አለው? የዘሪሁን ፉጨት *ትራንስደንታል*[3] ነው። በአንዱ ደብዛዛ ምሽት ካፏጨ ባይገባቸውም የታቦት ማደሪያ ልጃገረዶች ያጋጠማቸውን ይስማሉ፣ ብዙ ወይዘሮዎች የሚፀንሱት ያን ቀን ነው። ማን ይችላል እንዲህ? ይሄ ዘሪሁን ነው። ዘሪሁን ገጽ ላይ ኮስታራነት የሚነበበው ያኔ ነው።

## ○ ገለታ

ገለታ ትንሽ ጎበጥ ያለ ቋሚ መስመር የመሰለ፣ ዓይኖቹ ሊያናውዝ እንደ ጀመረ ሁሉ የሚስለመለሙ፣ አፉ የተዘጋ ልጅ ነው። በቶንዶስ የእናቱን ፀጉር በየሳምንቱ የሚገፍ ብርቱ መላጣ ስለሆነ ያለ ፀጉር የተወለደ ይመስላል። ገና ያቀመቀሙ ፀጉሮቹን ሁልጊዜ ስለሚዳብሳቸው በመዳፉ ላብና ወዝ ያብለጨልጫሉ። የሚያምር ፀጉር እንዳለው የሚያውቁ አብሮ አደጎቹ ራስታ እንዲሰራው ሲመክሩት አይሰማቸውም። ወዳጁ ሰናይት አትፈልግም: *በሌላ ይጠረጥሩሃል፣ የእኛን ሰው ታውቅ የለም*: በ'ሌላ' ማለት በእጠፋርስ ማለት ነው። 'የእኛ ሰው' ማለት 'የታቦት ማደሪያ ሰው' ማለት ብቻ አይደለም። ጠቅላላ አለም ላይ ያለ ሐበሻ ማለት ነው። የገለታ ውበት የግራ ጉንጩ ስንቡክ[1] ናት። በጣም የተከረከመች፣ ገና ለፈገግታና ለሳቅ

---

1 ይህቺ ግራ ጉንጩ ላይ የወጣች ረባዳ ነገር ሰዎችን (ወዳጅና ጠላትን) ብዙ አናግራለች። አንዳንድ ቁም ነገረኛ ነን ባዮች 'አማሃይ አመታዊ ገቢው ከመቶ ዶላር ማለፍ አቅቶት መከራውን የሚያይ ችጋራምና ደንቆሮ ሕዝብ ስለምን ብሎ የጎረምሳ መልክአፊት ላይ ያተኩራል? የታቦት ማደሪያ ሰው ከቁም ነገር የተላቀቀ፣ በርካሽ የነገር ፈሳሽ ስክሮ፣ ወይ በማይረባ ጉዳይ ሞቶ፣ በማያምር ፈጣን የቄስ ፍታት የሚያልፍ

---

አደለ እንዴ:: ኧረ የቁምነገር ያለህ?!' እያሉ ይተቻሉ:: የገለታን የጉንጭ ትሙክ በተመለከተ ሰባት አይነት የተለያዩ የሙግት ሃሳቦች እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ዙሪያዋን ሲሽመኑባት ነበር:

***አንደኛው:*** የገለታ እናት ፎርቱና ለቡና አጣጮቿ፣ ለዘመዶቿና በሉ ተገረሙ ላላቸው እንግዶች እንዲህ ብላ አውርታለች ይባላል: 'ልጅ እያለሁ አያቴ ወደ ተኛችበት ሄጄ ስሙን እየጠራሁ ለማይረባ ምክንያት ከእንቅልፉ እቀሰቅሰው ነበር......በትንንሹም በትልልቁም ነው ታዲያ:: ቢወደኝም በተፈጥሮው ቁጡ፣ ትእግስቱም በቋፍ ነበር......ነፍሱን ይማር:: ቢመክሩኝ፣ ቢያስጠነቅቁኝ፣ *ነጋ ጠባ እንደዛ አታድርጊ* ቢሉኝ አልሰማሁም:: አንድ ቀን እርሻ ውሎ መጥቶ ደክሞት መደብ ላይ ተኝቶአል:: ያለበትን አያውቅም፡ ያንኮራፋል:: እናቱ ጋ ቆሜ 'አባባ!! አባባ!!' እያልኩ ብጣራ አልሰማኝ ቢል አመልካች ጣቴን እሹዬ የተከደነ ዐይኑን ዝንቁል አሳደርገው መሰላችሁ:: በጣም እኮ ነው:: ምን ልሁን ብዬ እንደሆነ እንጃ:: እንግዲህ *ውሃ ስጠኝ* ይሆናል......ደንግጦ ባኖ ተነስቶ እጄን ያዘኝ:: ተናደደ:: ዐይኖቹ ፈጠጡ......ገላው ተንቀጠቀጠ:: ሁለተኛ እንዳላደርግ ሊያስፈራራኝ ይህቺ አመልካች ጣቴን፣ የቀኝዋን ጨብጦ ይዞ ረገማት:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ይሄውላችሁ ይህቺ የረገማት ጣቴን፣ በወር በወሩ ምን እንደሚቀሰቅሳት እንጃ፣ እሾህ እንደወጋኝ ሁሉ፣ እሳት እንዳቃጠለኝ ሁሉ ታመኛለች:: ዛሬም አልፎ አልፎ እንደ መርፌ ትወጋኛለች፣ እንደ እሳት ትፈጀኛለች:: ገና ሲጀምረኝማ በየሰአቱ ነበር:: እናላችሁ ገለታን ስወልድ እንዴት ያምር እንደ ነበር እኮ......ጉንጩ እንዲህ እንደ ኳስ የተነፋ ቀይ ነበር......አባባኝና......በዚህች በታመመች ጣቴ ግራ ጉንጩን ስነካው እይ መድሃኒያለም ማን ያምነኛል?......ጉንጩ እንደ ፊኛ ተነፈሰ:: እንዴት እንደደነገጥኩ አትጠይቁኝ:: ፊርጬ ቀኙን ሳልነካው ቀረሁ:: ያው እንደምታዩት ያ የነካሁት ቦታ ላይ እንደተነፈሰ አደገ:: ለአባቱ የሆነውን ብነግረው ሳቀብኝ:: እኔ ግን አውቃለሁ ያን ቀን ከተነፈሰ ጀምሮ የልጄ ጉንጭ እንዳልሞላ:: እንግዲህ ይሁን ብሎታል ምን ይደረጋል?......እና የእግዜር ጥበብ አሁን ይሄውላችሁ ቁንጅና ሆኖት ቁጭ::'

***ሁለተኛው:*** የዘሪሁን አባት የሚያወራው ነው:: እሱም እንዲህ ይላል: 'የገለታ አባት እኮ ሁለት ስርጓዳ አለው:: እንዴት አንድ ስርጓዳ ይገርማችኋል? ሶስት ቢሆን ምን ልትሉ ነው?'

***ሶስተኛው:*** የራሚሱ እናት ዶክተር መቅረዝ ባይናገሩትም ተናገሩት የተባለው ነው: 'በመጀመሪያ ይሄ ነገር ለምን ብዙ እንደሚያስወራን አላውቅም:: እንግዲህ ካወራነው ላይቀር እንዲህ ይመስለኛል:: የጉንጭ ስርባዳ የሚፈጠረው ዚይጎማቲክስ ሜጀር የተባለ የፊት ጡንቻ እላዩ ካለው የፊት ቆዳ ጋር ይያያዛል፣ እናላችሁ አንድ

ሰው ፈገግ ሲል ይሄ የተያያዘው ጅማት ይሰበሰብና ስርጓዳ ይፈጠራል:: ሌላ ተአምር የለውም:: እንዳየሁት የታቦት ማደሪያ ልጃገረዶች በተደጋጋሚ የሚማረኩት ጉንጫቸው ላይ ስርጓዳ ባላቸው ወንዶች ነው:: ገለታ በዛ አይነት ጉንጭ የተወለደበት ምክንያት ይሄን የዝግመተ ለውጥ አምሮት ለማሟላት መሰለኝ:: 'የተመኙት ይደርሳል' ማለት እንዲህ ነው:: ታቦት ማደሪያ የዝግመተ ለውጥ ስነልቡና ጠቢብ (evolutionary psychologist) የላትምና ይሄን ቀላል ነገር እንዴት ትረዳ? ስንቡክም እንደ ሌላው ተፈጥሮ በዝግመተ ለውጥ ሂደት ይቀነበባል፤ ወደ ፊት ገለታ ልጅ ቢወልድ ይሄን ስርጓዳ ለማስተላለፍ በቂ የዝግመተ ለውጥ ድንጋጌዎች ይደግፉታል'

*አራተኛው*፡ የጌርሳሞት አባት አቶ ኮላሴ ባርያው የተናገረው ነው: 'ሰርጓዳ ሰርጓዳ ነው:: እንደ ታቦት ማደሪያ ጣጣ ፈንጣጣ የሚያበዛ ሰፈር አላየሁም::'

*አምስተኛው*፡ የቤቴሉ የማስታወቂያ ካምፓኒ ሂቨን ኮሚኒኬሽንስ ፒኤልሲ ታቦት ማደሪያ አንዱ ጎዳና ላይ የለጠፈው ባለቀለም ፖስተር ለገለታ ሰርባዳ መወደድ ዋናው ሰበብ ይመስላል የሚሉ አሉ፡ 'ይሄ ፖስተር ኤችአይቪን ለመዋጋት የተሰቀለ ቢሆንም እዛ ላይ የወጣችው *መቅደስ* የተባለችው ልጅ ጉንጮች ላይ የሚያምሩ ስርጓዶቶች ነበሩ:: በዚህ መልኳ 'መቅዲን' ያላደነቀ ወይም ያልወደደ አልነበረም:: በእሷ ምክንያት የሰፈሩ ኮረዶች ቀድሞ ልብ ያላሉትን የወንዶችን ጉንጭ ማየት ጀመሩ:: ገለታ በዚህ ጊዜ በልጃገረዶች ዐይን ገባ:: በአጭሩ የገለታ ስንቡክ በማስታወቂያው ካምፓኒ በአጋጣሚ ተወዳጅ እንዲሆን የተደረገ የገላ ንዑስ ክፍል ነው::'

*ስድስተኛው*፡ ታቦት ማደሪያን በፍፁም በማይወድ የሌላ ሰፈር ሰው የተነገረ ነው ይባላል:: እሱም እንዲህ ነው: 'ገለታ ስርጓዶት የለውም:: እንዴት ነው የምታዩት? ገለታ ግራ ጉንጭ ላይ ያለው ስርጓዶት ሳይሆን ብልጭ ድርግም የሚል ጥላ ነው:: ልጁ ለጥቂት አመታት እንደ ማንም ጎረምሳ በቡግንጅ ይሁን በቡግር ይሰቃይ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን አደንጓሬ የሚያክል ነገር ግራ ጉንጩ ላይ አብጦ ፈነዳና ያ ቦታ መጀመሪያ ቁስል ከዚያ ስርጓዶት ሆነ:: ገለታ ይሄን ሊታከም አለርት ሲመላለስ ታይቷል:: በሽታና ውበት አምታቱ እንዴ? ወይ ዘመን?'

*ሰባተኛው* : የሰላማዊት እናት የእትዬ ዘውዱ ፍቺ ነው: 'ደሞ ምን ያምራል እሱ እቴ:: ቀጫጫ በልቶ የሚያድር ያልመሰለ:: አጥንቱ የገጠጠ:: ችጋራም እኮ ነው:: በረሃብ የሞገገው ሁሉ ጉንጩ መልካም ተባለልኝ:: አያስማን የለ::'

---

ጉንጮቹ ወደ ላይና ወደ ጎን ሲሳሳቡ የሆነች ውበቷ ልብ የሚሰብር የለስላሳ ቆዳ አዟሪት ግራ ጉንጩ መሃል ላይ ትወጣለች:: ጨዋታቸውን አቋርጠው ዐይኖቻቸው እዛ ላይ ተተክለው የሚቀሩባቸው ስንቶች ናቸው? ያ ሁሉ የገለታ ገልጃጃነት በዛች ትንሽ የጉንጭ ስብራት ግርማና ማደንዘዣ ያወጣል:: የሺህ ልጃገረዶች ልብ የተወጋው በዚህች ነጠላ ጥይት ነው:: ስንት የአየር ጤና ኮረዳ ፊቷን ጋርዳ 'ውይይይይ ሲያምር' ብላለች:: ቾኳን በቀኝ እጅዋ ይዛ ፊዛ ከቀረች ካድሬ አስተኔ የሲቪክ አስተማሪ ጀምሮ፣ ሽፍቷን ጨርሳ ወደ ቤቷ ከመሄዷ በፊት ይህችን ትዕይንት በዐይኖቿ ለማስገባት መማሪያ ክፍሉ በር ተጠግታ እስከ ምትጠብቀው ሌላ ክፍል የምትማር የትምህርት ቤቱ ቁንጅና ውድድር አሸናፊ ድረስ::

በእንጨት ስራ ሊሰለጥን ተግባረእድ ኮሌጅ ገብቶአል:: እጆቹ በእንጨት ስራ መደደር ቢጀምሩም ጣቶቹ ገና ለምለም ናቸው::

ከልጅነቱ ጀምሮ ታቦቶች ለጥምቀት ከየአቅጣጫው ሲመጡ ሰፈሩን፣ የሰዉን ልቦናና መላዕክትን በማራም ድምፁ ያደምቅ ነበር:: ዕድሜው እየጨመረ ሲሄድ ከታቦት ማስገቢያና ማስወጫ የ ዳ ዳ ዳ ዳ ዘፈን ወደ ረቀቀ ዜማ ቀስ በቀስ ተሸጋገረ:: ከአለማየሁ እሸቴ *ኮቱማ ፍቅርዬ* ተነስቶ ከዛ በአሊቢራ *እሹሩሩ ያ ብርቱካኔ* በኩል አድርጎ በመስፍን አበበ *አይሽ አይሽ*ና አሳልጦ በቅርብ ደሞ የዊትኒ ሁስተንን *አይ ዊል ኦልዌይስ ላቭ ዩ*ን ተረጋግቶ ማፍሰስ ደረሰ:: ከጥቂት አመታት በፊት ሲጫወታት የነበረችው የሉ ቤጋን ዘፈን ነበር:: ታቦት ማደሪያ 'ሉ ቤጋን አያችሁ?' ከተባለ እሱ ገለታ ነው:: *ኤ ሊትል ቢት ኦፍ ሞኒካ......ኤ ሊትል ቢት ኦፍ ሜሪ......*:: ጓደኞቹ ሊተርቡት *ኤ ሊትል ቢት ኦፍ ሰናይት* ይሉታል::

ገለታን ቀረብ ብለው ሲያዩት ከረዥም ፊቱ ላይ የሚነበብ ነገር የለም:: ልሙጥ ፀጉርየለሽ ለስላሳ ቆዳው ምንም አይነት መልዕክት ሊያወጣ የማይችል አንሸራታች ነገር ነው:: አፉ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ገፁ ዝምተኛ ነው:: በላይኛው የጥርሱ ድርድር ደስታን፣ በታችኛው ደሞ ድብርት ይዞአል ብለን ብንጠረጥርም አያሳየንም:: እዚህ እያለ

የለም። ገሊታን ሰዎች ቢያውቁትም በትክክል አይረዱትም። እያዩ አያዩትም። እሱን የሚያይ እንግዳ ሰው የሚያየው እንግዳ የሆነውን የገፁን ውበት ብቻ ነው። ከፋብሪካ ሲወጡ ጥቁር የነበሩ በመታጠብ ብዛት ቡላ የሆኑ ቲሸርቶች ሁልጊዜ ይለብሳል። ሲበርደው፣ ወድቆ የተገኘ የመሰለ ዕድሜው ትንሽ፣ ቁመቱ አጭር ለነበረ ጊዜ የገዛውን ርካሽ ጃኬት ይደርባል። አንዳንድ ጓደኞቹ በዚህ አለባበሱ ይተርቡታል። በተለይ ራሚሱ፡ *ይሄን ካናቴራህን ለልጅ ኢያሱ መልስላቸው* እያለ። ደሃ በመሆኑ መቀለጃ ነው። ሁልጊዜ ሲመሽ ሲመሽ ሰላማዊት የሰራችለትን ስካርፍ ያደርጋል። በጋና ክረምት የሰላማዊት ስካርፍ እንደ ቀለማም ዘንዶ አንገቱ ዙሪያ አለ።

○ ባካፋ

ባካፋ ትከሻም፣ ፊቱ ክብ፣ በስብና በፕሮቲን የተሞላ፣ ከቀፈቱ ከበድ የሚል ደልደል ያለ መሳቅ የሚወድ ልጅ ነው። ራሚሱ 'ቦቴው' ብሎ ቀፅሎት አላኮረፈውም። መወፈር ይወዳል። ብዙ ባይሆንም ዕድሜው ከሌሎቹ ጓደኞቹ ጠና ያለ፣ ቅንድቡ ደማቅ፣ የተቀነደበ የመሰለ ነው። ከንፈሮቹ እሱ እንደሚለው ከክትፎ በጠለለ ኮላጀን ተሞልተዋል። ፊቱ በመስፋቱ አይኖቹ ጠባብ ይመስላሉ። በአፉ ጫትና አልኮል ገብተው አያውቁም። ከቃሚ ጓደኞቹ ጋር በርጫ ሲቀመጥ ጎኑ የሚጎልተው ኮካና የስጋ ሳምቡሳ ነው። ቀበቶው ትክክለኛው ቀዳዳ የገባ፣ ሸሚዞቹ በትሁትነት እስከ አንገቱ የተቆለፉ፣ እጀታዎቹ እስከ ክርኖቹ የተጠቀለሉ ናቸው። ሁልጊዜ ኮት የሚለብስ፣ ሲያሰኘው ክራቫት የሚጨምር ነው። ጃኬት ከለበሰ፣ የሆነ የሲኒማ ፖስተር ወይም የባዴ አክተር ያለበት *ስዌት ሸርት* ከስር አለ። ሁሉም የስሜት ህዋሶቹ የሚያስቡ ይመስላሉ። በፕላን እንደሚሰራ አይኖቹ ይናገራሉ። በአካውንቲንግ ዲግሪውን ለማግኘት ያቀደው ገና ፕሬፓራቶሪ ስኩል እያለ ነው። አካውንቲንግ ግን አይወድም። ከልቡ የሚወደው ሲኒማ *ፕሮዲዩስ*[4] ማድረግ ነው። ሲኒማ ፕሮዲዩስ ለማድረግ ገንዘብ ያስፈልገዋል። እንደሚገምተው ገንዘቡን

የለም። ገለታን ሰዎች ቢያውቁትም በትክክል አይረዱትም። እያዩ አያዩትም። እሱን የሚያይ እንግዳ ሰው የሚያየው እንግዳ የሆነውን የገፁን ውበት ብቻ ነው። ከፋብሪካ ሲወጡ ጥቁር የነበሩ በመታጠብ ብዛት ቡላ የሆኑ ቲሸርቶች ሁልጊዜ ይለብሳል። ሲበርደው፣ ወድቆ የተገኘ የመሰለ ዕድሜው ትንሽ፣ ቁመቱ አጭር ለነበረ ጊዜ የገዛውን ርካሽ ጃኬት ይደርባል። አንዳንድ ጓደኞቹ በዚህ አለባበሱ ይተርቡታል። በተለይ ራሚሱ፡ *ይሄን ካናቴራህን ለልጅ ኢያሱ* መልስላቸው እያለ። ደሃ በመሆኑ መቀለጃ ነው። ሁልጊዜ ሲመሽ ሲመሽ ሰላማዊት የሰራችለትን ስካርፍ ያደርጋል። በጋና ክረምት የሰላማዊት ስካርፍ እንደ ቀለማም ዘንዶ አንገቱ ዙሪያ አለ።

## ○ ባካፋ

ባካፋ ትከሻም፣ ፊቱ ክብ፣ በስብና በፕሮቲን የተሞላ፣ ከቀፊቱ ከበድ የሚል ደልደል ያለ መሳቅ የሚወድ ልጅ ነው። ራሚሱ 'ቦቴው' ብሎ ቀፅሎት አላኮረፈውም። መወፈር ይወዳል። ብዙ ባይሆንም ዕድሜው ከሌሎቹ ጓደኞቹ ጠና ያለ፣ ቅንድቡ ደማቅ፣ የተቀነደበ የመሰለ ነው። ከንፈሮቹ እሱ እንደሚለው ከክትፎ በጠለለ ኮላጀን ተሞልተዋል። ፊቱ በመስፋቱ አይኖቹ ጠባብ ይመስላሉ። በአፉ ጫትና አልኮል ገብተው አያውቁም። ከቃሚ ጓደኞቹ ጋር በርጫ ሲቀመጥ ጎኑ የሚጎልተው ኮካና የስጋ ሳምቡሳ ነው። ቀበቶው ትክክለኛው ቀዳዳ የገባ፣ ሸሚዞቹ በትሁትነት እስከ አንገቱ የተቆለፉ፣ እጀታዎቹ እስከ ክርኖቹ የተጠቀለሉ ናቸው። ሁልጊዜ ኮት የሚለብስ፣ ሲያሰኘው ክራቫት የሚጨምር ነው። ጃኬት ከለበሰ፣ የሆነ የሲኒማ ፖስተር ወይም የባዴ አክተር ያለበት *ስዌት ሸርት* ከስር አለ። ሁሉም የስሜት ህዋሶቹ የሚያስቡ ይመስላሉ። በፕላን እንደሚሰራ አይኖቹ ይናገራሉ። በአካውንቲንግ ዲግሪውን ለማግኘት ያቀደው ገና ፕሬፓራቶሪ ስኩል እያለ ነው። አካውንቲንግ ግን አይወድም። ከልቡ የሚወደው ሲኒማ *ፕሮዲዩሰ*[4] ማድረግ ነው። ሲኒማ ፕሮዲዩስ ለማድረግ ገንዘብ ያስፈልገዋል። እንደሚገምተው ገንዘቡን

መአት ነው:: የሚያማርረውን ሁሉ በከፊል የሚረሳው ከወዳጆቹ ጋር ብቻ ሲሆን ነው:: ዩንቨርሲቲ የገባው በአራት ነጥብ፣ ከዩንቨርሲቲ ደሞ ስዎች እንደሚሉት የሚመረቀው በአራት ነጥብ ስለሆነ አንዳንድ የሚያውቁት በዚህ ባልተገራ ብሩህነቱ እንዲኮራ ይጠብቃሉ:: በእሱ ፍቺ ሁለት አመታት ካምፓስ እያለ ያጋጠመው የዞረበት ህዝብ ነው: *4 ፖይንት ስታመጣ ከሚቀናብህ፣ 2 ፖይንት ስታመጣ ከሚስቅብህ ምን ትጠብቃለህ? ይሄ አገር አማሃይ ያመልካል:: የአገራችን ፈጣሪ ፀጉሩን እንዳይረዝም እንዳያጥር አድርጎ የሚስተካከል አጎብዳጅ ነው:: ከነዚህ ዜጎች ጋር መኖር እንደመረገም ነው* ይላል:: አዲስአባ ውስጥ የሚጠላቸው ቦታዎች የተማረበት ዩንቨርሲቲውንና ስታድዮም የተባለውን በረት ነው:: አቡ በሰበብ የተሞላ ነው::

ለአቡ (በቤት ስሙ) ታቦት ማደሪያ መኖሪያው ሳትሆን መሸሺያው ናት:: ባያወራውም እንደ ባካፋ፣ ገለታና ዘሪሁን የሚያቀርበው ሰው የለም:: አባቱ አራት ኪሎ ዩንቨርሲቲ የፊዚክስ አስተማሪ ስለሆኑ የሚበላው ባያጣም 'የምበላው አጣሁ' በማለት መበሳጨት ይችላል:: እናቱ አለርት ሆስፒታል ከአንገት በላይ ሃኪም ለነበረች ጊዜ ከሙት በሽተኞች የምትሰርቀውን ዐይን እየሸጠች እንዳሳደገችው ይቀባጥራል:: ልብሱን ሰላማዊት ላውንደሪ አስገብቶ መንገድ ዳር ትምባሆውን እያንፎለፎለ ወዳጆቹን እሱ እንደሚለው 'እስከ መጨረሻው ደም ጠብታ ይጠብቃል':: እያሳጠበ ሊጠብቃቸው፣ እየጠበቃቸው ሊያሳጥብ:: ካልመጡለት የጫት ባሊስቲክ ሚሳይሉን (እነ ኢራቅ የሚመፃደቁበት አይነት ባይሆንም) በግራ ክንዱ ብብት አቅፎ መኝታ ቤቱ ይገባል:: ሲያገኝ ከሰው የሚግባባ፣ ሲያጣ ከሰው የሚሸሽ ነው:: ሲያወራ ክንዱንና እጁን ማወናጨፍ ይወዳል:: በአንድ(ግራ) እጁ ሁልጊዜ መፅሐፍ ወይም መጽሔት አይጠፋም:: ማንበብ የሚወድ ግራኝ ነው:: ግራኝነቱን ይጠላል:: ግራኞችን ይጠላል:: የግራኞች ፖለቲካ ይጠላል: ባይጠቅምም ቢጠቅምም 'ግራ' በመባላቸው ይጠላቸዋል:: መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ እያለ አንዳንድ የክፍሉና የሰፈሩ ልጆች *ፈላስፋው ግራኝ አፈንድደህ ጥራኝ*[2] ይሉት

---

[2] ማይክል አንጄሎ ሲስቴይን ቻፔል ውስጥ የሰራው '*የመጀመሪያው ሰው*' የተባለው ስዕል የመፈጠርን ወይም የሕይወትን ስጦታ አዳም *በግራ* እጁ ከአምላክ *ቀኝ* እጅ ሲቀበል ያሳያል (በአመልካች ጣቶቻቸው ንክኪ)::

---

ነበር። እንዲህ ያብጠለጠሉትን የሰፈሩን ልጆች በግልፅ ይጠላል፡ እንደዛ ከሚሉት ሁለቱ ባድሜ ጠርቶአቸው ሄደው ቀርተዋል (*ደግ አደረግሽ ባድሜ*)። አንዱ አሜሪካ በዲቪ ገብቶ የዲሞክራሲ ቤት ይጠርጋል (*ደግ አደረክ ኦባማ*)። እዚህ ሰፈር የቀረው አንዱ ሹገር ማሚ ይጠልዛል። ታዲያ አቡ ተስፋ መቁረጥ በገረዛቸው ሰበብ እዳኘ ነፍስና ምላሱ፡ *ሰዳቢም ተሳዳቢም ድራሹ የሚጠፋው እዚህ የከተማ ወረዳ ከተማ ነው ይላል፡*

---

ስለዚህ ግራኝነት ስለምን ብሎ መሽማቀቂያና ማሽማቀቂያ ይሆናል? የሰው ልጅ ፍርሃቱን የሚገልፅበት ስሩት ግን አስገራሚ ነው። ማለት ሲረቅ የራሱንም ገላ ይፈራል። አቡ ልዩ ብሩህነት የነበረው ልጅ ነበር። ይሄ ብሩህነቱ ከሰዎች ፊት ፊት እየጎተተ ይወስደዋል። ደብተሩን ገልጦ ሳያይ ፈተና ይደፍናል። ኳስ ሲጫወት አስገራሚ ነበር። በአዳዲስ ቤቶች ወረራ መጥበብ በጀመሩ ከርካሳ ሜዳዎች ላይ ክብ ቆዳ እንደ ብይ እያሽከረከረ የሚጫወት ቀልጣፋ ነበር። ይሄ ክህሎቱ ቶሎ ስለታየ በግራኝነቱ ቅፅል ለመሰየም ተጋለጠ። ሰያሚዎቹ ቅልጥፍናውና እነሱን መብለጡ በሌላ ሰው (የክለብ ሰዎች፣ ጋዜጠኞች) እንዳይታይ ያማረ ስራው ላይ ቶሎ ብለው ተሊስ ሊያነጥፉበት ተስማሙ። ቀሽምነታቸውን ከማረም ይልቅ ሊያሳንሱት ግራኝነቱን መስ'ደቢያ አድርገው ቀመሩለት። ራሚሱ በልቡ ቂም ይዞ 'መቆሚያ እጡ' ብሎ ረግሞአቸው ሄደ። ብዙ ሳይቆይ ሜዳውን መንግስት ሽቀለው። የተሸቀለው ሜዳ ላይ የጫት፣ የሺሻ፣ የስልክ ካርድና የሞባይል አፎት መሸጫ ሱቆች ቆሙበት። የኳስ ድምፅ ሲሰሙ ለሃጫቸው ይዝረበረብ የነበሩ ጎረምሶች ጫት አላምጠው መጠጡ። መንገድ ዳር ቆመው ሽንጣም ልጃገረዶችን በፉጨታቸው ያማለሉ ጎረምሶች ጆሮአቸውን ሞባይል ላይ ለጥፈው የማያዩትን በማባበል ጊዜ አሳለፉ። ኳስ የሚወድ ጎረምሳ ማንቼና ባርሳ ማለት ጀመረ። ብዙዎቹም እግሮቻቸው ተነባብረው የላሙ ዐይኖቻቸው ቲቪ ላይ አፈጠጡ። ግራኝም ቀኝም ሳይሆኑ ምንም ሆኑ። የአቡ እርግማን ሁላቸውንም ይዞ ሄደ። አሁን አሁን አቡ መንገድ ዳር ቆመው ስለሮናልዲኖ ስለ ሳላዲን ሲያወሩ ሲሰማቸው ከስድባቸው የተረፈች ግራ እጁን ይስማል።

[3] *ደስ ባር* 'በአንድ ሕንፃ ውስጥ ያለ አዲስአባ ነው' ይባላል። የታቦት ማደሪያ ሰፈረተኛ ግራ ተጋብቶ 'አንድ የወረዳ ፍራክሽን (እራፊ ለማለት) ውስጥ እንዴት አንድ ከተማ ይቋቋማል? አይጠባትም? የሰፈራችን ቆዳ ብቻ ሳይሆን የእኛም ነፍስና ስጋ ተወጠሩ። እባክህ አንተ የአውራጃ ሃላፊ

---

ይሄ ደስ የተባለ ሬስቶራንት አላስደሰተንምና አስወጣልን' እያሉ ደጋግመው በደብዳቤ አቤቱታ ቢያቀርቡም፣ በቃል ቢያለቃቅሱም የሰማቸው የለም:: ደስ ባር ጀርባ ዳርት መጫወቻ፣ ቢሊያርድ ቤት፣ ቴቢል ቴኒስ ማንቀርቀቢያ የፒሌክሲ ግላስ ድንኳን፣ ከፊትና ከጎን ሰፊ የቴሌቭዥን ስክሪን ያላቸው አዳራሾች፣ ትልቅ አስራ አምስት ገጽ ሜኑ ያለው የፈረንጅና የአበሻ በላተኛ የሚያስተናግድ ሬስቶራንት፣ በግማሽ ጨረቃ ስልት በእንጨት ብቻ የተሰራ አርባ ሃምሳ ሰው የሚያስተናግድ ባር፣ ገና ሲያሸቱት ልብ የሚነሳ ጠረን (ባለቤቱ ኮኛክ፣ የባልና ሚስት አረቄ፣ ጂንና ጠጅ ከሽቶ ጋር ደባልቆ እንደ ፍሊት ቤቱን ይነፋበታል እየተባለ ይታማል) አሉ:: በተጨማሪም በግድግዳዎችና በምሶሶዎች ላይ የተለያዩ አይነት ጥቅሶች ጨርቅ ላይ ተጠልፈው ወይም በወረቀት ላይ ተፅፈው ይሰቀላሉ: **'ይሉኝታ ያለበት አይግባ' 'ይሄ ቤት የነፃነት ቦታ ነው' 'በባለጌ ከሳቀ ያዝናናው ፀደቀ' 'ይሉኝታ ቢስን ና በሉት' 'ትዝብት የመዝናናት ደንቃራ ነው'**:: በመጨረሻም በሳምንት ሁለት ቀን በአገሪቷ የታወቀው ዲጄ ኤም ወይም ዲጄ መኮንን ተወዳጅ ትዕይንቱን ያቀርባል:: ከጀርባው ጀርባ ብዙ ጊዜ ሆን ተብሎ መብራት በማይበራበት ጥግ ዕጠፋርስ ይሸቀላል:: ደፍረው ባያወሩትም፣ ደስ ባር የስፈሩ ብቻ ሳይሆን የዛ ንዑስ ከተማ ቤተ ሐኖት ነው::


ከዕለታት አንድ ቀን አቡ እዚህ ቤት ሲጠጣ በዕፅና በቢራ ራሳቸውን እስኪስቱ የሰከሩ አንድ ከእሱ የበለጠ የሚያግርሩ የዛ ትውልድ እንጥፍጣፊ አዛውንት ምን አቅደው እንደሆነ ያኔውኑ ባይደርስበትም ያላሰበውን ጨዋታ ጀመሩ: 'ወንድምና እህት ቢጋቡ ዝርያው ይረባል? አይረባም: አሸናፊና ተሸናፊ ስየማ ነው እንጂ ተጠግተው ሲያዩት ሁላችንም ጀርባ ላይ የቆመው ወገቡን የያዘ ተዋናይ የመሰለ ዘናጭ እርግማን ነው:: ግራኝ ሆንክ አልሆንክ ድራሽቢስነት አባሮ ይይዝሃል' ሱሪያቸውን ዝቅ አድርገው ሙታንታቸውንም አውርደው እንዳልተገረዙ አሳዩት:: 'ሰማህ ሥልጣኔንና አለመሠልጠንን በመገረዝና ባለመገረዝ ሊከፋፍሉት የሚጥሩ አይጠፉም:: ብዙ ሰዎች ይሄ ሙርጥ ተኮር ፋሊክ እንደ እውን የሚመስጣቸው ለምን መሰለህ? ልዩነትን በተገኘው ቀዳዳ ፈጥረው ተደናቅፎ መውደቅን የሚወዱ ስለሆነ ነው:: ግራኝ ሆነ ቀኝ ስለት ሁሉን ይቆርጠዋል:: ሰዳቢም ተሰዳቢም ተያይዞ ይጠፋል:: ይሄ የምታየው ደስ ባር መዝናኛ አይደለም ልጄ መሰዳደቢያ ነው:: እዚህ የምመጣው እንድሰደብ ነው:: ግን አልገባህም:: እዚህ የምመጣው ስላልሰደብከኝ ልሰድብህ ነው:: አስገራሚው ደማችን የሶስተኛ ደረጃ ቅራሪ ነው:: እንደበተርትዕ ዞምቢዎች ነን:: ለምን ያልኩህ ተያይዘው ይጠፋሉ? ሁለቱም ደደቦች ስለሆኑ' ልብ ብሎ ሲያያቸው የደባሪው የአበበ ይርጉ አባት እንደሆኑ አወቀ:: እዚሁ ሰፈር እያለ ብዙ

---

ሰዎች እየረሳ ነው:: ሰውዬው እንዲህ የተናገሩት ግራኝ በመሆኑ ሲሰደብ እንደኖረ ገብቷቸው ሊያፅናኑት ይሆናል:: ልጃቸው እሱን ሲሳደብ ሰምተው ይሄን እንዳወሩት ስለጠረጠረ ተወው እንጂ ደባሪ ነገር ሆኗል አለ:: 'ሰዳቢም ተሰዳቢም ተያይዞ ይጠፋል' ያሉት አባባላቸው ግን ለእሱ ተረትና ምሳሌው ሆነ::

---

# ቅልልቦሽ



ስሜ ጌርሳሞት ኮላሴ ይባላል:: ይሄ ዝርዝር ያልጠቀመው ካለ ጌርሳሞት ኮላሴ ባርያው[4]: የመበርበሪያ ዘመን ነው:: ሌላ ቢቀር እንደ

---

[4] ኮላሴ የሚጠ'ራው ባሳደጉት ሰውዬ ስም ነው:: አቶ ባሪያውና (በሚስታቸው አጠራር 'ባርቾ') ሚስታቸው ወይዘሮ ንግሥት ሃምሳ አመት ያለፋቸው ልጅ በሞላበት አገር ልጅ ያልነበራቸው አዛውንቶች ነበሩ:: አቶ ባርያው ድሮ ጣሊያን አቋቁሞት የሄደ ከየማንብርሃን አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት አጠገብ ያለ የእንጨት ፋብሪካ ውስጥ ይሰሩ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን ሊነጋ አካባቢ ከእንቅልፋቸው ባንኑና ተመልሶ መተኛት ስላልቻሉ ንጹህ አየር ለመተንፈስ ለባብሰው እዳሪ ወጡ:: ደሞ ጎሕ ሊቀድ ሰማይ ይቅበጠበጣል:: እውጭ በጋቢያቸው እስከ አፍንጫቸው ተከናንበው ሲያዛጉና ሲንጠራሩ በስተደቡብ ካለው የድንጋይ ማምረቻ የካባ ገደል ሁካታ ሰሙ:: ሁካታው ለደቂቃዎች ያህል ቆየ:: ያን አይነት ድምፅ ከዚህ ቀደም ሰምተው ስለማያውቁ በጉጉት ወደ ገደሉ ምዕራብ ጫፍ ሄዱ:: ጠፍጣፋ ድንጋይ ፈልገው፣ እንዳይበርዳቸውም የለበሰውን ጤዛ ከልተው ተቀመጡ:: የረጠበ እጃቸውን በጋቢያቸው አዳርቀው የሰሙት ድምፅ የምን እንደሆነ ለማጣራት ረጋ ብለው ዙሪያቸውን በጆሮአቸውና በዐይኖቻቸው ማተሩ:: ብዙ ሳይቆይ በምስራቅ በኩል ፀጥ ያለው የካባ ገደል እንደገና በጩኸት ታመሰ:: የጎህ ወጋገን የሳተው ገደል ላይ የበቀለው ቅጥልጣይ ውስጥ ትርምስ አዩ:: ገደሉ በትናንሽ ዕፀዋትና ዛፎች የተሞላ ነው:: አንዳንዶቹ ዛፎች ከመግዘፋቸው የተነሳ እዛ ገደል ደረት ላይ በቅለው የመቆየት አቅም ያላቸው አይመስልም:: ከገደሉ ስር ዳክዬዎችና ቁራዎች ይበራሉ ይዋኛሉ:: በወሬ ወሬ ወዲያ ሰፈር ያሉ ሰዎች 'ዝንጀሮ ያስቸግረናል' እንደሚሉ ቢሰሙም እንዲህ አይነት የደራ ሁካታ ይኖራል ብለው አልገመቱም:: ትርምሱ ልክ እንደ ፈረሰኛ ወንዝ የገደሉን መሃል ተከትሎ ቅጠልጣዩን እየመሰ ወደ ግራ አለፈ:: ከትርምሱ መሃል የሆነ ነገር የሰስት የአራት ዛፍ ቅርንጫፍ እየመታው ወርዶ ወንዙ ላይ አረፈ:: ውሃው ላይ የነበሩ ዳክዬዎች በግርታ ተነስተው የንጋቱን ሰማይ በአደንቋሪ ካካታቸው ሞሉት:: አቶ ባርያው ከተቀመጡበት ተነሱና የወደቀውን ነገር ለማየት ሞከሩ:: የወደቀው ነገር የወንዙን ስርበት ተከትሎ እንደመሄድ እወደቀበት ቀረ:: የሆነ ዝንጀሮ እንደሞተ ጠረጠሩ:: ትንሽ ግራ ገባቸው:: *ዝንጀሮ ከገደል ይወድቃል? ደሞ ሲወድቅ ዛፎች እየበረዱት የመጣ ነው:: ድንጋይ ቢሆንስ? ከላይ ከገደሉ ደርዝ ካሉ ቤቶች የተጣለ ቆሻሻ እንደሆንስ?* እያሉ ሲያስቡ ቆዩ:: ጥያቄአቸው ጉጉት አሳደረባቸውና ቀርበው የሆነውን ለማየት ከተቀመጡበት ተነስተው ጋቢያቸውን በስርአት አጣፉ::

---

መሂጃ መንገዳቸውን ከቆሙበት አቀዱ:: በስተቀኝ በቀስታ እያዘቀዘቀ የሚሄደውን የእግር መንገድ ቢከተሉ አስር ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ የፈለጉበት መድረስ ይችላሉ:: በላይ በኩል ቢሄዱ ከፊሉ የመኪና መንገድ ስለሆነ መንገዱ ቢመችም ረዥም ጊዜ ይወስድባቸዋል:: ስለዚህ ለቀኛቸው አማራጭ አዳልተው መንገዳቸውን ጀመሩ..................................በገመቱት ጊዜ ገደሉ ስር ደርሰው ዞር ብለው ቀድሞ የተቀመጡበትን ቦታ አዩና የደረሱበትን ቦታ ትክክለኛ አቅጣጫ በስሜት ለክተው አገኙ:: ትንሽ ወደ ግራ ፈቀቅ ብለው የወደቀውን ነገር--የሚፈልጉትን ባያውቁትም--ብቻ የወደቀ የመሰለ ለየት ያለ ነገር ከሆነ እሱ ሊሆን እንደሚችል ገምተው በአይናቸው ማሰስ ጀመሩ:: ብዙም ሳይለፉ ሁለቱም እግሮቹ ጥልቀት የሌለው ወንዙ ውሃ ውስጥ ያረፉ፣ ሁለመናው ራቁቱን የሆነ፣ በብርድ የሚንዘፈዘፍ አንድ ሞሳ ወድቆ አዩ:: በድንጋጤ አናታቸውን በሁለት እጆቻቸው ይዘው ጮሁ:: ቀና ብለው ወደ ገደሉ አዩ:: ከቅርባቸው ያለ ቅርንጫፍ ላይ አንድ ገመሬ ጋማውን እየነሰነሰ መቀመጫዋ እንደ ፍሬቻ የቀላ እንስት አጠገብ ይንጎራደዳል:: ዝንጀሮው አቶ ባሪያውን አተኩሮ እያየ ቀጭ አለ:: ዝንጀሪት ተጠግታ የገመሬውን አንገት መቅመል ጀመረች:: ገደሉ ላይ አስር ወይም አስራ አምስት የሚደርሱ ደረተ-ቀይ ነጫጭ ዝንጀሮዎች ከዳር እዳር ተደርድረው አቶ ባሪያውን አፍጠው ያያሉ:: አቶ ባርያው ልብ ገዝተው ወደ ልጁ ሲጠጉ ብዙ የጉዳት ምልክት እንዳሌለበት አዩ፡ አይኖቹ ይቁለጨለጫሉ፣ ከፊቱ በስተቀር ገላው በፍዝ ቡናማ ፀጉር ተሸፍኗል፣ በስተግራ የታች ከንፈሩ ተሰንጥቆ አብጦአል እና ብዙ ባይሆንም እስከ አገጩ ማለቂያ ደም ሸፍኖታል:: በደንብ ሊያዩት አቶ ባርያው ወደ ፊቱ ሲጠጉ፣ እንዲያቅፉት አይነት በስስ ፀጉር የተሸፈኑ ክንዶቹን ወደ እሳቸው ዘረጋ:: አቶ ባርያው ዙሪያ ገባቸውን ሰልለው ከውሃው ሸሸት አድርገው በጋቢያቸው ጠቀለሉትና ምናልባት *ባለቤት ይኖረው ይሆን?* በማለት ወንዙ ዳር ደረቅ ጥቁር ድንጋይ ላይ እየበረዳቸው አቅፈውት ተቀመጡ:: ግማሽ ሰአት እንዲህ ሆነው ቢጠብቁም ማንም ሰው 'ልጅ ጠፋብኝ' ብሎ አልመጣም:: ተሰብስበው ሲያፈጡባቸው የነበሩትም ዝንጀሮዎች ወደሚገቡበት ቀዳዳ ገቡ:: አቶ ባርያው ማንም እንዳልመጣ ሲረዱ ልጁን በጋቢያቸው እንደጠቀለሉ እየተገላመጡ እያዩ ቤታቸው ገቡ:: ሚስታቸውን ከተኙበት ቀስቅሰው የሆነውን ሁሉ ሲነግሯቸው ሲትዮዋ ከመፍራትና ከመደንገጥ ይልቅ ያለማመንታት 'እናሳድገዋለን' አሉ:: ለዚህም እንዲመቻቸው 'ወድቆ አገኘነው' ከማለት ይልቅ 'አንድ ያላገባች ዘመዳችን ከአንዱ ወጠጤ ማግጣ ዲቃላ ወልዳ በደረቅ ሌሊት መጥታ ጥላብን ሄደች' ብለው ለማስወራት ወሰኑ:: በታሪኩ ዝርዝር ላይ እንዳይሳሳቱ፣ የተዘባረቀ ምላሽ

------------- I

ቀበሮ እየማስኩ እስከ አያቴ አጀማመሬን ላቃጥር እስኪ:: እናቴ መግደላዊት ጳውሎስ[5] ትባላለች:: የተወለድኩት ደጉ ሰፈር ታቦት 25

ሰጥተው እንዳይጠረጠሩና ወንጀለኛ እንዳይባሉ የፈጠራ ታሪካቸውን በደንብ አጠኑት......ወሬአቸው በአጭር ጊዜ በሰፈሩ ከታመነ በኋላ ቀራንዮ መድሃኒያለም ወስደው አስቆረቡትና ልጃቸው ሆነ:: በዛው ክርስትና በተነሳ ሰሞን አርባ የሚደርሱ የካባ ዝንጀሮዎች ከተማው ስለሰፉና ይሄም ለደህንነታቸው አስጊ ስለሆነባቸው ኋላና ፊት ሆነው ቀን በቀን ወደ መናገሻ ተራራ በሰልፍ ሄዱ የሚባል ወሬ አቶ ባሪያው ሰሙ:: እንዲህ በተወራ በሁለተኛው ቀን አንድ ዕድለኛ የአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ ብስራተወንጌል ሬድዮ ጣቢያ በር ላይ ዝንጀሮዎቹን ተከትሎ ፎቶ አንስቶአቸዋል ሁሉ ተባለ:: ጋዜጣውን የመስሪያ ቤታቸው ሰዎች እየተቀባበሉ ሲያዩት አቶ ባርያው እስኪ ላንብበው ብሎ ለመጠየቅ ድፍረቱ አልነበራቸውም::

ኮላሴ ሲያድግ አገጭ የሚባል ነገር ያልተፈጠረለት፣ ትንሽ ጎበጥ ያለ፣ ክንዶቹ ረገርጃም የሆኑ፣ አባትና እናቱ ግን የሚኮሩበት ጎረምሳ ሆነ:: አንድም ቀን አምልጦአቸው እንኳን 'ወላጅ አባትና እናትህ ሳንሆን አሳዳጊህ ነን' አላሉትም:: ዕድሜው አስራ ስምንት ሲሆን አባቱ ባርያውና እናቱ ንግሥት ተከታትለው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ልክ አስራ ዘጠኝ ሲሞላው መንጃ ፈቃድ አውጥቶ ከሟቾቹ የወረሰውን ቤቱን አከራይቶ እግሩ የትም የሚረግጥ የዚታዎ ሾፌር ሆነ::

[5] የጌርሳሞት እናት መግደላዊት ቀጫጫ፣ ረዥም፣ የሳር ውስጥ መንገድ የመሰለ አንገት ያላት ወይዘሮ ናት:: ጌርሳሞትን ጨምሮ ሁለት ልጆች አሉዋት:: ከጌርሳሞት በፊት የወለደችውን ልጅ አርግዛ ያያት ሰው የለም:: የላም በረት ሰው 'እንዴ!' እያለ ነው ዲቃላዋን ጠብ ያደረገችው:: ቆዳዋ ላይ (ያው ራቁቷን ስትሆን የሚታይ ነገር) ከወጣው ደንና ዱር አራዊት ድርጅት ውስጥ ባዮሎጂስት ሆና ትሰራለች:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተነገረላት ሰካራም ነበረች:: ብዙ ጊዜ በስካር ራሷን እየሳተች አንጉል ቦታ ወድቃለች: ሽራ የተከለለ ፒካፕ ጀርባ፣ የወታደር አልጋ የተዘረጋበት ድንኳን፣ አፈር አፈር የሚሸት አንሶላ የተነጠፈበት የገጠር ሆቴል፣ ላንድሮቨር ጀርባ፣ ወዘተ:: እንደሚወራው እሷን ከመስሪያ ቤቷ አላወጣሁዋትም የሚል ሰው አልነበረም:: የቆዳ ሽንተረርና ሽብሽብ የተለየ የእናትነት ምልክት አይታይባትም::

ከኮላሴ ጋር የተገናኘችው ለስራ ጉዳይ ሰበታ አካባቢ ሄዳ ነው:: አንድ ቀን ከጠዋቱ ሶስት ሰአት አካባቢ ዛፍ ስር ከተከለችው ድንኳኗ ውስጥ ተኝታ ስትባንን ኮረብታ የሚያክል፣ ሶስት አራተኛ ገላው በፀጉር የተሸፈነ ሰውዬ ጎኗ ተኝቶ አገኘች:: አስቀያሚነቱ አስደንግጦ ሳያሮጣት

---

ማደሪያ አዲስአባ ነው። በአየር ጤናና በቀራንዮ መሃል። በተወለድኩበት ዘመን ቦታው እንደ ዛሬ ብዙ ሰው አይኖርበትም ነበር። ለመጀመሪያ አይኖቼን ስገልጥ ያየሁት የሰፈሬ ልዩ መለያ ምልክቶች፡ ሳር፣ ቀዳዳ በቀዳዳ የተሞላች ቀጫጫ አስፋልት መንገድና አንጀባቸው ጎጆ የአሰደደ ጥቂት ቢላ ቤቶች ነው። ቢላ ነው ቪላ? ግድ የለኝም።

'ጌርሳሞት' የተባለ የንግሥት ስም ለምን እንደተሰጠኝ እንጃ። ብዙ ሴቶች የማይጠሩበት ስለሆነ እናትና አባቴ ሌላውን ዜጋ እንዳልመስል ብለው ይሆናል። ማለት ጉረኛነት ይሆን እንዴ?

በሆነ አመተምህረት በመጋቢት ማርያም እናቴ የሆነ ቦታ የታሪክ ኤግዚቢሽን ልታይ ሄደችና ነጭና ጥቁር ቀለም የሽክላ ወለል ላይ ተገላገለችኝ። ከማሕፀኗ ገና እንደወጣሁ አይኖቼን ስከፍት ያየሁት የሆኑ ንጉሠ ነገሥት ከሆነ ወራሪ የማረኩትን መድፍና የመድፍ ቀዳዳ ነው። እማማን ምን አንቀለቀላት? እንደደረሰች እያወቀች ምን እዛና እዛ አሮጣት? ካልጠፋ የሚታይ የታሪክ ቁስ መድፍ ስር ምን አስቆማትስ? አንዳንዴ የተሳተ ነገር ሳስብ ከዚህ ጊዜ ገጠመኜ ተውሰው ስሜን መድፌት፣ ደጃዝማቿት፣ ባላንባራሲት፣ ካሌቢት፣ አብረሃ አጽብሂት ለምን እንዳላሉኝ ይገርመኛል። ነፍስ አወቅሽ ከተባልኩ ጀምሮ አንዳንዴ በሕልሜ እንግዳ ፍጡራን የሚገቡበትና የሚወጡበት ባዶ አየር ላይ የተንጠለጠለ ትልቅ ጥቁር ቀዳዳ አያለሁ። ያ የመድፉ

---

በፊት እንዳትጮህ አፏን ይዞ አወቃት። የስራ ባልደረቦቿ እዛው አካባቢ በየድንኳናቸው አድረው የነበሩት ከተኙበት ተነስተው ቁርስዋን እንድትበላ ጠሯት፡ *መግዲ! መግዲ! መግዲ!* ሲጠሯት ብትሰማቸውም ከላይዋ ላይ ሆኖ የሴትነት ጥልቅ ሚስጢር ከሚያሳያት ከአቶ ኮላሴ ገላ መላቀቅ አልፈለገችም። እኩለ ቀን ላይ ይሄ ሰው ከድንኳዋኑ ሲወጣ የስራ ባልደረቦቿ ግራ ተጋብተው፡ *ማነህ አንተ? የታለች መግደላዊት?* አሉት። *ይሀቺትና* ብሎ እንደ ክር የቀጠነች፣ ላብ እንደ ቅባት ከላይዋ የሚወርድ፣ አፏ እንደ በር የተከፈተ፣ አይኖቿ ግንባሯ ውስጥ የተሰነቀሩ መግደላዊትን ክንዱ ላይ ተጋድማ አሳያቸው።

ፈገግ ብለው፣ በልባቸው ግን *እንኳን ገላገልከን* አሉና ምሳ እንዲበላ ጋበዙት። ከዚያን ቀን ጀምሮ መግደላዊት የሌላ ወንድ ዐይን አላየችም።

---

አፍ መሆን አለበት:: ማርያምን:: ልጅ እያለሁ ሕልሜን ለእናቴ ከነገርኩዋት እየተነጫነጨች ጠበል ልታስረጨኝ በጋቢ ጠቅልላ እዚህ አለርት ጀርባ አቡነ አረጋዊ በሌሊት ትወስደኛለች::

አባቴን የሚቆጨው መድፍ ስር መወለዴና በመድፍ አፈሙዝ ቅኝት መሰቃየቴ አይደለም:: ሌላ ነገር ነው"

«ምናለበት እንደው ምናለበት እንደው ምናለበት (አንዳንዴ አራቴ ይለዋል ይሄንን) ፈጣሪ ጌርሳሞትን ወንድ ቢያደርግልኝ ኖሮ» ይላል:: እኔ ፊት:: ከዛ ሊያባብለኝ አቅፎ ይደባብሰኛል:: እንዲህ ተናግሮ እንዲህ ሲደባብሰኝ እጠላለሁ:: አባታችሁ መጀመሪያ አጣጥሎ ቀጥሎ ደሞ በማይሆን ፍቅር ቢፎግራችሁ የምትወዱ እስኪ እጅ አውጡ::

አለ አደለ ልገምት: ወንድ ብሆን መድፈኛ ሊያረገኝ ነበር መሰል የባርያው ልጅ:: አባቴ አነጣጣሪ ቅልጥም ሰባሪ ያደንቃል:: ግን ቅልጥሚ ለቁመቴ ብቻ ነው:: ክንዶቼ ሰላላ ስለሆኑ ቀጫጫ ወንድ ከማቀፍ ይልቅ ሳይንቲስት ብሆንና የማይክሮስኮፕ ብሎን ባዞርባቸው ይቀላቸዋል:: እኔ እንደ እናቴ ሰናና፣ ቀርፋፋ፣ አልቃሻ፣ መንጎላምና አንጎላም ሁለመናዬ ከትንንሽ ነገሮች የተሰራ በኩረዳነቴ ወዝ የማብለጨልጭ የምቅበጠበጥ ገና ሲያዩኝ በወንዶች ልቦና ሃሴት የምቀሰቀስ የዐይን ማር፣ ይታያችሁ መድፍ አገላባጭ ስሆን:: ያውም ብቻ ለብቻ:: እንጀራ አባት ሆኖ ያሳደገው ታላቅ ወንድሜ ገና ሃያ አምስት ሳይሞላው ራሱን ችሎ ሄዶአል (ላፍቶ):: እማማ ከማን እንደ ወለደችው አታውቅም:: ኮሌጅ የበጠሰች (ባዮሎጂ) ዲቃላ ቀፍቃፌ ናት:: ምን አይነት ብሬይን[5] ነው ያላት በገብሬል? የመጨረሻዋ የአብራካቸው እንጥፍጣፊ ነኝ:: ማለት ለእሱም ለእሷም::

እናቴ ጌርሳሞት ሳይሆን 'ባፈና' ትለኛለች (አበሻ የማይጠቅም የስም በዘበዛ እንደሚወድ ይሄውልሽ ጀለስ አንድ ምሳሌ):: አንዳንዱ የሰፈር ሰው እሷን ተከትሎ 'ባፈና' ይለኛል:: የእስዋን የአጠራር ልማድ የቀለቡ 'ስም ይወጣል ከቤት ይከተላል ጎረቤት' ተረትና ምሳሌ አማኞች ይሆናሉ:: ወይስ በተመቸን እንጠራለን ነው? ይታይሽ ባፈና የተባለ ስም ሲመች:: የሚያፍን ቢያፍንልኝ::

---

ወዳጆቼ ብዙ ብዙ ስም ሰጥተውኛል:: እነዚህ እርቢዎች እየረቀቁና እየደቀቁ ይሄዳሉ:: ከጌርሳሞት ወደ ጌርሳ: ከጌርሳ ወደ ጌርሲ: ከጌርሲ ወደ ጌራ: ከጌራ ወደ ጌ:: ነገ ደሞ ምናልባት ወደ ምንም::

ከሁሉ ከሁሉ በአያቴ ስም አፍር ነበር:: ማፈሬን ግን ማንም አያውቅም:: 'ባሪያ' ብሎ ስም:: በአባቴ በኩል ወንድ አያቴ እንጨት ፋብሪካ የሚሰሩ ወዛደር፣ ሴት አያቴ ከወጨጫ ጦስኝ ከደን እያጨዱ ዘነበወርቅና ቀራንዮ ጉልት የሚቀመጡ ነበሩ:: በአያቴ ስም ሊያበሽቁኝ ከቃጡ ወይም ካደረጉት 'የእናቴ አባት ሌላው አያቴ የታወቁ ሰው ነበሩ' ምናምን ብዬ የተተረተላቸውን ወይም የተወራላቸውን የማምነውንና የማላምነውን ጀብዱ እዘከዝካለሁ:: የገደሉትን የአንበሳና የዝሆን ብዛት:: በሰይፍ ስንት የባዴ አንገት እንደቀሉ ምናምን:: በዚህ ዘመን ደሞ ቢያንስ በአፍ፣ አርበኛነት እንደ 'ኩል' ነገር ስለተቆጠረ ትንሽ ውሸት ቀማምሜ አድማጮቼ ብዙ ታሪክ የማያውቁ መሆናቸውን ጠቅሼ «ጊቭ» አደርጋቸዋለሁ:: ግን ደሞ ጉራዬን ሰምተው በዚህም ጉራዬ መታመኔን ዘንግቼ በሆነ አጋጣሚ 'ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ስም ከነአያት ተናገሩ' ሲባል ልቦናዬ መውጫ ቀዳዳ ፍለጋ ይባዝናል:: እስኪ በሩን ባትችሉ መስኮቱን ትንሽ ክፍት አድርጉልኝ (የወንድ በር እንደሚሉት):: እናላችሁ በአያቶቼ በኩል እንደታጠበ ጨርቅ ብጠመዘዝ የሚወጣኝ ጦስኝና ሰጋቱራ ነው:: በእናቴ በኩል ደሞ ብጠመዘዝ የሚፈሰኝ ቁሊነትና ምንም ነው:: በአባቴ በኩል ብጠመዘዝ ምን እንደሚወጣኝ ለእማማ እየቀለድኩ 'አባትሽን ስነግራት፣ 'ይሄ ያስጠጣል' ትላለች:: ግን አትጠጣም:: ካወቅሁ ወዲህ ይህቺን ያህል አልቀመስኩም' ትልና ብርጭቆ አንስታ ውሃ ወለል ላይ ጠብ ታደርጋለች:: የሚገርመኝ የመሃላዋ ቄንጥ ሳይሆን፣ ይሄን መግለጫዋን በምታደርግበት ቀን፣ ሰአትና ደቂቃ ሁልጊዜ ውሃ የተሾመ ብርጭቆ አጠገቧ አለ:: ልክ ያን ቀን እንደዛ መናገሯ እንደማይቀር አስባ ቀደም ብላ ጎንዋ ያስቀመጠችው ይመስላል::

አባቴ ስታድዮም መሄድ፣ ብዙ ፍራፍሬ መብላት፣ ብዙ ሰላጣ ያውም ጥሬውን መቆርጠም ('መቆርጠም' ያልኩት ይሄን አረንጓዴ

---

ሲያጋፍፍ አምስት ሜትር እርቄ ሙዚቃ እስከ መጨረሻው ከፍቼ እንኳን ስለምሰማው ነው) አንድ ብቸኛ ናሽናል ጂኦግራፊክ መጽሔት[6] (ብቸኛ ስል የምር አንድ ማለቴ ነው) ማንበብና በተለይ እንጀራ በጎመን ወጥ መብላት ይወድ ነበር:: ሁልጊዜ ድፍን እንጀራ ዘርግቶ መሐል ላይ አዘፋዝፋ የኮረብታ ቅርጥ ያለው፣ ትንሽ ከረሱት በረቀቀ ፊዚክስ እንደ ባቢሌ ድንጋይ በእሽኮኮ የቆመ፣ በሽሮ ትከሻ የዳበረ ወፍራም የጎመን ወጥ ይቀርብለታል:: ጥርሶቹ ፍንጭት ውስጥ ከሰአትና ማታ በበርበሬ የቀላ የእንጀራ ደለልና ቆስጣ አይጠፋም:: ጥርሱ እንደ ኩታ ቢሆን አረንጓዴና ቀይ ጥለት እፉ ውስጥ ያስሸመነ ይመስላል::

---

[6] ይሄ መፅሔት የታተመው ከብዙ አስርታት በፊት ነው:: ኮላሴ ሁልጊዜ የሚያነበው ይሄን ብቻ ነው:: ብዙ ዘመን ስለተጠቀመበት ልባሱ በተለያየ አይነት ቆሻሻ ተሸፍኗል:: የፊት ልባሱ ላይ እንባቢውን አተኩሮ የሚያይ የሆነች ሴትዮ አቅፋ የያዘችው ገላጻ ባቡን (በሳይንሳዊ ስሙ ቴሮፒቲከስ ጌላዳ የተባለ) ዝንጀሮ አለ:: መጽሔቱ ከመጀመሪያው ቢገለጥ ከጥቂት ገፆች በሁዋላ በኪሊማንጃሮ ተራራዎች ላይ የሚኖሩ የኮንጎ ዝንጀሮዎች የየቀኑ አኗኗር በፎቶ ተመዝግቦ ይታያል:: ኮላሴ ባለችው ሰናና እንግሊዘኛ የውስጡን ዘገባ ራሱ ባልገባው ምክንያት ከመቶ ጊዜ በላይ ደጋግሞ አንብቦታል:: ከሚስቱ ከመግደላዊትና ከልጁ ቀጥሎ የሚወዳት ይህቺ በአፍሪካ አህጉር ኮንጎ በተባለው ደናማ አገር ከነዚህ ዝንጀሮዎች ጋር የምትኖረውን ዳያን ፎሲ የተባለች ነጭ ሴትዮ ነው:: ለብቻው ሲሆን ይህቺ ሴት ስለዝንጀሮዎቹ የተናገረችውን መልካም መልካሙን እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ በቃሉ ያነበንባል: (ዘ ሞር ዩ ለርን አባውት ዘ ዲጊኒቲ አፍ ዘ ጎሪላ ዘ ሞር ዩ ወንት ቱ አቮይድ ፒፕል:: The more you learn about the digAnity of the gorilla, the more you want to avoid people. ስለዝንሮዎቹ ግርማ ሞገስ ስታውቁ ከሰዎች ለመራቅ ትፈልጋላችሁ) (ዩ ቴክ ዚዝ ፋይን ሬጋል አኒማልስ፣ ሃው ሜኒ ፋዘረስ ሃቭ ዘ ሴም ሴንስ አፍ ፓተርኒቲ? ሃው ሜኒ ሁማን ማዘረስ አር ሞር ኬሪንግ? you take these fine regal animals. how many human fathers have the same sense of paternity? how many human mothers are more caring? እንደ እነዚህ ዝንጀሮዎች ልጆቹን የሚወድ የሰው አባት አለ? ለልጆቹስ እንደነዚህ የዝንጀሮ እናቶች የምታስብ የሰው እናት አለች?)::

---

በኩራት እንደሚያወራው ከአስራ ስምንት አመቱ ጀምሮ የጊዮርጊስ እግር ኳስ ቡድን ደጋፊ ነው:: ‘ያለ ጊዮርጊስ ስታድዮም አያምርም’ ይላል:: ውሸቱን ነው:: የምር የሚወደው አምባጓሮ ለመቀስቀስ የሚያመቸውን ቡድን ነው:: አንዱን ቡድን እያሞጋገሰ ግን ሁሉንም ይተርባል: አንዱን የሚያሞጋግሰው ሌላውን መተረቡ እንዲያምርለት ነው:: ‘ምን እንደው የሚያስመርር ነገር ኳስ ዱሮ ቀረ፣ ደርግ ስፖርቱን ገሎት ሄደ’ ይላል:: እንዴት ነው ስፖርት የሚገደለው? ሜዳው በቦንብ ይመታል? ወይስ ሱቆች ኳስ አትሽጡ ይባላሉ? ምናልባት አላየሁምና ደርግ ኳሱን ጠፍጣፋ ወይም ሬክታንግል አድርጎት ሊሆን ይችላል:: እንዴት ነው ሳንጆርጅ የአገሪቷ እግር ኳስ ባህል ‘ሰብሴት’[6] (ንዑስ ክፍል) አይደለም እንዴ? (‘ሰብሴት’ ያልኩት ልዘንጥባችሁ ነው)::

ልጅ እያለሁ ቅዳሜና እሁድ (ዛሬ ሳሰላው ነው) አባቴ ሰባት ሰዓት አካባቢ ምሳውን በልቶ ከቤት ይወጣና ማታ ሊጨልም ሲል ይመለሳል:: ቀጭ ብዬ ቡና የሚጋቱ የሰፈር ሴቶችን ወሬ ሳዳምጥ፣ መረጃ ስሰበስብ፣ የእንስትንነት ቄንጥ ስማር ከተቀመጥኩበት ሳልነሳ ቁና ቁና እየተነፈሰ ይገባል:: በዛ ሰዓት ከየት እንደመጣ ማንም ስለሚያውቅ ቡና አንቃራሪዎች:

--አይደክምህም እንደው እዛ ስትደርቅ ይሉታል

ቡና በጦስኝና በጨው እንድሰጠው ይጠይቀኝና፣ ቡጢ ባዛለው ጸጉራም ግራ እጁ እየተቀበለ:

--ስታድዮም ዛሬ ዘፈነው ይላል::

--ምን ዘፈን ያ የፈረደበትን ጌርሳሞት ጌርሳና?[7] ብለው ይስቁበታል

---

[7] (አዲስአባ ስታድዮም እግር ኳስ ጨዋታ ሊያዩ የገቡ ሰዎች የቡድናቸውን ስም እያስገቡ እንደ ጆከር የሚጠቀሙበት የሜዳ መዝሙር ነው::)

*ሆሆሆሆሆ ሃሃሃሃ!!! ጌርሳሞት ጌርሳና!*

*አንጠጣም የእሁድ ቡና!*

*ብቅ በሉ ወንዶች ተራ!*

*በሽበሽ በሉ በሳንጆርጅ ቢራ! ሆሆሆ ሃሃሃሃ!!! ሲል*

*የጊዮርጊስ ደጋፊ......*

*የቡና ደጋፊ ደሞ:*

*ሆሆሆሆሆ ጌርሳሞት ጌርሳና*

---

--ቂል ሁሉ ይልና ራሱ በሳቅ ይፈርሳል

(ስሜን የቀዳው ከዚህ ዘፈን አዝማች ይሆን እንዴ?)

ለመሆኑ አሮጌ መጽሔት፣ ኳስ፣ መደባደብ፣ አተር ሽሮና ቆስጣ ምን ያገናኛቸዋል? ኮላሴ ይሄ ነው::

አባቴ ግዙፍ ሰው ነው:: ቁመቱ ሁለት ሜትር ይሆናል:: ፊቱ በጢም የተሸፈነ ነው:: ስለዚህ በየቀኑ ይላጫል፣ በገጠር ስራው መንገድ ላይ እያለ ከሚፈልገው በላይ ያደገ ከመሰለው መኪናውን አቁሞ ወንዝ ዳር ይላጫል:: ይሄን ሲያወራ በኩራት ነው:: ቅንድቡ ከግንባሩ ወደ ዐይኑ ውስጥ ለመውደቅ የሚጥር ይመስላል:: እንዲህ ስል የምሬን ነው:: ሰዎች ሲያዩት የተጋነነ ወንድነት ይሆንባቸዋል:: ስፊ አፉን ለወሬ ሲከፍት በፍርሃት ብቻ ያለክርክር የተናገረውን ነገር ሴቱም ወንዱም ያምኑታል::[8] የግንባሩ ጠባብነት፣ የጥርሶቹ ትልልቅ መሆንና

---

*አንጠጣም የእሁድ ቢራ*
*ብቅ በሉ ቡና ተራ*
እንዲል::

[8] ኮላሴ 'ቋሚ የምደግፈው የእግር ኳስ ቡድን አለኝ' ይላል እንጂ የለውም:: የሚደግፈው በመረጠው ሰአትና ደቂቃ ደስ ያለውን ቡድን ነው:: ሌሎች ተመልካቾች ድጋፉን በመቀያየሩ *የዞረበት* ያደርጉታል:: ኮላሴ የስታድዮም አድርባይ ነው:: ለመሆኑ የአዲስአባ እግርኳስ ቡድኖች አንዱ ከአንዱ ምንድነው የሚለያቸው? ለመሆኑ ለያደርጋቸውም *ታዲያ? እሱ ማነው? ያ የዞረበት!* ብለው በንቀት የጠሩትን አንዳንድ እግር ኳስ እናውቃለን ባዮች እንዳይረሱት አድርጎ ቀጥቶአቸዋል:: የብዙዎችን የስታድዮም ሰዎች አፍ የዘጋበት ቀን እንዲህ ሆነ: አንድ በዛን ቀንና ሰአት በሚደረገው ጨዋታ ላይ የደበረው የአንደኛው ቡድን ደጋፊዎች ያሉበት ቦታ ሄዶ የእነሱን ባላጋራ ቡድን እየደገፈ ረበሻቸው:: ገለባብጠው በአራድኛ ተረቡት:: የተረቡትንና ለተረቡ መልስ የሰጡትን ብልጣ ብልጦች፣ ንቀው ሊመቱት የዛቱበትንና የቃጡትን ተንጫጪዎች ከደረጃ ወደ ደረጃ እንደ እቃ እየወረወረ ፈጃቸው:: እንዲህ ማድረጉ አልበቃውም:: ሽቦ አጥር ዘሎ ሜዳውን አቋርጦ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ መሮጥ ጀመረ:: ከተቀመጡበት ቦታ ሆነው የሚያዩትና የሚታዘቡት ወደ ወዳጆቹ የሚሄድ መስሎአቸው ሲጠብቁ እዛ እንደደረሰ ትቶት የመጣውን ቡድን በመደገፍ

---

የተቀላቀላቸውን አዲስ ሰዎች ከዳር እዳር አመሳቸው:: ፖሊስ ሲ.መጣበት ከስታድዮሙ ከፈፍ ላይ ወደ መሬት ዘለለ:: ዘሎ ግን ምንም ሳይጎዳ በቀኝ እጁ ግራ ፊቱን እየዳበሰ ጥፋት እንዳላጠፋ ሁሉ ወደ መስቀል አደባባይ አቅጣጫ በቀስታ እርምጃ ሄደ:: ያ ድርጊቱ ባዩት በስታድዮም አፍቃሪዎች እንደ ልዕለሰብዕ ድርጊትና እንደ ተረት ይወራል:: ስታዲዮም በገባባቸው ጊዜያት ያልመታው እዩኝ እዩኝ ባይ አምባጓሮኛ ጥቂት ነው:: የቲፎዞ ፊታውራሪ ነን የሚሉ ፈርተውታል:: እስከዛሬ ግን እንዴት ያጋጠመውን ክለብ እንደሚደግፍና ለዛም አጭር ፍቅሩ የሰው ደም እንደሚያፈስ አጥንት እንደሚሰብር አልገባቸውም:: መልሱ ቀላል ቢሆንም መልሱን ማመን አልቻሉም:: ኮላሴ መደባደብ ይወዳል:: ለምን ግን እንዲህ ያደርጋል? እነሱ ምክንያቱን አያውቁም:: አቶ ኮላሴ ግን ምክንያት አለው.......

በየወሩ ወይ በየሁለት ወሩ ወይ ከፈረደበት በየሁለት ሳምንቱ ከልጅነቱ ጀምሮ ሲያይ የነበረውን ሕልም ያያል:: ይሄ ከአእምሮው ሚስጢራዊ ተራራ የተፈለፈለ የሌሊት ልጁ ነውና የገደል ሕልም ብሎ ሰይሞታል==ስም ያስፈልገዋል:: የሕልሙ አካሄድ፣ አወቃቀር፣ ስፋትና የሴራው ጥብቅነት ቢለያይም ያው ያ ሕልም እንደሆነ ይገባዋል፡ አንዳንዴ ሕልሙ ከመጀመሪያ፣ አንዳንዴ ከመሃል አንዳንዴ ከመጨረሻ አንዳንዴም በተዘባረቀ ተከታታይነት ቢመጣም፣ ያው ሕልም እንደሆነ ያውቀዋል:: በሩብ በሩብ ተቆራርጦ ቢመጣ እንኳን እሱ እንደሆነ ይገባዋል:: ይሄ ያስገርመዋል:: ሲመስለው ከመጀመሪያው (ገና ሙሉ በሙሉ ትዝ በማይለው ልጅነቱ) ሕልሙን በተሟላ መልክ እንደ ፊልም ደጋግሞ በማየቱ የደረሰበት እውቀት ይሆናል:: ሙሉው ሕልሙ እንደዚህ ይሄዳል፡ የዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ተቀምጦ ወደ ታች ያያል:: ታቹ ገደል ነው:: ገደሉ ስር በቅጠል፣ በዛፍና በቁጥቋጦ የተጋረደች ዝቡጥቡጥ ጅረት አለች:: ከፊት ለፊቱ ትልቅ የኮሶ ዛፍ አለ:: የኮሶ ዛፍ አንዴም በዐይኑ ሳያይ ነው የኮሶ ዛፍ መሆኑን ሕልሙ የነገረው:: የኮሶ ዛፍ ይሄ ነው ለካ ብሎ ለራሱ ያረጋግጣል:: ቀዝቃዛ ነፋስ በላዩ ላይ ያልፋል፣ የሞቀ ገላውም ይንቀጠቀጣል:: ራቁቴን ነኝ እንዴ? ብሎ ራሱን ዝቅ ብሎ ሲያይ ክንዶቹ ነፋስ ውስጥ የሚርገፈገፍ ረዥም የፀምር ኮት ለብሰዋል:: ሁለመናው በጸጉር ተሸፍኖአል:: ትክክል እንደሆነ ሁሉ ግን ኮላሴ አልደነገጠም:: ለምን አልደነገጠም? ባለመደንገጡም ይገረማል:: ግራ እግሩን የሸፈነው ፀጉር ላይ ኩበት ደርቆበታል:: ዝንጀሮ ነኝ እንዴ?! ብሎ ጮኸ፣ ይሄን እሪታ ተከትሎ ቀዝቃዛው ደን ለሰኮንዶች በአራዊት ሆታ ታመሰ:: የድምፁን ማሚቶ እየሰማ እያለ አካሄዷ ቀልጠፍ ያለ ደረተ ነጭ ዝንጀሪት (ገላዳ ባቡን) ተፍ ተፍ እያለች አግድም በተዘረጋ የዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ወደ እሱ አቅጣጫ መጣች:: ለአፍታ ቆማ

እነዚህ ጥርሶቹ የተንጠለጠሉብት ድዱ ቅላት እንደዛ ያስኛል። ሁልጊዜ ከራቫት ስለሚያደርግ አይታይም እንጂ ደረቱ በሙሉ እስከ

---

አየችውና ፊቷን አዞረች። የመቀመጫዋ ቅላት ከቆመበት እርቀት እንደበሰለ ሾላ ያበራል። ዐይኖቹን ከዛ ያበጠ ኳስ ላይ መንቀል አልቻለም። ሁለመናው በስየታ ተቁነጠነጠ። ያኔውኑ አንድ ገመሬ በስተግራ በኩል ካለ ትልቅ ቅርንጫፍ ላይ ብቅ አለና በፍጥነት ዘሎ ያለችበት ቅርንጫፍ ላይ አርፎ ዝንጀሪትን ታከካት። ያኔውኑ እግሩ ስር አዙሮ ወደ መጣበት ከመመለሱ በፊት ጀርባዋን ዳበሳት (ዘፋኝ የልቡን ይሆን? እያለ አሰበ)። ከዛፍ ዛፍ፣ ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ እየዘለለ እንስቲቷ ወዳለችበት ሄደ። ገመሬው ዞር ብሎ የአዘላለሉንና የአቋራጭ መንገድ መረጣውን እንደሚያደንቅ ሁሉ አየውና ፊቱን አዙሮ የሚበላ ቅጠል ተረጋግቶ መቀንጠስ ጀመረ። ቸል ያለ ቢመስልም እንስቲቷን እንዳይቀርብ ገመሬው የሚያስፈራራው ይመስለዋል። ከመሃል እንስቲቷ ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ እየዘለለች ወደ እሱ መጣችና ከእሱ ሳትርቅ ቆም ብላ ግራና ቀኝ እየዞረች የቂጥዋን የበሰለ መላጣ አሳየችው። የዝንጀሪት በልቡ ይጠይቃል። ፍርሃቱ በረደለት። ለምን ይፈራል? እሷ ጋ ለመድረስ የሚቀረው አንድ ቅርንጫፍ ወደ ታች መዝለል ብቻ ነው። አንድ ጊዜ እመር ብሎ ዘለለና እንስቲቱ አጠገብ ቅርንጫፍ ላይ ጠብ አለ። እንስቷ እንደ ኮሸሽላ ትሸታለች። እንደ ጦስኝም ትሸታለች። በእጁ አፉን ታከከችውና ከጎኑ ተንበለበለች። ከሁዋላዋ በፍጥነት ወጥቶ መንቃነቅ እንደጀመረ ከየት እንደመጣ ያልገባው ጥፍራም ጥፊ አፉ ላይ አረፈ። ደኑ በዝንጀሮ ጩኸት ታመሰ። ካካታውና ሆታው የትም ይሰማል። እሱ ከእንስትዋ ጀርባ ተላቆ የሚስቀጥጥ ጉልዛና እያሰማ ወደ ወንዙ መውደቅ ጀመረ። የሚያልፍባቸው የዛፍ ቅርንጫፎች ጀርባውን እየመቱ የአወዳደቁን ፍጥነት አበረዱት። በመጨረሻ የወንዝ ዳር ፊላ ላይ አረፈ............ልክ እዚህ ላይ ከእንቅልፉ ይባንናል። ሲባንን ፊቱን ያቃጥለዋል። ሲባንን ይበርደዋል። በእጁ ይዞ ነው። ሲባንን የተመታውና የተቧጨረው አፉን እያመመው ነው። ሲባንን ሚስቱ መግደላዊት በጩኸቱ ተቀስቅሳ በቀኝ ክርንዋ አልጋ ተደግፋ ዐይን ዐይኑን ስታይ ነው። ሲባንን ሁለመናው በሀፍረት ተሞልቶ ነው። አፉን እያሸ፣ ቁና ቁና እየተነፈሰ ጨለማ ውስጥ ሲያፈጥ መግደላዊት *አፍህ ምን ሆኖ ነው እንዲህ የሚሸተው?* ትለዋለች። አፉ የሚሸተው እንደ ኮሸሽላና እንደ ጦስኝ ነው።

---

አለብላቢቱ ድረስ በፀጉር የተሸፈነ ነው:: ሆዱ ሁሉ ፀጉር ነው:: ማለቴ ቆዳው አይታይም:: እጆቹ ከመዳፉና ከጣቶቹ አንጓ በተቀር በፀጉር የተሸፈኑ ናቸው:: በግራ በኩል ስስ ከንፈሮቹ ላይ እሱ እንደሚለው ሲወለድ ጀምሮ አብረውት የተወለዱ ሶስት የጠባሳ መስመሮች አሉ:: አንገቱ አጭርና ሰፊ ነው:: ሲራመድ ፈጠን ጎበጥ ይላል:: አንዳንዴ ከመፍጠኑ የተነሳ የሆነ ቦታ ከባድ ቀጠሮ ያለበት ይመስላል:: የሚሄደው ግን ስታድዮም ነው:: የማይፈልጋቸው ሰዎች ሲቀርቡኝ በቁመናው ብቻ ሳይሆን ከቁመናው በሚጣረስ ቀጫጫ ድምፅ ሲናገራቸው ለአፍታ እቆሙበት ፈዘው ይቀራሉ:: ሁለቱን ነገሮች ማስታረቅ ጊዜ ይወስድባቸዋል:: የአባቴን ሁለመና ስለለመድኩት አልሸሸውም፣ አልጠላውም፣ አላፍርበትም:: የአባቴ ውበት ግርማው ነው:: አጠገቡ ስሆን ሞቅ ያለ ተራራ ያስታውሰኛል:: 'ተራራ እንዴት ነው ሞቅ የሚለው?' አትበሉኝ:: ግን እንደዛ ነው::

በሰው በሰው ወሬ እንደሚደርስን አባቴ ለቁጥር ለሚያታክት ጊዜ ተደባድቧል:: ኳስ አይቶ ቤት ተመልሶ ሲመጣ እወደዋለሁ የሚለው ቡድን መሸነፉን በለምቦጩ አወዳደቅ እንጠረጥራለን፣ ባይነግረንም እንደተደባደበ ይገባናል:: ያን ቀን ማንም ምንም ሳያናግረው 'ማንም እንዳያናግረኝ ሁላችሁም ዞር በሉልኝ' ይላል:: ሺህ እማማ አትሰማውም:: ጎኑ ተቀምጣ እንደ ልጅ ታባብለዋለች:: ቢያጠፋ እማማ በማቆላመጥ *የእኔ ጌታ ደሞ ምን አደረክ?*[9] ትለዋለች::

---

9 መግደላዊት ባሏ ኮላሴ ማን እንደሆነ ሳታውቅ ነው ቤቱ የገባችው:: የት እንደተወለደ፣ የት እንደተማረ አታውቅም:: ስለልጅነቱ አታውቅም:: ስለእሱ ብዙ አለማወቋ እየከነከናት ከእንቅልፍዋ አልጠየቀችውም:: ስለእሱ ብዙ አለማወቋ እየከነከናት ከእንቅልፍዋ የባነነችበት አንዳንድ ጊዜ ነበር:: ስሙን ብቻ ነግሯት ከሰበታ አካባቢ በመስሪያቤት መኪናው ጭኖ ወጨጫ ተራራ ግርጌ ታቦት ማደሪያ ቤቱ ይዞአት መጣ:: መግደላዊት ራሷም አባትና እናቷን ሞሳ እያለች ነው ከሕይወቷ የተሰወሩት:: ሁለቱም ትዝ የሚሏት እንደ ሕልም ነው:: አልፎ አልፎ በቅዠትዋ ታያቸዋለች:: በቅዠትዋ የምታያቸው ሰዎች ወላጆቿ ይሁኑ አይሁኑ ግን ማረጋገጫ የላትም:: በየዘመድ ቤቱ እየዞረች ነው ያደገችው:: አንዱ ሲጥላት፣ አንዱ ሲያነሳት፣ አንዱ ሲደፍራት፣ አንዱ ሲያባብላት:: የእነዛ ሁሉ የበደሏት ሰዎች ትዝታ ከውልብታ የደመቀ አልነበረም:: አይደለምም:: ራሷን ማስተዳደር የቻለችው እጅግ ብሩህ አእምሮ ስለነበራት ብቻ ነው:: አንዳንዴ እናትዋን ወይም አባቷን ወይም

---

ሁለቱንም አንድ ጊዜ እንኳን ብታያቸው ከልጅነቷ ጀምሮ እየንዳ ያመጣት ስለመኖሩ የማትናገርለት ድብርት ከላይዋ ላይ የሚረግፍ ይመስላታል:: ከላሴን ስለቤተሰብ ጀርባው የማትነተጉተው ራሷ በትክክል ከየት እንደመጣች ስለማታውቅ ነው:: ጥያቄዋ ለኮላሴ ጥቃት ቢመስለው እሷም ላይ የተሰነዘረ ጥቃት ይሆናል::



በወጣትነቷ መግደላዊት ዘመዶቿ ቢጎዷትና ቢያቆስሏትም በራሷ የምትተማመን በርትዕ እንደበት የምትከራከር፣ አፏን ሰቅላ የምትሰቅና ደስ ያላትን የምታደርግ ልጅ ነበረች:: ወንዱ ቢራ ከጠጣ ሴቷስ? ወንዱ ሰፈር አደንቁሮ ከሳቀ ሴቷስ? ሃያኛው ክፍለዘመን እያለቀ አደለ እንዴ? ይሄ ይሄ የግልፅነትና የደፋርነት መንገድ ግን ያልጠበቀችው ቦታ ወሰዳት:: ስለሴቶች እኩልነት የሚሰብከው ተምሬአለሁ ባይው የሕብረተሰብ ክፍል ስለሴቶች እኩል መሆን ግድ እንደማይሰጠው፣ ነፃነት እንደማያበዛ ቆይቶ ገባት:: ነፃነት የሰፈነበት ህብረተሰብ ወሬ መቀበሉና መስጠቱ በደመነፍስ ስለሚመጣ እንዳለውም አያውቅም:: እየቆየ ተሟጋችነቷ፣ ወንድ በተረብ አብጠልጣይነቷና በገላዋ የፈለገችውን ማድረግ ‘ባለጌ’ የተባለ የማታመልጠውን ስም አሰጣት:: ይኼ ይኼ እያስጨነቃት ቢራ ላይ አተኮረች:: ቢራ መጠጣቷ ሞቅታ ሆነ:: ሞቅታው ልብ ሳትለው ስካር ሆነ:: ስካሩ ራስን እየሳቱ የትም መውደቅ ሆነ:: ስድቡና ሽሙጡ ረቀቀ:: የተወረወረባት ዕርፈት ከቃል አልፎ እውን መሆኑን ስታይ ሁሉን ሰው ፈራች:: ሁሉን ሰው ጠላች:: ዞር ግድ አልሰጣትም:: ስካር ስትደጋግም ገንዘብ እያነሳት ጋባዥ ፈለገች:: ጋባዥዋም በመልሱ እሷን ፈለገ:: የስብዕናዋን ምድር ምሳ የምትጠጣ የጥፋት ሞተር የጫነች ወይዘሪት ሆነች:: ለአንጓጠጧትም በግድየለሽነት እግሯን አነሳች:: የማሕፀንዋ ምጣድ ላይ ሊጡን ያላዞረ ማነው? (አእምሮዋን የምትጠቀም ጠንቃቃ መሆኗ አልቆ ግድየለሽ የሆነችበት የጊዜ ወሰን የትና መቼ ጋ እንደሚጀምር ሁልጊዜ ይሳታታል) ሕብረተሰቧ በአሉባልታው እንደፈጠራት ሲገባት ብልጠቱን ፈራችው:: መሸሽና መደበቅ ፈለገች:: መሸሺያና መደበቂያ ግን አልነበረም:: ኮላሴ አንድ ቀን መጣ:: አያት:: አብሮአት አመሸ:: ወደዳት:: አወቃት:: የሰደባትን ያዋረዳትን አለም ሰብሮ ድንኳን ሆናት:: ባትፈልግም የገላመጥዋትን መልሳ ገላምጣ ማደር ቻለች:: እሷ ላይ አፉን ለስድብና ለሽሙጥ የከፈተ ለዘላለም ይዘጋበታል:: መግደላዊትን አናውቅሽምና ነው፣ የሆነ አውሬ የመሰለ ባል አገባሽና መፎለልሽ ነው? ያሉዋት ሁለት ስዎች ዛሬ ድረስ ያለመንገጭላ ለሃሜታቸውን እያዝረበረቡ ይሄዳሉ::

---

ሲበዛባት ታኮርፋለች፡፡ አኩርፋ መኝታ ቤት ገብታ ትዘጋለች፡፡ ማኩረፉዋን እንዲያይባት ወይም እንዲያውቅባት አትፈልግም፡፡ አይገርምም? ማኩረፌን የማኮርፊው ሰው ካላየ ለምን አኮርፋለሁ? አባቴ ወላጅ ብቻ ሳይሆን የቤታችን የፖለቲካ ጉዳይ ሃላፊ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የባህል ሚኒስትርና ያው የማይቀረው የስድብና የጥፊ ሚኒስትር ነው፡፡ ሹመት በደራረቡ በአገሩ መሪዎች ሲያላግጥ ሳቄ ይመጣል፡፡

---

እያደረጓት ከሚያሟት አደርባይ ወንዶች የሚጠብቃት፣ ለእሷ ክብር ጅራፍ የሚያነሳ ኮላሴ ባርያው ወደዳት፡፡ ሲወራ የነበረውን ሰምታለች፡ *ገላገለኝ*፡ ለኮላሴ መሆን የተመኘችው ለመጀመሪያ የተገናኙ ቀን ክንዱ ላይ ሆና ነው፡፡ መጀመሪያ አምቶ ከዛ አባልጎ ከዛ አምቶ ያባረራት ህብረተሰብ ካፈረና ከፈራ ለምን ግድ ይኑራት? መግደላዊት የተባለች ቆሬ የተባለች ቁሌታም የተባለች ሰካራም የተባለች ልክስክስ የተባለች ምናምን ረጋች፡፡ ሚኒስከርት የማይበቃት ልጅ ቀሚሷን እስከ ቁርጭምጭምቷ ዘረጋች፡፡ ኮላሴን ከወደደች በኋላ የትም አይደረስምና መጀመሪያ ያደረገችው ነገር መፅሐፍ ማንበቧን ማቆም ነበር፡፡ በአሉባልታ አገር ላይ ምርምር ምን ይጠቅማል?

የመናገሻ ተራሮች ደን በመራቆቱ ባሳሰባቸው ዜጎችና በመስሪያቤቷ ከተቋቋመው ፕሮጀክት ስራ በተቀር ለሌላ ጉዳይ ቢሮ መግባቷን ቀነሰች፡፡ ኮላሴ ሁልጊዜ የሚበላው ጥሬ ቅጠላቅጠልና ዱለት ነው፡፡ ዱለቱ ከሌለ የሚተካው ለጋ የምላስና ሰንበር ጥብስ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በስራ ምክንያት ቤት ካልመጣ ለምሳ የሚቋጠርለት ደህና ሆኖ የተጠበሰ ሳር ሳር የሚል ድፍን ምላስ ነው፡፡ ይሄ ፀባዩ አንዳንዱን ሰው ግራ ስለሚያጋባው የሚበላው ከሰዎች ተደብቆ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከስራዋ ስትመጣ የኮላሴ እራት ተሰናድቶ እንደሆነ ሰራተኛዋን ትጠይቃለች፡፡ ራቱ እንደተሰራ ካረጋገጠች በሁዋላ መግደላዊት ነጠላዋን ደርባ ሶፋዋ ላይ ትጋደማለች፡፡ ገና ከስራ እንደገባ የሚበላ (ብዙ ጊዜ ግን በቁና ላይ የተቀመጠ ታጥቦ የደረቀ ቆስጣ ይቆረጥማል) የሚጠጣ ሳይጠይቅ ጌርስዬ አለች? ይላል፡፡ መግደላዊት የነጠላዋን ጥለት እያላመጠች 'እዚህ ነኝ' ትለዋለች፡፡ የነጠላዎችዋ እድያት ከዚህ ቅርፃቸው  ወደ  ተለውጠዋል፡፡ ኮላሴ መግደላዊትን ከሶፋው ላይ ሰቅስቆ ያነሳና ነጠላዋን ከላይዋ በጥርሱ እንደ ሙዝ ልባስ ይገፋዋል፡፡ ራቁቷን መሆኗን ሲያይ የሰውና የእንስሳት ማህበር ደባልቀው የሚስቁት አይነት ሳቅ ያሽካካል፡፡ ወደ መኝታ ቤት ሲወስዳት መግደላዊት ክንዱ ላይ ምያኔ ውስጥ ትገባለች፡፡ ከግድግዳ ጀርባ የሚመጣው የመግደላዊት ድምፅ ወደ ሰፈሩ አልቃሻ ውሾች ጎላዘን ይጠጋል፡፡

---

ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አደገች ብሎ ከጎረምሶች እንዳልቀርብ የሚያደርገው ተንኮል ሰላም እየነሳኝ በመሄላችን የመቃቃር አጥር እየቆመ ነው:: ቢሆንም 'ጌርስዬ' ሲለኝ እንደ ሞሳነት ጊዜዬ ሄደሽ እቀፊው እቀፊው ይለኛል:: በፀጉር የሞቀና የሚመች ገላው ላይ መጠምጠም ያምረኛል::

……ከቤቴ ተነስቼ የክረምት ጎርፍና የበጋ ነፋስ የበጣጠሳት ቀጫጫ አስፋልት መንገድ ለመግባት አንድ ሰላሳ ሜትር መጉዋዝ አለብኝ:: ይህቺን ጎዳና ዘልቄ ብቅ ስል ሁልጊዜ የሚያጋጥመኝ ሱቅ በረንዳ ላይና የቦይ ድልድይ ላይ የተከማቸ፣ ሃሩር እንደ ጠበሰው ቡቺ ምላሱን እስከ ደረቱ የጎለጎለ የጎረምሳ ስብስብ ነው:: ይታያችሁ እንደ በጋ በሚሰራው ማንነቱ በጠፋው ክረምት እኔን የአስራ ስድስት አመት ልጅ ለማባለግ ወጠጤዎች እንደ ወናፍ እያበጡ እየተነፈሱ ተደርድረው ሲጠብቁኝ፣ ያውም ተኩዋኩለው (በጠባብ ኬኔተራ ትከሻቸውን አስፍተው፣ የክንዳቸውን ጠባሳና ንቅሳት እያሳዩኝ፣ የሚሰፍ ላባቸውን እየጠረጉ፣ በሲኪኒ ሱሪ ቆለጣቸውን አሳብጠው):: ነገረ ስራቸውን ጠልቼው አይደለም:: አለ አይደለ ድንገት ስዞጋቸው ወይም የዘጋኋቸው ከመሰላቸው 'ጌርሳ ባርያው!' ብለው ስሜን ጮክ ብለው መጥራት የለባቸውም ማለቴ ነው:: እንዲህ ነው: ለእነሱ ጨዋታ ሊመስል ይችላል ለእኔ ግን ደይን ነው…………ለነገር እንጂ የአባቴን ስም ምን አዘለላቸው? ዘላይ ሁሉ::

በስድስት ስምንት ዓይኖቻቸው ጥቅሻና ሳቅ እየተቀባበሉ (ቀኙ ለቀኙ ዐይናቸው፣ ግራው ለግራው ዐይናቸው፣ ግራው ለቀኙ አይናቸው፣ ቀኙ ለግራው አይናቸው = ከባድ የዐይን ጉባኤ) ሰላም ይሉኛል:: ይሄም ደስ ይለኛል (በልቦናዬ):: እራሴን ጨዋ እነሱን ስድ ለማድረግ ግን *የጎረምሶች አንጎል ከበሰለ ሙዝ ነው እንዴ የተሰራው በማርያም?* እላለሁ ለምትሰማኝ ወዳጄ:: *አልበዛም እንዴ?* ብልም (ደስ ባለው ልቦናዬ ሌላ ገጽ):: የግብዝነቴ ኪነጥበብ ጥልቅ ከሃዲ ነው:: ካስኘኝም *አገር በፖለቲካ ስትታመስ አንጎል እንዲህ በሴሰን ይበላሻል እንዴ?* እላለሁ:: ይህቺ ሁለተኛዋ ውስጧ ባዶ ወግ ቢሆንም ቁም ነገር የመምሰል ጉልበት አላት:: ማጣጣል የምፈልገውን ጉዳይ ሁሉ ከአገር

ፖለቲካ በማያያዝ የረባ ጉዳይ ማድረጌ ይሰራል። ታዲያ አንዳንድ ሞጥሟጣ የወረዳዬ ዜጎች እንደሚሉት ውሸት በርትታ ቤተመንግስት ከመድረሷ በፊት 'ፒሽአፕ' ሰርታ ጠብድላ የምትነሳው ከሰፈራችን ነው። ለምን አይገናኙም? ሰፈርና ዙፋን አይገናኙም ማን አለ?

ይኼው፡ በሚሆነውና በማይሆነው ትንሽ ዞሮብኝ ጎረምሶቹ ዳር ዳር እንደ ንብ አዙዋሪት ብሰራ ማለት ወደ እነሱ ብጠጋ ማነህ ተሳሳትሽ የምትለኝ ባለተራ---ያስጠምድህ በኩታራ---(እንደ እኔ) ያንጠልጥልህ እተራራ (ከዐይኔ አርቆ)--ይመልስህ እጎተራ (ጥራጥሬነት አያጣህምና)። ብትራከረኝ ምን ልበልህ? ጋሼ ምን ልበልህ? ያው የኮረዳ እርግማኔ ይከተልህ። ብትሰማኝም ባትሰማኝም፣ ቢደርስም ባይደርስም እንካ ከልቤ የወጣ እርግማን። ጥያቄ አለኝ ግን፡ ገላዬ ገና ከምጣድ እንደወጣ ህብስት ነው፣ ሲያተኩስብኝ ወደ ማንና ወደ የት ልወርውረው? ተቀምጬ የተነሳሁበት ኩርሲ እሳት እንደላሰው ሁሉ ሲፋጅ ምን ላድርገው? እውነት እውነት እልሃለሁ አትፍረድ፣ ገና የስምንተኛ ሚኒስትሪ አልፌ ዘጠነኛ ስገባ ነው ለታቦት ማደሪያ ወጠጤ የተከሰትኩለት፣ የብሄራዊ ፈተና ውጤት በምጠብቅበት ክረምት። አረማመዴ አልተለወጠ። አለባበሴ አልተለወጠ። ያን እለት ከቦኝ የነበረው መጋረጃ ተገለጠና አፍጠው የሚያዩኝን አየሁ። ምን ተፈጠረ?

ትንሽ ልዘርዝር?

እድሜዬ ወደ አስራ አምስተኛው አመት ሊገባ ደፍ ደፍ ሲል (ዕድሜ ደፍደፍ ይላል? ምንድነው ደፍ ደፍ? ወይስ ተፍ ተፍ?) የሆነ ነው። የግል ልምድ ጠብሶት የሚሄድ ራስን ብቻ ነው፣ ይኼው እምላለሁ። (ምን አስማለኝ ግን? የዘመኑ ወጣት ብሆንም መቼም ከእናቴ ከመግደላዊት የዛገ ወግ ሳይጋባብኝ ይቀራል?) እና የግል ልምድን ከፋም ለማም ወደ ሌላ ላጋባው ቢሉ የሚከብድ ቫይረስ ነው። እንደ ወሬ በኢንተርቪው፣ እንዲህ በጡፍ ማስተላለፍ አይቻልም። እንደዛ እንደዛ የሚሞክር ፈላስፋ ሁሉ ሲቀብጥ ወይም የሚሰራው

ሲያጣ ነው:: አላበዛሽውም? አትበሉኝ:: ባበዛውስ በራሴ ጉዳይ:: አደል? ይህቺ ጌርሳሞት ግለሰብ እንድትሆን ምልክት የተሰጣት በዛ የፍልስታ ጦም መፍቻ ቀን ነው:: ላፍቶ የሚኖረው ትልቁ ወንድሜ ለበዓሉ መጥቶ እማማ 'ባዶ ሆድህን ከምትሄድ በግ ስለታረደ እንደ ልጅነትህ ቆለጡን በልተህ ትሄዳለህ' አለችውና የተንገለጠጠ ከሰል ያውልሽ ብላ እንድጠብስለት አዘዘችኝ:: 'ያስጠላኛል' ብዬ ተከራከርኩ (ስድ ስለመሰለኝ):: እሱም እማማም 'አሁን አንቺ አደገሽና ማፈርሽ ነው' ምናምን እያሉኝ ሲስቁብኝና ሲሳለቁብኝ ጊዜ 'አላፈርኩም' ለማለት በእልህ ልጠብስለት ተቀመጥኩ:: የከሰሉ ፍም በተጫኑት ሁለት የእርጥብ ቆለጦች እርጥበትና የልፋጭ ክብደት እንዳይጠፋ ሳራግብ ቆየሁ:: ቆለጦቹ በእሳት እየጠየሙ ማበጥና ከርታሶቻቸው መስንጠቅ ሲጀምሩ የሚሆነውን የበለጠ ቀርቤ ለማየት ፊቴን በጉጉት ወደ ምድጃው ሳስጠጋ አንዱ ወደ እኔ በኩል ያለው ቆለጥ ድንገት ፈንዳና የሚያቃጥል ሞራ ተፈናጥሮ አፌ ላይ መታኝ:: ወይም ከንፈሬ ላይ:: በጣም ስላመመኝ ጮህኩ:: የመጥበስ እምቢታዬን አጋጣሚው አጠናከረልኝና እያለቃቀስኩ እማማና ወንድሜ እየሳቁብኝ ሁለቱንም ትቼአቸው መኝታ ቤቴ ገባሁ:: አልጋዬ ላይ በሆዴ ተንበልብዬ ለጥቂት ደቂቃዎች በእልህ አለቀስኩ:: ማለቃቀሴን ጨርሼ መታጠቢያ ቤት ገባሁና በመስታወት ፊቴን አየሁት:: ከንፈሮቼ አብጠዋል:: ቀልተዋል:: አደጋው ከባድ እንዳልሆነ ቢገባኝም እነ እማማን ላለማየት ሰበብ አድርጌው ተመልሼ መኝታ ቤቴ ገባሁ:: ከንፈሮቼ አብጠው መንገድ ላይ ብታይና 'ምን ሆንሽ?' ተብዬ ብጠየቅ 'ቆለጥ' የተባለ ቃል የሌለበት አረፍተነገርና ምክንያት ለመፍጠር ሳስብ እንቅልፍ ወሰደኝ:: ምናልባት ከአንድ ሰአት በኋላ ባነንኩ:: ከተጋደምኩበት በፍጥነት ተነስቼ መታጠቢያ ቤት ገባሁ:: መስኮት ከፍቼ የተመታሁበትን ቦታ በድጋሚ በብርሃን አየሁት:: ደነገጥኩ:: ከንፈሮቼ እንዳበጡ ነው:: ስነካቸው ግን አያመኝም:: እንዲህ በመሆናቸው ግን አላስቀየሙም:: ከንፈሮቼ በጣም ማለቴ በጣም አምረዋል:: ማለት ከንፈሮቼ እንዲህ አብጠው ቢቀሩልኝ ተመኘሁ:: ማለት በአምሳለ ምትሃቴ ውበት ራሴው ማለልኩ:: (ትንሽ 'ማለት' አላበዛሁም?)

---

በሚያቃጥል የቆለጥ ክርታስ ፍንጣሪ የተከተቡት ከንፈሮቼ የባሰ እያማረባቸው ሄዱ:: ከዕለታት አንድ ቀን አራት ልጆች: *ዘሪሁን ገሊታ ባካፋ ራሚሱ (አቡ)* ተደነጋግሮኝ እስከወድቅ ቢያፌጡብኝ ለምን? ብዬ ለመመራመር ፅላሎተ አምሳሌን ደግሜ አላየሁም:: እነዚህ ስፈረተኞቼ በዓይኖቻቸው ትኩረት እየነካኩ በአፌ ውበት የበለጠ እንድመካ አደረጉኝ::

ለመሆኑ የአፌ መደነቅ ጥርስን ይጨምራል? እንጥልንም ይጨምር ይሆን? ጉሮሮስ አለበት? ጠረንስ? ድድስ? የምላስን ቅላትና ልስላሴውንስ? ለመሆኑ 'ከንፈርሽ ያምራል' ሲባል የነዚህ ሁሉ ቅንብር ይሆን? ሌላው ገላዬ የት ሄደ? ለመሆኑ ማነው የሚወስነው? ለመሆኑ አንድን ሰው አውቀን ውብ የምንለው እንዲህ በቁንጣሪ መረጃ ነው? ማወቅስ ሲባል ምን ማለት ነው? ሌላን ሰው ማወቅ ቀርቶ ራስን ማወቅ አይከብድም? በትክክል የማንንም ሁለመና ማወቅ አይቻልምና ታዲያ ካልተቻለ በቁንፅል መረጃና ወሬ ውበትን እንወስን ነው? በቁንፅል አንድን ነገር 'ውብ ነው' ብሎ መደምደም በከያኒያን አያስከስስም? በፈላስፎች አያሰድብም?

የተሳሳተ ውሳኔ ቢመስልም እኔ በከንፈሮቼ ብቻ መወደዴ እንግዳ ጉዳይ ሳይሆን ሚስጢርነቱን ማወቅ እንደማይቻል ተረድቶ ብልጥ መሆን ነው:: አለም የሚያውቀው ያልደበቅሁትን ያልተደበቀውን ራሴን ነው: አፌን፣ ቀጫጫነቴን ለመግባቢያ ያስለጠንኩት ሳቄን ነው:: በደቃቃ ሰበብ ወደው ሊያወጡኝ ቢንሰፈሰፉ ለሰው ልጅ የተሰጠው ስልቱ ነውና አልፈርድባቸውም:: ደሞ በራሴ የምተማመን አልነበርኩም:: አንገቴን ደፍቼ አልፋቸው የነበሩት ወንዶች ጨዋ ሆኜ ሳይሆን አያምርም ብዬ የምጠረጥረው ሁለመናዬን ከእነሱ በቶሎ አርቄ ቤቴ ወይም የምጠፋበት ቦታ መፈለግ ነበር:: ዐይኖቼ ትልልቅ ቢሆኑም የሚገባኝ ፈጣጣነታቸው ነው:: ማስለምለም እንኳን አልችልም:: የፀጉሬ ደርዝና ግንባሬ የተለያየ መጠን ባላቸው ሽፍታዎችና ብጉሮች ተሸፍነዋል:: ጆሮዎቼ ቀራፋ፣ ጥርሶቼ ያልተስተካከሉ ናቸው:: ቂጤ ደሞ ቦክስ ያክላል:: ከላይ እስከታች ቀጫጫ ስለሆንኩ የራበው ጅብ ቢያገኘኝ መጀመሪያ ልሶና ነካክሶ

---

አጥንት መሆኔን ሲያውቅ፣ እንድሞከሙክ ለአሥር ቀኖች እቃቂ ወንዝ ዘፍዝፎኝ ያልተሻለኝ ጉልጥምታም መሆኔን ሲረዳ ትቶኝ ወጨጫ ይወጣል:: ማለት ራሴን እቆጥር የነበረው ከጅብ ግዕድ ያመለጥኩ አስቀያሚ አድርጌ ነው::

የምር ግን ብዙ ወንዶች ደስ ይሉኛል:: እነዚህ ደስ የሚሉኝን ባየሁ ቁጥር ገላዬ የማይሆነው ነገር የለም:: ከማውቃቸው በመጠኑ ከምደፍራቸው የሰፈር ልጆች አቡ ተረቡ ደስ ይለኛል፣ ዘሩሁን ልቅም ያለ ቆንጆ ነው፣ ሁኔታው ያባባል፣ ገለታ ደሞ በዲንፑላም ጉንጩ ሲያንጎራጉር ሲያምር:: ባካፉ ሁኔታው ረጋ ያለና ጠንቃቃ ስለሆነ በቃ የሚያስብልኝ ይመስለኛል:: ግን እነዚህ ዞር ብለው ሳያዩኝ ኖረው ኖረው ከንፈሮቼ ሁኔታቸው ከተለወጠ ጀምሮ አይናቸው አለቀኝ አለ:: ደስ ቢለኝም ትንሽ ቅር ይላል:: ማለት በቀደም ዕለት የት ነበሩ?

ያው መጀመሪያ ሰላምታ ነበር የሚያገናኘን (የሰፈር ሰው ሰላም አይባልም እንዴ?)፤ ቀጥሎ አብረን እዚያ ድረስ እንሂድ ይባላል (እግርን የሰራው እግዜር ታዲያ አያልቅ እና ብንወዛወዝበትስ?) ቀጥሎ ት/ቤት ቶሎ ደርሰን ምን እንሰራለን? እዚህ አዲስ ኬክ ቤት ተከፍቶአል ሻይ እንጠጣ፣ ኬክ እንብላ ይሆናል (እኔ ቤቢ እሱ ቤቢ፣ የምንማረው አንድ ግቢ፣ የምንጠጣው ውሃ የእቃቂ፣ ደሞ ስንዴው የከንታኪ) ዶንቺ አምሮብሻል ብለው (ቢያምርብኝም ባያምርብኝም 'ሰው የፈለገውን ሊያገኝ እንዲሁ ውሸትን ይቀባጥር ዘንድ ግዱ ነው' የተባለ ምሳሌ ተፅፎ ይሆናል) ገላዬን የሚገፉ መስለው መንካት::

የእኔ አይነት ኮረዳ ሃብቷ ዕውቀቷ ሳይሆን አይነገርም እንጂ አለመበላሸቷ ነው:: ማለት የከንፈሮቼ ነገር ይሄን መከለያ ይመስለኛል:: የማይደረስበትን ቦታ ዐይን በደረሰበት ቃል መሸፋፈን:: አይወራም እንጂ እነዚህን ልጆች እያሰብኩ በቀን ቅዥት ብነድ ለሌላ አይደለም የሚያበላሸኝ ልጅ ለመምረጥ ነው:: እንነጋገር ከተባለ ድምፄን ከፍ አድርጌ ባልለውም ለመገሠሥ ሲያቅበጠብጠኝ ነው:: ታዲያ ብቅበጠበጥም ብዙ አላውቅምና ገና ሲነካኩኝ፣ ሲላፉኝ፣ በላባም እጃቸው ሲጨብጡኝ ፍርሃት ፍርሃት ይለኛል::

---

ለመሆኑ እንዲህ ዓይነት ለውጥ ሲሆን አባቴ በዝምታ ያያል? የማያይ እየመሰለ ያያል፣ ታዲያ እንዲህ ይለኛል፡

(1) ከዚያ ልጅ ጋር ለምን ቆምሽ?

(2) ምን ይጠበስ ነው መንገድ ዳር ከማንም ጋር!

(3) ሰው ጠፍቶ ነው ከዚያ ጋ? ከትምህርት ትምህርት የለው፣ ከመልክ መልክ የለው፣ ከጎሳ ጎሳ የለው::

(አባቴ ራሱ ከመልክ መልክ የለው፣ ከዕውቀት ዕውቀት የለው:: ደሞ በእናቴ አገር ልጠርጥርና ወንድ ሁሌም ገምጭ ነው:: ጎሳህ ምንድነው አባባ? ፀጉር?)::

(4) ያኛው ምንትስ ነው:: ከምንትስ ምን ትሰሪያለሽ?

መልሴ ከአፌ ሳይሆን ከልቤ ያለገደብ እሱ እንዳያየው ሆኖ ይፈሳል:: ከአፌ ባወጣው ግን ማርያምን መድፍ ይጠራል:: ቅድም የጠቀስኩትን አይነት መድፍ:: ያውም ባለ አራት አፈሙዝ:: አለ እንዴ? ለእሱ ደፍሬ የማልለውን ልበለው? አባቴ የአንድ ጥሩ መፅሐፍ ገጽ ከማንበብ ስታድዮም መሄድ ይሻለዋል:: በንግግሩ ትኩሳት እንደላስቲክ እየተለጠጠ ሳያቋርጥ በሚሰፋው አፉ ስለሚያወራላቸው የባርሳና ማንቼ ጥበበኞች ሳንዘነጋ:: በሰማያዊ ቀለም የደመቀ የስፖርት ጋዜጣና መኪና ውስጥ የሚያስቀምጠውን ብቸኛና ዘላለማዊውን ስለዳያን ፎሲ የሚቀባጥረውን ናሽናል ጂኦግራፊክ ሳንረሳ:: ጋዜጣውን የሚጠቀምበት ተሰሚነት ለማግኘት ነው? ወዳጅ ሊያበጅበት ነው? ሰው ሊባልበት ነው? ለመሆኑ በዚህ ዕድሜዬ ብጫወት ስህተት ነው? እማማን ያገኛት ጠልፎ ነው እንዴ?

አንዳንዴ የቀናው ዕለት ባደገበት የአግቦ ጥበብ፡ --ነይ እስኪ ጌርስዬ የሚያስቅ አዝናኝ ዘፈን እዩ ይለኛል:: ቴሌቭዥን ፊትለፊት ሶፋ ላይ ተንጋሎ::

በቲቪ ይሄን አያለሁ፡ ነጠላውን ያጣፋ የሆነ ለምቦጫም አባት፣ ገፁ ያላበው በጭንቀት ኮልጌት ነክቶት የማያውቅ ካኪ ከለር ጥርስ ያለው የድሮ አራዳ፣ እየባለገች (አፍቅራ) ያስቸገረችውን ሴት ልጁን ለሌላ አላማ የተሰራውን ቲያትር ብልጡ አባቴ ሳሎን ይንተርካል::

መሃል በሾኬ ይጥለውና ወደ እኔ የተቃጣ ምክር ያደርጋዋል። የምር ሮጩ ፍራሼ ስር መቀበር እፈልጋለሁ። እንዴት ነው በዕድሜ ጠኑ የተባሉት ያፈቀሩበትን ጊዜ የሚረሱት? አላፈቀሩም? የማስታወሻ ብልታቸው ፊኛቸው ውስጥ ነው እንዴ? እና ማታ ማታ ከጠጡት ጠጅ ጋር ደርበው ሸንተውታል? ማለት እዚህ ዘመን እስኪደርሱ እየሸኑ ጨረሱት? ፊቱ ላይ የፈሰሰው የአባቴ ጢም አመድ ይመስላል። ፍቅር ማሸሽ ያስረጃል፡ ማለት የሰውዬው ገጽም በበረዶ ይሸፈናል።

ታዲያ ሳይቀናኝ ቀርቶ ነው መሰለኝ የሆነ የእገሩ ፖለቲካ በተበላሸ፣ ነገር በሚያበዛ፣ ከንተሮ እፍ፣ እፍረትቢሰ ሁሉ የጎረጥ በሚተያይበት እንከፍ ዘመን ኮረደድኩ። ሲባል እንደምሰማው ቢያንስ በዘፈን (የማንን ድምፅ ማን ያምናል?) ድሮ ድሮ ዐይን ተገልጦ የታየ ይወደዳል። ባይሳካም ይወደዳል። ዛሬ ዓይን ተገልጦ ይወደድና እንደ አባቴ 'ኅሳው ምንድነው?' 'ሣይማኖቱ ምንድነው?' ይባላል። ሲያልፍ ባይነካኝም--ወለተ አዲስ አባ። ያው መቼም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው እግዜር ያበጀው ሥርዐት ይመስገንና ከአራዊትና ከእእዋፍ በሚያዛምደን የድሮ ባዮሎጂያዊ ስርዓት ኅረምሳ መቀላወጥ እንጀምራለን (ልጃገረዶችን ማለቴ ነው)።

..............................ታዲያ ከቤቴ ወጥቼ የኮረኮንቹን ኅዳና አጠናቅቄ እዛች የተበጣጠሰች አስፋልት ላይ (ቅድም የነገርኳችሁ) ብቅ ስል የሰፈሬ ኅረምሶች ያጋጥሙኛል። ይደናገረኛል። ለእፍታ ቆም እላለሁ። ሰላም ልበላቸውና አልበላቸው ይምታታብኛል። እየፈለኩ ሳወራቸው ቀርቶ ስጠጋቸው እንኩዋን እፈራለሁ (እዚህ የአባቴ ስድብና ማስጠንቀቂያ ትዝ ይለኛል)......

*(ገለታ ዘሪሁን ባካፋ ራሚሱ* ፨ በግራ በኩል አንድ ልኳንዳ፣ በቀኝ በኩል ውድነሽ ላውንደሪ መሃል ያለ የቦይ ድልድይ ላይ ጎን ለጎን ተቀምጠዋል:: ክረምት ያቦዘነቻቸው ተማሪዎች ናቸው:: ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ ከአራቱ አራቱ ወይም ሶስቱ ወይም ሁለቱ እዚህ ቦታ አይጠፉም:: አንዳንዴ ሌሎችም የሰፈሩ ጎረምሶች እዚህ ስለሚሰበሰቡ ቦታው በጎረምሳ የሽሮ ወጥ ግሳትና በከበባቸው ማድቤት ጢስ ፣ በጥሬ ስጋ ጠረንና በወጠጤ ጫጫታ ይጥለቀለቃል:: *ራሚሱ* ከሶስቱ ፊት ለፊት ቆሞአል:: ነጭ የመስታወት ሳይተር በቀኝ እጁ እየወረወረ ይቀልባል:: ጠባብ ጥቁር ጂንስ ሱሪና ቢጫ የሸራ ስኒከር አድርጓል:: ጎፈሬው ወደ ላይ ወደ ታች ደሞ ግራና ቀኝ የቆመ ነው:: ግራ እጁን ኪሱ ከቶአል:: መሃል አየር ላይ ሳይተር የጨበጠ ቀኝ እጁ ለአፍታ ከቆመ ሁልጊዜ ሳቅ አለ:: *ዘሪሁን* አልፎ አልፎ የገለታን ትከሻ በትከሻው እየገጨ ያወራል:: በግራ እጁ የጥርስ መፋቂያ ይዟል:: መልከመልካምነቱ ከሩቅ ይታያል:: ጃኬት የመሰለ አጭር ኮት አድርጓል:: *ገለታ* የአሮጌ ጂንስ ሸሚዙን እጅጌ እስከ ክርኑ ጠቅልሏል:: ካላወራ ያንጎራጉራል:: ሰንበሌጥ የመሰለ ቁመናው በሳቅ ዝማሜ ይሰራል:: *ባካፋ* ሰማያዊ ሸሚዝ በቡናማ ካኪ ኮት ለብሷል:: በቀኝ ኮቱ ኪስ እንደ ከኮቱ ግራ ኪስ አፍ የከራቫት ጆሮ ይታያል:: ዘሪሁን ጠጋ ብሎ ሲያወራለት ማስታወሻ የቀጠነች መፅሐፍ ይዟል:: አንገት ሰበራው ልማዱ አንገቱን ወደ ጎን ሰበር አድርጎ ይስቃል:: በዛች ጠባብ አካባቢ የጠለቀ ነው:: ባካፋ ከተቀመጠበት አይነሳም:: የገለታ ድምፅ ለወሬ እርጋታ የሚታየው ዘሪሁን ሲያፋዋጭ ነው:: 'አንዴ እናቀጣጥለው' ይባባሉና ሲደክም ወይም ገለታ አጃቢ ሲፈልግ ይነቀንቃል:: አልፎ አልፎ መሞዘቅ ይጀምራሉ:: ዘሪሁን በዳንስ ራሱን የጥምቀት ታቦት ጣት ያጮሃል:: በፉጨት የታጀቡ ያማሩ ዜማዎች ይሰማሉ: *ምነው ከረፈደ፣ ከሚያድርበት መንፈሳዊ ቦታ ብዙም ሳይርቅ አድራሻሽ ጠፉብኝ ወዘተ::*

---

在



በወዲያ በኩል አንድ ትንሽ ልጅ ወደ እናቱ ለመሄድ እየሮጠ መንገድ ሲያቋርጥ የሆነ አንድ መኪና በ55 ወይም በ60 እየበረረ መጣ:: መሃል መንገድ ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል የጠረጠሩ ሰዎች ጭንቅላታቸውን ይዘው እየጮሁ ቆሙ:: እዛው አካባቢ የነበረች ልጁን ለምን እንደለቀቀችው ግልፅ ያልሆነ እናቱ ድምጽዋን አጥፍታ እጆቿን ዘርግታ ወደ መንገድ መሃል እየሮጠች ገባች:: የሴትዮዋ ወደ መንገድ መሃል እየሮጠች መግባቷ አነቃቅቶት ሳይሆን አይቀርም ባለመኪናው ፍሬን ያዘ:: ልጁን አፍሳ አቀፈችውና ትንሽ ተንገዳግዳ አስፋልት ላይ ከነሞሳው በጀርባዋ ወደቀች:: ለአፍታ በአካባቢው የድንጋጤ ፀጥታ ነገሰ:: ሰዎች ሴትዮዋን ከወደቀችበት ሊያነሱ እየተንጋጉ መንገድ መሃል ስለተአምርና ስለ እግዚአብሄር እያወሩ ሲገቡ ዘሪሁን በድንገት ዞር ብሎ ወደ ቀኝ አየ:: የዓይኖቹ ትኩረትና የአቋቋሙ ፍጥነት የሌሎቹን ጎረምሶች ልብ ሳበና ሁሉም አንድ ላይ ባይሆንም ተራ በተራ ዘሪሁን ወደ ሚያፈጥበት አቅጣጫ ዞር አሉ:: አስፋልቱን ከሚመግበው አንደኛው ጠባብ ኮረኮንች መንገድ ላይ ዛላዋ የሚያምር፣ ተሰብራ ማሚት ወደ እነሱ አቅጣጫ ትመጣለች::

ጌርሳሞት ጎረምሶችን ስታያቸው (ያላየቻቸው መስላ) የአቀማመጣቸውን ካርታ እንደ አቀዱት ትጠረጥራለች:: በትክክል ምን እንደሆነ ባይገባትም በደመነፍሷ የሚያስተላልፈው መረጃ አለ ብላ ትገምታለች:: ለምን ተዘርዝረው ይቀመጣሉ? ለምን ጉች አይሉም? በመሃላቸው ያለው እርቀት በማይታይ ጉልበቱ እንደመግነጢስ ይስባታል፣ እንደ ፀረ-መግነጢስም ይገፋታል:: ገላዋ ከነፋስ በረቀቀ ነፋስ እንደተገፋ ሁሉ ሲዋኙቅ ይሰማታል:: ባትፈራቸውም ፍርሃት በሁለመናዋ ይገደገዳል:: ዘሪሁን ቀድሞ ይጨብጣታል? በእሱና በሌላ ኋደኛው መሃል ለምን የአራት የአምስት ሜትር እርቀት ይኖራል? ጨባጭ እጇ የአንዱን እጅ ለቆ ሌላው እጅ እስኪገባ ያለው የጊዜና የቦታ እርቀት ማሰቡ ብቻ ሁለመናዋን በከባድ ይረብሸዋል::

---

ለምንድነው ከመሃላቸው ያለው ባዶ ቦታ ከሌላው ጊዜ የቀዘቀዘ፡ ወይም የሞቀ የሚመስለው?

የድርና ማግ መረብ ሆነው፡ ሁለቱ የድር የቀሩት የማግ ሆነው:: ፉክክርም ይመስላል:: ፉክክር መጓተት ነውና መረቡን የማይመች ውጥር ያደርገዋል:: እሱ ብቻ ነው? መረቡ የእነሱ ብቻ ነው? ሰበብ መደረት ካስፈለገ ይሄው፡ የታቦት ማደሪያ ሰፈር አቀማመጥ፡ የመሬቱ ተዳፋት፣ የእሷ በእነዚህ ጎረምሶች መማለል አስተዋፅኦ ይኖረው ይሆን? ስርጭታቸው ልትረዳው ያልቻለችው ሰዋሰው አለው? የገላ ንቅናቄ ግስ፣ የገላ ሙቀት ተውሳከ ግስና ቅፅል አለው? የሰፈራቸው ፌንግ ሹይ[7] ጉዳይ ይኖረው ይሆን? ለምንድነው ከሁሉ ገለታ ጋ ስትደርስ ቅጥዋን የሚያሳክካት? ሁለመናዋ የሚንሰፈሰፈው? ውስጥዋ የሚጨቀየው? ታዲያ ሰላምታዋን ከማን ከየት ትጀምር? ግራና ቀኝ ሁለት ካሉ ገለታ የት ጋ ነው? ደንቡ አጠገቧ ካለው መጀመር አለባት:: አካላዊ አጠገብነት እንዲህ የሚያናጋ ነገር ያለው አይመስልም:: ገለታ ለምን ከሁሉ ራቅ ብሎ ይቀመጣል? አራራቁ ውስጥ ለምን በስሜት ብቻ የሚለካ የመሰለ እርቀት አለ? ከሁለት ወይም ከሶስት አመታት በፊት ቀልቃላ የነበረው ይሄ ልጅ ብርድ እንደተነፋበት ሁሉ ለምን ቀዘቀዘ? በዕድሜ ከምትበልጠው ሰላማዊት[10] ጋር ግንኙነት በመፍጠሩ እርጅና ተሰምቶት ነው? አብሮ

---

10 ሰናይት የእትዬ ውዴ ልጅ፣ እንደ ሺን ሰዎች ዘቅዘቅ ያሉ ዐይኖች ያላት ዐይናም፣ ቂጣም፣ ባታም፣ እና ታኮ ጫማ አድርጋ ስትራመድ እንደው ብትራገጥ ዝሆን የምታሳምም የመሰለች ልጅ ወይም ሴትዮ ናት:: ዕድሜዋ ለሰላሳ አንድ ፈሪ ነው:: በትምህርቷ መዝለቅ ስላቃታት ከትምህርት ቤት ደጃፍ ከራቀች ከርማለች:: እናቷ ውዴ 'አባቷ ከሞተ በሁዋላ የትምህርቷን ተውኝ፣ ሁሉ ነገር ልክ አይደለም የእሷ ነገር......ያው እሱ ሲፈጥራት......' ሲሉ 'አእምሮዋ ለትምህርት አልተደራጀም' ማለታቸውም ነው:: 'የሁለቱ እህቶቿ ታላቅ ስለነበረች ታናናሾቿን ስታሳድግ የቤት ሙያተኛ ሆና ቀረች' አይሉም:: ውዴ ብልጥ ስለሆኑ እግዜርን በማማት፣ ራሳቸውን ከሃላፊነት በማሸሽ ሁለት ፎቅ ያለው ክህደት ይሰራሉ:: ወሩ በገባ በ19ኛው ቀን መላኩ ገብሬልን ብሥራተ ገብሬል ሄደው እየተለማመጡት ሰው ፊት ግን እንደ አብሮ አደጋቸው ያሙታል:: እሱ ሲፈጥራት ማለት እኔ የለሁበትም ብሎ

---

ፈጣሪንና አሽከሩን መወንጀል አይደለም? ፃፍረተቢስነት አይሆንም? የሰናይት የማድቤት ሙያ ትምህርት ቤቷ ደጃፍ ደርሶ ገና የዘበኛውን ግንባር ሲያይ ወደ ታቦት ማደሪያ ተመለሰ::

በሁሉ ነገር ተግራ ስትነጫነጭባቸው እናትዋ ውዴ ከሦስቱ ገገድ ቤታቸው አነስተኛ ጣጣ ያለበትን እዛው ስፈራቸው፣ ከቤታቸው ምናልባት አምስት ደቂቃ በእግር ጉዞ የሚያስኬድ እርቀት ላይ ያለው ላውንደሪያቸው ከተቷት:: እንዳታከስሪኝ ብለው አስጠንቀቋት:: ሁልጊዜ ብልህ ሁሉን ነገር የሚችሉበት እሳቸው ናቸው:: ሰናይት ላውንድሪ ቤቱ ሲሰጣት በስራዋ ደንበኛ ያስደሰተች እንፀባራቂ ሆነች:: ሰናይት ለሰፈረተኛው ያቺ ጥሩ ልጅ ናት:: እንዳንዴ ግን ያደገችበትና እህቶቿ ን ያሳደገችበት፣ እናቷን የጦረችበት የማድቤት ጠረን ይናፍቃታል:: ማማሰያ ይዞ ተፍተፍ ማለት ያምራታል:: እንዲህ ሲሆን እምሮቷን ለመቁረጥ ትንሽ እህቷን ፀዳልን ተለማምጣ ሱቁን ለእሷ ትታ ማድቤቷ ትገባለች::

አንድ ቀን ከምሽቱ ሶስት ሰአት ላይ ሱቋን ያው እንደ ደንቡ ከጀርባ ዘግታ ልትወጣ ስትል የሚጢጢ ፏፏቴ ድምፅ ሰማች:: የምን እየደረበች ከግቢ ብቅ ስትል ረዥም ልጅ ፊቱን እሷ ወደ ምትመጣበት አዙሮ ሰማይ ሰማይ እያየ ይሸናል:: ዐይኖቿን ወደ ታች ጣል እንዳረገች ተደናግጣ፣ አፍራና በከፊል በአግራሞት ደንዝዛ ከቆመችበት ቁጢጥ አለች:: ሽንቶ ጨርሶ መንገዱን ሲቀጥል ፊቷን ወደ ሁዋላ መለስ አድርጋ የውስጥ ሱሪዋን በቶሎ አውልቃ ሱቁ ግቢ ውስጥ አፈር ላይ ተራዋን መሽናት ጀመረች:: የላውንድሪው ቤት የውጭ መብራት አጉልቶ ያሳያትን ነገር ባለቤት ገለታን ከዛን ቀን ጀምሮ ፈለገችው:: እሷ ለእህቶቿ የተናገረችውን የሰማት ሰምቷትም ያመናት፣ ገለታን የወደደችው በጉንጩ ትምክ አይደለም:: ከዛ ምሽት በኋላ እነዘሪሁን ሱቋ አካባቢ የሚሰበሰቡበትን ጊዜ ባንኮኒዋ ላይ ተለጥፋ ጠበቀች:: በአራተኛው ቀን ገለታን ስታገኘው፣ ከዛ ቀደም ፊቷን አኮሳትራ ሰላምታ ብቻ የምትለውን ልጅ ምሳ አብሮአት እንዲበላ ጠየቀችው:: ሁልጊዜ ደህና የማይበላ ልጅ ነውና እሺ አላት:: ቀስ በቀስ ከመንገድ ዳር የሚቆመውን ልጅ ከእሷ ጋር ላውንድሪ ቤት ውስጥ ማስቀመጥ ጀመረች:: ይሄን ግኑኝነታቸውን ባካፋ ለወዳጁ ለሰናይት እህት ለፀዳል በጨዋታ መሃል ነገራት:: ፀዳል ለእናቷ ነገረች:: ውዴ እንዳለ ሲያውቁ ቆሞ ቀር የሚሏትን ልጃቸውንና በእሳቸው አባባል ችጋራሙን ገለታን ሊያስደንግጡ እሳት ጎርሰው እሳት ተከናንበው ሄዱ:: ገለታና ሰናይት በፍቅረኛ ደንብ ጎን ለጎን ቆመው እጅ ለእጅ ተያይዘው

---

**አደግ ጓደኞቹን ለምን እንደ ባዕድ አርቆ ያያቸዋል? አጋጣሚ ነው? አጋጣሚነቱ ለገለታ ነው ወይስ ለተመልካች? ተወልዶ ላደገበት፣ ለቦረቀበት ዕድሜው እዚህ ለደረሰበት ታቦት ማደሪያ እንዲህ ከሆነ ለአዲስአባ እንግዳ አይሆንም? ለአዲስአባ እንግዳ ከሆነ ለአገሪቷ አይሆንም? ለአገሪቷ እንግዳ ከሆነ ለአፍሪካ አይሆንም? ለአፍሪካ እንግዳ ከሆነ ለአለም አይሆንም? ለአለም እንዲህ ከሆነ ለፍጥረታት እንግዳ**

---

ወሬ ሲቀዱ ብቻ ሳይሆን እየተሻሹ ሲሳሳሙ አገኙአቸው:: ማንም ሕሊና ያለውን ሰው የሚያስከፋ ብዙ ብዙ መጥፎ ነገር ከውዴ አፍ ወጣ: *ስራ ፈተሽ እዚህ ከማንም ችጋራም ጋር......የታደሉት ቤተክርስቲያን ይሳለማሉ፣ የተረገሙት ደግሞ ከችጋራም......የሆነላቸው አሜሪካ ምንም ብለው ቀን ያልፍላቸዋል ነፈዞች ደም፣ ሽሮአቸውን እየጠበሱ ከእኔ እንቶኔ ጋር በየስርቻው እንደ ውሻ......ገለታ የተናገሩትን ስምቶ* እንዳልሰማ ከላውንደሪው ቤት ወጥቶ አንድ ቦታ ለስላሳ ሲጠጣ ቆየ:: እናቷ ሲሄዱ ወደ ሰናይት ተመለሰ:: ሰናይት በእናቷ አፍ እላፊ አፍራ ገለታን እንዳይከፋው ፊቱን እየዳበሰች፣ አንገቱን እያቀፈች፣ የጉንጩን ስርጓዶት እየሳመች የእናቷ ባለጌነት ሁሉን ሰው እንዳስመረረና በአሮጊቷ አፍ ሰበብ እሷን እንዳይቀየማት በሚያምር አንደበት ለመነችው:: ምንም ቃል አልወጣውም:: የወደደችው በጉንጩ ስርጓዶት እንዳልሆነ ይገባዋል:: በሰፈር መንገድ ላይ አንገቷን ሰብራ አፏን በዝምታ መርፌ ጠቅማ የምትጓዘው ሰናይት እዛች ሱቅ ጀርባ ያለች መደብ ላይ ሲያቅፋት ልዩ ልዩ ነገር እንደምትለፈልፍ የሚያውቀው እሱ ነው:: (ለአለም አዲስ ነገር ባይሆንም) ገብቶት የታዘበው ነገር ሰዎች የሚያደርጉት ነገር፣ ከሚመስሉትና ከሚያወሩት አለመጣጣሙ ነው:: ብዙ ጊዜ ይሄ ዝም ያሰኘዋል:: ደሞም ሰዎች በትንሽ ጉዳይ ሌላውን ሰው ይገምታሉ:: ገምተው ትክክል እንደሆኑ ሁሉ ከልባቸው ይረካሉ:: ማወቂያ መንገድ ባይኖራቸው አይጠረጥሩም? እትዬ ውዴ ልጃቸው ሰናይት ገለታ ስር በጀርባዋ ስትሆን ጎንትደርሳ የተመለሰች እንደሚመስላት ቢጠረጥሩም አያምኑም:: ይሄን አይነት ትራንስፖርት እግዜር ከፈጠረው የገለታ ገላ ሌላ ማን ሊሰጣት ይችላል? ማን በመሳሳት በሽታ እለቁ ተብለው ተረግመዋልና አይተዋቸውም:: ለውዴም ይሁን ለሰናይት ወይም ለአሕዛብ ወይም አብሮአቸው ለሚያቻፈችፍ ሞላጫ እውነታን በግምት አሳንሰው እየስፈሩ አእምሮን በሽራፊ ሞልቶ መኮፈስ ብልጠት ይባላል::

---

አይሆንም? ለአምላክስ? በትክክል ግን ገሊታ እዚህ ቦታ[11] የለም። ስፍራ በገላ ብቻ ሳይሆን የሚሞላው በድምፅ ነው ይላሉ ሳይንቲስቶች፣ ጨዋታ ዘፋኞችና የለቅሶ መርዶ ነጋሪ ጥሩምበኞች። ማለት ዝምታ ቦታ እንደማይዝ ሁሉ። ከቀጭኔ የበለጠ ዝምተኛ አለ? በገላዋ የምትሸፍነው ቦታ ግን ከአራት ጅብ ይበልጣል።

ይሄ የወጣቶቹ የስብሰባ ቅርፅ ብዙ ጊዜ አይለወጥም። አቅደውት ነው? አንዳንድ ጊዜም ለመሮጥና ወዲያና ወዲህ ለመበታተን ያቀዱ ይመስላል። ምናልባት ወዳጅነታቸው ውስጥ የተገነባው ግን የተደበቀው ጊዜ የሚያወጣው የሕይወት ጉዞ በጨረፍታ እራሱን ሲያሳይ ይሆናል። ሁሉ ነገር ተለዋጭ ከሆነ፡ በረሃው ካበበ፣ የአበበው ከረገፈ፣ የረገፈው ከፀደቀ እንዲህ የተሰበሰቡት ወጣቶች የማይበታተኑበት ምክንያት ይኖራል? ማንንም ማስገረም የሚገባው ጉዳይ ባይሆንም በዚያች አፍታ ግን ከዛ አቋቋማቸው ይሄ የተፈጥሮ ሕግ እንዳለ መጠርጠርን ይገፋፋል። ይሄንንም በቃል የሚገልፅ የቡከን አረፍተነገር አይጠፋም፡ *እንዲህ የሚያምሩ ወጣቶች እንዲህ እየተጫወቱ ይዘልቁ ይሆን?*

---

11 'ገሊታ ሲወለድ በዝምታ ነበር። እንደማንም ጩቅላ ከማሕፀኔ ሲወጣ የደንቡን አሳለቀሰም። አዋላጁ ሐኪም እንግዳ ቢሆንበት ምናልባት የማሕፀንሽ ሙቀትና የውጭው ሙቀት እኩል ስለሆነ የተወለደ አልመሰሰለው ይሆናል አለ። ግራ ገብቶኝ ፈርቼ አለቀስኩ። ሁለተኛዋን ልጄን ስወልዳትም እንደፈራሁት ትንሽ የደበታት ሆነች። ገሊታ ጤና አይደለም እል ነበር። ግን እሱ ይመስገን በደህና አደገ። ቁመቱም ተመዘዘ። ሞላ እያለ እንደእሱ ተጫዋች ማንም አልነበረም እኮ። የፈራሁት ግን ደረሰ መሰለኝ አድብቶ አድብቶ ከፍ ሲል ጋግርታም ሆነብኝ። 'ያው የሞላነቱ ጊዜ ተመልሶ ይምጣበት?'......'እንደዬን ማን-ይታገለዋል?' ብዬ ዝም ብዬአለሁ። ሁልጊዜ ግን እፀልይለታለሁ። ድሮ ከወዳጆቹ ጋር ሲንቀለቀል የማየው ልጅ አሁን አሁን እጆቹን ኪሱ ከቶ ሲያስብ አየዋለሁ፣ ወይም ሲያንጎራጉር እሰማዋለሁ። ከመሃል ተማ አለለት እንጂ፣ ዝምታው ሲወለድ የጀመረው ነው' *(ሚስጢሯን መጠበቅ የምትወድ የገሊታ እናት ፎርቱና፣ የማንቦት ልደታ አድባር ላይ ጠላ ሞቅ አድርጓት፣ የበግ አጥንት መቅኒ እየመጠጠች ለዘሪሁን እናት ያወራቻት።)*

— — —

ሌላም ነገር ታያለች፡ እጥፍ ዘርጋ የሚለውን የአካላቸውን ንቅናቄ፣ ቡጉር የተሸከሙ የደነገጡ ፊቶቻቸውን፣ እሷን በጎሪጥ እያዩ ያላዩ መምሰላቸውን፣ እሷ ስታያቸው ተቻኩለው ያልተቻኮሉ ለመምሰል የሚያደርጉት የረቀቀ የመረጋጋት ቲያትራቸውን:: ለምሳሌ ጌርሳሞት ሁልጊዜ በዚህ ሰአት እንደምታጋጥማቸው በልባቸው ታዝበዋል:: ግን እንዳልተነጋገሩበት ያስታውቃሉ::

አጠገባቸው ስትደርስ ከባካፋ ጀምራ ከዛ ራሚሱን ቀጥላ ዘሪሁንን እየተሽኮረመመች ጨበጠች:: *ታዲያስ ጌርሳ! ታዲያስ! ምነው ኮራሽ?*

እና የጎረምሳ ድርና ማግ መሃል ቆም ብላ፣ አንዳንዶቹን በምላስ ጎነታትላ፣ በእነሱም ተጎነታትላ፣ በሰዩ ትኩስ ዓይኖቻቸው ተልሳ፣ እስዋም በትንሽ መንተክተክ ቁመናቸውን ማማራቸውን ምናምናቸውን ቀለዋውጣ (ደስ እንዳላት ያስታውቃል) ገና መፍላት ስትጀምር ከሦስቱ ፈቀቅ ብሎ ሳቅ የመሰለ ነገር በከንፈሮቹ ነክሶ---ገለታ---ነክሶ ይመስላታል---የሆነች ጠፍጣፋ እንደ ወረቀት የቀጠነች ሳቅ---ሳቁ አምልጣው እንደምትሄድ ዓይነት ከንፈሮቹንና አገጩን በክንፏ እየመታች (የእድለኛ ሰው ሳቅ ክንፍ አለው)---ጌርሳሞትን ከሌሎች ልጆች ጋር ስታወራ በጥሞና ያያታል:: ኩርደዳ አሳብጦ የሸሚዟን የደረት ቁልፍ ያስከፈታትን ደረቷን እየነካካች (ረስታ ነው ታዲያ?) በዓይንዋ ቂጥ ታጤነዋለች:: ወደ እሱ እንዳትሄድ አለ አይደለ 'ፈለገችው' ተብላ 'መጠጣትዋ' ነው::

እሱስ የፈለጋት እየመሰለ ለምን ይርቃታል? ለምን እንደዚያ እያያት ይሸሻታል? *ምናባቱ*::

ደሞ ሰላምታ ብቻ ሰጥቶ ማለፍ ክልክል ነው:: አንደኛ ጨዋነት አይደለም:: ደሞ አባቷ እንደነገራት ስታድዮም ከሚያሳየው ብልግናው በስተቀር ሁለመናው ጨዋ ነው:: እናም የጨዋ ልጅ ናት:: ዘረ ጨዋ:: ዘሪሁን እያወራ ግራ እጇን ይዞ አልለቅ አላት:: እሱን በልምምጥ ነጥቃ ገለታን ተሽኮርምማ በሚያስገምት መንገድ ሰላም አለችው:: የሆነ ነገር እያወራች ከጓደኞቹ ጋር ከቆየችው ጊዜ ከገለታ ጋር ትንሽ ሰከንዶች ጨምራ ቆየች:: የቀሩት ጎረምሶች አፍጠው

---

ያዩሉ:: አስተያየታቸው የቅናትም ይመስላል:: ከሁሉም በፈረቃ የሚወረወርባትን አንዳንድ የወዳጅነት ተረባቸውን እየሳቀችና እየተቅለሰለሰች ቀልባ መንገዷን ቀጠለች::

ትታቸው ስትሄድ መደነጋገሯ ባሰባት:: ግን ሁልጊዜም ይደነጋገራታል:: ስታገኛቸው አንዱ የምትፈራው ነገር ሰላምታ ካለቻቸው በኋላ መደነጋገሯን ማሰብ ነው:: ገና ሳትደርስ የምትሄደው ወደ መደነጋገር ይመስላታል:: አራት ሰዎች ወዶ መውደድን ለመሸፈን ያዳግታል:: እግር እንዳላት ትዝ ይላታል:: እግሩ ትናንት አልነበረም? ዛሬ ዳሌ እንዳላት ትዝ ይላታል፣ ከቤቷ ይዛው አይደለም የወጣችው? ደረቷ የተጋለጠች እስከዛሬ ያልነበረ ነፋስ የሚነፍስባት ይመስላታል: ከዛሬ በፊት ያቺ ደረት የት ነበረች? ሁሉም የሚያዩአት ይመስላታል:: ሁሉም ቢያዩአት ደስ ይላታል:: ታዲያ አብረው ከበሰሉ፣ አብረው ከጠጡ፣ ከሰማይ ስር በወረደ አንድ አይነት ዝናብ ከተመቱ፣ ፀሐይዋንም ከሞቁ፣ በኮረኮንቿ ከተናቀፉ፣ በጭቃው ከተዳለጡ፣ በአቧራው ከታፈኑ፣ በአንድ ምላስ አምተው በመንታ ጆሮ ከሰሙ፣ በአስቴር አወቀ እንጉርጉሮ ከተተማመሱ፣ በአንድ አይነት ቀልድ በሳቅ ከተንፈቀፈቁ ለምን ልቧ ይከፋፈል? መምረጥ አለመቻል የእግዜርን ሕግ መቀናቀን ነው? የፈጠራቸውን የሚያምሩ ነገሮች ጎረምሳም ይሁኑ የማር ጠጅ፣ እንጀራም ይሁን ቂጣ፣ በድቡል አለመውደድ ሐጢያት አይሆንም? ፈጣሪን እንደመናቅ አይቆጠርም? ገለታ እንዲቀጥራት ትመኛለች:: እርዝመቱ እንደ መከላከያ ሚኒስቴር ሰንደቅ መስቀያ ከሩቅ ይታያል:: የገለታን ለግላጋነት ለሰላማዊት ብቻ ማን መደበላት? ፀጉሩን አሳጥሮ በቅርፅ የሚስተካከል:: ከንፈረ ከባድ:: አፈ ሰፊ:: ለወሬ ሌሎች መሃል ሲገባ እንኩዋን በድምፁ ነው---ከተቀመጠበት ቦታ አይነሳም:: *ቅጠረኝ የእኔ ጌታ የእኔ ባለ ትምክ......ባለስርባዳ......*

---'ወሬ ይደርሰኛል፣ ከዚያ ከጠንቀዋይ ልጅ ጋር(ምን ማለት ነው?) ገለታ ምናምን ከሚባል ነው'ዝ ጋር አይሸና ነገርኩ' ይላታል

| ------------



አባትዋ:: ፀጉራም ቡጢ ጨብጦ:: የገለታ አባቱ ጠንቋይ አይደለም:: አባቱ ወዲያ ወዲህ የሚሯሯጥ ነገ ምን እንደሚደርስበት የማያውቅ የትናንሽ ጉዳይ ደላላ ደሃ ነው:: ኮላሴ ፊቱ ላይ ቅሬታ ሳያሳይ እንደዛ ይላታል:: ገለታን ለምን እንደጠላው በትክክል አይገባትም:: አባቱን ስለምጠላው ልጁንም ጥዬልኝ ነው? አባቱንስ ምን አስጠላው? እንዲህ ሲላት ጌርሳሞት ጌርሳ እየተቁለጨለጨች ታየዋለች:: ጥንድ ፍርሃቶች: ገለታንም አባትዋንም:: አባትዋን በጭቅጭቁና በማስፈራራቱ:: ገለታ ደሞ ባልተወሰነው በአለሁ የለሁም ሁኔታው:: መከራን ማየት ነው:: የስሜት መተላለቅ:: ደሞስ ሰላማዊት የምትባል ወዳጁ የሆነች አሮጊት በምኑዋ ትበልጣታለች?

ሙሽራዬ ሆይ ከከንፈርሽ ማር ይንጠባጠባል፡ መሃልየ መሃልይ (4:11) ፨ ገለታ ጠዋት ቁርሱን ሳይበላና ፊቱን የታጠበበትን ውሃ እንኳዋን በትክክል ሳያደርቅ አውቶቡስ ለመሳፈር አምስት ደቂቃ የሚወስደውን የእግር ጉዞ ጀምሮአል:: በጠዋት ተነስቶ እግሩ እንደጣለው የሚሄድበት ምክንያት የሆነ የማይመቸውን ሕልም ሲያልም ነው[12]:: ሕልሙን ማየት ከጀመረ አምስት አመታት

---

[12] 'ስሜ አበበ ይርጉ ይባላል:: እዚህ ቀራንዮ መድሃኒያለም ዲያቆን ነኝ:: ሃይማኖት ብዙ ባይመስጠኝም ለእንጀራዬ ስል ቲኦሎጂ ኮሌጅ ገብቼ ኑሮ ላቃረው ክርስቲያን ነኝ ባይ ጠበል የተባለ የዝናብ ውሃ፣ ጸሎት የተባለ ወሬ አጠጣለሁ:: ከኃጢያቱም ይሁን ከበሽታው ቢድንም ባይድንም ግድ የለኝም:: አንድ ያጋጠመኝን ጉዳይ ልንገርሽ:: የሆነ ጊዜ ከስአት በሁዋላ ቤተክርስቲያኑ ግቢ ገለታን ምን ማድረግ እንደጠፋው ሰው ወዲያ ወዲህ ሲል አየሁትና ምን ፈልጎ እንደሆነ ጠየቅሁት:: ገለታን አውቀዋለሁ:: እሱ ግን አያውቀኝም:: *ገርል ፍሬንዱ* ሰናይትን አየር ጤና አስራ አንደኛ እያለች አወጣት ነበር:: አንድ ሁለቴ ከታቦት ማደሪያ ወደ ቤቴል በሚወስደው መንገድ ላይ ከገለታ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ለሽርሽር (መሆን አለበት) ሲጓዙ በመኪና ሳልፍ አይቼአቸዋለሁ:: ከእሷ የተለያየነው በሁለት ተደጋጋፊ ምክንያቶች ነው:: አንደኛውን እኔ ብቻ የማውቀው ሲሆን ሁለተኛው ግን ለሌሎች የምንግረው ነው:: ሁለት ባይባልም ሁለት እለዋለሁ:: ዋናውና እኔ የማውቀው ምክንያት ይሄ ነው፡ ሰናይት እራሷም ልብ ሳትለው የሌሎችን ሰዎች የበላይነት በቀስታ ገፋ የራሷ የምታደርግ ናት:: ብዙ አታወራም ግን አፏን ዘግታ ቆይታ የልቧን ስትናገር *ይሄ ሁሉ ይገባታል?* ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ:: እንደዛ ስታደርግ ብልጥነቴ ገና ከድሮ ራቁቱን እንደቀረ እረዳለሁ:: ያታለላችሁት የመሰላችሁ ሰው ከረዥም ጊዜ በኋላ እንዳላታለላችሁት ስትረዱ፣ እስከአሁን የሰራችሁበትን ነገር ሁሉ እንደሚያውቅ ቢገባሽ ደምሽ አይፈላም? ነገርግን ሰናይት ቀልጣፋ መሆኗ የሚከሰተው የምትወደውን ነገር ስታደርግ ብቻ ነው:: ከሁሉ ከሁሉ ነገር ምግብ መስራት ትወዳለች:: እንደ መስራቷ ግን አትበላም:: ለበአል እቤታችን ከመጣች ተሰርቶ ያለቀውን ምግብ እራሷ በመስላት መልክ በታትናና ገጣጥማ ስታቀርብ የእማማ የበላይነት ይጠፋል:: እንዴት ነው ያለቀው ቀይ ወጥ የበለጠ ቀይ ወጥ የሚሆነው? ተቆርጦ ያለቀውስ ዳቦ የእሷ ቢላ ሲያልፍበት የተለየ ያማረ ዳቦ የሚሆነው ለምንድነው? የወለዷትና ያሳደጓት እናቷ

እንኳን የማያውቁት የተለየ ሥልጣን አላት:: የምትሸኮረመም አሜሪካ ማለት ነው:: ለትዳር ያልፈለኳት ለዚህ ነው:: ስርቃት እንኩዋን በሐሰት ነው: ለዘመናዮቹ ቀርፋፋነቷ አማሮኝ የሸሸሁዋት አድርጌ አስወራለሁ:: ለድሮ ሰዎች ደሞ 'ልባ አይታወቅም' ብዬ አስወራለሁ (እኛ ከተማ ይሄ ይሰራል:: ምንም ትርጉም የለውም ግን:: *የልባ ካልታወቀህ እንዴት አወቅሃት?* ብሎ የሚጠይቀኝ አይኖርም መቼም:: ለምን? ወይ ደደቦች ወይ ከርፋፋ ይሉኝተኞች ነን):: ከእሷ ከተለያየሁ በኋላ ሚስቴ የሆነችውን ልጅ በግል ስለምታውቃት መበለጧና ሃፍረቱ አንገቷን ሰበራት:: የሰናይት በዚህ መልክ መዋረድና እኔ ደሞ እንደነገርኩሽ እሷን በሚስጢር መፍራት ጥሩ አድርጎ ለያይቶናል:: ይግረምሽና ከእሷ በመለየቴ ግን እቆጫለሁ:: ለምን ይቆጨኛል? እየተስለመለመችና እየተለኮለታተፈች ስትስመኝ ትንሽ ፊቴ (ዛሬ ሙስና ያስፋት) በደስታ ትንቦገቦጋለች:: ዐይኖቼ ስፍራቸውን ይለዋወጣሉ:: ሰናይት ሁለመናዋ የሚሞቅ ረግረግ ነው:: ወፍራም ሴት ስለምወድ ይሆናል:: ሰናይት ልብሷን ስታወልቅ ያላትን መለኮታዊ ውበት ሌላ ሰው ማለት የሆነ ገለታን አይነት ድራሽ ቢስ ሲያይብኝና ሲነካብኝ ቀናሁ::

እና ገለታን ቀራንዮ ያገኘሁት ቀን ሁኔታው ያሳዝን ነበር:: እሱን የመሰለ ወጣት ቤተክርስቲያን መምጣቱ የአዲስአበባ የመንፈስ ንቃት እንደተሻሻለ ጥሩ ምልክት እንደሆነና እሱን የምረዳው ነገር ካለ ዝግጁ እንደሆንኩ በጨዋ ስልት ጠየቅሁት:: እየነቃ ይሁን እየተንቃቃ ግድ አልነበረኝም:: ትንሽ አንገራግሮ በቅዥት እንደሚሰቃይ፣ ፀሎት ሞክሮ እንዳልተሻለው፣ በአጠቃላይ መፍትሄ እንዳጣ ነገረኝ:: አፌ እንዳመጣልኝ ሶስት ቀን እንዲጠመቅና ቢችል እሁድ እሁድ እንዲያስቀድስ ነገርኩት:: ይሄንን ሃሳቤን ይቀበለኛል? እምነት የጠፋበት ዘመን እንደሆነ ስለማውቅ ግር አይለኝም:: ደሞስ ባያዳምጠኝና ባያምነኝ ግድ አለኝ?

የገለታን ሚስጢር ማወቅ ስለፈለኩ ችግርን ለሰው መናገር ሸክም እንደሚያቀል ለእኔም ብትነግረኝ መፍትሄ ሊገኝ እንደሚችል በማባበል ጠየቅሁትና እያንገራገረም ቢሆን በአጭሩ እንዲህ አለኝ: *በሕልሜ የሆነ ነገር ያሳድደኛል:: ዛሬ ከማየት ይልቅ መሮጥ እጀምራለሁ:: በሕልምህ ደንግጠህ ታውቃለህ? በድንጋጤ መሮጥ እጀምራለሁ:: ከሁዋላዬ ድው ደው ድው የሚል ኮቴ እሰማለሁ:: ምን እንደሆነ ሳላረጋግጥ ብቻ እሮጣለሁ:: ይከተለኛል አይለቀኝም:: ትንፋሹ ማጅራቴ ጋ ይሰማኛል:: ዞሬ ማየት እፈራለሁ:: ደሞ ዞር ብል ከሚያባርረኝ ጋር የምላተም እየመሰለኝ እፈራለሁ:: በመጨረሻ ደፍሬ በፍጥነት ዞር እላለሁ:: አንገቴን ያመኛል:: የሚከተለኝ ይገርምሃል ድምፅ ነው:: ፍጡር*

አልፈውታል:: ሕልሙን አይቶ የሚጨርሰው ሁልጊዜ ከጠዋቱ አንድ ሰአት ተኩል ላይ ነው:: አልሞ እንደጨረሰ ቁርሱን ሳይበላ ውሃ ብቻ ጠጥቶ ከቤቱ ይወጣል:: በውሃ የታጠበው ሆዱ ቢሞረሙረውም እስኪደክመው በቤቴል አቅጣጫ ይጓዛል:: አንዳንዴ ከቀራንዮ መድሃኒያለም፣ አንዳንዴ ከጦር ሃይሎች፣ አንዳንዴ ከቤቴል ድልድይ ወደ ቤቱ ይመለሳል:: እንዲህ ለአጭር ጊዜ ስለሚያሰድደው ሕልም ለማንም አልተናገረም:: ለምን ይናገራል? ስለሕልሙ ከተናገረ ስለተፅዕኖው መናገር አለበት:: ተፅዕኖውን ከተናገረ እንደ ዕብድ

---

*የለም:: ድምፁ እንግሊዘኛ ነው:: ድምፁ አንደ አግር ዳና አለው:: ዲድ ሔኒ በዲ ተች ዚስ ጋይ?* (ይሄን ሰው የነካው አለ?) *ይላል:: ደምስ በእንግሊዘኛ የማልመው ለምንድነው?*

ሕልሙ የልጅ የሚመስል፣ ምሳሌ የሌለው ትርጉም የማይወጣው ቅዠት ነበር:: ከእኔ መልስ እየጠበቀ ሲቁለጨለጭ ስለሚስቴ አሰብኩ፣ ስለ ጓደኛዋ አሰብኩ፣ ስለ እሷ የጓደኛ ጓደኛ አሰብኩ:: ይህቺ የመጨረሻዋ ልጅ ሰናይትን ታውቃታለች፤ እስከ አሁንም አንዳንዴ ይገናኛሉ:: ቅዥታም በሽተኛ ቦይ ፍሬንድ እንዳላት እንድታውቀው ወሬውን እንዴት በጎን ለሰናይት እንደማደርስ አሰብኩ:: መፍትሄ እንዳገኘሁ ሁሉ አይኖቼን ጨፍኜ በማይገባው ግዕዝ፣ በተሰባበረ ሰዋሰው ገሊታን ደደብ ነገር መከርኩት:: *ሰማህ አንተ ልጅ ቅዥት ነው:: ከመተኛትህ በፊት ውሃ ጠጥተህ ተኛ:: ካልተወህ ያው እየመጣህ ጠበል ተጠመቅ፣ ቤትህም ወስደህ ጠጣ* አልኩት:: በቸልታና በጥርጣሬ አይቶኝ ከቤተክርስቲያኑ ግቢ ወጣ:: ከአረመኔ ምን ይጠበቃል? ገሊታ ሕይወቱ ውስጥ በማይጠብቀው መንገድ እኔ እንደምኖር፣ እንደምቀናበትና ወሬ እንደምነዛበት አያውቅም (ያወራው ስለሕልሙ እንጂ ስለሰናይት አይደለ፣ እኔ የማወራው ስለሰናይትና ስለእሱ እንጂ ስለሕልሙ አይደለ):: ፍቅራቸውን ከገፉበት (የትም አይደርስም እንጂ፡ እንደ እሷ አይነት የሃብታም ልጅ ለምን ብላ የተግባረዕድ አናጢ ታገባለች?) ገሊታ ምን አይነት ልጅ ሚስቱ እንደሆነች የሚያውቀው ትዳር ይዘው (እዛ ከደረሱ) ምድጃ ዳር ቁጭ ብሎ በቀይ ወጥ ጢስ ሲታጠን ነው:: ማንስ ቢሆን እንዴት ነው የከበበውን እውነት በፍጥነትና በግልፅ የሚያውቅ? ሁላችንም በየራሳችን ሕይወት የተሰተርን የጋሪ በቅሎዎች አይደለንምን? (እኔ ለምሳሌ የሁለትና የሶስት አይነት ቤተክርስቲያኖች ተወካይ እንደሆንኩ የሚያምኑ ስንት ምእመናን ናቸው?) ማለት ለራሳችንም እንግዶች ነን:: ይሄ ስራዬ ክፉ ሊባል ይችላል፤ እና ምን ይጠበስ?'

---

መቆጠሩ አይቀርም:: ብዙ ሰዎች ነፈዝነት ዙሪያ ተያይዘው ማደም ስለሚመቻቸው በቀላሉ ተቀባይነት ባገኝ ስያሜ እግራቸው ስር እንደሚጥሉት ይጠረጥራል:: ስድቡ ባያሳብደውም ሁልጊዜ ከጀርባው ተከትሎት የሚተም በየቦታው አብሮት የሚቀመጥ አውድ ይሆናል:: ገለታን የሆነ ነገር እንደሚያሳስበው ከዐይኖቹ ዋህይ መጠርጠር ይቻላል: ትምህርት ቤት? ቤተሰብ? ሰላማዊት? ጌርሳሞት? ጓደኞቹ? አገር? ሕልሙን እያወጣና እያወረደ? ወዘተ

በዚህ አይነቱ አንድ ጠዋት ዋናውን መንገድ በመሻገር ላይ እያለ ሊታከከው ደርሶ ካለፈ ትንሽ ከእሱ ፈቀቅ ብሎ ከቆመ ውይይት ታክሲ ውስጥ ስሙ ሲጠራ ሰማ:: በጠባቧ የታክሲዋ መስኮት የጌርሳን ፊት ሳቅ ለብሳ አያት:: ፈገግ አለ፣ እና የጉንጩ ሰርባዳ ቦግ አለች:: ጌርሳ የሆነ ቦታ በአካል እንደተነካች ሁሉ ተሽኮረመመች:: መንገዱን እንደተሻገረ እስዋ ከታክሲ ወረደች:: ሲገናኙ ተጨባበጡ:: የጌርሳሞትን የዋህ ወሬ ይወደዋል:: የምትናገረው ተራ አረፍተነገር በጥላው የሚጫወት ሞሳ ይመስላል:: እሷ የምትተነፍሰው ቀላሉ መረጃ ('ዛሬ ፀሐይዋ ደስ አትልም?') ወረቀት ላይ ቢፃፍ ደብተራችንን ወለላ ሆኖ ያበላሻል:: 'ያ ቤቢ[8] ደስ ሲል' ስትል *አሁን እዚሁ ቆጢጥ ብዬ እሱን የመሰለ ደስ የሚል ሞሳ ብወልድልህ* ለማለት የሚቀሯት አስር ቃላት ናቸው::

---ገለታ ደህና አደርክ? ወደየት ነህ? አለችው:: ብቻውን ሲሆን ትደፍረዋለች:: (*ከታክሲዋ የወረደችው ይሄ እንዳያመልጣት ነው:: እንደ እናቷ እንደዛች እንደ መግደላዊት የነፃነት ምኞት ልክፍት እንደሆነባት አታውቅም::*) ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ:: በልታ እንደወጣችው እንቁላል በፉርኖ ትሸታለች::

---ሰው *ጋ*

---*የታጠብከው ፀጉር ሳይደርቅ ነው የምትወጣው? ሂሂሂ* ከሳቋ ተግ ብላ ግንባሩ ላይ ከተጣበቀው አጭር ፀጉር ላይ አንድ ሁለት የለገዳዲ ጤዛዎች በጣቶቿ አራገፈች

---የረፈደብኝ መሰለኝ:: ምን አንቀለቀለኝ:: ፊቱን በእጁ አሻሸ::

---ቁርስ አልበላሁም እንብላ አለች

---

አፉ እንዳመጣ እሺ አላት:: እሱ እስዋን የት እንደምትሄድ እንኳዋን አልጠየቃትም:: ብትጠብቅም አልጠየቃትም::

የሚያምር ሃብል አድርጋለች:: የሃብሉ ሰቅል ሳንቃ ድሪ ነው:: ሳንቃ ድሪዋ እንደ ጎጆ የተሰራች ናት:: ጎጆዋ በሶስት የተዛነቡ መስመሮች የተሰራች ትንሽ በር አለቻት:: ክፍክፋቷን ለማሳየት አስራ ሁለት የአግድም መስመሮችና አራት የቁም መስመሮች ተሰርተውላታል:: ለዐይን የሚታዩት በግድና በግምት ነው:: በመስመሮቹ ቦይ ውስጥ አልፎ አልፎ ጉድፍ ያጠቆራቸው ብርማ ሸንተረሮች አሉ:: የሰቅሉ የታቹ መሰረት ሁለቱ ሚዛኖች እንደተቦረሹ ወይም እንደታጠቡ ሁሉ ያንፀባርቃሉ:: ገለታ እዚህ የሚያምር ነገር ላይ ለአፍታ አፈጠጠና በጣቶቹ አገላብጦ አየው:: ቃል ሳይወጣው ያደረገው ይሄንን ብቻ ነው:: አንገቷ ጋ ቢይዛትስ? አገጭዋን ይዞ ቢስማትስ? የትኛው ተንኮለኛ አምላክ ነው የምንፈልገውን እንድናፍርበት አድርጎ የፈጠረን? በዛም አልበዛም ተምረን ተምረን ተሳስተን ተሳስተን መልሰን መላልሰን ለተመሳሳዩ ነገር የምናፍረው ለምን ይሆን? በራሳችን ልቦና ላይ ስለምን ይሉኝታ እንይዛለን? በይሉኝተነታችንም እንኮራለን? ግን ሳንቃ ድሪው ምን ማለት ነው? ጠርጣራነት ሁሉ ነገር ውስጥ ምሳሌ ይከታልና እንጠይቅ::

ውይይት ታክሲ ውስጥ ገቡ:: ታክሲዋ ያረጀች ናት:: (ያላረጀ ውይይት ታክሲ እስኪ እንፈልግ) በተሳፋሪ ሙሉ ናት:: ታክሲዋ ጌርሳሞትን ብታንገጫግጫትም ገለታ ጎኗ ስላለ ብቻ ተመችቷታል:: አንድ ወንበር ላይ ለሶስት በሰልፍ ተቀምጠዋል: ከቀኝ ዳር የሆነች ጡታም ጥርሳም ልጅ፣ ከዛ እሷ እና ከዛ ገለታ:: ስስ ቀሚሷን አልፎ ስፖንጁ የተቦዳደሰው መቀመጫ ቂጥዋን ይጎረብጣታል:: ቢሆንም የተቦተረፈ ስፖንጅ መሃል በሚዛን ተቀምጣለች:: ከጉልበቷ ጀርባ ጠርዙ ይፍቃታል:: በዛ ሁሉ ግፊያና ላቦት መሃል ይሄ ምቾት ወደ ነፍሷ የተጋባ አይነት ተረጋጋች:: ይህቺ ግራ ምቾት ሌላ መልካም ምቾት እንደምትቀሰቅስ ሁሉ ግራ እጅዋን ገለታ ትከሻ ላይ ጣል አደረገች (ቦታ የጠበባት መስላ--እሱስ ይጠባል) ደሞ ወደ አንገቱ ጠጋ ብላ በቀራፋ ጆሮው ለዚህ ገና ላላሬዘ፣ ገና እንደ ጠበል ለሚሰራው እርጥብ ልጅ የጉንጩ ትንቡክ እንደሚያምራት በቃል ያውም ከፍ አድርጋ ልትነግረው ዳዳት:: ገላዋን ብትታጠብበት በገለታ ብተለቃለቅ

ሁለመናዋን እሷ። ጭኖቿን ቢከፍት እሱ። በአፏ ቢገባ አፉ የእሱ። ስርባዳው ነክሮ ቢያወጣት እሱ......በሚቁለጨለጩ ዐይኖቹ በለሆሳስ ሲያያት ቁምነገር የማይወጣው የመብራት ሃይል ባለሥልጣን ፊዩዙን በሁለመናዋ እንደለኮሰ ሁሉ መንደድ እንደምትጀምር ልትነግረው ይዳዳታል። ተፋዘውና ለየብቻቸው በሃሳብ ተቀፍድደው እያሉ ታክሲያቸው ተሳፋሪ ልታወርድና ልትሰቅል ደጋግማ ቆመች።

በልባቸው ውስጥ መፈላለግ እንደሌለ፣ የሚያስቡትም ስለመፈለጋቸውና ስለመፈላለጋቸው ሳይሆን ከልቦናቸው ውጭ ስላለው አለም እንደሆነ ሁሉ ልሙጥ ቲያትረኛ ፊታቸውን ወደ ውጭ አዙረዋል። ካሉበት መንገድ በወዲያ በኩል አራት መኪናዎች ቂጥ ለቂጥ ተገጫጭተው ኋላና ፊት በሰልፍ ቆመዋል። ከተጋጩት መኪናዎች ከሁሉ ፊት ያለችው ብቻ በጎኗ ተገልብጣለች። የታክሲው ተሳፋሪዎች ግጭቱን እንዲያዩ ከመኪኖቹ ወይም መኪኖቹን ከሚነዷቸው ሰዎች ጋር ቀጠሮ የያዙ ይመስላል። የመጀመሪያው ገጪ አውቶቡስ ነው። እሱ ሶስተኛውን መኪና ሲገጭ ሶስተኛዋ ፊቷ ያለችውን ሁለተኛ መኪና ትገጫለች ሁለተኛዋ ደሞ ፊት ለፊቷ ያገኘችውን ትገጫለች። የጥፋቱን ቅልልቦሽ ማስተላለፍ ያልቀናት ከፊት ለፊት ያለችው ደሞ ገጭታ የሚያቆማት ስላልነበረ ተገልብጣለች። ታክሲ ውስጥ ያለው ተሳፋሪ ሁሉ አደጋውን በመገረም ያያል። ጌርሳሞት ልታሰግግ በማዘንበሏ ገለታን ሲተነፍስና ገላው ሲያብጥ ተሰማት። የሆነ የሚያስፈራ ደስ የሚል ስሜት በመላ ገላዋ እንደ እንሽላሊት ሽር አለ። እንዳያያት አድርጋ ዐይኖቿን በቀስታ ከድና ከፈተች። ጌርሳሞት ካዘመመችበት ቀና ብላ የገለታን ጉልበት ተደግፋ ልፍስፍስ ፀጉሯን በፊቱ ስር አሳለፈች። የገላው አጥንታምነትና ምቹነት። ግን ከራራ ይመቻል? የተለኮሰ ገላዋን ለማረጋጋት ለጋ ቂጥዋን ቀድሞ የነበረችበት የስፖንጅ ቆሬ በጭንቀት ያለሙሉ ልቧ መለሰች። ታክሲዋ ወሬ ካሳየቻቸው በኋላ ጉዞዋን ቀጠለች። የታክሲዋ ውዝዋዜ እሱ ላይ እየጫነ ይመልሳታል፡ ቢቻላት ከፍ አድርጋ መናገር ትፈልጋለች፡ *እባክህ አንተ ባለታክሲ ወዝውዝን*፡ እዛው እስከ ማታ መክረም ፈለገች፣ እስኪነጋም፣ ዘመኑ ማርቆሱ እስኪያልቅ......በልጉ እስኪጠናቀቅ። የምታስበው፡ *ያቺን ሰላማዊት ምን አየህባት? ያቺን ደንደሳም ምን ብለህ ወደድክ? ከአሮጊት ምን አለህ?......ታሰርክ ሲባል*

---

*ልቤ እንዴት እንደመታ ታውቃለህ? መአት ጊዜ በሕልሜ አየሁህ::* ጌርሳ ጌርሳሞት በሕልሟ ያየችውን፣ ነቅታም የተመኘችውን፣ ተመኝታ የወደደችውን፣ ወደ የሻተችውን፣ ውስጡ ብልግና አይጠፋምና አታወራውም:: ማን ራሱን ትዝብት ዐይን ስር ይጥላል? እግዜር የመውደድ ወጉን ለምን ከኃታችንትና ከስንፍና ጋር ሰፋው?

ጎኑ ተቀምጣ ግን በሁኔታው የዘነጋት እየመሰለ:: ቸል ያላት እየመሰለ:: ግን በሁለመናው ንቅናቄዋን እያዳመጠ:: ፈገግ ብሎ አቀማመጧን ሰርቆ አየ:: ወንበር ወደ ላይ የገፋው የትንሽ ዳሌዋን ስፋት:: የሚያማምሩ ቆዳቸው ለስላሳ የሆነ ቀይ ዳማ እግሮች አሉዋት ቢነካቸው የማይጠላ:: ቢዳብሳቸው የሚሻ:: ቀሚስዋ የገጠሙ እግሮችዋ ስር ተጣጥፎ መልካም ጣቢታ ይመስላል:: ጌርሳሞት ራሷ ወጥ ናት፣ ከንፈሮቿ አዋዜ ናቸው:: ገላታ ደሞ ሰሃን ነው፣ ቢጠልፋት የምትፈልስበት:: በእጁም በዐይኑም ሊደርስበት የማይችለውን፣ ሱሪውን አልፎ የሚታከከውን ለስላሳ ቆዳዋን በዐይነሕሊናው ያወራዋል: *እንደ ሃር መሆን አለብህ እንደ ፈቷ መሆን አለብህ እንደ ውሃ መሆን አለብህ......*ልብ ሳይለው ቀኝ እጁን በከፊል ጉልበቷ ላይ በከፊል ቀሚሷ ያልሸፈነው የጭኗ ቆዳ ላይ ጣል እንደ አደረገ:: ሞከረ ሊክድ ሰላማዊትን:: *አመልካች ጣቱን እያነቃነቀ ቆዳዋን ቢዳብሰው* ከዛ ስር *ያለውን ሙቀት የሚያተነውን አጥንቷን ቢነካካው......ለመሆኑ* አንገቷ ነፋስ እንደነካው ዛፍ ያዘምማል? ደሞስ ይሄ አጠገባቸው ያለው ሕዝብስ ይሰወራል? ይበተናል? እንደ ጉም? እንደ ዱቄት? የላይና የታች ከንፈሮቿ ሲከፈቱም ሲከደኑም እንደ አበባ አበባማ አበባም አባቢ እብብ አበቡቴ አበቢት እንደ አበባ ጉንጉን (እሱን ማሰሪያ) እንደ አበባ እቅፍ (ከንፈር ማቀፊያ) የአበባ ዋንጫ (የአፉን ዝናብ የምትሰበስብበት) እንደ እቴ አበባሽ እቴ አበባዬ......እንዲዘግነው የዛን አፏን–የብርሃን ጨሌውን......ሊጠይቃት እንደተጠራጣሪ ጠቢብ *ለመሆኑ እንደዚህ የሚያምር ነገር በየትኛው የዓለም አልጀብራ እኔ ምስኪኑ ሊያጋጥመኝ ይችላል?* የከንፈሯ ስልቱ የሆነ አቀማመጡ የቦታ አወሳሰዱ: እንደ ዙፋን የሚያደርገው እንደመከዳ የሚሰራው: ቢጋደምበት ቢቀመጥበት ቢነግሥበት......ለመሆኑ ከንፈሮች የት ጋ መሆን ነበረባቸው?

አንድ ቀን ህሩይ የተባለ የውድወርክ አስተማሪው ለሆነ ቁምሳጥን የመሳቢያ ንድፍ እየሰራ ቀና ብሎ ተማሪዎቹን በፈገግታ

'የመሳቢያውን ኩላብ የት ላስገባው?' እያለ ሲጠይቅ እሱም ራሱን የት ስኬታም ስፍራ (ለዐይን ያማረ ደሞ ለስሜትም) ላይ ማድረግ እንዳለበት ሲገምት--ልክ እንዲህ አስተማሪውና ተማሪው በመንፈስ እንደተነታረኩበት መሳቢያ አፏ እንደ ኩላብ ገጽዋ ላይ ስክ ሆኖ:: ድንገት ዞር ስትል እጅ ከፍንጅ ይዛው ሲያፈጥባት እንደ ሌባ......ስለመኪናዎቹ ስታወራ ባታወራ ባታወራ አቤት ባታወራ...... አፏ ቢዘጋ እንደ ዱዳ ሲወለድ ጋግርት እንደ ተጣባው በሽተኛ......የከንፈሯ ሙቀት ከገጽዋ ላይ እንደማይታይ ሞገድ ደረቱን ሲያሞቀው......በቀስታ ተነቃንቆ ለአመል ስጋ የሰበሰበ ቀኝ ዳሌዋን በዳሌው ገፍቶ ቦታ እንዲጠባት እና እንድትሰማው እና መልሳ እንድትገፋው......እንደ በረሃ የሆነው የልጅነት ገላውን ትናንት ሰላማዊት እንደላበረደችለት ሁሉ ለአፍታ መሰወርዋን እየተመኘ: እንደ አለመወለድ ባለ ጥበብ:: በቀስታ ዞር ሲል ሊያያት እንደ ስርቆት...... ጌርሳሞት ጌርሳ ፊቷን አዙራ ስለ ተጋጩት መኪናዎች የነበር ወሬ ስታወራ: ወሬኛ:: ፀጉር የፈሰሰበት ማጅራቷን፣ እንደ ዋሽንት የቀጠነ አንገቷን ቢነፋት ቢዘምርባት: እንደ ቀናው እረኛ:: በሁለንተናዋ ቀዳዳ:: ለምን እንደሚፈራት እንደሚንቦቀቦቅ ቢያውቅም: አባቷ እንደአሳደገው ውሻ ስለሰደበው--በዚህ ሰበብ ልጁን በበቀል አበላሽቶበት......ከዛ ምላሱን እንደ ባለጌ ሊያወጣበት ቢያስብም: እንደ ሐጢያተኛ ወይ ከራሱ እንደተጣላ እንደ መንፈስ ደካማ:: ለምን ከንፈሯ እርዝ ሆነ? ለምን በእርቃኑ ስየታ ፈጀው?

እሱ ሲሆን መናገር ያቃተው እሱ ሲሆን ዱዳው እሱ ሲሆን እኩል አባቷን እንደ ሰላማዊት የፈራው......በድምፅ የለሽ ፉከራ ተደፋፍሮ በግራ እጁ ጉልበቷን ብቻ እንደያዘ ዐይኖቿን ለማየት ፈርቶ:: *ለምን ከአመት በፊት እሀ ያላልኩዋት ልቤን ወሰደችው? ተንኮል አለው? ነገርስ?* ለምሳሌ እንደምቀኝነትስ: ከሰላማዊት ገፍትራ ሰፈር ቦይ ልትጥለው: እንደ እቃ እንደ ሰባራ ጠርሙስ እንደ እንቅፋት: እንደሚታይና እንደማይታይ አሽከላ......

ሁለቱም የሚወርዱበት እስከሚደርሱ የተነጋገሩት ትንንሽ ጉዳዮችንና (*መከራ ነው ትራንስፖርቱ......ይገርምሃል ከትናንት ወዲያ*

*የሆንኩትን ብነግርህ......)* በየራሳቸው ወደ የግል ጉዳያቸው ከመሄዳቸው በፊት ሻይ አብረው ለመጠጣት መስማማታቸውን ነው:: በስርቅ መተያየታቸውን አላቆሙም:: ሰርቆ ማየት (እንደ ዘሪሁን አባባል--ገለታ ብቻ የሚያውቀው) 'ናይስ'[9] ነገር ነው:: የተቆራረጠ ሁኔታቸውን ከታዛቢ አፋተው በአእምሮአቸው ብላክቦርድ ላይ የትናንቱን፣ የአሁኑንንም፣ ምናብ የተቀባ ነገንም እየገጣጠሙ የሚደሰቱበት ነው:: ሰርቆ ማየት የመሰልጠን ክፊል መሰረቱ ሳይሆን አይቀርም:: መፈላለግ ያሳፍራል? ለስንት ሺህ ዘመን ሰው ያልተወው ምናልባት ጣፍጦት ያስቀረው ጥቅንጥቁ ነው:: ደሞ ይህ ተገልጦና ተሞሽሮ አይባል እንጂ መውደድ አይደል? ምክንያቱ በአፍ ልፍለፋ ባለመብራራቱ ግልፅ አይደለም ያሉት:: የልብ ዐይን ካየው የታየው ተደበቀ ይባላል? የግድ የመፋቀር ጉዳይ አደባባይ ላይ ከውጭ አገር እንደ መጣ ቁሳቁስ ለጉራ መሰጣት አለበት? ወይም ወደ ሎንዶን ለዲያስፖራ እንደሚጫን የድርቆሽ በርበሬ መልካምነቱና ማማሩ በየዌብ ሳይቱና በባዴ የስነምግብ እክስፐርቶች መዘዬር አለበት?............

......ሁለቱም የተስማሙበት ቦታ ሲደርሱ ከታክሲ ወርደው አንድ ቢጫ ሕንፃ ስር ያገኙት ካፊቴርያ (ሶሲ ባር) እውጭ፣ ክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጡ:: በግማሽ ሰአት ኬካቸውን በልተውና ቡና በወተታቸውን ጠጥተው ተነሱ:: በጣም ተጠግታ ስታየው ቅር ያለው ይመስላል::......ሲለያዩ መንገድ ዳር ጎን ለጎን ቆመዋል:: አጠገባቸው ጋዜጣ ሺያጭ በአዲስ የፖለቲካ ወሬ ሊማርካቸው ወረቀቱን ያውለበልባል:: ገለታ በትኩረት አየውና ዞር ብሎ ለጌርሳሞት:

---ምንም አዲስ ነገር የለም እኮ አላት

---ምን? አለችው::

ሰምታዋለች ግን ወሬውን እንዲቀጥል:: እዛ እዛ ታየዋለች: የጉንጩን ስርጓዶት፣ በትኩስ ቡና በወተት ያበጡትን ከንፈሮቹን: እዚህ ከፊቱ ላይ ቢወድቁ ቀልባ ቀሚሷን በትንሹ ከፍ አድርጋ ጭኖቿ መሃል አጣብቃ ይዛ ሲንፈራፈሩ ሲገለባበጡ ልትሰማቸው:: ዓይኖቿን ጨፍና ጆሮዋን ኮረኮረች:: አልተመቻትም::

---የሚያስፈልገን ጋዜጠኛ አይደለም

---ዝም አትላቸውም:: ምን ማለትዋ እንደሆነ አልገባትም

---የጎደለው ወሬ አይደለም ፍቅርና መተሳሰብ ነው አላት

---

---እንዴት? እሱ መቼ ጠፋኝ የተናገረው ከገባችበት ግላዊ ሰመመን አወጣት

---መውደድ ከውስጥ ነው የሚመጣው:: አንድ ሰው በአመለካከቴ ወይም በጎሳዬ ቢያርቀኝ ወይም ቢጠላኝ ደካማነት ነው:: የማያውቁትን ያልገባቸውን በልበሙሉነት የሚናገሩ አይገርሙም?

---*አይገርምም? ምን አመጣው ይሄን እዚህ? ነካ አርጎሃል? ፖለቲካ ከሚለፈልፍ ምናለበት አፍህ አፌን ቢደፍር?*

---ማለቴ ማስተማር ይከብዳል:: በጣም ቀላል የሆነውን ነገር አንዳንድ ጊዜ ማስተማር አይቻልም:: አንድ ኮሌጅ የጨረሰን የሂሳብ አዋቂ ሁለትና ሁለት አራት ብሎ ለማስተማር መሞከር ነው:: አልችልም ሲልሽ አውቆ ነው:: ዘርዓ ያዕቆብ ምን ይላል መሰለሽ?

---ማነው እሱ?

---በአስራ ስድስተኛው ክፍለዘመን የኖረ ኢትዮጲያዊ ፈላስፋ

---አስራ ስድስት? ሩቅ ነው

---የሚያሳዝነው እሱ ነው

---ለምን ያሳዝናል?

---አንድ ሰው ዱሮ የጨረሰውን ነገር ሺህ ጋዜጦች ዛሬ እናብራራ ሲሉ:: ማብራራት አያስፈልግም:: 2+2= 4 ነው:: ምን ማብራሪያ አለው?

---ሂሂ ሊሆን አይችልም:: *ቅንነት ማንን በየትኛው የወንዙ መልካ አሻገረች? አለነገር ሸቤ አልገባህም:: አንድ ወር መታሰር እዚህ ያደርሳል እንዴ?*[13]

---

[13] ለምን እንደታሰረ የተሰራጨውን ወሬ የሰማ ሰው ይስቃል:: ወሬው እንዲህ ነው: መማሪያ ክፍሉ ብቻውን ተቀምጦ ('እሱ እኮ ሰው አይቀርብም') ሲተክዝ አንድ ልጅ ይመጣና ትምህርት ቤቱ የገንዘብ ማሰባሰቢያ በአል አዘጋጅቶ መንገድ ተዳዳሪዎችን ለመርዳት ስላቀደ ሲዘፍን ስላየው ያቅሙን ይረዳቸው ይችል እንደሆነ ጠየቀው:: ገለታ አፉንም ሳይከፍት በጭንቅላቱ ንቅናቄ ብቻ አልፈልግም ብሎ ወደ ዴስኩ አቀረቀረ:: ገለታ እንዲህ ሲያደርግ የልጁ ፊት በንቀትና በብስጭት ሲለዋወጥ አላየም:: ገለታ ብቻውን በመቀመጥ ተሰላችቶ ከክፍሉ ሲወጣ በስተቀኝ በኩል ውለታ የጠየቀው ልጅ ከሌሎች ልጆች ጋር ቆሞ በሆነ ጉዳይ በስሜት ሲከራከር አየው:: ገለታ የሚሰራው ስላልነበረው እንደቁምነገር (ክርክር መስጠት ባያውቅም) ለአንድ ደቂቃ ያህል ቆሞ

ሲባል የሰማችው ወር ነው[14]

ልጁ የሚናገረውን ሰማው:: ወንድሞቼ ለምንድነው ከእኛ በማይጠበቅ ነገር በዚህ በሰለጠነ ዘመን በጎሳ የምንከፋፈለው? አባቶቻችንና እናቶቻችን ይህን አድርገዋል? ነቅተን ነው? ተሻሽለን ነው? አንድ ነገር ማድረግ አለብን ብሎ እንደተናገረ ገለታና ልጁ ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ:: ልጁ ጮክ ብሎ ለመሆኑ ያ አዝማሪ ልጅ ጎሳው ምን እንደሆነ ይታወቃል? እስኪ ልጠይቀው:: ወንድም! ሰማህ? ጎሳህ ምንድነው!? ማለቴ ብሄረሰብህ?! እዛ የተሰበሰቡ አስርና አስራ አምስት የሚሆኑ ልጆች ዞር ብለው ከገለታ መልስ እንደሚጠብቁ አይነት አፈጠጡበት:: ገለታ ግራ ገብቶት አፉ እንዳመጣለት ምንም አይመስለኝም:: ጎሳዬ ተጻፈ አልተጻፈ አለ:: የጠየቀው ልጅ ከት ብሎ ሳቀና በንቀት ከፍ ዝቅ አድርጎ አየው:: ገለታ የልጁን አሳሳቅ አይቶ ትርጉሙ ስለገባው ካልወደዳችሁ ለምን መታወቂያችሁን ሰብስባችሁ በህብረት አታቃጥሉትም? ቀላል ነው አለና ቀና ብሎም ሳያይ የማትበላ ወፍ ተይዛ በጭራ የተባለች ዘፈን እያንጎራጎረ ወደ ቤቱ የጀመረውን መንገድ ቀጠለ:: እንደሚሉት ከሳምንት በሁዋላ ከሚማርበት ትምህርት ቤት በር ላይ ሁለት ሰዎች ጠብቀው አግተው ይዘውት ሄዱ:: አንደኛው አጋች ምክንያቱን የገለጸበት መንገድ ግራ አጋባው: የትምህርትቤቱን ተማሪዎች መታወቂያቸውን ልክ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በአፓርታይድ ጊዜ እንደተደረገው እንዲያቃጥሉ ስለቀሰቀስክ ነው የታሰርከው አለው:: ገለታ ግን የተናገረው አንዱም ነገር ትዝ አይለውም::

14 በትክክል ግን ለሳምንት ጠፍቶ ነው የተገኘው:: ገለታ ጠፋ እንደተባለ የጠፋበትን ምክንያት የሚያጣሩት የታቦት ማደሪያ ጥቂት ሰዎች፣ ላይ ወጥተው ታች ወርደው ሊያገኙት አልቻሉም:: ከተማው ውስጥ ቦታ አልቀራቸውም:: በአእምሮ ጥናት ሳይንስ ሳኩናር አምኔዢያ ወይም ሴሌክቲቭ አምኔዢያ (አንዳንዶች ዲሶሺዬቲቭ ፉጉ) ይሉታል የሚባለው በሽታ ገለታ እንዳለበት የሚያውቁት እናትና አባቱ ብቻ ናቸው:: ይሄ በሽታ ያለበት ሰው አንድ አሁን የተሰጠውን መረጃ ወይም ያሳለፈውን የቅርብ ልምድ እንዳላደረገው ወይም እንዳልኖረው ሁሉ ያኤወኑ ይረሳዋል:: አንድ እለት ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ እግረ መንገዱን ሰናይትን ሰላም ሊላት በሱቋ በኩል ሲያልፍ አለባበሷ ማርኮት፣ ቁልምጫዋና ዳበሳዋ ልቡን ነስቶት፣ ቶሎ በር ዘግተው እጅግ ያደከመው እኳንም ያሳዘናትና ያስለቀሳት ፍቅር ሰሩ:: እዛች የተቃቀፉበት አልጋ ላይ ተጋድሞ ትምህርትቤት ልሂድ አልሂድ እያለ ሲያስብ ሰናይት ወደ ግጥም በተጠጋ አማርኛ፣ ወደ ዘፈን በተጠጋ ድምፅ እንዳይሄድባት ስትለማመጠው ደንበኞች በር አንኳኩ:: እንደምንም ከአልጋው ተነስቶ

---

በከፊል ራሱን እያዞረው በጀርባ በር ወጥቶ ትምህርት ቤት ሄደ:: ክፍል ከመግባት ይልቅ ደብሮት ትምህርት ቤት ፊት ለፊት አንድ ግንብ ተደግፎ የመንገድ ወሬ እያየ ሲያንጎራጉር፣ ልጆች ይመጡና አሪፍ ዘፋኝ ስለሆነ *ፈንድ ሬይዚንግ* ላይ እንዲሳተፍ ጠየቁት:: ከዚህ በሁዋላ እሱ የመለሰውም ይሁን እነሱ የመለሱለት ትዝ አይለውም::

ከላይ እንደተጠቀሰው ይሄ በሽታ እንዳለበት የሚያውቁት ወላጆቹ ብቻ ናቸው:: የበሽታው አይነት በአጭሩ እንደዚህ ነው: እተቀመጠበት ይጫወት እንደሆነ ፈዞ የት እንዳለ ይዘነጋል:: ሲጠሩት አይሰማም:: ቢሰማም እሱ ሳይሆን ሌላ ሰው የተጠራ ይመስለዋል:: ለመጀመሪያ ጊዜ እናቱና አባቱ በአስራ አንድ ይሁን በአስራ ሁለት አመቱ ታሞ አጋጥሞአቸዋል:: ለጥቂት ወራት አቡነ አረጋዊ ጠበል፣ ብስራተ ገብሬልና ቀራንዮ ሲወስዱት ቆዩና ስለ ተሻለው አቆሙ:: እናቱ ፎርቱና ማን እንዳሻለው ባያውቁም ሶስት ዣንጥላ ገዝተው አንዱን ለገብሬል አንዱን ለአቡነ አረጋዊና ሶስተኛውን ለመድሃኒያለም ቤተክርስቲያን ከሰጡ በኋላ ቆይቶ ለጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አራተኛውን ዣንጥላ ሰጡ: *ከቅዱስ ቅዱስ ቢለዩ አመትም አይቆዩ::* በሽታው አደፈጠ እንጂ አልተወውም::

ሰዎች ሁሉን ነገር ከፖለቲካ ማያያዝ ስለሚወዱ እንጂ ገለታ ያን ቀን የተሰወረው ታግቶ ሳይሆን በሽታው ተቀስቅሶ ለሳምንት የቤቱ አድራሻ ጠፍቶት መመለስ ስላልቻለ ነው:: በሶስት ቁጥር ማዞርያ፣ በፒያሳ፣ በሳር ቤት አካባቢ፣ በሌላም ቦታ ሲንከራተትና በመንገድ ላይ ሲያድር ቆይቶ አንድ ቀዝቃዛ ጠዋት ላይ የሆነች ጠባብ ክፍል ውስጥ ነቃ:: አልጋ ውስጥ ነው:: ራቁቱንም ነው:: ክፍሉ የሽቶ ጠረን አለው:: ጎኑ ሴትዮ ተኝታለች:: ዞር ብሎ ሲያያት ፈገግ ብላ እያየችውና ሆዱን እየዳበሰች: *ተነሳህ? እግዜር ሰርቶሃል አንተ መቼም ሰናይት ታድላለች:: ምን የመሰለ ቁርስ ሰርቼ ነው የምሸኝህ:: አግባኝና ገላግለኝ በማርያም* አለችና ከት ብላ ሳቀች:: ጮክ ብሎ *ንገሪኝ የት ነኝ?!* ብሎ ጠየቃት:: *ሰፈርህ ነሃ! ለደቂቃ ዐይኖቹን ጨፍኖ ጸጥ* አለ:: *ሰፈሬ ሰፈሬ ሰፈሬ:: ሜሮን ነሽ አይደለ?* አላት በጥርጣሬ:: *አበዛኸው አሁንስ ሂሂሂ ይልቁን ቀስ በል ጎረቤት እንዳይሰማህ* አለች:: ከተጋደመበት ግራና ቀኝ አየ:: ከአልጋው ራቁቱን መውጣት ፈርቶ ልብስ ፈለገ:: ሱሪውና አመዳም ካናቴራው ተጣጥፈው ራቅ ብለው ወንበር ላይ እንደ ደከመው ፍጡር ተቀምጠዋል::

ሜሮን የሰናይት የድሮ የትምህርት ቤት ጓደኛ ናት:: ሜሮን በዱርዬነት (ትኩስ ዱርዬ ለነበረች ጊዜ *ምን ታደርጊዋለሽ፣ ስምሽ ሜሮን ከሆነ እጣሽ ያው ስድነት ብቻ ነው* ትል ነበር) ሰናይት በደደብነት በህብረት ትምህርት ያቋረጡ ናቸው:: ሜሮን አየር ጤና

---

አካባቢ ያለ ሬስቶራንት ውስጥ አሳላፊ ሆና ትሰራለች:: መልከመልካም ስለሆነችና ከጀርባ ደንበኛ የማስደሰት ስራ ትሰራለች ስለሚባል ቀጣሪዎቿ ልዩ ክብር ይሰጧታል:: ገለታ አይኖቹን ጨፍኖ እዚህ እልጋ ላይ እዚህ ቦታ ምን እንደጣለው ያስባል:: *ያለኸው አየር ጤና ነው:: ትናንት እንኳን አልሰከርክም ነበር* አለችው:: *ያቺ ጋገርታም ሰናይት ታድላለች:: ገለታ ሰማህ ኮንዶም አድርገናል: አይዞህ::* በልጅነቱ አንድ ሁለቴ ያጋጠመው ፉገ (የመርሳት) በሽታ ተመልሶ እንደመጣ ገባው:: ከተኛበት ተነስቶ ልብሱን ለብሶ ሜሮንን ደህና ዋይ እንኳን ሳይላት ወጥቶ በቀጥታ ወደ ቤቱ ሄደ:: ቤቱ እንደደረሰ እናቱን እንዳታለቅስና እንዳትጮህ እየመከረ ሳምንቱን የጠፋ ጊዜ ያጋጠመውን፣ ትዝ የሚለውን አንዳንድ ነገር አስቀርቶ ነገራት:: እናቱ ንፍጥዋን እየጠረገች ሜሮን የተባለችውን ልጅ ስለጠለለችው ድምፅዋን ከፍ አድርጋ መረቀቻት:: ለሳምንት የት እንደጠፉ ጓደኞቹ ሲጠይቁት የሆኑ ሰዎች አግተው አይቶት የማያውቀው ቦታ እንደወሰዱት ነገራቸው:: ባልንጀራቸው ስለሆነ አመኑት:: ይሄ ቅጥፈቱ፣ መሰረት ያለው እውነት ሆንና ካልጠበቀው እውቀት ጋር አሳተመው:: ለሳምንት ታስሮ እንደነበረ ለሰናይት ሲነግራት ደምዋ ፈልቶ: *ምንድነህ አንተ? ምን አገባህ? ምን ታውቃለህ? አርፈህ አትቀመጥም?* አለችው:: ሰናይት እሱን በትክክል እንደማትወደው ገባው:: አላደረገውም እንጂ፣ ለመሆኑ 'ያገሬ ነገር ያገባኛል' ካለ ለምን አያገባውም? እሱ ከማን ያንሳል? ይሄን ያህል ደንቆሮ ነው? *አርፎ መቀመጥ* ማለት ምን ማለት ነው? ከእባባሏ የምር የመታሰር ዕጣ ቢደርስበት ደደብነቱን፣ ቂልነቱን፣ በማያገባው መግባቱን ሰበብ አድርጋ ከሚወነጅሉት ጋር መጻበሏ እንደማይቀር ጠረጠረ:: ለጌርሳሞት: *አዲስ ነገር የለም፣ መጠራጠር፣ መገለማመጥና መናናቅ ያለበት አካባቢ መኖር አይመችም* ሲላት ለፖለቲካና ለዲሞክራሲ ግድ ሰጥቶት አልነበረም:: ሰናይት፣ መሰሎቿና አለም ስለእሱ ያላቸውን ግምት እየታዘበ ነው:: ለዚህ አገር ፖለቲካ እንኳን በወዳጆቹ ለመታጨት አቅም የለውም:: ማለት ከሰው በታች ነው:: ማለት በጣም በጣም ቀሽም ነው:: ከሰናይት ጋር ፍቅር ሲሰራ በገላዋና በእጇ የምትሰራው ዘፈንና ምጥ ሁሉ ወደ ልቡ መሻገሩን አቆመ:: ማንጎራጎር በማያቆም መልክ የሳበውና በአያኖም መልክ ቀስ በቀስ በዝምታ የተዋጠው ለዚህ ነው::

ሰናይትን እየሳመ፣ ከሰናይት ገንዘብ እየወሰደ አየር ጤና፣ ቤቴልና ጀሞ መደበሩን ቀጠለ:: ከወደቡ በቀስታ የሚርቅ ጀልባ እንደሆነ ሁሉ ተሰማው:: የጌርሳሞትን አፍ ቢወድ እንኳዋን ልብዋን አላመነውም:: አብረው አደጉ እንጂ እነጣጥሬ እንደማታውቀው ይጠረጥራል:: ከቆመበት ትንሽ ቦታ ጀምሮ እስከዛ አድማስ ድረስ ሊዋጋው የማይችል ስር የሰደደ ድንቁርና እንደሰፈረ ሲገባው አፉን

---

*---መገለማመጥ፣ መጠራጠርና መናናቅ ባለበት ቦታ መኖር አይመችም*

---አዎ እሱስ

---ወደ ውጭ ለመሄድ አስበሽ አታውቂም?

---ማለት?

---በዘመድ ወይም በዲቪ? ወደ አውሮፓ ወይ አሜሪካ

---እኔ እንጃ……ለምን ብዬ?

---ነገሩን ነው

---ከአባባልህ የቋመጥክ ትመስላለህ:: ትምህርትህስ?

---ትምህርት እዚህ አገር ብቻ ነው ያለው እንዴ? እዛ እማራለሁ……

---እናትህስ ማለት ቤተሰቦችህ?

---ምን አደርግላቸዋለሁ፣ ሸክም መሆን ነው

ይሄን ሁሉ እያወራ ግን በየመሃሉ ደስ ትይኛለሽ ሊላት ይፈልጋል:: መውደድና ጣጣ አብረው ሲሸመኑ እንደዚህ ነው:: ሁለቱ ቃላቶች ('ደስ' እና 'ትይኛለሽ') አይኖቹ ውስጥ በነጩና በጥቁሩ ተጽፈዋል፤ እንደ መብራት ብልጭ ድርግም ይላሉ:: ሚስጢር ግን ያደርገዋል:: የማይላት ማን አለ ግን? የምር ያን አፍ መሳም የማይፈልግ ማን ነው? ወዳጆቹ ስሟን አያነሱም፤ ሲያይዋት ግን

---

ለክርክር ሳይከፈት መታዘቡን ቀጠለ:: ይሄንንም በዝምታ መከታተል ስላደከመው ከዚህ አገር መሸሽ ነበረበት:: ብስራተ ወንጌል ከሚኖሩ ሁለት ልጆች ጋር ተማክሮ (እንደሚባለው) ከአገር ወጣ:: የገሊታ ሸፍትነት ተደጋግሞ ከሚነገረው ተቀባይነት ካገኘውና እንደ አየር ከከበበው በማንም ወሬኛና ፖለቲከኛ በሚነዛ አግኖስያ ላይ ነው:: የት እንደሄደ ባለመናገሩ ለተወሰነ ጊዜ እናትና አባቱ በልጅነቱ ጊዜ የያዘው በሽታ ተነስቶበት እየባከነ እንደሆነ ሲጠረጥሩ ቆዩ: *ሕመሙ የት ሰዶት ይሆን? እዚህ ቄራ? እዛ ጀሞ? ወይ ቦሌ? ወይ ባሌ? ወይ ሰላሌ? ወይ ነገሌ? የት ወድቆ ይሆን? መቼ ነው የሆነች ቆንጆ ጠልፋ አድና መልሳ ቤቱ የምትሰድልን?* ሲጨነቁ ቆይተው አንድ የሰፈር ልጅ ቀን ጠብቆ ምን እንዳደረገ ነገራቸው:: ለአፍታ ዝም አሉና *እንዴት እንዲህ ያደርጋል? ምን ጉድ ነው? ምን አደረግነው?* (አሁንም ስለበሽታው ማጋለጥ አልፈለጉም) የበለጠ ግን አንደማይገናኙ በመጠርጠር ልቅሶአቸውን ጀመሩ:: እስከ አሁን አባቱ ባይሆኑም እናቱ ፎርቱና ደረት መድቃታቸውን እንዳላቆሙ ይወራሉ::

---

ዓይኖቻቸው ይፈጣሉ:: አባቷንስ ስለሚፈራ ነው? በእርግጥ አባቷን ይፈራዋል:: 'አባትሽን' እፈራዋለሁ ሊል አይችልም:: ወንድነት አይደለም:: አምባጓሮው ከደመቀ ሰላማዊት ትሰማለች:: መመኘቱን ቀጥሎ መፍራቱን ለማንም መናገር አይችልም:: የቦቅቧቆች ነጋድራስ ((ቦቃራስ) ሊሆን ነው::

---ከወጣህ በኋላ ሲመችህ እንዳትረሳን፡ እንዳትረሳን ማለት እንዳትረሳኝ እንደሆነ ይግባህ::

ሁለቱም ተያይዘው ሳቁ::

---ለመሆኑ አንድ ቦታ ብንሄድ ምን ይመስልሻል?

---የት? ልቧ ጠብ ያለ መሰላት

---የኢየሱስ ቃል የሚነገርበት ቦታ አለ::

እንዲህ ሲላት ባይታይባትም ትንሽ ደነገጠች:: ቆዳዋ ስር ደሟ ተንተከተከ:: *እኔ የምፈልገው እሱን፣ ክርስቶስን መቼ ሆነና*

---እኔ ጴንጤ አይደለሁም አለችው ቁጣዋን ውጣ

---ምን ማለትሽ ነው? ስለ እግዚአብሄር ስለ ፍቅር ስለ ሰላም ነው የምትማሪው::

'ለምን ከሰላማዊት ጋር አትሄድም' ልትለው ፈለገች:: ገለታን እንደዛ ለማንጓጠጥ አንጀቱ የላትም:: አሁን ጊዜው የእግዚአብሄር ሳይሆን የሌላ ነገር ነው:: ከልጅነቷ ጀምራ በቤተክርስቲያንና በምንትስ እናትዋ አማራታለች:: እሷን አይደለችም እሷ የምትሰራውን የምትሰራው:: የሚያበሽቁዋት ኮረዶች በነጣላ ተጀቡነው እናታቸውን ተከትለው በየደጀሰላሙ የማያገኙትን ወይም የማይሰጣቸውን ቅድስና ለመጨበጥ የሚንጠለጠሉት ለማኞች ናቸው:: እግዚአብሄር እንዲህ በቀላሉ የሚፎገር ነው እንዴ? ሌሎችን ልጆች አትሆንም:: አለምን አለም መስከ ሳይ:: እሷ በምትሄድበት ገለታ እንዲሄድ ፈለገች:: በእነዚያ እጆች መታቀፍ:: ካስፈለገም ስራ ስትፈታ የፀጉሮቹን ጥምዝ ብዛት መቁጠር:: *ደጀሰላምን ምን አመጣው?* ጃኬቱን ይዛ ነቅንቃ አንቅታ ልብ አስገዝታ 'ሌላ ቦታ እንሂድ' ልትለው ፈለገች:: 'እንዴ ከፈጠረህ በሁዋላ አርፎ እንዳይቀመጥ አምላክን ለምን ትጨቀጭቀዋለህ፣ ቦቅቧቃ' ልትለው ፈለገች:: የደደብ አፍቃሪዎች አቤቱታ ጵረአርያም አይደርስም:: ከመሃል መንገድ አርቦትና ከስቶ ይወድቃል:: አስር አመት ከጸለየ አንድ ደቂቃ የሳመ እንደሚበልጥ ምዕመን ገና አልተረዱም:: አተኩራ በቅሬታና በፀፀት ዐይን አየችው:: ወንድ ልጅ መሆን ተመኘች:: የምትፈልገውን ልትጠይቀው:: ስለምትወደው ነገር ልታወራው:: የባጥ የቆጡን:: የሰማይና የመሬቱን::

አንድ እሁድ ዕለትም በሕልምዋ እንዳየችው:: ባታየውም:: የሕልም ተረክ ታስባለች ድንገት ቢጠይቃት--እንደ ማይጠይቃትም ደሞ ታውቃለች::

በቅርብ የሆነ ደባሪ የኅዳር ማታ ላይ ዘመድ ጠይቃ ወደ ቤትዋ ስትመለስ ገለታን ወደ ቤቱ በእግሩ ሲሳብ አገኘችው:: ቤትዋ ከእሱ ቤት አለፍ ይላል በዘገምተኛ አካሄዷ ውስጥ እሱ ቢያጋጥመኝ ግምት ተሰንስኖ ተኝቷል:: እንዳይሰማት አድርጋ ለጥቂት ሰከንዶች አረማመዱን እያጠናች ከሁዋላው ተከተለችው:: ለብቻው የሚነጋገር ይመስላል:: አንድ እጁ ይነቃነቃል:: ካሰከረው ሃሳቡ ልታወጣው ፈለገች::

--ታዲያስ ገለታ!
በድንጋጤ ዞር ብሎ::
--ታዲያስ ጌራ! አለ
ቆሞ ጠበቃት::

......መንገዱ ፒስታ ነው የሚያደናቅፍ፣ ታዲያ መደገፍ ነበረባት ግድግዳ፣ ከዘራ ወይም ሰው:: እጅዋን ይዞ ጥቂት እንደሄዱ ይሂ መንገድ መቼ ይሆን የሚሰራው? እያሉ የተለመደ ሂስና ፀረ ማዘጋጃ ቤት ሃሜታ እየነሰነሱ:: የሰማዩ ጥቁረት ውስጥ ጠይምነትዋ ወደ ኑግ ቀለም ቀልጦ እናም ፀጉርዋ በዝምታ ለመታቀፍ እየጮኸ፣ የተያያዙት እጆቻቸው በላብ እያዳለጡ ኧረ አንድ ነገር አድርግ በልቧ እያለች ቤትሽ ልሸኝሽ ብሎአት ከሰው ቁመት ሁለት ሜትር በሚበልጥ የቤትዋ ግቢ ግንብ አጥር ስር ወገቡን ይዛ ወገቧን ይዞ ቆሙ:: ጠጋ ብላ ወደ ደረቱ ያን የማይለውጠውን ካናቴራ እየነካካች ስትዘፍን እኮ ደስ ትላለህ (ማንም ይላል) አሪፍ ነህ የምር (ሰላማዊትም ትላለች) ለምን ዘፈን መርጬ አትዘፍንልኝም? ሂሂሂ (ማንም ያለውን) ስትለው አይመልስላትም፤ ጆሮዎቹን አቁሞ እየተነፈሰ ይሰማታል:: ከእግሮቹ መሃል የሚነሳው ሙቀት እንደ ቆላ ወላፈን ይሰማታል:: ደረቱን በግንባሯ ተደገፈች:: ከንፈሮቿ ይንቀጠቀጣሉ::

የማይመልስላት ስለማያምናት ነው:: የማያምናት የምታወራው የተለመደውን ፍሬከርስኪ ስለሆነ ነው:: በግራ እጁ ቀኝ ጉንጭዋን ዳበሳት:: ይሄንን ሰላማዊት ጋ ያደርጋል:: ሰላማዊት ግን አንገቷን ሰበር አድርጋ እጁን በፊቷና በትከሻዋ አጣብቃ ትይዘዋለች:: ምክንያቱም

ሰላማዊት ለምዳለች:: ጌርሳሞት አፍጣ እያየችው ከንፈሮቿ ተንቀጠቀጡ:: ቀኝ እጁን ግራ ጉንጯ ላይ ጣል አደረገ:: ከአፏ ከነዚያ ከሚያምሩት ከንፈሮቿ፣ ጨለማ የረታ ውበት ይወጣል:: እነሱን በመገረም ሲያይ ቆየ::



እንዴት እንዲህ ቅርጻቸው አማረ? እንዴት እንዲህ ሁልጊዜ ሊፈነዱ የደረሱ ይመስላሉ? ለምን እንደመግነጢስ ይጎትቱታል? በሁለት እጆቹ ፊትዋን ይዞ አቅርቦ አያት:: ጌርሳሞት የሚያደርገውን ትጠብቃለች:: ደረቷ በትንፋሽዋ ከፍ ዝቅ ይላል:: እንዲህ ያማረ አፏን እያየ ትዝ ያለው አንድ ጠዋት......*ከወር በፊት?* ቀንና ማታ የማይለወጥ ጥቁር ኮት ለባሽ የውድወርክ አስተማሪው አቶ ጎሩይ ጥሩ መደርደሪያ እንዴት መስራት እንደሚቻል የተለያዩ ቴክኒኮች ሲጠቀም እግረመንገዱንም ተማሪዎቹ ስለ ዲዛይን ሰፊ ሀሳብ እንዲኖራቸው ***ወርቅማው ሬሾ/ልክ/ሚዛን***[15] በእንግሊዘኛ *ጎልደን ሬሾ*[10] ስለተባለው የዓለም

---

15 **(ከወይዘሮ መቅረዝ አዝማች መፅሐፍ *<u>ወደ ፊት ለመወንጨፍ ወደ ኋላ መንደርደር: ባህላዊና ዘመናዊ ፈውሶች</u>* ከአፍን ሲመቱት ዐይን *ያለቅሳል*** ንዑስ ምዕራፍ (ከገጽ48 እስከ 52) ካለው የተቀነጠሰ 2001 **አም)**

**(**......በግል ካጋጠሙኝ ልምዶች በመነሳት የአገራችንን ወይዛዝርትና ወይዘሮዎች ፊት (ወንዶችንም ሊጨምር ይችላል) እንዴት መረዳት እንደምንችል ብዙ ከተነገረላቸው ብልሃቶች አንዱን ፅንሰሃሳብ በማጤን ቀላል የመሰለው ጉዳይ ምን ያህል የተወሳሰበ ሊሆን እንደሚችል በአጭሩ ለማሳየት እሞክራለሁ:: ፅንስ ሃሳቡ ***ወርቃማው ሚዛን*** (በእንግሊዘኛ ***ጎልደን ሬሾ***) ወይም መለኮታዊ ሚዛን (ዲቫይን ፕሮፖርሽን : Dvine proportion) ይባላል:: እንዲህ እንዳደርግ ያነሳሳኝ ወይም የቀሰቀሰኝ ከረዥም ጊዜ በፊት ያጋጠመኝ ተራ ልምድ ነው::

አንድ ማታ ልጄ አቡና የስፈር ወዳጆቹ ገና የኮሌጅ ተማሪዎች እያሉ፣ ለፋሲካ ወይም ለገና መሰለኝ፣ ግቢያችን ተቀምጠው የበዓል ጠላ እየጠጡ፣ እኔ መኖሬን ልብ ሳይሉ እንዳሻቸው ሲያወሩ ሚስጢራቸው ጆሮዬ ገባ:: የልጄ አንዱ ጓደኛ አንዷን የስፈር ልጅ በስም ጠርቶ ከንፈሮቿ ውብ እንደሆኑ በሚገርም አድናቆት ሲናገር የቀሩት በህብረት *ትክክል ነሀ* ሲሉት ሰማሁ:: በፍርዳቸውም መመሳሰል ራሳቸው ተገርመው

---

መሰለኝ ሞቅ ያለ ሳቅ ሳቁ:: አራት ጎረምሶች (ከልጄ ጋር አራት ነበሩ) ሳይነታረኩ በአንዲት ልጅ ውበት ሲስማሙ ስላጋጠመኝ ገርሞኝ ነበር:: በሚቀጥሉት ቀናት፣ ሳምንታትና ወራት ልጅቷ በመንገድ ስታጋጥመኝ አፏን በማየት፣ ከንፈሮቿን በመሰለልና ሲመቸኝም ጉዳይ ፈጥሬ በማዋራት የልጆቹን ፍርድ ትክክለኛነት አረጋገጥኩ:: እንዲህ ሆኖ ጥቂት አመታት አለፉ::

ይሄንን መፅሐፍ በማዘጋጅበት ወቅት ስለ ሊፕስቲክ (የከንፈር ቀለም) አንድ ነገር ማለት ግዴታዬ እንደሆነ ስረዳ የልጆቹንም ይሁን የራሴን የከረመ ፍርድ በመጠራጠር የቀድሞ መደምደሚያዬን በሆነ መላምት ለመፈተሽ ተነሳሳሁ:: መላምቱ የሚለው ለመሆኑ ፊታችን ላይ ያሉ የተለያየ ስም ያላቸው ትንሽም ይሁኑ ትልቅ ብልቶቻችን ብቻቸውን ናቸው? ብቻቸውን ከሆኑ አፍን በጥሬ ሲመቱት ዐይን ለምን ያለቅሳል? በሌላ ፈርጅ ወይም በስነ-ውበት ፈርጅ የአፍን ውበት ከዐይን ወይም ከሌሎች ብልቶች ነጥለን መረዳት እንችላለን? ወይስ ሆን ብለንም ይሁን ሳናውቅ ስሌታችን ውስጥ ያልከተትነው ፍርደ ገምድል የሚያደርገን መረጃ አለ?

ልጁ *የልጅቷ ከንፈር ወይም አፍ ቆንጆ ነው* ብሎ ሲናገር መመዘኛው ምንድን ነበር? እዚህ አይነት መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ልምድ አለው? ማለት ስንት ከንፈሮችን ማየት፣ መገምገምና በሚቀምስበት መቅመስ አለበት? የተናገረው ከአፉ አምልጦት ነው? በተጨማሪ ጓደኞቹ የተናገረውን ለምን አመኑት? ከዚህ በፊት አውርተው የተግባቡበት ጉዳይ ይሆን? ካሉት አራት ሰዎች አራቱም *ታምራለች* ስላሉ ትክክል ናቸው? ማለት 100 ፐርሰንት መስማማት የተባለው ጉዳይ ቢበረበር በእርግጥ መስማማት አለበት? ማለት በይሉኝታ ሊከተሉት አይችሉም? ምናልባት ስለወደዳት እሱን ላለማስቀየም *ልክ ነህ ልክ ነህ* እያሉት ከሆነስ? እንዴት ነው ከንፈሯ ሲጀመር መነጋገሪያ ኪነታዊ ተስህቦ [ኤስቴቲክ ኦብጀክት (Aesthetic object)] የሆነው? እነዚህ ልጆች የሚስማሙበት የሃሳብ (የግል) ወይም የባህል(ማህበራዊ) መሰረት ሲጀመር ነበር? ሌሎች በእሱ ዐይን ልጅቷን እንዲያዩ የማድረግ ግለኛ ፍላጎትና ያበጀው ወይም የተከተለው ሴራ ይኖር ይሆን? ፈላስፋው *አማኑኤል ካንት* እንዲህ አይነቱን ሁኔታ ኤስቴቲክ ዩቶፒያ (**Aesthetic Utopia**) (ኪናዊ ተምኔት) ይለዋል:: በኪነታዊ ፍርድ ሁሉ የተስማማበት ማለት ነው::

ብዙዎቻችን ቀድመው በተናገሩ ደፋር ብልጣብልጥ ሰዎች ጽንሰ ሃሳብ ወይም አንድ ወጥ አባባል ስር ተስማምቶ ማደርን ስለቻልንበት ነገሮችን አቅልለን በማጣጣም መርካት ለምደናል:: እንደ አሳቢና አመዛዛኝ ፍጡራን ቀዳሚያችን ትክክል ቢሆንም ባይሆንም ማንኛውንም

አይነት መረጃ ለመቀናቀን ፍላጎትና ሃሳብ እንዲኖረን ግን ግድ ነው:: ሥልጣኔን ወይም ደህንነትን እንደ ሚካፕ መበደርና መግዛት አንችልም:: ከሆነ ግን ጉልቻ እየለዋወጥን ሊኖር ስለማይችለው አዲስ ሾርባ ማውራት ይሆንብናል:: ቀድሞ ትክክል ናቸው ብዬ የማነባቸው ነገሮች ሁሉ ዛሬ አይደሉም:: በራሴም ልምድ ከአምስት አመት በፊት ውብ የመሰለኝ ጉብል ዛሬ አይመስለኝም:: አሳዛኝ ቢሆንም የአለም አለዋወጥና የእኔ መለወጥ ውጤት ነው:: አሳፋሪ ሳይሆን ስለራሳችንና ስለተፈጥሮ የምናውቅበት አንዱ ፈርጅ ነው:: ግን እንደአንዳንዶቹ በአለፈው ስህተቴ ውስጥ ከሚመስሉኝ ጋ ተሰብስቤ 'አልተሳሳትኩም ሞቼ ልገኝ አልልም':: የአንዳንድ ትዳር መፍረስ ምክንያት (በእርግጥ አልተጠናም እንጂ) እንደሚመስለኝ በማርጀታችን ቁንጅናችን ስለተበላሸ ሳይሆን ሲጀመር በትክክል በራሳችን ወይም በግላችን የውበት መገምገሚያ አለመተያየታችን ነው:: በወጣትነቴ ብዙ መልከመልካም የተባሉ ጎረምሶችና ልጃገረዶች አይቼአለሁ:: ከአመታት በኋላ ግን ወደ ሌላ ጉዳይ ተለውጠዋል:: ይሄ የሆነበት ምክንያት መመዘኛ ስልቴ በተወሰኑ እኔ ሳልሆን ብዙዎቹ በተስማሙባቸው፣ በቁጥር አንድ ሁለት በሚባሉ በሚያረጁ፣ በሚያፈጁና ብሎም በሚውረገረጉ ነገሮች ላይ ብቻ ያተኮረ ስለሆነ ነበር::

እንደው ምሳሌ ብዬ አነሳሁ እንጂ ትዳር ላይ ብቻ ሳይሆን እንዲህ አይነት ጠባብ ብቃታ ላይ ተመስርቶ የተወሳሰበ ሁኔታን መስመር ለማስያዝ መጣር በጥቂቱም ይባል በብዙ ለሜክአፕ አጠቃቀማችን የሆነ ዕውቀት ይሰጠናል:: ከመጀመሪያው የአስያየማችንን መነሻ ማወቅ ተከትሎት የሚመጣውን ፍርዳችንን ያሳምረዋል::

ይሄን ሃሳቤን በመጠኑ መሬት ለማስያዝ ልጃገረዶች ከንፈር ዙሪያ ቀላል ውይይት ብከፍት ደስ ይለኛል:: ስለከንፈር ለመናገር ስፈልግ ያኔውኑ በሃሳባችን የሚመጣው *አፍ* ነው:: በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ውስጥ *አፍ ማለት ከንፈር፣ ጥርስ፣ ምላስ፣ ላንቃና እስከ ጉሮሮ ድረስ ያለው 'ባዶ' ቦታ* ነው:: ከንፈር የአፍ *ንኡስ ክፍል* እንደሆነ ልንግባባ ግድ ይላል:: ከንፈር ፊት ለፊታችን የምናየው የሚከደነውና የሚዘጋው ምግብና አየር ማስገቢያው ስጋ አስተኔ ብልት ነው::

የአንድን ሴት ልጅ ከንፈር እናይና ቆንጆ ወይም አስቀያሚ ወይም ሌላ የመሰለንን ስያሜ እንሰጣለን:: ለመሆኑ አንድ ከንፈር ውብ የሚባለው መቼ ነው? ለምን ውብ ተባለ? አንድ ነገር ውብ ከተባለ በኋላ ውብ አለመባል የሚጀምረው መቼ ነው? ከንፈሮች የማይለወጥ ዘላለማዊ የሆነ የውበት ባህርይ [ኤሰንስ (essence)] አላቸው?


የተለያዩ ሰዎች አንድ ነገር ውብ ነው የመባሉን ምክንያት የተለያየ ያደርጉታል:: *ዊትጌንሽታይን* የተባለ ፈላስፋ አንድ ነገር ስናየው ብቻ

ውብ እንደሆነ ይገባናል ወይም እናውቃለን ይላል:: *ዴቪድ ሁም* የተባለ ፈላስፋ ደሞ ውበትን ማድነቅ ከተወለድን በኋላ የሚመጣ በልምድና በትምህርት የሚፈጠር ችሎታ ነው ይላል:: *ኤፒኩርየስ* የተባለ የግሪክ ፈላስፋ ደስ የሚለን ነገር ሁሉ ቆንጆ ነው ይላል:: የዚሁ የግሪክ አገር ቀንደኛ ፈላስፋ *አፍላጦን* ውብ ነገር *ሲሜትሪና ሃርሞኒ* ያለው ሃሳብ ነው ይላል:: ሲሜትሪ ለምን? ሲሜትሪ ጤነኛነትን ያሳያል:: ጤነኛነት ደሞ ለርቢ ይፈለጋል:: ይሄ የርቢ ጉዳይ በእንስሳትም ይሁን በሰው ልጅ በዝግመተ ለውጥ (**evolution**) ውስጥ ለረዥም ጊዜ የነበረና እስከ አሁንም ያላቆመ የብቆታ መደምደሚያ ድርጊት ነው:: ተባዕት እንስሳት ሚስት ሲመርጡ ወይም እንስቶች ባል ሲመርጡ ውበት ያያሉ:: የአእዋፍ በተለያየ የሚያምር ላባ መንቆጥቆጥ አላማው ይሄ ነው:: ያ ውበት ግን የሚያስተላልፈው የጤነኛነትን መረጃ ብቻ ነው:: ይሄን ሁሉ የተለያየ ፍቺ ያለው ቃል ሊለካ በሚችል መረጃ የማይቀርብ የፈላስፋውን የአማኑኤል ካንትን *ሳብጀክቲቭ ዩኒቨርሳልስ* (**subjective universals**) ያስታውሰናል:: ፅንሰሃሳቡ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የውበት መለኪያ አለው፣ ከግለሰቦቹ አምልጦ የሚገመገምበት ፍፁም ፅንሰሃሳብ የለም እና እንዲህ ሆኖም ብዙ ሰዎች የሚስማሙበት የሆነ ነጥብ ይኖራል ማለት ነው:: ይሄ አይነት ተመሳሳይ የውበት ፍርድ ያላቸው ሰዎች ስብስብ በዚህ ፈላስፋ *ሴንሰስ ኮሚኒስ* ይባላሉ (ተመሳሳይ የኪነት ጣዕም ያላቸው ማለት ነው):: እነዛ ተደብቄ ያዳመጥኳቸው ጎረምሶች ሴንሰስ ኮሚኒስ ናቸው::

ግን ብዙ ሰው ሊግባባበት የሚያስችል ሳይንሳዊ መለኪያ ሊኖር ይችላል? ወደ ወርቃማው ሚዛን የምመጣው አሁን ነው? በእርግጥ ውበት ይለካል? *ሴንሰስ ኮሚንስ* ቢኖር ባይኖርም መሰረታዊው አላማዬ ከንፈር ለብቻው ተነጥሎ የሚታይ ብልት እንዳልሆነ ለማሳየት ነው:: ከ2500 አመታት በፊት የነበሩት ፓይታጎራውያን (የፓይታጎራስ ተከታዮች) አንድ ነገር ውብ ነው የሚሉበት ምክንያት የምናየው ወይም ያጤነው ነገር (በዐይን በአፍንጫ ወዘተ) የተፈጥሮን ሁኔታ ስለሚያንፀባርቅ ወይም የተፈጥሮን ስሌት ስለያዘ ነው ይላሉ::

እንዲህ ተዘበራርቆ የምናየው አለም ለእነዚህ ፈላስፎች በሆነ መልክ በውስጡ ስሌትና እቅድ እንዳለበት ይናገሩ ነበር:: እንደውም ፍጡር ሁሉ ከጀርባው በቁጥር እንደሚገዛ፣ በተለይ የእነሱ ግኝት የሆነው 'ወርቃማው ሚዛን' መሰረታዊው እንደሆነ ይሞግታሉ:: የአበባ ቅጠሎችን አደራደር (ሱፍ አበባን ያጢኑ) የቀንድ አውጣ ዶቃ ሽምልል፣ የዲኤን ኤ ሞሎኪውሎች አሰዳደር፣ የጥርስ አደራደር፣ የሳንባችን የውስጥ ቅጥ ወዘተ......የወርቃማው ሚዛን አሃዝ የሚከሰትባቸው ጥቂቶቹ ምሳሌዎቻቸው ናቸው ብለው ዛሬም የሚያምኑ አሉ:: ይሄ አሃዝ በአጭር

ስሙ **'ፋይ'** ይባላል:: ይሄ አሃዝ የሚወለድበትን ቀመር በስዕል 1 እዩ:: የቀመርነት ወይም የአሃዝ ምልክቱም በስዕሉ (ስዕል 1) ላይ የምናየው Φ ነው::



ስዕል 1

ይሄንን ቀመር የሰው ልጆች በምሕንድስና፣ በኪነ ሕንፃ፣ በቅርጻ ቅርጽና በቤት ቁስ ስራ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ይገለገሉበት እንደነበር ይወሳል:: በዚህ ስሌት የተሰሩ የሰው የጥበብ ስራ ውጤቶች ውብ እንደሆኑ ይነገራል:: የጥንቱ የምዕራውያን ፒራሚድ ግንባታዎች፣ የሊኦናርዶ ዳቪንቺ ስዕሎች (በተለይ ብዙ ጊዜ የሚወሳው ቬትሩቪያን ማን (የቬትሩቪየስ ሰውዬ/ vitruvian man) የዚህ ስሌት ውጤቶች ናቸው ይባላል::

የበለጠ ወደ ወለሉ ልቅረብና ይሄንን የሚዛን ዕንሰ ሃሳብ ስሟ ስለተነሳው ልጅ ከንፈር/ አፍ ውበት ልመራመርበት ብል እንዴት እጠቀምበታለሁ? ስዕሉ ላይ (ስዕል 1) በግራ በኩል ያለው ቋሚ መስመር የልጅቷን ፊት ይወክላል እንበል:: ይሄን መስመር የተለያየ እርዝመት ባላቸው ሁለት ጓዳዎች እንክፈለው:: የመጀመሪያው (የላይኛው ክፍል) 'ሀ' ከፀጉሯና ከግንባሯ መገናኛ እስከ አፍንጫዋ መጨረሻ ያለው እርቀት 'ለ' ከአፍንጫዋ መጨረሻ እስከ አገጭዋ ያለው እርቀት ነው እንበል:: ሙሉው ቋሚው መስመር 'ሀ' + 'ለ' ጠቅላላ የፊቷ እርዝመት ይሆናል:: ወርቃማው ሬሽዮ የሚሰላው መስመሮቹ ጎን ባለው ቀመር ወይም ፎርሙላ ነው:: የዚህ የአሃዝ ውጤት ወይም Φ ሁልጊዜ 1.618... ከሆነ ወርቃማ ሚዛን አለ ማለት ነው:: ይሄ ቁጥር ውበትንና ያማረ ሚዛንን ወይም ሲሜትሪን ይጠቁማል:: ቀጥዬ ሊላቀቁኝ ያልቻሉትን ጥያቄዎቼን ልዘርዝር:

ይሄ ቁጥር ለብቻው የልጅቷን ከንፈሮች ውበት ሊገልዕ ይችላል? የከንፈሮቿ ቅላትና አከፋፈታቸውስ? በተገረበቡት ከንፈሮቿ ቀዳዳ የሚብለጨለጨት መንታ ማውለቢያዎችስ? የታች ከንፈሯ ግራና

ቀኝ እብጠትስ? እነዚህ ትንንሽ የመሰሉ ነገሮች ለመሆኑ ወደ የቱ ተደምረው በየቱ ሊካፈሉ ነው? ከንፈሯ ያማረው ከዐይኖቿ ከአገጪ ጋር ባለው አንፃራዊ አቀማመጥ ነው? ያማረ ድምፅ ስለሚወጣበት ነው? (ልጅቷ ዘፋኝ ወይም አንጎራጓሪ ባትሆንም) ከንፈሮቿ ለብቻቸው ፍጽምና የላቸውም? ለምንስ እርዝመት፣ መቀራረብና መራራቅ እየተደመረ ይካፈላል? የጠቅላላ ከንፈሯ ውበት የምንጭሯ የላይኛው ደርዝ ከአፍንጫዋ መጨረሻ ባለው እርቀት፣ ደሞም የታች ከንፈሯ ከአገጭዋ ባለው እርቀት ሊደነገግ አይችልም? ይሄ የአገጭ ቅርፅ፣ የአፍንጫዋ ስፋትና ከምንጭሯ ያለው እርቀት፣ የጉንጪ ሰፋትና ስርጓዷ፣ የጆሮዎቿ ከአፍዋ ያላቸው እርቀት ለምን ከቀመሩ አይገቡም? ገና ለገና ሂሳቡ እግዜር በሰራው ተፈጥሮ ውስጥ አለ ተብሎ የልጅቷ አፍና ፊት በዚህ ቁንፅል ስልት መገምገም አለባቸው? ስለ አፍጫንዋ ቀዳዳ ጥበትና ስፋት እንርሳ? (ስለ አፍንጫዋ ኗንተም ውበት እናንሳና) ከጆሮዎቿ ያለው እርቀት ለምን ብሎ ለከንፈሯ ግርማ ይሰጠዋል? የጆሮዎቿ ከጸጉሯ በተበደሩት ቅባት መብለጭለጭ ከከንፈሮቿ ነጸብራቅ ጋር ምን አወዳጀው? የምናውቀው በማናውቀው ሌላ መመጠኑ የሆነ ግራ መጋባት አያመጣም? ለምን ከንፈር ከንፈር መሆን አቁሞ በግንኙነትና በመተሳሰር ቅርጽ ስር ኪነቱ ይመዘናልስ? የዐይን ስፋት፣ የአፍ ስፋትና በመሃላቸው ያለው እርቀት ለምን የከንፈርዋን ነጠላ ውበት ይጋፋል? ሊነጥቅስ ይፈልጋል? ሰፊው የገጽ ርዕዮት ለምን የከንፈርን ነጠላ ውበት ሊነጥቅ ይፈቀድለታል? ለምንድነው የአንድ ነጠላ ቁጥር ፍርድ የበላይነትን እንዲወስድ የተደረገው? የሚገባን እኔንም የገባኝ ከንፈሮቿ እንደ ልጅቷ ብቻቸውን አለመሆናቸው ነው:: ቢሆንም የሆነ በየቀኑ መተዳደሪያ የሚሆነን የሚያስማማን መለኪያ ያስፈልገናል:: ‘ይሄ ውብ ነው’ ‘ይህቺ ውብ ናት’ ማለት ቀላል የሚመስል ግን ማህበራዊ፣ ግለሰባዊ፣ ሕብረተሰባዊ፣ አለምአቀፋዊና ተፈጥሮአዊ ፈርጅ ያለው ውስብስብ ጉዳይ ይመስለኛል:: ፊት ባህልና ተፈጥሮ የተገናኙበት ቦታ ስለሆነ አንድን ነገር ‘ውብ ነው’ ብሎ መሰየም አስቸጋሪና ከተባለም አላፊ ተለዋዋጭ እንደሆነ እንረዳለን:: ኡምቤርቶ ኤኮ የተባለ የስነምልክት ጠቢብ *የውበት ታሪክ* (History of Beauty, 2004) በተባለ መፅሐፉ ‘ውበት ፍፁም ሆኖ አያውቅም:: በታሪካዊ ሁኔታ ተለዋዋጭ ነው:: ይሄ ደሞ የሰዎችን ውበት ብቻ የሚመለከት ሕግ ሳይሆን አማልክትን፣ ቅዱሳንንና አመለካከቶችንም የሚጨምር ነው’ ይላል::

የበላይነት ባንሰጠውም፣ ወርቃማው ሚዛንን በተከራካሪ አንፃራዊነት በማሸት አስታራቂ የውበት መለኪያ ልናገኝ እንችላለን::

ቀጥሎ............)

---

አሳየቸው። እንደ እሱ ትረካ ይሄን ቀመር ከጥንት እስከዛሬ በምሕንድስና፣ በኪነ ሕንፃ፣ በቅርጻ ቅርጽና በቤት ቁስ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች እየተጠቀሙበት ውብ የሆነ የስራ ውጤት የሚያገኙበት ነው። በዚህ ስልት የተሰሩ የሰው እጅ የስራ ውጤቶች ለዐይን የሚስቡ ውብ ናቸው። የዚህ ወርቅማ ሬሽዮ ስሙ 'ፋይ' ይባላል። አስተማሪው የሆኑ ቁጥሮች ደምሮና በሆነ ስልት አካፍሎ **የፋይ እሴት 1.618** ነው ሲል ትዝ ይለዋል። የዚህ ቀመር አፈጣጠርና አሰራር አስገርሞት በደብተሩ ግራ በኩል አንድ ሙሉ ገጽ ላይ እንደፃፈው ትዝ አለው። የጌርሳን ፊት ይዞ ከንፈሮቿን ሲያይ የሚያስበው እግዜር ይህቺን ልጅ ሲሰራት ፋይ ተጠቅሞ እንደሆን ነው። ይሄ ከንፈር በፋይ ባይሰራ ኖሮ እንዲህ ያምር ነበር? እንዴት ቢሳም ደንብ ነው? ጌርሳሞት ዳሌውን ግራና ቀኝ በፍርሃት ይዛ በትንሹ እንኳን ስባ ወደ እሷ ማስጠጋት አፍራ ዐይኖቿን ወደ መሬት ጣል አድርጋ የሚሆነውን ትጠብቃለች። በላይኛው ከንፈሩ የላይ ከንፈሯን ሊነካት በከፊል ድፍረት ሲሳብ ተረከዞቿ መሬት ለቀቁ። ለመብረር እንደፈለገች ሁሉ ተንጠራርታ ቀረበችው። ዳቦዋ እንደ አቃቂ መፍሰስ ጀምራለች። *ከልቡ ነው? እሱ ምናልባት ሰላማዊትን እያሰበ ነው።* እያንዳንዱ ሰው ውስጥ ተፈቅዶለትም ይሁን ሳይፈቀድለት የገባ ፖሊስ አለ። ከሱሪው ስር የሆነ የምታውቀውና የማታውቀው ነገር ይጎራብጣታል። ከቆመችበት አንስቶ እጆቹ ላይ አጋድሞ በዝምተኛ አፉ ደጋግሞ ቢነፋት ምን ዘፈን ይወጣታል? አንድ ወይኔ እማዬ ብቻ የማጥሙ ስንኝ የሆነ እንጉርጉሮ አለ? እንደ አልሞ ተኳሽ በቀኝ ዐይኗ ንፁሕ ውሃ የደበቀ የመሰለ ስርጉዳቱን ታይ ነበር። ልዩ ድራት የሆነባት የስርጓዳው ጨለማ ነበር። በዚህ ስሙት ባሕር እንዳየች......ያ የማትዋኝበትን። ስሙቱ ምድራዊ አልነበረም። የገለታን ስም ከግስ ጋር ልትጠራው ትፈልጋለች። ቢቁነጠንጥም አፏ እንዲት ሆሄ ሳይወጣው ቃጥቶ ቀረ። የጥርሶቿ ስልፍ፣ ሞቃት የተንሰራፋ የሆነ ነገር የሻተ ምላሷ። ሞሳ ሞሳ የሚሉ ደግ ምሳ ያለፈባቸው ፍንጭቶች። ሀ ሐ ኃ ብላ ሁሉን ተንፍሳ ብታወጣው ታቦት ማደሪያ አረንጓዴ ዳሎል ትሆን ነበር። ከመሀል ከግምቡ አጥር ወዲያ አነፍናፊ እናቷ ጠራቻት፡

–ጌራ! ጌራ ነሽ!!!? ከማን ጋር ነሽ? ምን እየሰራሽ ነው?!!!

አንዳንድ እናቶች የሚያበሳጭ አይነት ወሬ አነፍናፊ ናቸው። ገለታ ቀና አድርጎ ወደ አፉ ሊያቀርባት ሲል ከእጁ ላይ ፈቷ

---

እንደተነነ ሁሉ ጠፋ:: አባቷን ይፈራዋል:: አባቷ ኮሳሴ ከእናቷ ጎን ቆሞ ወይ ግድግዳ ላይ እንደ ቀለም ተለስኖ፣ ዛፍ ላይ እንደ ወፍ ጎጆ አበጅቶ፣ ቦይ ውስጥ እንደ ተሰበረ ጠርሙስ ወድቆ ይሰልል ይሆናል:: አባቷ ከመናገሩ በፊት እናቷ እንዲህ የደንቧን በጩኸት ታለቃቅሳለች:: ማስጠንቀቂያ ይመስላል:: አባቷ ዘሎ መግጨት እንጂ ማስጠንቀቅ አያውቅም:: ገለታ ሰምቶ እንዳልሰማ፣ እንዳልሰማ ሰምቶ በደከመና በፈራ ድምፅ ጌርሳሞትን *ደህና እደሪ* አላትና ዞር ብሎ ቶሎ ቶሎ ወደ ቤቱ መራመድ ጀመረ:: ጌርሳሞት በሩጫ ሄደችና የግቢዋን በር በግራ እጇ አንኳኳች፣ በቀኝዋ ያልተሳመ አፏን ጠረገች፣ ያልተነካ ቁመናዋን ልክ እንደተነካ ሁሉ አስተካከለች (አሁን ሱሪዋን ምን አስዳበሳት?)::

ገለታ ለአፍታ ቆም ብሎ ሁኔታዋን ትንሽ ታዝቦ አንገቱን እንደሰበረ ከንፈሮቹን እየላሰ ወደ ደብዛዛው ጨለማ በቀስታ ሲራመድ የአስተማሪውን የጎሩይን የዕውቀት ፕሮፓጋንዳና የጌራን የከንፈር ሂሳብ እያሰበ ነበር:: እንዴት ከንፈር ፍፅምና ይኖረዋል? ፊቷ እጁ ውስጥ እያለ እናቷ ስትጠራት የደነገጠችው ድንጋጤ እሱም አባቷን የፈራው ፍርሃት በመሳም የሚያገኘው ደስታ እንዲቋረጥ መሆኑ የጌራ ከንፈር ውስጥ አስተማሪው የሰበከው አይነት ስሌት መኖሩን ጠረጠረ:: የጎደለ ነገር ያለ መሰለው:: ራሱንም አመመው:: ወደ ሁዋላ ዞር ብሎ በበረገጉ ዐይኖቹ ያየው ጌራ አባቷና እናቷ እጅ ለእጅ ተያይዘው በብርሃን ከሚንቦገቦግ በረንዳቸው ወደ ቤታቸው ሲገቡ ነው:: ልክ እንደ ሰዎቹ ከንፈሮቻቸው ብቻቸውን አይደሉም::

ገለታ ድምፁን ዝቅ አድርጎ *ደህና እደሪ* ሲላት ጌርሳሞት ብትሰማውም በሚስጢራዊ ረቂቅ የፍርሃት አደብ ታስራ አልመለሰችለትም:: ከእሷ እየሸሸ የሚሄደውን የእግሩንና መሳም ያልደረሰውን የትንፋሹን ዳና በሃዘን ትዝታ እያዳመጠች ያን አስቀያሚ ቀዝቃዛ የብረት በር አንኳኳች:: ያን ዕለት ማታ ትክክለኛ እንቅልፍ አልወሰዳትም:: በሆዷ ተንበልብላ፣ በጀርባዋ ሆና፣ ፊቷን ትራስ ውስጥ ቀብራ አስር ጊዜ አለመችው:: በሚቀጥለው ቀን ሁሉን የዘረዘረ የውሸትም ቢሆን ወሬ ቢወራ ትወድ ነበር:: በጠቢያ፣ በሚኒሊክ፣

በኢትዮፒስ፣ በአዲስ ዘመን፣ በሪፖርተር፣ በቃ በተገኘው ጋዜጣና በሁሉ ቦታ የአስራ ስድስት አመቷ ጌርሳ ወጨጫ ተራራ ስር የሆነ መንገድ ዳር በቆሊያምዋ ልጅ ተሳመች:: ደረቷም ተጎነተለ:: ፍቅራቸውን ለመግለፅ: ደደቦች ይገጥማሉ:: ደደቦች ይዘፋፈናሉ:: ፈዛዞች ይጸልያሉ:: ፈጣኑ ዘመን እንድትጎነታተል ያዝሃል:: ጎንትል:: ከዚያች ቀን በሁዋላ ግን ጠፉ:: *የት ነህ ገለታ? የት ነህ?*

በሚቀጥለው ወር ታሕሣሥ አይደል፣ የመጀመሪያው ሴሚስተር የእንግሊዘኛ ቴስትና የገለታ ነገር እግር በራስ እየሆኑ ጌርሳሞት ጭንቅላት ውስጥ እየተፈራረቁ---ከንፈሮችዋ ላይ ካለው ወጋገን ትንሽ ቀለምሲስ ጭሮ ወስዶ እንደ ሻማ አብርቶ ሲያጠናቅቅ ሊመለስ ነው?

ደሞ ሶፋዋ ላይ ተቀምጣ በፍሬንች ዊንዶው ቀዳዳ በወዲያ በኩል ቡላ ያጥርዋ ሲሚንቶ ላይ የገለታን ፎቶ በሃሳብዋ ትሰቅላለች፣ የአሳሳሙን ሲኒማ ትፈልጋለች፣ የፍርሃት ድራማ ትደግማለች፣ በዚህም ትኮራለች እንደ ትንሽ ነፍስ ሰርጓዳው ኩሬ ራቁቷን ትዋኛለች ምናምን ምናምን:: ስዕሉ ሲሰወር ትኩረትዋ ቀልጦ ከንፈሮቿን ትመጣለች፤ ልቧ ውሃ እንደሞላው ቅል የሚወድቅ ይመስላታል::

ገለታ ከሰፈር እንደ ለቀቀ፣ ከሰፈር ብቻ ሳይሆን ከአገር እንደለቀቀ ሰማች:: የማንንም ወሬ አላመነችም:: ሰላማዊትን መጠየቅ አልደፈረችም:: አንድ ሁለት ቀን የሚቆምበት ቦታ ተመላለሰች:: አላገኘችውም:: ስላላስቻላት ቤቱ ሄደች:: ገና በር እንኳኩታ ከእናቱ ከፎርቱና ጋር ዐይን ለዐይን ሲገጣጠሙ ወሬው ልክ እንደሆነ ገባት:: ገና ሲያዩአት *አይ ባፊና! አይ! አይ! አንድ ወንድ ልጄ ይጠረኛል የምለው ትቶኝ ሄደ ባፊና!* አሉና እተቀመጡበት (ተቀምጠው ነበር) ማልቀስ ጀመሩ፤ ተቀምጠው አልቀሩም ቆመው እየተንጎራደዱ ወገባቸውን ይዘው እንደ ሚች ሸኚ እዬዬአቸውን አቀለጡት:: ጌርሳሞት ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ገብቷት አፏን ይዛ ዕንባ

እየተናነቃት ትታቸው ሄደች። ቤቷ ገብታ አልጋዋ ላይ በሆዷ ተንበልብላ ባልገባት ምክንያት አለቀሰች። ሲበርድላት በጎንዋ ጋደም ብላ ወደ ውጭ እያየች ሁኔታውን ስታወጣ ስታወርድ ቆየች። የወይዘሮ ፍርቱና ለቅሶ የአይናቸው አንዴም ሳይገለጥ የሚወርዳቸው ዕንባ አባባት።[16] በዚህ አለቀሰች። እና ደሞ አለም ጠቅላላ እንደ ታቦት ማደሪያ በማያልቅ ክረምት የተዋጠ መሰላት።

---

[16] የገለታ እናት እትዬ ፍርቱና ልጃቸው ከአገር ከወጣ ጀምሮ ስራቸው በትጋት እያለቀሱ ቤተክርስቲያን መመላለስ ነው። ካላቸው ትንሽ ሃብት ቆርሰው በብብታቸው ጧፍ ወይ ዕጣን ሸክፈው በየቤተክርስቲያኑ ይሄዳሉ፡ ወደ ደቡብ አቡነ አረጋዊን፣ ወደ ሰሜን ጊዮርጊስና መድሃኒያለም፣ ወደ ምሥራቅ ገብሬል። በጣም ከማልቀሳቸው የተነሳ አይናቸው ማየት እየተሳነው ሄደ። የሚቀርቧቸውም የማይቀርቧቸውም እንዲህ ብለዋቸዋል፡ *ኧረ ፍርቱና ይሄ ለቅሶ ዐይንሽን አጠፋው። ልጅሽ ሲመለስ ዕውር ሆነሽ ልትጠብቂው ነው? ይሄኔ በምን በምን ብሎ ጣሊያን ገብቶ ይሆናል። ሳውዲማ ከሆነ ያሳልፍልሻል። አይዞሽ አይዞሽ። አልሰሙም። ቤተክርስቲያን አፀድ ገብተው ደክመው በግንባራቸው እስኪደፉ ይፀልያሉ። ዲያቆናትና እመምኔቶች እየተቆጡ ያባርሩዋቸዋል። ከተባረሩበት ይወጡና መንገድ ዳር ግንብ እየጠፉ፣ ከእኔ ቢጤ እየተጋፉ ይጸልያሉ። ወር ባልሞላ ጊዜ አይናአቸው እርጥበት ማውጣት አቆመ። ዕንባ 95 ከመቶ ውሃ ቢሆንም በውስጡ ኤሌክትሮላይቶች፣ ኤንዛይሞችና ፀረ ቫይረስና ባክቴርያ ቅመሞች ስላሉት ዐይናቸውን ሳያቋርጥ ከጀርም የሚያፀዳው ፈሳሽ ጠፋ። በዚህ ሰበብ ሁለቱም ዐይኖቻቸው መግል በመሰለ ፈሳሽ ነገር ተሰፉ። እንዲህም ሆኖ መቋሚያ ይዘው ባገኙት ቀዳዳ ብልጭልጭ ብርሃን እያዩ ደጀሰላም መሄዳቸውን ቀጠሉ።*

*እንዲህ በሆነበት ሰሞን የራሚሱን እናት ዶክተር መቅረዝን መንገድ ላይ አገኙዋቸው። ዶክተሯ የፍርቱናን ጣጣ በወሬ በወሬ ሰምተው ስለነበር ለሰላምታ አቆሙዋቸውና ምንም እንደማያውቁ ሁሉ ስለጤንነታቸው ጠየቋቸው። ፍርቱና ፀሎት አይጎዳኝም ብለው ስለሚያምኑ ደህና ነኝ እንዲሁ ዐይኔን ትንሽ ጋረደኝ እሱ ያድነኛል። የዘመኑ መድሃኒት መድሃኒት እኮ አይደለም ብለው ዋሹ።*

*ወይዘሮ መቅረዝ ፈገግ ብለው ወደ ፍርቱና ጆሮ ተጠጉና፡ ገንዘብ የማያስወጣ መድሃኒት አዝልሻለሁ። ቀላል ነው። ለመሆኑ ትያሚያለሽ? ፍርቱና በፍጥነት ቀበል አድርገው፡ እህል በልቼ እንዴት ቤተክርስቲያን ልሄድ? አሉና ለመቅረዝና ለአለም የቁጣ ጥያቄ አቀረቡ። መቅረዝ ከአፋቸው ላይ ሊወድቅ የደረቀ ነጠላቸውን እያመቻቹ፡ ውሸችን አይተሻል?*

ፎርቱና ግራ በመጋባት እም አሉ:: መቅረዝ ቀስ ብለው: ውሾች ሲቆስሉ በምላሳቸው ቁስላቸውን ይልሳሉ:: ለምን መሰለሽ? ምራቅ መድኃኒትነት አለው:: እንዲህ መጥቀሙን ያወቅሁት እኔም በቅርብ ነው:: የድሮ አዋቂዎች ለእንቺ አይነት ችግር ምራቅ ያዙ ነበር:: የምትጸም ምራቋ ወፈር ያለች ሴት መድሃኒት ናት:: የምመክርሽ በጠዋት እህል ሳትበይ ከምላስሽ ላይ ምራቅ በጣትሽ ዘገን አድርገሽ ዐይኖችሽን ተራ በተራ ቀቢ:: ትዝ ሲልሽ ሁሉ ተቀቢው:: ፎርቱና ይሄን ሰምተው ቢገረሙም በልባቸው 'ምን አይነት ዘመናዊ ዶክተር መጣብን እቴ:: ካረጁ አይበጁ' ብለው ለይስሙላ ግን: ታምር ነው ዶክተር፣ ታምር ነው አሉ:: መቅረዝ ፎርቱና እንደተጠራጠሩ ገብቷቸው: የምር ጥሩ ነው:: አይገልም:: ደም ያንቺው ምራቅ ነው:: ካልሆነ የሌላም ሰው ይሰራል:: ግን ያው አንቺ ምራቁ አለሽ በእሱ ታከሚ:: ወይዘሮ መቅረዝ የፎርቱናን እሺታም ይሁን እምቢታ ሳይሰሙ አፋቸውን በነጠላቸው እንደጋረዱ መንገዳቸውን ሲጀምሩ፣ ፎርቱና ከዳር ቆመው ሳቅ ሳቅ እያላቸው ነበር::

ያው ችግር ብዙ ያሰራልና በሚቀጥለው ቀን ብሞክረው አልጎዳም ብለው ፎርቱና ከሰው ገለል እያሉ ወይም ፀሎት ሲጨርሱ እንደሚያደርጉት መዳፋቸው ላይ ትፍ ትፍ ብለው ዐይኖቻቸውን ምራቅ ቀቡ:: በሁለተኛው ቀን ተሻላቸው:: እርግጠኛ ለመሆን ሳምንት ያህል ራሳቸውን እንዳከሙ ሽፋሽፍቶቻቸውን እያይዞ ዐይናቸውን የጨፈናቸው ቆበር ጠፉ:: በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ ሰባት ቁጥር ሰላሳ ሁለት ላይ የሆነው ተፈፀመ:: ልክ በዚህ ቀን ጠዋት ተደስተው መቋሚያቸውን እየጎተቱ (መቋሚያ ለምደዋልና) መቅረዝ ቤት ሄዱ:: ገና በር ሲያንኳኩ የከፈቱላቸው እሳቸው ነበሩ:: ገና ዐይኖቻቸው ሲገናኙ መቅረዝ የሆነው ነገር ገባቸው::

ፎርቱና ጎንበስ ብለው ምስጋናቸውንና ምርቃታቸውን አንደቀደቁት: አይ ዶክተር ያን ቀን ሲነግሩኝ አላመንኩዎትም ነበር እና ሲጨንቀኝ እንዳሉኝ ለሳምንት አደረኩት:: ድኜ ቁጭ:: እግዜር ዕድሜዎን ያርዝመው:: ጤና በጤና ይሁኑ:: ልጅዎ አቡ እግሩ ይክበደው፣ አገሩን አይልቀቅ አሉና መቋሚያቸውን ጥለው እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ሰቀሉ:: የእኔ አይድረስብዎት ብለው የመቅረዝን ጉልበት ሊስሙ በርከክ አሉ:: መቅረዝ ጎንበስ ብለው እየተቆጡ ቀና አደረጉዋቸውና: አሁን እቤት ግቢ ሃዘንሽንም በቅጡ አድርጊው ብለው ሲሏቸው ፎርቱና የሚገርምና የሚያስቅ መልስ ሰጡ: አሁንማ እንደ ልቤ እያለቀስኩ ዕንባዬን መቀባት ነው ብለው እንደ ኮረዳ ፈንጠር ፈንጠር እያሉ ሄዱ::

---

ገሊታ በወለቴ ሱቅ በኩል በዝናብና በጭቃ ወይ በጎጃም ወይ በድሬዳዋ ወይ በጎሙጎፋ ወይ በከፋ ዝናብ እየወረደበት ጎበጥ ብሎ እየሮጠ ገደል እየዘለለ ዳገት እየቧጠጠ ሲሄድ ታስባለች:: ግንጥላም ይዞ የሄደ ይመስላታል:: ስደት ልዩ የሚያምር እጣ እንደሆነ ሁሉ ያወራት ውሸት ቢያበሳጫትም በምትችልበት ስልት ፀለየችለት:: የእናቷን እግር ተከትላ ነፋሻ የሰፈሯ ደጀሰላሞች ግድግዳ ስር ተከዛ አለች፡ *የእኔ ጌታ ከነሰርጓዳህ ተመለስ::* ወደ ትምህርት ቤት ወደ ገበያ ወደ ሲኒማ ወደ የትም ስትሄድ ዛላው ሕሊናዋ ውስጥ አለ ተብታባነቱም ቀጫጫነቱም የአንዳንድ እንጉርጉሮውም ወዝ:: ወደ ጥልቁ ወደ አይቶ መነፈግ ባዶ ጉድጓድ አፍጣ፣ በአዝማሪ እዩዬ፣ በተደባሪ ዜማ፡ ከአንተ ወዲያ ሸጋ ከእኔ ወዲያ ልጅ፣ ኮኮብህ ኮከቤ ባይገጥም ነው እንጂ......

ይህቺ የፓይታጎራስ እመቤት አንገትዋን ሰበር አድርጋ የብር ሃብልዋ ደረቷ መሃል እንደ ደራጎን ዕንባ እየፈለቀ የቀሯትን ቃላቶች፡ *ስደት ይሙት::*

*(ዘሪሁን ራሚሱና ባካፉ።*  ሰፈራቸው ውስጥ በአንጀት ካንሰር ወይ በሆነ ያልታወቀ በሽታ የሞተ ሰውዬ ቀብረው የለቅሶ ቤት አግዳሚ ወንበር ላይ እንደ ስኒ ተደርድረው ተቀምጠዋል።

በሦስት አራት አመታት ውስጥ በወጣቶቹ መሃል የመራራቅ ነፋስ ገብቷል። ወሬአቸው የጋራ ይዘት ስለጎደለው ሳይሆን አይቀርም የተኮራረፉ ይመስላሉ። የድሮውን ድባብ በተረቡ መልሶ ለመፍጠር የሚሞክረው ራሚሱ ነው።  ባካፉ መኖሪያውን ወደ ሲ ኤም ሲ አካባቢ ቢለውጥም አልፎ አልፎ የሚቀርባቸውን ሰዎች ለማየት እዚህ የድሮ ሰፈሩ ታቦት ማደሪያ መጥቷል። ከዩንቨርሲቲ በተመረቀበት በአካውንቲግ ትምህርት የሆነ ባንክ ውስጥ ተቀጥሮ እየሰራ ነው። ገሊታ በሥርዐት ሳይሰናበታቸው ጥሩ ፓርቲ ሳይደግሱና ትንሽ ሳይለክሩ መሄዱ ከጓደኛ ወደ ታዛቢ ለውጦአቸዋል። ራሚሱ ስድቦች ይደረድራል፡ *ስሚ ዜድ ገሊታን ከአሜሪካህ ጋር ገደል ግባ በለው።* ራሚሱ እየደጋገመ ለእርዳታም ባይሆን ድምፅና ደጋፊ ፍለጋ ባካፉን *'አይገርምህም በእናትህ? ክሪሚናል ናት ምንድናት የምትሸልከው? እንዴት ሰው እንመን? አይመስልህም? መሰደድ ትልቅ ጉዳይ አደረከው? ደሞ ጌይ ካደረጉት እንዳትደብቀን ሃሃ።* ዘሪሁን በመሞጣሞጥ ከማንም እንደማያንስ ለማሳየት ጭንቅላቱንም እየነቀነቀ 'ቅናት እንዲህ ያደርጋል እንዴ? ወይ ሐበሻ አለ ፈገግ ብሎ። ራሚሱ መልሶ፡ 'ለመሆኑ የታለ ዶላሩና ዩሮው? ሳያቸው እናቱ እንደተደበሩ ነው። ካሹን አይልክም እንዴ? ከተሰደድክ ያው ለካሽ ነው። ሰዎች እንዴት ነው በሰው አገር የሚያነጅቡት? እህትህን ልቀምጭልልህና ደሞ ማን ሲቀና አየህ ወሬኛ' አለና እስኪንፈራፈር ሳቀ። ባከፋ ውብ ጥቁር ኮቱ እተቀመጠበት ትቶት እንደሚሄድበት ሁሉ እሱን እየሰበሰበና እየቆለፈ እንደማይሰማ ሁሉ ይሰማል። የስድብ ይሁን የመከራከርያ ቃል ከአፉ አይወጣም። በአፉ የያዘው ሳቅ ገፁ ቆዳ ስር በዝምታ ይፈሳል።  የሚመቹና የማይመቹ ተረቦች ከተለዋወጡ በኋላ ሦስቱም ለረዥም ጊዜ በዝምታ ተቀመጡ። ሦስቱም ዝምታው ለምንና

| ------------

ከየት እንደመጣ አይጠይቁም:: ከመሃል ባካፋ *ቀጠሮ አለብኝ* ብሎ በነጭ ሰሀን ላይ ከቀረበላቸው የሽንብራ ንፍሮ ዘግኖ በኮቱ ቀኝ ኪስ ከተተና ሰላም ብሎአቸው ወጣ:: የእሱን እግር ተከትሎ አምስት ደቂቃም ሳይሞላ ዘራሁን *ራሚሱን ጉዳይ አለኝ* ብሎት እተቀመጠበት ትቶት ወደ ሚሄድበት ሄደ:: ራሚሱ/አቡ ጨዋታና ፌዝ ስለሚወድ አንዳንድ ለቀስተኛ እያሳቀና እየሳቀ አለበት ቆየ::)

ጌርሳሞት አቡን ካየችው ስንት አመታት ያልፋሉ? ያ ግራኝ አውደልዳይ ትንሽ ሰርቶ ብዙ አላጋጭ:: የአንዱ ክፍለከተማ የሕዝብ ግኑኝነት ረዳትነት ስራ እንዳገኘ ሲወራ ነበር:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፊቱ ላይ ባልተጠበቀ ፍጥነት የአባቷን የሚያስንቅ ፀጉር አብቅሏል:: *የሚያውቁት ጺም አስተከልክ?* ይሉታል:: አንድ ጠዋት ተኝቶ ሲነሳ ፂም በፂም ሆኖ የተገኘ አይነት:: እንደ ዕድሜ እኩዮቹና እንደ አብሮ አደጎቹ መንዘላዘልን ያደንቃል:: መንዘላዘል ግን ቀላል ጉዳይ የሚመስለው አለ:: ሲንዘላዘሉ ነገር አለ:: መቼ ዕለት ከለቅሶ ቤት ወጥቶ ከመሰሎቹ ጋር ሲንዘላዘል በመንገድ ጌርሳን ከቤት ሰራተኛዋ ጋር ስታልፍ አያት:: አያት አያትና ጠራት:: ጠራትና እንዳዋለዳት፣ አዋልዶአትም ከተወለደች ጀምሮ እንደሚያውቃት ወይዘሪት ወይም የምትጠባውን ጡት እንደተጋራት ሞሳ ወይም አግብቶ እንደፈታት ወይዘሮ፡

—ታዲያስ ጌርሳ ምነው ስጠራሽ እንዳልሰማሽ?......ኮራሽ አንቺም! አላት

ከሁዋላው ሱቅ ተደግፈው ግሮሰሪ ግሮሰሪ የሚሸቱት አዲስ ጓደኞቹ በሳቅ ፈረሱ:: አቡ ደስ የሚል ደረት አለው በጠባብ ካናቴራ ታቅፎ የተያዘ:: በአንገቱ ሃብል ይጫወታል:: ስቅለ ወርቋ የምትከፊት የምትከደን ያበጠ የልብ ቅርፅ አላት:: ሲያዩአት እቃ የታጨቀባት ትመስላለች:: ቢከፍቷት ግን ውስጧ ጥቁር አረንጓዴ፣ ቀይና ነጭ ዝገት ነው::

---

'ታዲያስ ጌርሳ' ጌርሳ ማለት ደሞ አይ አም ቤተር ዛን እነዛ ማለት ነው። እነዛ ትተውት የሚሄዱ አዲስ ወዳጆቹ። አቀራረብ የላቸው ጢም የላቸው። የማታውቃቸው፣ ገለታ ያልሆኑ ድምፃቸው ለዘፈን ያልመጠነ፣ ደሞ ዘሪሁንን ያልሆኑ ኢስልካኮች፣ በካፋ ያልሆኑ ግርማ ሞገስ ያልነካቸው፣ ቆዳቸው በጫትና በቅባኑግ የዘይት ወጥ በተፈተፈተ እርካሽ እንጀራ ያብረቀረቀ ቅጠልያ። የክሎሮፊል ምርኮች። የፎቶሲንቴሲስ ባሪያዎች። አገራቸው ቁርጥ የለም?

---አውቅሃለሁ?

---የሰፈሬ ልጅ ነሽ

---አላውቅህም

---በቲቪ ምናምን ብቻ ነው የምታየው። የምር ቀልዳችንን እናቁምና ለምን ኔክስት ዊክ አትመጪም ብሎክ ፓርቲ አለን የሰፈር ልጆች። ዳንስ አለ። በኮካ አድርጎ በሳንጆርጅ በኩል እስከ ቮድካ ድረስ መጠጥ አለ። መዝናናት ነው።

አዲስአባ ለመሆኑ ብሎክ አላት እንዴ? ይቦልከውና። አዲስአባ ቀበሌ ነው ያላት። የዛም ፓርቲ ስም ቢባል 'መቀለብ' ወይ 'መቆለብ' ወይ 'ቁለባ' ነው። ልጆቹም ቆላቢ። ቅልብልብ ሁሉ። አቡነ አረጋዊህን ትተህ ወደ ቁልቢህ ተቅለብለብ።

---ፓርቲው ለምን አስፈለገ?

---በድብርት አለቅና። ደሞ እህቶቻችንን ለማዝናናትና ዓለም የተለያየ ገፅ እንዳላት ለማሳየት።

---እስከ ዛሬ አላየህም ገጽዋን? አሹፍ። ለመሆኑ ከባካፋ ጋር አትገናኙም? ዘሪሁንን ካየሁትስንት ጊዜዬ። እዛ ቦታ ጠፋችሁ።

---አሁን እዚህ ለቅሶ ላይ ነበሩ። ሰማሁ ኢ ኤስ ኤል ሲ በጠስሽ አሉ። ግራጁዌሽን ፓርቲሽን እዛው ብሎክ ፓርቲው ላይ ማድረግ ትቺያለሽ። ልጅነታችንን ስንዳረቅባት ባይ ባይ ልንላት እኮ ነው። ለመሆኑ የት መቀጠል አሰበሻል?

---አዳማ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለማጥናት። አንተ ስትመረቅ ደግሰሃል? ደሞ ሌላ የሚያሳስብ ቁም ነገር ጠፋ?

---ምን መሆንሽ ነው? ከመዋደድ የበለጠ ቁም ነገር አለ? ቢቃ ፓርቲያችን ላይ መጥተሽ ስለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አንጀባ አድርጊ። አንድ ቀን አሸባሪ ነህ ተብዬ ቂሊንጦ ከመጫኔ በፊት

እህቶቼና ወንድሞቼ ሲደሰቱ ማየት እፈልጋለሁ:: ገለታ ለመሆኑ ይጽፍልሻል?

--ገለታ? ለምን ይፅፋል?

—እንዴ ምነው? ሽርክና እንደ ነበራችሁ ሰፈሩ ብቻ ሳይሆን ቢቢሲ የሚያውቀው ነገር ነው

—ምነው የሌለ ነገር አወራህ? ከሰናይት ልታጣላኝ ነው? ሰው ሰላም ለማለት ደሞ ማንም አይከለክለኝም:: ቢሆን እንኳን ስንት ዘመን አልፏል ማለቴ ነው፣ በሌለ ሰው ባልታማ ደስ ይለኛል::

—ሃ ሀ ሃ ለማንኛውም ለምን አትመጪም የምር?

—ከተመቸኝ እመጣለሁ

—ነይ በእናትሽ:: እንደዋወል:: ለማንኛውም ስልኬን ውሰጂ የአንቺንም ስጪኝ::

ሲያወራ ልበሙሉነቱና የራሱን ቅጥፈት እንደዘመኑ ፖለቲከኛ እስከ ሞት ድረስ ማመኑ:: እና አራድኛ ልምምጡ ማረካት:: ተረብ፣ ማራኪ ልምምጥና ገለታ አብረው ቢገናኙ ኖሮ......እንዱ ቆንጆ አንዱ ተለማማጭ:: ሁሉ ጎረምሳ ባለው:: ያለውን ከወረወረ ሁሉም አማላይ ነው አለች የሰራት::

ከሳምንት በኋላ ለራሚሱ ቤቱ ደወለችለት:: ተኝቶአል ተባለች:: አንድ ሰአት ቆይታ ደግማ ደወለች:: በእናት ትሁን በእህት ትሁን በአክስት 'እየታጠበ ነው ገላውን' ተባለች:: የመባ'ል መአት:: የማለት አይነት:: አልጋዋ ላይ በጀርባዋ ተኝታ ልብሱን ሲያወልቅ ማሰብ ጀመረች:: ከየት ይጀምራል? ዕውቀትዋ የአፍ ልምምጡ ብቻ ነው:: የጣቶቹ ንቅናቄ ነው:: ዕውቀትዋ የከባድ ከንፈሮቹ መርገብገብና የጎረምሳ ውሽቱ ነው:: ዕውቀትዋ ደጋግሞ ቢያምርም ባያምርም ስለ ፓርቲ ያወራው ጥዝጠዛው ነው:: ከአንድ ሰአት በኋላ ራሚሱ ደወለ:: ራሚሱ ያላትና ስሙን አሳጥራ እንድትጠራው ያግባባት እንዲህ ነው:

—ታዲያስ ጌርሳ ሁልጊዜ አስብሻለሁ

ጌርሳ ደስ እያላት ግን በዛባት:: መስመር የሳተ ሃይለኛ ቬሎሲቲ ውስጥ ያለው ቀጣፊ አፉ፣ ወዛም ተምር ያደርቃል::

—ፓርቲው ቦታ ከመሄዳችን በፊት ቡና ልጋብዝሽ::

---

ሶሲ ካፌ ቡና ሊጠጡ ተቀጣጠሩ። አዲስአባ ውስጥ ግድያትና ብርቱካን ጎን ለጎን በሽርክና መኖር ከጀመሩ ስንት ጊዜአቸው። በመስኮት ቀዳዳ የምታየው ማታ። እየተቁነጠነጠች እየሳቀች በስልክ ስታወራ እናቷ መግደላዊት ከጀርባዋ ትንሽ ፈቀቅ ብላ ቆማ ትሰማታለች። እናቷ ብትሰማ ግድ የላትም ነበር። ከዛች ደቂቃ ጀምሮ ግን ግድ አላት።

--አንቺ አምጪ ያን ሞባይል። አምጪአት! አለቻት

--ምነው?

--ከማን ጋር ነው የምታወሪው? እ? ከዛች ልጋጋም ልጅ ጋር ነው አደለ? ሰው ጠፋ?

--ራሚሱ ነው እኮ

--ማን ይሁን ምን ይሁን ምኑም ከማይታወቅ ዱርዬ ጢ˙ገም ጋር......

--አብረን እዚህ ሰፈር ያደግን ነን። ደሞ ጢም ምን አ˙መጣው እዚህ?

--አምጪአት!

አላስጨረሰቻትም። ከእጅዋ ላይ ሞባይሏን ነጠቀቻትና ሶፋ ላይ ዘጭ ብላ ተቀመጠች። ጌርሳሞት ልትነጥቃት ስትመጣ ልትመታት እጅዋን አነሳች። ጌርሳሞት በብስጭት ከቤት ወጣች። በረንዳ ላይ ሆና እናቷ ሞባይሉን ስትጠቀጥቅ ታያታለች።

--ምን እያደረግሽ ነው?

--ምምም ን አገባሽ? አንቀለቀላት ልጅቷ። እንዲህ እንዲህ አደረገሽ......ሞባይል ያልያዘችበት እጇን ሰቅላ እንደ ባይ ባይ አወዛወዘች። የነካካችውን ነካክታ እናት በቢሮዋ የታወቀች ስልጡን የኮምፒዩተር ተያቢ ናትና:

--ነይ ስልክሽን ውሰጂ

ጌርሳሞት እየፈራች ሄዳ ከእናቷ እጅ ስልኩን ተቀበለች

--የትም አትሄጂ.የትም!።[17]

---

17 ኮላሴ *ደስ ባር* ሲጠጣ ቆይቶ ለማምሸት ስላሰበ የለበሰውን የስራ ቱታ በታጠበ ካቦርታ ለመለወጥ ወደ ቤት መጥቶ ግቢው ውስጥ እየገባ እያለ መግደላዊትና ጌርሳሞት ሲጨቃጨቁ ያላበው ጭንቅላቱን እያከከ አዳመጠ። ሚስቱ ስምቶት በማያውቀው ቁጡ ቅላፄ ልጇን 'የትም አትሄጂ.የትም!' ስትል ሰማት። ቤት ሳይገባ በብስጭት በቀጥታ ራሚሱ

የራሚሱ ስልክ ተሰርዟል፡፡ ራሚሱ ብቻ ሳይሆን ዘሪሁንና አባድር ተሰርዘዋል፡፡ የሴት ጓደኞቿ አልተነኩም፡፡ ለሞባይልዋ ፓስ ወርድ ማበጀት እንዳለባት ገባት፡፡ የአባድርን ቁጥር በቃልዋ ታውቀዋለች፡፡ ያልገባት በስድስት ወር አንዴ ቤተክርስቲያን የምትሄደው እናት ዛሬ ምን እንዲህ እንደ ቄስ እንዳበሰጫጫት ነው፡፡ *ራሚሱ የሚስጢር ወንድሟ ይሆን እንዴ?*

---

ቤት ሄደ፡፡ እንደደረሰ የአጥር በር በቡጢ አንኳኳ፡፡ ትንሽ ጠብቆ ተከፈተለት፡፡ ግቢው እንደዚህ ሰፊ አይመስለውም ነበር፡፡ በግቢው ስፋት ደንግጦ ፈዞ እንደቆመ አንዲት ልጅ እግር ሴት *ምን ነበር የፈለጉት ጋሼ?* አለችው፡፡ *ሳይመልስላት* ከላይ እስከታች እንደ እንግዳ ፍጡር ገላመጣት፡፡ አስተያየቱ ደስ አላላትም፡፡ *ራሚሱ የሚኖረው እዚህ ነው፡፡ አይደለም?* አለ፡፡ ትዕዛዝ ይመስላል፡፡ ልጅቷ ሁኔታውን አይታ፡ *ምነው?* አለችው፡፡ *እዚህ ነው አይደለ?* አለ ቆጣ ብሎ፡፡ *እንዴ? ንገሩኝ ለምን ፈለጉት?* አለች ኮስተር ብላ ልጅቷ፡፡ *አውቃለሁ እዚህ እንደሚኖር* አለ፡፡ *እንደዛ የሚባል ሰው እዚህ የለም* አለችና ልጅቷ በሩን ልትዘጋው ስችል በእርግጫ መትቶ ከፈተውና አልፏት ገባ፡፡ የራሚሱን ነገር እንደረሳ ሁሉ ግቢውን እየተገላመጠ አጠና፡፡ ከሰከንዶች በኋላ *ጥሪልኝ!* አለ እንደ ትዕዛዝ፡፡ *የለም* አለች ልጅቷ እንዳመረረ ገብቷት፡፡ *እንዳለ አውቃለሁ ሰፈሬ እኮ ነው* ብሎ ወደ ዋናው ቤት ጉዞ ጀመረና መለስ ብሎ *ልጆ አጠገብ ብትደርስ ለዘላለም እንድታነክስ አደርግሃለሁ በዪው፡፡ መልዕክቱን ማድረስ ያንቺ ሃላፊነት ነው፡፡ አልምረውም* አለ በቁጣ፡፡ ልጅቷ ደንግጣ ማልቀስ እየዳዳት፡ *ምን አደረጋት?* አለች፡፡ አመልካች ጣቱን ወደ ዋናው ቤት ቀስሮ እያወዛወዘ፡ *ደስ የማይለኝን አድርገህ በሰላም አትኖርም፡፡ እዚሁ አሪትህ መሃል ነው የማጋድምህ በይው* አለና እየተንጎራደደ ወደ ውጭ ወጣ፡፡ ልጅቷ በግራ መጋባት አፏን ከፍታ ቆማ፣ በሩን መዝጋት ረስታ ኮላሴን ከዐይኖቿ እስኪሰወር ከጀርባው ስታየው ቆየች........

---

*(ዘሪሁን ባካፋ።* ሐሙስ ሰለት (ሐሙስ የቀን ቅዱስ) ዘሪሁን የነርስነት ኮርሱን ተምሮ ስለጨረሰ በየቦታው ማመልከቻ አስገብቶ (እሱ እንደሚለው *ሺ ቦታ)* ተዳክሞ በእግሩ ወደ ቤቱ እየሄደ ነው። ከንፈሮቹ ደርቀዋል። ከንፈሮቹ ቢደርቁም እነሱን በምላሱ እያራሰ ያጯጯል። አንድ ቦታ ሻይ እየጠጣ ትንሽ ለማረፍ ፈልጓል። ግን እርቦታል። መብላት የሚፈልገው ሊጠቁር ትንሽ የቀረው ትኩስ ቀይ የሽሮ ወጥ ነው። ያ አይነት ወጥ ደሞ የሚያገኘው ቤቱ ነው። ቤቱ ለመሄድ ታክሲ መውሰድ ቢኖርበትም የተሳፋሪ ግፊያ አስጠልቶታል። እና በእግሩ መንገድ ጀምሯል። የጃኬቱ ደረት ኪስ በፎቶ ኮፒ አራብቶ ሳያስራጫቸው በተረፉ የሲቪ ወረቀቶች አብጧል። ሁለቱንም እጆቹን ሱሪ ኪሱ ሲጨምር ሥራ ፈላጊ ሳይሆን ዝይን ሆነ። ፈረንሳዮች ፍላነር[11] የሚሉት አይነት። በክፍለከተማው ሃላፊ ቢቀጠርና በወረዳው ጎዳናዎች ቢመላለስ ገላውና አለባበሱ ስለአገሪቱ ጎረምሶች ቢያንስ የትንሽ ዘመን ሕልም ይናገራል። ቆጨቱ ወፈር ያለ ቅጥ ያዘ፡ ወንዳወንድ ባሱ፡ ከነዛ ስስ ከንፈሮች የወጣ አይመስልም። ውፍረቱ በትክክል እንደ እንደ አሰሳ ዙምባራ ነው። ከነዛ ሚጢጢ ከንፈሮች የሚወጣው ድምፅ 1000 ጆሮ-ዶላር ያወጣል። ግን ቆጨት እንደ አድማጩ ነው። ጆሮ አኞ እንጂ ልቡና አይደለም፡ *በአንድ ትንሽ ሰፈር አንድ ልጅ ነበረ ከጠዋት እስኪመሽ ስራ ያባረረ፣ ጥሩ ዘመድ የለው ጥሩ አልተማረ......*ለብቻው እንደሚነፋ ያውቃል። ከመሃል አፉ በምራቁ ብቻ መርጠብ እንደማይችል ተረድቶ ከሱቅ ውሃ ገዝቶ እየጠጣ አለፍ እንዳለ አንድ መኪና አጠገቡ መጥቶ ቆመ። ዞር ብሎ ሲያይ መስኮት ተከፈተና አምሮ የተላጨ ክብ የባካፋ ቀይ ፊት ብቅ አለና፡

'የፈረደበት እግረኛ እናደርስሃለን' አለ።

'አ ባካፋ! አ ባካፋ! ሲያሰኝኝ ነበር ሲያሰኝኝ ነበር ታውቃለህ'

'ቤትህ በር ባናደርስህም እስከ ሰፈር እንወስድሃለን' ዘሪሁን ከመኪናው ጀርባ ገባና ከባካፋ ጋር ተቃቅፈው ተጨባበጡ።

---

'በጣም እንጂ:: ታክሲ ጥበቃው አቦ ይገልሃል:: የወያላ ብብት አማሮኛል:: ብብታቸውን አፍንጫህ ጋ ያመጡና ስትነጫነጭ ምነው ኮራህ? ይሉሃል ሃሃሃ'

ባካፋ ጋቢና ከተቀመጠ ኢሳያስ ከተባለ ልጅ ጋር አስተዋወቀው::

'መኪና ገዛህ እንዴ?' አለ ዘሪሁን የመኪናዋን ጣራና ዳሽ ቦርድ ምናምን እያየ::

ባካፋ ፈገግ ብሎ:

'ሁለት ቀን ሆነኝ ከገዛኋት' አለ::

'አይ ባካፋ አይ ባካፋ ዘነጥክ:: ታዲያ አትነዳውም እንዴ?'

ጋቢና ያሉ ሁለት ሰዎች ገልመጥ ብለው አዩት:: ዘሪሁን ያለውን ሳይደግም:

'ታዲያስ ደህና ነህ ግን ወይ ባካፋ!......' እያለ ጨዋታውን ቀጠለ:: አንድ ሁለት ደቂቃ ከነዱ በኋላ

'እዚህ ክሊኦ መልታይ ሚዲያ ጉዳይ አለኝ:: እሱ ወንድሜ ኢሳያስ የሲኒማ ዳይሬክተር ነው:: ፕሮጄክት አለው እዛ'

'ኧረ ባክህ ምን ሲኒማ ሰርተሃል?' አለ ዘሪሁን ወደ ጋቢና ጎንበስ ብሎ

'አጉል ፍቅር የሚባል' አለው ባካፋ ልጁ ከመመለሱ በፊት::

'አንተ ነህ እሱን የሰራኸው?' አለ በመገረም ቅላፄ

ልጁ ዞር ብሎ ፈገግ አለ::

'በጣም አክባሪህ ነኝ' አለ እጁን ዘርግቶ:: ልጁ ዞር ብሎ በፈገግታ ጨበጠው:: ገና እንደተጨባበጡ መኪናዋ ወደ ዘሪሁን ቤት አቅጣጫ የሚወስደው መገንጠያ መንገድ ጋ ቆመች:: ዘሪሁን ከመኪናው ሊወጣ ሲል ባካፋ ጃኬቱን ይዞ አስቀረው::

'አንድ ነገር ትዝ አለኝ:: ስሚ ኢሳያስ ስለአንድ ልጅ አላወራሁህም? በጣም በሚገርም መልክ የሚያጭጭ፣ እሱ ነው' አለው:: ኢሳያስ ዘሪሁንንና ባካፋን እያቀያየረ አይቶ:

'የምር?'

---

ዘሪሁን ሁለቱን አቀያይሮ አየና ምነው? አይነት በገፁ ቅጥ ጥያቄ አቀረበ።

'ምን መሰለህ ኢሳያስ ለፊልም ሳውንድ ትራክ ሲሰራ ዘፈንና ክላሲካል ሙዚቃ ሰለቸኝ ምናምን አለ። እና በፉጨት ለማድረግ አስቦ ነበር። ጥሩ የሚያፏጭ እየፈለገ ነበር' ከመሃል ኢሳያስ ባካፋን አቋረጠና ፡ 'ያፏጫሉ ግን አይመቹም። ሜሎዲ እንዳለ አይገለብጡም፡' አለ ፀጉሩን እያከከ።

'ለምን አንድ ቀን ብቅ አትልም? አለ አደለ እንዴው' ከተቀመጠበት ወደ ግራ ገልበጥ ብሎ ከሁዋላ ኪሱ ጠፍጣፋ ጥቁር የቆዳ ቦርሳ አወጣና እሱን በርብሮ ለዘሪሁን ነጭ የካምፓኒውን ካርድ ሰጠው።

'ፊልም ልንሰራ እንሄዳለን፣ የመጀመሪያ ሹት መተከል ነው። ከዛ ባህር ዳር ከዛ አዲስአባ አራት ኪሎ። መጨረሻችን እዚህ ወለቴ ሱቅ ነው። ጊዜ አይወስድም እንመጣለን። ስንመለስ......አለ አደለ......ደውልልኝና ብቅ በል'

ዘሪሁን ካርዱ ላይ ያለውን እያነበበ ወይም እዛ ላይ ዐይኖቹ እየተንከራተቱ ምን መመለስ እንዳለበት የሚያስብ ወይም የሚያስበው የጠፋው አይነት ሆነና፡

'እሺ እሺ' ብሎ ባካፋን አየው

'አየሽ አጋጣሚ' አለ እየሳቀ ባካፋ

'ጥሩ እደውላለሁ። ጋይስ አመሰግናለሁ' ዘሪሁን ከመኪናዋ ወጣና ባካፋን እንደዘነጋው ሁሉ ኢሳያስ ለተባለው የፊልም ዳይሬክተር እጁን አወዛወዘ።

በቀስታ እየተራመደ ሲጓዝ *ኮምቤ ፌቨን አበባ ሱቅ*፣ አደይ መስላ ወንበር ላይ የተቀመጠች ሻይ የምትጠጣ ልጅ አየ። ፌቨንን ሰላም በማለት አሳቦ ሊለክፋት ወደ ሱቁ ሲጠጋ ጌርሳሞት መሆኗን ተረዳ። ድንጋጤ ገፁ ላይ ብቅ ብሎ ጠፋ። በአጭር የተቆረጠውን ፀጉሩን በእጆቹ መዳፍ አመቻቸ። ከላይ የተንዘላዘለ ቲሸርቱን ቀበቶው ስር አስገባ። ወገቡ እህል የበላ አይመስልም (ምሳውን ስላልበላ አይደለም) በፀጥታ እየተራመደ ሄደና ጌርሳሞት የተቀመጠችበት

| -------------

ወንበር ጎን እሷ ሳታየው ቀስ ብሎ ተቀመጠ። ዞር ስትል አየችውና ደነገጠች። በደመነፍስ ትከሻው ላይ በጥፊ መታችውና 'ያስደንግጥህ እቴ' አለችው)

(ምላሳችንን እናበረታለን፣ ከንፈራችን የእኛ ነው። ጌታችን ማነው?: *መጽሐፈ ምሳሌ 12፡4*)

ሐሙስ ዕለት (ሐሙስ የቀን እርኩስ) ጌርሳሞት ከቤትዋ ስትወጣ ከአባትዋ ጋ ደጃፍ ላይ ይገጣጠማሉ። አባትዋ ምን ይላታል? ወደ ለበሰችው ቀሚስ በጢማም ወፍራም አመልካች ጣቱ እያመለከተ *በይ አሁኑኑ ተመለሽና ለውጪያት!!* በዝምታ፣ በትዝብትና በብስጭት ቆማ ስታየው ባሕር በሚያደርቅ ትኩሳታም ድምፅ *ምን ቆመሽ ታዩኛለሽ?! ቶሎ ብለሽ ለውጪያት! አምሮብኛል መስሎሻል! ከማንም ባለጌ......* የጀመረውን ሳይጨርስ እየተቆናጠረች ወደ ቤት ውስጥ ገባችና አሮጌ መጋረጃ የመሰለ ቀሚስ ለብሳ ተመልሳ ወጣች። ኮላሴ ቆሞ ይጠብቃት ነበር። *ምን?! ምን?! ስሜን በክፉ ለማስጠራት ነው እንዲህ ደመወዝዋ ያልተከፈላት ገረድ መስለሽ የምትወጭው? የነጋድራስ ማነው ሚስት ለብሰው የተቀበሩበት ቀሚስ ከመቃብር ቢወጣ እንዲህ አያስጠላም። በይ ግቢ......*የተናገረውን ሳይጨርስ ትታው ሄደች ('በስተርጅና አላርፍ ብዬ ወልጄ አደረቀችኝ' ይላል ሁልጊዜ። *ውለዳት ብሎ ያስገደደህ አለ?*)

*መሻታ* ቤትዋ ገብታ ወዲያ ወዲህ እያለች የሚያናድዷት ጥቂት ጉዳዮችን በሰልፍ አሰበች። ባትደሰትም አባትዋ የሚወደውን ዓይነት ልብስ ለብሳ ወጣች። በግራ ጎንዋ ትልቅ ቦርሳ ይዛለች።

--እናትሽ የለችም? አለ ውስጥ ገብቶ ፈላልጎ ካገኛትና የአለባበሷን ትክክለኛነት ካረጋገጠ በሁዋላ

እንዳልሰማች ሁሉ መልስ ሳትሰጥ (*አትነዝንዘኝ*) የአጥሩን በር ዘልቃ ወጣች። በቀጥታ ጓደኛዋ ፌቨን የምትሰራበት ቦታ ሄደች። ፌቨን ገና ስታያት፡

---

--ምነው ጌርሲ? ላሟ የጠፋችባት የገበሬ ሚስት መሰልሽ:: መልበስሽ ነው? አለቻት

--ይልቁን የጀርባ ክፍል ክፈችልኝ አለች ጌርሳሞት ቆጣ ብላ

--ክፍት ነው

ጌርሳሞት ወደ ጉዋዳ ገብታ በአባቷ የተፈቀደላትን ቀሚስ ያጋጠማት የካርቶን ሳጥን ውስጥ ከተተችው:: እንደ ኑግ ልጥልጥ የሚፈልቅ የተከለከለችውን ጥቁር አጭር ቀሚስ ከቦርሳዋ አውጥታ ለበሰች:: በረንዳ ላይ አንድ የብረት ወንበር ስባ ቀጫጫ ቀይ ዳማ እግሮቿን ዘርግታና አነባብራ ዘና ብላ ተቀመጠች:: የምታስደነግጥ አይነት አምሮባታል:: በልስላሴው እንደተማረከች ሁሉ ቀሚሷን አልፎ አልፎ ትዳብሰዋለች:: ፀጉሯ ውስጥ ከግራ በኩል ደርቆ መዘለስ የጀመረ የከሰል ፍም የመሰለ አበባ አለ:: ከቦርሳዋ ውስጥ ቀለምና መስታወት አውጥታ ከንፈሯን ቀባች:: አለባበሷ ፈጣጣ ቢሆንም ዐይነአፋርነቷ ገና ትቷት እንዳልሄደ አንገቷ ድረስ አፍኖ የያዛት ቢጫ ሹራብ ያቃጥርባታል:: አበባ ገዢ ደንበኞች ሲመጡ ደሞ ዐይኖቿን ዞር ታደርጋለች:: አንዳንዴ መሬት መሬት የምታይ መስላ በስላች ታያቸዋለች:: ከሴት ጋ አበባ ሊገዛ የመጣ ወንድ ሲያተኩርባት፣ እዛው ደፍራ ባታየው እንኳን አበባውን ገዝቶ ሲወጣ አረማመዱን፣ አለባበሱን ወይም ያጋጠማትን የፊቱን ክፍል ከጀርባ ታየዋለች፡ አፍም ቢሆን በቂ ነው::

ነፋስ በቀስታ ይነፍስባታል:: በጭኖቿ መሃል ሲሳብ በጠባብ ሙታንታዋ ላይ በለስላሳ መዳፉ ሲድህ፣ የማታውቀው ነገር ያብሰለስላታል:: አይኖቿን ከድና ለአፍታ አብርዷት ከመሄድ ይልቅ እዛው እንዲከርም፣ ሚዛኑም እንዲከብድ ትመኛለች (ይሄንን ለወዳጇ ለፌቨን እንኳን አትነግራትም):: ቦርሳዋን ከፍታ የጥፍር ቀለም አወጣች:: ብርቱካንማ ቀለም ነው:: ጣቶቿ ወፍራም ይመስሏታል:: ጥፍሮቿ የዋንጫ ቅርፅ አላቸው፣ ስፊ በመሆናቸው ቀለሟን ጨረሱባት እንጂ ለእሷ አምረው የታዩአት ጊዜ የለም:: ብልቃጡን ነቀነቀችና አገላብጣ አየችው:: በእንግሊዘኛ ካፒታል ሆሄያት የተጻፈ ሜድ ኢን

| ------------

ቻይና የሚለውን አነበበችና በንቀት አፏን ጠመም አደረገች[18]:: የቀረው ደቃቃ ጽሑፍ አይታይትም:: *በአማርኛ አይፅፉትም?* ብልቃጡን በጥንቃቄ ከፈተችና በሆዱ በሸሸገው በራሱ ብሩሽ ጥፍሮቿን በቀስታ መቀባት ጀመረች:

--ፌቪ በእናትሽ ኬክ እንብላ

--አልሰራሁም ዛሬ፣ ካሽ የለም

--ቆንጆና በቃ እገዛለሁ ሻይ አፍዪ

--ልደውላ

--ምን ትጠብቂያለሽ?

ፌቨን ሞባይሏን አንስታ ጎረቤት ኬክ ቤት ደወለች

--ትራሚሱ በያቸው

---

[18] ጌርሳሞት ማንበብ አትወድም፣ ምክንያቱም እሷ እንደምትለው *'ምር'* *የሂሳብ ሰው ናት::* አባባሏ የሆነ እውነትነት አለው:: ችግሩ ግን ለምን ጨርሳ ሳታነብ የማይታማ ታማለች? አንብባ ሳትረዳ ስለምን ትነዛነዛለች? ስለምንስ ትንቃለች? በትክክል እስከመጨረሻው የታተመውን ሁሉ ብታነብ ሜድ ኢን ቻይና ከሚለው ስር: Manufacured in shensi province, changqing Township. Dongling. All natural. 2001. ይሄን ይላል:: ከዛ ቀጥላ ሼንሲ የተባለው ቦታ የት አካባቢ ነው? የሼንሲ ፋብሪካዎች ምን ይመስላሉ? የሰራተኞች መብት ይጠበቃል? ለመሆኑ ሊፒስቲኩ ሲሰራ ምን ያህል ጥንቃቄ ይደረጋል? ኦል ናቹራል ማለት ምን ማለት ነው? ኦል ናቹራል (ሁሉም ከተፈጥሮ የተገኘ) ብለው ብልቃጡ ላይ ስለጻፉ እውስጡ ያለው ሊፒስቲክ ኦል ናቹራል ነው? ሊፕስቲክ ተብሎ የገዛሁት ነገር የምር ሊፒስቲክ ነው? የተባሉ ጥያቄዎች ከተጠየቁ በኋላ ሃሜት ዕውቀት ተደግፎ ይሰነዘራል:: እንዲህ ማለት ወይም በፀጥታ አፍን ሸርመም ማድረግ ደግ አይደለም:: አለበለዛ ከባዶ ተነስቶ 'ቻይና ወረረችን' 'ቻይኖች ኦሪጂናል ያልሆነ እቃ እያመጡ ገደሉን' 'አሁን ይሄ እቃ እኮ አይደለም የቻይና ነው' አይባልም:: አለበለዚያ ገልባ እየሰጠች ተደፈርኩ፣ ፊቷን እያቀያየረች ሰጥታ በጥፊ ተጠፈጠፍኩ እያለች የምትዘባርቀውን እንከፍ ወይዘሮ መሆን ነው:: በትክክል የአእምሮ ዘገምተኛነት ነው:: ጥቅስ: 'የቻይና እቃ ሁልጊዜ ወደ እኛ የሚመጣበት ዋናው ምክንያት ቢስማማንም ባይስማማንም ስለፈለግነው ነው::' (መቅረዝ አዘማች 2003 አም)

---

ጌርሳሞት ገንዘብ ለማውጣት ቦርሳዋን ስትከፍት ያለፈው ወር አካባቢ የገዛችውን ቅጠሎቹ በቢጎዲ የተሰሩ የመሰለ መጽሐፍ አገኘች:: ሳታወጣው እዛው እተሰነቀረበት ገላለጠችውና ገጽ ሃያ አምስት ላይ እንደቆመች አየች:: የገጹ እልባት የማስቲካ ወረቀት ነው:: ትዝ ብሎአት ማስቲካ ለማግኘት የቦርሳዋን ጉያ አመሰችና የላይ ሽፋንዋ የወለቀ ብርማ የውስጥ ልብሷ በከፊል ተገፎ ቤቿ ስጋዋ የተጋለጠ ባለ ሙዝ ቃና ማስቲካ አወጣች::

--ማስቲካ ትፈልጊያለሽ?

ልባሷን አስፍታ ገልጣ ከላይዋ የተጣበቁ ደቃቃ ነገሮችን በጥንቃቄ አራግፋ በቸልታ ማስቲካዋን አፏ ከተተች::

--ተይ በእናትሽ እንደ ብርድልብስ እያራገፍሽ ትበያለሽ እንዴ?

--ማስቲካ እኮ ነው

--ቢሆንስ

--ሂሂ

ማራኪ በሆነ ሳቅ ጌርሳሞት የአበባዋን ሱቅ ሞላቻት:: ትንሽ ደስ ሲላት መሳቅ ብቻ ሳይሆን መዝፈን ያምራታል:: ግን ጌርሳሞት መዝፈን ቀርቶ ደህና አድርጋ ማንጎራጎር አትችልም:: ባትችልም በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ፣ እእእእእ እና እህእህእህ ብቻ ባለበት፣ የሕመም ምጥ እንጂ ዜማ በማይመስል የሁለት ሆሄ የድምፅ ንዝረት እየታጀበች ጥፍሯን ቀለም እየቀባች ሩብ ሰአት ያህል ቆየች::

በሩብ ሰአት ኬኩ መጥቶ ሻይም ተፈልቶ ከኬኩ ግማሹን እንደበላች፣ ከሻይውም እንደጠጣች የሰፈርዋ ልጅ ዘሪሁን ቀዛዛ፣ ጥቂት ብጉሮች የፈነዱበት ግን በውበቱ እንከን የማይወጣው ፊቱን እየገፋ መጣና ሳታየው ከጎኗ ተቀመጠ:: ዞር ስትል......

--ያስደንግጥህ እቴ! አስደነገጥከኝ......ምነው በእናትህ ሰላምታ ብለህ ብትቀመጥ?

--ሃሃሃሂሂ ዛሬ ዘንጠሻል አለ በረዶ ጥርሶቹን እያሳያት:: ዛሬ የበቀሉ ይመስላሉ::

--ተወኝ በእናትህ፣ ደብሮኛል

--በክረምት ሚኒስከርት ትለብሺያለሽ?

| -------------

--አባቴ ቢሰማህ ይመርቅሃል አለች ሳቅ ብላ፡፡ ልብ ሳትል በማፈር ቀሚሷን ወደ ጉልበቷ ሳበች፡፡ የሚሳብ ትርፍ የለውም፡፡ እሱም ገብቷት ዝቅ ብላ ወደ በረንዳው ወለል አየች፡፡ ከስር የለበሰችው የናይሎን ውስጥ ሱሪ ላይ ልብ ያላለችው ቀዳዳ ይኖራል፡፡ እነ ቻርሊ ቻን፣ እነ ቹንግ ቺና እነ ዋንግ ዩ እንትና እንድትወድቅባት ብለው በሴራ ያበጁት፡፡ ምን ይታወቃል? አለ አደለ ማታ ልብስዋን ስታወልቅ የለችም፡፡ ቤጂንግ ቹ ኤን ላይ ጎዳና ላይ ናት፡፡ ወይም ጃኪ ቻን አልጋ ላይ ፓንዳ ስታይል ስታደርግ፡፡ ወይ አቡዳቢ የሆነ የሱቅ ደረት ላይ 'ሐበሻ' የሚል የማስታወቂያ ፖስተር ስር ከኮፊ አረቢካና ከቢላል ስም ጋር ተንጠልጥላለች፡፡ ምን ይታወቃል?

ቀና ብላ ዘሪሁንን አየችው፡፡ የአናቱ ቁጥርጥር የዘመኑን ኮበሌ ዘፋኝ አስመስሎታል፡፡ ትንሽ ቢያጣጥቡት ወደ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ልጅ ይለወጣል፡፡ በአውሮፕላን ማረፊያና በታቦት ማደሪያ መሃል ላይ ያለው *ሉሉ ናይት ክለብ* ነው፡፡ እንደ ኬላ፡፡ ልዩነቱ እሱ ነው፡፡ ሉሉ የት አለ? ሲባል *ኦልድ ኤየር ፖርት* ይባላል? ታቦት ማደሪያን መናቃቸው ነው? ሉሉ ታቦት ማደሪያ ሰፈር አለ ቢባል ስር ነቀል የስም ለውጥ ይሆን ነበር፡፡ ዘሪሁን እንደ ሉሉ ነው፡፡

--አባትሽ ታዲያ የሚጎዳሽን ይነግርሻል? አለ ኮስተር ብሎ

--አንዳንዴ አዎ ሌላ ጨዋታ ጠፋ እንዴ? አለች የተናገረውን ባለማመን፡፡

--በሁዋላ ይቆጭሻል፡፡ በግልጽ ትክክሉን የሚነግርሽ አባትሽ ብቻ ነው፡፡

--ስህተትስ ከሆነ፡፡ የሆነ ምክር በግልጽ ተነገረ ማለት እኮ እውነት ነው ማለት አይደለም

--አዎ መናገሩ ራሱስ

--ብሎ ነገር አለ? መናገር ለብቻው ፋይዳ አለው? ይልቁን ኬክ ግዛልኝ፡፡

*አፍ መክፈት ለብቻው ፍሬ አለው? ዕድሜ ልኬን ስንቴ አዛግቼአለሁ? ስንቱ የትንባሆ ሱሰኛ በአራራው አፉን ሲበለቅጥ ይውል የለ፡፡ ሰው የመጀመሪያውን ቃል ያወጣው በአፉ አይመስለኝም፡፡ ከየት ሲሉህ ለመመለስ ከቋመጥክ የቀረ ቀዳዳ ፈልግ፡፡*

--እየበላሽ አይደለ

---

--እ......አልወደድኩትም ነበር

--ባለ ኬክ ቤቶቹ ሽርኮችሽ አይደሉም እንዴ?

--ቢሆኑስ

--ጋብዘውሽ ነው፣ ስላልከፈልሽበት ነው እንጂ ካዘዝሽ በኋላ ለምን አትበይውም?

--ለምን እንደዛ አልክ? ምን ማረጋገጫ አለህ?

--ይህቺን አልወቅ እንዴ?......ቆዬ እስኪ የገለታ ዴቱ[12] ነበርሽ አይደለ?

--ምን ታወራለህ? ከኬክ ወደ በሽርክና መብላት (*ከአፍ መከፈት*......በልቧ) ከዛ ወደ ገለታ ምን አመጣህ?

--ምን አለበት:: አንደኛ ቆንጆ ልጅ ነሽ፣ ሁለተኛ እኔ እውነት ከመናገር ያየሁትን ከመመስከር ዞር አልልም

--ነው እንዴ?

--ምን ማለትሽ ነው?

--የማታውቀውን ታወራለህ:: *እንደ ሴት ታወራለህ* ልትለው ፈልጋ እራሷን የሚጨምር ስለሆነባት ዝም አለችው::

ልትቀጥረው ወይም እንዲቀጥራት ትፈልግ እንደነበር ነገራው በቁጭት እንዲብሰለሰል ለማድረግ ፈለገች::

--ሌላ ቦታ ጁስ ጋብዘኝ ልልህ ነበር፣ አበለሻሸህ አለችው ሳቅ ብላ::

ዐይኖቿ በትዝብት አውድ ተሳስረዋል:: ዘሪሁን ይሄ የገባው አይመስልም::

--ያየን ሰው ለገለታ ቢፅፍለትስ? እዚህ እንደተቀመጥን ለምሳሌ በሞባይል ስልክ ፎቶ አንስቶ ቢልክለትስ? ሂሂ

አተኩራ አተኩራ አየችውና በተለይ ብጉሩን፣ በልቧ: (*ጉርምስና ሲበላሽ ብጉሩ ፈንጣጣ ይሆናል? ፈንጣጣም*) ምንም ማውራት አልፈለገችም ......ሻይውን እየጠጣ ዘሪሁን ወሬውን ይተረትራል......አትሰማውም:: ያላቋረጠ ቸልታዋ እንኳን ገብቶት 'ቻው' ብሎ ተነስቶ ለመሄድ ልቡ እሺ አላለውም:: የሽሽት ልጅ አይደለም:: ቢሆን ቢሆን እተቀመጠበት ፎሪ ይወጣል እንጂ አይሮጥም:: አፏን እያየ የልቡን መከራ በምላሱ ይቆጥራል:: እንዲህ አይነት በየቀኑ እያማረ የሚሄድ አፍ አይቶ አያውቅም:: በወሬ

| ------------

አልደረሰውም:: የዚህ አይነት ከንፈር ቢኖረው ለዘላለም ያፏጭ ነበር:: 'ሌላ ቦታ' ስትል አፏን በትንሹ ከፍታ በምላስዋ ላንቃዋንና ጥርሶቿን ስትነካ ('ሌላ') ከንፈሮቿ ተገናኝተው ሲለያዩ ('ቦታ') ሁለመናው ላይ እሳት ተቻለሰ:: አፏ አርፎ ቢቀመጥ እንኳን አይሰ'ማውም እንጂ ከዛ ያማረ ድምፅ ይወጣ ይሆናል:: የልባችን ምት ይሰማናል እንዴ? ደማችን ሲፈስ ይሰማናል እንዴ? ኩላሊታችን ሲያፀዳ የመጥረጊያው ስልት ጆሮአችን ደርሶ ኢያውቅም አይደለ:: የሰው ጆሮ የሰው ነውና አቅሙ ተመጥኖ እንጂ፣ ያ ከንፈር ምናልባት ራስ ምታት የሚፈውስ ፉጨት እያወጣ ነው:: ዐይኖቻችን የማያዩት ዓለም፣ ጆሮአችንም የማያዳምጡት ዓለም አለ:: ባክቴርያን እግዜር በሰጠው ዐይን መቼ ሰው አያት:: ጌርሰሞት ከንፈሮች ላይ ምናልባት መላእከት በከዋክብት ቅልልቦሽ ይጫወታሉ:: የገነት ዜግነት ያላቸው ሕፃናት ነጭ ስሌዳ ዘርግተው ቁጥር ያጠናሉ:: የእነሱም ታላላቆች የሙሉኩሌውን ካርታ እየሰሩ ልዋጤውን ይዘግባሉ፡ ዝግመቱንና ረብሻውን ያፀድቃሉ:: መላዕክት እዛ ከሌሉ ለምን ወጋገን አለው? ለምን ደርዙ በወርቅ የተዘመዘመ መሰለ? ከንፈሯን መስረቅ ቢችልና እየዞረ ቢያፏጭበት ደስ ይለዋል:: ገጠር ሜዳ ላይ ፉ ፉ ቢለው የጠወለጉ እህሎች ያሽታሉ:: የደረቀ ጅረትም ይሞላል:: የገበሬ እመቤቶች መንታ መንታ ይወልዳሉ:: ያን ከመሰለ ከንፈር የሚወጣው ፉጨት ምናልባት በታክሲና በአውቶቡስ ምትክ አይሮፕላን ያዛል:: በአዲስአባ እየዞረ ፉፉ ቢያደርግ ቁስልና እብድ የሌለበት ቆንጆ ነርሶች የሞሉት ሆስፒታል ያውም ያለ ሲ ቪ ስራ ያገኝ ነበር:: ጠቅላላ ሞዛርትን ጠቅላላ ያሬድን በዚህ በእሷ ከንፈር ማፏጨት የሚችል መሰለው:: ጠጋ ብሎ *ከንፈርሽ እንደ ቅዳሴ ያምራል* ሊላት ፈለገ፣ ግን ትዕቢቷን ማየትና መስማት አልፈለገም:: *ለምን ታየኛለህ?* ብትለው--*ምነው? ዐይን ከፈራሽ ለምን ገበያ አትወጪም?* ይላታል? ሁሉ ሰው በለመደውና ራሱንም በሰለቸው አባባል?

ከንፈሮቹ ደርዝ ላይ ነበር አፍሽን ልንካው የሚል አረፍተነገር:: ፈርጠም ብላ፡

--*ምን ታፈጥብኛለህ እንደዚህ? ፈራሁህ* አለችው

'*ፈራሁህ*' የሚለው ቃል ልቡን ነካው::

---

--አንቺ ደሞ......አለና ከተቀመጠበት ተነሳ። ድንጋጤውንና ቁጭቱን ረስቶ

--ሰላም በይኝና ልሂድ አለ ቆሞ

--እና? አለችው ከተቀመጠችበት ሆዱን እያየች። በልቶ ያደረ የማይመስለውን። በረዶ ጥርሶቹን። የሚለማመጧት ዐይኖቹን። እምቢ ማለት አልቻለችም። ዘሪሁን ፀባዩ ቢያናድዳትም ገላው ሳያቋርጥ የሚያማልል ውብ ነው።

--ፀባይህን አሳምራ አለችው ፈገግ ብላ።

--እየለመንኩ ነው። በዛ ከንፈር ብሰደብ ግድ የለኝም አላት

--በምኑ? አለችው እንዳልሰማች።

መጮህ ዳዳው። ወደ እሷ ሲመጣ ያላቀደው ስሜት ነው። ምራቁን ዋጠ።

--በነዚህ ከንፈሮችሽ የፈለግሽውን ተናገሪባቸው።

--ኡይ!

ከንፈሮቿ የሰሩት 'ኡ' ለጉድ ያምራል። ለምቦጬን ነከሰ። እተቀመጠችበት ጎንበስ ብሎ አቀፋት። ግራ ጉንጭዋን ስሞ ቀኙን ለመድገም ሲሄድ አስቆመችው።

--ሰው ምን ይለኛል እንኳን አትልም ሃፍረተቢስ ደረቅ። ትልሰኛለህ እንዴ? ሂድዛ ብላ በከፊል ሳቅ በከፊል መግደርደር ረጠበብኝ ያለችው ጉንጭዋን ጠረገች።

--በዪኝ

--ሂድዛ አበዛኸው አሁንስ። እንዲህ ብላ ፈገግ አለች።

ፈገግታዋ ጠቅሎ የያዘው ነገር ያለ መሰለው። የሆነ ደካማ ተስፋ። የሆነ ሁለቱም የሚጠራጠሩት እንጉ፡ ይህቺን ደካማ ፈገግታ እልባቷን አግኝቶ ቢተረትራት ከርሞ ከርሞ ከውስጥዋ ተግደርዳሪ እሺታ የሚወጣ። ምናልባት ቢለፋ፣ የምር ቢለፋ ያቺን እሺታ ተደግፎ እሷንና የአቀፋትን አፎት እንደዋሽንት ሊነፋቸው ይችል ይሆናል። ትቷት ሲሄድ በሁለመናው እያሰባት ነበር። *ሊፏ ነፋስና ፀሐይ እየመታው እንዲህ የማረ----ውስጥዋ ምን ይሆን?* አፉን ከአፏ ሳያላቅቅ እንዴት ከቆዳዋ ይራከባል? ለምቦጭዋን በለምቦጩ እየመጠጠ እንዴት በድንግል ቀዳዳዋ ይሰርጋል?

---

ዘሪሁን መንገድ እንደተሻገረ ልክ በመስማማት እንደተለያዩ ሁሉ እጁን አንስቶ ለጌርሳሞት ሰላምታ ሰጣት:: እሷም እጅዋን ከጠረጴዛ ላይ ሳታነሳ ጣቶቿን በቀስታ እየዘረዘረች በአጋጣሚ እንዳወቀችው ሰው ሰላም አለችው:: እወዲያ ጋ መንገድ ሲሻገር--በልብ ድካም ቢወድቅ ደስ ሳይላት አልቀረም:: ወይ መኪና ቢገጨውና ቢደማ፣ ወይም ፀረ ሰላም ተብሎ በፌዴራል ተይዞ ማረፊያ ቤት ለጥቂት ሳምንታት ቢወርድ:: አምላክ ብልህ ነውና መቼም ሳይደግስ አይጣላም......ማለት ይደግስና ይጣላል:: ወይ ይጣላና *ወይ ጉድ!!* ሲበዛበት፣ ሃሜት ሲጠናበት (*የለሀም እንዳልል ይነጋል ይመሻል፣ አለሀም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል......የመሳሰለ*) እንደ 'ኧረ የለሁበትም' ዓይነት ፈገግ ብሎ ይደግሳል:: አምላክ ጠያቂ ጌታ የለውምና አንዳንዴ አድርባይ ይሆናል አሉ:: ታዲያ እንዲህ ያለ ሸጋ ልቡ እንዲህ ቀጋ ሆነ?

ዘሪሁን ቶሎ ቶሎ ሲራመድ የሚያስበው ያልገባው ቢመስልም የጌርሳሞትን ቸልታና አዘጋጓን ነው:: እዛ መንገድ ዳር እሷን ለማየት ሲደረደሩ ከነበሩት ልጆች ከአራቱ አንዱ ገለታ ከድምፁና ከጉንጩ ትምክ ጋር የለም:: ሰካራሙን፣ በዱርዬነቱ ስሙ የጠፋውን ራሚሱን ምን ብላ ትፈልገዋለች? የቀራት ባካፋ ነው:: ባካፋ አሁን ያለበትን ሁኔታ አሰበ:: ባካፋ ያን ቦርጭ እና ቂጥ የመሰለ ፊት ይዞ ጌርሳሞትን ታግሎ ሊነጥቀው አይችልም:: የምር እየፈለጋት እሷን በቅንነት ከማዋራትና የልቡን ከመናገር ይልቅ ወዳጁን በማማትና በማጣጣል ራሱን ከፍ ለማድረግ መጣሩ ደበረው:: በቁጭት ራሱን ነቀነቀ:: ትክክለኛ አጠባበስ አልነበረም::

*በደስ ባር*[13] በኩል አንገቱን ሰብሮ እያለፈ እያለ አንድ ሰው ፊት ለፊቱ መጥቶ ቆመ:: ዘሪሁን ቀና ብሎ ሳያይ ወደ ግራ ተጠምዞ ሊያልፍ ሲል ሰውዬው ቀኝ ክንዱ ላይ ያዘው:: ዘሪሁን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተዋወቀው ሁሉ የሰውዬውን ፊት አተኩሮ አየው:: የጌርሳሞት አባት ኮላሴ ነው:: የኮላሴ ፀጉራም ደረት የሸተተው እንደ ተራራ ላይ ቅጥልጣይና መሬት ነው:: ግራ መጋባቱንና በዚህ ጠረን መረበሹን ችሎ:

---ጤና ይስጥልኝ ጋሼ ኮላሴ አለ

---

ኮላሴ አልመለሰለትም:: ለሰኮንዶች እየተያዩ ቆሙ:: ኮላሴ ዐይኖቹን እንኳን አያርገበግብም:: ከውስጣቸው ሥልጣን ይወጣል::

ዘሪሁን የያዘውን እጁን ነጥቆ አንገቱን ለድጋሚ ሰላምታ ሰብሮ ሊያልፍ ሲል ኮላሴ የበለጠ አጥብቆ ያዘውና አቆመው:: ዘሪሁን ግራ ገብቶት እጁን አየው:: ኮላሴ:

--ላናግርህ እፈልጋለሁ......እና እዚህ ቤት ገብተን ለስላሳ እንጠጣለን:: ማለት እንጫወታለን::

ጥያቄ ሳይሆን፣ ልመና ሳይሆን፣ ትዕዛዝ እንደሆነ ይታወቃል:: የዘሪሁንን መልስ ሳይጠብቅ ኮላሴ ወደ ደስ ባር እየጎተተ ወሰደው::

ደስ ባር በምሽት እንደሚሆነው አይደለም:: በሰፊው አዳራሽ ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ ለምሣ የተቀመጡ ሰዎች አሉ:: አየሩ ውስጥ መስኮት ቢከፋፈትም የማታው የሰዎች ላብና የጌሾ መአዛ ከተለሰኑበት የሰጋቱራ ወለል ላይ እንደ ጨረራ ይነሳሉ:: ከጀርባ የከረምቦላ ኳስ ሲንካካ ይሰማል:: ጨለም ካለ ሰው ከማይደርስበት ጥግ እንደ እጠፋርስ የሚሸቱ ጎረምሶች እየተስለመለሙ ያዩአቸዋል:: በየምሰሶው ላይ የወሩ ተረኛ ዲጄ መኮንን ማይክ የያዙ ሁለቱንም እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ የሚጮህበት ፖስተር ተለጥፏል::

ኮላሴ የዘሪሁንን እጅ ሳይለቅ በተረጋጋ መልክ ቆሞ ቦታ መረጠና መስኮት አጠገብ ወስዶ አስቀመጠው:: መስኮቱ ወደ ጠባብ የአትክልት ቦታ የተከፈተ ነው:: ከመስኮቱ ለጥቆ ነጭ ክብ የብረት ጠረጴዛ ዙሪያ የተቀመጡ ሰዎች አሉ:: ከአትክልቱ ቦታ ቀጥሎ ያለው የሰፈር ውስጥ መንገድ ነው:: ሰዎቹ ዘሪሁንና ኮላሴን እንዳዩ ራስ ለራስ ተጠጋግተው የሆነ ነገር አንሾካሾኩ:: ይሄ ድርጊታቸው ዘሪሁንን አሳሰበው::

--ምን ትጠጣለህ? አለ ኮላሴ እንደተቀመጡ:: ወደ ዘሪሁን አያይም:: ይሄም ዘሪሁንን አሳሰበው::

ዘሪሁን አፉ እንዳመጣለትና እንደለመደው:

--ኮካ አለውና ተገላምጠው ወደ አዩአቸው ሰዎች አየ:: ከሶስቱ ሰዎች አንዱ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ መስኮቱ የውጭ ጠርዝ መጥቶ እጁን ለሰላምታ ዘረጋና

--ሰላም ኮላሴ አለ

ኮላሴ ከተቀመጠበት ሳይነሳ እጁን ሰዶ ጨበጠውና:

--እንዴት ነው ሚ:ታ? አለው

--ወደ እዚህ ቀረብኩ:: አሁን የምኖረው አየር ጤና ነው:: እዚህ ነህ እንዴ?

ኮላሴ በዝምታ አየውና:

--ትንሽ ጉዳይ ስላለኝ በሁዋላ እንጫወታለን አለው ኮስተር ብሎ:: ሰውዬው ያልጠበቀው ነገር እንዳጋጠመው ሁሉ ኩምሽሽ ብሎ ወደ ነበረበት ወንበር ተመለሰ

አሳላፊ መጣና የዘሪሁንና የኮላሴን ትእዛዝ ወሰደ:: አሳላፊው ፈቀቅ እንዳለ

--የዚህ ሰፈር ልጅ ነህ አይደለ:: 'አቡ' የሚባል ልጅ ታውቃለህ? ታውቀው ነበር አውቃለሁ:: በቅርብ ጊዜ አይተኸዋል? አለው

--አሁን ብዙ አንገናኝም:: ምነው?

--ጥሩ:: አንድ ማሳሰቢያ ልነግርህ ነው:: አሁን ስመጣ መንገድ ላይ ከልጁ ጋር ፌቨን ሱቅ ተቀምጠህ አየሁህ:: አበባ ገዝተሃል? አልገዛህም:: ምን እያደረክ ነበር?

ዘሪሁን ኮላሴ ከውጭ ጀምሮ የያዘው እጁን እንዳለቀቀው አየ::

--የሰፈሬ ልጅ ስለሆነች አወራታለሁ

--ጥሩ አይደለም::

--ለምን? ሰላም ለማለት ነው

--ሰላም ለማለት መቀመጥ የለብህም:: ሰላም ብለህ ማለፍ ትችላለህ:: እና ለምን ተቀመጥክ?

ኮላሴ የዘሪሁንን ክንድ የበለጠ ጨምቆ ያዘው:: ዘሪሁን ቀና ብሎ ለመጀመሪያ ለመሰለ ጊዜ የኮላሴን ፊት አየው:: ፊት አይመስልም:: ፊቱ ሳር የለበሰ ገደል ነው:: ፊቱ በፀጉር ሊሸፈን የቀረው ቦታ ሁለት አውራጣት ቢያስተኛ ነው:: ፊሆ ሲያየው ቆየና:

--እኔ ለሰላምታ ነው......አለ ቀጠን ባለና በፈራ ድምፅ

--አትዋሽ:: ለመሆኑ ምን አወራችሁ?

ዘሪሁን ሲያወራው የነበረው የጠፋው አይነት ለአፍታ አሰበና

--ስለማስተ:ካ አለ ዐይኖቹን ከኮላሴ ፊት ላይ ሳያነሳ:: ከእሱ ቁጥጥር ውጭ ገላው መንቀጥቀጥ ጀመረ::

---

--እእእእ አለና ኮላሴ የበለጠ ደም ስሩን የሚዘጋው ያህል ጠበቅ አድርጎ ያዘው

--ጋሼ እጄን አሳመሙኝ አለ:: አፉን ሞልቶ መቆጣት አልደፈረም::

ኮላሴ በቀስታ ወደ ጆሮው ቀርቦ:

--ከፈለኩ እዚህ በቦክስ እዘርርሃለሁ:: አታውቀኝም በደንብ:: ምን አወራችሁ? ቀላል ጥያቄ እኮ ነው

--እ እ ስለ ማስቲካ

የኮላሴ እጅ እጁን ለቀቀና ጥፊ ሆኖ ፊቱ ላይ አረፈ:: ዘሪሁን ከዚህ ቅጣት ሳይነቃ፣ ኮላሴ አናቱን ይዞ ወደ ታች ገፍቶ ከጠረጴዛው ጠለል ጋር አጣበቀው:: ቡና ቤቱ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ዞር ብለው የሆነውን አዩና ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ወደ ጉዳያቸው ተመለሱ:: ኮላሴ ለስላሳ ማምጣት ላይ የነበረውን አሳላፊ ወደ መጣበት እንዲመለስ እጁን እያራገበ ነገረው:: አሳላፊው ኮካ ከተሸከመበት ትሪ ጋር ወደ ጀርባ አፈገፈገ:: ኮላሴ አጥብቆ የያዘውን የዘሪሁንን ጭንቅላት ሳይለቅ ወደ ጆሮው ተጠግቶ እንዲህ አለ:

--አንተ ካልፈለካት ለማን ፈለካት?

ዘሪሁን ጥያቄው ከባድ ሆነበት:: ሰውዬው ምን ማለቱ ነው? እያለ ያስባል:: አፉ ከጠረጴዛው ጠለል ጋር ስለተጣበቀ ለመናገር ቀርቶ በትክክል ማቃሰት አልቻለም:: በዝምታው መሃል ኮላሴ የዘሪሁንን አናት በፍጥነት አንስቶ ከጠረጴዛው ጋር አጋጨው::

ዘሪሁን ከዚህ በሁዋላ ምን እንደተናገረ ትዝ አይለውም:: የሚነቃነቁት አፉና አይኖቹ ናቸው:: በደከመ ድምፁ ለጠረጴዛው ጠለል እንደሚያንሾካሹክ ሁሉ ለደቂቃዎች ኮላሴ ለሚያቀርብለት ጥያቄ መልስ ሰጠ:: ኮላሴ የፈለገውን ካገኘ በሁዋላ የዘሪሁንን አናት ከጠረጴዛው ላይ ቀና አድርጎ አይኖቹን አተኩሮ እያየ:

--እም እም ባካፋ አልከኝ? አነጋግረዋለሁ አለ

--የምን ባካፋ? አለ ዘሪሁን የደከሙ አይኖቹ ፈጠው:: ኮላሴ አሳላፊውን ጠራውና ተመልሶ መጥቶ ያዘዙትን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦላቸው ሄደ:: ኮላሴ ለራሱ ያዘዘውን ኮካ ወደ ዘሪሁን ፊት ገፋ አድርጎ እተቀመጠበት ትቶት ወጣ:: ዘሪሁን አምስት ደቂቃዎች ያህል ሁለት ሙሉ ኮካዎች ላይና አየር ውስጥ እያፈጠጠ ተቀመጠ::

---

--ሰውዬው እንደዛ ነው አለው ከመስኮቱ ወዲያ ያለው ቀድሞ ኮላሴን የጨበጠው ሰው:: ይስቃል:: ዘሪሁን ግራ በመጋባት፣ በማዘንና በህመም ራሱን ነቀነቀ::

--ምን አድርገኸዋል? አለ ሰውዬው

ዘሪሁን በዝምታ አሁንም 'አላውቅም' አይነት ራሱን ነቀነቀ

--ለመክሰስ ከፈለክ ብዙ ምስክር አለ እዚህ:: ግን ሰውዬው ምስክርም አይምርም:: ይልቁን ከካህን ተራ በተራ ጠጣና ወደ ቤትህ ገብተህ የምትታከም ከሆነ ታከም::

ዘሪሁን ምንም ሳይጠጣ የተመታበትን ቦታ እያሻሸ ወደ ቤቱ ለመሄድ ከደስ ባር ወጣ::

(ባካፋ።     ያው ሐሙስ (ያው የቀን ቅዱስ) የኮንትራት ታክሲ ውስጥ ከጀርባ ባካፋ፣ ጋቢና ውስጥ ደሞ ዘመዱ ኢሳያስ ተቀምጠዋል። ኢሳያስ (በአጭሩ 'ሶል ዮ' የሚሉት) የሲኒማ ዳይሬክተር ነው። የባካፋ አጎት (የእናቱ የገነት ታላቅ) ልጅ ነው። አንድ የቴሌቭዥን ፊልምና አንድ የቪዲዮ ክሊፕ ሰርቷል። ብዙ ማውራት አይወድም። ስሙ የተጠራ የቪዲዮ ሙዚቃ ዳይሬክተር መሆን ይፈልጋል። ሁልጊዜ ደሞ ሙዚቃ እንደሰማ ነው። አናቱ ላይ ወይ አንገቱ ዙሪያ ሄድሴት[14] አይጠፋም። በወላጅ እናቱ በኩል የባለሥልጣን ልጅ ስለሆን ሁሉ በእጁ ሁሉ በሳሎኑ ነው። በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም የተረጋጋ ነው። የጓደኞቸው የአርቲስቱ እዝቂኤል (በአጭሩ 'ኢዚ' የሚሉት) ሠርጉ ነገ ስለሆነ አበባ ሊገዙ ወደ ፌቨን ቤት እየመጡ ነው። እዝቅኤል አበባውን ከሌላ ዝነኛ ሱቅ መግዛት ቢፈልግም ባካፋ ፈቃደኛ አልሆነም። ባካፋ ከታቦት ማደሪያ ቢሄድም ልቡ በከፊል ገና እዛው ነው። ባካፋ ብዙ ጊዜ ከኪነት ሰፈር አይጠፋም። ከእዝቅኤልና ከአርቲስቶች ጋር የሚያውለው የኪነት ፍቅሩ ነው። በታክሲ ወደ ታቦት ማደሪያ ሰፈር የመጣው የኢሳያስን መኪና 'አሰፋ' የተባለ ጓደኛቸው ተውሶ በተነጋገሩበት ሰአት ሊያመጣት ስላልቻለ ነው። ባካፋ ይህቺ የድሮ ሰፈሩን ከጥቂት ሳምንታት በፊት እንዳላያት ሁሉ ከንፈሩን መጠጠ። ለአፍታ በመስኮት የደረሰበትን ቦታ አየና እንደደነገጠ ሁሉ ዐይኖቹ ፈጠጡ። ባለታክሲውን እንዲቆም ነገረው። በወዲያ በኩል መንገዱን ተሻግሮ ፌቨን አበባ ቤት በረንዳ ላይ ሁለት ልጆች ተቀምጠዋል። የኢሳያስን ትከሻ ነካና ወደ አበባ ቤቱ እንዲያይ ጠቆመው። ኢሳያስ ምን *ትረብሸኛለህ?* እንደ ማለት ተከሳትሮ ዞር ብሎ አየው። ባካፋ በድጋሚ በግንባሩ ወደ ውጭ እንዲያይ ጠቆመው።

'ቅድም የሸኘነው ባለቶጩቱ ልጅ ነው አይደለ?'

'አዎ'

'ግን ለምን ዋሸሽው?'

'ደስ ይለኛል ለእሱ መዋሸት፡፡ ወሬኛ ነው፡፡ ሁልጊዜ የሚወራ ይፈልጋል፡፡ ልፍጠር ብሎ ራሱን ከሚያመው ለምን የሚወ'ራ አልሰጠውም? ሃሃ፡፡ አሁን ያወራሁት ከነገ ወዲያ በሰፈሩ ይደርሳል፡፡ እኔንም አዲስ መኪና የገዛሁ የደላኝ ሃብታም ያደርገኛል፡፡ ሃሃሃ፡፡ አላስጠጣህም፡፡ አብረሽኝ ሄድሽ አይደለ?' አለና ትከሻውን መታው፡፡

'እስከዚህ ወሬኛ ነው?'

'አዎ፡፡ ሌላ ክፋት የለበትም፡፡ ነርስነት ይማር ነበር፡፡ ይጨርስ አይጨርስ እንጃ'

'አዲስ መኪና ገዛህ......እኔ ደሞ አጉል ፍቅር የሚባል ፊልም ሰርቼአለሁ አሉ'

'ሰማህ አይደል፡፡ ሳላይ አልቀርም ሲል'

'እሱ አይፈረድበትም ፊልሙ ሁሉ ተመሳስሎበት ነው ሂሂ...... ምን ያደርጋል እዛ?'

'እሷን ሊያወጣ ይፈልጋል፡፡ እሺ የምትለው አይመስለኝም'

'ለምን እንደማትለው ይገባኛል፡፡ ምነው አፈጠጥክ?'

'እዚህ ነዋ የምንወርደው፡፡ የአበባው ቤት ይሄ እኮ ነው፡፡ በእናትህ ቆይ ያ ልጅ እስኪሄድ' አለ ወደ ታክሲው ሾፌር እያየ

'ያስጨምራል'

'ግድየለም'

'ሂሂሂ ኦኬ' አለና ኢሳያስ ሄድፎኑን ወደ ጆሮው መለሰ፡፡

ባካፋ በዝምታና በጥሞና ጌርሳሞትን ያያል፡ ሰዎች እንደ አስቀያሚ አጣና የሚቆጥሩአቸው እግሮቿ የለበሱት የቀረፋ ዱቄት የመሰለ የጠራ ቆዳዋን፣ ማር የሚፈልቅበት የመሰለ አፏን፣ እንደ ጥቁር የተራራ ፏፏቴ በላይዋ ላይ የምትፈሰው 'ስከርቷ[15]'......

ዘሪሁን የጌርሳሞትን ጉንጭ ስሞ ተሰናብቶአት ሄደ፡፡ ኢሳያስ ታክሲ ውስጥ መቀመጥ ስለሰለቸው የባካፋን ትከሻ መታና የታክሲውን ሂሳብ እንዲከፍል ነግሮት ወረደ፡፡ ባካፋ ዘሪሁን ከዐይን እስኪርቅ፣ ለደቂቃዎች እግሮቿን ዘርግታ ዘና ብላ የተቀመጠችውን ከንፈረ ፅጌ ጌርሳሞትን ሲያይ ቆየ)

---

(ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፡ *ማቴዎስ 15፡11*) ከ***ጂማ በር ካፌ*** ፊት ለፊት ሁለት ልጆች ከምትንገጫገጭ የኮንትራት ታክሲ ወርደው ቆሙ። ይነጋገራሉ። አንዱ በካናቴራ ነው። ቃሪያ ቅድ ጂንስ ሱሪ ለብሷል። ኢሳያስ ይባላል። ሌላው ኮትና ባለስንበር ሰማያዊ ሸሚዝ በሚያብለጨልጭ ክራቫት አድርጓል። የዚህ የሁለተኛው የተጠረገ ጫማ ሲፈልቅ ከአቡዳቢ ይታያል። እሱ ደሞ ባካፋ ይባላል። ሁለቱ ወጣቶች እሷ ወደ አለችበት ኬክ ቤት መንገድ አቋርጠው መጡ። ባለ ኮቱ ልጅቷን ከግንባሯ እስከ እግሯ ጫፍ አጠናትና በቲያትረኛ ፈገግታ፡

--ጌርሳሞት ነሽ?

ፈገግ አለች

--እንዴ ጌርሲ!

ባንክ ሰራተኛ ከሆነ በኋላ ባካፋን አይታው አታውቅም። መንገድ ዳር የሚቆሙት የደረሱ እንጂ ያለፉት ስላይደሉ ነው። እስኪጠጋት ቀሚሷን ጎተት ጎተት እያደረገች ቆማ ጠበቀችው። የቀሚሷ ጉተታ አልተሳካላትም። እንዴ ሴክሲ ልሁን ካሉ በኋላ በባዕድ ዐይን ከመቃጠል አይድኑም። ኢሳያስ በግምገማ ስልት ከላይ እስከ ታች አያት። ባካፋ እጅዋን በጉጉት ጨበጠና ሳይግደረደር አቀፋት። የልጁ ሁለመና በቬርሳቼ ኮሎኝ የታጠበ ነገር ነው።

--ምን ትሰሪያለሽ እዚህ?

ግልፅ አይደለም እንዴ? ቢያንስ ኬክ ልትበላ። ሰፈሯ መሆኑን እንኳን ቢረሳ።

--አይቼህ አላውቅም። ደህና ነህ?

--ሰፈር ለወጥኩ። ሲ ኤም ሲ ሄጄአለሁ ተከራይቼ። ምን እያደረግሽ ነው?

--ኬክ እየበላሁ።

*መቼ ዕለት ሳስብህ ነበር ልትለው ፈለገች። ምን ያደርጋታል? ባካፋ ይሄን ያህል የሚታሰብለት ነው ለመሆኑ?*

--ለጓደኛዬ ሰርግ አበባ ላሰራ ነበር። የማወራሽ ነገር አለ ጠብቂኝ መጣሁ። ወደ አበባ ቤቱ ውስጥ ከኢሳያስ ጋር ተከታትለው ገቡ።

---

ባካፋ የሆን ባለ ብዙ ፎቅ ባንክ ውስጥ ዶላር የሚነግድ ነው:: የው ዶላር ወረቀ እንጂ ወርቅ አይደለ? ዶላር ከባንዲራ አይበልጥም? የሆኑ ዶክተር ማናቸው አገራቸውን በእሱ ለምን ይለውጣሉ? የአባቷ ድንቁርና ምሁር ካለመሆኑ የመጣ ነው:: ተገላብጦ ቢማር *ምን ለበሽ? ዮት ነሽ?* አይልም:: የባካፋ ኮት ሃር ወይም ሱፍ ወይም ጥጥ ወይም ፖሊስተር እንደ ጥርሱ ንፁህ ነው:: ሲጋብዝ ከቁንጣን ወዲያ ነው:: ማለት አድማሱ አይያዝም:: ጌርሳሞት ሊመሽ አካባቢ ሶሲ ካፌ ገብታ ፌሸን ቤት በኬክ የሳሳ ሆዷ ላይ በሸኖ ቅቤ የተበወዘ የጥሬ ክትፎ ፈተና ስትጥል:: ያኔ የበላችው ለብዙ ቀን ከገላዋ አይጠፋም: እነሆ ወይዘሪት ሌሊት ሌሊት ስለስጋ ታልማለች፣ ጠዋት ጠዋትም ኮሰረት ታገሳለች:: ከቁንጣን ወዲያ ያለው ጀብድ ሁሉን ነገር መርሳት ነው:: የአእምሮ ዝግመት መምጫው አንዱ መንገድ ይህ ነው:: እንዲህ ሲባል ሰማች እንጂ መቼም አንዲት ፍሬ ልጅ ስለቁንጣንና ስለመርሳት ምን ታውቃለች? ከሌላው ወዳጁ ጋር ሲያወራና ከእሷ ጋር ሲያወራ ሞባይሉ አስራ ምናምን ጊዜ ጮኸ:: አላነሳውም:: (የዚህ ትርጉም: ጌርሳሞት *ኢዝ ሞር ኢምፖርታንት* = gersamot is more important = *ጌርሳሞት ከሁሉ ትበልጥብኛለች*) መኪናውን በሌላ ጓደኛው አስመጥተው ባካፋና እሷ ከጀርባ ተቀምጠው......የሆን የምትወደው ሙዚቃ በዛች ማዝዳ ዙም ዙም ውስጥ እየፈሰሰ:: የባካፋ ቀኝ እጁ በዐይነስውር ጉዞው ከአጭር ቀሚሷ ስር ውስጥ ሱሪዋን ሊጎትት ሲሳብ:: እጁን አቅባ ወደ ጆሮው በቀስታ ተጠግታ:

--ማርያምን እንዲህ ያለ ነገር አላውቅም፣ በሁሉ ቀዳዳዋ ላብ እየገነፈለ:: ኢሳያስ ያው ጆሮውን በኢር ካንዲ ሂድሴት ደፍኖ በሂፕ ሆፕ ተመስጦ ውስጥ ቁንጳላውን እየፈተለ::

--አትይኝም አላት በለሆሳስ:: አይኖቹ በጉጉት ተበልጥጠው

--ባካፋ ሙት

ከብ ፊቱ መሃል ከመሃል በደስታ ለሁለት ተከፈለ: ከፉ እንደወጣ ሽማ በትናንሽ መስመሮች እዛና እዛ ተሸነሸነ:: ከሲታ ጥርሶቹን ለጨለማው እያሳየ፣ እጁን በቀስታ ከጭኖቿ መሃል እየጎተተ አወጣ: አንድ ደቂቃ ሳይፈጅ ይቀራል?

---

--ሌላ ቀን እንጫወታለን አላት ወደ አንገቷ ቀርቦ:: ትከሻዋን በፍርሃትና በደስታ ሰበሰበች:: ደሞ እንደገና ትከሻውን ተደገፈ (ለምን ትከሻ ይሰባታል? ቀንበር ናትን? የሞፈር ዘር አለባትን? የድግር ደም?) ቤቷ እስክትደርስ ማናወዝ ፈለገች: እየሸኙዋት:

--እደውልልሻለሁ:: ስልኬን ያዥ:: ያንቺንም ስጪኝ

--እሺ

የስልክ ቁጥር ተለዋውጠው ለአፍታ ዝም ተባባሉ:: መኪናዋን ያመጣት የመሸፈሩን ቦታ የያዘው የባካፋ ወዳጅ በኋላ መስታወት ያያታል:: ለአመል የተከፈቱ እግሮቿን ገጠመች:: ባካፋ ያደረገው ነገር ሁሉ እውነቱን እንደሆነ ሊያሳያት ያልፈረሰ ፀጉሯን ሊያስተካክል አይነት ነካካላት:: አጀበችለት:: ምሁር ነውና በሰማንያ ፐርሰንት እንግሊዘኛ በሃያ ፐርሰንት ብሄረሰብኛ ከሁለቱ ጓደኞቹ ጋር እያወሩ ቤቷ ደጃፍ ቆሙ:: ባካፋ ቀድሞ ከመኪናው ወረደላት:: ተከተለችው:: በአጭር ቀሚስ በጨለማም ቢሆን መገላለጥዋ ስለማይቀር እሱ ቆሞ እያያት መውረድ ፈራች:: የውስጥ ሱሪዋ ሚጢጢነት ትዝ አለቻት:: ባካፋ አፉ በትንሹ ተከፍቶ ጉሮሮው እንደ ፒስተን ላይና ታች እየተነቃነቀ ያላየ መስሎ ያያታል:: ከመኪናው ስትወርድ መሬት የራቃት መሰላት:: ሚዛኗ ተዛብቶ ነው ወይስ ምድር ቀን ቀን አላት ሽፈፍ የምትልበት: ማለት የሰው ገላ መቅለብ የሚሽከካት? ወይስ መኪናዋ አየር ላይ ነበረች? ጌርሳሞት አነከሰች፣ ወይም በትንሹ አረገደች:: ደህና? አላት:: ባካፋ አፏን እያሳደደ ያያል:: ሰዎች አፏን ሲያዩ በአእምሮአቸው የሚመጣው እዝዝዝዝ የሚል ድምፅ ነው:: ንብ ፍለጋ በየአቅጣጫው ይማትራሉ:: ሲመሽ ጌርሳሞትን ወስደው እዛ መስከ መሃል ቢያስተኟት ጠዋት የምትገኘው በሁለመናዋ ንብ ገብቶ ነው:: የአፏ ተስፋ የማር ባሕር ነው:: ባካፋ ላንጋኖ ጠልቆ እንደወጣ ሁሉ ይተነፍሳል:: የትንፋሹ ላቦት እንደ ግንቦት አየር ነው:: አቀፋትና:

--አትጥፊ......አትጥፊ አላት:: መናገር አልቻለችም:: አይኖቹ ውስጥ የምታየው ፍላጎቱ ትኩረቷን በታተነው

ባካፋ ልክ ገብቷል:: አንድ እጇዋን ይዞ እያሸ:

--ለስራ ጉዳይ ከነገ ወዲያ ኬንያ እሄዳለሁ:: ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ስለምመለስ እደውልልሻለሁ:: አቀፋት ግን መልሳ ለማቀፍ አልቻከለችም:: ጣቶቹ ወገቧን ነከሱ ለቀቁ:: ደሞ ነከሱ:: ደሞ ላይና

ታች ዳበሱ:: ትንሽ ደሞ ሳባት ወደ ራሱ:: የአምስት ሰከንድ ስራ ለእሱ:: ስለ ወንድ ባታውቅም የሚሰማት ግን የመኪናውን በር ከፍታ መንገደኛ እያየ ለባካፋ መንጋለል ነው:: እንዴት ነው ሲንጋለሉ?

ሳምንት አለፈ:: ደሞ ሌላ ቀን:: ሌሎች ቀኖች እየተያያዙ ሳያፍሩ ባዶአቸውን አለፉ:: ወደየት ነው በእግዜር? ይሄ ሁሉ ተሰልፎ መንጎድ? ይሄ ሁሉ ደቂቃና ሰአት፣ መአልትና ሌት ለመሆን የሚቸኩለው ስለምንድነው?

ባካፋ ባልና ሚስት የተጋቡበትን ቀን እንደሚያከብሩ እሱም ጌርሳሞትን ያየበትን ቀን ማክበር ነበረበት:: ከዛ ቀን በፊት፣ ከዛ ጠዋት አራት ሰአት በፊት ጌርሳሞት የትም ሱቅ ብትገባ የምትገኝ አይነት ቢክ ስክሪፕቶ ማለት ነበረች:: አፍሮ ያላት፣ ቀጭን፣ ማን እንደሆነች እያወቅሃት በግድ የማትታወቅ የሚመስላት (የቢክ ስክሪፕቶ መስታወት ሰደርያዋ ዐይነባር አይደለ)፣ ሳይጠይቋት ራሷን በውሸት ሽሽት የምትክብ፣ ተለማመጡኝ እያለች የምትለማመጥ አስቸጋሪ ወይዘሪት ነበረች......

ባደገበት በዛ ሰፈሩ ባካፋን 'ባካፋ' ብሎ የሚያውቀው ጥቂት ሰው ነው፡ የሚጠሩት ባኪ ወይም ባኩ ብለው ነው:: ታቦት ማደሪያ የመጣው ገና የአራት አመት ልጅ ሆኖ ነው:: አክስቱ ሊዲያ ምዕራብ አዲስ አበባ የምትኖር እህቷ ገነት ጋ ሄዳ ነጠላዋን ወለል ላይ ዘርግታ በግንባሯ ተደፍታ ታቦትና እግዜር ተውኝ:: ባረግዝ ብዬ ያልተኛሁት ወንድ የለም:: አምላክ ለቃቃሚ አደረገኝ:: ሃጢያተኛ ሆንኩልሽ:: መረረኝ:: ከስድስቱ ልጆችሽ አንዱን ጎራዳ ስጪኝ:: እናት ብቻ ሳልሆን ባሪያው ሆኜ አሳድገዋለሁ:: ባኩን ልውሰደው:: እሺ ካላልሺኝ እዚሁ ተደፍቼ እጠብቃለሁ:: አልሄዳትም:: ይሄ መማጠን የመማጠኖች እናትና አባት ነበር:: እንዲህ ስትል የገነት ባል አቶ መዝገቡ ዱባለ፣ አንድ ጎረቤት፣ አንድ ቀለም የለሽ አዛውንት፣ አንድ የሆነች ሴትዮ፣

አንድ ካድሬ፣ ባካፋና ሌሎች እሱን መሰል ሶስት ሞሳዎች በተሰበሰቡበት ነበር:: ገነት ውሳኔውን ከመወሰኗ ቀድሞ ማንም ሳይጠይቀው ልጇ ባካፋ ሊዲያ ጋ ካልሄድኩ ብሎ እሪ አለ:: 'በይ ጉልበትሽን አታድክሚ፣ እሱም አንቺ ጋ መሆን ፈልጓል፣ ውሰጂው' ስትባል መጀመሪያ በግንባሯ ወለሉን፤ ቀጥሎ እያለቀሰች ተነስታ እዛ የነበሩትን ሰዎች ተራ በተራ፣ ከዛም ከላም በረት ተነስታ ታቦት ማደሪያ እስክትገባ በመንገድ ላይ ሺህዎችን ያለድካም፣ ያለማፈርና ያለመጠየፍ ሳመች::

ሳይንስ ሊያስሰው፣ ሊደርስበት በማይችል፣ ቢደርስበት እንኳን ሊገልጸው በሚከብደው የጠለቀ ፍቅር ባካፋ አደገ:: ከአክስቱ አልጋ ወጥቶ የራሱ አልጋ የገባው አስራ ሶስት ሲሞላው ነው:: አክስቱ ሊዲያን ዛሬ ድረስ የሚጠራት ሊዲ ብሎ ነው:: እሷም በአራት አመቱ እሱ ከሰጣት የሚጣፍጥ ስየማ እስክትሞት መላቀቅ አትፈልግም::

ሊዲያ ወደ ቤቴል በሚወስደው መንገድ ዳር ድልድዩ ሳይደርስ ብዙ ገቢ ባይኖረውም ትልቅ ግሮሰሪ አላት:: ከጠዋት እስከ ማታ እየሸቀለች ባካፋ ምንም እንዳይጎልበት አድርጋ በሥነስርአት አሳደገችው:: ቅዳሜ ጠዋት ልብሱን አጥቦ ሲኒማ አይቶ፣ በቀረው ጊዜ ደስ ያለውን እንዲያደርግ ትፈቅድለትና እሁድ ግን ከጠዋት እስከ ማታ የትምህርት ንባቡንና ጥናቱን ይሰራል:: ከቤት የሚወጣው አስር ሰአት ላይ ነበር:: ነፍስ አውቆ ምን ማንበብ እንዳለበት እስኪገባው ድረስ እሷ ከምታውቃቸው ያውቃሉ ከተባሉ ሰዎች የሚበጀውን ጠይቃ መጽሐፍም ይሁን መጽሔት ገዝታ ታመጣለታለች:: እያስጨነቀችው እንደሆነ ሲነግሯት 'የት ለመድረስ ነው ይሄ ሁሉ' እያሉ ሲያሸሟጥጧት፣ መንገድ እንዲያይ ከፈለገም እንዲሄድበት ማድረግ ግዴታ አለብኝ ትላለች:: ትበል እንጂ በልቧ የምትፈልገው፣ ምን እንደሆነ የማታውቀውን ዓይነት 'ትልቅ ሰው' እንዲሆንላት ነበር::

ባካፋ አዋሳ ዩንቨርሲቲ ለትምህርት ሲሄድ (ለማንም ባታወራውም) ሊዲያ ድምፅዋን አውጥታ አለቀሰች:: ለሳምንት እንቅልፍ አልወሰዳትም:: ለገና እረፍት አዲስአባ እስኪመለስ በየሁለት ሳምንቱ ደብዳቤና ገንዘብ ትልክለታለች:: ለመጀመሪያ ጊዜ የሊዲያ

ደብዳቤ ደርሶት የፃፈችውን ሲያነብ አለቀሰ። የዶርም ጓደኞቹ የምትልክለትን ደብዳቤ ሊዲያ ይሉታል። ከመልካም ቤተሰብ የሚላኩ ቼክ ውስጣቸው የያዙ ደብዳቤዎች ሁሉ በአዋሳ ካምፓስ ሊዲያ ይባሉ ነበር። (አይ ጎት አ ሊዲያ/ I got a lydia/ ካለ አንዱ ለፈለጣ የሚሰበሰበው የኮሌጅ ኡሪ መአት ነው) አዲስአባ አምስት ኪሎ ከቀረችው ከሴት ጓደኛው ከፀዳለ የባሰ የአክስቱ ደብዳቤ እንደሚናፍቀው ለማንም አይነግርም። ይሄ ናፍቆት ስህተት ይመስለዋል። ከአንድ አመት በሁዋላ ማልቀሱ አሳቀው። ጺም ያበቀለ ልጅ ምን ብሎ አክስቱን ይናፍቃል? ሶስተኛ አመት እያለ ደብዳቤዋ ሲደርሰው ጌርሳሞትን ካየበት ጊዜ ጋር ተመሳጥሮበት ሳይሆን አይቀርም አስተከዘው። ለክረምት እረፍት ሲመጣ ግሮሰሪ ስራ ሊረዳት ወዲያ ወዲህ ሲል ስታየው በኡኡታ ታስቆመዋለች፡ 'እኔ እናትህ ነኝ፣ ስላልወለደኩህ ውለታ መክፈልህ ነው? ትምህርት ሲሰለችህ ማንበብ ሲሰለችህ ሄደህ መንጃ ፈቃድ አውጣ እ......ቋንቋ ተማር......ቻይና ተማር......ደሞ ቻይናው በዝቷል......ፈረንሳይኛ ተማር። ሂድና ተዝናና ተጫወት። አቡ አለ። ፀዳል አለች!' አንዳንዴ ፀዳል ቤቱ ስትመጣ ሊዲያ የምትሄድበት ባይኖርም ሰው ጠይቄ መጣሁ ብላ ትወጣለች።

ከአብሮ አደጎቹ ጋር ባካፋ ብዙ ጊዜ ቀልደኛ ነው። ኮስታራ ውይይት ካደረገ ከአቡ ጋር ብቻ ነው። ስለ አፍላጦን ማውራት የሚችለው ከአቡ ጋር ነው። ስለ ኒቼና ስለ ማርክስ የሚያወራው ከእሱ ጋር ነው። አዋሳ ዩኒቨርሲቲ አካውንቲንግ ዲፓርትመንት ውስጥ ከጁኒየር እስከ ሲኒየር ከባካፋ ሌላ ስለ ሄርሜኔቲክስና ስለ ፊኖሚኖሎጂ የሚወያይ ተማሪም ይሁን አስተማሪ አጋጥሞአቸው አያውቅም። ከቲያትር አርትስ ልጆች ጋር ስለፊልም ቲዮሪ ሲያወራ ሆሊውድ ያደገ ይመስላል። ባካፋ የአዋሳን ቅዳሜ የሚያሳልፈው ፊልም ሲያይ ወይም ሚታፊዚክስ ሲያነብ ነው።

ከወዳጁ ከፀዳል ጋር ግን ይበላል ይጠጣል ይጫራል፣ የስፈርና የአገር ፖለቲካ ወሬ ያወራል። ፀዳልን ያወቃት በቀለ ይርጉ ሰርግ ላይ ስለአስትሮኖሚ ጨዋታ ተነስቶ ሲወያዩ ነው። ሰርግ ላይ ማን የነካው ነው ስለ አስትሮኖሚ የሚያወራው? እሱ፣ አቡ፣ የፀዳል ትንሽ እህትና

ፀዳል ነበሩ። *የፀሐይ ስርአት በስበት መስክ (ግራቪቴሽናል ፊልድ) ሀልውና የቆመ ነው። ለዚህም የፕላኔቶቹ ዝፈት (ማስ) ወሳኝ ነው* ብላ ስታወራ ፀዳለን ሰማትና ነገረኛው አቡ *በዝፈት ብቻ መሆኑ ያበሳጫል፣ ግኑኝነታቸው በውበትም ላይ መመስረት ነበረበት። The world is also organized aesthetically* (አለም የተዋቀረችው በኪነጥበባዊ ስልትም ነው) አለና ሳቀ። ይሄ አባባሉ ሰበብ ሆኖ በመሃላቸው ድብርት ስለገባ ውይይቱ ሊቀጥል አልቻለም። ይሄን አባባሉን ባካፋ አይረሳም። ፀዳልም ይሄን ሽሙጥ አትረሳም። ፀዳል መልከመልካም አይደለችም። ፀዳል ጎራዳ፣ ትልቅ ፊት ያላት፣ ወገበ ሰፊ (ብዙ 'ማስ' የአላት) እና ይሄን እጥረቷን ሁልጊዜ *በውበት አያስፈልግምና* በኬሚካል አንጂኒዬሪንግ ተማሪነቷ ጉራ ለመሸፋፈን የምትጥር እንደ አቡ አባባል *ቢቻ*[16] ናት። በዚህ ጉረኛነቷ መአቶች ያሚታል። መልክ ጠፊ ነው እንደሚባለው አእምሮም እንደሚረግፍ እንደ ፀዳል ያሉ አሕዛብ ይረሳሉ። አእምሮና ገላ ተብሎ በቀሽም ፍልስፍናና በወግ ግፊት የበላይና የበታች ምደባ ይደረግ እንጂ ሁሉ ማለት ታቹም ላዩም ረጋፊ ነው። የአእምሮን ነገር አማኑኤል መሳለሚያ ወይም ኪዳነምህረት ጠበል ማጥመቂያ ሄደሽ ጠይቂ።

ከፀዳል ጋር መውጣት የጀመረ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ለመጋባት የቀረቡ እንደሆነ አምነው ቁጭ አሉ። አንድ፡ ባካፋ ከእሷ ጋር ብዙ ማውራትና ምሁራዊ ቀልድ መቀለድ ይችላል። ሁለት፡ መብላት ስለሚወድ እሷም መብላት ትወድ ነበር። ሦስት፡ *ስራ አለብኝ አይመቸኝም* ሲል ሊዘጋት እንዳልሆነ ትረዳለች። 'ፕራይቬሲ' ወይም 'የራስ ጊዜ' የሚሉት ፈረንጃዊ ጉዳይ ይገባታል። አራት፡ መተዳደሪያ ሀብት በሚቸግረው ህብረተሰብ መመራረጫው ካሽና ካሽ በሚያመጣ ብቆታ መሆኑ አይገርምም። ሁሉም ደበቀው አልደበቀው ትንሽ ቢታሰስ ልቡን ይ፣ እዛ ሳጥን ውስጥ ሲቁለጨለጭ ይገኛል። ወደ ፊት ተቀራራቢ የግል ሃብት ይኖራቸዋል።

ችግር ግን ይኖራል፡ ፀዳል ማሺን ናት። *ብዙ ነገር አውቃለሁ ብሩህ ነኝ* ከማለቷ የተነሳ የምትፈልገውም የማትፈልገውም አይታወቅም። ከአንዱ መከራከሪያ ወደ ተቃራኒው መከራከሪያ ቅር

ሳይላት በቀላሉ አቋሟን መለወጥ ትችላለች፡፡ ይሄ ምድር ያልረገጠ በዕውቀት የበላይ የመሆን እምነቷ ምናባዊ እንደሆነ ገና አልገባትም፡፡ ገና በሙሉ ዲግሪ ያልተደገፈ ፈንጠዝያ ነበር፡፡ ለባካፋ ይሄ ክሰት አቋሟ ከእሷ ጋር ያለውን ግኑኝነት ደረቅ አድርጎበታል፡፡ ሁሉን ካወቀች ታዲያ ሕይወት ውስጥ ምን አስገራሚ ነገር ይቀራል? ይጠበቃልስ? ሁሉን ከማወቅ ቀጥሎ ያለው ሞቶ ማረፍ አይሆንም? ብዙ ግን አታውቅም፡፡ 'ብዙ' ግን ምንድነው? ቢነግራትም አትሰማም፡፡

አንድ ጠዋት አራት ሰአት ላይ አክስቱ ያስገባችለትን ልብሱን ከላውንደሪ ሊያወጣ እግረ መንገዱንም ሰላማዊትን ሃይ[17] ሊላት ውዴ ላውንድሪ ሲሄድ ጌርሳሞት ጉዳይዋን ጨርሳ ከሱቁ ስትወጣ በር ላይ አጋጠመችው፡፡ ቀለል ያለ በሰው ትንፋሽ ሊገለብ የሚችል የመሰለ ነጭ ቀሚስ ለብሳለች፤ ከከንፈሮቿ ላይ ውበት እንደ በጋ ንጋት ይንተገተጋል፣ ግራ አይኗ ወደ ፊት በተደፋ የፀጉር አለላ ተጋርዶአል፣ ቀኙ ዐይኗ ቆቅ ልጅ መሆኗን ይናገራል፡፡ ቅጥነቷ ያባባል፡፡ ሰላማዊት የሴት ጓደኛው እህት ስለሆነች ጌርሳሞትን እዚያው ሊያናግራት አልቻለም፡፡ ሰላማዊት ከአንዳንድ ሁኔታው (ከመርበትበቱ፣ ከአፈጣጠጡ) እቅዱን ጠርጥራ የታጠበለት ኮቱን ወስዶ (ደሞ አይከፍልም) ከወጣ በኋላ ሱቋ በረንዳ ላይ ሆና የሚሄድበትን አይታ ተመልሳ ገባች፡፡ ባካፋ ጌርሳሞትን እንዳያት ሊቀጥራት ሲያስብ ሁልጊዜም በገላው ውበት እርግጠኛ አይደለምና (አክስቱ ሊዲያ የእኔ ጎራጸ እያለች ስላሳደገችውም ይሆናል) ጌርሳሞት መለኮታዊ አፍ ፊት ለፊት ደፍሮ መቆም የሚችል አልመሰለውም፡፡ ይሄ በራሱ አለመተማመኑ ብዙ ጊዜ አስቀያሚ የተባለችውን እንዲንቅ፣ ቆንጆ የተባለችውን እንዲፈራ የሚገፋፋ ሊያጠፋው ያልቻለ የውስጥ ስሜት አሳድሮበታል፡፡ ደፍሮ ጌርሳሞትን ሰላም እንኳን ያላት ሰፈሩ አብረው የኖረች፣ ዐይኖቹ እስኪደክሙ በመንገድ ያያትና ሰላምታ ማለቱን ቀድሞ ስለለመደ ነው፡፡

ያን ቀን ላውንደሪው ጋ ሲያያት የሚያውቃት የድሮዋ ጌርሳሞት ገና እውስጧ እንዳለ ስለገባው (እሷ መሆኗን ማወቁ

ምልክትነቱ ነው) የድሮ ልምዷንና የአሁኑን ፍርሃቱን ደምሮና በሁለት አካፍሎ ባጋጠመው አማሃይ ስሜት ሊያናግራት አቀደ። ይሄ ብቻ አይደለም። መጠየቅ ባይወድም ማወቅ ይሻልና ለምን ይሀቺን ልጅ እንዲህ ፈለኩዎት? ይላል። ትዝ ይለዋል አንድ ጊዜ፣ ለአውቃለሁ ባይነት ጉራም ይሁን ለምን ብቻ የአገራችን ሰው የኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መጠቀም እንደሚከብደው ስታወራ ነበር። ሌላ ጊዜ ደሞ ገና አፕሎድ የምታደርገው ስለኢትዮጵያ የምግብ አይነቶች የሚያስረዳ ዌብ ሳይት እንደሰራችና ኮዱ የበግ[18] ወይም የቫይረስ ችግር እንዳለበት ስትናገር ሰምቷታል። ከዕለታት አንድ ቀን ይሄ ችሎታዋ የሚሰራውን ሲኒማ በኢንተርኔት ፕሮሞት ሲያደርግ ሊጠቅመው ይችላል። ይሄ ሁለተኛው እሷ በቀጥታ ካሳደረችበት ስሜት የሚጋጭ ቢሆንም ከራሱ ሌላ የሚያውቀው የለምና በግብዝነት የሚያሳማውም አልመሰለውም። ስለማያሳማው አላፈረበትም። ግን ይሄን ሁሉ ጠንካራ መሰረት የሌለው መልሱን ሳያወላውል የሚረታበት ዋናው ምክንያት ጌርሳሞትን የወደዳት ከንፈረ ቆንጆ በመሆኗ ተማርኮ ብቻ ነው።

እናም ጣጣ ያለዘለበቱ አይመጣም እንዲሉ (ወገኞች) በዚህ እምነቱ ላይ የሰላማዊት ጠርጣራ ማፍጠጥና የአባቷ ነገር ተደረበ። አባቷን ይፈራዋል። አንገት የሌለው ሰው ያስፈራዋል። የተረጋጋ ሕልሙ ውስጥ ያልተወሳሰበች ከንፈረዕጌ ልጅ ገብታ በጠበጠችው።

አክስቱ እንደለመደችው አንዱን የክረምት ወር ዘመድ ጥየቃ እያለች ገጠር ለገጠር፣ ሐረር፣ ናዝሬት፣ ወንድሞቹና እህቶቹ ጋ ስታንከራትተው ቆይታ ስፈር ስትመልሰው ጉዞ አማሮትና አርፎ መቀመጥ ሽቶ የሚያጫውተው ሰው ፍለጋ አይነት በልቡ እንደሰነቀ፣ ልብ ሳይለው ጌርሳሞት ቤት በድፍረት ሄዶ ትኖር እንደሆነ ጠየቀ። ማንም አልነበረም። እንደፈራው አንዳንድ ልጆች እሷ ቤት ደጃፍ ቆሞ ሰራተኛዋን 'ጌርሳሞትን ጥሪልኝ' እያለ ሲለማመጥ እንዳዩት ለፀዳል ነገሯት። ፀዳል ወሬውን እንደሰማች ሳታረፍድ ቤቱ መጥታ ለመሆኑ ከዘመድ ጥየቃ እንደተመለስክ ሰፈር እንደመጣህ የት ሄድክ? ስትለው፣ ጌርሳሞትን ቢያነሳ አጉል የቅናት ፋክክር የሚቀሰቅስ ስለመሰለው

ቀሻት:: *ከዛ ደባሪ ነገረኛ ሰውዬ ቤት ምን ልታደርግ ሄድክ? ሰው አይቶህ ነገረኝ* ስትለው እጅ ከፍንጅ ስለተያዘ በመቁለጭለጭና በመንተባተብ ጌርሳሞትን ሰላም ሊላት እንደሄደ ነገራት:: *ምን? ምን አለህ ከእሷ!? ምንህ ነች?*

ፀዳል ከባካፋ ጋር ያላት ነገር መጠናቀቅ መጀመሩ አልጠፋትም:: *የመራራቃቸው መነሻ* እሷ ስለስለቸችው እንጂ የጌርሳሞት የአፍ ውበት አልመሰላትም:: መሐንዲሷ ፀዳል የትም ያልደረሰች ቀላል ስህተቱን ሰበብ በማድረግ 'ራሴን የምችል ነኝ፣ *ማንንም አልለማመጥም'* ብላ ብዙ ሳትነጫነጭ ተለየችው:; *ታዲያ* ነፃነት ተሰምቶት አዋሳ ሲከርም በልቡ ጌርሳሞትና አፏ ነበሩ:: ቢሆንም ያደገበት ስነስርአት ለቅዳሜና ለእሁድ እንኳን ትምህርቱን ትቶ *ታቦት ማደሪያ* እንዲመጣ አላደረገውም:: ተሳክቶለት *ለዊክ ኤንድ*[19] ከመጣ *ሊዲያ ገነትንና ወንድሞችህን እያቸው* ብላ *ታክሲ ማቆሚያ* ድረስ ትወስደውና *መንገድ* ዳር *ቆማ* ('ሂጅልኝ' አይላት ነገር) ፂሙን ጎንትላ፣ አገጩን ስማ ሌላ ነገሩን እንደ ልጅ ነካክታ ትሸኘዋለች:: ሱቋ ገብታ እናቱ ቤት ደርሶ እንደሆነ *ለማረጋገጥ* ስልክ ትደውላለች:: የአዲስአባ *መንገዶችንና መኪናዎችን አታምንም::*

አቡ ባካፋ ከፀዳል *መራራቁን* በወሬ በወሬ ሲሰማ *ፎርጌት ዛት ዱባ ፊት አቦ:: መሃንዲስ መሆን ከሰው በላይ መሆን መሰላት? ሺህ ምሁር ብትሆን መዋደድ ግድ ነው:: የተያያዝንበት ላስቲክ በመለጠጡ የተራራቅን ይመስለናል እንጂ የመያያዝ ባርነት ውስጥ ነን:: አእምሮአቸው ብሩህ ባህላቸው ግን የባሪያ የሆኑ ስንት አሉ በእግዜር:: ባላምንበትም ልግልበት:: አይ አም ኢንተለጀንት*[20] *ብሎ የሚናገር ግን ዘር ማንዘሩ በቁንጫ የሚበላበት፣ በጎጥ ብራንድ የነደደ ሰው አያበሽቅህም? በ'ነኝ' ሰው የሚበላለጥ ቢኮን የአለም ጌታዋ ብዙ ነበር:: `ውበት ሀሰት ነው ደም ግባትም ከንቱ ነው' እንደሚባለው አእምሮም ሃሰት ነው ብልጥነትም ከንቱ ነው:: ሁሉ ረጋፊ ነው:: መደ'በር ደሞ የጋራችን ነው::* ባካፋ ብቻውን ሲሆን ብዙ ጊዜ ከለምቦጫም አቡ ጋር ተመሳሳይ መፅሐፍ አንብቦ ለምን እንደ ሊዲያ እንደሚያስብ ይገርመዋል:: አቡ የንባቡን ግልባጭ ሲያስታውስ፣ እሱ ለምን ያየውን ብቻ ያስታውሳል? እንዲህ ነው: አቡ የሚጠረጥረውን ባካፋ በእምነት

---

ይቀበላል:: አቡ ገልቦ ገበር ሲመረምር፣ ባካፉ በደበሎው ቀለም ይመሰጣል::

ባካፉ በመጀመሪያ ዲግሪ ከሐዋሳ ዩንቨርሲቲ ተመርቆ የተሻለ ገንዘብ የሚያገኝበትን ቦታ አማርጦ በአካውንታንትነት ሙያ የሆነ የታወቀ ባንክ ውስጥ ተቀጠረ:: ብዙዎቹ ወዳጆቹ ግን አካውንታንቶች ሳይሆኑ ሲኒማ ፕሮዲዩሰሮች፣ የሲኒማ ተዋንያኖችና ዳይሬክተሮች ነበሩ:: ለስራው እንዲያመቸውና ለአክስቱም ትልቅ ሰው መሆኑን ሊያሳይ ሲኤምሲ አንድ ዘመዱ ቤት የይስሙላ ኪራይ እየከፈለ መኖር ጀመረ:: ጌርሳሞትን ግን አልረሳም:: ትክክል ትሁን አትሁን የፀዳል ፈጣን ንፍገቷና ቆራጥነቷ ትምህርት ሆኖት አለፈ:: እሷም ከአቡ አባት ጓደኛ አራት ኪሎ ካምፓስ ከሚያስተምር የሆነ ባዮኬሚስት ጋር እንደምትወጣ አሉባልታ ሰማ:: ታቦት ማደሪያ በየጊዜው ቢመጣም የቀድሞ ጓደኞቹን ግን ማግኘት አልቻለም:: ገለታ መሰደዱን የሰማው ወር አልፎ ነው:: ከማዘኑ የተነሳ ቤቷ ሄዶ የገለታን እናት ፎርቱናን እሷ እንደፈለገችው እሱም እንደመሰለው አብሮአት እያለቀሰ አፅናናት:: አቡ የሚያፈቅረው የጋዜጠኛነት ስራው በአጭር ጊዜ አማሮት ጫት ቃሚ፣ ሰካራም ስለሆነበት ለአንድ ሰአት እንኳን አብሮት ሊቆይ የሚችል ሰው አልሆነም::

ዘመዱ ሊሠርግ አበባ እንዲገዛ ባካፉ ሲመደብ ትዝ ያለው የኮምቤ የአበባ መሸጫ መደብር ነው:: አክስቱን ለማየት፣ እግረ መንገዱንም መስራት የጀመረውን ፊልም ኤዲት አድራጊው ልጅ በታካችነት ስላስቸገረው የሚኖርበት ቤቴል ዘልቆ ሊያባብል፣ ታቦት ማደሪያ መጣ:: ያን ቀን አበባው ሱቅ ሲደርስ ጌርሳሞትን አያት:: ልቡ ለአፍታ ቀጥ አለች:: በመጠኑ ልምድ አካብቷልና እሷን ለማዋራት የእሷን ሁኔታ ይሁን የአባቷን አውሬ ፀባይ አልፈራም::

ሳምንት አልፎ ሌላ ሳምንት:: ለባካፉ ስልክ ደጋግማ ብትደውል አይነሳም:: ከለብ ሶፋ ላይ እግሮቿን አነባብራ ተቀምጣ፣ ቀዝቃዛ የበረንዳና የጽድ ጥላ ስር የሎሚ ጭማቂ እየጠጣች ለባካፉ

| ------------




ያላትን ጥልቅ ፍላጎት እያሰበች......ፍላጎት ሰባዊ ነው ደሞ። የሚያመጣውን ጭንቀት መጨነቅ ልምድ ይጠይቃል። የቀለበችው ሁሉ ከእጇ እያፈተለከ። ምኞቷ ነው ወይስ ዘመኑ ነው ጠማማ? ይሄን የጠለቀ ስሜቷን መስመር የሚያሲዘው ባካፋ የለም። *ታስባለች፡* ለምን ማንም ያልደረሰበት ቦታ ደረሰ? ምናምን። ለምን እንደዛ ለኮፈኝ? ምናምን። ነፍሷ ሰው የሌለበት አለም ዜጋ ናት......ጊዜም ያልፋል......ልብ ቢሉም ባይሉም ሰዎች ከወዲያ ወዲህ ሳያፍሩ ይመላለሳሉ። እየተመላለሱ ለአላፊ አግዳሚ መንገድ ይለቃሉ። በቀስተኛ አንደበቷ 'እዚህ ምድር አላችሁ?' ትለናለች። ባያምርም፡ 'እ ዚ ህ ነ ን' እንላለን......ብንስማማም ባንስማማም።

......ትዝ ይላታል በልጅነቷ መንገዱ የዛፍ ጥላ ነበረበት። በረንዳ ላይ ቆማ ግንባሯን ከሚመታው የአስር ሰአት ፀሐይ የምትሸሽግበት ቦታ ትቀላውጣለች። ከዚህ ሐሩር ለመጠለል ብትፈልግ የሆነ ካፌ መግባት አለባት...... ......ማኪያቶ ያነቃው ጎረምሳ ጀርባዋ ላይ በእሾሃም ብሌኑ ይፅፋል። እዛ ስትገተር ከማጅራቷ እስከ ባቷ ያሳክካታል። ዞር ብላ የሚያዩአትን ማየት ታፍራለች። ዐይኖቿ ከሌላ ወንድ ዐይን ሲገጣጠሙ አትወድም። ሲገጣጠሙ የሆነ የሚለዋወጡት ዲስኩር አለ፡ *'ምን ታፈጥብኛለህ?'* 'ምናለበት አትሞቺ'። እነዛ ሰዎች ገለታ፣ ራሚሱ፣ ባካፋ አይደሉም። በቃ አይኖች ናቸው። ወደ ቤት ስትገባ ኮላሴ የጎማ ጫማውን አጥልቆ (በነጫጭ ሰንበሮች የደመቀ የግስላ ስዕል የሚዘልበት ነገር) ሶፋ ላይ ተጋድሞ፣ ትከሻው ላይ ጋቢ እንደ ሻል ጠምጥሞ (እንዴት ሆነለት?) የስፖርት ፕሮግራም በቲቪ እያየ ይጮሃል፡ *አቀብል!! ምን አይነቱ ነው ጃን!* አባቷን እንደዛ ልታየው አትፈልግም። ስታድዮምን ትጥላ አባቷን ግራ ይገባታል።

# መልካ መልክ

## ፱



## ዝ ባካፉ

ባካፉ ወደ ኬንያ ሊሄድ ማታ ላይ ቤቱ እንደገባ ለሱቁ ሃላፊ ስልክ ደወለላት:: የቀጠራት ፀሐፊ ማውራት የማትወድ፣ አንድ ዐይናᎍ ልጅ እያለ ላም በረት የሚያውቃት የጎረቤቱ ልጅ ናት:: ስሟ እንኩዋን ቶሎቶሎ ወደ አፉ አይመጣም: 'ሰማሽ አንቺ እም እም ትሩፋት':: *ፀሐፊዬ* የሚል ተተኪ ቅፅል በመኖሩ ስሟን የበለጠ እየረሳው ነው:: መሳሳቱ ቢገባትም አታርመውም:: የስራ ጉዳይ ካልሆነ ዝምተኛ ናት:: ከ'ፀሐፊዬ' ደሞ *የጋሼ ደጀኔ ልጅ* ብሎ ሲጠራት ይቀለዋል:: የደጀኔ ልጅ ግን ሜካፑዋን ስታከፋፍል ካልመሰላት ማንንም በጥፊ ከመምታት አትቆጠብም:: ዝምታዋ ብስጭት ድበቃ ይመስላል:: ደወለላትና መጋዘን ካለው ከሁሉ የሚካአፕ አይነት በተሟላ መልክ ታቦት ማደሪያ *ኮምቤ አበባ ቤት* ፊቨን ለምትባል ልጅ እንድትሰጥ አዘዛት:: በምትሰራው 'ፓኬጅ'21 ላይ *ለጌርሳሞት ኮላሴ* ብለሽ ፃፊ ሲላት ትንሽ ስለዞረባት ተንተባተበች:: ስጦታው ለጌርሳሞት እንደሆነና ፊቨን ደሞ ለጌርሳሞት እንደምትሰጣት ነገራት:: ሌላ የሰለቸውን ጉዳይ እንዳትጠይቀው ፈርቶ ሞባይሉን ሊዘጋ ሲል አልቀረለትም:: '*ሰርፕራይዝ*22 *ነው?* አለች:: ጥርሱን ነክሶ በመሰላቸት *አዎ* አላትና አዎንታውን ለመሰረዝ ማለት በሚያበሳጨው የሰርፕራይዝ ባህል እንዳልታሰረ ሊነግራት ሃሞት የሌለው ትዛዝ ደረደረላት: *እስከመለስ ሁሉን ተቆጣጠሪ:: ቀልድ የለም:: እሺ?* የማስፈራራት ችሎታ የለውም:: ምክንያቱም የድምፁ ጠረን የፔፐር ሚንት ማስቲካ ነው::

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ገላው ቀርቶ ጫማው እንኳን የባንክ ሕንፃ ከገባ ልብሱ ላይ የሚቀረው የሳንቲም ወዝ፣ የገቢጋባንት አቧራ ነው:: ኮቱ ላይ ተጣብቆ የሚቀረው የብር ጠረን ነው:: የራስ ልብስ የምታደርግ ሐይማኖተኛ ብትሆንም ከኀጢያቱ አትርቅምና ቆብህን ገልብጠህ ከርክ መሰብሰቢያ ታደርገዋለህ:: የገንዘብ ሥልጣን ነው?

ሃሞተቢስነት ነው? ወይስ ደንብ ነው? ካፒታሊዝም ረቂቅ አይደለም:: ከእሱ በፊት የነበሩ ሥርአቶች ትተውት የሄዱትን ገብጋባነት ሰብስቦ ሰፍቶ እያይዞ በባይተዋርነት ቋንቋ የመሸፈን ነው: 'ይሂ ይሂማ ድሮም ነበር' እንዳንል:: ባካፉ ሲኒማ የማዘጋጀት ወይም ፕሮዲዩስ የማድረግ ፍቅሩን ስራ ላይ ለማዋል ሲመኝ በመጀመሪያ የተገነዘበው ቀላል ነገር በቂ ገንዘብ በእጁ ሊይዝ አለመቻሉ ነው:: አንድ ቀን አዋሳ ኮሌጅ ካወቀው ወዳጁ ጋር ሶሲ የተባለ ካፌ ተገናኝተው ስለገንዘብ ችግሩ ነገረውና ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰአት ሲነታረኩና ብዙ ነገሮች ሲተነትኑ ቆዩ:: በመጨረሻ ወዳጁ የሚካፕ ንግድ ውስጥ እንዲገባ ጠቆመውና ትንሽ አንገራግሮ ምክሩን ተቀበለ:: በአራት ወሮች ውስጥ ባካፉ ካዛንቺስ መሃል የአንድ ክፍል ጭቃ ቤት ውስጥ ትንሽ ቢሮ ከፈተ:: ከዛን ቀን ጀምሮ ካሽ የሚሰበስብ፣ መፅሐፍና የፊልም ስክሪፕት ማንበብ ያቆመ ስራ የበዛበት ሰው ሆነ:: የንግድ ግኑኝነቱ ከታወቀ የቻይና ኩባንያ ጋር ነበር (ባይታወቅም የታወቀ መባል አለበት):: ብዙ ጊዜ ባካፉ በትክክል ነጋዴ ነኝ ብሎ ራሱን ማስተዋወቅ ያፍራል:: ሊዲያ ያሳደገችው እንዲያነብ፣ የተመረጠ ተማሪ እንዲሆን፣ ራሱን እንዲጠብቅ፣ ጥሩ ጥሩ እንዲበላ፣ ከማይረቡ ሴቶች እንዲሸሽ፣ ከመጥፎ ወንድ ጓደኞች እንዲጠነቀቅ፣ ህብስቱን ያለማር እንዳይበላና ቡና በወተቱን እንዳይረሳ እንጂ ሱቅ ከፍቶ እንዲነግድ አልነበረም:: ልጅዋን ቢያሳድግላትም ነጋዴነቷ ጠዋት ማታ እንዳበሳጫት ነው:: ወይም ያበሳጫት ይሆናል:: ባካፉ የሚፈልገው ለፊልም ስራ የሚያግዘው ገንዘብ ነው:: በሁለት አመታት ውስጥ ከከንፈር ቀለም፣ ከቅንድብ መኳኳያ፣ ከብሩሽና ከመሳሰሉት ባገኘው ትርፍ የመጀመሪያውን ፊልም ለመስራት አቅም አገኘ::

የአለም ባንክ ለምስራቅ አፍሪካ አካውንታንቶች ያዘጋጀው ሴሚናር ላይ መስሪያ ቤቱ እንዲሳተፍ ወደ ኬንያ ናይሮቢ ለሁለት ሳምንቶች እንዲሄድ እድሉን ሲሰጠው በጣም ደስተኛ ነበር:: ጉዞው ጥቅሞች ነበሩት: ደህና ዶላር ከአለም ባንክ ማግኘትና በትንሹ ደሞ

ያላየውን አገር ማየት፡፡ እንግዳ አገር ማየት የሚመኘው እንግዳ ተራሮች ለማየት አይደለም፡፡ ተራራ የትም ተራራ ነው፡፡ ተራራው ላይ የሚኖረው አንበሳ የተባለው የዱር እንስሳ የትም አንበሳ ነው፡፡ *መሄዱ* እንደማይቀር ሲያውቅ ባካፉ በመጀመሪያ የጠየቀው *ጥያቄ የኬንያ ብሄራዊ ምግብ ምንድነው?* ብሎ ነው፡፡ አዲስ አይነት ምግብ መብላት መቻሉ ሁለተኛው ጥቅሙ ነው፡፡

ለሊዲያ ስለጉዞው ሲነግራት ከመርበትበቷ የተነሳ *በደህና እንድትመለስ እዚህ ጊዮርጊስ ሄደን ስለት እናስገባለን* አለችው፡፡ ልጁ ባካፉ በመመረጡ ደስ ቢላትም ከአገሩና ከእሷ በመራቁ ባር ባር አላት፡፡ *እዛ ምን ይበላሉ ብለህ ነው፡፡ የሆነ አፍሪካ አገር በየመንገዱ የአይጥ ጥብስ ይሸጣል ሲሉ ሰምቼአለሁ፡፡ አረመኔ ነገሮች ናቸው የሚበሉትን እንዳትበላ፡ ከዚህ ፍትፍት ይዞ መሄድ ቢቻል፡፡ እስኪ ጠይቅ ከተቻለ፡፡*

ባካፉ *ስለቱንም አልፈልግም፤ ያጋጠመኝን እበላለሁ* ብሎ ሊያሳስባት አልፈለገም፡፡ ቤተክርስቲያን እንሳለም ብላው በታክሲ ጊዮርጊስ ይዛው ስትሄድ በአፉ እምቢ ባይላትም በልቡ እንደሚከራከራት አታውቅም፡፡ *አቡ እኮ ሊዲን ይሰማል* የሚሉት ጎረቤቶችና እናውቃለን ባዮች 'አድርግ' ያለችውን ብዙውን ነገር በልቡ እየጠላው መስራት መጀመሩ አይገባቸውም፡፡ ዕድሜው ወደ እዛ ወስዶታል፡፡ ይሄን የማስመሰል ችሎታውን ግን መስሪያ ቤት ውስጥ ፈታ ብሎ ተጠቅሞበታል፡፡ ማስመሰል እንደ ዶላር *ሃርድ ከረንሲ* ተጠየቀ ከአንዱ ወደ አንዱ የአኗኗር ይትብሃል በቀላሉ ይሸጋገራል፡፡ ቲያትረኞች እንዳለ ወስደው በዚህ ስልት እንጀራቸውን ይጋግራሉ፡፡ የሲሚናሩን የጉዞ ዕድል ያገኘው አብረውት ከሚሰሩት ሰዎች የበለጠ ብሩህ ሆኖ ሳይሆን በማስመሰል ችሎታው ነው፡፡ ማንም ሳያየው የአለቃውን እግር ይስማል፡፡ ምንጣፍ ላይ ተንበርክኮ ጫማውን ሲጨመጭም በቂጡ ነፋስ እንዳይገባ የማይታይ ፎጣ ለራሱ ያቀብላል፡፡ በተለይ አለቃው የሚካፕ ቢዝነስ እንዲከፍት ከረዳው ጓደኝነቱና ደጀዝማችነቱ ከተምታታ ጠዋት ጠዋት ከቁርስ በኋላ፣ ከስአት ከምሳ በፊት፣ ማታ ራት ሳይበላ፣ ቤቱ እየጠራው ሳም ያለውን ቦታ ስሟል፡፡

ከዛ ስኮላርሺፕ ያገኛል። ከዛ *ታድለሃል* ይባላል። *አሪፍ ነህም* ይባላል። ከዛ *ስክስስቶል*[23] ይባላል። ከዛ *ቴክኖክራት* ይባላል። ከዛ *መአት መአት* ጥሩ ጥሩ ነገር ይባላል። ዋናው *መባል* ነው።

ጊዮርጊስ ሲደርሱ የአቡ እናት ወይዘሮ መቅረዝ ጸሎት ጨርሰው ከደጀሰላም ሲወጡ አገኙዋቸው። ወይዘሮ መቅረዝ እያዩት ስሙን ሳይጠሩት ቆሙ። ትርጉሙ ስለሚገባው ወደ እሳቸው ሄዶ ጎንበስ ብሎ በሁለት እጆቹ ጨበጣቸው። አፋቸው *ጋ* ነጠላቸው ረጥቦአል። ይሄን ቦታ ላለማየት አይኖቹን ያሸሻል። አንድ: ሊያሳፍራቸው አይፈልግም። ሁለት: የጤነኛነት ዘመናቸውን በትዝታ ሊቀሰቅስባቸውና ሊደብራቸው አይፈልግም። ሶስት አንዱ ሕመም ያደረገውን አንዱ ድክመት አድርጎ ይተረጉመዋል: እሳቸው ራሳቸውን ደካማ አድርገው እንዲያዩ እሱም የበላይ መሆኑን ሊጠቁማቸው አይፈልግም። በወፍራም፣ በተግበሰበሰ በቅጡ በማይሰማ ድምፅ:

--እርጅተህ እኮ ልትጠፋኝ ነበር። አቡን እጠይቀዋለሁ። አይቼው አላውቅም ይለኛል። ስታድጉ ትራራቁ? አዎ እሱስ አይቻልም። እንዴት ነህ? ትምህርቱስ? አሉት

--ደህና ነኝ ከአዋሳ ተመርቄ ባንክ እየሰራሁ ነው። ለሴሚናር ናይሮቢ እሄዳለሁ ስላት ሊዲያ ጊዮርጊስ ካልሄድን ብላኝ......አለና መሳቅ ጀመረ። መቅረዝ ፈገግ አሉና (የዐይኖቻቸው ዳርቻዎች ሲሸበሸቡ ይታያል) ለአፍታ ኮስተር ብለው (ግንባራቸው ይሸበሸባል)

--እስኪ እዚህ የምትሰሩትን ስትጨርስ ቤት ብቅ በል የማወራህ አለ። አቡ ስልክ ይደውላል እንጂ ቤት ከመጣ ስንት ጊዜው። እሱም እግር ከጣለው ትገናኛላችሁ። አላቁማችሁ --ደህና አምሺ ሊዲያ ብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ባካፋ አንዴ ዞር ብሎ አይቶአቸው አረማመዳቸው እንደደከመ አየና ትንሽ ትርጉም የሌለው ሃሳብ አሰበ። ከአሁን ጋር የማይያያዝ በልጅነቱ በጋቢና መስኮት አንገታቸውን ብቅ አድርገው *አቡን አላየኸውም?* የሚሉት አፊ-ጤነኛ መቅረዝ ትዝ አሉት። አንዳንዱ ያለፈ ነገር ሲታወስ ጎኑ የሚያሳዝን ለውጥ ቆሞ ነው: ገጠመኝ እንደ ጥለት ሪጋ ሰፍቶአቸው: ነጭ ስንብራት፣ ቀይ ስንብራት ሌላም መአት አይነት ስንብራት። ሊዲያ ዐይኖቹን ተከተላ:

---

--ይህቺ ሴት ሃኪምነቷን ትታ......ልክ አይደለችም ብላ ከንፈሮቿን መጠጠች:: ባካፋ አክስቱን ኮስተር ብሎ አያት::

--የገለታን እናት አይኗን ቢያማት ምራቅሽን ተቀቢው ብላ ልታሳውራት

--ተይ እማማ:: ካልሰራ አታደርገውም:: ተሻላት ግን?

--አዎ ተሻላት:: ምራቁ ነው ታዲያ?

--ምን አዳነኝ አለች ፎርቱና?

--ጊዮርጊስ ነዋ! ምራቅ ደሞ......ሁለቱም ነካ ያደረጋቸው

ሊዲያ እሱን ለማሳደግ ከእናቱ ከገነት ስትወስደው ሌሎች ሰዎች ምስኪን አድርገው ሲቆጥሯት እንደነበረ ረስታለች:: በሆነ መልክ ሌላ ሰው መዋረዱ ደስ ያሰኛት መሰለው:: እሱ ላይ ያፈሰሰችው አቅሟ ሁሉ የልጅ ባለቤት ለመሆንና በመሆንም የመኩራት: 'የተሳካለት ልጅ አሳደኩ' ትምክህት ይሆናል:: 'በለጥኳቸው' በቀል ይሆናል:: በዚህ የትዕቢት አፈራረድ ዙፋኑ ላይ ያለችው ሊዲያ ናት:: ቢሆንም ሊያቆማት አይችልም:: ደሞ ታዝቦ ሊያልፋት አልፈለገም:

--እማማ የጓደኛዬ እናት ናት እኮ አላት የማሳዘን ቅላፄ ጨምሮ

--ውይ ውይ ባኪዬ አፌ አፌ......

አፏ አልነበረም:: ሊፀልይ እንጂ ስነምግባር ሊያስተካክል አልመጣም:: አንገቱን ሰብሮ የቤተክርስቲያኑ ዋና በር ጎን ቆሞ የሚፀልይ መሰለ:: በጠራራ ፀሐይ መብረቅ ጥሎ ቢድን ለእግዚአብሄር ይፀልያል:: ጫማ ሰሞ በሰው ለተሰጠው የጉዞ ጉቦ ምን ተብሎ ይፀለያል? በሰው ጥበብ ያገኘውን ነገር ለምን ለእግዚአብሄር ያስተላልፋል:: እሱ አምላክ አይደብረውም? *ሺ ትህን ወዲያ አይለውም? አምላኬ ሆይ በማቃጠር እንትናን ፎግሬ ዋሽቼና አስመስዬ ይህቺን ትንሽ ዶላር ያለችባት ጉዞ ስላቀናበርክልኝ ብሎ ፀሎት ይቻላል?*

ከቤተክርስቲያን ሲመለስ ቤቱ ሳይገባ ወይዘሮ መቅረዝ ጋ ሄደ:: በር የከፈተችለት ሙና የተባለች ሰራተኛቸው ነበረች::

--ደህና ባኩ? ምነው እንደዚህ ጠፋህ? አለችው ሳቅ ሳቅ ያለች::

---

--ሰላም ሙና! ደህና ነሽ?

ከእሷ ጋር ስለነበረው ግኑኝነት ሰላማዊት ላውንደሪ ፊት ለፊት በሚደረደሩ ጊዜ አቡ ያወራቸው ትዝ አለው:: እሱን እያሰበ ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ:: አሳሳሟ የዛ አይነት ስድ ሁኔታ ያሳለፈች መሆኗን አይናገርም:: *እትዬ መቅረዝ አሉ ወይ?* ብሎ ጠየቃትና እንዳሉ ስትነግረው፣ በለመደው የዘመድና የሰፈረተኛ መንገድ በጀርባ ዞሮ ሊገባ ሲል፣ ልክ እሱን ይጠብቁት እንደነበረ፣ እንደሚመጣም እንዳመኑ ሁሉ፣ ዋናው የቤቱ በር ተከፈተና ወይዘሮ መቅረዝ በግራ እጃቸው አረንጓዴ መፅሐፍ ይዘው ብቅ አሉ:: የሆነ ነገር ቢናገሩም ባካፋ ያየው አፋቸውን የጋረዱበት ነጠላ እየተርገበገበ ቃላትና ሆሄያት ተተረማምሰው ወደ ማጉተምተም ሲለወጡ ነው:: ልዩ ቋንቋ እንደተናገሩ ሁሉ ሙና ተረጎመችለት:

--ሰላም እያለችህ ነው አለች በፈገግታ::

--ሰማሁ አላት ጨዋ ለመሆንና የአገጫቸው ጉዳይ እሱ ጋ አስቸጋሪ ጉዳይ እንዳይደለ ለማመልከት:: ባካፋ ግን አልሰማቻቸውም:: የቆዳ ጫማው የመኪና ማቆሚያው አስፋልት ላይ ይጮሃል፣ በነፋስ የሚንኳኳው የሙና ቀሚስ፣ ቤቱን የከበቡት የሚንሿሹት ዛፎች፣ የሰፈሩ ጫጫታ፣ በዚህም ላይ መቅረዝ የተሸፈኑበት ነጠላ መሰማትን የምር አስቸጋሪ ያደርጋሉ:: ሙና ውሸቱ ቢገባትም እንዳልገባት ሁሉ ኖራ የመሰለ ሳቅ አፏ ላይ ለጥፋ ወደ ጀርባ ሄደች:: መቅረዝ ደረጃውን በቀስታ ወረዱና:

--ባኩ ትቆያለህ? አሉት

--ጠዋት ሂያጅ ነኝ፤ ገና የምይዘውን እቃ አላስተካከልኩም

--ከርመህ ብትመጣ የሻይ ጊዜ እንኳን አላስተረፍክም

--ሌላ ጊዜ እመጣለሁ

ገና አረፍተነገሩን እንደጨረሰ ቀጭን መፅሐፍ የነከሰ እጃቸውን ዘርግተው

--እስኪ ይሄን አንብበው......ለመንገድ ይሆናል አሉት

ወሬ እንጂ መፅሐፍ አልጠበቀምና ባካፋ መጽሐፉን በድንጋጤ ከእጃቸው ላይ በቶሎ ቀልቦ የፊት ልባሱን አየው:: አርዕስቱ *ወደ ፊት*

*ለመወንጨፍ ወደ ኋላ መንደርደር፡ ባህላዊና ዘመናዊ ፈውሶች* ይላል:: የተፃፈው በነጭ ነው:: የመፅሐፉ ቀለም የክረምት ሳር የመሰለ አረንጓዴ ነው:: ብዙ የዛፍ፣ የአበባና የቅጠላቅጠል ስዕል አለ:: ፎቶም አለ:: ከስር የሴትዮዋ ስማቸው አለ:: ባካፋ የአባታቸውን ስም እንደረሳ ልብ አለ:: *አዝማች?* ሁሉን ሊሆን ትንሽ የቀረው ሕይወቱን እዚህ አብሮአቸው ኖሮአል ግን......:: ከመጽሐፉ ጀርባ ላይ አስተያየት የሰጠ ሰው አለ:: አስተያየት ሰጪው የባለቤታቸው ጓደኛ ባዮ ኬሚስቱ ፕሮፌሰር *መንግሥቴ ነገዎ* ናቸው:: መንግሥቴ በወሬ እንደሰማው የፀዳል ወዳጅ ሆነዋል:: ስለ ፀዳል ቢያውቁም ባያውቁም ትንሽ ተረበሸ:: *አየሀ ከአንተ ብትሄድ ልጅቷ ሆነላት* እይ የሚሉት መሰለው:: ለአፍታ ፀዳለንና እግሮቿን አሰበ፤ ከዛ ምንጭራሙን ባዮኬሚስቱን አሰበ:: የላይ ከንፈር ለምን ብሎ ከውሃ ልክ ይዛነፋል? የአጋጣሚዎች ሴራ እንዲህ የሚያደርግ ስሜት ሊፈጥርበት የሚችል አልመሰለውም:: ቅኙቱን ተቆጣጥሮ መፅሐፉ ጀርባ ላይ ያለውን አስተያየት ለማንበብ ሲጀምር መቅረዝ:

--ደራሲ ሆንኩ አሉና እጃቸውን አፋቸው ላይ አድርገው ከት ብለው ልጋጋቸውን ያዝረበረበ ሳቅ ሳቁ:: ባካፋ በአሳሳቃቸው መቀፈፉ እንዳይታይ የውሽቱን መፅሐፉ ላይ አተኮረ:: ወይዘሮዋ መንገጭላቸውን ቦታ አስይዘው የልጋጋቸውን አወራረድ ፈር ስጥተውና ጠራርገው:

--ልብወለድ አይደለም ግን:: አንብብና ሃሳብህን ትስጠኛለህ:: አሁን እዚህ ቆመን አናወራም:: ደሞ ተጠንቀቅ ባዕድ አገር ያላዩት ብዙ እንቅፋት አለ:: ከተጠነቀቅህ ቆንጆ ይሆንልሃል:: ስትመጣ እናወራለን::

--እሺ እሺ አነበዋለሁ::

--አውቃለሁ እንደምታነበው:: አቡ......ተወው እሱን አሉና ሁለቱንም ክንዶቻቸውን ዘርግተው ባካፋን ሲጠጉት አቅፈው ሊስናበቱት እንደሆነ ገብቶት በመግደርደር አንገቱን ሰበር አድርጎ አፋቸውን ከጋረደው ነጠላ (አንዳንዴ ስለሚሸት) ለማምለጥ ያቀደ ላለማስመሰል እየጣረ (እንደዛ እያደረገ እንደሆነ ቢያውቁም) ጉንጭ ለጉንጭ ሲነካኩ:

---

–ደህና ተመለስ አሉት::

በመጠኑ ከልጃቸው የበለጠ ስላመኑት ቢኮራም ተረበሸ:: ግራ በተጋባ መልክ ደህና ቆዩኝ ብሎ ሲወጣ ሙና ከጀርባ:

--ቻው ሳትለኝ ልትሄድ ነበር? ጉደኛ ነህ አለችው

ባካፋ ስህተቱን ለማዘናጋት እየሳቀ ድምፁን ከፍ አድርጎ ደህና እንድትጠብቀው ስላምታ ሰጣትና ቆመው ለሚያዩት መቅረዝ እጁን አወዛውዞ ከግቢው ወጣ::

*

አይሮፕላን ውስጥ ሲገባ ለመጀመሪያ አስር ደቂቃዎች ከዛ ደሞ ሰማይ ላይ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ሲደሰት ቆይቶ ተሰላቸ:: እንደውም ከዛን ቀን በፊት ብዙ ጊዜ እዚያ ውስጥ የነበረ መሰለው:: አይሮፕላን በፊልምና በተለያዩ የመገናኛ መንገዶች ስላየ አእምሮው ውስጥ የተሰበሰበው መረጃ የመብረር ብርቅነቱን እንዳሳነስበት አልጠፋውም:: የሚሰራው ጠፍቶት ጥቂት ጊዜ ለሆስቴሶቹ ፈገግ ፈገግ ሲል ቆይቶ እግሩ ስር ካስቀመጠው ቦርሳ የመቅረዝን መፅሐፍ ሲያወጣ የሚያውቀው ሰው የመሰለ የፓይለት ድምጽ አይሮፕላኑ ከኢትዮጵያ ክልል ወደ ኬንያ ክልል እንደገባ ተናገረ:: ቦርሳው ውስጥ ለስራው የሚገለገልባቸው ዶኪመንቶች፣ *ኒኦ ዳሪዊኒዝምና ዘ ታኦ ኦፍ ፊዚክስ*[24] የተባሉ መጽሐፍት ነበሩ:: እጁን ሲሰድ ጣቶቹ መጀመሪያ የነኩት እሱም ጎትቶ ያወጣው ደካማ ልባሱ የተጠራመሰውን የመቅረዝ መፅሐፍ ነበር::

ቀና ብሎ በመስኮት ሳር፣ ድንጋይ፣ ጠራራ ፀሐይ፣ ገደልና ኮረብታ፣ ቀይና ቢጫ ግራር የሸፈነውን የኬንያን ቆላማ መልካምድር እያየ የሆነ አርእስቱን ሊያስታውሰው ያልቻለ ፊልም ትዝ አለው:: ከፊልሙ ትዝ ያሉት አንዲት ቆንጆ ሴትዮና የለበሰችው ሰማያዊ የሐር ቀሚስ ነው:: ምን ነበር አርዕስቱ? ማስታወስ አልቻለም:: ወደ መፅሐፉ ተመለሰና መቅረዝ ስም ላይ ስህተት ወይም መገረም እንዳየ ሁሉ ሲያፈጥ ቆይቶ በልጅነቱ የሚያውቃቸው ከንፈረ መልካም መቅረዝ ለአፍታ ታውሰውት የመጽሐፉን ሶስት ገፆች ገለጠና ማውጫውን አነበበ:: 125 ገፆች እንዳሉት ካየ በኋላ ገፆቹን በአውራ ጣቱ በቀስታ

እንደ ደስታ ብር ቸር አደረጋቸውና በየመሃላቸው *መግቢያ......ስለደራሲው......ዘመናዊነት.......ጫማዎቻችን......አፍ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል......ጤንነት ምንድነው?......ጤንነት ውበት ባህልና...... ዘመናዊነትና......*በእንግሊዘኛ *ሊፕስቲክ* የሚል ፅሑፍ አየ። በጉጉት ነቃ ብሎ ወደ ኋላ በመመለስ የመጨረሻውን አርዕስት ያነበበበትን ገጽ ፈለገና አገኘው:: *የከንፈር ቀለም (ሊፕስቲክ)* የሚል አርእስት ነው::: ከአርዕስቱ ስር ጥቅስ ይቀጥላል:

> **'የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው:: የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናሃል ይከናወንልሃልም** *እያሱ ምዕራፍ 1 ቁጥር 8*

*ምን አገናኘው ሊፕስቲክና መፅሐፈ ኦሪት? እትዬ ሃይማኖተኛ ሆኑ?* መግቢያው በማያውቀው ጉረኛ የመሰለ መረጃ ይከፈታል: ***'ኮስሜቲክስ' የተባለው ቃል የተገኘው 'ኮስሞስ' ከተባለው የግሪክ ቃል ነው:: ትርጉሙም 'ሥርአት' ማለት ነው:: ቃሉ ሙሉኩሌውን የሚመለከት ቢሆንም ወደ ሰው ልጆች ጸባይና ተጨባጭ ግብር ሲመጣ ትርጉሙ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ መልካቸውና ቁመናቸው መልክ መልክ ወይም ሥርአት እንዲይዝ ማድረግ ማለት ነው***......እሱን ትቶ ወደ ሚመለከተው ምዕራፍ ዘለለና ማንበቡን ቀጠለ::[19]

---

19 (......ብዙ ጊዜ (?) ሴቶች እግዜር የሰጣቸውን የከንፈር ውበት ይጠራጠራሉ:: ውብ ነው ተብሎ የተሰየመ አይነት ከንፈር ይፈልጋሉ:: ማን ውብ ብሎ ሰየመው? ለምንና እንዴት ተሰየመ? የሚያምር ከንፈር ምን መምሰል እንዳለበት የሚደነግግልን ማነው? አሁን አሁን እንደ ፍፁም የተቆጠረ የከንፈር ዚቅ በቀጥታና በእጅ አዙር (በፎቶና በሲኒማ) በቀዶ ጥገና አምላኪ የሆሊውድ ተዋናዮች ሲሸጥልንና ሲወደስልን እናያለን:: በግል ሕይወቴ እንኳን በላይና በታች ከንፈሯ ኮላጅን ያስገባች የእኔ ዕድሜ እኩያ የሆነች የአገሬ ሰው በቅርብ አጋጥማኛለች:: ይህቺ ሴት ከምትኖርበት የአሜሪካ ግዛት ካሊፎርንያ ከረዥም ጊዜ በኋላ ወደዚህ ተመልሳ መጥታ ስንገናኝ ከንፈሯ አጓጉል አይነት ተለቀብኝ::

---

ካየሁዋት ብዙ ጊዜ ስለሆነ የመርሳት ነገር መስሎኝ ነበር:: ስለዚህ ግራ ቢገባኝ ጠየቅሁዋት:: በከንፈሮቿ ኮላጄን እንደተወጋች ነገረችኝ::

ከንፈርን በቀለምና በቀዶ ጥገና ለማስዋብ መሞከር አሁን የተጀመረ አይደለም:: በ1900 መጀመሪያዎች ላይ በአውሮፓ ሴቶች ከንፈራቸውን ድንቡሼ ለማድረግ ('ኢትዮጵያዊ ከንፈር' ይሉታል በቅፅል ስሙ) ፓራፊን ይወጉ ነበር:: በዘጠናዎቹ ደሞ ፓራፊን ገላ ውስጥ ማስገባት ጎጂ ነው ተብሎ *ቦቫይን ኮላጅን* ቦታውን ወሰደ:: አሁን አሁን ደሞ *ሬስታይሌን* *ጁቨንደርም* የተባሉ አሲዶች ይሁንታ አግኝተዋል:: በአገራችን የተለመደው የከንፈር ቀለም ወይም ሊፕስቲክ መቀባት ነው:: ግን ስለሊፕስቲክ ምን እናውቃለን? ስለ ሊፕስቲክ ከማወቃችን ቀድሞ ባለጉዳይ ስለሆነው ስለከንፈራችን ምን ያህል እናውቃለን? አወቅን ካልን በእርግጥስ ምን እናውቃለን?

የሚመሳሰሉ ከንፈሮች ለዐይናችን መሰሉ እንጂ በቅርበት ከተጠኑ የተለያዩ ናቸው:: ልክ እንደ ጣት አሻራ የከንፈሮች ቅርፅ ከግለሰብ ግለሰብ ይለያያሉ:: ማለት የአንዷ ሴት ከንፈር ፍፁም በሆነ መልክ ከሌላዋ የተለየ ነው:: ልክ እንደ ጣት አሻራ የከንፈር አሻራ ፖሊስ ምርመራ ላይ ወንጀለኛን ለማግኘት እንደሚጠቅም የምናውቅ ስንቶች ነን? በተጨማሪም የከንፈር አሻራዎች ባለከንፈሯ ባሳለፈችው የልምድ አይነት የሚለዋወጡ ናቸው:: ማለት ከንፈሮች እንግሊዘኛ ልጠቀምና ዳይናሚክ ወይም ተለዋዋጭ ናቸው: *መወፈር፣ መክሳት፣ መበሳጨት፣ መሳቅ፣* ወዘተ የከንፈርን ፀባይና ቅጥ ይደነግጋሉ:: ማለት ከንፈሮች *ሕልውናዊ* **(existential)** ባህርይ አላቸው:: በዚህ ጉዳይ ላይ በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የቆመ በቂ ግንዛቤ ባይኖረኝም ብዙ የተሳመ ከንፈር ካልተሳመው ሁኔታው ይለያል:: ቀለም ሲቀባ ከከረመው ያልተቀባው ይለያል:: ይሄም የከንፈሮችን አሻራ፣ ቀለም፣ ፀባይና ቅጥ ይለዋውጠዋል:: ቀለም ለዳይናሚኩ አንድ ግብአት ነው:: ሊፕስቲክ በወጣትነቷ ጊዜ ስትቀባ የኖረች ሴት በስተርጅና ከንፈሮቿ የገረጡ፣ ወዘቢስና የማያምሩ ይሆናሉ::

የከንፈርን ፀባይና ቅርፅ መለወጥ ስርነቀል ሲሆን ወደ አገራችን የሙርሲ ጎሳዎች ጋ እንመጣለን:: ከንፈር በመዋቢያ ባህላችን የሆነ ትልቅ ስፍራ እንደነበረው እነዚህ ጎሳዎች በከባድ ያሳዩናል:: የአያቴ አያት አያት አያት ወዘተ ምናልባት ሙርሲዎች ነበሩ:: ሙርሲዎች የከንፈርንና የአፍን ትርጉም ለማዳበር የአፈር ተቀጥያ ሰርተውላቸው እኛ ከምንረዳው የየቀኑ ጠባብ ማንነት አውጥተዋቸዋል:: ማለት ከንፈር ምጣድ የሚሸከም ሆኗል:: እናም አዲስ ልምድ ነው:: ቀዳዳ ያለው ከንፈር የሳመ አለ? ፍሩዮዳዊ ልሁንና፣ የሴቶች ምንተፍረት ቦታ ለውጦ ወደ ፊታቸው መጣ? ሳያቋርጡ ድንግል የመሆንና ሳያቋርጡ የመገሠሥ ምልክት

ይሆን? ምናብ ጎጥ የለውም......ስለዚህ ሊፕስቲክ ከመጠቀማችን በፊት ከንፈሮቻችንን እንደ አንድ ራሳቸውን እንደቻሉ ቁሶች መጀመሪያ በአናቶሚ፣ ቀጥሎ ደሞ ባህላችን ውስጥ ያላቸውን ስፊ ቦታ ማጥናት አለብን:: (በአጠቃለይ ስለፊታችን ውበት ስናስብ ምን ማየትና ማጥናት እንዳለብን 'በራስ መተማመንና የፊት ጂኦሜትሪ' ንዑስ ምዕራፍ ውስጥ፣ 'ፊት' የተባለው ምዕራፍ (ምዕራፍ አራት) ውስጥ ያለውን አንባቢዬ ከዚህ ሃሳብ ጋር እንድታገናዝቢው እጠይቃለሁ)

ከንፈር ጡንቻ ነርቭና ስስ ቆዳ ነው:: *ኢንፌሪየር ላብያልና* (ለምቦጭ)፣ *ሱፒሪየር ላብያል* (ምንጭር) የተባሉ የተለያዩ ስሜቶችን ለመግለፅ የሚያገለግሉ ክፍሎች አሉት:: አንዳንድ ባህሎች ደሞ (ለምሳሌ ቻይና) በ***ፊት ንባብ*** በተለይ በ***ከንፈር ንባብ*** እጣ ፈንታ ይተነብያሉ ወይም ይጠነቁላሉ: የአንድ ሰው ወይም ሴትዮ ለምቦጭ ከወፈረ ማራኪ ተናጋሪ፣ ከቀጠነ ገለልተኛ ወይም ዐይነአፋር ወይም ሚስጢረኛ ተደርገው ይቆጠራሉ:: ይሄን የምጠቅሰው ትክክል ነው ብዬ ሳይሆን ከንፈር በማህረሰቦች ሕይወት ውስጥ የማይናቅ ስፍራ እንዳለው ለማሳየት ነው::

በልጅነታችን የከንፈር ቀለም ስለማይኖረን ወይም ስለማናገኝ ወይም ቤተሰቦቻችን ስለሚከለክሉን ፅገሬዳ እያፈረጥን ደሙን ስንቀባ ትዝ ይለኛል:: ይህችም ብልግና ተብላ እንዳትታወቅብን ስጋታችን ከፍተኛ ነበር:: እኛ እንዲህ በምንሆንበት ተስተካካይ ዘመን ሊዲያ ፍሊት የተባሉ አሜሪካዊ ሴትዮ The American frugal wife: dedicated to those who are not ashamed of economy (*ኀዘጋቢዋ የአሜሪካን የቤት እመቤት: ቁጠባ ለሚያሳፍራቸው የተሰጠ ስጦታ*) በተባለው በ1829 እንደገና 1880 በታተመው መፅሐፏ ከሰው ልጆች የሚወጣው የጆሮ ኩክ ለተሰነጣጠቀ ከንፈር መድሃኒት እንደሆነ ትጠቁማለች:: የጆሮ ኩክ እንደ ሰም ስለሚቆጠር (ከሰው የሚገኝ ሰም እንበለው) ሻካራ ነገር የማለስለስ ፀባይ አለው ተብሎ ይታመን ነበር:: የሆነ እውነትነት አለው:: ብዙ አሜሪካውያን የቤት እመቤቶች በዚህ ይገለገሉ ነበር:: ዛሬ ጊዜው ተለውጦአል:: አሁን አሁን ይሄ አስራር ቢቀፈን የተለየ ዘመን ውስጥ በመኖራችን ስለሆነ አይፈረድብንም::

እና ሌላ ጥያቄ ላቅርብና የጥንት ልምዳችንን እንደተቸሁት የዛሬውን የከንፈር ቅባቶችን ትክክለኛ መሆንና አለመሆን ልጠርጥር? የሆነ ጉድለት ይኖራቸው ይሆን? የከንፈር ቀለም ዕድሜው እንዲበረክት *እርሳስ፣ ካድምየም፣ ባዜቃና አንቲኖሚ* የተባሉ ንጥረ ነገሮች ወይም ኬሚካሎች ይገቡበታል:: እነዚህ ኬሚካሎች ከንፈርን ማሳመር ብቻ ሳይሆን እርግዝናን የማጨንገፍ፣ የወንድ ዘርን ቁጥር የማሳነስ፣ የአእምሮ ዝግመትና ሌላም አይነት የጤና እክል ያመጣሉ ተብሎ ይታመናል::

ጫቶን ብናየውም ሴት ልጆቻችን በከንፈሮቻቸው እንዳይተማመኑ፣ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው እንዲገምቱ፣ የተለያየ የስነልቡና ፕሮፓጋንዳ ሊያካሂድ የሚቻልበት ዘመን ላይ ነን:: ይሄን ምዕራፍ ያዘጋጀሁት የአንባቢን ትኩረት ስቤ ትርጉም ያለው ከንፈርን የማስዋብ ምርጫ ወይም እራስን የማስዋብ ቴክኒክና ስትራተጂ እንድናስብ ይገፋፋናል ብዬ በማመን ነው:: ለመሆኑ አሁን በአገራችን ያሉት ሊፒስቲኮች ከየት ይመጣሉ? ማነው የሚሰራቸው? የሚሰሩባቸው አካባቢ ከላይ የጠቀስኳቸው ኬሚካሎች እንዳይገቡበት ጥንቃቄ ይደረጋል? አይመስለኝም:: ያልመሰለኝ የሶስተኛው አለም አባልና የምንናቅ ሰዎች ስለሆንን ነው:: ለምሳሌ ሁሉም ሊፕስቲኮቻችን በሚያስብል መልክ የሚመጡት ከቻይና ነው:: የሚመጡትም ሺሲ ከተባለ ቦታ ነው:: አንድ ጊዜ በጋዜጣ እንዳነበብኩት በሺሲ ጠቅላይ ግዛት በባኦጂ ከተማ የሚገኘው ፋብሪካ በእርሳስ መርዝ ተበርዞ ነበር:: (እዚህ ላይ በትክክል ያ ከተማ ይሁን ወይም ሞክሼ አልመረመርኩም:: ነገር ግን የደረሰው አደጋ ሊፕስቲካችን ብልቃጥ ላይ ካለው የቦታ ስም ጋር አንድ ነው) በዚህም ምክንያት ፋብሪካው ተዘግቷል:: ለመሆኑ ይሄ ፋብሪካ የሰራው እርሳስ ለምን ፍጆታ እንደዋለ እናውቃለን? ለሊፕስቲክ እንደሆነ ብንጠረጥር፣ ሊፕስቲኩም በአብዛኛው የሚላከው ወደ አፍሪካ ነው ብለን ብንል፣ ከዚህም ውስጥ እኛ አለንበት ብለን ብንጠረጥር ተሳስተናል? ይሄን የንግድ ሥርአት የተከታተለ ሰው እንደማይኖር ሺህ ከመቶ እርግጠኛ ነኝ:: ሊፕስቲክ ገና ለገና 'እርሳስ አለበት' ብለው ገንዘብ ያወጡበትን እቃ እንዲሁ አይጥሉትምና ቻይናዎች የሚሸጡት እንደኛ ላሉ አገሮች ነው:: ነጋዴ ደሞ ገብጋባ እንጂ ሳይንቲስት አይደለም:: ጠቢባን ወይም ላብራቶሪ አጥተን ሳይሆን ይሄን ለመግዛት የሚገፋፋንን ለባዕድ ሽቀላ የሚሰግድ ስነልቡና ቀደም ብለን ስለፈጠርን ነው:: አንደኛ አትዮጵያዊ መልካችንን የሚጠሉ የራሳችን ልጃገረዶች እየተፈጠሩ ነው:: ሁለተኛ ይሄ ጥላቻችንን የሚያደንቅ ማህበረሰብና ተቃራኒ ፆታ እያበበና እያፈራ ነው:: ጤንነታችንን ከመጠበቅ ጋር እንድናምር የሚረዱንን ሊፕስቲኮች ከአገር በቀል ተክሎችና ቅመሞች ማዘጋጀት ግዴታችን ሳይሆን አይቀርም:: ከንፈሮቻችንን እናሳምራለን ብለን በካንሰር ለምን እንያዝ? ልጃገረዶቻችንስ ለምን መሃን ይሁኑ?..........ከዚህ ቀጥሎ ከንፈሮቻችንን እንዴት በቀላሉ አገራችን ባሉ ተክሎችና ቅመማት ልናሳምር እንደደምንችል አንዳንድ ሃሳብ አጋራችኋለሁ......) **(ይሄ የመፅሐፉ ክፍል በባካፋ ገፋፊነትና ጠቋሚነት በተለያዩ ኤፍ ኤም ሬድዮ ጣቢያዎችና መፅሔቶች ላይ ወጥቷል:: ወይዘሮ መቅረዝ በዚህ ምክንያት ስለ መፅሐፋቸው ሁለት ጊዜ በቲቪ፣ ሶስት ጊዜ በሬድዮ ተጋብዘው በሃሳባቸው አዲስነት አንድ ሰሞን የከተማው መነጋገሪያ ነበሩ::**

---

*

የወይዘሮ መቅረዝን የሊፒስቲክ ምዕራፍ በከፊል አንብቦ ናይሮቢ እስኪደርስ የሚያንገላታ እንግዳ ሃሳብ ውስጥ ገባ:: የሚቀጥለውን ምዕራፍ *('ስም ምንድነው?')* ማንበብ አላሰኘውም:: አጠቃላይ የመፅሐፉን መልዕክት ለመረዳት ብቻ መግቢያውንና አልፎ አልፎ አንዳንድ ንዑስ አርእስቶችን አነበበ:: ስለ ከንፈር፣ ስለ ቆዳ፣ ስለ ዐይን ሕክምና ብሎ ከፋፍሎ ዘመናዊ መድሃኒት ላይ ሂስ ሰርቶ አገርኛ መድህን መኖር እንዳለበት ይጠቁማል:: ጥቆማው ንግዱን እንደሚተችበት ቢያውቅም የወይዘሮዋ ሃሳብ ምን ያህል እርቆ እንደሚሄድ ገመተ:: የትም አይሄድም:: እንደ ብዙ ቁም ነገሮች ይጻፋል እንጂ የትም አይደርስም:: ምክንያቱም ሕብረተሰቡ በባህርዩ ተሻሚ እንደሆነ ያውቃል:: ሻሞ ይወዳል:: በመቀናናት የሚነቃነቅ ነው:: ከትልቁ እስከትንሹ ከደንቆሮው እስከ ተማረው በቅናት አጀንዳ የተወጠረ ነው:: ሁለቱ ጉብሎች በሊፕስቲኩ ካመኑ ሃያ ሁለቱ ሳለመበለጥ በፍጥነት ይከተላሉ:: ነጋዴ ሲሆን ያጋጠመው ማመን የከበደው መንጋነት ነው::

መፅሐፉ ተመቻችቶ የተቀመጠበት ዋናው መላምት ሃይማኖት ደደብ ስህተቶች እንደማያጣ ሳይንስም እንደዛ አይነት ነገር አያጣውም የሚል ነው:: የሁለቱ ልዩነቶች የተመሰረቱባቸው ቀኖናዎች እውነታን የሚያዩበትና የሚያጠኑበት መንገድ ቢለያይም ከመጠ'ርጠ'ር አያመልጡም:: የተቀመጠበት አይሮፕላን የሳይንስ ውጤት እንጂ የጸሎት እንዳልሆነ ድሮም ይረዳል:: በበረራው ወቅት ደህንነቱን ቢጠራጠር ከፈሪነቱ ብቻ ሳይሆን የሰውን ልጅ ፍፁምነት ከመጠራጠር የመጣ ነው:: ይህም ምንም አይደለም:: ቀስ ብሎ በጊዜ ሂደት ሳይንስን በራሱ የመቆጣጠሪያና መረጃ የማቅረብ ስልት ይፈታተነዋል:: ባካፋ

---

የዝግጅቶቹ አርዕስቶች በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ጋዜጠኞች የግል ፍላጎት እየተለዋወጡ ቀርበዋል: *ባህል መድሃኒቶች በዶክተር መቅረዝ አዝማች* ('ዶክተር ብላችሁ አትጥሩኝ: ወይዘሮ ይበቃኛል' ቢሉአቸውም) *ዘመናዊ መድሃኒትን የሸሹት ስፔሻሊስት ሐኪም ምን እንደሚሉ እንስማ* ('ነቀፋ እንጂ ሽሽት አይደለም' ቢሉም)

---

ከሃይማኖት ለመራቅ ቢለፋም ያደገበት ነውና ትንሽ ሲጨንቀው ወደ አምላክ ጉዩ ለልመና መንሸራተቱ አልቀረም:: ሆኖለት ግን አያውቅም:: ማለት አምኖና ጸልዮ ያገኘው ትርፍ ነገር የለም:: (*ባርያ የሆንክለት ሃይማኖት ራሱ ዘቅዝቆ በትንታ ቢገልህ ውሃ የማያቀርብ አምላክ የሚዘከርበት ከተማ ውስጥ የተወለደ ነው ልጅ ባካፉ::* አቡ ነበር እንደዛ የሚለው?):: ቅጠል በጥሶ አዳሪ ጠንቋይ ሀሁ አስቆጥሮትም ይሆናል:: አሁን ቢያንስ በልቡ ከሳይንስ ሸሽቶ የትም መሄድ አይፈልግም::

ለመሆኑ ለማን ለማን ይሆን ወይዘሮ መቅረዝ መፅሐፋቸውን ስጦታ የሰጡት? ለምን አቡን አንጓጠጡት? ባካፉን ቤተክርስቲያን ያገኙት ገጠመኝ ነው? የሚካፕ ነጋዴ መሆኑን ሰምተው ሊያሹዋጥጡት ከሆነስ? አፋቸው ደህና ለነበረ ጊዜ ሊፕስቲክ ተቀብተው ምሁር ከጠበሱበትና የሚፈልጉትን ጎረምሳ በከንፈራቸው ውበት ካጠመዱበት በሁዋላ ሌሎችን ልጃገረዶች ለመደበር ምን እንዲህ ይለፋሉ? ቆንጆና ሃብታም ዛሬ ተራክበው ነገ በካንሰር ቢያልቁ የጉዳቱ ሚዛን የሚወጣው በተደሳቾቹ ነው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር?

ባካፉን ታክሲ ከኤርፖርት ጭኖ ቀድሞ ወደ ተሰናዳለት *ዳውን ታውን ቦማ አን ሆቴል* አደረሰው:: አምስተኛ ፎቅ 505 ቁጥር ገብቶ ለግማሽ ሰአት ከነልብሱ አልጋ ላይ ወጥቶ አናወዘ:: ነውዙን አጠናቆ ካልሲውን ሲያወልቅ፣ ሸሚዙን ሲያወልቅ፣ ሱሪውን ሲያወልቅ፣ ክራቫቱን ወንበር መደገፊያ ላይ አመቻችቶ ሲያስቀምጥ፣ ፊቱንና ፂሙን ሲዳብስ፣ ሻወር ሲወስድ፣ ራሱን በፎጣ እያዳረቀ የሆቴሉን የናዝሬት ከተማ ጎዳናዎችን የመሰለውን የሆቴሉን ግቢ ሲያይ፣ ስለመቅረዝ እያሰበ ነበር፡ በልጅነቱ ከሚያውቀው ሰፈ ወንዳወንድ ፊታቸው አሁን እስከሚያውቀው እንደ ሳውዲአረቢያ እንስቶች በነጠላ ሂጃብ እስከተጋረዱበት ያለውን:: የጊዜ አስተላለፍ ፍጥነቱንም:: የሰዎችን የዝግመት ወይም ስርነቀል አለዋወጥ:: ከፊት ወደ ሁዋላ:: እልም ያለው ለሰይጣን ያቀነቅን የነበረው ዛሬ ለክርስቶስ ክበሮ ሲደልዝ:: እንደገናም ነገ በገበናሩ ለጋንጩር ሲዘምር:: ገብረክርስቶስ

የተባለ ልጅ ጠዋት ጊዮርጊስ ጸልዮ ማታ ሺሻ ጢስ ስር እንደ አብደላ ሲቀመጥ:: ወይዘሮ መቅረዝ ከሳይንስ ወደ ኢ-ሳይንስና ወደ አጃቢው ቅጠል ብጠሳ በዕድሜና በፀፀት መርከብ ላይ ሲንሳፈፉ::

ባካፋ በሃሳብ ሲንገላታ ስልክ ተደወለና ሪሴፕሽን ሰው እንደሚፈልገው ተነገረው:: ያለ ኮት በሸሚዝና በክራቫት ወደ ታች ለመውረድ አሳንሰር ውስጥ ገባ:: ሊፍቱ ባልጣመው የሽቶ መዓዛ የተሞላ ነው:: ትንፋሹን ውጦ ወለል ደረሰ:: አንድ ኬንያዊና ለወርልድ ባንክ የናይሮቢ ሕዝብ ግኑኝነት ሆኖ ከሚሰራው፣ የአዲስአባ አለቃው 'ሄነሪ' እያለ ስሙን ከሚያነሳው ቀጫጫ፣ መነፅራም ረዥም ፈረንጅ ጋር ተገናኘ:: እራሱን አስተዋወቃቸው: *ባካፋ መዝገቡ ዱባለ እባላለሁ፣ ከኢንተርናሽናል ዲቨሎፕመንት ባንክ ነው የመጣሁት፤ የተጋበዝኩበት ወረቀት ይቅርታ መኝታ ክፍሌ ውስጥ ነው::* ኬንያዊው ከባካፋ ፓስፖርቱን ተቀብሎ ወደ ውጭ ወጣ:: ከሆቴሉ መግቢያ ፊት ለፊት የቆመ ጥቁር ላንድሮቨር በር ከፈተና ተንጠራርቶ በጥቁር የላስቲክ ፎልደር የተቀመጠ ፋይል ከመሳቢያ አወጣ:: የሚገላለጥ ወረቀት ገላልጦ የሚያመሳክረውን አመሳክሮ ተመልሶ መጣና ሞቅ ባለ ድምጽ *እንኳን ደህና ገባህ አቶ ባካፋ* አለው:: ኬንያዊው ስሙ ፊሊፕ ሙኒራ ይባላል:: ሄነሪ የባካፋን *ማንነት ለማረጋገጥ* በተወሰደው ፍተሻ ማፈሩን ለመደበቅ ሳቅ አለ:: ከሆቴሉ ላውንጅ ሳይወጡ እዛው ቆመው ለጥቂት ደቂቃዎች ትናንሽ ወሬ ሲያወሩ ቆዩና ባካፋ ወደ አዲስአባ ስልክ ለመደወል እንዳሰበና ሞባይሉን እንዴት መጠቀም እንደሚችል ጠየቀ:: እንግሊዙ *እንዴት ይሄ ይጠፋሃል?* አይነት ገጹን ከስከሰና በስዋሂሊ ኬንያዊው እንዲያሳየው ነገረው:: በሩብ ሰአት ባካፋ ስልኩን አስተካክሎ አዲስአባ ጸሐፊው ትሩፋት ጋ ደወለ:: አላማው የሜካፕ ፓኬጁን ለጌርሳሞት እንዳትሰጣት ሊነግራት ነበር:: ገና ድምጹን ስትሰማ በሙሉ ስሜትና ኩራት:

--ያዘዝከኝን ያኔውኑ አድርጌአለሁ:: እዛ ፌቨን ለተባለችው ፓኬጁን ስሰጣት ሲቀናህ ጌርሳሞት እዛ ነበረች::

ባካፋ ስለተናደደ የሚለው አልነበረውም::

--ሰማኸኝ?

--ሰማሁ:: የስራ ችግር ካለ ቁጥሬን ሴቭ[25] አድርጊና ደውይልኝ:: ቻው:: ስልኩን ዘግቶ አክስቱ ጋ ደወለ::

--የእኔ ወርቅ ደህና ገባህ? ስለቴ ይሰራል አትጨነቅ:: ቶሎ ናልኝ:: ማልቀስ ጀመረች:: ደህና እንደሆነ ነግሮ፣ ናይሮቢ ደስ እንደሚል፣ ያልጠበቀው ብዛት ያላቸው የሐበሻ ሬስቶራንቶች እንዳሉ እና አሁን ወደ አንዱ እየሄደ እንደሆነ እውነቱንና ውሸቱን ደባልቆ ነግሮ ተሰናበታት:: ስልኩን ቶሎ ዘግቶ በመመለሱ የተደሰተው እንግሊዛዊ ሌላ ነገር ሳያወራ:

--እንዴት ነው? የምሳ ሰአት ነው አሁን እና ምን መብላት ትፈልጋለህ? *አድቬንቸር* ትወዳለህ?

--የምን *አድቬንቸር?*

--የምግብ:: ኩሊናሪ[26] አለና መነፅሩን ከሰርኑ ላይ ቶሎ ዝቅ አድርጎ እንደ መታዘብ አየውና ወደ ነበረበት መለሰው::

--ታዲያስ:: ያለ አድቬንቸር ሰው ይኖራል? *ኩሊናሪ አድቬንቸር ኢዝ ማይ ኔም*[27] አለ ባካፋ እንደ ታርዛን በሁለቱም እጆቹ ደረቱን እየመታ:: ከሆቴሉ የሪሴፕሽን ቦታ እያዘገሙ ወጡ:: ቀና ብሎ ወደ ኋላው የተከራዩለትን ሕንፃ አየ:: ሲገባ ልብ ያላለው የሕፃን ልጅ ቅዘን የመሰለ አስቀያሚ ቀለም የተቀባ ነው:: ባካፋ ሕፃን ልጅም የሕፃኑንም ቅዘን አይወድም:: ኪነሕንፃው በበለጨ ንግድ የጠገበ አንዱን የሐረር አውራጃ ከተማ ያስታውሳል::

ቆሞ የሚጠብቃቸው ላንድሮቨር መኪና ውስጥ ተሳፍረው (እሱ ከጀርባ) ዋናው መንገድ ውስጥ ገብተው ከሌሎች መኪኖች ጋር መሽቀዳደምና መጋፋት ከመጀመራቸው በፊት እንግሊዙ ወደ ላይ መነፅሩን አንስቶ ሙኒራን አየውና:

--ወደ *ካርኒቮር ሬስቶራንት* ላጋንታ እንሄዳለን አለ:: ወደ ባካፋ ዞር ብሎ ሬስቶራንቱ የናይሮቢ መዲባ ውስጥ ስለሆነ ትንሽ ለአንድ አስር ደቂቃ በሃይ ዌይ28 ላይ መንዳት እንዳለባቸው ነገረው:: ወደ ሙኒራ ዞር ብሎ በሞምባሳ መንገድ በአ104 ላይ እንዲነዳ አዘዘው::

--ለመሆኑ አዲስ እንዴት ነው? የአዲስአባ ሰው ነህ አይደለም?

---

--አዎ ተወልጄ ያደኩበት

--ጥሩ ጥሩ:: ካዛንቺስን፣ ሳር ቤትና ቦሌን የምወዳቸው ቦታዎች ናቸው:: አራት ጊዜ አዲስ ነበርኩ:: ከአዲስአባ የበለጠ የምወደው ከተማ ግን ናዝሬትን ነው:: ሞቅ ያለ የአየር ፀባይ እወዳለሁ......በነገራችን ላይ ሴሚናሩ እዚሁ ያረፍክበት ሆቴል አዳራሽ ነው የሚደረገው እና ጥሩ ነው አትንከራተትም አለ ሄንሪ::

ናይሮቢ ከአዲስአባ የተለየ ጠረን እንዳላት ባካፋ የተረዳው ያኔውኑ ነው:: ለባካፋ አዲስአባ ማለት ታቦት ማደሪያ ናት:: ታቦት ማደሪያ ስርጎድጓዳዎች ውስጥ አክርማ ለብሶ ገና ተመግምጎ ያላለቀ የሔዋን አደስ እንደ ጉም እንደተኛ ነው:: የታቦት ማደሪያውያን ሳንባ እንደ ንብ ሳንባ ነው፣ ይሄን ሁሉ ትንግርት ተንፍሰው አልጨረሱትም:: ምናልባት የጌርሳሞችን ከንፈር ያሳመረው እሱ ይሆናል:: አልፎ አልፎ የናይሮቢ ከተማ ጠረን በነፋስና በድምፅ እየተገፋ በመኪናው መስኮት ሲገባ የፈረንጁን የዲኦዶራንት መአዛ ይከናነብና ድርብ ባዕድ ድርብ ሶላቶ ይሆንበታል::

--ኢትዮጵያ እየተለወጠች ነው አለ እንግሊዙ ዞር ብሎ

--አዎ አለ ባካፋ በቀልበቢስ አፍ፣ ዐይኖቹን ከውጭው ትእይንት ሳያነሳ

ፈረንጁ ዞር ብሎ መነፅሩን ዝቅ አደረገና፣

--ታምናለህ?

--ምኑን? አለ ባካፋ በፍጥነት እ እ አዎ እንዴ፣ ማመን ሳይሆን ያየሁት ነው

--የእውነት? አለ ፈረንጁ ዞር ብሎ

መነፅሩን ዝቅ አድርጎ እያየው ሌላ መልስ ጠበቀ:: ባካፋ ከመመለስ ይልቅ የመነፅሩን ስርን በቀኝ እጁ አመልካች ጣት ወደ ታች ይዞ የምሩን ይሁን የውሸቱን የሚጠብቀው ሄንሪ ላይ በዝምታ አፈጠጠ:: ምን ፈለክ ሊለው ዳዳው:: አቡ ትዝ አለው:: አቡ እዚህ ቢኖር ወደደ:: አቡ በዛ ምላሱ ልክ ያስገባለት ነበር::

--ለቦታው አዲስ ነኝ እና ማተኮር አልቻልኩም:: ናይሮቢ የሚያምር ከተማ ነው::

ኬንያዊው ዞር ብሎ አየው፡፡--ለመሆኑ ጀብዱው ምን በመብላት ነው? አለ ቀጥሎ

--ታየዋለህ፡፡ እኛ ለምደነዋል፡፡ ከዛ አካባቢ የምትመጡ ሰዎች አንጉል ምግብ ትመርጣላችሁ፤ ለመሆኑ የአገራችሁ ብሄራዊ ምግብ ምንድነው? አለ ሄንሪ

--አዲስአባ ነበርክ አይደለ እንዴ? አላየኸውም?

--እሱ አልነበረም አለ ወደ ፊሊፕ እያሳየ፡፡

እየዋሸው እንደሆነ ቢገባውም ባካፋ ያልገባው መስሎ ቀጠለ፡

--ልዩ ዳቦ አለን እንጀራ የሚባል፡፡ ቆጮ የሚባል፡፡ ልዩ ናቸው፡፡ (*ከአገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ*......ተረትን እያሰበ) እዚህ ናይሮቢ አይጠፉም፡፡

--አይቼዋለሁ፡፡ ለእኔ በተለይ ለቱሪስቶች እንግዳ ነገር ነው፡፡ ሁለቱም እንግዳ ናቸው፡፡ አንዱ ስፖንጅ ይመስላል አንዱ ጣውላ ይመስላል፡፡ ያስፈራሉ አለ እንግሊዙ

እንጀራ ያስፈራል? 'ፊትህ ነው የሚያስፈራው' ሊለው ፈለገ፡፡ 'የአፍንጫህ ነገር ያስፈራል' ሊለው ፈለገ፡፡ 'ባርያ ሸቃይ' ሊለው ፈለገ፡፡ መስታወት ቤት ውስጥ እየኖረ የፈለገውን አይነት ድንጋይ ሁሉ ሰው ላይ እየወረወረ ማንም የማይነካው ነው አቶ ሄንሪ፡፡ ድሮ ብቻ ሳይሆን አሁንም አጠገቡ ሙኒራን የመሰለ ባርያ አለው፡፡ ሙኒራ መስመር የያዘ ባርያ ነው፡፡ ሙኒራ የበቃው ነው፡፡ ሙኒራ እንደውም አገር የለውም፡፡ ባካፋ በሙኒራ ተርታ የተሰለፈ መሰለው፡፡ በሄንሪ ትምክህት፣ በሙኒራ ተዝናንቶ ሹፌራና በመኪናው ዙሪያ ያለውን ጋጋታ ሲደማምረው ሊገልፀው የማይችል ግን እውን የሆነ የበላይነት በእሱ ላይ ያላቸው መሰሉት፡፡ ሊፈራ ግን አልፈለገም፡፡

--ለመጀመሪያ ለመጀመሪያማ የእግዜር ሳቅም እንግዳ ነው አለ ባካፋ.

ፈረንጁ ዞር ብሎ መነፅሩን ዝቅ አድርጎ አየውና በማሾፍ አይነት ፈገግ አለ፡፡ ግንባሩ ላይ የነበረውን በባካፋ አባባል ብቅ ያለውን የመደነቅ ስሜት በለንቋሳ ፀጉሩ ዋጠው፡፡ ስለነካካው ሳይሆን አይቀርም ባካፋ ለመጀመሪያ ጊዜ የዚህን ፈረንጅ ቢጫ፣ ረዣዥምና ሰፋፊ የሆኑ

ማውለቢያዎቹን አየ:: እንደዚህ አይነት ጥርስ ያላቸው ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆኑ ሲስቁ አፋቸውን በብርድልብስ ጋርደው ነው:: (ጥርስ እንዴት እንደ ብብት ይቆሸሻል?) ሊነግረው ይፈልጋል በዛ አይነት ጥርስ ከምትስቅ አልዲቫይ ሸለቆ ከተገኘው የዝንጀሮ ራስ ቅል ላይ መንጋጋ ነቅለህ ብታስተክል ይሻልሃል:: ስለፈራ አልተናገረም::

--የእናንተ አገር ሰዎች እኮ 'ልዩ ነን' ትላላችሁ አለ እንግሊዙ አዋቂ በሚያስመሰል ኮስታራ ድምጽ፣ በጣም እውነት በሚመስል የቃል አጣጣል::

--አልኩ አሁን በማርያም?

ሙኒራ ዞር ብሎ አየው

--ሴቶቹ ግን ቆንጆ ናቸው:: እዛ እያለሁ አራት ገርል ፍሬንድ ነበረኝ:: ገንዘብ ካዩ ሆሆ::

ሙኒራ መንገዱን ማየት ትቶ ባካፉን ዞር ብሎ በፈገግታ አየው::

--ገንዘብ ከሌለህ ዕድለቢስነት እንግሊዝም ይኖራል:: የአለም ባንክ ሪስትራክቸሪንግና የሴቶች ስራ አጥነት የተያያዘ ከሆነስ? ለመሆኑ ጠማማ የኢኮኖሚክ ፖሊሲ ስራ ላይ አውሉ ብላችሁ የምታስፈራሩት አዲስአባ ስትመጡ አራት ገርልፍሬንድ እንዲኖራችሁ ነው? ከዛ ደሞ የሴቶች መብት ምናምን እያላችሁ ጉራ አለ ባካፉ ድምፁ እየተንቀጠቀጠ:: ከፍርሃቱ ግን አልወጣም::

ሄንሪ ፊቱን ወደ ባካፉ አላዞረም:: አውራ ጎዳናውን እያየ በሳቅ ፈረሰ:: ባካፉ ግራ ገብቶት ማጅራቱ ላይ አፈጠጠ:: በዐይኖቹ ምን ያስቃል? የሚል ይመስላል:: መጽሐፍ ላይ ሳይሆን በድርጊት 'የዓለም መሳቂያ መሆን' ማለት ምን እንደሆነ ባካፉ ገና አልገባውም:: አንዳንዴ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ወይስ ስሟ ሲጠራ ሲሰሙ ለሃያ አራት ሰአት የሚስቁ እንዳሉ አልደረሰበትም:: የማይረባ ነገር እንድትሰራ ያማከሩህና ትንሽ ራቅ ብለው ያልነበሩበት መስለው ይስቃሉ:: ሲበላሽ የምትደርስበትን የራስህን ሰው ታማለህ:: ሲኒማቸው ምኑ የራስህን ሰው እንድታማ እንድትጠራጥር ይሰብክሃል::

ዋናውን መንገድ ትተው ወደ ግራ ተገነጠሉና ደናም አካባቢ ገቡ። ምናልባት ከሚያድርበት ሆቴል አንድ አስር ደቂቃ እንደነዱ አንድ ሜዳ መሃል ላይ የተጎለተ ቤት ግቢ ገቡና መኪናቸውን አቆሙ።

--እዚህ ነን። እዚህ ነን አለ ኬንያዊው ቦግ ባለ ነጭ ፈገግታ።

ባካፋ ሁለቱም ተከታትለው ከመኪናው እስኪወጡ ጠበቃቸውና ከኋላ ከኋላቸው እየተከተለ ሆቴሉ ዋና መግቢያ ደረሱ። በሩ ቅስት ላይ የነበልባል ቅርፅ አለ። የመግቢያው ዝባዝንኬ ባይኖር የውጭው የሕንፃ ኪነት የተራ ሬስቶራንት ሊሆን ምንም አይቀረውም። እዛ ላይ ደሞ በትልቁ የጥሬ እንጨት ስሌዳ ላይ ሜኑ ተሰቅሏል። ለአፍታ ባካፋ ቆሞ አነበበ: *የሜዳ አህያ ስጋ አሮስቶ፣ የበሬ ቆለጥ ጥብስ፣ የአዞ ስጋ ጥብስ፣ የበሬ ቅቅል፣ የሰጎን ስጋ ወዘተ*። ዋናው አዳራሽ ሲገባ በስጋ ጥብስ ጠረን ውስጥ እየተራመደ ነው። እዛ ቦታ በትክክል የእግዜር አየር የለም። ነጭና ጥቁር የለበሱ የሜዳ አህያ የመሰሉ አስተናጋጆች ወዲያ ወዲህ ይላሉ። ፈረንጁ ቦታ መረጠና ባካፋንና ሾፌሩን እንዲቀመጡ በስርአት እየጋበዘ:

--ይሄ በአለም የታወቀ ሬስቶራንት ነው አለ።

መልዕክቱ ለሙኒራ ሳይሆን ለእሱ እንደሆነ ባካፋ ይገባዋል። ባካፋ በሁለቱም ሰዎች እንዳልተደሰተ ለማሳየት ያለ የሌለውን የቲያትር ችሎታ ቢጠቀምም አልሆነለትም። በቸልታ የውሸቱን እንደ 'ገባኝ' ራሱን ነቀነቀ። ገና መኪናው ውስጥ ከመግባቱ ባይነጅሰው ኖሮ ባካፋ ብዙ ብዙ ማዳነቂያ ቃላት መናገሩ አይቀርም ነበር። ሁለት ደቂቃዎች ያህል በዝምታ እየተያዩ እንደተቀመጡ አንድ ወፍራም፣ በአንደበቱ ሊግባባቸው የሚንቀለቀል አሳላፊ ሜኑ አመጣላቸው። ሙኒራ ከተዘረዘሩት ምግቦች አንዱን ያኜውኑ አዘዘ። ባካፋ ምን እንዳዘዘ አልሰማውም፤ ቢሰማውም አልገባውም። ሙኒራ የባካፋን ግራ መጋባት አይቶ:

--ስጋ ነው ያዘዝኩት። በትክክል ቤቱ የስጋ ቤት ነው። የፈለከው አይነት አለ። አልፈራም ብለህ የለም? የቀጭኔ ስጋ፣ የአዞ ስጋ፣ የሰጎን ስጋ አለ። ጀብዱ ካላማረህ በሬና ፍየል አለ። ቤቱ ከ350 በላይ ሰው ይይዛል። ተጠቃሚዎቹ ቱሪስቶች፣ የኬንያ ኤሊቶችና ለስራ

ጉዳይ የመጡ የውጭ አገር ሰዎች ናቸው:: አንዳንዱ አይነት ስጋ የተከለከለ ቢሆንም በጥቁር ገበያ ይቸረቸራል:: ሕገወጥ ስለሆነ እሱን አንጋብዝህም አለ ራሱን በመነቅነቅ::

--ታውቃለህ የአፍሪካን ሙስና አለ እንግሊዛዊው ሜኑውን እያነበበ:: ልክ በማባለጉ ሙያ የእሱ ተሳታፊነትና አሠልጣኝነት እንዳሌለበት::

--እኔ ልዘዝልህ? አለ ሙኒራ

--መጀመሪያ ከአንተ እቀምሳለሁ:: እኔ የሰጎን እንቁላል ፍርፍር እሞክራለሁ አለ ባካፋ::

ዕንቁላል ፍርፍሩ ከመሃል ላይ ያለ ምግብ ስለመሰለው ነው:: የለመደው እንቁላልና ትልቁ የዶሮ አውሬ ሰጎን ሳይጣሉ ሳያስጨንቁት የሚኖሩበት:: ሄንሪ ያዘዘው የሆነ እንስሳ ጎድን ጥብስ ነው::

--ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን እንዴት ነው? የድርቅ ነገር:: በቂ ምግብ አለ? አገሪቷ ራሷን ችላለች? አለ ሄንሪ::

ባካፋ አልተመቸውም:: ኬንያዊው እንዳልሰማ ሁሉ ፊቱን ዞር አደረገና ከንፈሮቹን ለሳቅ ዘረጋ:: ፈረንጁ የራሱን አገር ጋዜጣና መፅሔት አንብቦ ማወቅ የሚችለውን ጉዳይ እዚህ ቦታ እሱን መጠየቁ፣ እሱን መጠየቁ ብቻ ሳይሆን ከጠየቀው በኋላ የመነፅሩን ስረስር በአመልካች ጣቱ ዝቅ አድርጎ እያየው አተኩሮ እያየው መልስ መጠበቁ አበሳጨው:: ከአሳሳፊ ጋር ያደረጉት ምግብ የማዘዝ ጨዋታ ጭቅጭቃቸውን በእንጭጩ የሚገለው መስሎት ነበር::

--ከእኔ ይልቅ አንተ ታውቃለህ አለ ባካፋ እንደ ሽሙጥ ጥርሱን ላለማየት ዐይኖቹን እዛና እዛ በመጣል::

ሙኒራ የጠበቀው ነገር እንደሆነ ሁሉ የሚነጋገሩትን እየሰማ ግን ላለመስማት የሚጥር ይመስላል:: እየተንጠራራ የማያስፈልገውን፣ ትቶአቸው የሄደውን አሳላፊ የሚፈልግም ይመስላል:: ሄንሪ ፈገግ ብሎ መነፅሩን እቦታው መለሰና:

--ኬንያ ከምስራቅ አፍሪካ ብቻ ሳይሆን ከብዙ አፍሪካ አገሮች የተሻለች ናት አለ:: እንዲህ ሲል ባካፋን አያየውም::

---

--እዚህ የመጣሁት ልበላ እንጂ አገር ላወዳድር አይደለም አለ ባካፋ:: ይሄን ካለ በሁዋላ መልሱ ትክክል አልመሰለውም:: እንግሊዙ በፍጥነት ዞር ብሎ፣ መነፅሩን ወረድ አድርጎ ሳቅ እያለ:

--አዎ እሱስ:: አዎ:: እሱስ ኬንያ የምግብ አገር ነው:: ሰዎቹ ደሞ ፍቅር ያውቃሉ:: ብዙ ጎሳ አለ ግን ተስማምተው ይኖራሉ

--አልገባኝም አለ ባካፋ ዞር ብሎ እያየው

--አንድ ህብረተሰብ የኬንያ አይነት ባህል ሲኖረው ለቢዝነስ የተመቸ ነው:: ቢዝነስ ከሌለ ደሞ አገር ረሃብተኛ ይሆናል አለ ፈገግ ብሎ:: ፈረንጁ የተናገረው እንዳደፋፈረው ሁሉ ኬንያዊው ባካፋን ዞር ብሎ አይቶ ፊቱ በፈገግታ ተበለቀጠ::

--አገራቸውን የሚወዱ የአፍሪካ መሪዎችን አትወዱም እኮ አለ ባካፋ

--የእንግሊዝ ወታደር እዚህ ኬንያ አይተሃል? አለና ፈረንጁ መነፅሩን ዝቅ አድርጎ ባካፋን አተኩሮ አየው:: *አስተያየቱ ምን ታወራለህ? አፍህን ያዝ፣ እ? ማነህ?* የሚል ይመስላል:: አስተያየቱ የተከፋ ጌታ ነው::

--እዚህ የመጣሁት ለመብላት ነው ለመጨቃጨቅ አይደለም አለ ባካፋ ፊቱን ፈረንጁ ወደ ሌለበት ወደ አጋጠመው አቅጣጫ አዙሮ::

--*ማን* ሰደበህ? አለ ኬንያዊው:: እናንተ *ኢትዮጵያውያን ሴንሲቲቭ* ናችሁ አለ በሳቅ *ታጅቦ*፣ ቀልድ እንዲመስልለት::

--እንጃ አለ ባካፋ ጨዋታውን በአጭር ለማስቀረት:: --እጄን መታጠብ አለብኝ ብሎ ከተቀመጠበት በፍጥነትና በድንገት ተነሳ:: መታጠብ ይገባው አይገባ'ው እንኳዋን አያውቅም:: ከተቀመጠበት ጠረጴዛ *በበቂ* ከራቀ በሁዋላ አንዱን አሳላፊ አቁሞ መፀዳጃ ቤቱ የት እንደሆነ ጠየቀው:: ክፍሉ ያለበትን ከእርቀት በጥቆማ አሳየው:: ወደ ተጠቆመበት አቅጣጫ እየሄደ እያለ ሸሚዙ ደረት ኪስ ያስቀመጠው ሞባይል ተንቀጠቀጠ:: ሞባይሉን ከኪሱ እያወጣ መታጠቢያ ቤት ገባ:: ትሩፋት ናት፣ መላክ ያልነበረባት አላስፈላጊ የሆነ የጽሑፍ መልዕክት ነው:: ስልኩን ዘግቶ መስታወት ፊት ቆሞ ውሃ ለቀቀ:: እጁን ታጠበና ክራቫቱን ከአንገቱ ላይ ፈቶ ሱሪ ኪሱ ከተተ:: ሰው እንደዛ መማታት

ፊልን አያውቅም:: አንድ እጁን ጨበጠና ክብነቱንና ጥንካሬነቱን በመስታወት ውስጥ አየው:: እዛ ሄንሪ አፍ ላይ ቢያርፍ የሚያደርሰው ጉዳት ከፎክላንድስ ጦርነት ያንሳል? ቡጢው ትልቅ ነው:: እንደውም ፊት ይመስላል፣ ፊትም ያከላል:: ደረት ይመስላል:: እውስጡ ልብ ይኖራል:: እናቱ ሊዲያ ያስተማረችው ግን እንዲደባደብ ሳይሆን ቢገባውም ያልገባው መስሎ እንዲሸሽ ነው:: ሊዲያ ያስተማረችው ፈሪ ተብሎ እንዳይሰየም አድርጎ ፈሪ መሆንን ነው:: እንኩዋን ይሄን ፈረንጅ ጌርሳሞትን እንዳገኛት ያኔውኑ ያልቀጠራት ፈርቶ ነው:: 'ጨዋ ለመሆን' ብሎ ሽሽቱን ያስማምር እንጂ ተንቦቅቡቆ ነው:: እራት በልተው ከተለያዩ ከሁለት ቀን በሁዋላ ጌርሳሞትን ልቅጠርሽ ቢላት እምቢ ትለው ነበር? ለአንድ ሰአት አጠገቡ ተቀምጣ በአንደበቱ ፀባዩን አሳምሮ ግን በልቡ ልብሷን እያወለቀ አልደፈራትም? የማያውቀውን ገላዋን በቅጥፈት ሃሳብ አድርጎ ፈጥሮ ከሁለመናዋ አልተራከበም? ጨዋ ቋንቋ አቅም አንሶት አገልግሎቱ ሲጠናቀቅ በእሱና በፈረንጁ ወይም በእሱና በሙኒራ መሃል የሚፈጠረው ባዶ ቦታ በግዴታ የሚሞላው በአንዳቸው ጥፊ ነው:: ግን ልብ የለውም:: የባካፋ ቡጢ ሁለቱንም መዘረር የሚችል አቅም አለው:: ልቡ ግን ወንድነት የለውም:: ክርስቲያንነት አይደለም:: ክርስቶስ ባለአለንጋም ነው:: ከመሃል የሚፈሰው የመታጠቢያ ቤቱ ውሃ ኩላሊቱን ቀስቅሶት ሳይሆን አይቀርም ሽንቱን ለመሽናት ዩሪናል ጋ ሄዶ ቆመ:: ስልጡንነትን ተከልሎ አደባባይ ያልወጣ ወንድ ፍርሃቱን የሽክላ ገበቴ ውስጥ ካልቀናውም ሱሪው ላይ ያፈሳል:: ጠረኑ እየቀፈፈው ሽንቶ ሲጨርስ በድጋሚ እጁን ታጥቦ ከመፀዳጃ ቤት ወጣ:: ጋባገሮቹ ወደ ተቀመጡበት ሲያይ አሳላፊዎች ትሪዎችን ይዘው መጥተው ጠረጴዛቸው ላይ ሲያኖሩ አየ:: በቀስታ እየተራመደ ሄደና እንዳልራበው ሁሉ ተረጋግቶ ተቀመጠ:: የሚያምሩ የስጋ ጥብስ አይነቶችና የእንቁላል ፍርፍሩ በተለያዩ ሰሃኖች ላይ ተዘርግተዋል:: የመብላት ሃሞቱ ተነሳሳ::

ኬንያዊው ያኔውኑ መብላት ጀምሮ የጎማ ቀረጢት የመሰለ ለምቦጩ በቅባትና በስጋ ወዝ አብለጨለጨ:: የባካፋን የተገረሙ ዐይኖች አይቶ ከእሱ ሰሃን ላይ እንዲበላ ጋበዘው:: ባካፋ በጥርጣሬና

በጥንቃቄ ከሙኒራ ማዕድ ከሚያጓጓ አጥንት ላይ የሚንቀጠቀጥ ለስላሳ ስጋ ቆርጦ ወደ አፉ አስገባ፡፡ እንግሊዛዊው ሊያደፋፍረው ጭንቅላቱን በአወንታ ነቀነቀ፡፡ ኬንያዊው የራሱን ስጋ በስሜት እያኘከ ባካፋን በፈገግታ ያየዋል፡፡ ባካፋ ስጋውን አላምጦ ከዋጠ በሁዋላ ስለጣፈጠው በአድናቆት የቀኝ እጁን አውራ ጣት ለሙኒራ ቀሰረለት፡፡ አውራ ጣቱን እንደቀሰረ ትንሽ ዞር አደረገው፡፡ አውራ ጣቱን በመገረም የሚያይ እየመሰለ ከወንበሩ ላይ ተንሸራቶ ወደቀ......

የባነነው ሆስፒታል አልጋ ላይ ነው፡፡ መተንፈስ አይችልም፡፡ ምላሱ እንደ መጅ ይከብደዋል፡፡ ለመጀመሪያ ዐይኖቹን ሲገልጥ ያየው ባለአበባ መጋረጃ አልፎ እንደ ጢስ የሚንሳፈፍ የብረት ጠረን ያለውን ብርሃን ነው፡፡ ፊት ለፊቱ ከአልጋው ግርጌ ወንበር ላይ ከሆቴል ተቀብሎ ወደ ሬስቶራንት የወሰደው ሙኒራ አለ፡፡ የሚታየው በስስ ጉም ውስጥ ነው፡፡

--ተርፈሃል አለው ዐይኖቻቸው ሲገናኙ፡፡ አይስቅም፡፡

ምን ሆንኩ? ለማለት ሞከረ ባካፋ፡፡ አፉ ፈዘዘበት፣ ቃል አልወጣውም፡፡

--ቢያንስ የዝንጀሮ ስጋ አለርጂ እንዳለብህ አውቀሃል፡፡

ሙኒራ የሆነ ነገር እያወራው እያለ እንቅልፍ የመሰለ ነገር ጣለው፡፡

ባካፋ ወደ አዲስአባ ሲመለስ ኬንያ ስላጋጠመው የምግብ መመረዝ ለሊዲያ አልነገራትም፡፡ እንዲህ መሆኑን ለማንም የታቦት ማደሪያ ሰው፣ ለማንም የመስሪያ ቤት ሰው፣ ለማንም የፊልም ተዋናይ አልነገረም፣ ለኢሳያስ እንኳን አልነገረም፡፡ በአጭሩ ማንም እሱን የሚቀርበውም ይሁን የሚርቀው ሰው አልሰማም፡፡ የሲኒማውንና የንግዱን ነገር ቦታ ቦታ አስይዞ ለጌርሳሞት ደወለላትና ሶሲ ካፌ ቀጠራት፡፡ የመጣችው ሰአቷን አክብራ ቢሆንም ያልጠበቀው ነገር አጋጠመው፡፡ የገጣሚው ስንኝ ተሸርፎ በሃሳቡ መጣ፡ ***በሞቀው ነፍሴ ውስጥ............አንድ ትልቅ በረድ መጥቶ ተወተፈ***[29]......ጥርሶቿን ብሬስ ተሰርታለች፡፡ እሷ እንዳለችው ለጥርሷ ብሬስ በተሰራች በሁለተኛው ቀን ከንፈሮቿ አብጠውና ቆስለው ሕመምተኛ ሆነች፡፡ ምክንያቱ

አይታወቅም:: ምክንያቱን ማንም አያውቅም:: ከንፈሮቿ ጥቁር፣ አባጣ፣ ከርፋፋ ሆነዋል:: የበቅሎ መስለዋል:: በሙሉ ልቧ አብራው ለመብላትና ለመጠጣት ፈቃደኛ አልሆነችም:: ሳይጠግት ሳይርባት ቀርቶ ሳይሆን የአፏ ሁኔታ ስላበሳጫት ነው:: ቢያንስ ባካፋ የገመተው እንደዚህ ነው:: ከእሷ ጋር ተቀምጦ የሚያስበው ልብሷን ስታወልቅ ምን እንደምትመስል መገመት ሳይሆን ናይሮቢ እያለ ያ እንግሊዛዊና ያ ኬንያዊው ራሳቸው ባለጌዎች ቢሆኑም የተረቡት ተረብ፣ ያሳገጡበት ልግጫ ነው:: ምናልባት የተራብነው ለመጥገብ የሚቋምጥ ግን ከራሱ የተጣላ ልብ ስላለን ነው? ሳይጎልብን እንደጎደለብን ስለሚሰራን ነው? የሚያጋጭ ነገር ሳይኖር ግጭት ስላፈቀርን ነው? ጌርሳሞት ለአፍታ ሰፊ መልዕክት ሆነችበት:: ሲሰነባበቱ ደግሞ እንደማያገኛት እያወቀ ነው::

--እደውልልሻለሁ ሲላት መለያየታቸው ፍፁም እንደሆን ከድምፁ ቅላፄ ገብቷታል::

ለአፏ ብቻ ‘ጥሩ’ አለች

‘ጥሩ’ ስትል ከንፈሮቿ አላሞጠሞጡም:: ‘ተረ’ ያለች መሰላት:: የተናገረችው ጠርቶ እንዳልተሰማ ጠርጥራ ጭንቅላቷን ላይና ታች ነቀነቀች::

## ፍቅርን 'እንካ' ያለችኝ አሥራት

ጠዋት ነው:: ከአድማስ ጥቁር መስመር ከፍ ብሎ ትልቅ ፈዛዛ ቢጫ ፀሐይ አለች:: ዙሪያዬን እንደ በጋ የሚሰራው ሕመምተኛ ሐምሌ ነው:: ወደ ፀሐይ ሳንጋጥጥ በቀዝቃዛ ጨረር አይኖቼ ይነዳሉ:: አንገቴን ወደ ትከሻዬ ሰብስቤ ጎንበስ ብዬ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ:: ራስ ምታት እንደተሞላ ጮጮ ይንጠኛል:: አልፎ አልፎ የማያምር የስካራም ምጥ እንደ ቅቤ ገፈት አወጣለሁ:: የአለመመቸት ትኩሳት ከውስጤ ይነሳል:: የምረግጠው መሬት ክርሳሴ የስኒከሬን ጫማ አልፎ ይሰማኛል:: ካናቴራዬን ቀበቶ ስር መሰቅሰቁ ከብርዱ አላዳነኝም:: ሁለቱንም እጆቼን የሱሪ ኪሶቼ ከትቼአለሁ:: በቀኝ እጄ፣ ኪሴ ውስጥ ባሉ ገላዬ ባሞቃቸው ሳንቲሞች እጫወታለሁ:: አልፎ አልፎ ጣቶቼን ዝቅ አድርጌ እየገፋሁ ከአመለመለ አፍረቴ ግለት እዋሳለሁ:: መንገዱ የመኪናዎች መተላለፊያ ቢሆንም ደህና ኮረኮንች እንኳን አይደለም:: እግዜር ይሁን ሰው የተከላቸው ድንጋዮች አልፎ አልፎ አሉ:: እነዚህ ከሌሎቹ ልሙጥ በመሆናቸው ለጭቃ ጊዜ እግር ማሳረፊያ፣ ከሚያበሰብስ ማጥ መሸሺያ ይሆናሉ:: በየመሃላቸው መወደስ የሚገባው ልፍስፍስ ከረምታችን ያሳመራቸው ድንክ የሳር ቁንጮዎች አሉ:: ጫማዎቻችን በጭቃ ሲቆሽሹ እነዚህ ላይ እንጠርጋቸዋለን:: በእርግጥ መንገዳችን በከርካሳ አሰራሩ ሊስትሮ የታጠቀ ነው:: ዛሬ 106ኛ ሃንግአቨሬ ላይ ነኝ:: የሰከርኩበትን ጊዜ ቆጥሬአለሁ:: በየሳምንቱ እየሰከርኩ ስገባ ሁለት አመት ሆነኝ:: አንዳንዴ በሚስጥር እንዲህ እንዳደርግ የአገሬ ጠላቶች ጠንቋይ መልምለው ያስደገሙብኝ ይመስለኛል::

መኖሪያ ቤቴ ታች ነው:: ታች ካሉት ቤቶች ሁሉ የሚለየው ግቢውና የግቢው በር ከሁሉም ትልቅ ስለሆነ ነው:: ቤቴ ውስጥ እኔን

ጨምሮ አራት ነን። ሌሎቹ አባባ፣ እማማና[20] ሙና[21] የምትባል ሰራተኛችን ናቸው። ቤቴ ካሉት ሰዎች ሁለቱ የሚነሱት ከጠዋቱ አስራ

---

[20] የአቡ እናት ወይዘሮ *መቅረዝ አዝማች* 'ዶክተር' ሲባሉ አይወዱም። የአንገት በላይ ሃኪም ሆነው አለርት ሆስፒታል ለአስርታት ሰርተዋል። አንድ ቀን እዛው ሆስፒታል ውስጥ ሊኖሊየም ወለል ላይ የፈሰሰ ዠራራ ቫዝሊን ረግጠው ሲወድቁ የብረት ጠረጴዛ ጠርዝ አገጫቸውን ገጭቶአቸው መንጋጋቸው ተሰበረ። ዓለም ባወቃቸው ባለሙያዎች ቀዶ ጥገና ቢደረግላቸውም፣ ስብራቱ ሊስተካከልላቸው ስላልቻለ ያለማቋረጥ ለሃጭ ይወርዳቸው ጀመር። የለሃጫቸውን መዝረክረክ ከተመልካች ለመጋረድ ማስክ ለብሶ መስራት አማሮአቸው ስራ አቋርጠው ጡረታ ወጡ። *የላጭን ልጅ ቅማል በላው* ሲሉ እንዲህ ነው። አደጋው በደረሰባቸው በሁለተኛው አመት በሆርሞን መበላሸት ሳይሆን አይቀርም በአገጫቸው ግራ በኩል ጥቂት ፀጉሮች አብቅለው ባለጺም ሆኑ። በነዚህ የገላ ለውጦች ሲያልፉ ቀድሞ ያልነበረባቸውን ጥቂት ፀባዮች አበጁ። አንደኛ ዝምተኛ ሆኑ፡ ድሮ መኪናቸውን አቁመው ነዳጅ እያቃጠሉ ረዥም ሰላምታ የማይሰጡት ሰፈረተኛ አልነበረም። አሁን አሁን ከቤታቸው ሲወጡ (ብዙ ጊዜ አይወጡም እንጂ) ላጋጠማቸው የሰፈር ሰው ቃል ሳይተነፍሱ አንገታቸውን እየሰበሩ በአጭሩ በአካል ንቅናቄ ብቻ ሰላም ይላሉ። ሰላምታቸውን ጠንከር ካደረጉም፣ መንገጭላቸውን በማፈር ደገፍ አድርገው ከተሸሸገ አፋቸው በግድ በሚሰማ ድምፅ *ደህና...... ደህና......ደህና ነህ? ደህና ነሽ? እግዜር ይመስገን......*ብለው አንገታቸውን ሰብረው እንደተገናኙ አንገታቸውን ሰብረው ያልፋሉ። ሁለተኛ፡ ቤተክርስቲያን ሳሚ መሆናቸው ሆኑ።። ሶስተኛ፡ ደሞ ከልጅነታቸው ጀምሮ ከተማሩት የሕክምና ሳይንስ ራቁ፡ ሃያ ስድስት አመታት የተማሩትና ለሃያ ስድስት አመታት የሰሩበት ሳይንስ የተሰበረ አገጫቸውን ሊያድናቸው አልቻለምና ቂም ያዙበት። ቢሆንም ሃኪምነታቸውን መሰረዝ ስላልቻሉ ቤት ከዋሉ ጀምሮ የተፃፈም ይሁን ያልተፃፈ ከአዋቂም ይሁን ከተርታ ሰፈረተኛ ስለአገር ቤት የመድሃኒት ጥበብ ለማወቅ ሀሰሳ ማድረግ ጀመሩ ('ምርምር' የሚባለው)። ባለቤታቸው አቶ ያዕቆብ ይሄን ፍላጎታቸውን እንደ ስንፈትና እንደ መበላሸት አላዩትም። እንደውም በየቦታው ከመንገድ ዳርም ይሁን ከመፅሐፍት ቤት ያገኙትን ስለባህላዊ መድሃኒት የዘገቡ መፅሐፍትን ያመጡላቸው ጀመር።

አቶ ያዕቆብ ቅር ያላቸው ነገር ቢኖር ወይዘሮ መቅረዝ 'ውዴ በዚህ አፌ አልስምህም' ማለታቸው ነበር። በእርግጥ ለሃጭ የሚያዝረበርብ አፍ መሳም የሚወድ ባይኖርም፣ *እንዴት እንዲህ ብዙ ዘመን አብረን ኖረን፣*

---

*አቡ የተባለ ረቂቅ አንጎል ያለው ልጅ ወልደን (ባህርዩ እንከናም ቢሆንም) አፏን ላጥላላባት?* በሚል የአፍቃሪ ይሉኝታ ሳይሆን አይቀርም ስለመሳሳማቸው አስፈላጊነት አቶ ያዕቆብ አዘውትረው ተከራከሯቸው:: እትዬ መቅረዝ በአቋማቸው ፀኑ::

ከታመሙ ጀምሮ ያዕቆብ ከሚስታቸው ጎን ነበሩ:: እንኳን አሁን ታመው ይቅርና ስፔሻላይዝ ሊያደርጉ ለትምህርት ሎንዶን የሄዱ ጊዜ ‘ብቻዋን እንዳትሆን’ ብለው የአመት ፈቃድ ወስደው ተከትለዋቸዋል:: መቅረዝ ከወጣትነታቸውም የያዕቆብን ፀባይና ገላ ይወዳሉ:: አንድ ልጃቸውን አቡን የሚወዱበት ምክንያት አንድ ሆኖ ብርቅ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ‘ቁርጥ አባቱን’ በመምሰሉ ነው::

አቶ ያዕቆብ አራት ኪሎ ዩንቨርሲቲ ስለሚያስተምሩ እንደገናም ለምርምር ስራ እዚያው ስለሚቆዩ ብዙ ጊዜ ቤት የሚመጡት ከምሽቱ ሦስትና አራት ሰአት በኋላ ነው:: አንዳንዴ ስራ ባይኖራቸውም ትንሽ ራሳቸውን ለማፍታታት ከወዳጆቻቸው ጋር አንድ ሁለት ሊሉ እዚሁ ሰፈር ያለው ደስ ባር ይቆያሉ:: ታዲያ ያዕቆብ ሲያመሹ ወይዘሮ መቅረዝ ይባልጉብኛል ብለው ባይጠረጥሩአቸውም ሙሉ ቀን ስላላዩአቸው ቅር ይላቸዋል:: በስሜታቸውና በምኞታቸው ካሉበት ጎትተው ማምጣት እንደሚችሉ ሁሉ የግቢ መብራት ያጠፉና በረንዳ ላይ የረጅ ዮፓርቲ ሶፋ አውጥተው ዘና ብለው ተቀምጠው እስኪመጡ ይጠብቁአቸዋል:: ዐይኖቻቸውን ጨፍነው በወጣትነታቸው ጊዜ አብረው ያደረጉትን ያስታውሳሉ:: ያዕቆብ በቁመት ከእሳቸው ቢያጥሩም ሃይለኛ ኩሩሩ ነበሩ:: ከሺህ የፍቅር ሩካቢያቸው ጥቂቶችን እያሰቡ ባላቸውን ማንም እንዳይነካባቸው ይሄን ፍትወተኛ ዘመን ይረግማሉ:: ምናልባት ከምሽቱ አራት፣ ሶስት ወይም ሶስት ተኩል ላይ በግቢያቸው አቅጣጫ የሚያውቋት ቶዮታ መኪና መብራት ይበራል:: ከአካሄዷ ከዛዛታዋ ከእእዋ ከሌላም አይነት የምጥ ድምፅዋና የእርጅና ለቅሶዋ የእሳቸው መሆኗን ያውቋታል:: ከሶፋቸው ላይ ቶሎ ተነስተው ቤት ይገባሉ:: ሙናን ‘ብይ መቀመጫውን አስገቢ እዚህ ነበረች አትበይ’ ይላሉ:: ብታውቅም ደግመውም ይነግሯታል:: ለምን ይደግሙታል? ያሉትን እንድታወራላቸው ሲነካኳት ነው? ‘መቅናቴን እኔ ከምነግረው ከአንቺ ይስማው’ ብለው ነው? መኝታ ቤት ገብተው የመስኮት መጋረጃ በትንሹ ከፍተው መኪናዋ ስትገባ ያያሉ::

ያዕቆብ ከመኪናዋ ዱብ ብለው ይወርዳሉ:: የመኪና ቁልፋቸውን ኪሳቸው እየከተቱ የመቅረዝ ጥበቃ ያልገባቸው መስለው ወደ በረንዳው ይወጣሉ፤ እዛም ሙናን ያገኙዋታል:: ከዛ ‘መቅረዝዬ ተኛች?’ ይላሉ:: ሙናም *ከተኙ ቆዩ* ትልና ውሸቷ እንዳይታወቅባት ፊቷን ቶሎ ታዞራለች:: ያዕቆብም አንገታቸውን ሰብረው ፈገግ ይሉና ቤት ይገባሉ::

---

ዋናው በር ሲከፈት መቅረዝ መስኮቱን ዘግተው፣ ጋቢያቸውን ጥለው አልጋቸው ውስጥ ይገቡና ያዕቆብ ራታቸውን በልተው ጨርሰው እስኪመጡ ይጠብቃሉ:: ይሄ ሁሉ ሲሆን መቅረዝ ማስካቸውን እንኳን አያነሱም:: ያዕቆብ አፋቸውን ተጣጥበው ልብሳቸውን ለውጠው መኝታ ቤት በፒጃማ ሲገቡ መቅረዝ በግድ በሚሰማ አማርኛና እንግሊዘኛ 'እንዳታበራብኝ ፕሊዝ የኮሪዶሩ መብራት ይበቃል ዛት ኢዝ ኢነፍ' ይሉአቸዋል:: እንዲህ ሲሆን ምን እንደታሰበ ስለሚገባቸው ያዕቆብ ፈገግ ይላሉ:: ፈገግታቸው ግን ገፃቸው ላይ አይቆይም:: ብርድልብሱን ከሚስታቸው ላይ ገፈው ጎናቸው ሲጋደሙ መጀመሪያ 'ደህና ዋልሽ እስኪ ያንን ጨርቅ ከአፍሽ ላይ ዞር አድርጊው ልስምሽ እፈልጋለሁ' ይላሉ:: መቅረዝ የእንግሊዘኛ መሃላቸውን ከነትርጉሙ ይደረድራሉ:: 'ሃው ሜኒ ታይምስ አይ ቶልድ ዩ......ነግሬህ ነግሬህ ስንቴ ልንገርህ? አይሆንም::' ያዕቆብ ወደ ነጩ ማስክ አቅጣጫ ገብስማ ከንፈራቸውን አሞጥሙጠው ሲያስግጉ መቅረዝ ፊታቸውን የበለጠ ይሸፍናሉ:: ያዕቆብ ሲጨንቃቸው 'ሳልስምሽ ማድረግ እኮ ቅር ይለኛል' ይሉና የመቅረዝን ቦርጭ ለአፍታ ዳብሰው ጡቶቻቸውን ነካክተው እላያቸው ላይ ይወጣሉ:: መቅረዝ ፊታቸውን አዙረው እያማጡ በፈረንጅኛ 'ሀ ሃኒ ሀሆሀ ሃ ዩ ኪሊንግ ሚ' እያሉ የፊታቸውም ማስክ በሚያደርጉት ንቅናቄ ተንሸራቶ እንዳይወርድ አድርገው ጠፍረው ይይዛሉ:: ሁልጊዜ የሚሉት እንግሊዘኛ ስለሆነ (ከታመሙ በፊትም) በደንብ ባይሰማ እንኳን አቶ ያዕቆብ ምን እንዳሉ ያውቃሉ:: ሁሉ ነገር ሲያልቅ ባል ቁና ቁና እየተነፈሱ ወደ ግራ ሲገለበጡ መቅረዝም በእፎይታ የአፋቸውን ማስክ ቶሎ አውርደው በምትኩ ደረቅ ፎጣ ይይዙና ወደ ቀኝ ዞር ይላሉ:: በዚህ መሃል አንዳንዴ ያፋቸው ነገር ከሌላው ጊዜ የበለጠ ገኖ ይሰማቸውና ቀላል ለቅሶ ያለቅሳሉ:: ያዕቆብ ፊታቸውን መልሰው ከጀርባቸው ያቅፉአቸውና ያባብሉአቸዋል:: እዛው በቅርብ ሩቅ እንደተነካኩ ይነጋል:: መቅረዝ በጠዋት ማስካቸውን አጥልቀው፣ በአፋቸው እህል ሳይገባ ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ::

[21] አቡ (የቤት ስሙ) የሙናን አባት ስም አያውቅም:: ባያውቅም አያፍርም:: ሙና የዶክተር መቅረዝ ጓደኛ ዘመድ ናት:: አቡ ዱርዬ ነው:: እኔ ሳውቀው ጠጥቶ ያልሰከረበት ካልሆነም ጫት ቅሞ ያልፈዘዘበት ጊዜ ያለ አይመስለኝም:: አባቴ የዶክተር መቅረዝ ጓደኛ ስለሆነ 'ልጄ አንቺ ጋ መጥቶ ይቆፍር፣ ጫት እየቃመ ከሚበላሽብኝ' ብሎአቸው በጋ ከሆነ በየሳምንቱ፣ ክረምት ከሆነ በየቀኑ ጓሮአቸውን እየመጣሁ አሳምራለሁ::

ዶክተር መቅረዝ ብዙ ጊዜ ቤት ውስጥ ወይም ግቢው ውስጥ ነጭ ለብሰው እንደመንፈስ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ይውላሉ:: ከምኖርበት ሰስት

ቁጥር ማዞሪያ ቶታል በጠዋት ከደረስኩ ከቤቱ በታች በመስመር ከበቀሉት ባዚንጀን ዛፎች ጥላ ስር ይመጡና የጀርባ መደገፊያ ያላት ከቦታዋ የማትነሳ ወንበር ላይ ጋለል ብለው ተቀምጠው አገኛቸዋለሁ:: አፋቸው ወይም አገጫቸው ሕመምተኛ ስለሆነ (አባባ የነገረኝ እንደዛ ነው) በነጠላ ጋርደው ለሁለት ምናምን ሰአቶች ያህል ይቀመጣሉ:: አንዳንዴ እንደሚነጋገሩ ሁሉ እጃቸውን እያነሱ ይጥላሉ:: ወይም እኔ አለሁበት ድረስ እስኪሰማ ይተነፍሳሉ:: ምናልባት በፈቃዳቸው ስራ በመልቀቃቸው ዛሬ ዛሬ እየተበሳጩ ይሆናል:: አንዳንድ ሰዎች ከሚወዱትና ብዙ ጊዜ ከሰሩበት ሙያ ሊላቀቁ በማይችሉበት መልክ የተያያዙ ይመስለኛል:: ቁጭት ደሞ ጥሩ አይደለም:: ሁለት ሰአት ምናምን ያህል አሉበት ቆይተው ከተቀመጡበት ይነሱና ልክ በዛች ደቂቃ እንዳዩኝ ሁሉ ግራ በሚያጋባ ድምጽ (ማንኳረፍና መከላተፍ በደባለቀ): 'ደህና አደርክ ልጅ ውድነህ? አባትህ ደህና ነው?' ብለው በግድ በሚሰማ ድምፅ ይጠይቁኛል::

አንድ ቀን ሰላምታቸውን በሰላምታ መልሼ ወደ ቁፋሮዬ እንደተመለስኩ እንዲህ አሉኝ: 'ይሄ ግቢ ደስ ይለኛል:: ይሄ ሁሉ የምናየው ግኡዝ የመሰለው ዛፍ፣ ቅጠልና ሳር መናገሪያ አፍ አለው:: የሚያዳምጠው ከተገኘ:: ይሄ ሁሉ የባዚንጀን ዛፍ በተለያየ ጊዜ የተለያየ አይነት ቋንቋና መልዕክት ያስተላልፋል:: ሲያፈራና ሲያብብ የተለያየ ቅላፄ አለው:: በጋና ክረምት የተለያየ መልዕክት አለው::' መቅረዝን በአደብ ሰማሁዋቸው:: ('አደብ' የአባቴ ቃል ነው:: ከዛ እስከ 'አደብ የለሽ') አባቴ *እሷ ሴትዮ አንዳንዴ ነካ ያደርጋታል:: የሆነ መስተማርር አለባት፡ የለቀቀችው ስራዋን የለቀቀች ዕለት ሳይሆን አይቀርም:: አውደልድላም ብሯን እንደመብላት:: ግራ የሆነች ሴትዮ:: ጥሩ ሴትዮ ባትሆን እንጃላት ያለኝ* ትዝ አለኝ:: አባባላቸውን ገና ሳመነዥክ መቅረዝ ጥለውኝ ቤታቸው ገቡ:: ቤታቸው ባለመረባ ነው:: *ሲመስለኝ ፎቁ ላይ ወጥተው ደመናዎች ሲነጋገሩ ይሰሙ* ይሆናል እላለሁ:: ታዲያ ከሄዱ በኋላ በውድ የቧንቧ ውሃ የመሰመሰ መሬት እየፎገልኩ ስለ ምላሳም ዛፎች፣ ስለ አንደበታም ነጭ ሽንኩርቶች፣ ስለ ለፍላፊ ጤናአዳሞች፣ ስለ አፋም በዚንጆኖች እያሰብኩ እስቃለሁ::

*ወደ ሙና ልምጣ:: ሙና አቡን ለአራት አመታት መግባዋለች::* ልብሱን አጥባለታለች:: ውሃ ቀድታለታለች:: አሁን አሁን በወዲያ በኩል መንገዱን ተሻግሮ በተቃራኒ አቅጣጫ ብታልፍ እጁን እንኳን አንስቶ ሰላም እንደማይላት አይነት ልጅ ናት ግን:: ቆይቷል አንድ ቀን ስራ እየሰራሁ እያለሁ በስሜ ጠራኝና ('ውድነህ!') ዞር ስል ወደ ሙና ጠቁሞ ጠቀሰኝ:: ምን ማለቱ እንደሆነ ገባኝ:: ሙና ደስ የምትል ልጅ ናት:: ከአዲስአባ አቧሬ ነው የመጣችው:: ቤተሰቦቿን ለመርዳት ከአስረኛ ከፍል

ትምህርቷን አቋርጣ እዚህ መኖር ጀመረች:: በትምህርታችን እኩል ብንሆንም አንድ አምስት አመታት ያህል በዕድሜ ሳትበልጠኝ አትቀርም:: ድንቡሼ ናት:: ቂጥዋ ጥብቅና ጉንጯም ነው:: ጡቶቿ ባሊ ምናምን ያክላሉ:: አፏ ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ረዥም ፊት ያላት ትመስላለች:: አፍ ምግብ ማስገቢያ ብቻ ሳይሆን የፊትን ቅጥ እንደሚያበጅ የገባኝ ያኔ ነው:: እና ስታወራ ያ ልሙጥ ረዥም ፊቷ ያልተጠበቀ ቦታ ላይ አግድም ስንጥቅ ያወጣል:: ካለለመድዋት ታስደነግጣለች:: እኔ ሁልጊዜ ገና በደንብ እንኳን ሳላውቃት *የእኛ ወንዶች በስማብ ይለክፉህና*......ስትል እሰማታለሁ:: እንዲህ ማለት የጀመረችው የድብቅ ወዳጅ ሆነን አንድ አራቴ ከወጣን በሁዋላ ነው:: አለርት ለሚሰራ አንድ ጎረምሳ ጀርመናዊ ለሦስት ወሮች የጭን ገረድ ነበረች:: አልፎ አልፎ የምትለብሰውን *ባየር ሙኒክ* የሚል ቲሸርት እሱ የሰጣት እንደሆነ ታወራለች:: ወዶኛል ብላ ስትጠብቅ ወደ አንዲት ከደቡብ አፍሪካ ወደ መጣች ነርስ ተሸጋገረ:: ጀርመኑን እኔ ጋ የምትጠቅስበት ምክንያት *ፈረንጅ ያደረጋትን ቆንጆ አፍሰሃልና ተረጋጋ* ይመስላል:: *ያ ፈረንጅ ሺህ ጊዜ ቢገለባብጠኝም ኦሪጂናሌ ነኝ* ማለትም ነው:: ሁለቱ እንዴት ይሆናል? ምንም የባዕድ ጓሮ ብቆፍር ደደብ አይደለሁም:: ከዕለታት አንድ ቀን ባልተዘጋ በር በጠራራ ፀሐይ ስናደርግ ከእንትኗ ጀምሮ ቂጥዋ የሚደርስ የሚቀፍ ስስ ከንፈር ያለው አፍ የመሰለ ጠባሳ አየሁ:: ጠባሳው ምንም አልነበረም:: ግን ጠባሳው እንደ ደህና ቆዳ ሽንጎበት ማብቀል ጀምሯል:: በአእምሮዬ የመጣው መጀመሪያ ጀርመናዊው ከዛ አቡ ነው:: ትዝ ይለኛል ለአቡ በፈገግታ ከሙና ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደ ጀመርኩ ስነግረው *ምንም አላጋጠመህም?* ያለኝ:: ያን ጊዜ ግራ ገብቶኝ ትከሻዬን ከፍ ዝቅ አደረኩ:: አቡ ተጫዋች በመሆኑ የጠቀሰኝ ለቀልድ እንጂ እንዲህ አይነት የዱርዬ ተንኮል ሊሰራኝ አቅዶ አልመሰለኝም ነበር:: ሙና በአፍ ልማድዋ *በመድሃኒያለም* (ቤተክርስቲያን ሄዳ አታውቅም) *የእኛ ወንዶች* የምትለው ሲበዛብኝ፣ እንደገናም የአቡ ሽወዳ አብሽቆኝ ለምን ከእሷ ጋር 'ዱቅዱቅ' እንዳቆምኩ *ቀስ ብዬ ነገርኳት* (ይሄ ነገር በአደብ ሊነገር ይችላል ጀለሶቼ ሆይ?) ማማ ትሙት ደደብ ነኝ:: ግን ስትነዘንዘኝስ:: *ዞር በል የሚደቀድቅ ይደቅድቅህ እቴ......ምን ይላል? እንዴ የት ያየኸውን ነው:: ስም አጥፊ:: ዝንጀሮ ነች እንዳትለኝ:: ፈለኩህ አልኩህ እንዴ? ለምን አትቀረቀርም? ወንድ ጠፋ አሉት በአገር:: አልቻልኩበትም አትልም:: አንዳንዱ እኮ ወንድ ይሁን ወንዳገረድ አይታወቅም:: ለመሆኑ አለህ? የእኛ አገር ወንዶች አማረሩኝ:: የት እንስደድላችሁ?* ይህቺ ዝምተኛ የመሰለች ጠባሳም የሴት አፈሉ በናጨርቷ ካናጠበችኝ በኋላ ስስ ከንፈር ያለው ሰው ሁሉ ያንቦቀቡቀኝ ጀመር::

ሁለት ሰአት ላይ ነው:: እነዚህም እማማና ሰራተኛዋ ሙና ናቸው:: በር ሳንኳኳ የሚከፍቱልኝ ወይ እማማ ናት ወይ ሙና ናት:: ውጭ ሳድር ረስቼ ስልክ ካልደወልኩ ግን ቀድማ የምትከፍትልኝ ብዙ ጊዜ እማማ ናት:: እናቴ አደጋ ይደርስበታል ብላ ስለምትፈራ እራሴም ሳላውቅ አደጋ ይደርስብኛል እያልኩ መፍራት ጀምሬአለሁ:: እማማ ቦቅቧቃ ናት:: እማማ በር ከከፈተች አንዴ ብቻ ፊቴን ታይና በሩን እንደከፈተችው ትታ ጭንቅላቷን ወደ መሬት ሰብራ የመልስ መንገዷን ትጀምራለች:: ያለ ወንጀለኛነት ስሜት በሩን እኔው እራሴ እዘጋዋለሁ:: እማማ መናገርና ብዙ መብላት አትወድም:: የእማማን አፍ ከፍተን ብናይ ሳቅ አናገኝም:: አፏን በጋቢዋ ጋርዳ (አፏን ያማታል) አንገቷን ሰብራ ስትሄድ በጭንቅላቷ ንቅናቄ ከባድ የትዝብት ዲስኩር ታደርጋለች:: የእማማ ምላስ ይሄ ነው:: ልዕለ ቋንቋም ነው:: ወደ እንግሊዘኛ ወደ እብራይስጥ ወደ ፋርስ በቀላሉ ይተረጎማል:: ማንም በማይገባው እኔን ሊመዘምዘኝ በሚለፋ ድምጽ በሌለው ቀበሌኛዋ *ምን ሳድርግህ?* እያለችኝ ይሆናል:: እናቴ ሜዲካል ዶክተር ያውም የአንገት በላይ ስፔሻሊስት ብትሆንም ዘመናዊና ፈረንጃዊ ነገሯን ማጠፋፋት ከጀመረች ሦስት አመታት ሆኖአታል::

እማማ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የባህል መድሃኒት ሰብሳቢና አጥኚ *ሆሚኦፓቲስት*[30] ሆናለች:: አሁን አሁን እንደውም ዳማ ከሴ የምታዝ፣ ጉንፋን ላመማቸው ሰዎች ባሕር ዛፍ እንዲታጠኑ የምትመክር ደብተራ ሆናለች:: ከጥቂት አመታት በፊት ፀጉሯን ትተኩስ ነበር:: አሁን አሁን አየር የማያስገባ ስፌት የመሰለ የጉንጉን አይነት ትሰራለች:: ከሳይንሳዊው አለም እርቃ አገራዊ መድሃኒተኛ መሆኗ ለእኔ ለመጀመሪያ አድናቂዋ ከብዶኛል:: እንቅልፍ እምቢ ሲለኝ የምታዝልኝ ቫሊዩም መሆኑ ቀርቶ ወተት በማር ሆኗል:: ተኮሳትሬ ካየችኝ እንዲያረጋጋኝ የጠስኝ ሻይ እንድታፈላልኝ ሙናን ታዛታለች:: አትክልተኛ ቀጥራ ግቢያችንን በአሪቲ፣ በጤና አዳም፣ በዝንጅብል፣ በዕፀ ፍሕሶ፣ በነጭ ሽንኩርትና በዳማከሴ እየሞላችው ነው:: ታዲያ ስራዋ የሁዋልዮሽ ኢቮሉሽን ይመስለኛል:: ባሕር ትተው የመጡ

እንስሳት ወደ ባሕር ሲመለሱ:: ፍናወት ቢስ የዛሬ ዘመን ሃና የተባለች ቆንጆ ወይም አበባ የመሰለ ከንፈር ያላት ጌርሳሞት ኮላሴ አፋር ሃዳር ወርዷ ዛፍ ለዛፍ እየዘለለች እንደ ድንቅነሽ አፈንዳጅ ሲያደርጋት ማለት ነው:: እማማ ዛሬ የኮባው ሰንበር ከሚታይ ንፁህ ድፎ ዳቦ አመድ እንደ ላስቲክ የለበሰ ርሚጦ ትመርጣለች:: አመድ ለጤና ጥሩ ነው ብላ:: ታዲያ ይሄ ሕመም አይደለም? ለነጭ ጤፍ እንጀራ ሳይሆን ለጥቁር ጤፍ እንጀራ ታዳላለች:: ጥቁር ጤፍ ተፈርፍሮ ሲከመር ቤት ለመለሰኛ የተዘጋጀ ጭቃ የሚመስለው እኔ ብቻ አይደለሁም:: እማማ የባህል *አታቪዝም* ውስጥ ገብታለች:: ከእሷ የቀሩኝ የዘመናዊነቷ ምልክቶቿ ከፍ ያለ የጡረታ ገንዘቧ፣ እናቱ 'ዶክተር ናት' ተብዬ ጉራ ሲነስንሰልኝና የእንግሊዘኛና የፈረንሳይኛ ጉራማይሌዋ ናቸው (አምሽቼ ስመጣ አንዳንዴ why do you do this to me? (ለምን ታስቸግረኛለህ?) እና Pour quoi? (ለምን?) ስትል ነው:: ድሮ የአማርኛ ስድቧ ውስጥ *ድራሽቢስ* የሚለው ቃል አይጠፋም ነበር:: ድራሽቢስ የምትወደው ስድብ ቢሆንም ዛሬ ማለት አትልም (እንግሊዘኛ አለው?):: ሳላበሳጫት ቀርቼና በአማርኛ መናገር ደብሯት ሳይሆን በታመመ አፏ ስትናገር ደስ የማይል ድምፅ ስለሚወጣት ይሆናል:: ከእማማ የወረስኩአቸው ዞማዋን፣ ቁመቴን፣ መልኳንና የአፒታይቷን አቅም ነው:: ከአባቴ የወሰድኩት ወንዳወንድ የሚያስመስለኝ እናቴ አንዳንዴ ልታጫውተኝ ስትፈልግ ጎተት አድርጋ *ዮ አር ላይክ ዩር ዳድ* ('እንደ አባትህ ነህ') ብላ ትስመው የነበረው ለምቦጬ ነው:: መልኬ አባቴን የሚመስለው በአፌ ብቻ ነው:: ትንሽ ይገርማል:: በአፌ መልክ ብቻ በእኔና በእሷ መሃል ማናችንም ልንደፍነው የማንችል የተጨረሰ የዘረመል እርቀት አለ:: 'አቡ' ብላ የምትጠራኝ እናቴ ናት:: *አቡ* ስትለኝ ያረጀች ሕፃን ልጅ ትመስላለች:: ፊቷ ጎራዳና ክብ፣ ቆዳዋ ለስላሳ፣ አፏና ከንፈሮቿ ትናንሽ ነበሩ:: በመታመሟ ታባባኛለች:: ከታመመችና ስራ ካቆመች በኋላ አንዳንዴ ሳቅፋት የምትሸተኝ ሽቶ ሽቶ ሳይሆን ማድቤትና ክሊኒክ ነው:: ጡረታ ወጥታ ንፁህ የታቦት ማደሪያ አየር ቢነፍስባትም እስከ አሁን የሰላሳ አምስት አመታት የሆስፒታል ጠረን በቆዳዋ ስርጎ ገብቶ ከደሟ ጋር እየፈሰሰ ነው::

---

ታዲያ ሙና በር ልትከፍትልኝ ባትመጣም ማድቤት በር ላይ በሚበስል የቁርስ ጢስና ጠረን መሃል እንደ ሳጥናኤል ቆማ ትጠብቀኛለች:: *እንኳን ደህና መጣህ* ልትል ሳይሆን ዱርዬኔቴን ልትመዘግብ ነው:: ቤታችን ስራ ከጀመረች አራት አመት አልፏታል:: ሙናን ከሶስት አመታት በፊት በሩካቤ ስጋ አውቄአታለሁ:: በትክክል ልበለውና በስካሬ ባሳብብም ደፍሬአታለሁ:: እንዲህም አድርጌ የደፈርኳት አልመሰለኝም:: እንዳይመስልም ሞክራለች:: ደስ የሚል ቂጥና አወራር ያላት ድቡልቡል ሴት ናት:: የምር ጠንካራ ናት:: እምቢ ብላኝ ተጋፍታኝ በመደባደብ ቄንጥ አሸንፌአት ከላይዋ ልነሳ ስል *በእትዬ መቅረዝ ሞት ቆይ* አለችኝ:: ስሙ መድፈር ቢባልም ይሄ አባባሏ እስከዛሬ በቀፋፊ ስራዬ እንዳላፍር አድርጎኛል:: የሚገርመው ግን ከዛን ቀን በሁዋላ አልደረስኩባትም:: ተመልሼ እንድመጣ ግን በአይኖቿ፣ በድርጊቷና በመሳሰለ የድሪያ ጥቆማ *የማማለያ አስቴቲክስ*[31] ሞክራኝ ሞካክራኝ እምቢ ሰላልኳትና ተስፋ ስለቆረጠች የቀራት ነገር ሰክሬ ስመጣ ጠብቃ ሰው ሰቅዬ እንደመጣሁ ሁሉ ማድቤት በር ላይ ቆማ ሰካራሙ አቡ፣ ሰካራሙ ራሚሱ፣ ከእናቱ ኋላ ኋላ ዐይኖቹ ቀልተው ከንፈሮቹ ደርቀው፣ ፀጉሩ ተሞነጫጭሮ ጦል ጦል እያለ ሲመጣ ማየት ነው:: እና በዛ የገረድ ትኩረቷ እኔ ብቻ የሚገባኝን *የማያልፍልህ ሰካራም፣ ወራዳ ፣አርጅቶም እናቱን የሚያስቸግር* እንደምትል አውቃለሁ:: የማላውቅ ብመስልም እንዳውቅ ትለፋለች:: ብዙ እንዳትጥር የአራዳ ልጅ ነኝና ቀድሜ አውቅላታለሁ::

ተመልሼ ያልሄድኩባት ግን (ሚስጢር ላውጣና) ከእንትኗ አጠገብ ግራ ጭኗ ላይ ሰፊ ጥቁር አፍ የመሰለ ጎድጓዳ ጠባሳ ስላየሁባት ነው:: ያን ቀን የጀመርኩትን ልጨርስ ብዬ እንጂ ልክ መርፌና ክር እንደሆንን አጠገቤ ውይይት ታክሲ መጥቶ ቢቆም እተንጋለለችበት ትቼአት ወደ ወለቴ ሱቅ ተሳፍሬ እሄድ ነበር::

እንደ ፀባዬ አቀርቅሬ እየተራመድኩ እያለሁ ፊትለፊቴ ኮቴ ሰማሁ:: ልብ ያልኩት ስደርስ ነውና ቀና ብዬ ማየት አልፈለኩም:: ፍጥነቴን ቀነስኩ:: መንገዱ ሰፊ ቢሆንም የሚመቸው ባለሁበት ጠርዝ

---

ነው:: መደንቃቀፍ አልፈልግም:: መጀመሪያ ቀይ ሸራ ጫማ ውስጥ ያሉ ቀጫጫ እግሮች አየሁ:: የሸራ ጫማው ሲር ንጣቱ እርጎ ይመስላል:: ከዛ ከፍ ብሎ ጥቁር *ታይት*:: እዛ ውስጥ ያሉት እግሮች የተመለመለ አጣና ይመስላሉ:: ከዛ ከፍ ብሎ ከባቶቹ ለአመል የሰፉ ጭኖች:: ከዛ ላይ የካኪ ቀለም ያለው የካፖርት ደርዝ:: ከዛ ካፖርቱ ወገብ ላይ ያለው ግራና ቀኝ የተንዘላዘለ መቀነት:: ከዛ ክርኖች፣ ከዛ ጠባብ ትከሻ፣ ከዛ ነጭ ባንዳና:: ከባንዳናው በላይ ቀይ ጣሪያ ያለው የዳኒ *ግሮሰሪ* ሕንፃ:: ወጣት ሴት መሆኗ ግልፅ ነው:: ምክንያቱም የዐይኖቼን ትኩረት ከታች ወደ ላይ ስጎተት ያየሁት ንቅናቄ የሌለው ደረቅ የሆነ ቡጢ የሚያክል ቂጥ ነው:: በአእምሮዬም *ይሄ ነገር ለምን ትንሽ እንኳን አይንቃነቅም?* እላለሁ:: በከፊል ያለሁበትን ሁኔታ ለመደበቅ በከፊል ላለመንቀልቀል ፍጥነቴን ከቀድሞው የበለጠ ቀንሼ ኋላ ኋላዋን ስሄድ በድንገት ቆመችና እንዳልፍ አይነት መንገድ ለቀቀችልኝ:: በጐንዋ እያለፍኩ ዐይኖቼን ለዘበት ጣል አደረኩ:: እሷም ጣል አደረገች::

–*ታዲያስ* አቡ! አለች

በትክክል ዞር አልኩ::

–ሃይ! *ታዲያስ* ጌርሳ!

ባንዳናዋ ስር የተሞነጫጨረ ፀጉር አለ:: ከዛ ጠባብ ግንባር:: ከዛ ስር ምናልባት ሰላሳ ፀጉሮች ያሉዋቸው የቅንድብ ጭረቶች፣ ከዛ ገና በብርዳም ጠዋት ሰርኑ የሚያብለጨልጭ አጥንታም አፍንጫ:: ደሞ ከዛ ስር *የታመምኩለት* አፏ፣ ወደ አፏ እያሳዩ 'ይሄ ለመሆኑ ምንድነው?' ቢሉኝ *ወይን የተሾመ ዕዋ ነው* እላለሁ::

–በሌሊት ምን ትሰሪያለሽ?

ይሄን ጥያቄ እንኳን የጠየቅኋት በዚያን አፍታ፡ *ከንፈሮችሽ ለምን እንዲህ ያምራሉ? ስለምን አፍሽን ላይ ሁልጊዜ እደነግጣለሁ? ስለምን ተደናበርኩስ? ሃንግአቨሬስ ለቀቀኝ?* አምልጦኝ ላለማለት ነበር::

–አንተስ በሌሊት?

–ሃሃሃ እውር ሳቅ ወረወርኩ:: –በቃ አንቺ ሰው አላናገር አልሽ:: ግን ወደየት ነሽ?

---

--ፋርማሲ እማማ ራሷን አሟት መድሃኒት ልገዛ

*ከየት ነው?* ብላ አላፋጠጠችኝም:: ዱርዬነቴ በብዙ ሰዎች ዘንድ ይታወቃል:: ባይታወቅም አሁን ፊቴ ላይና የምነሰንሰው የገላዬ ጠረን ውስጥ ደምቆ ተፅፏል:: መንገዷን እንዳትቀጥል አይነት እየሳቅሁ ፊቷ ለፊቷ ተገትሬ አቆምኳት::

--ምነው አቡ? እየሄድን እናውራ

--መድሃኒት ቤቱ ልትደርሺ ነዋ

--ጊዜ የለኝማ

--እኔም እኮ......አይመቸኝም:: አንድ ነገር ልንገርሽ......ታውቂያለሽ በቅርብ የኢሕአዴግ ፕሬዝዳንት ሁን ሲሉኝ ከፈለጋችሁ እሰሩኝ እንጂ ከጌርሳሞት ጋር ተማክሬ *እሺ ሁን በቂ ጊዜ አለህ ለአገርህ አውለው* ካለችኝ ነው፤ ከእሷ ጋር የማሳልፈው ጊዜ ብዙ ነው ምናምን ብዬአቸው ኢሕአዴግ ተደበረ:: ይሄ አሁን ያለውን ሰውዬ በእኔ ምትክ መረጡ::

--ሂሂ ታሾፋለህ:: መድሃኒት ገዝቼ ናዝሬት እሄዳለሁ:: የሐኪም ቀጠሮ ስለአለብኝ እቸኩላለሁ

--ምን ሆንሽ?

--ለአንድ ጉዳይ:: አይነገርም:: ትንሽ ከአዲስአባ ይረክሳል እዛ::

--እሺ ግን የምር ደህና ነሽ?

--የምር ደህና ነኝ

ለአፍታ ሳቅሁና አሁን ልንገራት አልንገራት እያልኩ ሳስብ ፋርማሲው በር ደረስን::

--ላጋዛሽ?

--ግድየለም ግባና ተኛ

--ሃሃሃሃ

ለሰኮንዶች ተፋጠን ቆምን:: ለማሳሳቅ መጣሬ ፍላጎቴን ሊያስፈፅም እንደማይችል ገብቶኛል::

--እንኳን ናዝሬት አንታርክቲካ ሄደሽ እስክትመጪ እጠብቅሻለሁ የምር:: ተረሳሳን እኮ፣ ለምን እንደዋወልም?

--ምነው እስከዚህ የሚያስዋሽ ነገር የለም አለችና ሞባይሏን ከካቦርታዋ ግራ ኪስ አወጣችና የምትነካካውን ነካከታ

--አንቺን በተመለከተ በሕልሜ እንኳዋን ብዋሽ ደንግጬ እነቃለሁ

--ሂሂሂ አይ አቡ:: ይልቁን ቁጥርህን ፃፍልኝ:: ያን ቀን እማማ ነጥቃ ስናወራ ስረዘችብኝ::

ተቀበልኩና ቁጥሬንና ስሜን ሞልቼ ሰጠኋት:: ቁጥሩን አይታ:

--ወላሂ እደውላለሁ አለችና አድሮ ወደ ነጋበት እኔን መሰል ፋርማሲ ለመግባት ፊቷን አዙራ ደረጃ ተፈናጠጠች:: ባትመልስልኝም ስላምታ ሰጠኋትና ወደ ቤቴ በፍጥነት መራመድ ጀመርኩ::

ሙና በር ከፈተች:: *ደህና አደርክ?* እንኳዋን አላለችኝም:: አላልኳትም:: 'እማማ ሲጠብቁህ ቆይተው ቤተክርስቲያን ሄዱ' አለች:: አልመለስኩላትም:: ሌሎች ሰዎች ቤተክርስቲያን በመመላለሳቸው ባይመለከተኝም እኔን ይደክመኛል:: የሐበሻ ሃይማኖተኞች የቀራቸው ነገር በጸሎት ሃይል ሽሮ ወጣቸውን በመልአክ ማሰራት ነው:: ፈጣሪ የሚወዳቸው ከሆነ የሚፈልጉትን ሳይለምኑት አይሰጣቸውም? ፈጣሪ እንደ ምድራዊ ሹም ለምን ልምምጥና ደጅ ጥናት ይፈልጋል? ይሄኔ ሰዎቹ ደጀሰላም ገብተው ደጋግመው በቁስ የሚጠዘጥዙት እሱ ያመጣውን እሱ እስከሚመልሰው የተባለውን አረፍተነገር ነው:: ሃይማኖት ተስማምተን ስልጣኔ ብለን የተቀበልነው በርጫ ነገር ነው:: መኝታ ቤቴ ስገባ የተለመደው ውሃ በጠርሙስ የለም:: ተመልሼ ሙናን ጠራኋትና የምጠጣውን ውሃ እንድታመጣልኝ ነገርኳት:: ገና ልብሴን አውልቄ በውስጥ ሱሪ አልጋዬ ላይ እንደተቀመጥኩ አዞረኝ:: ውሃ መጠጣት ግን አለብኝ:: ሙና ጠርሙስ ይዛ ገባች:: እጅዋም ጠርሙሱም ውሃ ያንጠባጥባሉ:: ረስታ አሁን መቅዳቷ ነው:: እግሮቼ መሃል ምን ልስራ ብሎ እንደሆነ አላውቅም የውስጥ ሱሪዬ ፍየል የደበቀሁ ያህል አብጦአል:: ልብ አላልኩም:: ሙና እዛ እያየች ፈገግ ብላ ደሞ እንደ አፈረች ሁሉ ፊቷን ቶሎ መለሰች:: ቢደክመኝም አሳፍሮኝ ትራስ ጎትቼ አለበስኩት:: ጠርሙሱን ጠረጴዛ ላይ የሚያስቀምጠው እጇ እርጥበቱና ቅዝቃዜው እንደነካችኝ ሁሉ

በሁለመናዬ ተሰማኝ:: ትራሴጌዬ አጠገብ ያለው ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ እንደወጣች በጀርባዬ አልጋ ላይ ወደቅሁ:: ከአሁን አሁን ቀና ብዬ እጠጣለሁ እያልኩ የሚያምረውን፣ ከደቂቃዎች በፊት ያየሁትን ለዐይን የሚጣፍጥ የጌርሳሞት አፍ ሰንቄ ወደ ሕልም አለም ገባሁ::

✱

ሁሉ ያልተወራላቸው ሀሚና ናቸው: እነዛ ልባም ነን የሚሉ አፈኞች: እንደ አበው የሚሰራቸው የሥነቃል ጭቃ ሹሞች፣ ነጋዴ ሐይማኖተኞች፣ የመድፍ ምስል ምላሳቸው ቀይ ጀርባ ላይ የተነቀሱ ፖለቲከኞች:: ዐይኖቹን ጨፍኖ እነዚህን የሚከተለው ደደብ ወቦም:: ከምሳ በኋላ ከመስሪያቤቴ ወጥቼ የሆነ ካፌ ቡና ለመጠጣት አስቤ ወደ የት መሄድ እንዳለብኝ ለመወሰን መስሪያ ቤት መውጫ ደረጃ ላይ ቆሜ ግራና ቀኝ ሳይ፣ ታች መንገድ ተሻግሮ ያለው *የኢንተርናሽናል ዲቨሎፕመንት ባንክ* ሕንፃ ጀርባ ከአጥር ግቢው ውጭ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው አየሁ:: ሰዎቹ እዛ ምን እየሰሩ እንደሆነ ለማወቅ ጓጓሁና የብረት ወንበር ላይ እንደ ጥቁር ደመና የተከመረውን ነዝናዛው ዘበኛችንን ዘበነን ያ ሁሉ ሰው የተሰበሰበው ለምን እንደሆነ ጠየቅሁት::

--ኧረ ጉድ ነው አንዲት ሴትዮ ከፎቅ ላይ ወደቀች! አለኝ

ለማስፈራሪያ (ካለፈም ለመደብደቢያ) የሚጠቀምበትን አጭር ዱላውን ጭኖቹ ላይ እንደአጋደመ ለአናቱ የጠበበውን ባርኔጣ አወለቀና እንደ አናሎግ ቴርሞሜትር ለረዥም ጊዜ አራገፈው:: ገና ፀጉሩ ያልተመለጠ ጠንካራ አናት አለው:: ጠንካራም ይመስላል: የመስሪያቤቴን ሦስት ፎቅ አንዴ ብቻ ጥሩ አድርጎ በቴስታ ቢገጨው የሚፈነግለው ይመስለኛል:: ሰውዬው ለዘበኛነት የተሰራ ነው:: ለማጣራት ደደብ ጥያቄ ጠየቅሁ:

--ከዚህ እንዴት ሴትዮ መሆኗ ታየህ?

--ይታያል:: እንዲህ እያየሁዋት ነው የወደቀችው

--ከስንተኛ ፎቅ ላይ?

--ከመሃል ስትደርስ ነው ያየሁዋት

--የምር ሴት ናት?

--እንዴ! ሴት ናት:: የዛ አይነት ቀጭን ድምፅ የሴት ነው

--ወንድም ቀጭን ድምፅ ይኖረዋል እኮ

---

--እንደዛ? ቀሚስም ለብሳለች እኮ:: ቀሚሷ ሲውለበለብ ነበር:: ይታወቃል

--ሄድክ ለማየት?

--እንዴ ምን መሆንህ ነው ጋሼ ራሚሱ ስራዬን ትቼ? ከመስሪያ ቤት የሄዱ ሰዎች አሉ ሊያዩ:: ሲመለሱ እጠይቃለሁ

--ስትጮህ ሰምተሃል? ምን ብላ ጮኸች?

--እንዴ የጭንቅ ጩኸት ነው እኮ::

ዞር ብዬ አየሁት:: የቀባጠረልኝ ወሬ ብዙ ስላልተመቸኝ ትቼው ወደ ምናወራለት ሕንፃ ጀርባ፣ ፎቁ ከቆመበት ግቢ ውጭ እየተርመሰመሰ ወደ ሚንጫጫው አጀብ ወጀብ ሄድኩ:: አጥሩ በር ጋ እንደ እኔ ወሬ ለመለቃቀም (ወይስ የሚሄዱበት የላቸውም?) አንድ ሃያ ሰዎች ተሰብስበዋል:: አንዱ ያወራል ሌላውም ያወራል ሌላውም አያዳመጥም ሌላውም ያዳምጣል ሌላውም ከንፈሩን ይመጣል: ከስብሰባ በታች ከጫጫታ በላይ ነው:: ማንም እንዳይገባ ነው አሉ የግቢው የጀርባ በር ተዘግቷል:: ግን ትዝ ሲለኝ ሁሌም እንደተዘጋ ነው:: መኪና ሲገባና ሲወጣ ይከፈታል እንጂ ሁልጊዜም ዝግ ነው:: የሕንፃው የጀርባ በር በስድስት ነርሶች፣ በአራት ፖሊሶችና በአርባ አራት ወሬኞች ይጠበቃል:: የሚሰራውን ይሰራ የነበረ ምንም መረጃ የማይሰጠን አምቡላንስ እያለቃቀሰ ከግቢው ወጣ:: ሰዎች ይሄን ነጭ መኪና እንደ ፍቅረኛቸው በአይኖቻቸው ሸኙና ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ *'ጉድ ነው!' 'ወይ ጉድ!'* እያሉ መበታተን ሲጀምሩ ወደ አንዱ ሰው ጠጋ ብዬ:

--ምንድነው የሆነው? አልኩት

--አንድ ሰውዬ ከመጨረሻው ፎቅ ላይ ዘሎ ወደቀ

--ሰውዬ ነው ሴትዮ?

--ሰውዬ:: እንግዲህ ሰውዬ ሲሉ ነው የሰማሁት

--እኔ ደሞ ሴትዮ ናት ሲሉ የሰማሁ መሰለኝ

--ሴት እንዲህ አታደርግም:: ሴት በአይጥ መርዝ በምናምን አልጋ ላይ ራሷን ትገላለች ወይ ወንዝ ትገባለች:: ወንድ ራሱን በሽጉጥ ይገላል ወይ ከገደል ራሱን ይጥላል......

--እንዴት? አይተሃል? ወንዝና ገደል የለ እዚህ

---

| ------------

--ፎቅ ምንድነው? ገደል አይደለ? ሰው ሰራው እንጂ:: ወንድሜ ሲያወሩ ነው የሰማሁት:: አልገፋሁት:: ደሞ ሰውዬው አእምሮውን ሳይታመም አይቀርም ይላሉ

--ሞቷል?

--ከዚህ ላይ ወድቆ ሰው ይተርፋል እንዴ?

--ከስንተኛ ፎቅ ወደቀ ይላሉ?

--ከላይ ነው ሲሉ ነው የሰማሁት፣ ከመጨረሻው

--ከመጨረሻው ቢወድቅ የሚነሳ ገላ ይተርፈዋል ብለህ ነው?

--ባይተርፍ አምቡላንስ ይመጣል እንዴ? ምኑን ሊያነሳው?

--ልክ ነህ እሱስ አልኩት::

ታዲያ ምን ልበል? ቀና ብሎ አየኝና ካውያ እንዳልደረሰበት አቡጀዲ ጨርቅ የተሰባበረ ፈገግታ አሳይቶኝ ትቶኝ ሄደ:: ወደ ሕንፃው ፊት ለፊት ሄጄ ስለሰማሁት ወሬ በቀጥታ የሚመለከታቸውን እንዳልጠይቅ ግማሽ ኪሎሜትር ያህል የእግር ጉዞ ማድረግ አለብኝ:: ስራ ስገባና ስወጣ ግን ታክሲና አውቶቡስ የሚወስደኝና የሚጥለኝ እዛ ፊት ለፊት ነው:: ደሞ ያለገደብ ባስገባሁት የመስሪያ ቤቴ ካፊቴርያ ፓስታና ነጭ ዳቦ ሆዴ ተነፍቶ ስራመድ አይመቸኝም:: ግራና ቀኝ በገመድ አስረው እንደ ከበሮ ቢደበድቡኝ የምር አንድ ቀጫጫ ግራዚያኒ ሳልተፋ አልቀርም:: የተሰበሰቡት ሰዎች እስኪበታተኑ አልጠበቅሁም:: ቡናዬን ለመጠጣት የለመድኩት *ሶሲ ካፌ* ገባሁ:: እዛ ያጋጠመኝ ሰው ሁሉ ወሬው ስለ ቤት ኪራይ፣ ስለክልል፣ ስለመንገድ፣ ስለ ሕንፃ፣ ስለ ኑሮ ውድነት፣ ስለ ንግድና ስለ ትርፉ፣ ስለ እንግሊዝ ፕሬሚየር ሊግ፣ ስለ ስፓኒሽ ሊግና ስለ ሎተሪ ነው:: ባይመለከተኝም ይመለከተኛል አለ:: ባልናገረው ባልሳተፍበትም ወሬውን በጆሮዬ ብቻ ከተነፈስኩት ዜጋ ነኝ አለ:: ግን 'ሶሲ' ምን ማለት ነው?

ቡናዬን ጠጥቼ ከካፌው ወጣሁና ወደ መስሪያ ቤቴ ሕንፃ ልገባ ስል በስተቀኜ ጫጫታ ሰማሁ:: ድምፁ የአንድ ምስኪን ሆቴል ጥላ ተገን አድርገው ከተሰሩ መፅሐፍ መሸጫ ሱቆች የሚመጣ ነው:: እዛ በሬድዮ ኳስ ጨዋታ ይተላለፋል:: በዚህ ሰአት ኳስ መስማት አስገራሚ ነገር አለው:: ለመሆኑ ኳስ ጨዋታ እንዴት በጆሮ ይሰማል? *ይሁ ሄደ!*

---

ይሆ ሄደ! ይላል። ለመሆኑ ተጫዋቹ ምን ያህል ሜትር ነው ይዞ የሮጠው? አቅጣጫው ወደ ሰሜን ነው ወደ ደቡብ? ያልያዘኝ የከተማው ወረርሽኝ ይሄ ስራ አስፈቺ የኳስ ባህል ነው። ግን ደሞ ከመፅሐፍ የበለጠ ስራ አስፈቺ ነገር አለ? የምር መጽሐፍ ጠቃሚ ቢሆን ያ ሽቃይ ኳሱን ትቶ እጁን ወደ ኋላ ሰዶ ደስ ያለውን ከመደርደሪያው ላይ ስቦ ማንበብ አይችልም ነበር? በሰውዬው ሁለመና ላይ የባርሴሎና ሸረሪት ድር ወይም የሊቨርፑል ከተማ ጉም የተጠመጠመበት ይመስላል። ጥርሱ እንደ ሙና የሸቦ አልጋ የዛገ ነው።

'ኳሷን ቀለባት! አስገራሚ ነው አያያያ!'

አሀያ

በአየር ላይ የምትበረው ኳስ ሳትሆን ሴት ጓደኛው ብትሆን እመኛለሁ። እና ከቻላችሁ ቅለቡብትና አድርጉበት በአሳሀ። ተከላክሎ እስኪነጥቅዎ ድረስ እንደ ምንም ብለው አስረግዘው ይስጡት። የስፖርት ጋዜጠኞች የኳስ ሚስት ሳይኖራቸው አይቀርም። እነሱን ደሞ ባል ናቸውና ወደ ፖምፕ መለወጥ። የልጆቻቸው ስም የአየር ነው፡ ናይትሮጂን፣ ሂሊየም፣ ኒኦን፣ አርጎን ምናምን። መጽሐፍ ይሁን ወረቀት ሻጩ በአላማ ማጣትና (ልክ እንደ እኔ) በሲጋራ ያበለዘው ጥርሱን አሳየኝ። *ቡልሺት!*

ከቢሮ ስወጣ ያየኝና እዛ እንደምሰራ የሚያውቀኝ ያ ዘበኑ የሚሉት ዘበኛ፣ ገና ዛሬ ያወቀኝ፣ ገና ዛሬ እዚህ አገር የገባሁ ፀጉረ ልውጥ፣ የአገሪቱን ሕልውና የምቀናቀን የተረገመ አሸባሪ እንደሆንኩ እናም እኩይ ድርጊት ለመፈፀም ከገላዬ ጋር የተጣበቀ እንደ ወረቀት ስስና ጠፍጣፋ የሆነ ሮኬት ደብቄ ይገፍ ሕንፃው ውስጥ አስርጌ እንደማስገባ ሁሉ ምህረት የለሽ ፍተሻ አካሄደብኝ። ይሄ ሃጠራው ከተቀጠረ ሁለት ወሩ ነው። እንዲህ ከአደረገ በሁዋላ በወንጀለኛነት ስሜት ቀና ብሎ አየኝ። በጣም ከፈተሸ በኋላ ምንም ነገር ካላገኘ ያፍራል። ስለዚህ ሁልጊዜ እንዳፈረ ነው። ከኋላዬ አራት ሰዎች ተራቸው እስኪደርስ እየተከዙ ቆመዋል። መጨረሻ ላይ ያለችው ወዳጄ *አሥራት* ናት። አንድ ዲፓርትመንት ስለምንሰራ አብረን ቢሮ እንድንገባ በሴቷ ዘበኛ ተፈትሻ እስክትመጣ ጠበቅኳት። ፈታሽዋ

ቀጫጫ፣ አስቀያሚ በትክክል ባልገባኝ ምክንያት የወፍራም ሰው ብብት የመሰለች ናት:: የሽሚዟ ነጭ ኮሌታ እንደታምፖን ነው:: አሥራት ወደ ሴቷ ዘበኛ ቀርባ እየተፈተሸች በቀዘዙ አይኖቿ አየችኝና:

--የት ጠጣህ ቡና? አለች

የት እንደምጠጣ ጠፍቷት ሳይሆን ፀጥታውን በድምፅ ለመሙላት አስባ ወይም መጠበቅ ተሰላችቼ ትቼአት እንዳልገባ በወሬ መያዟ ነበር:

--እዛው ቦታ አልኳት::

ሶሲ ካፌ የጉረኞች መሰብሰቢያ ነው ይባላል:: ሌሎች ሰዎች ስምተው 'የምን ጉራ ነው' እንዳይሉኝ ስሙን መስሪያ ቤት አካባቢ አላነሳም:: የሚሉት እንኳን *ማን ላይ ጉራ ይነፋል?* ነው:: ማንም ሳይለምናቸው ራሳቸውን ምስኪን፣ ጸሎተኛ ሳይሆኑ ጸሎተኛ ያደርጉና ('ሰላም' ሲባሉ ጠቅላላ አፍሪካ እንዲሰማ አድርገው 'እግዜር ይመስገን' የሚሉ)፣ ካመቻቸው ግን ከጸለዩበት ቦታ ብዙ ሳይርቁ የጸሎታቸውም ቃል ገና ከአየር ላይ ተበታትኖ ሳይጠፋ በሾኬ ጠልፈው ለመጣል የቦት ጫማቸውን ሲር የሚያጠብቁ ኮማንዶዎች ናቸው:: ልክ እንደተጨቆኑ ሁሉ የምስኪንነት ድባብ ዐይኖቻቸውን አልብሰው እኔ ዱርዬውንና ቺስታውን ይገላምጣሉ:: የዚህን ካፌ ስም እዛ እጅብ ብሎ የቆመ ተፈታሽ መሃል ቢሰሙ እነዚህ እከክና ደደብነት የሚጋሩ ያልታደሉ ሰዎች ወንጀለኛ እንዳገኙ ሁሉ በዐይኖቻቸው ይጠቃቀሳሉ:: እንደዚህ አይነት ድምፅ አልባ ወሬና ፍርድ እጠላለሁ:: አሥራትንም ማስጠመድ አልፈልግም: *ከየት ለቅማ አመጣችው ይሄን ልክስክስ በማርያም?* ሊሉ ይችላሉ:: የሚያቆማቸው ማነው? ቺስታ ብሆንም የምዝናናው በክላስ ነው::

አሥራትን የምትፈትሻት የጥበቃ ሰራተኛ ከወዳጇ ጋር ሴራ የተለዋወጥን ሁሉ ቦርሳ እየበረበረች ቀና ብላ እያቀያየረች አየችን:: አሥራት ቦርሳዋን ተቀብላ:

--መጥፎ ቡና ጠጣሁ አለች:: አሟት እንደሆነ ከመጠየቄ በፊት ወደ እኔ ተጠጋችና:

--የሚያሳዝን ነገር ሰማህ? አለች

---

ምን ማለቷ እንደሆነ ሳልጠይቃት ከፎቅ ስለወደቀው ሰው እንደሆነ ገባኝ:: እንዳልገባኝ:

--ምንድነው? አልኳት::

ትኩስ ወሬ ለብቻዋ ቀድማ ማወቋ አሥራትን ያኮራታል:: *ብሬኪንግ ኒውስ*[32] እንደሚሉት:: *ኦሪጂናሌነት* ይሄ ነው ለእሷ:: ጎን ለጎን እያወራን ሊፍት ወደ ላይ ለመውሰድ የሚያስፈራ፣ በከፊል ዝገት የለበሰ የማያስተማምን የብረት በር ፊት ለፊት እንደቆምን:

--ከዛ ከአይ ዲ ቢ ባንክ (IDB) ፎቅ ላይ አንዱን ሰውዬ ሰዎች ገፍትረው ጣሉት ምስኪን አለችና ተለምኖ አልመጣ ያላትን ዕንባ ለማባረር የውሸት ለፋች::

--ሰውዬ ነው?

--ምን?

--ሴት ከሆነችስ?

--ወንድ ነው

--በዛ ስታልፊ ነበር?

--እያየሁት ነው የወደቀው:: ሱሪና ኮት ለብሶአል:: ክራቫት አድርጓል:: በእጁ ወረቀት ይዟል መሰለኝ ወረቀቱ ሲበታተን ነበር:: አንድ ወረቀት ከግቢው ወጥቶ ሲገለባበጥ ቆይቶ መሬት እንደወደቀ አንድ ጆብሎ አግኝቶ ለፖሊሶች ሰጣቸው:: እዛ የሚሰራ ሰውዬ እንደሆነ ነገሩኝ::

--ምን ሆኖ ወደቀ?

--ሰው ገፍቶት ሊሆን ይችላል

--ነው ብለሽ ነው?

ሊፍቱ ተከፈተና ሁለት የስራ ባልደረቦቻችን እየተሳሳቁ ከሊፍቱ ወጡ:: አሥራት ገላመጠቻቸውና ወደ ሊፍቱ ገባች:: ተከተልኳት:: እዛ እውስጥ እንደቆምን አራት ሰዎች እያገሱ፣ እያዛጉ፣ እየተቁለጨለጩ፣ እየተስለመለሙ ተከትለውን ገቡ:: ወደ ጆሮዋ ቀርቤ:

--ለምን ሰው ገፍቶት ሊሆን ይችላል አልሽ? ስላት

ጥያቄዬን ቶሎ እንደመመለስ ግራና ቀኝ አብረውን ሊፍት የተሳፈሩትን ሰዎች አየች:: ሶስቱ ሌላ ዲፓርትመንት የሚሰሩ

| ------------

የራሳችን መስሪያ ቤት ሰዎች ናቸው:: አራተኛው ክፍሉ የተባለ የዲፓርትመንታችን ግራፊክ ዲዛይነር ነው:: የጥርሱ ሰማንያ በመቶ ከከንፈሮቹ እውጭ የሚታይ ገጣጣ ነው:: ጠዋት ጠዋት ብርድ ሲሆን ወንድሜ ክፍሉ ሆይ ጥርስህን ፎጣ አልብሰው ወይም ሹራብ አሰራለት ማለት ያምረኛል:: እዚህ አብረውኝ የተሳፈሩትን ጨምሮ የመስሪያቤቴን ሰዎች ብዙዎቹን አልወድም:: እንደገና ወደ አሥራት ጆሮ ቀርቤ ጥያቄዬን ልደግም ስል ኮስታራነቷ አቆመኝ:: ፊቷ በቆልት በስናፍጭ እንደበላች ሁሉ ተኮማትሯል:: የሞተው ሰው ስላሳዘናት የተደበረች መሰለኝ:: አሥራት እንኳዋን ሰው ሲሞት አይታ ይቅርና በጤነኛው ቀን ደባሪ ናት:: እንግዲህ በተደበረች ሴት ላይ ደባሪ ገጠመኝ ሲጨመር:: ከሊፍቱ ስንወጣ ቀድማኝ ስለነበር ከበሩ ፈቀቅ አለችና ቆም ብላ:

--ያ ክፍሉ ስለሚደብረኝ ማውራት አልፈለኩም:: ምን አደረኩት የሚገላምጠኝ? ደደብ

--ዝጊው

ብዙ ነገር ይደብራታል:: ከመንፈስ ሌላ ምንም ሥልጣን የሌለው ይሄ ባዶው እሷም እኔም የምንተነፍሰው አየር ሊደብራት ይችላል::

--ሰው ገፍቶት ነው አልኩህ አለች::

ማንን ማለቷ እንደሆነ ገብቶኛል

--ምን ብለው ይገፉታል?

--እዛ ቤት የማይሰራ ነገር የለም:: ስንት የተጠማመዱ አሉ መሰለህ

--ይሆናል:: ምን ይታወቃል?

--ሲወድቅ ሱሪው ወልቆ ነበር:: ወገቡን በእጁ ይዟል::

--ሱሪው ለምን ይወልቃል?

--እንጃ

--የእውነት ወልቆ ነበር? ወገቡን የሚይዘው ሊዘንጥ ነው? ላስቃት ሞከርኩ:: አልሳቀችም::

--አታምነኝም? ቀይ የውስጥ ሱሪው ይታይ ነበር:: ደሞ የሚሰራበት ቢሮ መስኮት ተሰብሮ ነበር

---

--የምን መስኮት? መስታወት አላየሁም

--እንዴት? እዛ ነበርክ?

--ከመሬት ሳይ

--እንዴት ከመሬት ይታያል?

--አይ ቀረብ ብዬ ነበር

--ምንም ብትቀርብ የአስረኛ ፎቅ መስኮት ይታይሃል?

--አምስተኛ ፎቅ ሲባል ነው የሰማሁት

--ከአምስተኛ ፎቅ ቢወድቅ ሰው አይሞትም:: ከመንገዱ አይታይም እንጂ ፎቁ ስር አትክልት ቦታና ሳር አለ እኮ

--ምንም ሆነ ምን ያሳዝናል

--ምን ብሎ ያሳዝናል?

--እንደውም ፊትሽን ሳየው ይገርምሻል ያለቀስሽ መስሎኝ ነበር

--እኔ እቴ:: ስራ አጣሁ

--ዐይንሽ

--ሌላ የሚያሳዝን ነገር አጋጥሞኝ ነው......እራት አትጋብዘኝም?......ወይም *ደስ ባር* ወይን ግዛልኝ አለች ዞር ዞር ብላ አይታ:: ልክ እሷን በመጋበዜ ልዩ ነገር ማለት መርከብ አህጉር ምናምን እንደምትሰጠኝ ሁሉ

--ያን ነገር ደሞ እናደርጋለን አለች:: እንዲህ ካለች ማድረግ አለብኝ ማለት ነው

--ቀጠሮ አለኝ አልኩ ፈጠን ብዬ (የተቃጠርኩት ከገርልፍሬንዴ[33] ከአስቴር ጋር እንደሆነ ትጠረጥራለች)

እንዳልሰማችኝ ሁሉ:

--ንጉሡ ሐዋሳ ሄዷል:: አለቃዬ ደሞ ዛሬ የለም አለች::

*ምን ታስባለህ?* ማለቷ ነው:: ሳይመሽ ልገላገል ፈለኩ:: ፈገግ አለችና የተላገ ጣውላ የመሰለ ቁመናዋን እየጎተተች ቢሮዋ ገባች:: እሷን ተውኩና በቀጥታ ወደ ሽንት ቤት ሄጄ ባዶ ክፍል ገብቼ ቆለፍኩ:: ሱሪዬን አውርጄ በመጀመሪያ እንትኔን እ.የየሁ ፀሎት አደረስኩ: 'ጌታዬ ሆይ እግሮቼ መሃል የምትኖር፣ ስምህ ይቀደስ......' የመሰለ:: ቀጠልኩና የእንጀራ ጉዳይ እንደሆነና ጊዜውና ቦታው

| ------------

ባይመችም ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ተለማመጥኩት:: የመጨረሻ ማሳረጊያ: 'ጉልበትህ ለሴት ጓደኛዬ እንደሆነ ሁሉ እንዲሁ ለዚህችም ይሁን' አልኩና አሥራት ቢሮ ቶሎ ቶሎ እየተራመድኩ ገባሁ:: ከሁዋላዬ ቀረት ብላ በሩን ከፊት አድርጋ ግራና ቀኝ አየችና ቆለፈች:: ምንም ሳትናገር እንደለመደችው ጎንበስ ብላ በግራ ክርኗ ጠረጴዛ ተደገፈችና ቀሚሷን ከኋላ ወደ ላይ አነሳች:: ወንፊት የመሰለ ቀይ የውስጥ ሱሪ አድርጋለች:: ብዙ ዝቅ ብዬ ሳላይ ተጠጋሁዋትና በዳሌዬ ጋረድኳት:: ከጠረጴዛው ላይ ስክሪፕቶ አንስታ እስክሪፕቶውን ከክዳኑ እያወጣች ታስገባዋለች:: ያጎነበሰችው እንዲህ ለማድረግ ይመስላል:: የሰደደችው ስክሪፕቶ ክዳኑን ሲስት አያለሁ:: እንዳላሳፍራት ዋጥኩት እንጂ ክዳኑን ስለመሳቷ ልናገር ያሰብኩት ቃል አፌ ላይ ነበር:: ቆዳዋ ያልጠበቀሁትን አይነት ይሞቃል::

--አላላመመንንከኝምምም አይደለ ሰው ገፍቶት ወድቆ ይሆናል ስልልልህ......እ?

ምን አገባኝ አልኩ በልቤ:: ምን አገባን? የሰማያዊ ሹራቧ ጀርባ ላይ ደቃቃ ነጫጭ ነገሮች አሉ:: አንድ ሁለት ሶስቱ እንደውም ከካራቶሬ ይታያሉ:: እየቀረብኩ እየራቅሁ ምን እንደሆኑ ለማየት ሞከርኩ:: እዚህ ሳትመጣ እቤቷ ሹራቧ ላይ ነጠላ ወይ ጋቢ ደርባበት ነበር:: ትንሽ ሲበርዳቸው ጋቢ የሚደርቡ፣ አንድ ሄክታር ላይ የበቀለ ጥጥ ተሸክመው የሚንጓለሉ ሴቶች ይደብሩኛል:: ቤታቸውም ቢሆን:: ገና በልጅነታቸው 'መፍጠን በቃን' ያሉ ስለሚመስሉኝ ነው:: ብደበርም ድብርቴን አንድ ሁለት እያልኩ እየቆጠርኩ አረጃታለሁ እንጂ የሃይማኖትና የባህል አሥርቱ ቃላተ ኦሪቶች ላይ ሙጭጭ አልልም:: ሰባኪ ፈጣን ሲሆን፣ ተሰባኪ ንፍጣም ይደረጋልና:: የሸሚዟ ኮሌታ መቆሸሽ ጀምሯል:: ደስ የሚል ሽቶ ከላይዋ ይነሳል:: ጠረኗ ቢያምርም የምትረባ ውሽማ ያለኝ አይመስለኝም:: የመስሪያቤታችን ካሌንደርና የፕሬዝዳንታችን ፎቶ ጎን ለጎን ሆነው ፊት ለፊቴ ግድግዳ ላይ ተሰቅለዋል:: የሰውዬውን ሞጥሟጣ አፍና ስፊ ክብ ፊት እያየሁ ፊገግ አልኩ::

---

--እእእእዛዘዘአ ቤት አአእኮ ያለው ሸርርር አለች ዝግ ባለ ድምፅ። ለራሷ የምትናገር ትመስላለች።

የሆነ ሰው በር አንኳኳ። ዞር ብላ ወደ በሩ አየች። ፊቷ ላይ ምንም አይነበብም። በጎን የማየው አንድ ዐይኗ በቀስታ ተከፍቶ ተከደነ። መንኳኳቱን ችላ ብላ በእስክሪፕቶው ጥርሷን ነካካች......ጆሮዋን አቁማ፣ የሆነውን ስታዳምጥ ቆይታ እንደበቃኝ ሲገባት እንደምታርፍ ሁሉ ዐይኖቿን ጨፍና ፊቷን ጠረጴዛው ጠለል ላይ አስተኛች። ለአፍታ ላም መሰለችኝ። በእጇ እጄን አጥብቃ ያዘችኝ። ከጀርባዋ ቆሜ ወገቧን ይገፉ የሚንቀጠቀጡ እግሮቼ እስኪረጋጉ ጠበቅሁ። እጄን ለቃ ቀና ብላ የውስጥ ሱሪዋን አጠለቀችና፡

--......ያሳዝናል የዛ ሰውዬ ነገር አለች

ሱሪዬን ወደ ላይ ስቤ፣ ቀበቶዬን እንደነገሩ አስሬ ቀና ቀና እየተነፈስኩ ወንበር ላይ ቶሎ ተቀመጥኩና እጄ እንዳመጣልኝ ጠረጴዛ ላይ ያገኘሁትን ስቴፕለር አጥብቄ ያዝኩ። ለምን አጥብቄ እንደያዝኩት እንጃ።

--ታጥቤ ልምጣ አለችና ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ እየተንቀለቀለች ወጣች።

በስቴፕለሩ ራሴን መግደል ፈለኩ። ስንት ሽቦ ይበቃኛል?

አሥራት ከበላይ አካል ጋር ግኑኝነት ስላላት ስለሚለዋወጠው የመስሪያ ቤቱ ፀባይ በቶሎ ስለምትሰማ ቢጠቅመኝም ባይጠቅመኝም ምን ዘመንና የት ቦታ እንዳለሁ እንዳውቅ ትረዳኛለች። ቁመቷ ትከሻዬ የሚደርስ፣ ቀጭን፣ በትንሽ ነገር ሁሉ ባለጉዳዮችን በሽሙጥ ማናገር የምትወድ ሴት ናት። ሲመስለኝ ለአሥራት ምናልባት፣ ከምናልባትም በላይ ድብርት መፈወሻ መድሐኒቷ ነኝ። ፕሮዛክዋ[31] ነኝ። አንዳንዴም የማስታወቂያ ስሌዳ የሆንኩ ይመስለኛል። 'ብቀጥንም፣ ጡት አልባ ብሆንም፣ ግንባሬ ላይ አውስትራሊያ በማድያት ቢሳልም፣ በዚህ ሳተና (አፈር ድሜ ሳተና) መፈለጌ የተወዳጅነቴ ምልክት አይደለምን? ሳትቀምሱ አትገምቱ' የምትል ትመስላለች። በቂ ተጨባጭ መረጃ ገና ላላገኘሁላቸው ስለእነዚህ

---

ጥርጣሬዎቼ አልነግራትም፡ በስሱ እንኳን ሽሙጥ ቀባብቼ አላወራትም:: እምልጦኝ ክሱት ባደርገው ዘበኛውን *በደንብ በርብረሀ አስገባው* ብላ ጣፊያዬን ልታስወጣብኝ ትችላለች:: ደስ ያላት ጊዜና ቦታ ሩካቤ እናድርግ እያለች ብትነዘንዘኝም፣ ለእኔ ሙዚቃ ወዳጄ የታቦት ማደሪያ ስድ ይሄው ስንቴ ማስኜ ዳቦዋ ውስጥ ዜማ አላገኘሁም:: ለእኔ ምናልባት ብገምት ዳቦዋ መዝፈን ካቆመ አመታት ከረመ:: አስቀያሚ የምትባለው ሴት ፎናና ቂጣም ቀጫጫ ወፍራም ዲግሪ ያላገኘች አይደለችም:: ወሲብ እያደረገች ያላደረገች የምትመስል ናት:: እኔ እንደ ማራቶን ሯጭ በሮማና በቶክዮ ሳለከልክ እሷ መርካቶ ትሄዳለች:: አልጋ ላይ ስለአስቤዛና ስለአለቃዋ ታስባለች:: ቀዝቃዛነቷን ሳስብ ሁለመናዬ በመደበር ይሰበሰባል:: የመጀመሪያው ቀን የራሴ ስህተት ሁሉ መሰለኝ:: ባይሆንም:: ለሁለተኛው ቀን ግን በትክክል ማን እንደሆነች አየኋት:: የእሷን ዳቦ የመሸሸ ነገር ሰፍቶ የአለምን ዳቦ መሸሸ እንዳይሆንብኝ ፈራሁ:: የአሥራት መሳሪያ ነኝ:: እኔም አስመስላለሁ:: እጄን ይዛ እየጎተተችኝ በሰዎች መሃል ታልፋለች:: ካፊቴርያ ውስጥ እንዲህ ስታደርግ አረማመዷ ውስጥ 'መውረግረግ' ልታስገባ ትለፋለች:: ቀጫጫ ይውረገረጋል? የሚንቃትን አለም የምትጋፈጥብኝ ሰብአ ሠላጢን ነኝ:: አይጎዳኝም:: አያጎልብኝም:: ምናልባት ይሄ ገብቷት ይሆናል፡ ይጎልበታል ብጠቀምበት? እዚህች ምድር ላይ ከሚኖረው ስንቱ ነው ግን በልቡ የሚያስበውን ሳይፈራ ሳይቸር የሚያደርግ? ሁላችንም ቲያትረኞች ነን:: ከዐይኖቿ ትልልቅ ክብ ወዲያ ነፍሷን ቲያትር ያበላሸባት፣ በራሷ የማትተማመን፣ መተማመንም የከበዳት ልጅ ትሆናለች:: ያቺ ውሽታም ሴት ጓደኛዬን አስቴርን አታልዬም ይሁን አስፈራርቼ መግራት ያልቻልኩ ጉረኛ ነኝ:: ግን የእኔን ደካማነት ለምን የአሥራት ጥፋት አደርገዋለሁ? ስታወራስ የአንደበቷን ማማር መካድ አለብኝ? ለመሆኑ እኔ ማነኝ?

አሥራት በቅርብ ስፈራችን የገባው (ሁለት አመት ይሆነዋል) የጓደኛዬ የንጉሡ ትልቅ እህት ናት:: ከእሷ ጋር በቅርበት የተዋወቅነው ሰፈር ብሎክ ፓርቲ አድርገን የቀጠርኳት ጌርሳሞት አብራኝ እንዳትወጣ በድጋሚ ቤተሰቦቿ ከልክለዋት ስትቀር በመነፈጌ ተደብሬ

ነው:: ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ላይ ንጉሡ በጣም ሰክሮ ቤቱ ሳስገባው እየተጓተትን ስንሄድ *አሥራት* የግቢ በር ከፈተች:: እሱን እየተቆጣች መኝታ ክፍሉ አስገባችውና እኔን እንዳርፍ አዘዘችኝ:: ትእዛዝ ባልሰማም፣ ከእኔ ቢያንስ አስር አመት ታረጃለችና ላከብራት ብዬ ሳልከራከር ተቀመጥኩ:: በተጨማሪም ስካር ስላደከመኝ ያገኘሁት ቦታ በረንዳ ስር ተቀመጥኩ:: ንጉሡ እንደተኛ አረጋግጣ ወደ እኔ ተመልሳ መጣችና እስከ ሌሊቱ አስር ሰአት ስናወራ ቆየን:: *አንድ* ከመኝታዋ ተነስታ በር ከፈተች፣ በፒጃማ ናት፣ ፒጃማዋም ከግንባሩ የተከፈተ እየተከደነ የጡቶቿን የውስጥ ደርዝ አሳየኝ:: *ሁለት* ቆልቶኝ ጌርሳሞትን ስጠብቅ ነበር:: ጌርሳሞትን ብጠብቅም ብጠብቅም አልመጣችም:: *ሦስት* ደስ የሚል ጨለማ ነው:: *አራት* አሥራት ጨዋታ እያስመሰለች ነካካችኝ:: *አምስት* ቀጫጫ ብትሆንም አውቃ የምትገላልበው ፒጃማ የሚያሳየኝ የታች ገላዋ ስጋ ያለበት፣ ለስላሳና የሚያባባ ነው:: *ስድስት* ገና ሃያ አምስት ያልሞላኝ ሳተና ነኝ:: *ሰባት* ሳምኳት:: *ስምንት* እየፈለገችኝ ስትግደረደር የበለጠ ፈለኳት:: ለምን? በዘጠኝ ገመድ ስተበተብስ? *ዘጠኝ* እቃቸውን እደጅ እየተው ሰውን ሌባ ይላሉ:: ከአሥራት ጋር መኝታ ቤቷ ገብቼ ፀሐይ እስኪወጣ ቆይቼ ቤቴ ገባሁ::

በሚቀጥለው ቀን ማታ ሁለት ሰአት ላይ ቤት መጣች:: 'የማወራህ ነገር አለ' ብላ ከአልጋዬ ጎትታ አውጥታ ደስ ባር አስገብታ (ግራ ቢገባኝም) ለምን ስራ እንደማልይዝ ጠየቀችኝ:: *ስንት ጊዜዬ ዛሬ ምነው ጠየቅሽኝ? ትናንት ነው ያወቅሁት ብዙ አወራሽኝ:: ነገርከኝ::* እንደነገርኳት ትዝ አይለኝም:: ሰክሬ ስለነበር ማስተባበሌ እውነት እንኳን ቢሆን ተአማኒነቱ አጠራጣሪ ነበር:: ንጉሡ ግን ትናንትና እና ከዛ በፊት እንደነገራት መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ:: እናቴ መቅረዝ እንደዚህ አላሞካሸችኝም:......*ብሩህነት ያለ ፀባይ የትም አይደርስም......ስራ መያዝ አለብህ......አንተን የመሰለ ልጅ የውም ዲግሪ ያለው መንዛላዘል የለበትም*......ከመጽሐፍ ቅዱስ በተቀዳ አማርኛ ጠዝጥዛኝ ብቅ እያልኩ እንድጠይቃት፣ ስራም በአጭር ጊዜ ልታስይዘኝ እንደምትችል ጣቷን አቀላጥፋ አጨኝ ሞራልና ስነምግባር ትን እስኪለኝ ግታኝ፣ ለምጠጣው ቢራና ሃምበርገር ከፍላ ሄደች:: ስትሄድ

---

| .............

በአትኩሮት እሰማት ስለነበር ቢራዬን አልጨረስኩትም፣ የሃምበርገሩም እሩብ እዛ አለ:: *ግራ የገባኝ እሷ ጋ የምሄደው በየቀኑ ነው ወይስ በየሶስት ቀኑ?*

......አላሳሰበኝም:: እየደወለች ትጠራኛለች:: መኝታ ቤቷ ይዛኝ በገባች ቁጥር: 'ያለአንተ እዚህ የገባ የለም' ማለቷ ትንሽ አማረረኝ::

ከሶስት ሳምንታት በሁዋላ ድንገት ብቅ ባለው አዲሱ ዕድለኛነቴ የምትሰራበት መስሪያ ቤት ቦታ እንዳገኝችልኝና ቶሎ እንዳመለክት ነገረችኝ:: ,ያለ ብዙ ጣጣ እሷ መስሪያ ቤት እዛው እሷ ሃላፊ ሆና የምትሰራበት የሕዝብ ግኑኝነት ዲፓርትመንት ውስጥ ተቀጠርኩ:: የስራ ባልደረባዎቼ ወሰን የለሽ ጨይባ ናቸውና፣ ሲያበሳጩኝ ሁኔታዬ ስለሚገባት ወደ ቢሮዋ ጠርታ: 'ለአንተ አይነት ዘልዛላ ይሄ ሲበዛበት ነው' ትለኝና የበለጠ እንዳልማረር በሳቅ ጠቅላ ልክ ታስገባኛለች:: አቅም የለኝምና አብሬአት እስቃለሁ:: 'አልተቀየምኩሽም' ለማለት አንገቷን እስማለሁ:: ጉንጭ የላትም ግን ቆዳውን እጎትታለሁ:: ከንፈሮቿ ስስ ከመሆናቸው የተነሳ የሚታየኝ አፍ ነውና ከንፈር አያጣም እያልኩ በነሲብ እስመዋለሁ:: ብዙ ጊዜም ስቼዋለሁ:: አንድ ጊዜ የጌርሳን አፍ ያየ የሌላ ሴት ላዕላይ በር ግራ ያጋባዋል:: ወላ ማርያምን::

ከአሥራት ጋር በቅምጥም ይሁን በቁም ተንጋልዬም ይሁን እየሮጥኩ አንሶላ ከተጋፈፍኩ መታጠብ አለብኝ:: ቆሻሻ ሆና አይደለም ግን ብዙ ጊዜ በተለይ ስራ ካልሄደች ጠረኗ የእቃና የልብስ ነው:: አንዳንዴ ማጋነን ሳይሆን እንደ ሰፌድ፣ የሆነላት እለት ደሞ ገና ከተሰጣበት እንደወረደ እርጥብ ጨርቅ ትሸታለች:: ጓደኛዬ ናት የምትባለው አስቴር የምትደውለው ሞባይሌ ላይ ነው:: *አስቴር የአቡ ገርል ናት ይባላል::* እግረኛ ናትና በትክክል የሻሞ ቦይፍሬንድዋ ነኝ:: ምናልባት አንዳንዴ የመጀመሪያዋና የመጀመሪያዬ ናትና ከሌሎች ቅድሚያ አላጣም:: ከአስቴር ጋር ገና ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ አብረን ነበርን:: አብሮ የመቆየት ይሉኝታ አለብኝ:: እሱ ብቻ ሳይሆን እህቴ ሁሉ ትመስለኛለች:: ይሄ ይሄ ከልጅነታችን ባልና ሚስት ጨዋታ ጋር በመያያዙ ይሆናል የባለቤትነት ታፔላ

---

ያስለጠፈብኝ:: አሥራትን የምወዳት ታማኝ በመሆኗ ነው:: በትንሹም በትልቁም ለእኔ ታዳላለች:: አስቴር ጊዜዋ ሲደርስ በራስዋ ሰአት ወደምትፈልገው ትሄዳለች:: አሥራትም እንደ እኔ በቻልታው የማያበሳጪት ሌላ ስራ የምታስይዘው ጎረምሳ ታገኝ ይሆናል:: እንዲሁ እየተወዛወዝኩ እኖራታለሁ እንጂ በማንም አልወሰንም እላለሁ—ቢያንስ ሞቅ ሲለኝ:: ሌላ ነገራቸው ተረስቶ ስማቸው አያምታታም? ማለት የአስቴርና የአሥራት?

| -------------

## የሳብእች ንግሥት

አንዳንዴ ቁጭ ብዬ ሳስብ የምፈልገውን ሳላደርግ ምናልባት እተቀመጥኩበት ምናልባት እተኛሁበት ምናልባት ቢሮዬ ኩቢክል ውስጥ ተቀምጬ ሳንጋጥጥ ምናልባት የመጀመሪያዬን ቢራ ሳጠናቅቅ ቡትሌ ሳጤስ ምናልባት ገና በምርቃና መፍሰስ ስጀምር ምናልባት ሽንቴን ለመሽናት የሱሪ ዚፔን ስፈታ ምናልባት ሳነጥስ ምናልባት በሹካዬ ጎንጉኜ ያነሳሁት የመጀመሪያ የፓስታ ጉርሻዬ አየር ላይ እያለ ምናልባት አርፌ እተኛሁበት ወይም ዝም ብሎ አሁን ከሩብ ሰአት በኋላ የምሞት ይመስለኛል:: እግዜራችሁ የማልማት ብቻ ሳይሆን የማጥፋት ጥበበኛ ነውና:: ከዚህ ፍርሃት ምንና ማን እንደሚያድነኝ ግን አላውቅም:: በግልፅ ልበለው: ለምን እንደምኖር አላውቅም:: ምን እንደምፈልግ አላውቅም:: በቆራጥነት የምጠጣውና ጫት የምቅመው የመሞቻ ጊዜዬን ለማፋጠን ይመስለኛል:: ለመስከር የምጠጣው መዝናናቴ መስሎህ ልትቀናብኝ የልብህ ጥርስ የገጠጠ፣ የበለጥኩህ መስሎህ 'እኛ የምንበላው አጥተናል እሱ.......' ምናምን ብለህ ለመነጫነጭ የምትቃጣ እውነት እውነት እልሃለሁ የምሰራው ስለጠፋኝ ነው:: *ለአስራ ስድስት አመታት የተማርከው ትምህርት ምን ጠቀመህ? ማንን ጠቀምክበት?* ብባል የምመልሰው የለኝም:: ከሆነ ከምጠላው ዩንቨርሲቲ ካልጠፋ ትምህርት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ዲግሪዬን ወስጄ በጥበቡ ያታለልኩት ወይም የመሰጥኩት ሰው የለም:: ምክንያቱም ስራ ሰርቼ አላውቅም:: እንዴት? ለምን? ምን መሆንህ ነው? ቢሉኝ፣ እነዛ ቢረባም ባይረባም መጠየቅ የሚቀላቸው፣ እነዚህ በጀግናና በፈሪ ሊ.መድቡኝ ምላሳቸው የተቅለበለበባቸው ወይ እነሱ ቁም ነገረኛ ለመምሰል በአፋቸው የሻፈዱ እላቸዋለሁ: እኔ የተማርኩት የማንም ፖለቲከኛ መጠቀሚያ ላለመሆን ነው:: ዛሬ ዛሬ እግዚአብሄር እንኳዋን ሳይቀር የግዱን ፖለቲከኛ ሆኗል፣ የአየራችን ናይትሮጂን ፖለቲከኛ ካልሆንክ ብለውት ተማርሮ ወደ ደቡብ ዋልታ ተሰዷል:: ዛሬ ዛሬ የታቦት ማደሪያ አየር ናይትሮጂን የለውም:: ኦክሲጂናችን እንዲረጋጋ የኮይራ ዞርባ አሲዘነዋል:: አስተማሪ (ሌክቸረር ነው የሚባለው

---

አይደል?) ስድስት ኪሎ ቀርቼ እንደጂነስ ቆጥሮ የሚያደንቀኝ ዲፓርትመንት ውስጥ እየለፈለፍኩ ከመዝናናት፣ እየተዝናናሁ ከመለፍለፍ ይልቅ አድቬንቸር ልስራ ብዬ አደባባይ ወጣሁና ሜዳ ቀረሁ:: ዕውቀት ልሰብክበት ያቋቋምኩት 'በር' የተባለው መፅሔቴ (ከግርማ ቻርሚንግ፣ ከካህሳይ ፋን፣ ከዮናስ ቅልጥፍናና ከመሰበወርቅ አንጎል ጋር) በአሕዛብ *ምን ይኮሳተራሉ? ምን ልፈላሰፍ ይላሉ?* በተባሉ ስም መበከያ አባባሎች ተደብድቤ ድራሼ ጠፋ:: ይረዱናል ብዬ የገመትኳቸው ሰዎች አውቀው አልገባቸውም:: የውሸታቸውን ደነዝ መስለው ደነዝ አሳደሙብን:: መንግሥታትና ፀረመንግሥታት ፍልስፍናውን፣ ሳይንሱን፣ ኪነጥበቡን አበዛችሁት አሉን:: ማይ ዲር ፍሬንድ[35] ግርማ ተበሳጭቶ *አዲስ ሪፖርተር* ጋዜጣ አዘጋጅ ሆኖ ገባ:: ካህሳይ አርባምንጭ ዩንቨርሲቲ ሊያስተምር ሄደ፣ ዮናስና መሰበወርቅ 'እንግዲህ ካልፃፍን ልጅ እንውለድ' ብለው ደቃቃ ጎጆ ቀልሰው በብርቱ መሳረር ጀመሩ---10 ዲግሪ ወደ መሬት ያዘመመ ቤት ውስጥ መለስተኛ የሰው እርባታ ጀምረዋል:: ሁሉንም ወዳጆቼን ካየሁዋቸው ብዙ ጊዜ አልፎኛል:: ከእነሱ ተገናኝቼ የተበላሸውን ውብ ዘመኔን ስሙን እያነሳሁ ማለቃቀስ አልፈልግም:: ለማንም አላወራውም (እደብቀዋለሁ) እንጂ ሞራሌ ከተቀመጠበት ከዚህ ከእንጦጦ ኮረብታ መንከባለል የጀመረ አጋዴን ግመል ቂጥ ስር እበት ይጠጣል:: ስሜቱን እያዝረበረበ በመንገድ ሲያልፍ መጠለያ የሰጠው የለም:: ያበላው፣ ያጠጣው፣ እናሳድርህ ወይ ቆሻሻውን ከላይህ እንክላልህ ያለው የለም:: እንደውም በቶሎ ፋንድያ ላይ ወድቆ ትል እንዲረባበት ተንከባክበው በባቡር ላይ አሳፍረውታል፣ በአውቶቡስ ወደ ሚሄድበት ምሥራቅ ለስንቅ ጥሬ ቋጥረው ጭነውታል:: ይኼው ልናገረው:: አስተማሪነት እንዳልገባ የተማሪ ፊት ያስጠላኛል:: እንደገናስ በበርጫ ያበጠ የጎረምሳ ዐይን ልይ? በርካሽ ጂንስ ያፈጠጠ ቂጧን የምታሳይ ልስልጥን የምትል ቅባታም ባላገር ልይ? እንዴት ነው ጆኒዎች ዲሞክራሲው ቁንጥ የለውም እንዴ? የሕልም እንክቱ እንዲህ ይወጣል:: በደባሪ ጥበባችሁ የተገረፈው ጀርባዬ አባጣ ጎባጣ አለው:: ባለሁለት እግር ጉንዳን ነኝ ከዳቦ ፍርፋሪ ስር የተጠለልኩ:: የሐሞቴ ቀረጢት በተስፋ መቁረጥ የጫት ጭማቂ ሙሉ ነው:: እሱንም ፀሐይ አይቶ የማያውቅ የዋሻ እንሽላሊት ይጠባዋል::

---

ከዚህ ጋር ይያያዝ አይያያዝ አላውቅም እንጂ እና ያለ ይሉኝታ ይሄው ልበለው የማልጠላው ነገር የለም:: ይሄ ጥላቻ የሚመጣው ልገልፀው ከሚከብደኝ እውስጤ ካለ ጉድጓድ ነው:: ጉድጓዱ እንዳለ ይታወቀኛል:: ውስጡ በሬንጅ የተለሰነም ይመስለኛል (ጠበል እንዳይገባው ነው?):: ቦታው ግን ልቤ ውስጥ ይሁን፣ አንጀቴ ውስጥ ይሁን፣ ጉበቴ ጋ ይቀመጥ ማወቅ ይከብደኛል:: የማውቀው ጥቁር አፉ ከመንዘርጠጡ የተነሳ ነፍሴንና ገላዬን መዋጡ ነው:: አንዳንዴ እንደ ቀለም ፍቄ ላነሳው የምችል አይነት ቁስ ሊሆን ትንሽ ይቀረዋል:: በልጅነቴ እንዲህ ሆኜ ቀባጢሶ የሚባል ነገር አላውቅም:: ቤተሰቦቼ ሃብታሞች ነበሩ:: የቸገረኝ ጊዜ ትዝ አይለኝም:: በየሳምንቱ መጨረሻ ምሳ እበላ የነበረው ከፈረንጅ ጋር ነበር:: በልጅነቴ በጣቶቻቸው መሃል እከክ ያለባቸው ጉረኛ ቀኞች ግራኝ እያሉ ስለጠሩኝ አልነበረም:: የምር ግድ ሰጥቶኝ አያውቅም:: ግራኝ እያለ የጠራኝ ከፊሉ ንፍጣም ነው ከፊሉም እከካም ነው ከፊሉም እዚህ ግባ የማይባል ደደብ ነው:: ግን ሳይሰማኝ ልክ እንደተሰማኝ ሁሉ ስድቡ ጠባሳ ትቶ የሄደ ይመስለኛል:: እንዴት ሊሆን ይችላል? የማይጎዳኝ ነገር እንዴት ጉዳት ያደርስብኛል? አደረሰብኝስ ብል ይሄ ተራ ስድብ የምንቀው ስድብ ለምን ወደ ጨለማ ይነዳኛል? እንዲህ መራራ የሆንኩበት ምክንያት ግራኝ በመሆኔ ሳይሆን ምናልባት ምናልባት እድለቢስ ስለሆንኩ ነው:: እናቴ እኔን የፀነሰችው በግራ ጎኗ ተኝታ ስለሆነ ይሆናል:: ምናልባት አባቴ እናቴን ያስረገዘው በግራ ጎኑ ተኝቶ ነው:: ምናልባት ስወለድ እናቴ ታምጥ የነበረው በግራ ጎኗ ተኝታ ነው:: የተገላገለችኝም ወደ ግራ ዞር ብላ ፀሐይ ስትጠልቅ እያየች ነው:: ምናልባት ያዋለደኝ ሐኪም ግራኝ ነበር:: ምናልባት ስወለድ ወይም ተወልጄ ግራኝ እንድሆን በሆነች የእናቴ ወይ የአባቴ ጠላት ተረግሜ ነበር:: እንደዚህ ተራ የመሰሉ ነገሮች የፈበረኩኝ ፍጡር ከሆንኩስ? ሰበቡ ብዙ ሊሆን ይችላል:: አያፍሩምና 'ጥሩ አእምሮ አለው ግራኝ ባይሆን ኖሮ' ማለታቸው አይቀርም:: ሰበብ አምላኪ ጠባብ ምድር ላይ የሽል ክርታሴን ቀድጄ መውጣት የከበደኝ እሆናለሁ:: በቀጥታም ይሁን እንዲህ በድኩም የእጅ አዙር ስድብ አጎብድጄ አላውቅም:: ለምን እንዲህ ሆንክ? ቢሉኝ በትክክል ምክንያቴን መንገር ይከብደኛል:: እንግዲህ ይኼው ምክንያቱን ሳላውቅ ወይ ምክንያቱን

እየገመትኩና እያማረርኩ ሰው የተባለ ፍጡር እጠላለሁ:: ይሄ እንደ እኔ በሁለት እግሮቹ ቆሞ የሚሄደውን፣ *በእግዜር አምሳል ተሰራሁ* ብሎ ጉራ የሚቸረችረውን ማለቴ ነው: ልነግራቸው እሻለሁ አይደለም ብዬ: አይጥ ዘጠና በመቶ የሰው ዘረመል (ዲኤንኤ) አላት እና ምን ልንላት ነው? እዛ ወፍጮ ቤት አንዲት የባቄላ ጥሬ በጉንጩ ይዞ የሚያልጎመጉመው ወንዴ አይጥ አጎታችሁ ነው:: ዝንጀሮ ዘጠና ስምንት በመቶ ጂኑ እንደ ሰው ነው ብዬ ልነግራት እፈልጋለሁ ያቺን ነገረኛ: *አትጎርሪ ሰማሽ እቱ ያ በመንገድ ስታልፊ መናገሻ ተራራ ላይ ያየሽው 'ውይ ሲያስቅ' ብለሽ የገመገምሽው ዝንጀሮ አማችሽ ነው::* ለከንቲባዬ ለዛ የለበጣ ለፍቶ አዳሪ እለዋለሁ: እዛ መናገሻ ተራራ ዋርካ ጫፍ ላይ ቆሞ ወደ አዲስአባ የሚያይ ገመሬ *ዘመዶቼ ምን ሊፈጥሩ እንዲያ ተሰበሰቡ?* እንዳለና ሁላችንንም እንደታዘበ እገምታለሁ::

አ! አምላኬ (ባላምንበትም ልማልበት) የማልጠላው ነገር የለም: የሚፈስ ወንዝ በሉት፣ የቆመ ሃይቅ:: አንዴ እንኳን አልጮኽብኝም ግን ያ እዛ ጋ ያለው ጎረቤቴ ያሳደገው ውሻ ያስጠላኛል:: ተራራውና ሜዳው ለመለሙ ይባል ደረቁ ያስጠሉኛል:: ኧረ ተራራው ምን ልሁን ብሎ አበጠ? መስኩስ ለምን ጠፍጣፋ ሆነ? የሚነፍሰው ነፋስ ያስጠላኛል፣ ምን አንቀለቀለው? ምን አንከወከወው? ከልባቸው የሚስቁ 'ሰው ነን' የሚሉ ፍጡራን ያስጠሉኛል:: ሲያወሩ ሲበሉ፣ እየበሉ ሲያወሩ ያስጠሉኛል:: ወሬአቸው ለብቻው ማለት ድምፁ ያስጠላኛል:: እህል ያቀለመው ጥርሳቸው ለብቻው ያስጠላኛል:: በጉርሻቸው ጉንጫቸው ሲያብጥ--ያበጠ ጉንጫቸውን ማየት ያስጠላኛል:: ምን ልሁን ብሎ ያብጣል? ምን ልፍጠር ብሎ ኳስ ይመስላል? የሚነቃነቅ አፋቸው፣ የጎረሱበት እጃቸው፣ የለበሱት ልብሳቸው (የፈለገውን አይነት ይሁን) ተራ በተራ ያስጠሉኛል:: ውሃ ሲጠጡ ጠጥተውም ጠግበውም ሲያገሱ ያስጠሉኛል:: ምክንያት ያስፈልጋልን? ይሄ ራሱ ምክንያት አይሆንምን? ኮታቸውን ሲቆልፉ፣ የሸሚዛቸውን ኮሌታ ሲያስተካክሉ፣ የሆነ ነገር ሲያደንቁ፣ ደሞ ሲያፋዋጩ፣ ደሞ ጆክ ሲቀዱ ያስጠሉኛል:: ፖለቲካ ሲያወሩ ያስጠሉኛል:: ዐይኖቻቸውን ሲከፍቱና ሲከድኑ ያስጠሉኛል:: ፊታቸው ያስጠላኛል:: የፊታቸው ወዝ ያስጠላኛል:: ለምን ወዙ? ለምን ያብለጨልጫሉ? ስለ ቆላ ሲያወሩ ስለ ደጋ ሲያወሩ ስለወይና ደጋና

ስለ አየር ፀባይ ሲያወሩ ያስጠሉኛል፡፡ ሞባይል ሲነካኩ 'ሚስኮል' ሲሉ ስለ ካርድና ስለቴሌ ስለመሳሰለ ሲቀባጣጥሩ ያስጠሉኛል፡፡ የጣታቸው ውፍረትና ቅጥነት ጥፍርና የጥፍር ቀለም ያስጠላኛል፡፡ የሴቶቹ እግሮች ያስጠሉኛል፡፡ እግር ነው ምንድነው? ጫማቸው ይባል ሊፒስቲካቸው ያስጠላኛል፡፡ ትንሽ ተረከዙ የተሸረሸረ ጫማ ሳይ ስጠላ፡፡ ቀሚሳቸው ያስጠላኛል፣ ተቀምጠው ሲነሱ የተጨማደደው የቀሚሳቸው መደብ ያስጠላኛል፡፡ ሲስቁ ያስጠላኛል፡፡ ኪኪያቸው ሂሂሂያቸው ያስጠላኛል፡፡ የጥርሳቸው ድርድር ያስጠላኛል፡፡ ያልታጠበ ወጥ ያረጠበው እጃቸውን አንቀርፈው ሲያወሩ ያስጠሉኛል፡፡ የሚበሉበት ትሪና የበሉት ፍትፍት ያስጠላኛል፡፡ በልተው የተረፋቸው ወይም ያስተረፉት ያስጠላኛል፡፡ የዐይን ኩላቸው ያስጠላኛል፡፡ የድድ የአንገት የክንድ ንቅሳታቸውም፡፡ የቂጣቸው ቅርፅ፣ የተንዘላዘለ ጡታቸውም ያስጠላኛል፡፡ ሃብላቸው ያስጠላኛል፡፡ 'ውይ ማርያም' ሲሉ 'ወይ ኢየሱሴ' ደሞ 'ወይ አላህ!' ሲሉ ያስጠሉኛል፡፡ ሲሽኮረመሙና አፋቸውን ሲይዙ ያስጠሉኛል፡፡ አድርገን ጨርሰን የውስጥ ሱሪያቸውን ወደ ወገባቸው ሲጎትቱ ያስጠሉኛል፡፡ የሱሪያቸው ላስቲክ ወገባቸው ላይ ያበጀው ሰንበር ያስጠላኛል፡፡ ጠረናቸው ያስጠላኛል፡፡ የወንዶች ፂም ያስጠላኛል፡፡ ክራቫታቸውን በአንድ እጃቸው እየተመተሙ በሌላ እጃቸው አፋቸውን ሲያፀዱ፣ አፅድተውም 'የተረፈ ሶፍት አለህ?' ሲሉ ያስጠላኛል፡፡ ስለ ትራንስፖርት ሲያወሩ ያስጠላኛል፡፡ ስለ ጠዋት ሲያወሩ ስለማታ ሲያወሩ ስለ ቴሌቪዥንና ስለ ዲሽ ሲያወሩ ያስጠላኛል፡፡ ስለ ብሄር ብሄረሰብ ሲያወሩ ያስጠላኛል፡፡ ስለ ቲቪ ቻነል ስለአረብ ሳት ስለ አልጃዜራ፣ ስለ ቢቢሲ፣ ስለ ሲ ኤን ኤን ሲያወሩ ያስጠላኛል፡፡ ስለብርድ ሲያወሩ ስለ ልብስ ሲያወሩ ስለ ስራ ስለአለመስራትና ስለመስራት ሲያወሩ ያስጠሉኛል፡፡ ስለ ዘፋኝ ስለ ሆቴል ስለ መጠጥ ስለ ቢራ ስለመሳሰለው ሲያወሩ ያስጠላኛል፡፡ ገንዘብ ሲከፍሉ ሳንቲም ሲያንካኩ ብር ሲቆጥሩ ስለ ደመወዝ ሲያወሩ ሲማረሩና ሲደሰቱ ያስጠሉኛል፡፡ ስለ ዶላር ስለ ዩሮ ሲያወሩ ያስጠላኛል፡፡ ስለትምህርት ስለ አስተማሪ ስለ ተማሪዎች ስለ ምንትስ ስለመሳሰለ ሲያወሩ ያስጠላኛል፡፡ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሰው ሲጠሩ ያስጠሉኛል፡፡ ሲሳሳሙ ያስጠላኛል፡፡ የሚሳሙት ጉንጫቸው፣ የሚስሙት ጉንጭ ያስጠላኛል፡፡ ጉንጫቸው ላይ የሚቀረው የምራቅ እርጥበት በዐይኖቼ

እንኳን የማይታየኝ በግምት እንኳን ያስጠላኛል:: ሲያንጥሱ ያስጠላኛል:: ሲያንጥሱ ያፌናጠሩት የንፍጥ ካፊያ የልጋግ ዶፍ ባላየውም ያስጠላኛል:: የአይናቸው ቀለምና ነጩ ያስጠላኛል:: ዐይናቸው ያስጠላኛል:: ቅንድባቸውም:: የዓይናቸው ዐይንአር እንደ ዓይናቸው ያስጠላኛል:: ሱሪው ያስጠላኛል፣ ሱሪዋ ያስጠላኛል:: ሹራቧ ያስጠላኛል:: ሹራቧን ስትቆልፍ ታስጠላኛለች:: የሹራቡ ቁልፍ የሚገባበት ጠማማ ቀዳዳ ያስጠላኛል:: ቁልፉም:: ሱሪዋ ተስማምቷት እንደሆነ ራሷን ስትደባብስ ያስጠላኛል:: ያ ቦርጫም ያስጠላኛል:: ያ ቀጫጫ ያስጠላኛል:: ቀይዋ ልጅ ታስጠላኛለች:: ጥቁሯ ልጅም ጠይሟም ቀይ ዳማዋም ያስጠሉኛል:: ሲጋራ የሚያጨሰው ያስጠላኛል:: የለኮሰለት ያስጠላኛል:: ሳይተኩ ያስጠላኛል የእሳቱ ነበልባልም:: ሲጋራውም:: ኮረኮንቹ፣ አስፋልቱ፣ የፀሐይ ብርሃኑ እና ጥላውም ያስጠሉኛል:: እዛ ቆሻሻ ቦታ የሚልከሰከሰው ድመት እንደ ቆሻሻው ያስጠላኛል:: ባለቤቱም:: ከብት እጠላለሁ፣ ቀንድ እጠላለሁ፣ አፍሪካን እጠላለሁ እና የአፍሪካን ቀንድ እጠላለሁ:: የቆምኩበት መሬት ያስጠላኛል:: የምቀበርበትም:: ሰማዩ ያስጠላኛል:: ደመናው ያስጠላኛል: እዛ ውስጥ ያሉ ፍጡራንም:: ለሐጭ እጠላለሁ፣ ሕፃናት እጠላለሁ፣ የሚያለቅሱ የሚስቁ ለሐጫም ሕፃናት እጠላለሁ:: ያን ሰው እጠላዋለሁ፣ ያን አህያ እጠላዋለሁ፣ እንደ አህያ የሚሰራውን ሰውዬ እጠላዋለሁ:: ጢም እጠላለሁ፤ ባለ ጢም ቄስና ሼካ እጠላለሁ:: ውሻ እጠላለሁ፣ እርግብ እጠላለሁ፣ እንሽላሊት እጠላለሁ፣ አህያ እጠላለሁ፣ ቁራን እጠላለሁ:: የአፍሪካ ቀንድ ውሻ ብሆንም ዐይነምድሬ የጅብ አይነት ነጭ ነው:: ይሄን ሁሉ የምጠላውን ሰብስቦ ሊይዝ የሚችል ገደል አለ? እነዚህን ሁሉ ሰብስቦ ወደገደል የሚገፋልኝ ታሪክ አለ? እኔንም ደብሎ ወደዛ ወደዛ የሚወስድ? ከእኔ ጥላቻ የሚያመልጠው ምንድነው? ማነው:ስ? ወይስ እንደአንዳንድ ብልጥ ነን ባዮች ጥላቻዬን ሁሉ አቅፎ የሚይዝልኝ የሆነ ፍልስፍና ላብጅ?

*ጌርሳሞት ኮላሴ:* የምወዳት በኪነጥበብና በዕውቀት ነው:: *ማናት እሷ?* በለኝ:: የሰፈሬ ልጅ የቀበሌዬ:: በትንንሽ መፎጋገር ነፍስህ የምትጠግብ ሳትሆን አትቀርምና ከፍታ ያለው ፍቅር የሚገባህ አለህ? እሷስ ከከንፈሮቿ ማማር ሌላ የመወ`ደድና የመውደድ ጥልቅ ዕውቀት አላት? ብነግራት ብተነትንላት 'ተነገረኝ' 'ተተነተነልኝ' ማለት

| ------------

ትችላለች? መውደቅ የፈለገ በዘጠኝ እግርም ያንሸራትተዋል: ማለት በእግዜር ደማቅ እርግማን ስር የወደቀ......የማወቅ ንፉግነት በአእምሮው ሸለቆ እንደ አውሬ ያደባበት በዛም የሚፈነጭበት:: እሷስ: ቢነግሯት የማትሰማ ጠባብ ዓይኖቿ ከከንፈሮቿ ወጋገን አልፈው የማያዩ ያልታወረች ዕውር:: አልገባትምና ይውጣላት አልልም::

==============================

| ከጌርሳሞት የምግባባበት የፊደል ገበታ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | | ሞ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ሀ | ሁ | ሂ | ሀ | ሄ | | ሆ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሔ | ሕ | ሖ | |
| የብዙኀኑ ‘ኀ’ ዝርያ በሙሉ | | | | | | |
| ከ ሀ እስከ ፐ ያሉት ሳብአች በሙሉ | | | | | | |

ጌርሳሞትን በአሥራትና በአስቴር ብቻ ሳይሆን በሺህ ሂጂራ እለውጣታለሁ:: ጌርሳሞት አፊ ውብ፣ ከንፈረ መአት የሚያምር ነገር ናት:: ሰው ፊት ላይ አበባ ይበቅላል ሲባል እውነትነቱ እሷ ጋ አለ:: ሳብዕ ሆሄዎቿ የጆሮ ጣዝማ ናቸው:: በከንፈር ገናናነት የሚነገሩ ሆሄያትን ስትጠራቸው አጠገቧ ቆሜ አስገራሚ ሰመመን ውስጥ እገባለሁ:: **ሖ** ስትል ከንፈሮቿ ተሰብስበው ከመሃላቸው በሚፈጥሩት ቀዳዳ የሚወጣው ቀይ ቀለም ያለው የሆነ ፍላትና ትኩስ አየር ነው:: **ሖ** ስትል የሰማት ይመረቃል:: ***በ*** ስትል ከከንፈሮቿ ንክኪ የጉድ ውበት ይታያል:: ***አበበ*** ስትል ከሰፈራችን ሰማይ የኦፔራ ቃና ይዘንባል:: እመረቅ ነበር እንዲህ ቢሆን: ከከዮም እስከ ዮም ሆሆ እያልነው......ሆላ ሆላ እያልነው......የባቢሎ ቆሎ እየበላላን...... መላመላን ስንሰማማ......ያማረ ኖታ በሎመሎመ አፏ......መላ መላ በጆሮ......የከንፈሯ ጎባ ቀለሙ ዮጵ: የልቤ

---

ካቦ......የከንፈሯ ጵጵ ......የሶታዋ መሃላ......ዞሮ ዞሮ መላ መላ ደሞ በዦሮ......ከዮም እስከ ዮም እ:: ዛሬ እየተሳመች ብታድር ሲነጋ ተመልሰው ድንግል የሚሆኑ ይመስላሉ:: ታች ከንፈሯ ላይ ያሉትን የደቃቃ ሰንበሮች ቁጥር አውቃለሁ:: ስራ ፈትቼም ቆጥሬ ነበር: 55:: በነዚህ ሰንበሮች መሃል የእሳተገሞራ ጅረት ይወርዳል:: በላይኛውና በታችኛው ከንፈሮቿ መሃል ባለው ክፍተት ነጭ ቀለምሲስ ይረቻታል:: የተረፈውም ወደ አገጭዋ ይንዣረራል:: አንዳንዴ ለልቤ ብቻ የሚሰማኝ መለኮታዊ ፉጨት ከዛ የሚፈልቅ ይመስለኛል:: በፈገግታዋ አፏ ግራና ቀኝ ሲሳብ የደረቴ ዚፕ ይከፈታል—ባልተጠበቀ ፍጥነት አእምሮዬ መስክ ላይ ከአድማስ አድማስ ፅጌሬዳ ይበቅላል:: ያን የቀለም ዘፈንና ድንቅ ትርምስ ዱርዬነቴ ይመከተዋል? ምን ይጎልብኛል የምዋሽህ? የከንፈሮቿን ክፈፍ አይተሃል? የደርዙን መስመር? ለእሷ ብቻ በተመደበ የፊደል *ገበታ* ልቤን ቀጻ መልሳ ባልሆነ ቅርፅ ስትገጣጥመው: እሱንስ አይተሃል? ማታ ማታ ቤቴ ተኝቼ በእንጨት መስኮቴ ሲገቡ እሰማለሁ:: ብርድልብሴን ገልጠው ገብተው ገላዬን አፍርሰውት ይሄዳሉ:: ስሜው እንኳን የማላውቀውን ከንፈር በቅዠቴ እንደ አፍረተ ብእሲት ስደክል አድራለሁ::

ብዬአት ነበር፣ ጆሮ የላትም: እንደ ቻርለስ ቦደሊየር *ከወይንና ከዕፅ፣ ፍቅር የሚርገበገብበት የከንፈሮችሽ ቅመም ይሻለኛል* ብላት:: አይገባትምና ግን ከከንፈሮቿ ጀርባ ያለውን አንጎሏን ቀልድ በተለሰነ የወሬ ቅራቅንቦ፣ የሳቅ ጠረን ባለው አንካሳ *ፖለቲካ*፣ ኮሚክ ነው በተባለ ኮሚክ ባልሆነ ጨዋታ ትሞላለች:: አንገቷን ሰብራ በዓይኖቿ አድማስ የምታየው *ጨዋ* የተባሉትን ነው:: ስለዚህ ጌርሳሞት ዘሪሁንን የምትወደው የሰፈር ሰው ስለሚወደው ነው:: ይሄ አደጋ የለውም:: ባካፋን የምትወደው የተሳካለት ኮስሜቲክስ ቢዝነስ ማን ስለሆነ ነው:: የማይሸጥ የማይለወጥ የለምና አልታዘባትም:: ቢሆንስ ውብ ከንፈሮቿ የተፈጠሩት ከሊፕስቲክ በፊት አይደለምን? ይሄ ሁሉ ግን ለምንድነው? መአት ነገር ጠልቼ እሷን የወደድኩበት ምክንያት ፍልስፍና ስለምታወራ አይደለም:: የሚባል አታውቅም:: አዎ ተጫዋች ናት እና ምን ይጠበስ? *ሥነሥርአት* ያላት ልጅ ናት:: አሁንስ ምን ይጠበስ? ጎበዝ ተማሪ እንደሆነች ይወራል፣ ከሁኔታዋም አይቼአለሁ:: አሁንም ምን ይጠበስ? የፀዳ ላድርገውና የወደድኩት አፏን ብቻ ነው:: ስህተት

ነው የምትል (መለስከልኝ አልመለስከልኝ አፍህን ከመከፈትህ በፊት ልንገርህ እጠላሃለሁ) መረጃውን እንካ በለኝ::

ስጋዬ የዱርዬ ነው:: ይገባኛል:: የሚቀርቡኝ ጓደኞቼ እንደሰለጠነ የሚሰራቸው እንኳን በፈረንጅ የልብስ ዝተት የሚኳሉት በዘመድ አዝማድና በጎጥ ጥቅሻ ስራ አግኝተው እኔን የማይረቡ ሰዎች ተራ እንደመደቡኝ አውቃለሁ:: ከዚህ ቀጥሎ 'ደደብ' እንደምባል አውቃለሁ:: ሽሙጣቸውን ብሰማም ያልገባው መስዬ እታዘባለሁ:: እንዲህም በማድረጌ 'ከብት' እንደምባል አውቃለሁ:: ቀጥሎም ቄራ እንደማድር ይወራል:: ከዛም በደንቡ አንዱ ልኳንዳ ስብሳብ ሽንጤ ይንጠለጠላል:: ይሄው:: *ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው* ይል የለ መፅሐፉ ምሳሌ:: ምንጩን ባልወደውም እስኪ ይሄን አባባል ልዝረፈው:: ጌርሳሞት እውነት ናት::

ከሰማይ በታች አዲስ ነገር የለም ይባላል:: ማነው ያለው? የዞረበት የብሉይ ሰው? ያ ዘመድህ? በቀቢፀ ተስፋ (እኔን መሰል) ትንሽ አሰማምሮ የዘባረቀውን ኮፒ እያወራህ አስቸገርክ እንጂ አዲስ ነገር አለ:: ጌርሳሞት አዲስ ናት:: የጌርሳሞት አፍ ነጋ ጠባ አዲስ ነው:: የማውቀው ይሄንን ነበር:: የማየውን የኖርኩትን የእውነቴን ሰረሰር በቅዱስ መፅሐፍ አልገርፈውም:: *ሁሉ ባለው ነው* እንዳለ: ባይ:: *አባቷ ግን ለምን ይገላምጠኛል? ለምን ያስፈራራኛል?*

*

ያደርኩበት የአንድ ጓደኛዬ ኮንዶ ውሃ ስላልነበረው ገላዬን መታጠብ አልቻልኩም:: በጠዋት ለአስቴር ወዳጄ ደውዬ መታጠብ ትፈልግ እንደሆነ ፍልውሃ መግቢያው ጋ እንድንገናኝ ነገርኳት:: እኔ ያለሁት ጦር ሃይሎች፣ እሷ የምትኖረው ሲ ኤም ሲ:: የማይሆን ቀጠሮ ባስብም ብቻዬን ውሃ ካፊያ ስር መቆም አልፈለኩም:: ደሞ ቀዝቃዛ ነው ጠዋቱ:: ትክክሉ የሞቀች ልጅ የሞቀ ውሃ ስር ማቀፍ ነው:: እንደማትመጣ ያወቅሁት ደውዬላት እሺ ካለችኝ በኋላ ያኔውኑ ሞባይሌ መልሶ ሲጮህ ነው:: አልከፋኝም:: ፍልውሃ ብቻዬን ሄጄ ያለብዙ ሰልፍና ድካም ታጥቤ እንደወጣሁ፣ መስሪያ ቤት ለመሄድ

ሃይገር ባስ ተሳፈርኩ:: ሳንቲሜን ለአስተናጋጁ ከፍዬ፣ ያልደረቀ ፀጉሬን ዳብሼ፣ ጨው የመሰለ ፊቴን በደረቅ እጄ አብሼ፣ በደንብ ያላዳረቅሁት ውሃ የያዘብኝን የውስጥ ሱሪዬን ለማስተካከል እልፎ እልፎ እተቀመጥኩበት ስንቆራረጥ ቆየሁና ትንሽ እንደተረጋጋሁ:

--ከየት ነው በሌሊት? አለኝ እዛ ውስጥ ይኖራል ብዬ ያልጠበቅሁት አንድ ሰው:: ፈገግ ብሎ::

በዚህ ጠዋት ፈገግ የሚል ሰው የታመመ ነው:: ብዙ ጠዋቶች ዝምታ ናቸው:: ለዝምታ የተመደቡ ናቸው:: ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲለኝ ምሳ ሰአት የደረሰ ወይም እማማና ሙና እራት እንድበላ የጠሩኝ መሰለኝ:: ይሄ የሰፈሬ ልጅ *ዘሪሁን* ይባላል:: ጌርሳሞትን ለመጥበስ በሚደረገው ሽሚያ ውስጥ አንድ ሰሞን አለሁ አለሁ ሲል ቆይቶ የነበረ አብሮ አደጌ ነው:: ግን እጠይቃለሁ: እንደዛ የሚያምር አፍ ያላትን ቀጫጫ ቂጠአልቦ ልጅ አራታችን ለምን ተዋደቅንላት? እና ዘሪሁን ከእኔ ጀርባ ሁለተኛው ወንበር ላይ ብቻውን ተቀምጧል:: እንዴት ስገባ አላየሁትም? እንዲቀርበኝ ዘሪሁን ወደ ተቀመጠበት ወንበሬን ትቼ ሄድኩ (በዛ ብርዳም ጠዋት ገና ባልተፍታታ መንገጭላዬ፣ ምላሴ፣ አፌና ላንቃዬ ጮኼ ላለመነጋገር):: ባይመቸኝም የዘረጋልኝን ቀዝቃዛ እጁን ጨበጥኩና ጎኑ ስቀመጥ ከት ብሎ ሳቀ:: በቀኝ እጁ የያዛትን አምስት ሳንቲም (ለአስተናጋጁ ከፍሎ የተሰጠው መልስ መሰለኝ) አውቶቡሱ ሲቆምለት ወደ ላይ አጉኖ ቀለባትና ግራ እጁ አይበሉባ ላይ ድብድብ ሰራት:: ቀኝ እጁን በቀስታ አነሳና ለራሱ አይቶ:

--ዛሬ ጥሩ ቀን ነው አለ::

*ጠንቋይ::*

በክርኑ በቀስታ ጎሰመኝና በድጋሚ ማራኪ ሳቁን ሳቀ:: የዘሪሁን ጥርስ የሚያምር ነጭ ነው:: እህል የሚበላበት አይመስልም:: ወሬ ሲያቆም የአፉን ቦታ የሚይዘው ፉጨትና መፋቂያ ነው:: ከንፈሮቹ ላይ ተጣብቀው የቀሩ የእንጨት ፍቅፋቂዎቹ እስኪረግፉ ያወራና ሲያርፍ እንጨት ይወትፋል:: ይቀጥላል:: አንዳንዴ የድድ ማሳጅ የሚያደርግ ይመስለኛል:: ብቻ በጥርሱ ንጣት የሆነ ዝቅተኛነት

ያሰማል። በወሬኛነቱ ግን ይጣጣል። ጥርሱ ደስ ሲል ብለው ሲያሞካሹ ደሞ ያ ወሬኛ ብሎ ማውረድ ነው። ይሄ የጠበሳ ፖለቲክስ ነው። ከፈለግህ ቴክኒኩን ለፖለቲካ ፓርቲህ ተገልገልበት።

ዘሪሁን ወሬ ለቃሚና በታኝ ነው። መረጃ ሰጥቶ መቀበል ስለሚችል የመረጃው ጮጮ ደርቆ አያውቅም። በሰዎች የሚወደደው ለዚህ ነው። በወሬኛነቱ እየወደድነው ግን ደሞ በወሬኛነቱ መልሰን እንሰድበዋለን። ያጋጠመውን ወሬ መተርጎም ሲጀምር የሚያስፈራ ነገር አለው።

ለምሳሌ ያ የምናውቀው የስፈራችን ልጅ *በቀለ* በርጫ ያደርጋል ልበል። የበቀለ አባት ቤተክርስቲያን ከድሮ ጀምሮ ያዘወትራሉ ልበል። ደሞ የበቀለ እናት በጠና ታመዋል ልበል (ኪንታሮት)። ዘሪሁን እነዚህን የተበታተኑ መረጃዎች በራሱ ፍላጎት ያደራጃቸዋል። *በቂ (ያቀላምጠዋል) አደንዛዥ ዕፅ ይወስዳል* እና *አባቱ የሚያሳዝኑ ሰውዬ፣* (ከንፈሩን እየመጠጠ) *እጅ ከፍንጅ ይዘውት ምክራቸውን አልሰማ ቢላቸው ቤተክርስቲያን ጠዋት ማታ ይሄዳሉ......እናቱማ ታለቅሳለህ ብታያቸው፣* (ጭንቅላቱን ይነቀንቃል) *በእሱ ምክንያት ታመው የአልጋ ቁራኛ ሆነዋል......ያሳዝናሉ* ብሎ ቅር ሳይለው ይተረትራል። ይሄ አይነት ወሬኛ በአገሩ ካለ መከላከያ ሚኒስቴር ያስፈልጋል? ወይም *ባዮሎጂካል ዌፐን?*[36] እንዲህ አይነቱን በሄሊኮፕተር ጭኖ ወስዶ በፓራሹት ጓንታናሞ መጣል ነው።

የገለታ ጎረቤት ስለሆነ ስለገለታ ጠየቅሁት።

ገለታ በትክክል ማን እንደሆነ አይታወቅም። አንገቱን በቋሚነት የደፋ እስስት ማለት ነው። ገለታ ወዳጆችን በአጭር ጊዜ ጴንጤ ሆኖ በአጭር ጊዜ በአንድ የአሜሪካ የክርስቲያኖች ድርጅት ስፖንሰርድ ሆኖ በአጭር ጊዜ ቪዛ እንዳገኘ አስወርቶ ከአገር የወጣ ነው። የገለታ ሁሉ ነገሩ ክርስቲያናዊ አልነበረም። ሰኞ ዕለት 'እናትክን' ብሎ ተሳድቦ፣ ማክሰኞ ጴንጤ ሆኖ፣ ረቡዕ በሲአይኤ እስፖንሰርድ ሆኖ፣ ሐሙስ *አድራሻሽ ጠፋብኝ* ብሎ አንጎራጉሮ፣ አርብ ገብሬልን ተሳልሞ፣ ቅዳሜ *ስደት* አማሮ፣ እሁድ *ስደት ከዚህ አገር ጣጣ ይሻላል* ብሎ አስወርቶ ይሄንንም የሚያምነው ማግኘት የሚችል

ልጅ ነው:: ገለታ ለብዙ ሰው ብዙ አይነት ሰው ነው:: ምክንያቱም እሱንም ጨምሮ ዊ አር ኦል ኢድዮትስ:: የምር አንረባም፡ ታዲያ ራሴን ጨምሮ እንዲህ አይነት ሰዎችን ልውደድ እንዴ?

ባሱ ውስጥ ገብቼ እስክወጣ በእኔ ጉጉት ልክ የተቀደደ፣ በስውር ስፌት የተሰራ ማመን የሚቻልና የማይቻል ወሬ አወራኝ:: በጣም ልክ ከመምሰሉ የተነሳ ማብራሪያ እንዲያቀርብልኝ መጠየቂያ ጊዜ አልነበረኝም:: የዘሪሁን ወሬ ፍሰቱ እንዲህ ነው:

----ስራ እንዴት ነው?----ተስማምቶሃል መቼም---ኤልፓ ዞን ነው የምትሰራው አይደል? ልክ ነኝ? እረሳለሁ---የት ነው ግን? የምር---እዛ ነህ?----እንዴ ቆይ የምታውቀው ከሆነ----ከትናንት ወዲያ የሆነ ነገር እዛ አካባቢ? በሚካኤል----የኛ ሰው እኮ---እንዴት?---መጨረሻው ፎቅ ላይ ቢሮ የለም መጋዘን ነገር ነው:: ታች መሬት ላይ የልብስ ሱቅ የለም? የእሱ መጋዘን ነው:: መአት ማንኪን[37] አለ እዛ---ታዲያስ እዛ ያሉ ሴቶች ተጣልተው ነው አሉ:: ያገኙትን ሲወራወሩ---ለምን ይሞታል? ምን ብሎ:: ማነኪን ከላይ ከመጨረሻ ፎቅ ላይ ወደቀ---ሰው ነው ብሎ ያመነው መአት ነው---የእኛ ሰው እኮ ወሬኛ ነው---አምቡላንስ አይደለም:: እሳት አደጋ ነው:: ያው እሳት አደጋ ሲመጣ አምቡላንስ መምጣቱ አይቀርም----ጩኸት? ሁሌም መንገዶች በጩኸት የተሞሉ ናቸው:: ወጣ ብትል እንደዛ ነው ቀንና ማታ:: ከዛ ሰዎች ከፈለጉት አጋጣሚ ጋር ጩኸቱን ያገናኙታል---ደረስክ? እዚህ ነህ እንዴ? ----እዛ መስሎኝ ነበር----ገለታን ሰላም እልልሃለሁ ከዓፊ.......

ከአውቶቡሱ ልወጣ ወደ በሩ ስጓዝ ከሾፌሩ ቦታ ከሬድዮ ዜና ያካፋል '.......ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ......ትናንት' ሲል ሰማሁት:: ትክክለኛ ዜና ሳይሆን አውቶቡሱ ውስጥ የነበረውን የአፍታ የጸጥታ ጉድጓድ ሊደፍን፣ የማይታይ ሰው የወረወረው ውታፍ ይመስላል:: አቀባይ ማነው? የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካቀበለኝ ላይቀር በርጫውን ነው:: አንድ ደህና ሉሉ ከአንድ ዶክተር አምባሳደር እንጂነየር ይበልጥብኛል.......................

182

ከአውቶቡሱ እንደወረድኩ መስሪያ ቤቴ አጠገብ ያለው ኢንተርናሽናል ዲቨሎፕመንት ባንክ ሕንፃ(IDB) ስር ቆምኩ:: የስራ ጊዜዬ እየደረሰ ለወሬ መቆሜ አልገረመኝም:: ከሕንፃው ስር ከግራ ወደ ቀኝ ወይም ከቀኝ ወደ ግራ የተሰለፉ ሶስት ሱቆች አሉ:: ዐይኖቼ ያረፉት በስተግራ ካለው *ፓራዳይዝ ፋሽንስ* የተባለው የልብስ መደብር ላይ ነው:: በግራ በኩል የወንዶች፣ በቀኝ በኩል የሴቶች ልብስ የለበሱ *ማነኪንስ* በተለያየ ቁንጥ ቆመዋል:: የሁሉም ሁኔታና መልክ የፈረንጅ ነው:: ትልቅ የፎቶ ማስታወቂያ በቀኝ በኩል በግማሽ የሕንፃው ግድግዳ ላይ፣ በግማሽ ደሞ የሱቁ መስኮት ላይ ተሰቅለዋል:: ፎቶው ላይ ሁለት ሴቶች ይሮጣሉ:: ሁለቱም እየሮጡ ወደ ሰማይ አንጋጠው ያያሉ:: በአንጋጠጡበት አቅጣጫ እንደፀሐይ የምታበራ አንድ ትልቅ የሱፍ አበባ አለች:: ከፊት ለፊት ያለችው ሴት አበባውን የምታይ ሳትሆን ከአፏ አከፋፈት ድንገት አበባው ቢወድቅ (ወይም እየወደቀ ነው) ቀልባ የምትውጠው ትመስላለች:: የሚያምር ጥርስና ደስ የሚል ሰፊ አፍ አላት:: ወደ ፎቶው ስቀርብ *የፍቅር ዋሻ* የተባለ ፊልም ስትሰራ እንዳየኋት ትዝ አለኝ:: ሲኒማው ላይ ፍቅርም ዋሻም አልነበረም:: ከእሷ ጀርባ ያለችው ሴት የሰባት ወይም የስምንት አመት ትንሽ ልጅ መሆኗን አየሁ:: የዚህች ልጅ አፏ ጌርሳሞትን አስታወሰኝ:: የዛች የጌርሳሞት አፍ ምን እየበላ ይሆን? ምን እየተቀባና ምንስ እየላሰ ይሆን? ደሞስ እየነከሰስ ይሆን? ክቡራትና ክቡራን (እነ ክኮች) የእናታችሁን ደግ ፊት የሚረሳ አንጀት አላችሁ? እንደዛ::

ባሱ ውስጥ ዘሪሁን የነገረኝን ወሬ ለማረጋገጥ ሰፍ አልኩ:: ጊዜ ሳላጠፋ መንገድ አቋርጬ የሕንፃው ሎቢ ውስጥ እራሴን እየጎተትኩ ገባሁ:: የተንቀለቀልኩ ይመስለኛል:: የመሬት ስበት ብቻ ሳይሆን ዛሬ የሚያዘኝ በወሬ ጥማት መገዛት ነው:: ሕንፃው ውስጡ ውብ ነው:: በዚህ ውበቱ የታወቀ ነው:: እዛ የሚሰሩ ሰዎች በውበቱ ጉራ ይነፋሉ:: ግን ገብጋባ ነው:: ሕንፃው ለዐይናችን ሃብታም ይሆንና እኛ ሰዎች ጋ ሲደርስ ገብጋባ ይሆናል:: ብዙዎቹ ሠራተኞች ደህና የሚከፈላቸው ናቸው ቢባልም ደሃ ይመስላሉ:: ሕንጻው ባለጨረር፣ ሰዎቹ

ባለማድያት ናቸው:: ሃብታም መሆን የሚገባቸው ችጋራም ችጋራም የሚሸቱት የሚውሉበት ቦታ ከእነሱ የተሻለ ስለሆነ ነው? ፊት ለፊቴ የተተኮሰ ዩኒፎርም የለበሱ ሰው መፈተሽ የሚያፍሩ የመሰሉ ወጣት ወንድና ሴት ዘቦች ጎን ለጎን ቆመዋል:: ወንዱ ገና ሲያየኝ ከስራ ባልደረባው ተነጥሎ ወደ እኔ አቅጣጫ እየመጣ እንደሚያቅፈኝ ሁሉ እጆቹን ግራና ቀኝ ዘረጋ:: እንደማላመልጥ ስላወቅሁ እኔም እጆቼን ግራና ቀኝ ሰቅዬ ቆምኩ::

--ምን ነበር ጉዳይዎ ጌታዬ? አለ

--አንድ ጓደኛዬን ለመጠየቅ ነበር::

ነካ ነካ አድርጎ ፈተሸኝና በግራ እጁ አሮጌ የእንጨት ጠረጴዛ ጀርባ የተቀመጠች ፊቷ በሊፒስቲክዋ ክብደት ወደ ፊት ያዘነበለ፣ ከርካሽ የቻይና ካናቴራ ስር የተደፈጠጡ፣ ትላልቅ ጡቶቿ እንዲታዩላት ወደ ሚመለከታት ገፋ አድርጋ የተቀመጠች ሴት አሳየኝ:: የፊቷ ቡናማ ቀለም ጀርባዋ ካለው ግድግዳ ጋር የተማሰለ ነው:: 'ና' እስክትለኝ ድረስ አልጠበቅሁም:: ወደ እሷ ስቀርብ ፈገግ አለች::

--ሰላም......አልኩ

ኮስተር ብላ

--ሰላም......ማንን ነበር? አለች

--ጓደኛዬን ለመጠየቅ ነበር

--ማንን? የተባልኩትን ሳልመልስ --የት?

--ፎሬይን አንቨስትመንት[38] የሚሰራ

--ማንን?

--ባካፋ

--ይቅርታ ጋሼ

--እንዴት?

--ታመው አልገቡም:: ጓደኛው ከሆኑ እንዴት አላወቁም?

--ምኑን ነው የማውቀው? መታመሙን?......ቀና ብላ ዘበኞቹን አየች:: አንዱ ወደ ጠረጴዛው ጠጋ አለና ጆሮውን ወደ እኛ አቆመ:: ሪሴፕሺኒስቶች የፊታቸው ቀለም (ከጠይም ወደ ጥቁር ከጥቁር ወደ

ጠይም ከተቃጠለ ወደ ጨስ ከጨስ ወደ ዘነበበት በተለዋወጠ ቁጥር፣ የዘበኞች የእግር ንቅናቄ ከጎረቤት ወደ ታጣቂ ይለወጣል:: ፊታቸው ከሚስቅ ወደ ሚናከስ ይንሸራተታል:: አስገራሚ ልዋጤ ነው)

--ከተደዋወልን ቆየ……ማለቴ ከተገናኘን አልኩ

ባካፋን ካየሁት መአት ወራቶች አልፈዋል:: እንኳን በወሮች በቀኖች ልዩነት ብዙ ነገር ይሆናል:: ትንሽ ገፆች ያላት ልቤን አንብባ የደረሰችበት መሰለኝ:: (ልብህ የአስር ሳንቲም ደብተር ነው ብላኝ ነበር ክፍታፍ ወዳጄ አስቴር):: ባካፋ አካውንታንት ሆኖ ስራ ሲይዝ ገና በጫት ቅጠል የምነድ የስድስት ኪሎ ሶፍሞር ነበርኩ:: እዚህ እንደሚሰራ ያወቅሁት ሲወራ ሰምቼ ነው:: በድርቅናዬ ፀናሁ::

--ማን ልበል ስምህን?

--ራሚሱ

--አቶ ራሚሱ ሰማህ አቶ ባካፋ ታመው አልመጡም

--ምን ሆነው? *አንተ ይባላል?* ከታመመ የት ሆስፒታል እንዳለ ባውቅ ደስ ይለኛል

--ኬንያ ለሳምንት ሄደው በምግብ መመረዝ ታመው መጡ

--ምግብ? *ሰው በሚወደው ይጠፋል ቢሉ እሱ የታደለ ነው*

--ይገርምሃል ከኬንያ ተመልሰው እንደመጡ አዲስ ሞባይል ገዝተው ነበር እና ሞቶባቸው ቻርጅ አድርጊልኝ ብለውኝ ምሳ ሰአት አካባቢ ላይ ትኩሳት ጣላቸው:: ከትናንት ወዲያ ነው?

--ምን? ከትናንት ወዲያ መስሪያ ቤታችሁ ጀርባ ያየሁት አምቡላንስ

--የምን አምቡላንስ?

ወደ አላሰብኩት አቅጣጫ እንዳይሄድ መጠንቀቂያ ጊዜዬ ያለፈ መሰለኝ:: ዘበኛው ኮስተር ብሎ:

--ሁልጊዜም እዚህ አምቡላንስ አለ:: 'የአትላንታ ጄኔራል ሆስፒታል' ቦታ ተከራይተው ግቢያችን ውስጥ ያቆማሉ:: በሆነ ባልሆነው ሳይረን ያጮሃሉ::

--ዝም ብዬ ነው አልኩ በማፈር

--በአምቡላንስ ሳይሆን በራሳቸው መኪና ነው ጓደኛቸው ወደ ሆስፒታል የወሰዱአቸው:: አይደለ? አለች ጠባቂውን እያየች:: የምታውቀውን አታውቅም? ጎንበስ ብላ አንድ ጥቁር ሞባይል ከነቻርጀሩ ከጠረጴዛ ስር አውጥታ እያገላበጠች :

--ቢሻላቸው እዚህ ይደውሉ ነበር አለችና ቀና ብላ አየችኝ:: ለመሄድ ከተቀመጥኩበት እንደተነሳሁ ስልኩ እጇ ላይ ጮኸ::

--ወይኔ እማማ! ብላ በድንጋጤ ጠረጴዛ ላይ ጣለችው:: ስልኳን ከጣለችበት እንደማንሳት ደረቷን በእጇ ይዛ በሳቅ ፈረሰች:: የአሳሳቋ ቅንነት ደስ ይላል:: ስልኩ እየተንፏቀቀ መጥቶ ከእንብርቴ ዝቅ ብሎ ገጨኝና በሚረብሽ ድምፅ እየተንቀለቀለ ቆመ

--ይቅርታ ይቅርታ እያለች በራሷ አደነጋገጥ ስትስቅ የስልኩን ገጽ በትኩረት አየሁት::

ከቁጥሮች ሰልፍ ከፍ ብሎ በእንግሊዘኛ 'ጌርሳሞት' ይላል:: ጂ ኢ አር ኤስ ኤ ኤም ኦ ቲ GERSAMOT

ይሄ ስም ቢያስደነግጠኝም ቁጥሮቹን በተቻለኝ አቅም ልብ ለማለት ሞከርኩ:: ሬሴፕሺንስቷ የሚጠራውን ስልክ አነሳችና:

--ማነው ድምፁን እንደዚህ ከፍ ያደረገው? አለችና መልዕክቱን አየች::

--ውይ ይህቺ ልጅ ሃያ ጊዜ ሳትደውል አትቀርም አለችና አቀርቅራ ለራሷ ፈገግ አለች:: ቁጥሩን እንዳልረሳው በአእምሮዬ አመላልሰዋለሁ::

--ሰማህ ወንድሜ ሌላ ጊዜ ብቅ ብለህ ጠይቅ አለችና ስልኩን ዘግታ በቡናማ ቆዳዋ አየችኝ:: ጡቶቿ የዝሆን ዐይን ይመስላሉ::

ወደ ውጭ መውጣት ጀመርኩ:: ሞባይሌን ከደረቴ ኪስ አወጣሁና የስልክ ዳታዬን በረበርኩ:: ጌርሳሞት የተባለችው የስፈሬ ልጅ እንደሆነች አወቅሁ:: ያቺ ባለ አፍ:: ያቺ ባለ ከንፈር:: ይሄን ጤይባ አካውንታንት ምኑን አይታ እንዲህ ተንሰፈሰፈች? ቀናሁ:: ባካፋ የምግብ አለርጂው ወይም በምግብ መመረዙ እንዲበረታበት ሳልፈልግ አልቀርም:: እንድጸልይለት ወይ ስለት እንዳስገባለት ሙጭጭ ብሎ አለቅም የሚል የአለርጂ አምላክ ኬንያ አላት?

---

*

መቼ ዕለት ለጌርሳ ደወልኩላትና ተቃጠርን:: የተቃጠርንበት ቦታ ሄጄ ለአስር ደቂቃ ያህል እሷን ጠበቅሁ:: እሷ ቀድማኝ መጥታ ፊት ለፊቴ ተቀምጣ እያየኋት አላወቅኋትም ነበር:: ማለት ጌርሳን:: ማለት ጌርሳሞትን:: ለምን? አትለኝም::

'አቡ' ብላ ስትጠራኝ ድምፅዋ ራሱ ተለውጦ ነበር:: ያ የሚያባባኝ የአፏ ውበት የለም:: 'ቡ' ስትል ጥርሶቿን ለቀቅ አድርጎ ወደፊት የሚመጣው ፍራፍሬ ከንፈሯ የለም:: ያበጠ ነው:: ሂደት የማይጫወትበት አፍ ነው:: ወደ ማሞጥሞጥ አይነቃነቅም:: ሆሄው 'ቡ' የተባለው ካዕብ ከአፏ ሲወጣ ከንፈሮቿ የተንቀሳቀሱት ከእብጠት ወደ እብጠት ነው:: በሚሰሩት ቀዳዳ መሃል የሚብለጨለጭ አሉሚኒየም ነገር አለ:: እሷ መሆኗን ለመረዳት ሰኮንዶች ወሰዱብኝ:: ይኼን መዘግየቴን እንደ ስድብ ሳትቆጥረው አልቀረችም:: ልክ እኔ እንዳዘናጋኋት እሷ ራሷን እንደዘነጋች ይሄንንም ሁኔታ መረዳት እንደተሳናት ማን በነገረልኝ?

--ታዲያስ ጌርሳ!

ፈገግ ስትል ጥርሷ ዙርያ የሽቦ አጥር አለ:: ያ የተስተካከለ ከንፈሯ የብረት ማገር ላይ እንደ ዳቢት ተንጠልጥሏል:: ወደ ሚስጢራዊ ጨለማ የሚጠፉት የከንፈሮቿ ዳርና ዳር የጥሬ ስጋ ቀለም አላቸው:: ከንፈሮቿን የሳተው የእነ ባካፋ የከንፈር ቀለም ሽቦው ላይ በመጠኑ ተለድሷል:: ገና ፊት ለፊቷ እንደተቀመጥኩ መናገር የሚገባኝን ግን መናገር የማይገባኝን ነገር ተናገርኩ::

--ለምን ብሬስ አስደረግሽ?

እንደ ማፈር ፊቷን አዞረች::

--ይሻላል:: ጥርሴ አስጠላኝ

--ከንፈሮችሽስ? እንደሚያምሩ አልተነገረሽም?

--ምንም አይሆንም ብሎኛል ሃኪሙ

--የምን ሃኪም?

--አሪፍ ሃኪም ነው:: እንግሊዝ አገር ተምሮ የመጣ::

---

ጌርሳ ፖለቲከኛ ናት፡፡ እንዳላማረ እያየችው ትከደዋለች፡፡ እየገባት ታጠፋፋለች፡፡ እና ቆይቼ ደደብ መሆኗ ገባኝ፡፡ ለመሆኑ ጌርሳ ስታወራ በድምፅዋ ያልተማረከ ይኖራል? ሆሄዎቹን ስትጠራ በሚወጣት ቅላፄ የተደሰቱ የታቦት ማደሪያ ላሞች በቀን ሃያ ጊዜ እየታለቡ አላጋቱም? እያጋቱ አልታለቡም? የታለቡትንስ ወተት አልጠጣንም? የፋፉ የባቄላ በቆልቶችን እሱን ወተት ጠጥተው በጠነከሩ የልጅ ጥርሶቻችን አልጠረጠርንም? ለመሆኑ ላሞቹ ምን ይላሉ?

ጌርሳ ለእኔ ታላቅ ነበረች፡፡ የገባኝ ነገር እሷን ጨምሮ በደደብ መንጋ መከበቤ ነው፡፡ በበልጣብልጦች ነገ-ቢሶች መወረሬ ነው፡፡ ከእነዚህ አይነቶች ጋር አንድ መሬት ተጋርቶ ከመኖር የተነፈሱትን ከመተንፈስ ጫት እየቃምኩ አረንጓዴ ውሃ ብሸና ይሻለኛል፡፡

አፍ ክሱት በመሆኑ ቸል አልነው፡፡ አፍ ብዙ ነገር ነው፡ ልጅ ሆነን የጠባንበት፣ ጎረምሳ ሆነን የቃምንበት፣ ወደን የሳምንበት ብዙ ሌላ ሌላም፡፡ ከንፈር ላይ ያለው ቆዳ ከሌላው የሰውነቷ ክፍል ከሃያ እጥፍ በበለጠ *አርቴርአቬነስ አናስትሮምሴስ* የተባሉ እርግብግብ የስሜት ሕዋሳት (ነርቮች) ተከማችተው የሚገኙበት ነው፡፡ ይሄም ለነገር ነው፡፡ ሁሉም ልጃገረዶች (እዚህም ያሉት፣ በሕልማችንም ያሉት) ለአቅመ ሔዋን ሲደርሱ ምልክት የሚሰጡን 'ናልኝ' የሚሉት በከንፈሮቻቸው ነው፡፡ አንዳንድ ፈላስፎች In a kind of visual synecdoche, lips sometimes represent the entire woman[39] ይላሉ፡፡ *አንዳንዴ የሚለውን አንተ ያልገባህ ወንድሜ አንቺም ያልገባሽ እህቴ ሁልጊዜ በሉልኝ፡፡*

የአባቷን ግልምጫ የእናቷን ማስጠንቀቂያ ችላ ብላ የተጠጋችኝ ዘሪሁን ስላስጠላት፣ ገሊታ ስለተሰደደባት፣ ባኪ ስለታመመባት ነው? ይሄ አቡ ተፈጥሮውን የሚቀበል ነው፡፡ እጣዬን ሳላመናታ እወስዳለሁ፡፡ ዝናብ ቢመታኝ አላማርርም፡፡ ደንቆሮ ሆኜ ብፈጠር አላማርርም፡፡ ዕውር ብሆን አላማርርም፡፡ ዝናብን አልረግምም፡፡ ደንቆሮነትን አልፈጥርም፡፡ ተፈጥሮዬ ባመጣውና እኔ ባመጣሁት ጉድ መሃል መለየት እችላለሁ፡፡ ጥፍሬ ሲረዝም መቁረጥ ሲገባኝ እሱ *የመጣውን እሱ እስኪመልሰው ብዬ ጆፌ መስዬ* አልሄድም፡፡ ጌርሳ

---

ብረታብረቱን አስገብታ የሆነች ፋብሪካ የመሰለችው በራሷ ፈቃድ ነው:: ተፈጥሮ ያለሳንክ ስራቻት እሷ ሳንክ ሰራች:: አፏ ውስጥ እንከን ገነባች:: ከዛን ቀን በኋላ ጌርሳሞት ጌርሳ አይደለችም:: *ከከንፈሮችሽ ማር ይንጠባጠባል፣ ከምላስሽ በታች ማርና ወተት አለ* አትባልም:: *ምላስሽ ዙርያ ሽቦና ቦንዳ አለ፣ ከከንፈሮችሽ ግድግዳ ቀይ ዝገት ይረግፋል* ብዬ እላታለሁ:: ወይም እንደ ችኑዋ አቼቤ she pointed her lips like a gun in my face[40] አይነት ልክ ልኳን:: ጽላቴ መበላሸቱ አሳዘነኝ:: ለመዛጉም አልጨነቅም:: ለእህቴ ይሄው አልጨነቅም:: ከጌርሳ ወዲያ የቀረው ሁሉ እኩል ነው:: ከፍ ዝቅ የለበትም:: ሰርታታዋ ታቦት ማደሪያ ሆይ ጤና እደሪ!

Φ

ዱርዬ ብሆንም ጥራት አለኝ:: እና ያው ጫቴን እየቃምኩ የማያልቅ ፈረንጅ የቸከቸከውን የትም የማያደርሰኝን መጽሐፍ አነባለሁ:: አባቴ በልጅነቴ ከዘራብኝ ሱስ መላቀቅ ከብዶኛል:: ከመፅሐፍ ስሸሽ ሳላውቀው ራሴን መጽሐፍ ይገፍ አገኘዋለሁ:: ተማርሬ ስወረውረው እንደ *ቡመራንግ*[41] ዞሮ ይመጣል:: ይሄን እርግማን የሚካፈለኝ ብዙ ሰው የለም:: *መፅሐፍን ካሳተመው ያቃጠለው ፀደቀ*:: መጽሐፍት ቤቶችን ላቃጥል ችቦ ይገፍ ብወጣ የትም የሉም:: ችቦውን ይዞ መዞር ደክሞኝ ጠላ ልጠጣ ደስ ባር ገባሁ:: ግጥም በጃዝ እንኳን ልሰማ ራስ ሆቴል ስሄድ ለመጣላት አቅጄ በወንዶ ከፍታ ነው:: ገጣሚዎቹ አለምን ሊለውጡ ይሁን ወይ በራሴው ነገር ሊያሳዝኑኝ ወይ ቆራጥ ሊያደርጉኝ ይለፋሉ:: የረገጥኩትን እዚህ የማየውንም መሬት ሳይጠፉ ጠፉ ይሉኛል:: የቤት አመታታቸውን ዜማ፣ የአርኬአቸውን ወዝ አድንቄ ወደምመለስበት እመለሳለሁ:: አለም በደራሲና በእሱ ግጥም አትገነባም፣ የምትገነባው በባርያ፣ በሚያምር ከንፈርና በጥፊ ነው:: በልቤ እንዲህ እላለሁ: ወይ ሳሙን ወይ ጠፍጥፉን ወይ ደህና የሚከፈለው ባርያ አድርጉን:: እናንተ ግን ከነግጥማችሁ ዳይ ወደ ጠጅ ቤት::

መኝታ ቤቴ ውስጥ ግድግዳ ተደግፎ የቆመ ሁለት ሜትር ስፋት ሁለት ሜትር ከፍታ ያለው የእንጨት መደርደሪያ አለ::

---

በመጽሐፍ ሙሉ ነበር፡ ከስነፅሑፍ እስከ ፍልስፍና። በጋዜጣ፣ በመጽሔቶች ሙሉ ነበር፡ ከአዲስዘመን እስከ ጦቢያ። ከአደፍርስ እስከ ለማ በገበያ። ብዙ አይነት ቃልና ሃሳብ በሰፈረባቸው ወረቀቶች ሙሉ ነበር። አብሮኝ ለሚፈርሽ ሳበድረውና ያበደርኩትንም ስረሳ፣ ርዕዮተአለማቸው ምን እንደሆነ የማይታወቅ፣ ልባሳቸው የተገነጠለ ጥቂት መፅሐፎች፣ መጽሔቶችና የገጻቸው ስልፍ የተረበሸ ጋዜጦች ቀርተውኛል። እነዚህ የቀሩኝን ነፍስ በመስኮት ገብቶ ወደ ወጨጫ ቢወስዳቸው ወይ ሙና ለማድ ቤት ብትገለገልባቸው ግድ የለኝም። የአንዳንዶቹ አላማ ጠፍቶኛል። ለምን እንደገዛሁዋቸውም ረስቼአለሁ። የአንዳንዶቹ መፅሐፍት ሰረሰር ላይ ያለው አርዕስት ከምቀመጥበት ቦታ ይነበባል። የነዚህን አርዕስቶች ትርጉም የሚያውቁት አብረውኝ የሚከድሙ ብቻ ናቸው። በጨዋታ መሃል ለብዙዎቹ አብራራቼላቸዋለሁ። ከግራ ስጀምር፡

1 **ሲቂ፡** ይሄን የፃፈው የአዋሳ ልጅ ነው። የተወለደው ግን ሻሸመኔ ነው። ድርሰቱ መአት ገጽ አለው። ከስንት አመታት በፊት ማትሪክ እንደወሰድኩ ከአሮጌ ገዛሁት። ተማሪ እያለሁ ለመደበሪያ አነበው ነበር።

2 **ጨገጌ፡** ደማቅ ቀይ ሽፋን ያለው መጽሐፍ ነው። የገዛሁት ሽፋኑና አርስቱ ስቦኝ ነው። ይዘቱም ጥሩ ነበር። ሌላ መፃሕፍት እንዳነብ ይገፋፋኛል። ያስቀረሁት ለዚህ የዘገየ ጣፋጭ ውለታው እንጂ አሁን አላነበውም። ደም ስሬን በጊዶሌ አሳብጬ አየዋለሁ።

3 **ወንዶ፡** ወንዶ ቢታተምም ጥሩ መፅሐፍ ነው። ወንዶ ከተማ ማተሚያ ቤት አለ እንዴ? ወንዶ ግን የት ነው?

4 **በለጬ፡** ዝዋይ ማተሚያ ቤት እዚህ ቦሌ ቡልቡላ የታተመ ነው። ደራሲው አይታወቅም። ምክንያቱም ስገዛው የመጀመሪያው ሁለቱ ገፆች ጠፍተው ነበር። ቢሆንም እሱን ባነበብኩ ቁጥር ላብ በላብ እሆናለሁ። የስጋ ፍላጎት የሚቀሰቅስ ታሪክ አለው።

5 **ጊዶሌ፡** ይሄን ያነበበ ወዮለት። ወደ ሌላ አለም በስሜት ባጃጅ ይሳፈራል። በመብላትና በመጠጣት መሃል ልዩነት እስኪጠፋ

ድረስ የድርሰቱ ፍሰት ነፍስን ይቀለብሳል። በሸንት ቤትና በሚስታችን መሃል ያለውን ልዩነት ያሳጣናል። እሱን ስታነብ አጎትህ የጠሩህ መስሎህ 'አቤት!' ብትል አብደህ አይደለም። የእያንዳንዱ አረፍተነገር ሉአላዊ እውትነቱ ለአንተ የተፃፈ ያስመስለዋል። ወይም ለሁልህም።

6 ኮይራ: የደራሲው ስም የመጽሐፉ አርስት ስም ነው። የሚገርም ነው። ሁለት ገጽ ብቻ ማንበብ ያረካል። ከባድ ከባድ ግጥሞች ናቸው። ይሄን ሳነብ አሥራት ውል ትለኛለች። ብዙ ጊዜ የምጠራት ይሄን ካነበብኩ ነው። አንብቤ የምሆነው ይጠፋኛል። እስኪ ያነበብከውን በቃልህ በልልኝ ትላለች። ማስታወስ ግን ያዳግተኛል። የደራሲው ሙሉ ስም ኮይራ ሙሳ ይባላል።

7 አሳኖ: ይሄን የጻፈው ሰው ሰካራም ይመስለኛል። በድርሰቱ መቅድም ውስጥ ይሄን ማንበብ ከአስጠላህ ወጥተህ ጠላ ጠጣ ይላል። ምን አገባው?

8 ኡመር ኩሌ: የአንድ ልብስ ሰፊ ታሪክ ያለባት የ120 ገጽ ድርሰት ናት። አንዴ ተቀምጬ አነባታለሁ። አንብቤ ስጨርስ ምግብ እጠላለሁ። ልምን እንደሆነ እንጃ። ገላዬን መታጠብ ቀርቶ ለመታጠብ ማሰብ ያስከፋኛል። የድርሰቱ መሪ ገፀባህርይ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚበላው እንጀራ ሳይሆን የሽንብራ ቆሎ፣ የስንዴ ንፍሮ፣ ፈንድሻና እንዱሽዱሽ ነው። የጠራ የዶሮ ዘር አለበት ፍጣሪ ነው።

9 አመርኮት: ይሄን ሲነጋ ካነበብኩ ቀኑን ሙሉ አይደክመኝም። ገላዬ ይነቃቃል፣ አሥራት ትደሰታለች። ስትደሰት 'ወይ ዛሬ' ትላለች። ዐይኖቿ ይቦዛሉ። እንደ ድንጋይ የሚያደርጋት ሴትዮ በእግሮቿ ቆልፋ ይዛ አቡ አቡዬ አቡሽ አቡቡ አቡቲ አቤ አበባዬ አበባ በሰባት አዲስ ስም ትጠራኛለች። ሁሉ አልፎ ስነግራት እንዲህ እንደጠራችኝ ትዝ አይላትም። ድንጋይነቷ እንዳላማረረኝ እንዲህ ስትለኝ ምንም አይመስለኝም። 'አመርኮት' ብዬ ደረቴ ላይ የፃፍኩበት ነጭ ቲሸርት አለኝ። *ምንድነው አመርኮት?* ሲሉኝ የካሊል *ጂብራን አጎት ነው* እላቸዋለሁ። ለሃይማኖት ማቃጠር የሚወደው ሃይማኖት የማይወደው የሃይማኖት ባለሥልጣናት የሚሸውዱት የአገሬ ሰው ደስ ሲል ይላል። የአገሬ አንባቢዎች ውሸማ ካሊል ጂብራን

---

ነው:: ቀጫጭን ገፆች ውስጥ በድብቅ የማይረባ ወሲብ ይሰራቸዋል:: የማያልቅ ተስፋ አርግዘው ይወጣሉ:: የአዲስአባ ጎዳናዎች ከፍ ከፍ ይላሉ: የቸርችል ጎዳና እርዝመት ሁለት ሜትር ብቻ ይሆናል:: ስጋደምበት ይሞላና ትራፊክ ይቆማል:: በሰማይ የምትኖር አባቴ ሆይ 'ጎረቤትህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ' ብለህ ከምትለኝ ይልቅ እርፌህ በርጫውን ግፋ::

**10 አቡ ምስማር:** ወፍራም ቅፅ ያለውና በታወቀ ደራሲ የተፃፈ ነው:: ***ገጸም ማርታ*** ሳይሆን አይቀርም:: 300 ብራሮቶቼን ላጥ አድርጌ ነው የገዛሁት:: ተራ ግን ልብ የሚስብ የፍቅር ታሪክ አለበት:: እሱን ማንበብ ወተት መጠጣት ነው:: እርጎ መዋጥ ነው:: አንድ ገጽ አንብቤ ዐይኖቼን ጨፍኜ አንድ ሰአት ተረጋግቼ ማሰብ እችላለሁ:: ምን አስባለሁ? ማን ግድ አለው?

**11 ቀጠላ:** ሁለት ክፍሎች አሉት:: የመጀመሪያው ክፍል ክፉ ሰውዬ፣ የሁለተኛው ክፍል ክፉ ሴትዮ የሚተርኩት ነው:: አንብቤ ስጨርስ ለማን ማዳላት እንዳለብኝ መምረጥ ከብዶኝ ልቤ ለሁለት ይከፈላል:: ይሄ እያስጨነቀ እንቅልፍ ይነሳኛል:: ስኪዞፈሬንያ ያስይዛል::

**12 ከረቡላ:** ይሄን ሳነብ ስኒከር ጫማ አድርገህ በሸገር ሸልል ሸልል ይለኛል:: ብጠጣም ባልጠጣም ከሚጠጡ ሰዎች ጋር በየቡና ቤቱ እዞራለሁ:: አሥራት እላዬ ላይ እንደ ጤፍ ሙቅ ተጣብቃ ታመሻለች:: ስትወድቅልኝ እንደ እንስሳ ነው:: አለቃዬ አትመስልም:: አ አሥራትዬ::

**13 ገለምሶ:** አሳዛኝ ታሪክ ያለበት መጽሐፍ ነው:: የፍቅር እስከ መቃብር መጨረሻ፣ የኦቴሎ መጨረሻ ምናምን:: ባነበብኩት ቁጥር አለቅሳለሁ:: ዛሬ ዛሬ ማን ነው ቂል የሚያለቅስ?

**14 ሂርና:** ቀሽም ደራሲ ስለ ስለላ የጻፈው ነው:: ማሞ ውድነህ የራሳቸውን የስለላ መፅሃፍ ቢፅፉ እንደማለት:: ወይም በአማርኛ የፃፉትን የራሳቸውን መጽሐፍ በአማርኛ ቢተረጉሙት እንደ ማለት:: የምር ግን ደራሲው ማን እንደሆነ ትዝ አይለኝም::

---

**15 አስበዋ፡** ጥሩ መፅሐፍ ነው ግን ሌላ ያነበብኩትን መፅሐፍ ደግሜ ያነበብኩ ይመስለኛል። ዴን ሾ።

በሳምንት አምስት የሴት ጓደኞች ያስፈልጉኛል። ማፍቀር መኖር ከተባለ፣ መኖር ማፍቀር ከተባለ ማለት ነው።

ሰው በእግዚአብሄር ቃል ሁሉ እንጂ በበርጫ ብቻ አይኖርም (የ........ወንጌል 4፡4) ሁልጊዜ እቅማለሁ:: ሁልጊዜ ስቅም እነባለሁ:: ታዲያ ጫት ማንበብ አይሆንም? በነገርህ ላይ ጫት ማንበብ ነው የምለው:: ቢያንስ ከዛሬ ወዲህ:: በርጫ እነባለሁ:: ማንበብን ለብቻው አድርጌው አላውቅም:: ሁልጊዜ ለመቃም ሲያቁነጠንጠኝ ሰው አስባለሁ......አሥራትን አሰብኩ:: እና ጠራሁዋት:: እማማና አባባ የሆነ ሪሆርት ቀጭኔና ድኩላ ሊያዩ ወይ የሆነ ስም የለሽ ወንዝ ውስጥ ሊዋኙ ወደ ሪፍት ቫሊ[42] ወርደዋል:: አሥራት የምጠላውን ጎተራ የመሰለ ቦርሳዋን ይዛ ትመጣለች:: እውስጡ ግን ሁልጊዜ ያለው ሜክአፕ ሳይሆን በቅቤ ሞቅ ያለ ድርቆሽ ፍርፍር ነው:: ለምን ባለ ድርቆሽ ትሆናለች? ስለምን *እወድሃለሁ* የምትል ልጅ በረስረስ እንጀራ ትመዝነኛለች? ምንስ አቅብጦ እሱን *'ወደድኩልሽ'* አልኳት—አልዋሽም ፍርፍሯ ማር ማር ይላል:: ሙና የመኝታቤቴን ተሊስ እንድትጠርግልኝ ነገርኳት:: ደሞ *ለምን?* አለች:: *ለምን* ስትል ስለተሊሱ ብቻ አይደለም የምትጠይቀኝ፤ ለምን አንዴ ብቻ አደረከኝ፣ ለምን የጌርሳሞት አባት በሞት እስኪያስፈራራህ ድረስ ከማንም ለምቦጫም ጋር የትም ከምትልከሰከስ እኔ እዚችው በሶ በሶ የምትል ዳቦ አልሰጥህም? የመሳሰሉ ሌሎች አቤቱታዎቿን በድባብ ስርታ ነው:: በዐይኖቿ ብቻ የእነዛን ጉዳዮች ጠረን አንድ ጥያቄ ውስጥ አስራ እንዳስቀመጠቻቸው ትናገራለች:: ይሄ የእሷ ችሎታ ይሁን የእኔ ጥርጣሬ የፈለሰፈው ምናባቴን አውቃለሁ:: አይኖቿ ባይወጠሩም ሲወጠሩ ይሰማኛል:: ለምን ይወጠራሉ? ሴራዋን የማላውቅ ይመስላታል:: ኮላሴ ደባሪው ጌርሳን እንዳልጠጋት ቤቴ ድረስ መጥቶ አስፈራርቶ እንደሄደ አልነገረችኝም:: ዝምታዋ ያለጥንቃቄ ጌርሳን ሊያገኝ ሲንጠለጠል ቢሞትልኝ ብላ ነው:: ብገደል እሷ የምትፈልገው እንትኔ አብሮ መሄዱ አይደለም? ኢትዮጵያውያን መልካቸው ዝንጉርጉር ብቻ ሳይሆኑ ጥልቅ ምቀኞች ናቸው:: ሰበብ ፈልገው እየተመቀኙ ከተመቀኙት ጋር ተያይዘው ቢሞቱ ግድ የላቸውም:: እስላምም ክርስቲያንም አይደለህም አንተ ምቀኛ ነህ:: ሙና ክፍሉን ጠርጋ እንደወጣች ፍራሼን ከአልጋ ላይ

አውርጄ ወለል ላይ ዘረጋሁ:: ብርድልብሱንና አንሶላዬንም አወረድኩ:: ይሄን ብታይ ቤቴ ቢሆንም ሙና ደሟ እንደሚፈላ እርግጠኛ ነኝ::

እሥራት ጉንጉንዋን ፈታ ወደ ሁዋላ ለንጥሳ አስራዋለች:: በጨርቅ ቀረጢት ያመጣችውን የሚበላ ነገር ወለል ላይ አስቀመጠች:: ቀረጢቱን ከፍታ መሃከለኛ መጠን ያለው አገልግል አወጣች:: 'የባሕርዳር አገልግል ነው' አለችኝ:: 'ፋክ ኢት' አልኳት:: 'ምን ሆነሃል? ደሞ አገልግል እንዴት ፋክ ይደረጋል? ታመሃል' አለችኝ:: አንደኛ ለአገልግል ግድ የለኝም:: ሁለተኛ ያመጣችው ያው ድርቆሽ ፍርፍር[22]

---

[22] የግል ልምድን ወደ ማህበራዊ ውይይት ማምጣት የናሙና ህግ ማክበር ብቻ አይደለም:: አብረን እንዳለን ማሳየም ነው:: በዛ በኩል በዛች በቅሎ ደረትዎን ነፍተው ቢያልፉ እልዎታለሁ ያቺ የአህያ ልጅ የጠጣችው ውሃ የወንዜ ነው:: የጋጠችው ከፍየሎቼ መንጋ ተጋፍታ ነው:: ፋንድያዋን እሳት ለኩሼበታለሁ:: ይሄ አሁን የማወራው ወሬ ደሞ ወደዱም ጠሉም ሳሩን፣ እኔን፣ ፍየሌን፣ እስዎን፣ በቅሎዋን፣ አባቷን ፈረስ ያያያዘን ናጥራን ነው:: ሙልጭ አድርገን ካልዋሸን በስተቀር ከዚህ ጉንጉን አናመልጥም:: ግን ሞላጫ በዛ::
አሁን የማወራዎት በጣም የግል ስለሆነ ልምዴ ነው:: ስለ አቶ ግርማ ደንቦባ ደግሜ ለመናገር ፍቼ መሄድ የለብኝም (ምዕራፍ አራትን ይመልከቱ):: በአጭሩ ልበለው? ድርቆሽ አልወድም:: ለምን አልወድም? እንደ አንድ ገጠር ተወልዶ እንደ አደገ ልጅ አይደለም ፀባዬ::
እንደ አንድ ገጠር ተወልዶ እንደ አደገ ልጅ አይደለም ፀባዬ:: ገጠር እንቃለሁ ማለቴም አይደለም:: ለእኔ እኮራበታለሁ ማለቴ አይደለም:: ገጠር እንቃለሁ ማለቴም አይደለም:: ለእኔ ከተሜ ማለት መኪና የሚነዳ፣ የባእድ አገር ዳንስ የሚደንስ፣ የውጭ አገር ልብሶች የሚለብስ ማለት ሳይሆን መንደሮችና ከተሞች፣ ሰዎችና ቁሶች እንደተሳሰሩ፣ መተሳሰራቸውንም ማንም ሳይነግረው ከግል ልምዱ ሊገነዘብ የቻለ ነው:: ይሄ በትምህርትቤት ብቻ የሚያገኙት ብቁታ ሳይሆን በአእምሮ ክፍታ፣ በአስተዳደግና በአኗኗር ጥልቀት የሚመጣም ነው:: ለምን ይሄን አዘበዘበኝ? አገራችን 90 በመቶው ገበሬ ቢሆን የቀረው ባያርስ እንኳን ራሱን በዘመናዊ ትምህርት የጋረደ ገበሬ ለመሆኑ ልዩ ጥናት አይጠይቅም:: ታዲያ ጤፍ የሚያመርት ገበሬ መሃል ተወልጄ ለምን ድርቆሽ ጠላሁ? ጥያቄው ቢያስቅም መልስ የሚለምን ነው::
በከተማ እድገታችን መሰልጠን የሚከሰትባቸው መስመሮች አሉ:: ከብዙ ምልክቶች አንደኛው ድርቆሽ በየሆቴሉ አለመሸጡ ነው:: ማንም የሆቴል ቤት ባለቤት የዚህ አይነት ምግብ አይሸጥም:: ለምን አይሸጥም? ከዚህ ከፖፖላሬ እስከ የአገራችን የከተማ ባህል አወላለድ የተወሳሰበ ነው:: ከዚህ ከፖፖላሬ እስከ ጅማ መንገድ ከላም በረት እስከ ጉለሌ ከቦሌ እስከ ሽሮሜዳ የከተማነት ዕንስ ሃሳብ ይሄን ያህል የጋርዮሽ ትርጉም የለውም:: ካለውም ከተሜነት የፈረንጅ አበላል፣ አጠጣጥ፣ አለባበስና ቋንቋ ከመልመድ ጋር የተያያዘ ነው:: ስልጡን የተባሉ ቤቶች እንጀራ በወጥ የላቸውም፡ ቢኖራቸውም ብዙ ጊዜ የላቸውም:: ከተሞቻችን ቢያንስ 90 ከመቶ ፀረኢትዮጵያ ሆነው ነው ከተሜነታቸውን

የጀመሩት:: እኔም ከተሜነቴን ለማስመስከር መስለኝ ከላይ እንዳልኩት ድርቆሽን ንቄአታለሁ:: አብረውኝ አድገው ሁለተኛ ደረጃ ስንገባ የተለያየን ልጆች ከሰፈራቸው ድርቆሽ አፍቃሪ በባይ ሳይላቀቁ እኔ ለምን? ዘፋኙ የእንጨኒው ወዳጄ ዳንዴው ሞላ እንደጉረኛ እንደሚቆጥረኝ የገባኝ ከርሞ ነው:: አብረን በልተን፣ ተጫውተን፣ ሆያ ሆዬና ፎሌ ብለን እሱ ድርቆሽ ሲወድ እኔ ለምን አልወድም?

ግን እኔ እንደእሱ ዘፋኝና ሃብታም ስላይደለሁ፣ አድማጮቼን 'እናንተን እመስላለሁ' ብዬ መደለል ስለማያስፈልገኝና ደሞም ቡና ኮርፖሬሽን የምሰራ የመንግሥት ተቀጣሪ ደመወዝተኛ ስለሆንኩ ተደማጭነት ስለሌለኝ አባባሌ ሁሌ እንደ ጉራ ከመቆጠር አያልፍም:: ለመሆኑ ጉራ ነው? አንድን ነገር በተፈጥሮ መጥላት አይቻልም? እሱ አብሮህ ያደገው በመደሰት የሚበላውን አንተ ማነህና ነው? ብለው በነገር እንደሚቆነጥጡኝ አውቃለሁ:: ሞላ ጊዜ ተርፎት ሊጠይቀን እቤት ከመጣ እኔን ማብሸቅ ስለሚያስደስተው እናቴን:

'እስኪ እማማ ድርቆሽ ፍርፍር ካለሽ ስሪልኝ' ይላል::

እሷም 'አይ ይኖር ብለህ? እዚህ ቤት ሁሉም ኮርተዋል:: ኑብዬማ የሰለጠነ መስሎት በዐይኑ ማየት አይፈልግም' ትለዋለች

ከዛ ግራና ቀኝ በክርክር ይጠምዱኛል:: ሙግት ሲመጣ መነሻዬ ሁልጊዜ አሳማኝ ቢሆንም ባይሆንም ሃይጂንን ተንተርሶ ነው:: እንጀራው ድርቆሽ እንዲሆን ያለ ምንም መከላከያ (ልባስ) እውጭ ስለሚሰጣ ዝንብ፣ ተባይ፣ እንሽላሊት፣ ጉንዳን እንደሚረማመዱበትና፣ የእባብ ወይም የእይጥ ዐይነምድር ሊገባበትም እንደሚችል አንዳንዴም ጉንፋን የያዘው ሰው ከቤታችን ግቢ እንኳን ባይሆን ከውጭ ሲያነጥስ ልጋጉ በነፋስ ተሳፍሮ የተሰጣው እንጀራ ወይም መድረቅ ከጀመረ ድርቆሹ ላይ ሊያርፍ እንደሚችል ቁና ቁና እየተነፈስኩ እነግራቸዋለሁ:: ይሄም በደንብ እንዲይዝልኝ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ የቀሰምኩትን *ባክቴሪያ* ቲዮሪ አክልበትና በምክንያቶቼ ሰልፍ ላደናግጣቸው እሞክራለሁ:: ሳይንሱንም ለማጠንከር ኪነታዊ ማጋነንና አሽቃቂነት እጨምርበታለሁ:: ታዲያ የሚሰማኝ አለ? የለም::

እማማም ድክመትን በምንደብቅበት የጋራችን በሆነው የዛገ ልማድ ተከናንባ (እንዲህ ግን አልላትም) 'ምን አደረግንህ እቴ ይሄን የሚያሳስብ ሰይጣን እንጂ ምን ሊሆን ነው?' በማለት ልክ ተባዮቹን ወይም ባክቴሪያዎቹን እኔ እንደማዛቸው ወይም ሕልውናቸው በእኔ ሚርት ላይ የተመሰረተ አድርጋ ሃሳቤን ታጣጥለዋለች:: ሞላም 'አይነግሩልኝም አይነግሩልኝም ይሄን ፈረንጅ' ብሎ ያሟሙቃትና ከእሷ ምርቃት ሲያገኝ (አይቀርበትም) 'ተባረክ ልጄ:: ባህልህን የማትረሳ፣ ያሳደጉህን የምትሆን' ስትለው፣ እንዳታየው አድርጎ ድል እንደነሳኝ ሊያሳየኝ ፈገግ ብሎ በግራ ዐይኑ ይጠቅሰኛል:: ከዛ እንደውም ፈተናው ይሰፋና 'ዋት አየህና' እባላለሁ:: 'እባብ አይተሃል ሲፀዳዳ? አይጥ አይተሃል እዚህ? በነፋስ የመጣውን ልጋግና ንፍጥ ወደ እዚህ ግቢ ሲበር አይተሃል?' መልሴ ምን እንደሚሆን

---

ስለሚያውቁ በሀብረት ይስቁብኛል:: በፀሐይ ቢደርቅ እንኳን (sun-dried injera) ድርቆሹ በፈላ ውሃ ስለሚበሰብስ የቅርብ ጀርም ይቅርና በድንጋይ ዘመን የነበረው ቆሻሻ ጎጂነቱ እንደሚጠፋ የራሴኑ ሳይንስ አስታክው ይስብኩኛል:: ይሄም ከተሳታቸው እንጀራው ምጣድ ላይ እንደሚደርቅና በጥንቃቄ እንደተሰራ ይዘበዝባሉ:: ፍላጎቴ ስለሚያስቃቸው ብቻ ሳይሆን ደደብነቴ አማርአቸው ሳቅ ሳቅ እያሉ ፊቴ ይቀመጡና እየተጋገዙ ድርቆሽ ፍርፍራቸውን ይበላሉ:: ቋቅ ስለሚለኝ የሚያደርጉትን ላለማየት ወደ ውጭ እወጣለሁ:: ሲጨርሱ አረጋግጥና እመለሳለሁ:: ቀጥለው ከአቦል እስከ በረካ ሊጥ የሞላ ሆዳቸው ላይ ቡና እየቸለሱ ይስቁብኛል:: እንዲህ ተደብሬ ዝም እላለሁ? አልልም......

አልፎ አልፎ ለምን ድርቆሽ እንዳልወደድኩ ዘና ብዬ እራሴን እጠይቃለሁ:: እሱ ብቻ ሳይሆን ድርቆሽ ራሱ ምንድነው እላለሁ? ሲጀመር ድርቆሽ ትርጉሙ ምንድነው? በከፊል የረቀቀ ወዳጆቼን የሚያሳፍር መልስ ፍለጋም የተሰማራሁ ይመስለኛል:: ጥያቃ ቂም መያዝ አልነበረበትም:: ምን ላድርግ ግን?

(ስለ ድርቆሽ ሳወራ ስለ ጤፍ መሆኑን ይታወቅልኝ::)

የጤፍ ዘር➔ ዱቄት➔ ሊጥ➔ እንጀራ➔ ድርቆሽ➔ ኮቾሮ::::

እነዚህ ዝርዝሮች ደረጃዎች ናቸው:: ልብ እንበል:: ይሄ ግን መስመር ነው:: ሲመስለኝ ይሄ መስመር አዙሪታዊ ለሆነው ሕይወታችን አይመጥንም:: ዞሮ ወደ ነበረበት ወደ ተነሳበት ለመመለስ የሆነ ዘላለማዊ ድግግሞሽ እንዲኖር ለሚመኘው፣ ከእግዜር እንደመጣ ወደ እግዜር ለመመለስ እቅድ ላለው የመንፈሳዊነት ዕውር ሱሰኛ የሚመጥን አቅጣጫ አይደለም:: (የአገራችን ሰዎች ሃይማኖተኛ ናቸው እንጂ የለም) ስለዚህ ይሄ መስመር ፈርሶ ክብ መሆን አለበት:: ክብ ሲሆን የእኛን የድብቁን ሕሊና ምስል ይይዛል::

ይሄን መስመርና ንጥሮቹን በሰው እድሜ ተርጉሜ ልውሰዳቸው:: (ዱቄት= ሕፃን፣ ሊጥ= ሞሳ፣ እንጀራ= ወጣት፣ ድርቆሽ= ጎልማሳ፣ ኮቸሮ= እርጅና) ወደ ነገሬ ልመጣ ነው:: ለመሆኑ ስንቱ ነው እርጅና ጋ ሲደርስ በፈገግታ ወደ ሞት መሻገር የሚፈልገው? ማንም መሞት አይፈልግም:: ዘላለማዊነትን ከመመኘታችን የተነሳ ዘላለማዊነት ባይኖር እንኳን ሃይማኖተኛ እንመስላለንና ወይም ለተገኘው ሃይማኖት አቃጣሪ ሆነናልና ዘላለማዊ ሕይወትን ቀርቶ ትንሽ ዕድሜ ለመጨመር ልጆቻችንን ለአውሬ ምሳ አድርገን ብንሰጥ ግድ የለንም:: በእኛ አገር ብቻ ነው እግዜር ሃይለኛና ቂል የሆነው:: እንዴት ነው ከሞቱ በኋላ መኖር? ወንድሞቼና እህቶቼ ሆይ ጫጫታ፣ ፉክክር፣ ተረብና ጠላ የሌለበት ሌላ አለም መኖር አልፈልግም:: ለመሆኑ ስሞት እንደ ጨርቆሱ ወዳጄ እንደ ልጅ ገዳም አባተ አይነት እርቦሽ ሙታን አለም ማግኘት እችላለሁ? እኔ ጥጃ ወይም ንብ አይደለሁም ወተትና ማር በሚያፈስ ዘላለማዊ ህይወት የምደለለው:: ምን ለማለት ነው? ድርቆሽና ኮቸሮ ሰሪዎች በተምሳሌት ለዘላለም ለመኖር የሚጣጥሩ ሰው

---

ነው:: ቀና ብላ በትዝብት አየችኝ:: አሥራት በትዝብት ስታይ ዕድሜዋ በአስር ዝቅ ይላል:: ፀጉሯ በቅባት እንደ ላስቲክ ሲፈልቅ አየዋለሁ:: ተሰርቶ የማያውቅ መርቱ ነበር:: እውስጡ ሰርዶ አይጠፋም፡ ሰርዶውን ተከትላ የገባች ጥጃ አትጠፋም:: ጥጃዋን ተከትሎ የገባ ጅብ አይጠፋም፣ ጅቡን ተከትሎ የገባ እረኛ አይጠፋም፣ እረኛውን ተከትሎ

---

መሆናቸውን የሳቱ ገብጋቦች ናቸው:: የሚበሉትን ነገር ሁደት ውስጥ በመክተት የሞት ፍርሃታቸውን በተምሳሌት ለማሸነፍ ይጥራሉ::

ድርቆሽ ፍርፍር ሲሰራ (ድርቆሽ ፍርፍር ሲሆን) በከፊል ወደ እንጀራ በከፊል ወደ ሊጥ የተጠጋ ከእርጅና ወደ ኋላ ወደ ጎልማሳነት የመመለስ የተስፋ ቆራጮች ምሳሌ ነው:: (እንጀራ ፍርፍር ወጥ ቅብ ነው:: እሱም ተነጥሎ የሚፈሰውን ወጥ በጉያው ከመሰብሰብ ሌላ ነገር አይሆንም::) ኮቸሮ እንጀራን መልሶ ወደ ጤፍ ማምጣትና ውሀ በማማከል ወደ ሊጥ ወይም ወደ ልጅነት የማምጣት ነው:: አጋጣሚ ሆኖ አይመስለኝም ገና ሳታረጅ እማማ 'አሁንስ አረጀሁ' እያለች ድርቆሽ ወዳጅ የሆነችው? ወዳጂ ሞላ በጣም ጨዋ፣ *ያለ ዕድሜው የበሰለ* የሚባለው ለምን ድርቆሽ ወደደ? ምናልባት ተደብቀው ጣት የጠቡበት ልጅነታቸውን እየተመኙ ይሆን? አብሮ አደጌ ሞላ የዞረበት ስለሆነ ብዙ ጊዜ ከወጣት ሴቶች ጋር ጊዜውን ያሳልፋል:: *ድርቆሽ ይወዳል* ማለት ምሳሌው ልጅነቱን እየፈለገ ነው:: ባለፈው አመት መስከረም ላይ ያወጣው ካሴቱ መሪ ዘፈን 'ሆያ ሆዬ' ነው:: እማማም በተራዋ 'አበባዬ ሆይ' የሚጫወቱ ልጃገረዶች ስታይ ደስታዋ ወደር የለውም:: ቆማ፣ ደረቷን በእጆቿ ደግፋ ልክ እንደኮንሰርት ታዳምጣቸዋለች:: ሳትዳብሳቸውና ሳትስማቸው የሄዱ ልጃገረዶች ወዮላቸው:

--አንቺ ምናባሽ ነይ ልሳምሽ!

--እንዴ የተስፋዬ ለማ ልጅ ነሽ አይደል? አምሮብሽ የለ! ነይ በይ ሳልጨመጭምሽ አትሂጂያትም

--አንቺ ቀልቃላ ሁሌ መንቀልቀል፣ ጉንጉንሽን ላስተካክልሽ

እማማን ያኔ ያየት ግሬድ 4 ሲ ያለች ትመስላለች::

እኔም እላለሁ ድርቆሽ የጠፋ ልጅነታቸውን ፈልገው ሊይዙ እዳኝ ውሻ ፊትፊታቸው እየነዱ የሚወጡ ወዳጆቻችን ናቸው እላለሁ:: እድምቄም እላለሁ: ***ድርቆሽና ኮቸሮ ይውደሙ!!*** የማላመልጠውን እርጅና እንጀራ በወጤን እየበላሁ ለሌላ አዙሪት በምኞት ለቀለመ ሕይወት ራሴን ሳላጭ እጓዛለሁ:: ማንንም አልፈራም:: ሞት ሆይ ነይ:: የዘጎነው ዘፋኞችንም ኮረዳዎቹን 'ቆንጆዬ' እያለ ከሞት ሊያመልጥ ይለፋል:: አብሮአቸው ፓስታ ይበላና ቤቴ ሲመጣ ድርቆሹን ይቅማል:: አሁንም እንደገና ድርቆሽ ይውደም:: ላባብል አልሚገትምና ትርጉሙን ላስቀምጥ:

***ድርቆሽ:*** (1)የተወቀጠ ኮቾሮ፣ (2)ደረቅ ሳር:: ተግባባን? ጋሼና እትዬ ሆይ!

(ንቢዩ ጎበና (ናቢ) *ከአራት ሺህ አመታት የምግብ ባህል: ሲጎዶና እንቅፋቴ::* 115 ገፆች አአ ብርሃን ማተሚያ ቤት 1963 እም)

---

የገባ ገበሬ አይጠፋም፣ ገበሬውን ተከትሎ የገባ ግብር ሰብሳቢ አይጠፋም:: እዛ ውስጥ ቅኝ የሆነ አገር ነበር:: ኩብትም:: ቦርሳዋን አስቀምጣ ወዲያ ወዲህ እያለች ጨዋታዋን ቀጠለች:: ወሬዋ ሁሉ የሚመች ሃሜት ነው:: የማነበው የሊሊያን ሮቢንሰን *ኢን ዘ ካኖንስ ማውዝ* (In the canon's mouth) *የቀኖናው አፍ የተባለው መጽሐፍና* የእሷ የወዳጇ የቤትና የቢሮ ወግ አይቀራረቡም:: ለምን እጠራታለሁ? እንደ እርጎ የቀዘቀዙ ሲነኩዋቸውም እንደዛ የሚያደርጋቸው የሚያማምሩ ትናንሽ ጡቶች ያላት ዘሪሁን ማለት ናት:: ከመመርቀኔ በፊት እነሱን እንደ ቡና እንድጠጣ ወደ አፌ ታስጠጋለች:: እንደ ስድስት ወር ልጅ ከእሱ ስታገል አናቴን ይዛ 'አትበሳጭ የእኔ ጌታ' ትለኛለች:: *ዋት ዘ ፋክ* እያልኩ እመዘምዛታለሁ:: *እሰይ* ብላ አፌን ከጡቷ አላቃ ከንፈሮቼን ስማ ትሰየማለች:: ውሸቱንም ምኑንም እንደ እውነት ታወራለች:: አልታዘባትም:: እማማ ድሮ ለስራ ጉዳይ ደቡብ የሄደች ጊዜ *ያመጣችልኝ* የደሳኔ ሴቶች ከንፈራቸውን ሰንጥቀው የሚሰኩት ሚጢጢ ምጣድ ላይ ሲጋራዬን እየተረኮስኩ:: እሱ ነው መተርኮሻያዬ:: ፋክር ሆይ ነፍጠኛነት አይደለም:: አስባለሁ ራቁቴን *ሃመሮች መሃል ቆሜ:: የሚያማምሩ ነገሮች:: የሚቀፉም ነገሮች::* *አሥራትን ምን ምን እሸታለሁ?* ብላት *አቧራ አቧራ* እንደምትለኝ ይገባኛል:: ስለ ጌርሳሞት አባት ስለኮላሴ *መጥፋት* አወራችኝ:: በእግር፣ በፈረስ፣ በበቅሎ፣ በታንኳ፣ በአይሮፕላን፣ በመኪና፣ በጋሪ፣ በሄሊኮፕተር፣ በተባበሩት *መንግስታት* እየተፈለገ ነው ትለኛለች:: ልላት እፈልጋለሁ: *ገደል ይግባ:: ለምን?* ብትለኝስ? የተናገረችውን በዝምታ *አዳምጬ* እንደ አዘንኩ ሁሉ ከንፈሮቼን እመጣለሁ:: ወይም ሌላ ወግ *እንድታመጣና* ኮላሴ ወሬ ላይ አዲሱ ወጓ ተደርቶ እንዲያጠፋልኝ እጥራለሁ::

ከአሥራት ጋር እንደ ማንኛውም ቆራጥ ዜጋ ቅጠል እየበጠስን በከረቡላና በአቡምስማር ጥይት ጊዜን *መረሸናችንን* እንቀጥላለን:: *መቃምዋን ትታ* ከማንባሬ እስከ ጭኔ ትዳብሰኛለች:: ለጫት ትላለች እንጂ የምትመጣው እኔን ለመዳበስ ነው:: እንደ ድመት እላዬ ላይ ተዘልሳ ማናወዝ የሚቃጡ ዐይኖቿን አየሁዋቸው:: እነዛ ውስጥ ያለው

ምርቃና ብቻ አይደለም የሚቀበለው ያጣ ፍቅርም ነው። በሁካታ ፍቅር ጥሩ ነው ብለን በዝምተኛ አቃቂር እንገለዋለን። በጎዳና ላይ የሚሄደው ሁሉ በሆነ ስታይል ፍቅሩ የተገደለበት የፍቅር ገዳይ ነው። ተራሻኖች ነን። የጎዳና ላይ ቱቦዎች በዛ እሬሳ ሙሉ ናቸው። የወደቀውን የዕዱን ቅጠል ብታነሳ ከዛ ስር ሳይገነዝ በችኮላ ያለፈ ፍቅር ነው። ቆዳው ቀዝቃዛ ነው። ጎኑ የወደቀው መገንገሮው የሰበብ ጨርቅ ነው። እኔ የአንተ ሰበብ ነኝ፣ አንተ የእኔ ሰበብ ነህ። ከአሥራት ጥበበኛ አፍ እዛ እንደ ተንጋለለች ይሄ ወጣ፡ *አቡ እወድሃለሁ።* ፊቷን ወደ ተራቆተው አልጋዬ መለሰች። ከአገጭዋ ስር ቅባት ያልደረሰበት አመዳም ቦታ አለ። እንዲህ ያለ ነገር የሰማሁት ዛሬ ነው። ድገሚልኝ ይባላል? እንደማረከኝ ሁሉ አፏን በመገረም ዳበስኩት ልብ ሳልለውም ከገጽዋ አፈላህብ ጥቂት ወዝ ወስጄ ለአገጭዋ አካፈልኩት። የተናገረችውን ያልሰማሁዋት መሆንን ፈለኩ። ያላየም። በቅባትዋ እንደ ዳበስኳት አልነገርኳትም። አገሩ የሰርጀሪ ነው። ራሱን መሆን የከበደው ተራነቱን የሚያንቆለጳጵስ ከርፋፋ ነው። ግድግዳ ተደግፌ ክሎሮፊሊን እያነበብኩ ስታወራ እሰማታለሁ። ስታደክመኝ እተቀመጥኩበት ዚፔን ከፈትኩ። ጭንቅላቷን ወደ ጉያዬ ሳብኩት። *ቆይ ጫቱን ላውጣው* አለች። ጎጢያት ፋታ አይሰጥም። በአፏ ልት ደስታ ትሰጠኛለች። አሥራት የማይካድ አንደበተ ርትዕ ናት። ቀና ብላ አየችኝ። እነዚህን ዐይኖች ይሄን ቁልጭ ያለ አስተያየት ከዚያ በፊት አላውቀውም። ልቀበለው ከሚከብደኝ ቦታ አሥራትን እንደምቀርባት ጠረጠርኩ። የሆኑ ትናንሽ ቦታዎች አሉ መሰለኝ በውስጣችን እንደ ነብር አድብተው ቀን የሚጠብቁ። ነጭ የደም ሴል እንደ ፈረስ እየጋለቡ ወይ ሐሞቴ ጀርባ ደቃቃ ልፋጭ ለብሰው። ከቆዳዬ ስር ጨለማ ነውና ስንቱን ደብቄ ይሆን? ሌላ ስለማያይብኝ ያላየኋቸው። አሥራት ያለችውን እያሰላሰልኩ ታጥቦ የፀዳ ፀጉሯን እየዳበስኩ እቀጣጠላለሁ። ስአታት ያለፉ መሰለ። ለደቂቃ ክንፎች አብቅዬ ሕንድ ውቅያኖስ ደርዝ ሞቃዲሾ አሸዋ ላይ የአሜሪካ ኮማንዶ ጎረምሳ ቅጠልያ ጃኬት ለብሶ ማካን ቢልኪስ  የተባለች የሶማሌ ቆዳ ሲስር አይቼ ተመለስኩ። አረንጓዴ ነባሪዎች ወርቅማ አሸዋ ላይ በውተት አረፋ ሲታጠቡ አየሁ።

---

|------------

አሥራት ከዚህ ሌላ ምንም ባትናገር ደስ ይለኛል። ወገቧ በመታጠፉ ሲያማት እላዬ ላይ ሆና እንደ ሞላ ፊቷን አንገቴ ውስጥ ቀበረች። አናቷን ወደ አንገቴ ስቤ ይሀቺ ጠግባ ያጠገበችኝን እህቴን አጥብቄ አቀፍኳት። አፏ አጠገብ ያለውን ጆሮዬን እየሳመች *ለምን ፊልም አናይም?* አለችኝ። እኔን ለቃ *ያመጣችውን* ሲዲ ማጫወቻው ለማስገባት ወደ ሞኒተሩ እየዳኸች ሄደች። ካናቴራዋ ራቁት ቂጥዋ ላይ ተጣብቆአል። ያየሁትን ነገርኳት። እየሳቀች ተመልሳ መጥታ ጭኖቼ ላይ ራሷን አስቀመጠች። ፊልሙ ቢጀምርም ጉዳይዋ ከእኔ ብቻ ነውና ተንጋላ ፊቴን ትዳብሳለች። ያለስሜት እነካካታለሁ። ራቁት ሆድዋን፣ በቅሬታ ሥልጣኑን የምጋፋውን አፍረቷንና አፍረቷ የለበሰውን ሉጫ። ልብ ሳልለው ግራ ጡቷን እየያዝኩ እለቃለሁ። ፍንጬን ይቆነጥጣል። በፍቅር የተሰነጣጠቀ ሌምቦዋንም እዳብሳለሁ። ከንፈሮቿ ሁልጊዜ ይሰነጣጠቃሉ። ቅባት ይቀባሉ፣ ግን ይነጡና ይሰነጣጠቃሉ። የምትቀባቸው እንዲነጡና እንዲሰነጣጠቁ ይመስላል። በፈዘዙ ዐይኖቼ የቲቪ ሞኒተር አያለሁ። ሲኒማው ጀመረ......ከፊል ልቤ በመሞቅ ላይ ያለ ገላዋ ላይ ነው። የሲኒማው አርዕስት ***ቅብብሎሽ*** ይላል። የተፃፈው በትላልቅ ኒያላ ቀጥ ቀይ ፊደሎች ነው። አርዕስቱን ያጀበው የሴማ ድምፅ ሙዚቃ *ጃኪ ቻን* የተባለ የሆንግ ኮንግ ተዋናይ *ባትል ክሪክ ብራውል* (battle creek brawl) የተባለ ሲኒማ የሰራበት የላሎ ሺፍሪን ድርሰት ነው። ይሄን የጃኪቻን ሲኒማ በዚህ ፉጨት ሰበብ እወደው ነበር። ስሰማው ደነገጥኩ። እንደ ደነገጥኩ ለአሥራት አልነገርኳትም። አሥራት ፊልሙን ማየት ትታ እንደ ልጅ ፊቷን ጭኖቼ መሃል አስቀምጣ እንደምትተኛ ሁሉ ተመቻቸች። ከወገቧ በታች ያለው ራቁቷን በችልታና በትብብር ጋቢ አለበስነው። ፊልሙን ለመመልከት በጣም አተኮርኩ። ሲኒማውን ከክንብንቧ ውስጥ ሆና ተረበችው። ሳታይ ትተቻለች፡ *ስለፊልም ሳያውቁ ፊልም ይሰራሉ። አፍረተ ቢስ ሁሉ ሂሂ። መርሃባ።* ነገረኛ የሚያስመስሏት ስስ ከንፈሮቿ የሚያስቡ ይመስላሉ። ለብሰው የመጡትን የከንፈር ቀለም በገላዬ ላይ በየቦታው አትመው ራቁታቸውን ቀርተዋል። ፊልሙ እንደቀላል ነገር ጀምሮ ለአንድ ሰአት ከሩብ አስሮ እንደያዘኝ ልብ ያልኩት ሲያልቅ ነው።

---

ታሪኩ ስለ አንዲት የቀርከሃ ዋሽንት ነው:: ሲጀመር ፓዊ የተባለ የገጠር ከተማ ውስጥ መኩሪያ የተባለ አንድ ገበሬ ዋሽንት ሰርቶ ሕይወት ለተባለች የዘመዱ ልጅ ሊሰጣት ከከተማው ምሥራቅ ጠርዝ ወደ ምዕራብ ጠርዝ ሲሄድ ገበያ መሃል ይጠፋበታል (ልክ ከጠዋቱ አንድ ሰአት ተኩል ላይ/ ብስጭቱ አይጣል ነው)......ዋሽንቷን ስሟ ያልታወቀ አንዲት ልጃገረድ ከመሬት ወድቃ ታገኛትና ይዛት እቃ ልትሸምት ሱቅ ገባች:: እሷም ሱቁ ባንኮኒ ላይ ዋሽንቷን ትረሳትና ትሄዳለች (ከመሃል መንገድ ትዝ ሲላት ለእኔ ባይለው ነው! ብላ ወደ ሱቁ ሳትመለስ ትቀራለች)......ባለሱቁ ዋሽንቷን ያያትና ልጅቷ ተመልሳ መጥታ ትወስደው ይሆናል ብሎ ዋሽንቷን ደበቅ አድርጎ ያስቀምጣታል......በሚቀጥለው ቀን ማታ ለገበያ ፓዌ የመጣ ቤቱ ያደረ አሰፋ የተባለ ዘመዱ በጨዋታ መሃል ስለዋሽንቷ ወሬ ይሰማና ለልጄ ልውሰድላት ሙዚቃ ትወዳለች ብሎ እንዲሰጠው ይጠይቀዋል:: ትንሽ አንገራግሮ እሺ ይለዋል (የትናንትናዋ ልጅ ድንገት ከመጣች ምን ውሸት ለእሷ መንገር እንዳለበት እያሰላሰለ ነበር):: በጠዋት አሰፋ ወደ ባሕርዳር ዋሽንቷን ለመውሰድ ቀረጢቱ ውስጥ ይከታታል:: አሰፋን የጫነው አውቶቡስ በከተማው ምስራቅ ሲያልፍ ዋሽንቷን የሰራው አቶ መኩሪያ ቤቱ ደጃፍ ጎንበስ ብሎ ሚስቱ ወይም የሆነች ሴትዮ ውሃ እያፈሰሰችለት ፊቱን ሲታጠብ ይታያል:: የውሃው ጢስ እንደ ጉም ከአናቱ ላይ ይነሳል:: አውቶቡሱ ውስጥ ካለው አሰፋ ጋር ይተያያሉ:: መኩሪያ ከሚታጠብበት ቀና ብሎ ይሄ አውቶቡስ ዛሬ ምነው ዘገየ? ይላል:: አሰፋ ባሕርዳር ደርሶ እቃ ከአውቶቡስ ላይ ሲያወርድ መቀመጫው ላይ ቀረጢቱን ከነዋሽንቷ ይረሳታል:: እቃውን ሁሉ ይዞ ቤቱ ደርሶ ገና አረፍ እንደ አለ ዋሽንቷ ትዝ ትለዋለች:: (የሆነውን ለሚስቱም ለልጁም ሳይነግራቸው ድምፁን ዝቅ አድርጎ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ እንግዲህ ብሎ ለራሱ ይናገራል)......አውቶቡሱ ውስጥ አሰፋ የተቀመጠበት ወንበር የደረሰው አንድ ተሳፋሪ ዋሽንቷን የጠፋ እቃ ነች ብሎ ስለአመነ ለሾፌሩ ይሰጠዋል......የአውቶቡሱ ሾፌር ይቀበልና አዲስአባ ይዞአት ይመጣል:: አዲስአባ እንደደረሰ ገና ከአውቶቡሱ ሲወርድ አንድ መፅሐፍ አዟሪ

ይቀርበውና የሆነ አረንጓዴ መፅሐፍ እንዲገዛው ለመነው:: ሾፌሩ መፅሐፉን ከመግዛት ይልቅ ወደ አውቶቡሱ ጋቢና ተመልሶ ዋሽንቷን አንስቶ ለልጁ ሰጠውና *ይሄን ሸጠህ ብላ* ......*ሂድልኝ* አለው......ይሄ መፅሐፍ አዙዋሪ ማታ ላይ ወደ ማደሪያው ሄዶ ለጓደኞቹ ዋሽንቷን ያሳያል:: ብሄራዊ ቲያትር አካባቢ የሚሸቅል እሱን የመሰለ *አበባው* የተባለ አዟሪ ወዳጁ *ልሸጥልህ* ይለውና አበባው በበነጋታው ዋሽንቷን ይዞ አራት ኪሎ ይሄዳል:: ይቀናውና ሳይረፍድ *አቦምሳ* ለተባለ አንድ ወጣት የሙዚቃ ተማሪ በጥሩ ዋጋ ይሸጥለታል......ሙዚቀኛው ዋሽንቷን በቦርሳው ከቶ ያሬድ የሙዚቃ ኮሌጅ ይዞአት ይሄዳል:: እዛም ከአንዲት ጓደኛው ጋ ይገናኙና ቡና ለመጠጣት ይወጣሉ:: እተቀመጡበት ካፌቴርያ ዋሽንቷ ከቦርሳው ትሾልክና ጠረጴዛ ስር ትወድቃለች:: መውደቋን ልብ ሳይሉ አርቲስቱና ወዳጁ ቡናቸውን ጨርሰው ወደ ሚሄዱበት ይሄዳሉ......ምሽት ላይ *ቃልኪዳን* የተባለች አንዲት አሳላፊ ዋሽንቷን ወለል ላይ ታገኛትና ፈላጊዋ ሲመጣ እንዲወስዳት ካፌው ጀርባ ወስዳ አንድ ክፍል ውስጥ ታስቀምጣታለች:: ከመሃል የሚወስዳት ይጠፋል (ወር ያህል)......ከእለታት አንድ ቀን ምሽት ላይ ቃልኪዳን እቃ ስታዘጋጅ ዋሽንቷን ታገኛትና የጠፋበት ሊወስዳት እንዳልመጣ ገብቷት ስራዋን ጨርሳ ወደ ቤቷ ስትሄድ ይዛት ውይይት ታክሲ ውስጥ ትገባለች:: ሰፈሯ ታቦት ማደሪያ ነው:: ታቦት ማደሪያ ስትደርስ ከወያላ ጋር በሂሳብ አከፋፈል ላይ ትጣላና (መልስ ያታልላታል) ረብሻ ይሆናል:: በዚህ መሃል ዋሽንቷ ከቦርሳዋ ውስጥ ትወድቃለች:: ልጅቷ ስለተበሳጨች እቃ መጣሏን ልብ አላለችም......ዋሽንቷ አስፋልት ዳር ወድቃ ትቀያለች (ካሜራው ያለመታከት ያሳያታል):: ጅብ ሲጮህና ዶሮ ኩኩሉ ሲሉ ይሰማል:: እንጭራሪቶች ይንጫጫሉ:: ውሾች እዬዬአቸውን ያስነካሉ:: ዋሽንቷን ሰዎች አያነሷትም:: ሰዎች አያዩአትም:: የተለያዩ ሰዎች በአጠገቧ ሲያልፉ ካሜራው የእግራቸውን ሁኔታ ብቻ ይከታተላል......መሸቶ ይነጋል:: ጠዋት ላይ ልክ አንድ ሰአት ተኩል ሲል አንድ የብስክሌት የፊት ጎማ ዋሽንቷ አጠገብ መጥቶ ቆመ:: የጃኬቱ እጂታ ብቻ የሚታይ አንድ እጅ አነሳት......ካሜራው ብስክሌትና ሊጋልባት

በመሳፈር ላይ ያለ አንድ እግር ብቻ ያሳያል። ተሳፋሪው ጀርባ ላይ ባክፓክ አለ። የተሳፋሪው ፊቱ ወይም ፊቷ አይታይም። የባክፓኩ የላይኛው ኪስ ላይ ዋሽንት ተሸጣለች። ካሜራው ተሳፋሪው ጀርባና ዋሽንቷ ላይ ብቻ ያተኩራል......ብስክሌቱ ላይ ያለውን ሰው የማውቀው መሰለኝ። በጣም የማውቀው ስለመሰለኝ የሆነ የሰው ስም አፌ ላይ ነበር......ካሜራው እንደቆመ ብስክሌቱ ከካሜራው እየራቀ ይሄዳል። ከዛ ፉጨት ይጀምራል። ፉጨቱ ፊልሙ ሲጀምር የነበረው የላሎ ሽፍራን ሙዚቃ ነው። ያኔውኑ በሲኒማው ስራ የተሳተፉት ሰዎች፣ ድርጅቶችና ተዋንያን ስማቸው ከታች ወደ ላይ በሚሳብ ጥብጣብ ላይ ተደረደረ። ፕሮዲዩሰሩ ባካፋ መዝገቡ ነው። የቲም ሙዚቃው ፉጨት በዘሪሁን ነው። ማስታወሻነቱ ለገለታ፣ ለእኔ፣ ለጌርሳሞት እና ለሌሎች የታቦት ማደሪያ ልጆች። ፈዝዤ ቀረሁ። ያየሁትንና ያነበብኩትን ለአሥራት አልነገርኳትም። አይኖቼን እንደገለጥኩ አስር አመታት ወደ ልጅነቴ ተንሸራተትኩ። ቶሎ ወደሚያልቁ ሽንቃጣ ቅዳሜና እሁዶች። የምሽት ፀሐይ ወደ ተቀቡ ቢጫ ምሽቶች፣ ወደ አረንጓዴ የነሐሴ ሆያሆዬ፣ ወደ ኮምቤ የእጠፋርስ አውሊያ ለመጠጡ ሕልመኛ ነጭ አሞራዎች፣ ወደ ወጨጫ የጦስኝ ነፋስ......እዚህ በመዳፌ ከጋረድኳት ሲጋራ ጢስ እየተነነ......ዘሪሁን ጣቱን እያጮኸ *ነይ ገላ ገላ—የልቤ አለላ—የሕይወቴ ጥላን* ሲዘፍን፣ *ተዘራ ከአንቺ ይደብራል* ስንለው። ገለታ በአጥንታም የሚያልም በመሰለ ኮስታራ ፊቱ እየዘፈነ በዲምፕሉ ጨረር የቺኮችን ዐይን ሲያወጣ......አ ድምጽ! ቀለም ነበረው? የምሽቱን የመሰለ? (ለአፍታ የሩቅ ከተማ ሰው መሰለኝ፣ የት ይሆን ይሄ ልጅ? እሱን በመተረብ ጭንቀቴን አብርጄአለሁ) ......ባካፋ እጁን አፉ ላይ አድርጎ ግጥም በድምፅ ሲያዳምጥ፣ የውዴ ላውንድሪ ቤት ጠረን፣ ጫጫታችንና ሳቃችን...............................የተለያየ ቦታ ያለን የመሰለኝ ጊዜ መአት ነው። የተቀመጥነው አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ እየተገፋፋን እንደሆነ ጠፍቶኛል............

እቅማለሁ፤ አሥራት አትቅምም፡ የተጋደመችበትን ፍራሽ እግሬን ውሃውን፣ ሙና የጠረገችውን ወለል፣ የእናትና የአባቴን ቤት፣ የዚህን ሰፈር አየር፣ የተራራዎችን የማታ ጥላና ቀጭን አየር

| ------------

እንጋራለን:: በእናቶቻችን ማሕፀን ውስጥ ሆነን የተጋራነውም ይኖራል: የግብር ውሃቸው ከዚህ የሐምሌ ሰማይ ሲወርድ የተሻሙት ማይ ነው:: ዝርያዬ ወደ ዝንጀሮ ቀረብ ስለሚል ይሄን ረስቼዋለሁ:: የብብቴ ፀጉር የዘር ማንዘሬ ምልክት ነው:: ትርፌ ምንድነው?..........ምን ያህል ጊዜ በትካዜ እንደቆየሁ አላውቅም:: ልብ ስል በጉንጮቼ ላይ ዕንባ ይወርዳል:: ቶሎ ጠረግሁት:: ዓለም እንዳየኝ ሁሉ አፈርኩ:: ከዐይኖቼ እየተሳበ የሚወጣው የዕንባ ስለት ውስጤ ተመቻችቶ የተዘረጋውን የመደ'በር ብራና ቀዶ ነጠላ ሰረዝ የምታክል ብርሃን እንደማያሳየኝ ይገባኛል:: ያነባሁት ወዳጆቼን እንደማላገኛቸው ስለጠረጠርኩ ነው:: የዚህ ሲኒማ ስክሪፕት ደራሲ ገፀባህርያቱን ሲስል እርቀት በሰጠው ጭካኔ አይደለም እንዴ? አምናለሁ ሰውዬው ልብወለዱ ውስጥ ደፍሮ ሲከተኝ እንደ ባዕድ ቆጥሮኝ ነው:: ይሄ ያሳዝነኛል::

የቀረችኝ ይህቺ ከአንጀቴ የማላፈቅራት ሴትዮ ናት:: አየር አልወድም ቢሆንም ከተወለድኩ ጀምሮ እስከ ዛሬ ተንፍሼዋለሁ:: ሽንቴን አልወደውም ግን እያማጥኩ፣ በማማጤም እየተደሰትኩ ተፀዳድቼዋለሁ:: እናቴን እወዳታለሁ ግን የፃፈችውን አንድ ብርቅዬ መፅሐፍዋን አንብቤ የመጨረስ ሃሞቱ የለኝም: አልጋዬ ስር ተጣጥፎ ወድቆአል: እዛ ትራስጌ:: የት ነው? እዛ ወዲያ እግርጌ:: የቀረኝ የማላፈቅረውን የማልወደውን ማስደሰት ነው:: ተስፋ መቁረጥ የጣለኝ ነኝ:: ወንድሜ ባካፋ ከእኔ ይለያል: ውጊያውን ያላቆመ ገና ከፈረሱ ያልወረደ ጊዮርጊስ ነው:: በለጠኝ?

ግብዳ ግቢ፣ ግድንግድ ቤት፣ የራሴው መኝታ ክፍል፣ እናትና አባት የሚሰፍሩልኝ ቀለብ፣ አፌ ውስጥ ደሞ የቁሞ ቀር ሴት የጡት ፍንጭ እንደ አብሲት አረፋ እየፈነዳ:: ጎዳናዬ ከዚህ አይወጣም:: አምላኬ ጨለማ ነው:: ግን እንዲህ እላለሁ፤ መፈፀሙን አውቄአለሁ:: ይሄም ምናልባት የመጨረሻ እውቀቴ ነው:: የሚወዱኝ እንዳሉ አውቃለሁ ግን ሁሉን እጠላለሁ:: ምናልባት ጥጋበኛ ነኝ:: ምናልባት በጥጋበኛነቴ እኮራለሁ፣ እመካለሁም:: ለመሆኑ እኔ ከባካፋ እርግብግብ ነኝ?

እንዲህ ነው: የተፈጠርኩት ለአንድ ሕልም ብቻ ነው:: የማዕረግ ተመራቂ ተማሪ፣ ችግር አይቶ የማያውቅ፣ ከከበርቴ አብራክ

---

የተከፈለ ከበርቴ፣ መፅሔት ቢያሳትም ማንን ምን ይጎዳል? ነው:: ቃል የገባሁላቸው ወዳጆቼ ተበትነዋል:: መበተናቸው ማንን ምን ይለዋል? ነው:: እንደ ብልጣብልጦች በአፌ እያሳለጥኩ ትናንሽ ሕልም እየፈለፈልኩ ለትናንሽ ግብ አልኖርም:: ወደዚህ ምድር እንዲሁ ለመኖር አልመጣሁም:: ምን ላድርግ? ከደቃቃ ችግር ማሕፀናችሁ ጭራቅ ጉዳይ ይወልዳል:: ከጥላቻዬ በፊት ያለው ከእናንተ አይነቱ ምንም አለመጠበቅ ነው:: በሕይወት እስከመጨረሻው ኖሬ ስትጠፉ ማየት እወድ ነበር:: ባይቻልም እጓጓለሁ:: ድንገት ቢሆን ደሞ ሳቄ እንዳይመጣ እፈራለሁ:: ግን በምንም ይሳቃል? ወደ ሲኦል የሚወስዳችሁን ጥርጊያ ማበጀት ከጀመራችሁ ከረመ:: እና በምንም ይሳቃል?

አንደጥንት ዘመዶቼ ወይ አንደዛሬዋ እማማ በየደጀሰላሙ አልገዘገዝም:: በቅዱስ መጽሐፍት ቸርቻሪዎች አልጠፈርም:: እዛ ፔርሙዝ ውስጥ ያለው ሻይ ሳይሆን ደም ነው ብልህ አንተ ምን አገባህ? አንቺስ? አሥራት ሁሉን ዝቅና ከፍ ለእኔ ትታ ተኝታለች:: ከንፈሮቿ ስስ ቅጠል ይመስላሉ:: የታችኛው ለአመል አበጥ ይላል:: በእኔ በኩል ያለው ቀለሙ ሙሉ በሙሉ አለቀቀም:: በቀስታ እጄን ሰድጄ በአመልካች ጣቴ ያን ለአመል ያበጠ ቦታ ነካሁት:: ዐይኖቿን በትንሹ ገልጣ ፈርጠም አለች:: ቀኝ እጇን አንስታ በዳበሳ ፊቴን ነካችኝ:: ጣቴ ከንፈሯ ላይ መሆኑን ረሳሁ:: ዐይኖቿን ሳትገልጥ *አቡሽ እወድሃለሁ እኮ.......መቼ ይገባሃል?* አለችና ወደ በለጠ ጥልቅ እንቅልፍ ለመግባት አይነት ተመቻቸች:: የተከደኑት የአሥራት ዐይኖች ቡጢ ያካክላሉ:: እንዲህ ተኝታ ሳያት ለመሆኑ የመጀመሪያዬ ነው? የመጀመሪያዬ ግን መሰለኝ:: ጎንበስ ብዬ በከፊል ፀጉር የሸፈነው ከሲታ ጉንጭዋን ሳምኩት:: በዳበሳ አመልካች ጣቴን መርጣ በአፏ ያዘችና በትናንሽ ጥርሶቿ በቀስታ ነከሰችው:: ደግሜ ልስማት አሰብኩ........ አልሳምኳትም:: ፊልሙን ደግሜ ለማየት ሪሞቴን ነካሁ::

---

# ሰርጀንት[43] ዴላኒ

ዴላኒ ጥላ ያለበት ቦታ መርጦ ቴሌፎኑን ከፈተና ለአንድ ወዳጁ ደወለላት:: የሚጠራት 'አልማዝ' ብሎ ነው:: 'አልማዝ' ማለት አቅቶት አይደለም......

በጭፍን ሲነዳ ቆይቶ---ልቡን ሳያማክር እንደማለት: መጓዝን በመርሳት:: ይሄ ስሜቱ ከሃላፊነቱ የሸሸ ወይም ሃላፊነቱን የናቀ ያስመስለዋል:: የነሐሴ አጋማሽ ሙቀት የሚጣፍጥ 25 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሆኗል:: የአየሩ ጠረን የሀብ ሀብ አበባ ነው:: (ዘንጊነቱን በዚህ ማሳበብ አይችልም):: ደሞ የለበሰው ዩኒፎርም የጠበበው ይመስላል እንጂ አቁመው እላዩ ላይ እንደሰፉለት ሁሉ ነው:: (በዚህም ማሳበብ አይችልም):: ሆዱ ላይ በእንብርቱ አኳያ ያለችው የሸሚዙ ቁልፍ የገባችበትን ቀዳዳ በልቅጣዋለች፣ ከስሯ ነጭ ክር በከፊል ተጎትቶ ወጥቶ ይታያል (የምትናቅ ትንሽ ግድፈት):: እግሮቹ መሃል የተወጠረው ካኪ ሱሪው ጨረር የመሰሉ ሰንበሮች አውጥቷል (ይህቺም ሌላ የምትናቅ ትንሽ ግድፈት):: ዴላኒ ሰፊ፣ ረዥም ፊትና ጠባብ አፍ አለው:: ከአፍንጫው ስር ከምንጭሩ ላይ ትንሽ ወደግራው ፈቀቅ ብላ ቋሚ *ኦቶራይኖላሪንጎሎጂስት ሐኪሞች ዩኒላተራል ክሌፍት* የሚሏት ነጭ የጠባሳ መስመር አለች:: ከኮሌጅ እስኪመረቅ ድረስ 'ፉኒ' ያስባለችው ቀዳዳ የጠፋችበት የቀዶ ጥገና ስፌት ናት:: በውልብታ ካዩት ከረሚላ የሚመጥ ይመስላል:: ዴላኒ ወፍራምና ግርማ ሞገሳም ነው:: ስያሜው ከሰዎች ጋር እንደአለው የቅርበቱ አይነት ይለያል:: የማይወዱትና ሊተርቡት የሚሹ *ቦርጫም*፣ የሚወዱት *ግርማ ሞገሳም* ያደርጉታል:: ለሚወዱትም ለማይወዱትም ሰዎች አባባል ግድ አይሰጠውም:: ሰርጀንት ዴላኒ እናቱ በምሽት ከኤኤን ሲ (የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ) ስብሰባ ስትመጣ ባልታወቁ ሰዎች ተደፍራ የወለደችው የአጋጣሚ ልጅ ነው:: እናቱ ብዙ የማታወራ ከፖለቲከኞች

ጋር መዋል የምትወድ ጠጪና ከባድ ሲጋራ አጢያሽ ነበረች፡፡ እሷም ልጁ ነውና አትናገረውም እንጂ በፉኒነቱና በውፍረቱ ተደብቃ የምትጠላው ይመስለዋል፡፡ የራስን ልጅ ስለመጥላት ማን ለማን ይናገራል? አካሉ ግን ባይማርክም እግዜር በሁሉ አልበደለውምና የክፍሉ ተደናቂ ተማሪ ነበር፡፡ እግዜር ወደ ቀጭን ቆንጆ ለውጦ ደደብ እንዲያደርገው መአት ጊዜ ለእግዜር ጸልዮአል፡፡ ለዚህ ሁሉ እሱን መሰል ዙሉዎች ደህና ምንጭርና ለምቦጭ ሰጥቶ ለምን አምላክ እሱን ነሳው?

በሸሚዙ ግራ ኮሌታ አለብላቢት ላይ በክብ ፒን[44] የሚስቅ የአገሩ ፕሬዝዳንት ማንዲባ ማንዴላ ተሰቅሏል፡፡ የፒኑ ዙሪያ በደቡብ አፍሪካ የባንዲራ ቀለም ተጌጧል፡፡ ዴላኒ ለዚህ ባንዲራና ለዚህ ፕሬዝዳንት ግድ እንደማይሰጠው አይናገርም፡፡ ሰዎች እሱ ከተማ ለጉብኝት ማንዲባ ሲመጣ ሊያዩት ሲንጋጉ እሱ በቀስታ ወደ ቤቱ ሄዶ አልጋ ላይ ተጋድሞ የምትመጣ ወይም የማትመጣ አድርባይ ሚስቱን ይጠብቃል፡፡ አሁን ከመኪናው ራዴዮ የሀ ማስካላ *ሶዌቶ ብሉስ* ዜማ ይተማል፡፡ ከቁጥር 35 ዋና ጎዳና ወጥቶ ዋንዴ ቼሌ መንገድ ላይ ጥግ ይዞ መድረሻ ቦታውን እየሰለለ ቆመ፡፡ የፊዘዘ ይመስላል እንጂ ተሰላችቶ ነው፡፡ የተሰላቸውም እንደሚገምቱት ቀኑ የሳምንቱ አምስተኛው ቀን ሐሙስ በመሆኑ አይደለም፡፡ የሚሰላቸው እሱን ሰላም በመንሳት የተጠበበችው ሚስቱ ጠዋት ለስራ ሲወጣ በቁርስ ምትክ ጭቅጭቅ ግታ ስለምትሰደውም አይደለም፡፡ ከሰፈር ጎረምሶች ጋር እንደምትዳራ እንደማያውቅ ሁሉ ጎረቤቶቹ በተገኘው አጋጣሚ በሽሙጥ ስለሚነግሩትም አይደለም፡፡ ለብዙ ጊዜ ጥሩ ደሞዝ ተከፍሎት እየሰራ ኖሮ ዛሬ ባንኩ ደብተር ላይ 1000 ራንድ ብቻ ስላለውም አይደለም፡፡ ይሄን አንዱንም ሰበብ አድርጎ አይናገርም፡፡ የሚከተሉት ጥያቄዎች ምን እንደሆኑ ስለሚያውቅ መስማት አይፈልግም፡፡ የሚቀጥሉት ጥያቄዎች ሁልጊዜም *ማንዴላን ትጠላለህ እንዴ? አገሩ ደስ አላለህም እንዴ? ከዚህ በላይ ምን ፈለክ?* ናቸው

ሕይወቱ አሰልችቶታል፡፡ ሕይወት ሰልችቶታል፡፡ ሰዎች የሚናገሩት ሰልችቶታል፡፡ ፊታቸውና መልካቸው ሰልችቶታል፡፡

ድምፃቸው በሬድዮ የሚሰማው፣ በቲቪ የሚያየው በመንገድ ሲያልፍ የሚሰማው ሁሉ ሰልችቶታል:: ያልሰለቸው ነገር ጥቂት ነው:: 'ደቡብ አፍሪካ በጣም ተለውጣለች' እያሉ ያወሩታል:: ምንም የተለወጠ ምንም የሚለወጥ እንደማይኖር ይሰማዋል:: የሚረዳው በደመነፍሱ ነው:: እውስጡ የሚሰማውን ቢናገር *እንዴት ደመነፍስህን ታምናለህ?* ቢሉት የሚመልሰው የለውም:: ስለዚህ ለሚናገሩት ግድ የለውም:: ለሚጠይቁት አይመልስም:: የሚገባው ነገር የየቀኑ ሕይወቱ በሽብር መሞላቱ ነው:: ማንዲባም ሚስቱ ዊኒም ለእሱ ምንም አይደሉም:: ሁለቱም አብረውም ይኑሩ ተለያይተው የት ሊደርሱ? እሱም የትም አይደርስም:: በሕይወት ይኑር አይኑር ማንዲባ ማንዴላ ከእሱ ደስታ ጋር የተያያዘ አይደለም:: ዜና አንባቢዎች ስለሰላም፣ ስለ አዲሱ ዘመን ብልፅግና፣ ስለእኩልነት የሚያወሩትን ሲሰማ የሆነ ነገሩን ሊያመው ይደርሳል:: የፈዘዘው በዚህ ሁሉ ተሰላችቶ ነው:: የሚበላው ቢያገኝ ድንጋይ እንኳን ቢሆንና ቢስማማው ስራውን ትቶ እሱን እየቆረጠመ በረሃ ለብቻው ለመኖር ይሰደዳል:: ሞቱ ከደረሰ እንቅልፍ ሲወስደው ቢሆን ይመርጣል:: አሁን እንደሚሆን ቢረዳ ቢሞት ቅር አይለውም:: የመኪናውን የፊት መስኮት ከፈተና ጋለል ብሎ ወንበሩን ተደግፎ አካባቢውን መቃኘት ቀጠለ::

የወንጀለኞች ርዕዮተ አለም ጠንካራ ነው:: መልካም ነገር ባያደርጉም መቼምና የትም በቀላሉ ተቀባይ ስለሚሆኑ አለምን ያለአንዳች ችግር እንደሚወርሷት ያምናል:: ቅርፃቸውን እንደ አካባቢያቸው የመለዋወጥ ችሎታ አላቸው:: ክብ መንግስት ሲያጋጥማቸው ክብ ይሆናሉ:: ኮኮብ የበዛው መንግስት ቢያጋጥማቸው ኮከባም ይሆናሉ:: በደጀሰላም በር ሲያልፉ ሃይማኖተኛ ይሆናሉ:: ግድ የማይሰጣቸው ቢሆንም የእርዳታ ድርጅት አቋቁመው እንደወለዱት ሁሉ የተቸገረ ሕፃን አቅፈው እየሳሙ ፎቶ ተነስተው ለተባበሩት መንግስታት ይልካሉ:: በቴሌቭዥንም ከጳጳሳትና ከኡላማዎች ጋር ይተቃቀፋሉ:: ዛሬ ዛሬ አደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪዎች ለትምህርት ቤት ገንዘብ ይለግሳሉ:: ለዚህም ለጋሽነታቸው ወጣቶችና መምህራን ከበው ሰማይ ቤት ድረስ የሚሰማ ጭብጨባ ያጨበጭቡላቸዋል:: ዴላኒ

---

ፖሊስ ቢሆንም እነዚህን ሕገወጦች እንዲሰግድላቸው ወይም ባይችል እንዲጨብጣቸው በአለቆቹ ታዞ መአቶችን ጨብጧል፣ ለጥቂቶች ሰግዶ ትልቅ ቂጡን ለተጨማሪ የማይቀርለት ስድብና ምርቃት አጋልጧል። የሚሰራውን ካልወደዱለት በተራ ነገር ተቆጥተው ከባድ እስር ቤት እንደሚከቱት ይገባዋል። ሕግ ጠባቂ ቢሆንም ሕግ እሱን አይጠብቀውም። አገሪቱን የሚያዛት ገንዘብና ወንጀል ነው። ዛሬ ባይሆንም ወደ ፊት የሆነ ቀን ክርስቶስን ነን ብለው ሊመጡ ይችላሉ። ቅዱሳን መፃሕፍት የተጠረዙ ማታለያዎች፣ የተገፉበት ወረቀት ጥቅሙ እሳት ከማያያዣ ያለፈ እንዳልሆነ ከገባው ብዙ ጨረቃዎች ወጥተው ጠልቀዋል። አስከፊ ሆነ አልሆነ የወንጀለኞቹን ባህርይ ሁሉም ሰው በቀላሉ የሚገለብጠው እና የዘላለማዊነት ተስፋ ያለው ነው። እና ወንጀለኞችን ላጥፋ ማለት አጉል ሕልም ነው። ዴላኒ መሞከር ካቆመ ሰነበተ።

በፖሊስ ሬድዮው ተጠራና ወደ ሎተስ ፓርክ፣ በኢስፒንና በኦሬንጅ ኮረብቶች መሃል እንዲሄድ ታዘዘ። ጠሪዋ ወይዘሪት ኖማቴምባ ናት። ፖሊስ ኮሌጅ አንድ ክፍል አብረው ይማሩ ነበር። 'መንገድ ዳር የሞተ ሰው ተገኝቷል' ስለተባለ እሱን እንዲያይ ምናልባት የቦዜኔ ሬሳ ከሆነ ማድረግ የሚገባውን እንዲያደርግ ነገረችው። ዝርዝር ጠየቃት። 'ምን ትሰራለህ፣ ራስህ አግኝ እኔ የማውቀው ይሄን ነው' አለችው። ስልኩን ከመዝጋቷ በፊት 'ዲክጋት[45]' አለችው። ኮሌጅም እያለ ቦርጫም ነበር። ስፈሩ ያወጣለት 'ዲክጋት' እና 'ፉኒ' የተባሉት ቅፅል ስሞቹ እየተወለወሉና እያብረቀረቁ ዛሬ ድረስ አብረውት መጥተዋል። ራሱን እያሳፈረው ባይናገረውም ጥሩ ስራ ባይዝ ኖሮ ሃናን የምታገባው አይመስለውም። ሃናን በቴሌቪዥ ማንም ለሚስትነት የማይፈልጋት ገና በተማሪነቷ የስፈሩ ፎክንደ ኮንት[46] ነበረች። ግን ወደዳት። ይሄን የማይናገረውን በእሷ የመናቅና በቀጥታ የመሰደብ ነገር ሲያስብ ያዝናል።

ዴላኒ ራሱን አነቃቃና ተስተካክሎ ተቀመጠ። ቬክተር ዜድ 9 ሚሊሜትር ሽጉጡና ሁሉ ነገሩ በስርአት እንደሆነ አረጋግጦ ወደ

ተነገረው አቅጣጫ ለመሄድ መኪናውን አስነሳ:: ዙሪያውን የቅጠላቅጠል አረንጓዴና አቧራ ነው:: እንዴት አረንጓዴው አቧራውን አያጠፋውም? ይሄ የማይታመን ሽርክና ነው:: መኪናው የሚያምር ዛዛታ ታሰማለች::

የሞተ ሰው አያስፈራውም:: ሙታን ለእሱ አለምን ፈለጉም አልፈለጉም በማያመልጡት ቁንጥ እርቀዋታል:: ከመዳፏ ስር አይደሉም:: ሙታንን እንደኗሪዎቹ አይፈራቸውም:: ሙታንነቱን ከእነሱ ቀድሞ የተቀበለው በመሆኑ የሚያያቸው ቀድመውት ሄደው ምንጭ ዳር ውሃ እየጠጡ አርፈው እንደሚጠብቁት ሰዎች ነው:: የሥራ ባልደረቦቹ ሚስቱን ጨምሮ ስለ ወፍራምነቱ እያነሱ፣ ስለ ልብ ድካም እያወሩ፣ ስለ ደም ግፊት እየጠቀሱ፣ መሞቱ ቅርብ እንደሆነ በእጅ አዙርና በቀጥታ ሲጠቁሙት ሳቁ ይመጣል:: ሁሉን ነገር አስቦ እንደጨረሰ አያውቁም:: እዚህ አለም ላይ መኖር አይፈልግም:: አንዳንዴ ከትዳሩ፣ ከስራው፣ ከሚበላውና ከሚጠጣው ብቻ ሳይሆን ከመፈጠሩ የተጣላ ይመስለዋል:: ቢሆንም ራሱን አያጠፋም::

ከመንገዱ ወዲያ በዚታዎ ላይ የተጫኑ ተማሪዎች እየዘፈኑ ያልፋሉ:: አንድ ነጭ አዛውንት ነጭ አሮጊት እየጎተተ ወይም እየመራ በቀስታ ይራመዳል:: የሚያወራ ይመስላል:: ሰውዬው ቦርጫም ነው:: በሆዱ የሚገባ ነፋስ ሸሚዙን ከኋላው እንደ ጀልባ ሸራ ወጥሮታል:: ሰውዬው ልጃገረዶች አፍ ላይ ያለ የተነፋ ማስቲካ ብቻ ሳይሆን እናቱን አስታወሰው:: የሚያየውን ማየት አልፈለገም:: ዐይኖቹን ወደ መኪናው ውስጥ መለሰ:: ጋቢና ውስጥ በስተግራው የስፖርት አምዱ የተጋለጠ፣ የክሪኬት ጨዋታ ውጤት ለማየት ከማማሽ ሰአት በፊት ከፍቶ አንብቦ ሳይጨርስ የተወው ስታር ጋዜጣ አለ:: ራሱ ያዘጋጀው ከፊሉ የተበላ የስጋ ሳንድዊች በወረቀት ተጠቅሎ ጋዜጣው ጎን ተጋድሟል:: ታውዘንድ አይላንድ ድሬሲንግ የሚፈስ ነጭ ምላሱን አውጥቶ እንዲላስ ይጠብቃል:: ሳንዲዊቹን ወገቡ ላይ እንደ ትንሽ ሕፃን ልጅ ይዞ በመስኮት ሊጥለው ፈለገ:: ደክሞታል፤ ሰልችቶታል:: ይሄ ድካምና ስልቹነት ከኬፕ ኮድ በሚመጣው ጣፋጭ አየር እንኳን ተከልሶ አልጠፋም::

---

እናቱ ተመልሳ ትዝ አለችው:: ከሺህ አመታት በፊት በመሰለ እርቀት:: አፏን አሰበና ዐይኖቹን ከደነ:: ለአፍታ ይሄን ቅፅበት ያስታውሳል:: በጀርባዋ ተኝታ በትኩሳት የደረቁ ድንቡሼ ከንፈሮቿን አነቃንቃ 'እስኪ የምጠጣው ውሃ አቀብለኝ' የምትለው:: እንዲህ የሆነው ለሶስት ቀናት ነው:: ሶስት ቀናት ከተኛችበት ሳትነሳ በጀርባዋ እንደተጋደመች 'ውሃ ስጠኝ' እያለች ሕይወቷ አለፈ:: ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ስትሮጥ ወድቃ ሰዎች በላይዋ ላይ ተረማምደውባት ነው:: በዚህም ሰላማዊ ሰልፍ ያስደረጋትን የአፓርታይድ ስርአትና እናቱን ረጋግጠው የገደሏትን የጥቁር ሰዎች እግር ጠላ:: ሺህ እግሮች በእናቱ ሆድ ላይ ተረማመዱ:: የውስጥ ብልቶቿ ቦታ ተለዋወጡ:: ሁሉ ነገሯ ቆስሎ የተረፉት ሊፕስቲካቸው የለቀቀ ድምቡሼ ከንፈሮቿ ብቻ ነበሩ:: እነዛ ሁሉ ሰልፈኞች እንደዛ የሚያስደነብራቸውን ያህል ከተንቦቀቦቁ ለምን ሲጀመር ከቤት ወጡ? እነዛ እግሮች ዛሬም በአፓርታይድ የታዘዙ ይመስለዋል:: 'ግን እነዛን እግሮች እጠላለሁ' ብሎ ለማንም አልተናገረም:: አይናገርም:: በሰፈሩ ጎዳናዎች ላይ ሲሄድ አናቱን ቀና አድርጎ ሰማይ ሰማይ እያየ ነው:: አናቱን ቀና የሚያደርገው የሚጠላቸውን ሰዎች ፊት እንዳያይ ነው:: አልፎ አልፎም በመንገድ ዳር ሲሄድ ምራቁን ወደ ቦይ ውስጥ ይተፋል:: 'ወገኖችህ ነን' የሚሉት ከእነሱ የተሻለ ጥሩ ስራ ስላለው የተጀነነባቸው ይመስላቸዋል:: ከእናቱ በእርግጥ ትዝ የሚለው አፏ ብቻ ነው:: ከዛ ሁሉ ሰውነቷ እንዴት የሚከፈትና የሚከደን አፍ ብቻ ትዝ ይለዋል? ሰዎች ሲያወሩ ብዙ ጊዜ ፊታቸው ላይ ወይም ሌላ የገላቸውን ክፍል እንጂ አፋቸውን ማየት አይወድም:: አንዳንዶቹ ሲያወሩ የሚያየው ግድግዳ ነው:: ኮሌጅ ተማሪ እያለ አይታመንም እንጂ አንድም ቀን የማንንም አስተማሪ አፍ ሳያቋርጥ አይቶ አያውቅም:: ዐይነፋር ያደርጉታል:: ለእነሱ ዴላኒ ፉኒ፣ ቦርጫምና ዐይነአፋር ነው::

ከትዝታው ተላቆ እንደ ተረጋጋ ዙሪያ ገባውን ስለሞተ ሰው የሚነግረው ምልክት ፈለገ:: ወደ ግራ በመስመር ከበቀሉ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች አጠገብ ደርዘን የሚሞሉ ሰዎች ቆመው አየ:: ዐይኖቻቸው በአንድ አቅጣጫ በአንድ ቦታ ላይ ተሰፍተዋል:: እዛ አካባቢ ጉዳይ

እንዳለ ጠርጥሮ መኪናውን ለግማሽ ደቂቃ ያህል ነድቶ ከሰዎቹ ጀርባ አቆመ። ማዕከላዊ አፐሬሽንስ ከመደወሉ በፊት ከመኪናው ዘሎ ወረደ። ቦርጫም ቢሉትም ገላው ቀልጣፋ ነው። ሃምሳ ሶስት አመቱም ነው። ዴላኒ በዚህ ዕድሜው በዚህ ውፍረቱ በእንዲህ አይነት ቅልጥፍና ከመኪናው ይወርዳል ብሎ ማንም አይገምትም።

በአንድ አቅጣጫ አተኩረው የነበሩት ሰዎች ትኩረታቸውን አፍርሰው ዞር ብለው አዩት። የቃል ማስጠንቀቂያ ባይሰጣቸውም በዝምታ ግራና ቀኝ ፈቅቀው መንገድ ለቀቁለት። በዚህ አፍታ ሥልጣን ከባዶ ሜዳ ብቅ ስትል ትታያለች። እንዲህ አይነት ቦታ ተልኮ ሲደርስ ሁልጊዜም ሰዎች ሲመጣ እንዳዩት በዝምታ መንገድ ሲለቁለት ይመቸዋል። ይህቺ ግን ብቻዋን ስራ አትሆንም።

ከፊት ለፊቱ ቀጫጫ ወጣት ያናወዘ መስሎ በጀርባው ዛፍ ተደግፎ መሬት ላይ ተቀምጧል። ዴላኒ ዐይኖቹን ከወጣቱ ላይ ሳያነሳ ስልኩን ከኪሱ አወጣና ሬሳውን እንዳገኘና ቦታው እንደደረሰ ለዲስፓች[47] አስታወቀ። ስልኩን ኪሱ መልሶ ወደ ወጣቱ በቀስታ ቀረበ። የልጁ ፊት ለጋ ፂም ያቆጠቆጠበት ነው። ዐይኖቹ ጭኑ አጠገብ ያለ ሳር የሚያዩ ይመስላሉ። በከፊል ተከፍተዋል። ቀላ ያለ ልጋግ በአፉ ቀኝ ደርዝ ፈሶ ወጥቶ አገጩ ላይ ደርቋል። ከጀርባው በሽቦ የታጠረ ግቢ አለ። እዛ *አፍሪካነርስ* እየተጨዋጨዋሁ የሜዳ ቴኒስ ይጫወታሉ። ማንዴላ ከእስር ቤት ሳይወጣም እንዲህ ሲጫጫሁ ነበር። የሚደበደብና የሚነጥር ኳስ ይሰማል። ዛፎቹ ስር የልጁ ቀኝ እጅ አረፈበት ድረስ ቢጫ አበባ ያላቸው ሱዛናዎች ይንቦገቦጋሉ። ምናልባት ለክብሩ ወይ ለቅሌቱ ነው። ዴላኒ ልጁ አጠገብ ቆሞ አተኩሮ አጠናው። ይሄን ልጅ የሆነ ቦታ ያየው ይመስለዋል። ቆሞ በነፍስ ቢያገኘው ሰላምታ ሰጥቶ ሊጨብጠው እጁን ይዘረጋ ነበር። የሙት ገጽታው ቢጠፋ በእርግጥ የሚያውቀው ነው።

መጀመሪያ የሚሰራውን መስራት አለበት። በቀላሉ የማይፈርስ ወደ ተሳሳተ መደምደሚያ የማይመራ ጥሬ መረጃ መሰብሰብ ግዱ ነው። ልጁ ብቻ አይደለም መረጃ፡ ልብሱ፣ ዛላው፣ ድባቡ የመሳሰሉት ተራ በተራ መለቀምና በሚተነተኑበት ሳጥን ውስጥ መጠራቀም

አለባቸው:: ከጃኬት ኪሱ የፕላስቲክ ጓንት አውጥቶ እየለበሰ ወደ ሞተው ልጅ ቀረበ:: ልጁ ያረጀ ሌቪስ ጃኬት ለብሷል:: የቆሸሸ ካኪ ቦላሌ አድርጓል:: ቀበቶው በቦታው ነው:: የቀበቶው ቆዳ እየተበላ ይሁን ልጁ እየከሳ፣ ሽቦው የመጨረሻው ዐይን ውስጥ ነው:: ከመቆሸሽ በስተቀር ሱሪው ላይም ይሁን ጃኬቱ ላይ የደም ምልክት የለም:: ደክሞት እዚህ ዛፍ ስር መጥቶ ሲያርፍ በዛው የሞተ ይመስላል:: ዴላኒ ጃኬቱን ገልቦ ከማየቱ በፊት ወደ ከበቡት ሰዎች ዞር ብሎ

*—ለመሆኑ የነካው አለ?* በአጋጣሚ ማለቴ ነው አለ

ሁሉም በዝምታ በአንድ ላይ ራሳቸውን ግራና ቀኝ ነቀነቁ:: የተማከሩ ይመስላል:: እነዚህ ሁሉ ሞትን እንደሚፈሩ ፊታቸው ላይ በደማቁ ተፅፏል:: ሳቁ መጣበት:: *የማይቀር ነገር እንዴት ይፈራል?*

ዴላኒ ያደረጋቸው ጓንቶቹ በሆነ አጋጣሚ ላልተው እንደሆነ አረጋግጦ፣ ግድ ባይሰጠውም ልማድ ነውና ወደ ልጁ የበለጠ ተጠጋ:: ጃኬቱን በቀስታ አነሳና አየ:: ሸሚዙ የካኪ ነው:: ሸሚዙ ላይ በቆዳ ማተብ ላይ የተንጠለጠለች ሚጢጢ የእንጨት መስቀል አለች:: ይህቺን አይነት መስቀል የሆነ ቦታ አይቶአል:: የልጁ ሸሚዝ ከአንገቱ አንድ ቁልፍ ወደ ታች ሸሽቶ የተቆለፈ ነው:: ኮሌታው ለአንገቱ ይሰፋዋል:: ምናልባትም የሌላ ሰው ልብስ ነው የለበሰው:: ሸሚዙ የባዕድ መሆኑን ለማቃጠር ይመስላል በተለያየ መልክ ተሸብሽቦአል:: የሸሚዙ ኪስ እፊያ የለውም:: ዴላኒ የሸሚዙ ግራ ኪስ ውስጥ የቀለጠ እስክሪፕቶ አየ:: በልቡ ፈገግ አለ:: የቀለጠ ስክሪፕቶ በኪሱ ይዞ የሞተ ሰው አጋጥሞት አያውቅም:: ስክሪፕቶ?--አዎ:: የቀለጠ ስክሪፕቶ?--ኔ::

ስክሪፕቶውን በቀስታ ከኪሱ አወጣና የተጋጠሙት የልጁ ጭኖች ላይ አስቀመጠው:: ቀጥሎ የኪሱን ውስጥ በጣቶቹ ዳበሰ:: የተጠረዙ የመሰሉ ጥቂት ወረቀቶችና መታወቂያ ካርድ በአመልካችና በመሃል ጣቱ ቆንጥጦ አወጣ:: ወረቀቶቹ ሁለት ናቸው:: አንደኛው ሁለት የስልክ ቁጥሮች የተፃፉበት ለሁለት የታጠፈ ሌጣ ነው:: ወረቀቱን ልጁ ላይ አስቀመጠና መታወቂያውን ገለጠ:: ደርባን ከተማ ያላየው አይነት መታወቂያና ፓስፖርት የለም:: ደርባን የመታወቂያ ከተማ ናት:: የመታወቂያው ግንባር መደብዘዝ ጀምሯል:: ይሄን

አይነት መታወቂያ አይቶአል:: ያወቀው በኢትዮጵያ ፊደል በመፃፉ ነው:: ይሄም ለትውስታው ጉልበት ሰጥቶት የልጁን የመስቀል ጌጥ ማን ጋ እንዳየው ትዝ አለው:: ያኔውኑ ጥላ ያለበት ቦታ መርጦ ቴሌፎኑን ከፈተና ለአንድ ወዳጁ ደወለላት:: ጓደኛው ናት:: ማለት የጓደኛው ሚስት አልማዝ ናት:: ስሟ አልማዝ ቢሆንም እሱ ሲያሾፍባት 'አልማዝ' ይላታል:: አልማዝን የሚያውቃት ማክስ ታቨርን ነው:: ከስራ ጓደኛው ከሃንሲ ጋር ቢራ እየጠጡ ሲዝናኑ ተገናኙ:: በቅርብ ከኢትዮጵያ የመጣች ስደተኛ፣ በትንንሽ ጡቶቿና በትንሽ ቂጥዋ፣ በጠባብ ዳሌዋና በቀጫጫ እግሮቿ ተስፋ የሰነቀች ልጅ ነበረች:: ካፌ ላቴ የቆዳ ቀለም ያላት:: አልማዝ ማለት ቀላ ያለች ወይዘሮ ዊኒ ማንዴላ ናት:: በአንድ ቀን ሰርግ እሱ ከሃናን፣ ሃንሲ ከአልማዝ ጋር ተጋቡ::

--ሄሎ አልማዝ የሆነ ነገር ትረጂኛለሽ

..................

--እዚህ አንድ ህይወቱ ያለፈ የአገርሽ ልጅ አለ:: ፎቶ እልክልሻለሁ መታወቂያውን ትተረጉሚልኛለሽ

..................

--ምን የመሰለ ልጅ ነበር መሰለሽ:: አዝናለሁ::

..................

--ያስለቅስሻል::

ሁልጊዜ አይገባውም:: አልማዝ በትንሹም በትልቁም እንዳለቀሰች ነው:: አንዱ ነገር ሁለቴ ከእጇ ቢወድቅ ሁለተኛው ላይ ታለቅሳለች:: ዴላኒ በደፋር ማጠቃለል *የኢትዮጵያ ሴቶች በሙሉ ሆደ ቡቡ ናቸው* ይላል:: አልማዝ 'ዞር በል' ብትለውም አይገባውም:: እንደ ቀልድ በተመጠነ መረጃ የጀመረው ማጠቃለል ርዕዮተ አለሙ ሆኗል:: ያኔውኑ የመታወቂያውን ገጽና ውስጡን ፎቶ አንስቶ ለአልማዝ ላከላት:: ስልኩን ዘግቶ ወገቡን ይዞ ልጁን እያየ ቆመ:: የስደተኞች መብዛት የደርባን ከተማ ፖሊስ ዲፓርትመንትን በክርክር ወጥሮታል:: በተለይ ገንዘብና ዕውቀት የሌላቸው ለደቡብ አፍሪካ ምንም ሊያበረክቱ የማይችሉ የወንጀል ቀፍቃፊ አፍሪካውያን ደርባንን

እያቆሸሿት እንደሆነ ፖሊሶቹ አምርረው ይናገራሉ:: ለዴላኒ አንዳንዴ የዚህ አባባል እውነትነቱ ይታየዋል፣ ከሌላ አገር የመጣ ትርፍ ስራ መስራት አይፈልግም:: አንዳንዴ ደሞ ግድ የለውም:: ምክንያቱም ግድ የለውም:: በፀባዩ ቅርቡ ያሉትን ብዙ ሰዎችን የሚያበሳጭ ትልቅም ይሁን ደቃቃ አጋጣሚ ደስታ ይሰጠዋል:: እነሱን ያስከፋ ነገር እንዳለ ሲያስብ ዘና ይላል::

ልብ ሳይለው የልጅነቱን አንድ ዘፈን መዝፈን ጀመረ፣ በቀስታ እያፏጨ:: ሶስት ሜትር ከእሱ የራቀ ሰዎች ድምፁን ባይሰሙም አፉ በማሞጥሞጡ እያፏጨ እንደሆነ ይገባቸዋል:: ጨዋ ድርጊት ባይሆንም ግድ አልሰጠውም:: ዞር ብሎ ወደ ኋላው አየ:: ተመልካቾች ቁጥራቸው መንምኗል:: ማፏጨቱን በፍላጎቱ ያለይሉኝታ ግፊት አቁሞ ወደ ሬሳው ተጠጋ:: ያኔ ስልክ ጠራ:: አልማዝ የላከችለት መልዕክት ነው::

አተኩሮ አነበበ:: ግራ ገባው::

መልዕክቱ በተራ ቁጥር ሰፍሯል

አንደኛ የሞተችው ሴት ናት

ሁለተኛ የልጅቷ ስም በቀለች ነው

ሶስተኛ ፆታ የሚለው ባዶ ቦታ ጋ የተሞላው 'ወ' ወይም ወንድ ነው:: የተሰረዘ ይመስላል:: ስለዚህ ፆታና ፎቶውን በመለወጥ ብቻ መታወቂያ መለወጥ ቻለ ማለት ነው::

ለምን ግን? ብሎ ተየበና ልጁን እያየ ለመልዕክቱ መልስ ጠበቀ

--እኔም ግራ ገብቶኛል:: ፎቶው የወንድ ነው:: መታወቂያው ላይ ያለው ስም የሴት ነው:: ወረዳው ቀራንዮ የተባለ የአዲስአባ ክፍል ነው:: መታወቂያው የአዲስአበባ ነው:: ሌላ ዝርዝር መረጃ ትፈልግ እንደሆነ እልክልሃለሁ:: ሃናን ሰላም በልልኝ:: ደሞ አላለቀስኩም::

አመሰግናለሁ አልማዝ::

ዴላኒ ስልኩን ዘግቶ ወደ ልጁ ቀረበ:: እግሮቹ መሃል የጎላ የወንድ እብጠት አለ:: እዚህ ሰዎች ፊት ከፍቶ ማየት አይችልም::

ሰዎች ባይኖሩም አይፈልግም:: ምናልባት መታወቂያው የሌላ ሰው ነው:: እዚህ አገር የእነዚህ ሰዎች የሴትና የወንድ ስም ተለይቶ ስለማይታወቅ ምናልባት መታወቂያው ጠፍቶበት የሌላ ሰው መጠቀሙ ነው:: ቢያደርግ ግድ የለውም:: አድርጎ ወንጀል ቢሰራም ግድ የለውም::

ከላይ ከዋናው ጎዳና ፖሊሶችና አምቡላንስ ሲመጡ ያያል:: ቶመና ማን እየመጣ እንደሆነ ለመገመት ሞከረ:: ከፖሊሶቹ መምጣት ይልቅ ከሩቅ አይቶ በተናጠል ሰዎቹ እነማን እንደሆኑ መገመት ይወዳል:: አጠገቡ ባይደርሱ ደርሰውም አልፈውት ቢሄዱ ግድ የለውም:: ለሙታን እንደሚሽቆጠቆጡ በቁም ላለ ሰው አይሽቆጠቆጡም:: ሬሳ ሲበሰብስ የሚያመጣውን በሽታ ፈርተው እንጂ ሰብአዊነት አይደለም::

የአቋቋሙን አቅጣጫ ለውጦ ዞር ሲል 'በቀለች' ፊት ላይ የጎደለ ነገር አየ:: የጎደለ ሳይሆን ፊቱ ነፍስ የዘራ መሰለ:: እንዴት ሬሳ ነፍስ ይዘራል? ለሰኮንዶች የሬሳውን ፊት በዐይኖቹ አገላብጦ አጠናና ምን እንደሆነ አገኘው:: ልጁ አንድ የጉንጭ ሰርባጻ ብቻ አለው:: ደላኒ ሁለት ሰርባጻ አይቷል፣ ሁለት ተኩልም አይቷል (አንዱ ደመቅ ያለ አንዱ ደብዘዝ ያለ):: ይሄንን ልዩ ነገር ከመጀመሪያው ልብ ያላለበት ምክንያት ቸልተኛ በመሆኑ እንደሆነ አልጠፋውም:: ወደ 'በቀለች' ቀረበና ሰርጓጻው ባለበት የፊቱ ጎን በኩል ቁጢጥ አለ:: የልጁን ፊት አተኩሮ ሲያየው ቆየና እጁን ሰዶ ሰርባጻውን በአመልካች ጣቱ ነካው:: የሰራው ትክክል ስላልሆነ ታዛቢ በመፍራት ዞር ብሎ ወደ ኋላው አየ:: ማንም የለም:: ፊቱን መልሶ ፈገግ እንዳለ ያኔውኑ ፈገግታው ወደ መደነቅ ተለወጠ:: ሰርጓጻው ነፋስ እንደ አነሳው ቅጠል ከልጁ ጉንጭ ላይ ተላቀቀ:: ስስ የአየር አሏሪት የመሰለች ትሙክ ከልጁ ፊት ላይ እንደ እፉዬ ገላ እየተንሳፈፈች ተነሳች:: ዴላኒ ዐይኖቹ ፈጠው ቆመና አንድ እርምጃ ያህል ወደ ኋላ ሸሸት ብሎ ቆመ:: ይሄ የሚንሳፈፍ ዐይነባር ጥላ ነገር ከመሬት አንድ ሜትር እንኳን ከፍ ሳይል ጠርዝ ጠርዙ እየተፈረፈረ በኖ ጠፋ:: ደላኒ አፉን ይዞ ዐይኖቹን እያቁለጨለጨ ይሄን ነገር በትክክል አይቶ ይሁን አይሁን ለማረጋገጥ

ወደ ልጁ አየ። ልጁ ፊት ላይ ምንም ሰርጓዳ አልነበረም። ከድንጋጤው ሳይሸር ዞር ብሎ ወደ መንገዱ አየ። ፖሊሶች አጠገቡ መንገድ ደርዝ መጥተው ቆሙ። የላንድሮቨራቸው ሞተር ገና አልጠፋም። ዐይኖቹን ከስራ ባልደረቦቹ አሸሽቶ መሬት መሬት እያየ ነፍስና ስጋውን ካጋጠመው ተአምር ጋር አላመደ። ለተለመደው ቲያትር ራሱን አዘጋጀ።

የሰበሰበውን አጠቃላይ መረጃ በአእምሮው አወጣና አወረደ። በፅሑፍ የተሟላ (ከልጁ የጉንጭ ትሙክ በተቀር) ሪፖርት ከማቅረቡ በፊት ለዋናው ዲቴክቲቭ አጠቃላይ መነሻ ሃሳብ ሊሰጠው ተዘጋጀ።

ሁለት ፖሊሶች ተራ በተራ 'ሃይ ሰርጀንት ዴላኒ!' እያሉ ከሁዋላቸው ስትሬቸር የያዙ ሁለት ረዳቶች አስከትለው መጡ። ፓራሜዲኮች ለምን ዩኒፎርማቸው እንዲህ 'ይቀይታል?' እናቱ የሚያምር አፏን ለመጨረሻ ከመዝጋቷ በፊት የተናገረችው ትዝ ይለዋል፡ እናት ታውቃለች የልጅዋን ጣጣ፡ 'ልጄ ኑሮህ ሰላም ይሁን።'

ወደ አለቃው ፓትሮል መኪና ሄዶ ሰላምታ ሰጥቶት ከጀርባ ተቀመጠ። ያጋጠመውን በአጭሩ ነገረው።

Φ

የወንድ ልጅ በብዙ ነገር ውስጥ ያልፋልና እና ቆዳው ብርቱ መሆን አለበት ሲባል ይሰማል። ግን ወሰን የለውም? 'ብዙ' የተባለው ቁጥር፣ የብርታቱስ ክብደት መጠን የለውም? ሺፍቱን ጨርሶ የመስሪያቤቱ ላንድሮቨር ቤቱ በር ጋ ሲጥለው እዛው መንገድ ዳር ጠርዝ ይዘው እያንሾካሾኩ የሚጠብቁት ሶስት ሴቶች ነበሩ። ሴቶች ከቤታቸው ወጥተው እሱን ሲጠብቁ አላጋጠመውም። ጎን ለጎን ቆመው በአምስት ዐይኖቻቸው አተኩረው ወይም እየተከተሉ ያዩታል። (አንደኛዋ አንድ ዐይናማ ነበረች) ከፍ ባደረገው ቁጥር በቦርጩ እየተገፋ የሚወርድ ሱሪውን ወደ ላይ እየሳበ አንገቱን ሰብሮ በዝምታ ሊያልፋቸው ሲል አንዷ፡

–ሳርጀንት ዴላኒ! አለች

ቀና ብሎ አያት።

---

--ወንድ እኮ ብዙ ነገር ያሳልፋል አለች

በሃሳቡ የመጣው ቀትር ላይ ዛፍ ስር ሞቶ ያገኘው ወጣት ነው:: ግራ ገብቶት የዛሬ ተራ ጉዳይ ደሞ በምኔው ለሬድዮ ወሬነት ደረሰ? እያለ ሲያስብ

--ሚስትህ ሃናን አሁን ሻንጣዋን ይዛ ሄደች አለች አንዷ በፍጥነት፤ በሌሎቹ ሴቶች ላለመቀደም የምትጥር ይመስላል:: የእሱን ስሜት ለማወቅ ሶስቱም ሴቶች አተኩረው ሲያዩት፣ ድንገተኛነቱ ለአፍታ ቢያስደነግጠውም ወደየት እንደሄደች፣ ለምን የሻንጣዋ ነገር ከመሄዷ ጋር አብሮ እንደተነሳ አልጠፋውም:: ጭንቅላቱን በሃዘን ይሁን በእሺታ በሚያምታታ መንገድ ነቀነቀና ትከሻውን አንዴ ብቻ ከፍ ዝቅ አደረገ:: የበለጠ ግልፅ ለማድረግ፡

--ቾሚ ሄደች ጥላህ አለች! የመጀመሪያዋ ከት እያለች

እጁን በንቀት አራግቦ መንገዱን ቀጠለ::

--ወንድ አይደለህም እንዴ?!! ምነው?!! አለች ዝም ብላ የቆየችው

--እናንተን ለመሰለ ቂጣም አልጨነቅም!!! አለ ፊቱን ሳያዞር

ሊያስደነግጡት የወጡት ሴቶች ተያይዘው ሳቁ:: ቤት እንደገባ ያጋጠመው ሚስቱ ሃናን የወሰደችው ሻንጣዋን ብቻ ሳይሆን ቤቱ ያስቀመጠውን ገንዘብና የዲቪዲ ላይብረሪውንም ነው:: ቢሆንም ግድ አልሰጠውም:: እየዞረ ሌላ የጎደለ ነገር እንዳለ አየ:: ቤቱ ቆሽሿል:: ሁሌ እንደ ቆሸሸ ነው:: የፒተር ስቴዩቬሳንት፣ የአስፐንና የቤንሰን ኤንድ ሄጂስ የሲጋራ ፓኮዎችና የትምባሆ መጠቅለያ ሪዝላ ወረቀቶች በየቦታው ወድቀዋል:: ሶፋው ላይ የድሪም ትንባሆ ቅጠል ተበታትኖ ይታያል:: ዩኒፎርሙን ለውጦ ቤቱን በከፊል አፀዳ:: ሳይመሽ ከቤቱ ወጥቶ የቤቱን ቁልፍ የሚለውጥለት ሰው ይዞ መጣ:: ሰውዬው የበር ቁልፍ፣ ጓጉንቸር ማስገቢያ ዘለበትና ቀዳዳ ሲሰራለት እሱ የቤቱን ቆሻሻ አፀዳ:: ሰውዬው ጨርሶ ሊሄድ ሲል እንደማያውቀው ሰው አየው::

--ምነው? አለ ዴላኒ

--ፊትህ ተለወጠብኝ:: ያው ሰውዬ ነህ ግን ተለውጠሃል እንጃ ጨለማው ይሆናል አለና እቃውን ሰብስቦ ወጣ::

---

ዴላኒ በሰውዬው የተሰራውን በር ፈትሾና ትክክል መሆኑን አረጋግጦ ሁሉንም በሮችና መስኮቶች ዘግቶ ወደ ማድቤት ገባ።

በማያውቀው ምክንያት ጉልበትና አዲስነት ተሰማው። በሁለት ዕንቁላሎች አመሌት ሰራና ቁራሽ ዳቦ ይዞ ሳሎን ካውች ላይ ተቀመጠ። በልቶ እንደጨረሰ እጁን በጨርቅ ጠርጎ እዛው ጋደም አለ። እንቅልፍ እንደጣለው ያወቀው ሌሊት ስድስት ሰአት ላይ ሲባንን ነው። ቶሎ ልብሱን አወላልቆ አልጋው ውስጥ ገባ። በትንሹ የሚስቱ የሃናን ሽቶ ጠረን ይሸተዋል። እንዳይሸተው ወደ ቤቱ ጣሪያ እያየ ተኛ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ለመተጣጠብ በውስጥ ሱሪና በካኔቴራ ባኞ ቤት መስታወት ፊት ቆሟል። አፉን ማታ ስላልታጠበው ደስ አላለውም። የቧንቧውን ውሃ ከፍቶ በእፍኙ ዘገናና በአፉ አስገብቶ ተጉመጥመጠ። የሚፈሰው ውሃ ትንሽ እስኪሞቅለት ሊላጭ ያቀደውን ያቀመቀመ ፊቱን ሲዳብስ የመስታወት ነፀብራቅ ውስጥ የሚያየው ፊተ ስፊው ዴላኒ ግራ ጉንጬ ላይ ጥልቅ ሰርጓዳ አውጥቶ አየ። እርግጠኛ ለመሆን ፊቱን ቶሎ ሳሙና ቀብቶ የተለወጠ የመሰለውን ጉንጬ ላይ ያለውን ደቃቃ በትክክል ምንም የማይደብቅ ፀጉር ላጨው። ሰርባዳው እውነተኛ ነው። ሰርባዳውን በጥንቃቄ በጣቱ ዳበሰው። አላመመውም። ቤተክርስቲያን ከሄደ ብዙ ጊዜ ቢሆንም በተአምር ማመኑን አልተወም። ቶሎ በሃሳቡ የመጣው ትናንት ያየው ሟች ነው። በሳሙና እንደተሸፈነና ሰርጓዳው ያለበት ቦታ ብቻ ተነጥሎ እንደተላጨ ፊቱን በጥሞናና በመገረም ሲያይ ቆየ። ቢቀናው ባይቀናው ግድ የማይሰጠው ፍጡር ስለሆነ ተረጋግቶ ፂሙን ተላጭቶ ከጨረሰ በኋላ ነፀብራቁን አተኩሮ እያየ ፈገግ አለ። እንዲህ ሲያደርግ የጉንጬ ሰርባዳ የበለጠ ጎላና ገፁ ላይ ያልጠበቀው አይነት ማራኪ ፈገግታ ብቅ አለ። ዩኒፎርሙን ለባብሶ ሲወጣ የሰፈሩ መንገድ ገና ከእንቅልፉ አልተነሳም። ገፁ ብቻ አይደለም የተለወጠው፣ ከአካሄዱም ከዕድሜውም አስር ቁጥሮች የቀነሰ ወጣት መስሎ ነው። ስደተኞች ወንጀል በሽታና ባዕድ ፀባይ እንደሚያመጡ

| ------------

ብዙ ሰዎች ያምናሉ፣ ጉንጭ ማሳመሪያ እንደሚያመጡ ምናልባት የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው:: ከተመቸው ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን እየተከታተለ ከሬሳቸው ውበት ይወስዳል:: ሁለቱንም ክንዶቹን በመደሰት ወደ ላይ አነሳ:: እንዲህ ሲያደርግ ሰው ያየው መስሎት እጁን አውርዶ ተገላመጠ::

## ዝምታ

አባቷ ኮላሴ ከወራት በፊት ለስራ ጉዳይ ወደ ሰበታ አቅጣጫ ሄዶ አልተመለሰም::[23] እንደተባለው ሲጠፋ (ወይም በእሷ ጥርጣሬ

---

23 **ከሙላድ ወይስ ወደ ሙላድ?**

ኮላሴ በሌሊት ገና ጎሕ ሳይቀድ ከአልጋው ተነስቶ *የምሄድበት ኣለ* ብሎ መግደላዊትን ሰላም ነሳት:: የሚሄድበት ይኑር እሺ የሚያስቸኩለው ምን እንደሆነ አልተረዳችም:: በመጀመሪያ ለምን ወደ ሰበታ አቅጣጫ መሄድ ግዴታው እንደሆነ አልገባትም:: እሱም ስላልገባው ጥያቄዋን መመለስ አይችልም:: ለጥርሷ ብሬስ ሊያሰሩላት ጌርሳሞትን ይዘው ናዝሬት ሄደው ከተመለሱ ገና ወር አልሞላም:: ዝም ብሎ የመንከውከው ፀባይ ይመስላል:: መግደላዊት ደሞ ኮላሴን ተከራክራ ጥሩም ሆነ ክፉ ወደሚሄደበት እንዲሄድ ወይም እንዳይሄድ የማድረግ አቅም የላትም:: ኮላሴ ከተናገረ ተናገረ ነው:: ያላትን ካልሰማች ያብዷል:: ያብዷል ማለት ያገኘውን እቃ ይወረውራል፣ አልጋ ይሰብራል፣ ጓዳ ሄዶ ፍሪጁን ጎትቶ ይገለብጣል ማለት ነው:: ጠረጴዛ ወደ ላይ አንስቶ ይጥላል ማለት ነው:: ይሄ ሁሉ ካላመቸው መግደላዊትን በጥፊ ያጮላታል ማለት ነው:: መግደላዊት ለማንም አትናገረውም እንጂ እሱ ያልቀጣው የገላዋ ክፍል የለም:: ግራ የከንፈሮቿ መገናኛ ላይ ያለው ጠባሳ የኮላሴ ቃሪያ ጥፊ የተወው ምልክት ነው (ቆዳዋ ላይ ያለው ሌላ ከንፈር የመሰለውና የሚያክለው ጠባሳ የነሐስ ቀለበቱ ያተመው ነው)::

ቁርሱን እንኩዋን ሳይበላ መኪና ማሞቅ ጀመረ:: ለቁጣ ፍርፍሩ የሚሞቀው ቅቤ መኪናው ጋቢና ውስጥ ሆኖ ይሸተዋል:: መብላት አላሰኘውም:: 'ደረሰኮ' ብትለውም ትዕግስት አልነበረውም:: ክረምቱ ደሞ በስሜታዊነት ተነስተው ለሚያደርጉት ጉዞ የሚመች አይደለም: ነዝናዛ፣ የጨቀየ፣ አሁንም ተስፋውም ድብርት የለበሰ ነው:: ታቦት ማደሪያ በስብሳለች:: አቃቂን አልፎ አየር ጤና እስኪደርስ ያለው ትራፊክ ራስ ምታትና የቂጥ ኪንታሮት ያመጣል:: የሆዱ ነገር ስለማያስችለው ብቻ ያፈረፈረችለትን በቁሙ በልቶ ገና ከጉሮሮው ሳይወርድ በመቅለብለብ መኪና ውስጥ ገብቶ እንደሰከረ ሁሉ እየነዳ ከቤቱና ከሰፈር ወጣ:: መግደላዊት ስትሸኘው ዐይኖቿ ዕንባ አቅርረው ጭንቅላቷን በሃዘን እየነቀነቀች ነበር::

---

አየር ጤና ሲደርስ ልቡ መምታት ጀመረ:: ለመግደላዊትም ለሚስቱም ያልነገራቸው፣ ግራ በሚያጋባ አለመዘጋጀት ከቤቱ የወጣበት ምክንያት ምን እንደሆነ ሊሰይመው ያልቻለ ድምፅ ሳያቋርጥ ስለጠራው ነው:: የወንድ ይሁን የሴት ግልፅ አይደለም:: ገና አልጋው ላይ እንዳለ ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ ነፋሻማ የሆነ የሴት ይሁን የወንድ ያለየ ድምፅ በጆሮው *ኮሳሴ ኮሳሴ ወደ ሰፈርህ ና* ይለዋል:: ጎሕ እስኪቀድ ድረስ ይሄ ድምፅ ጆሮው ላይ እንደተጣበቀ ሁሉ እየተነፈሰበት (እንደዛ ይመስላል) አላስተኛውም:: ከአልጋው ተነስቶ ልብሱን ሲለብስም አለቀቀውም:: ልብሱን ለብሶ ፊቱን ሲታጠብም አለቀቀውም:: ፊቱን ታጥቦ ልብሱን ለብሶ ሲጨርስም አለቀቀውም:: በመገረም ጆሮውን ይዞ እንደ ቆመ መግደላዊት *መጥታ ምነው በሌሊት ተነሳህ?* ስትለው አልሰማትም:: *ምን ሆንክ የእኔ ጌታ?* ብላ እጆቹን ከጆሮዎቹ ልታላቅቀው ስትል ጮኸባት:: እንቅልፍ አጥቶ ማደሩን ለምን ለመግደላዊት እንዳልነገራት ራሱን ቢጠይቅ መልስ አላገኘም::

ድምፁ ብቻ አልነበረም:: ከዕንቅልፉ የባነነው ልክ እንደ ለሐጭ አፉ ውስጥ የቅጠልና የአፈር ጠረን ታጭቆ ነው:: ከመሬት ላይ ተነጭቶ ሳያጥብና ሳያራግፍ አፍታ ሳይሰጥ እንደጎረሰው ለምለም:: በደንብ የሚያውቀው የመሰለ ጠረን እያፈነው ነበር:: ***የገደሉን ሕልም*** ሲያልም ይሸተው የነበረ አይነት ነው:: ጠረኑ የተለየ በመሆኑ ስም ሊሰጠው ሞከረል:: በትክክል ስም ያስፈልገዋል:: አፈር፣ እርጥብ ቅጠል፣ ውሃ፣ ኩበት፣ ሽንት እነዚህ ቢደባለቁ አይነት:: አንዳንዴ ይሄንን የጠረኖች ውኹንብር ጥሶ የተፈተፈተ ጥሬ እንጉዳይ ይሸተዋል:: ሕልሙ ሲያልቅ በልጅነቱ ይበላው የነበረው የኮሽሽላ ስር ጣዕም በአፉ ይሞላል:: ኮሽሽላ ይወድ ነበር:: ድሮ የታቦት ማደሪያ ሜዳዎች በኮሽሽላ ሙሉ ነበሩ:: ስኳር ስኳር የሚል ሃምራዊ አባባቸውን ሲያላምጥ ያስታውሳል:: ግራ የገባው ከዚህ አሁን ከሚሰማው የደመነፍስ ግፊት ጋር ይሄ ሕልም እንዴት እንደሚያያዝ ነው:: እንደገናም እነዚህ ተደጋጋሚ ቅዥቶቹን የሚያውቃቸውና የእውን የኖራቸው ይመስለዋል፣ ግን ደሞ የትና መቼ እንደሆነ ትዝ አይለውም::

በዚህ ሰአት ከመግደላዊት ጋር አልጋ ውስጥ ነበር:: የላቧ ጻጥና የክንዷ ምቾት ናፈቀው:: የመኪናውን ሬድዮ ጎረጎረ: ምንም የለም:: *እንዴት የለም?* ወለቴ ሱቅ ሲደርስ ሰማይ በብርሃን ቀላ:: እንደገና ያልገባው በዚህ በኩል እንዴት እንደመጣ ነው:: ሁሉ ነገር ሕልም ይመስለዋል:: ግራና ቀኝ የሚያልፋቸውን መኪኖች፣ ከብቶች፣ ሰዎችና ዛፎች በሲኒማ የሚያያቸው አይነት ነው:: መንገድ ዳር አንድ ሆቴል ገብቶ ራሱን ሊያረጋጋ ጠርሙስ ውሃ አዞ በረንዳ ላይ ተቀመጠ:: አንድ ሊትር ቢጨልጥ ከመረበሹ የሚገላገል መሰለው:: ግቢው ውስጥ

አጥር ተጠግቶ ከተሰራ የጎል እንጨት የመሰለ መስቀያ ላይ አራት ወንዴ በጎች ታርደውና ቆዳቸው በከፊል ተገፎ ተዘቅዝቀው ተሰቅለዋል። ሁለት ሰዎች ቢላ ይዘው ሙታኑ አጠገብ ይንጎራደዳሉ። ኮላሴ ከዚህ ትዕይንት ዐይኖቹን መልሶ የውሃ ላስቲኩን ሊያነሳ እጁን ሲሰድ በሆቴሉ ዋና በር ወጣት መልከመልካም የፊልም አክተሮችና አጃቢዎቻቸው እየተሳሳቁና እየተጯጯሁ ተከታትለው በእሱ አቅጣጫ መጡ። ሶስት የሚሆኑት ፊት ለፊቱ አለ ቦታ ገለል ብለው ሲቀመጡ የተቀሩት ቡና እንፈልጋለን እያሉ ወደ ሆቴሉ አልፈው ገቡ። አካባቢው ለአፍታ በጎረምሳ ጠረናቸውና በኮረዶች የሽቶ ጉም ታጠነ። ለኮላሴ ይሄ ቀላል ትርምስ አልተመቸውም። አጠገቡ ከተቀመጡት መጤዎች አንዱ ጮክ ብሎ 'በግ ታርዷል ትኩስ ቆለጥ መብላት የሚፈልግ ማነው?!' ብሎ ጮሆ ተናገረ። 'ሃናን ጥሯት ሃና ትወዳለች' አለ ከሆቴሉ ውስጥ ቀልቃላ የመሰለ የሴት ድምጽ። 'እንዳትሰማሽ፤ የምር እኔ እፈልጋለሁ። የሚፈልግ ይንገረኝ። ካልሽጡት ልጠይቃቸው' አለና እየሳቀ ተነሳ። ኮላሴ ፊቱንና ጆሮውን ከሰዎቹ መልሶ ውሃውን በፍጥነት ጠጥቶ ጨረሰ። ሆዱ ተነፍቶ እየተንቀራፈፈ ወደ መኪናው ሲሄድ የሆነ ሰው ጠራው። ለንግግር አፉን ማላቀቅ አልፈለገም። ወደ መኪናው ሲራመድ ብዙ ድምፅ የሚወጣቸው ሁለት *ነጫጭ ወረቀቶች* እግሩ ስር እየተርመሰመሱ አላስሮጥ ብለው እንቅፋት ሆኑበት። ቶሎ ጎንበስ ብሎ አንስቶ እየጨባበጣቸው ወደ መኪናው ገሰገሰ። አሁንም የሆነ ሰው ጠራው። ጥሪው ከሩቅ የመጣ ይመስለዋል። የመግደላዊት አይደለም። የጌርሳም አይደለም። ከሩቅ ከመጣ አጠገቡ ማንም አይኖርምና ለምን ዞር ይላል? የጨመደዳቸውን ወረቀቶች እንደያዘ በዝምታ መኪናው ውስጥ ገብቶ በሰማንያ መንዳቱን ቀጠለ። ምን ያህል እርቀት እንደተጓዘ ትዝ አይለውም። የጠዋት ፀሐይ ፊት ለፊቱ አለው መናገሻ ተራራ ላይ የብርሃኗን ክንፍ ጥላለች። ይህን ሲያይ በልቡ ሊሰይመው ያልቻለ ጥልቅ ደስታ ተሰማው። እንዴት ነው ሁልጊዜ የሚያየውና የሚያውቀው ተራራ ያን ብርጳማ ጠዋት የልዩ ደስታ ምንጭ ያደረገው? የተራራውን ጥቁር አረንጓዴ በትኩረት ሲያይ ሊሊት የሰማው ጥሪ ለአፍታ ጆሮው ላይ እንደ ነፋስ ነክቶት አለፈ። *ኮላሴ ወደ ሰፈርህ ና!* ድምፁ በእጁ የሚይዘው ያህል ቅርብ ነው። ለምን ይሄ ተራራ ላይ ያፈጣል? ለምን የሚወደው ይመስለዋል? ለምን ይወደዋል? ለምን ተንተርሶት እንደሚያድር የጥጥ ትራስ ዝም ብሎ የሚመቸው ይመስለዋል? ኮላሴ ቀስ ብሎ መኪናውን በቀስታ እየነዳ የመስኮቱን መስታወት አውርዶ ወዲህና ወዲያ አየ......ወደ ቀኝ ታጥፎ ከፊል ኮረኮንች፣ ከፊል ጭቃማ መንገድ ውስጥ ገባ። *ለምን እዚህ ገባሁ?* ይላል። መንዳቱን አላቆመም። ሌላ ጊዜ ቢሆን ይህቺን አሮጌ መኪና በዚህ አይነት መንገድ ላይ

አያመጣትም:: ማቆም ግን አልቻለም:: የኮረኮንቹ መንገድ ቢያልቅም ኮላሴ በጭቃና በሳር ላይ መንዳቱን ቀጠለ:: ባልገባው ምክንያት መጮህ ጀመረ:: የሚያወጣው ድምፅ ሀ ሀ ሀ ሆ ሆ ሀ ሆ ሆ ብቻ ነው:: ለምን እጮሃለሁ? ይላል:: መጮሁን ግን አላቆመም:: ለሩብ ሰአት ያህል እንደነዳ መተንፈስ አልቻለም:: ሁለመናው በላብ ተዘፈቀ:: ከውስጡ የሚወጣው ድምፅ ከራሱ ትእዛዝ ውጭ እየጎላ ሆሄ በሆሄ ላይ እየተደራረበ ይሰማዋል:: ኮላ ከኮ ኮላሰ ኮ ላኮሴ ሴሴሴኮላሴላላ:: መኪናውን በድንገት አቁሞ፣ ጆሮዎቹን በሁለት እጆቹ ይዞ ዐይኖቹን ጨፍኖ ጎንበስ ብሎ የጥሪውን ኳኳታ በጭንቀት ሲያዳምጥ ቆየ:: ቀስ በቀስ ድምፁ እየሰነሰነ ሲሄድለት ዐይኖቹን ገልጦ ቀና አለ:: የመኪናውን ሞተር ሳያጠፋ በር ከፍቶ ወጣ:: ዙሪያው ጭር ያለ አልፎ አልፎ ለምለም ቁጥቋጦ የበቀለበት ሜዳማ ቦታ ነው:: ከፊት ለፊቱ ሶስት ገላዳ ባቡን ዝንጀሮዎች መስክ ያቋርጣሉ:: ከመሃል አንድ ሙጭልጭላ ሮጣ ሄዳ እናቷ ሆድ ስር ገባችና ባቡኖቹ ሁለት መሰሉ:: በዙሪያው የአእዋፍ ጫጫታ ይሰማዋል:: ቀጥ ብሎ ቆሞ የሆነ ነገር የሚያዳምጥ ወይም የሆነ ነገር የሚያሸት መሰለ:: በፍጥነት ዞር ብሎ መኪናውን አየ:: የት ነው ያለሁት? ምን መሆኔ ነው? ለምን መኪናውን ያለ ጠባቂ ትቼው መጣሁ? ራቅ ብሎ ወደሚያየው ደን መሮጥ ጀመረ:: ደኑን እንደዘለቀ ከሩጫው ተግ ብሎ ዙሪያ ገባውን አየ:: ከፊት ለፊቱ በትላልቅና በትናንሽ ድንጋዮች የተሞላ ኮንኮለት ሜዳ አለ:: ከመሃሉ የመሬንዝ ቁጥቋጦዎች በቅለዋል:: የሚነፍሰው ነፋስ ቀዝቃዛ ጥራት አጥንቱ ድረስ ይሰማዋል:: ተራራው እንደ አንድ ቁስ ይሸተዋል:: እየተሰባበረም ይሸተዋል:: እወዲያ ያለችው ጅረት የደፈረሰ ውሃዋ ይሸተዋል:: የወንዙ አዣራ ይሸተዋል:: እርጥበቱም ይሸተዋል:: እመሬቱ ውስጥ እንደተኛ ሁሉ ጥቁሩ አፈር ይሸተዋል:: አጎንብሶ የሚችለውን ያህል ጭቃ በሁለቱም እጆቹ ዘግኖ አድቦልቡሎ ኳሱን በትኩረት ላሰው:: ፊቱ በጭቃ እንደተለወሰ ዞር ብሎ አየ:: እንደ ፈዘዘ ሁሉ አለበት ቆመ:: የት እንደሄድኩ ሚስቴ ልጆ መጣሁ ሳልላቸው:: ያለሁት የት? መሆኔ ምን ነው? ያስባሉ ጌርሳ መግደላዊት......ባዶ ቦታ ያለጠባቂ መኪናው......ከተራራውና ከዙሪያው መስክ ሺህ አይነት ማራኪ ጠረኖች በሁለመናው ገቡ:: የሚያውቀው ጠረን ነው:: የት? ጠባብ ሜዳና ትንሽ ጅረት ተከትሎ የደን መቀነት አየ:: ደኑ እንደሚንጠባጠብ እንደሚፈስ አረንጓዴ ቀለም ነው:: አንገቱን ሰበር አድርጎ አዳመጠ:: የኤባዎች ሳቅ ከተራራው ጫፍ ይሰማዋል:: የወፍ ላባ ከዛፍ ቅርንጫፍ ወደ ዛፍ ቅርንጫፍ እየነጠረ ሲወድቅ ይሰማዋል:: ሚስቴ ልጆ ሳልነግራቸው የት? ምነው? ጌርሳ መግደላዊት መኪናው ያለጠባቂ......ቀበሮ የሚያሳድዳት ጥንቸል ከሶስት ኪሎ ሜትር እርቀት

---

የምትለቀው እዬዬና ማለክለክዋ ይሰማዋል:: የማሽንብል እንኩርፍት እንደ ክራር ድዝ ዳዝ ይሰማዋል:: የሺህ ሰዎች ሹክሹክታ ከወለቴ ሱቅና ከሰበታ ይሰማዋል፣ ከመሬት ስር በትሎች ሚኒቅ ሚኒቅ አፈሩ ሲፈርስ ይሰማዋል፣ ተራራውን ተከልለው የሚያልፉት የቁሪዬዎች ምጥ ይሰማዋል፣ በሚወርደው ወንዝ ላይ ዳክዬዎች ላባቸውን ሲቆፍሩ ይሰማዋል፣ እርምቡቅ መሬት ላይ እንደ ቡግር የፈሉ ኩይሳዎች ስር ክንፋቸውን የሚጎትቱ አሸኖች ሲንሿሹ ይሰማል፣ ግራሮች ላይ ያሉ ዕርግቦች ዕንቁላል ለመጣል ሲያምጡ ይሰማል:: ዕንቁላሎቹ ጎጆአቸው ላባ ላይ ሲያርፉ ይሰማዋል:: ከእጢዎቹ አፉ ውስጥ ምራቅ ሲፈስ ሙቀቱ ይሰማዋል:: የዘገር እባቦችን ከቀያቴ ወደ ጠቋር ልዋጤን ያያል: እርቀታቸው ወዲያ ወዲያ ነው:: በጉም ከተጋረደው ከመናገሻ ጀርባ ካለው መንደር የዶሮዎች ኩኩሉ ይሰማዋል:: በአፍንጫውም የተልባ ፍትፍት: ሃ! *ሚስት ልጅ የት? ምነው? ጌርሳ መግደላዊት መኪናው::* ሕዋሶቹ የሰበሰቡትን መረጃ አእምሮው እስኪያደራጅ ዐይኖቹን ከድኖ ቆየና ጭንቅላቱ ለሁለት የሚከፈል እስኪመስል አምባቀቀ:: አረፍ ብሎ ወደ ግራ አየ:: ቦረቦርና ከቾ መሬት ላይ ባቡኖች ይላፉሉ:: የሚበሉትን ከመሬትና ከቁጥቋጦ ላይ ይለቅማሉ:: የቆሙት ራሳቸውን ያካሉ:: በነፋስ ውስጥ ቡላ ፀጉራቸው እንደ ደረስ ጤፍ እርሻ ይገላለጣል:: የተጎለተች ተሬ ላይ የተኮፈሰ ገመሬ ዞር ብሎ አየውና ጮኸ:: እሱን ተከትሎ ያኔውኑ ጫጫታ በሜዳው ላይ ተንሰራፋ:: ሁሉም ባቡኖች ዞር ብለው አይተውት እየዘለሉ ጮሁ:: ኮላሴ ፍርሃት አልተሰማውም:: ጫጫታውን አምኖ ወደ ባቡኖቹ መሮጥ ጀመረ:: ሩጫው መሃል ልክ እንደ አደናቀፈው ሁሉ ወደ ፊት ወደቀና መሮጡን ሳያቆም ከአናቱ ቀና አለ:: *ሚስቴ ልጇ ምነው? ጌርሳ መግደላዊት::* ሜዳው በደመቀ የባቡን ሁካታ ተሞላ:: ከፊት ለፊቱ የዝንጀሮው ጅር ከእሱ እንደሚሸሽ ሁሉ እየተንጋጋ በጎምበሌ መሬት ላይ ወደ ታች መውረድ ጀመረ:: ከሩጫው ተግ ብሎ ልብሱን እየቀዳደደ አወለቀ:: ከሬሉ ጨርቅ ሜዳው ላይ በሚነፍሰው ነፋስ ከላዩ ላይ እንደ ጉም እየተገፈፈ ወደቀ:: መሬቱ ዘቅዛቃ ሆነ:: ለእፍታ እጁን፣ ክንዱንና የቀረ ገላውን አየ:: ፀጉራም ሆኗል:: ሊያየው የሚችለው ሁለመናው በፀጉር ተሸፍኗል:: ወዲያ ወዲህ ዘለለ:: አጎንብሶ መሬት ያ.ጠጠ:: አለበት ተሽከረከረ:: እንደተጠለፈ ሁሉ ወደቀና እንደ እምቦሳ ተገለባበጠ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ተነስቶ ዙሪያውን ገረመመና ከዝንጀሮዎች ኋላ ኋላ መሮጥ ጀመረ:: ፊት ለፊቱ ገደል ነው:: ገደሉ ደርዝ ሲደርስ ዞር ብሎ ወደ መጣበት አየ:: መኪናው ዙሪያ የቆሙ እረኞችን አየ:: አፉን በሰፊው ከፍቶ አዛጋና እንዳመመው ሁሉ አቃስቶ የጠራ የባቡን ድምፅ አወጣ:: ፊቱን መልሶ ወደ ገደሉ

---

መውረድ ጀመረ። በገደሉ ላይ ጥቂት እንደሄደ ማላጊ ሳርና ድንጋይ አንሸራቶት ግማሽ መንገድ ወደ ታች ተንከባሎ ዛፍ ድባብ ላይ አረፈ። እንዲህ ሲገለባበጥ በግራ ክንዱ ላይ አስሮት የነበረው የእጅ ሰአቱ ከአምባር ማሰሪያው ወልቆ እንደ ወረቀት እየተውለበለበ ወደ ታች ወደቀ። እሱ አንድ ደህና ቅርንጫፍ በእጁ ይዞ እየተንጨዋለለ ተረጋጋ። ወደ ታች አየ። ትንሽ ድንጋያማ ጅረት በተለሸለሸ ሄቤሎ መሃል ትፈሳለች። የዱር ዝዬዎች ያቋረ ውሃ ውስጥ ይላፋሉ። እሱ የተከተላቸው ጥቂት ዝንጀሮዎች ገደሉን ወርደው ጅረቷ ውስጥ እየተላፉና ጅረቷን እየተሻገሩ ነው። ፊት ለፊቱ ትልቅ አሻል የመሰለ ገደልና የኮሶ ዛፍ ደን አለ። ይሄ *የገደሉ ሕልም* ነው። የኮሶ ዛፍ በዛ ሕልሙ አይቷል። እዚህ ነበር። አሁን ትዝ ይለዋል። ምናልባትም ይሄን የመሰለ ቦታ። ከዛ ሁካታ ነው። ሁካታው እንግዳ በሆነ ፀጥታ ይዋጣል።

ከቆመበት ግራና ቀኙ ደን ነው። ፊት ለፊቱ ትልቅ ዛፍ አለ። እሱን እያየ እያለ አካሄዷ ቀልጠፍ ያለች ዝንጀሪት በተዘረጋው የዛፉ ቅርንጫፍ ላይ በእሱ አቅጣጫ መጣች። ይህቺንም ያውቃታል። አተኩራ አየችው። የትኩረቷ ጥቅሻ አባበለው። ያውቃታል። ስታየው ቆየችና ፊቷን አዞረች። የሆነ ነገር በአፏ አልጎጠጎጠች። እየተናገረች ነው፡ *ደህና ነህ የእኔ አንበሳ......መጣህልኝ የእኔ ኮርማ*፡ አፍረቷ እንደደረሰ የበርጨቅ ስጋ ሲንቀለቀል አየው። ሁለመናው ተቁነጠነጠ። ያኔውኑ በስተግራ በኩል ካለ አንድ ቅርንጫፍ ላይ፣ የሚያውቀው ከመሰለው ቦታ አንድ ገመሬ እየተንጎማለለ መጣና ዘሎ ሴቷ ያለችበት ቅርንጫፍ ላይ ተንሸራቶ አረፈ። ለአፍታ ተጠግቶ ሴቷን ታከካት። ገመሬውን ያውቀዋል። ሴቷ እዛው ያለችበት ቅርንጫፍ ላይ ፊቷን ወደ እሱ አድርጋ በሆዷ ተንበለበለች። ገመሬው ከሁዋላዋ ወጣና ለአፍታ ተነቃንቆ ጀርባዋን ዳበሳትና ፊቱን አዙሮ ወደ መጣበት ተመለሰ። ከተንበለበለችበት ሳትነሳ የተደረገችውን እንዳልወደደች ሁሉ በሀዘን ፊት አየችው። *የእኔ ጌታ ምን ላድርግልህ?* ከዛፍ ዛፍ እየዘለለ እንስቲቷ ወዳለችበት ሄደ። ገመሬው ሆር ብሎ አይቶት የሚበላ ነገር ተረጋግቶ መልቀሙን ቀጠለ። ሲያጉተመትም ይሰማዋል፡ *እረፍ.....አላርፍ ካልክ አቀምስሃለሁ*። ወደ እንስቲቷ እንዳይቀርብ እያስፈራራው እንደሆነ ያውቃል። ***በገደል ሕልሙም*** ይሄ ገመሬ ያስፈራራው ነበር። እንስቲቷ ከእሱ ብዙ ሳትርቅ ግራና ቀኝ እየዞረች ገላዋን አሳየችው። እሷ ጋ ለመድረስ የሚቀረው አንድ ቅርንጫፍ መዝለል ብቻ ነው። ወደ ቀኝ ሲያይ ገመሬው የለም። *የት ሄደ?* አንድ ጊዜ እመር ብሎ ዘለለና እንስቲቱ አጠገብ አረፈ። ሴቷ እንደ ኮሸሽላ ትሽታለች። ዐይን ለዐይን ተፋጠጡ፡ *ውይ ውይ የእኔ ጌታ ያ ጉደኛ ሳይመጣ* መርቅ ዐይኖቿ ውስጥ ግልማጦ ፊቱን አየ። በአፏ አፉን

---

ታከከችውና በፍሳቸው ተላዘው እንደጨረሱ ከጎኑ ተንበለበለች:: አጉተመተመ፣ የሚያጉተመትመው ለራሱ ጠርቶ ይሰማዋል: *እንደ አንቺ የሚያምር በዚህ ሰፈር የለም……*አምባቀቀች: *ሳይመጣ ሳይመጣ ሳይመጣ*: ከሁዋላዋ ሊወጣ ሲል ሰፊ መዳፍ ወደ ፊቱ ሲሰነዘር አየ:: የእንስቷን ዳሌ ሳይለቅ ቀልጠፍ ብሎ አጎነበሰ:: ገመሬው የሰደደው ጥፊ ጨርቃሙን ዝንጀሮ ስለሳተው በብስጭት ሊከመርበት እያጓራ ተጠጋው:: ጨርቃሙ ጋለል ብሎ በታኮ ጠለፈው:: *ስታድዮም::* ቃሉን በአፉ ሊጠራው አልቻለም:: ከንፈሮቹ እምቢ አሉት:: ቃሉ አእምሮው ውስጥ ይገላበጣል:: ገመሬው የቆመበትን ዛፍ ስቶ ሊወድቅ ሲል አንድ ቅርንጫፍ ይዞ ተንጠልጥሎ ቀረ:: ገመሬው ፊት ላይ ድንጋጤ፣ ፍርሃትና መገረም አለ:: በሾኬ ተጠልፎ አያውቅም:: ዐይኖቹ ይቁለጨለጫሉ:: ከሰኮንዶች በፊት እየተጎማለለ ጉራ ሲነፋ የነበረው ገመሬ አይመስልም:: እንስቷን ለራሱ ማድረግ አለበት:: ሊምረው አልፈለገም:: በንቀት እያየው እጁን ከነቅርንጫፉ ረገጠው:: ገመሬው ጨምድዶ የያዘውን ቅርንጫፍ ለቆ ወደ ወንዙ እየጮኸ ወረደና የድንጋይ ስሌዳ ላይ ተለሸለሸ:: ያረፈበት ቦታ ያኔውኑ በደም አበላ ተሸፈነ:: ደኑ በገላዳ ባቡን ጫጫታ ተሞላ:: የገመሬውን እሬሳ ለማየት ከተለያየ አቅጣጫ ዝንጀሮዎች ወደ ታች ወደ ጅረቱ መንጋጋት ጀመሩ:: ዝንጀሪት የወደቀውን ገመሬ አልተከተለችም:: ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ጠጋ ብላ በከፊል የተቀዳደደውን የአሸናፊውን ካናቴራ እየገለጠች የደረቱን ፀጉር ልትቀምል ትጥራለች:: አልተመቻትም:: የቀረ ጨርቁን ሁለቱም ተረዳድተው እያሽካኩ ከላዩ እየቀዳደዱ ጣሉት:: ዝንጀሪትን እንደ አቀፈ ለአፍታ ወደ መጣበት አቅጣጫ አየ:: በትላልቅ ዛፎች መሃል ሰዎች ያያል:: መኪናውን ያያል:: መኪናዋን የማያውቃት፣ አጠገቧ ያሉትም ልጆች አደገኛ መሰሉት:: ዝንጀሪት በኩራት ዞረችውና አጉተመተመች: *የተለየህ ባቡን ነህ:* ከሚሊዮን ዝንጀሮዎች ቢያንስ በአንዱ ውስጥ ሰው እንደሚኖር፣ ከሚሊዮን ሰዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ ዝንጀሮ እንደሚኖር የሚገባው እሱ ብቻ ነው:: ሴቲቱን በቀኝ እጁ ስቦ ጉያው ከተታት: አዳምና ሔዋንን መሰሉ:: ደረቱን ተደግፋ ቀና ብላ እያየችው አዛጋች:: ከተከፈተ አፏ የሳር፣ የሽንት፣ የኮሸሸላና የጦስኝ ማራኪ ጠረን ሸተተው:: ከንፈሮቹ ደርቀው ሊጠራው ያልቻለ እውስጡ የሚያስገመግም *'መግደላዊት'* መ!መ!መመመ!መመመመ! መ! ሁ!ሁሀ!ሆሆሆ! አናቱን ወደ ሰማይ ሰቅሎ: ደሞ 'ጊርሳሞት' ገ!ገገ!ገገገገ!ገገገገ!ገገ!ጋ!ጋጋ! ጋጋገ!!! ወደ ገደሉ ፊቱን አዞረ:: እውነት ይሁን ውሸት አይገባውም:: እዚህ ቦታ እንደሌለ ያውቃል:: ዐይኖቹን ጨፍኖ የመናገሻንና የሚታን ቀዝቃዛ አየር ማገና ሴቲቱን

የሆን ሰው ገድሎ ሚስጢር ቦታ ሲጥለው) እርሻ መሃል ያቆማት የቤታቸው መኪና ሞተሯ እንኳን አልጠፋም:: አለችበት ጭስዋን እያትጎለጎለች ነዳጅዋን ጨርሳ ሞተሯ ተቃጥሎ ነበር:: በጠፋ በሦስተኛው ቀን ከፌዴራል ፖሊስ ቢሮ ስልክ ተደውሎ ለእናቷ ለመግደላዊት ተነግሯት ጉንጮቿ በዕንባ እየታጠቡ ከአንድ ኮንስተብል ጋር መኪናዋ የቆመችበት ቦታ ሄዱ:: ፖሊሶችና የገጠር ኡሪዎች ባደረጉት አሰሳ ከሜዳና ከገደል የሰበሰቡአቸውን የኮሳሴን የተቀደደ ሸሚዙን፣ የካናቴራውን ብጥቅጣቂ፣ ወንዝ ዳር ወድቆ ያገኙትን የተሰባበረ ሰአቱን፣ ግልፅ ያልሆኑ ነገሮች የተጻፈባቸው *ሁለት ወረቀቶችና* ገንዘብ የሌለበት የኪስ ቦርሳውን አሳዩአቸው:: እንዲገርማቸው አቅደው ሳይሆን አይቀርም የተቀዳደደ የውስጥ ሱሪ የለበሰ ዝንጀሮ ሜታ አካባቢ እንደታየ ነገሯቸው:: ተራ ሰዎችና መርማሪዎች ኮሳሴ በዝንጀሮ ሳይበላ እንዳልቀረ ይጠረጥራሉ:: ዝንጀሮ ሰው ይበላል? ምን ይታወቃል?

የአባቷ መጥፋት ወይም መሞት ልጁን ጌርሳሞትን እንደፈራችው አልጎዳትም:: አሁን የሚያሳስባት በሽቦው ምክንያት ከንፈሮቿና ድዷ ቆስለው እንቅልፍ መነሳቷ ብቻ ነው:: ምርቅዙ መቁሰል ብቻ ሳይሆን ጥቂት ቦታም መምገል ጀምሯል:: በቀን ሶስቴ ለአንፌክሽኗ የምትወስደው 500 ግራም አንቲ ባዮቲክ 500 ግራም አምፒሲሊን አማሯታል:: መስታወት ፊት ለፊት ቆማ ገጽዋን ስታይ የምታየው ቀድሞ ያልነበረ በቦምብ የተመታ ባግዳድ የመሰለ አስቀያሚ አፏን ነው:: ከአንድ አመት በላይ አባቷና እናቷ ሲነዘንዟት ቆይተው 'ትንሽ ይረክሳል' ብለው አዳማ ከተማ ወስደው ጥርሷን በሽቦ ገርግመው መለሷት:: ከውበቷ በሴራ እንደነጠልዋት ቢገባትም ወላጆቿን በዚህ መጠርጠር ከበዳት:: አፏን መግጠም ተስኗት ሃያ አራት ሰአት በዛ በኩል ያለ እሷ ፈቃድ አየር እንደ አሻው ይወጣል ይገባል:: ፊቷ የሌላ ሰው መሰላት:: ብሬስ የተሰሩ ልጃገረዶች አይታለች ግን እንዲህ እንደ እሷ አልተጎዱም::

---

አንገቷ ላይ በፍቅር ነከሳት:: ወደ አንዱ የኮሶ ዛፍ ጫፍ ላይ ለመውጣት እየተላፉ ዝላያቸውን ጀመሩ::

ፌቨንን ለመጠየቅ ገላዋን ታጥባ ልብሷን ለውጣ ወደ ኮምቤ አበባ ሱቅ ሄደች። ከፌቨን ጋር ተሳስመው 'ምነው ብትደውዪ' 'ምነው ብትደውዪ' ተባብለው፣ እስኪ ልይልሽ አለቻትና አገጭዋን ይዛ ፊቷን ዞር ዞር እያደረገች የአፏን ብረታ ብረትና ቁስል ስትመረምር:

--ገና እቤት ስደርስ ነው የጠዘጠዘኝ። ምች መስሎኝ ነበር አለች ጌርሳሞት

--አሪፍ ይሆንልሻል አለቻት። እንዲህ ስትል ከማቆለጳጰሷ ስር የተወሸከ መገረም ዐይኖቿ ውስጥ ይነበባል። መገረሟ ፍርሃት ይመስላል። በቃላት ወስኖ ለመናገር የሚከብድ የግራ መጋባትም ስሜት ይመስላል።

--ያመኛል ታውቂያለሽ። በሰላም ከተኛሁ ስንት ጊዜዬ አለቻት

--ምንም አይደለም፣ በኋላ ያምርልሻል፣ የምር። ሲያጌጡ ይመላለጡማ አይቀርም። ለማንኛውም ለደስታሽና በሰለጠነ መንገድ በማማርሽ ፍንጥር አደርግልሻለሁ አለቻትና ሻይ አፍልታ ልታመጣ ጓዳዋ ገባች። ጌርሳሞት የፍንጥር ሻይ ለመጠጣት የታጠበ ሲኒዋን ይዛ የተለመደ ቦታዋ ተቀመጠች። በትካዜ ወደ ሱቁ ውጭ ታያለች። ሁልጊዜ የሚከባት የተለያዩ አበቦች ጠረን አሁንም አለ። አስፋፈሩ የተለየ ነው። በእሷና በዓለም መሃል ነው። ዓለም ፊት ለፊቷ እንደ ቪዲዮ ስዕል ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ ይተረተራል። እዚህ ስትገባ ይቅበጠበጥ የነበረው የነሐሴ ደመና ወደ ሚሄድበት ሄዷል። ክረምቱ እንደ ድሮው ነገረኛ እርጥብ ሳይሆን ያለቦታውና ያለጊዜው ሳይጠራ እንደመጣ ዐይነአፋር እንግዳ በጋ ነው።

--ጌርሳሞት ሰማሽ? አለች ፌቨን

--እ? አለች ጌርሳሞት

--ረሳሁት በማርያም ምንዋ ነኝ በእናትሽ። አንቺ በጋሼ ኮላሴ መጥፋት ተጨንቀሽ ብዙ ነገር አልሰማሽም አውቃለሁ። ተዘጋጂ

--ለምን?

--ባካፋ በጣም ታሞ ጥቁር አንበሳ ተኝቷል

እንደ ማንኛውም የሰፈር ሰው፣ እንዳልጎደለባት ሁሉ ተራ ድንጋጤን ደነገጠች። ዝም እንዳለች የባካፋ ሳቅ፣ የባካፋ የተላጨ ክብ

| -------------

ለስላሳ ጉንጭ፣ የባካፋ የጉጉት የመሰሉ ዓይኖች፣ የባካፋ ቁምነገረኛ ድምፅና የመሳሰሉት በዓይነሕሊናዋ ቸው ብለው አለፉ:: እንግዳ ድካም ደከማት:: የምትናገረው ቢኖራትም የላትም::

--አልሰማሁም እንዳትዪ አለች ፌቨን ኮስተር ብላ:: ፌቨን ጨንቋት አይደለም:: የጌርሳሞት የማጣት ጉዞ ምን ተፅእኖ እንዳሳደረባት ለማየት ይመስላል:: ፌቨን አበባ ነጋዴ ብቻ ሳትሆን 'ሙድ' ትቸረችራለች:: በጥንቃቄ የያዘችውን ተወዳጅነቱ የሚያጠራጥራትን ቀጫጫ ገላዋን የምትከላከልበት ሌሎችን በመተረብና በማስቀቅ የገነባችው ምላስና የመንፈስ ድርጅት አላት:: የቀውስ ዘመን ሲከሰት እሱም ወዳጅ መስሎ ይከሰታል:: ጌርሳሞት የፌቨን እቅድ ግልፅ ቢሆንላትም ወይም ባይሆንላትም የውስጥ ስሜቷን ላለማካፈል፣ አስተዛዘኗ ለማንም ሙዋች የተዘጋጀ እንዲመስል እየሞከረች ሁለመናዋን አንጠራረርታ:

--አልሰማሁም......ውይ ሲያሳዝን! ደረቷን ያዘች፣ ከዛ አፏን ያዘች፣ ከዛ ወደ ውስጥዋ አተኮረች:: በዐይነሕሊናዋ የመጣው የባካፋ እጅ ነው:: የምናቧ ባውዛ ይንተገተጋል::

--ምን ሆኖ?

--ኮምፕሊኬሽን ነው አሉ

--ሲያሳዝን:: ምንድነው እሱ ደሞ?

--እንጃ:: ኮምፕሊኬሽን ነው የሰማሁት በአንድ ጊዜ መአት ነገር ሲያምሽ

ይገዝግዝሽ::

--እውነት አልሰማሽም?

--ፌቨን ሙች:: አሁን ሰማሁ:: ቤት ማን ይነግረኛል?

--አንቺ ምነው ያን ሁሉ ሚክአፕ ሰጥቶሽ ትንሽ እንኳን ማዘን ማንን ገደለ? አንድ የዕንባ ጠብታ ምንሽን ይጎዳል? ሂሂሂ

አሁን ለቅሶዋን መዋጥ አለባት:: እውስጥዋ ይሰማታል ለባካፋ ማልቀስ:: ዐይኖቿን ፌቨን ወደማታይበት አዙራ:

--አልሞተ አለች ደፈር ብላ

ከኬንያ እንደመጣ ለአንድ ቀን ለአንድ ሰአት ያህል ተገናኝተው እንደነበረ አልነገረቻትም:: አትነግራትም:: ተገናኝተን ነበር

ዘጋኝ ልትላት ነው? ይጠላኛል ልትላት ነው? ልቧ አልቆርጥ ብሎ ደጋግማ እንደ ደወለችለት አልነገረቻትም:: አትነግራትም:: አይወጣትም:: ሲለማመጥሽ ነበር ነገር ተገልብጦ ትለማመጪያለሽ? ብትላትስ? ልምምጥ ባይሆንም፣ ብትላትስ? የዛ ሁሉ የሚካፕ ፕሮፓጋንዳ የት ገባ? ብትላትስ? ብትሰማም ባትሰማም የትም ባይደርስም፣ አሸናፊ መስሎ መሸሽ ማንን ይጎዳል? ደሞስ የማይዙትን ነገር ሊይዙ ቢሮጡ ማን ይጠቀማል? ቦርሳዋን ከፍታ የከርከዴ ለዛ ያለው አዲስ የማስቲካ ፓኮ አወጣች:: ደብረዘይት ነው አክስቷ የገዛችላት:: ለፌቨን ልትሰጣት አንድ ዘረጋችላት:: ፌቨን ተቀብላ፡

--ስትገባበዙ አልነበረም እንዴ? እኔ እኮ......ሌላ ጠብቄ ነበር ሂሂ ይገርማል

--ከማን ጋር? እ......ባካፋ......ምን ይገርማል? እና ምን ይጠበስ? በግብዣማ ቢሆን ሃሃ......መገባበዝ ምንድነው? ለመሆኑ ጠየቅሽው?

--እንዴ ምኔ ነው? ሊፍት የሰጠሽ፣ ስጦታ የሰጠሽ፣ 'ጌርሲ' የመሳሰለ ያለሽ አንቺን:: ምናልባትም እ?...... አለች ሳቅ ብላ፡

--አንቺ ጠይቂው የአንቺን አበባ ሊገዛ ከሸኖ ምናምን አደለ እንዴ የመጣው? ሂሂ

--እንዴ ጌርሲ እንደ አንቺ አልቀርበው!? ምነው?! ተዘጋጋችሁ እንዴ?!

ፌቨን መልስ አልጠበቀችም:: እንደተዘጋጉ ትጠረጥራለች:: ሁሉንም ለመዘንጋት ባይሆንም ከሱቋ ውጭ ሆና ሞባይሏን አመቻችታ ጌርሳሞትን ፎቶ ታነሳለች:: ጌርሳሞት በሃሳቧ ነጭ ክፍል ውስጥ ነጭ አንሶላ ስር በፋሻ ታስሮ፣ ግንባሩ በፕላስተር ተሸፍኖ፣ የከሳ፣ የጠቆረ፣ በጀርባው የተዘረረ ባካፋ ይታያታል:: እሱን ለመጠየቅ የምትሄድበት ምክንያት የለም:: በፍቅር አፍጦ የሚያየው አፏን አበላሽታለች:: ፌቨን የምታነሳው ፎቶ ለታሪክ ትዝብት ብቻ የሚቀመጥ ነው:: ለምንድነው ፌቨን ዝተት የሆነች ዕለት ብቻ ፎቶ የምታነሳት? ብትሆንም ባትሆንም ይመስላታል:: ማለት ዝተት::

--በማርያም አታንሺኝ ደብሮኛል

--ሁሉንም ፎቶሽን በአንድ ፋይል እሰበስብልሻለሁ አለቻት

--ለምን?

ፌቨን አልመለሰችም:: ወይ ሰምታለች ወይ አልሰማችም:: ፌቨን ኪነት የጠጣች ነጋዴ ናት:: ማስመሰሏ ጨዋታ አለው:: ጥቂት ብልጦች ጨዋታዋን ረግጠው ቁምነገሩን አምጪ ይሏታል:: እንዲህም ተፋጣ ውልፍ አይላትም::

ጌርሳሞት መልስ ስታጣ በመሰላቸት ወደ ባዶው መንገድ ፊቷን አዞረች:: ቆሻሻ አስፋልት: ስስ ጭቃ የለበሰ:: ዝናቡ አዲስ ነው ግን መሬት ከመንካቱ ሽበት አውጥቷል:: የወጣት መንገድ ነው የጀመረችው ግን በቅቷታል:: ለመነቃነቅ እንደፈራች ሁሉ መታየት የማይገባውን መንገድ እያየች ብዙ ቆየች:: ሻይው የተቀዳው ቅድም ነው:: መቀዝቀዙን ልብ አላለችም::

## 'እነዛ ሁለት ወረቀቶች'

የዋናው ቢሮ የምርመራ ቡድን ወደ ወሎቴ ሱቅ እንዲሄድ ፍንጭ ያገኘው በተለመደው መዋቅር ከሰበታ ፖሊስ ሳይሆን ከግለሰብ የስልክ ጥሪ ደርሶት ነው:: የዚህ ስልክ ጥሪ ባለቤት ሃና የተባለች የአንድ ፊልም ስራ ቡድን ሜክአፕ አርቲስት ናት:: ሃኒ (ወዳጆቿ እንዲህ ብለው ይጠሯታል) የፊልም ስራ ኮንትራቷን ጨርሳ ወደ ውበት ሳሎን ሱቋ ስትመለስ ለአመታት ደንበኛዋ የሆነች ሴትዮ ባሏ ጠፍቶባት እየተሰቃየች እንደሆነ የስራ ባልደረቦቿ ይነግሯታል:: እንዲህ አይነት አቤቱታ ያሰማችው ሴትዮ መግደላዊት ትባላለች:: መግደላዊት በየወሩ ሃና ድርጅት ስትመጣ ፀጉሯን ተሰርታ እስክትጨርስ ድረስ ባልዋ ከሌሎች ሴቶች ጋር ተቀምጦ ይጠብቃት ነበር:: ይሄ ባሏ ኮላሴ ይባላል:: እዛ ከሚሰሩት የሜካአፕ አርቲስቶቹ ሁሉ ኮላሴን የምትወደውና የምታከብረው ይህቺ ሃና የተባለች የውበት ሳሎኑ ባለቤት ብቻ ነበረች:: በእሷ ግምት ኮላሴ እንዲህ የሚያደርገው ስለሚቀና ሳይሆን ሚስቱን እጅግ ስለሚወዳት ነው:: እናም የእሱ አይነት ባል ቢያጋጥማት እግዚአብሄርን አመስግና አብራው ለዘለአለም እንደምትኖር ትናገራለች:: እንዲህ ስትል ፀጉር ቤቱ በጫጫታ፣ በእርግማን፣ በስድብና በሳቅ ይሞላል:: እሷን ቢያዝናናትም፣ በዚህ ግምቷና አፈራረዷ ከአንዳንድ ሰራተኞቿ ጋር አልፎ አልፎ መራራ ክርክር ውስጥ ገብታለች:: መግደላዊት ተራዋን እየጠበቀች ይሁን ወይ ፀጉሯን በመሰራት ላይ እያለች በቀልድ እንኳን ስለ ወንድና ሴት ፍቅር ወይም ስለወሲብ ቀጥተኛም ይሁን የአግቦ ወሬ ከተነሳ ኮላሴ ገፁ ተለዋውጦ በቁጣ: 'ፀጉር ለማሰራት ነው የመጣሁት እንጂ የዚህ አይነት የልጅ ወሬ ልሰማ አይደለም:: እህቶቼ አፋችሁን ይዛችሁ ቶሎ ጨርሱላትና ልሂድበት፣ ነገር አትፈልጉ' ይላል:: ለኮላሴ ይሄ አይነት ጨዋታ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ስሜት የሚያስደስት አስቂኝና አስደሳች ጨዋታ ሚስቱን ከእሱ የሚያርቅበት ይመስለዋል::

---

ኮላሴ ጠፋ በተባለ በሦስተኛው ቀን ከሰአት በሁዋላ አንድ የፖሊስ ኢንስፔክተር አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ ሆርስ ክለብ በሚገኘው ባቢ የሴቶች የውበት ሳሎን ተገኝቶ ኮላሴን ወለቴ ሱቅ እንዳየሽው የሚያረጋግጥ ምን አይነት ተጨባጭ ታሪክ ይኖርሻል ሲላት ሃና ከዚህ የሚቀጥለውን መልስ ሰጠች፤

'አንድ ጠዋት ለስራ ጉዳይ (ቀኑና ሰአቱን በሞባይል ሜሴጂ ልኬላችሁዋለሁ) ኮንትራት የተቀጠርኩበትን 'ቅልልቦሽ' የሚባለውን የአቶ ባካፋን የፊልም ስራ ለማጠናቀቅ ከሌሎች አስራ አምስት ሰዎች ጋር ወለቴ ሱቅ በጠዋት ሄጄ ነበር:: ቀኑ ነፋሻማና ብርዳም ነበር:: ብዙዎቻችን በአየሩ ፀባይ አልተደሰትንም:: አንዳንድ አክተሮች ቁርስ አልበላንም ብለው መንገድ ዳር የሆነ ሆቴል ስለገቡ (ስሙን ረሳሁት) እነሱን ከሌሎች ሁለት ጓደኞቼ ጋር ሆኜ እውጭ እጠብቃለሁ፤ ማለት በልተውና ጠጥተው እስኪመጡ:: ያን ጊዜ ከሆቴሉ ውስጥ በጣም መልኩ የተለዋወጠ ብቻ የሆነ ነገር የደረሰበት የመሰለ የመግደላዊትን ባል አየሁት፣ ማለት አቶ ኮላሴን:: ስሙ ምን ማለት ነው ግን? እና ምክትል የሲኒማ ዳይሬክተሩ አቶ ኤርምያስ በአንድ አረንጓዴ ክላሴር የተሸፈኑ ዶኪመንቶች ያገርልኝ ብሎ ሰጥቶኝ......ወረቀት መስብሰብ ይወዳል፤ እና እሱን መኪና ጣሪያ ላይ አድርጌ እዛም ላይ ፔርሙስ አስቀምጬ ከአንዲት ጓደኛዬ ጋር እየተጫወትኩ የቡድኑ አባላት ቁርሰው እስኪመጡ እጠብቃለሁ:: ከመሃል ትንሽ ሻይ መጠጣት አሰኘኝና (እኔ ሻይዬን በፔርሙስ ይገፍ እዞራለሁ) ፔርሙሱን ሳልጠነቀቅ ሳነሳው ተጭኖአቸው የነበሩት ወረቀቶች በነፋስ መበታተን ጀመሩ:: እንዲህ እየሆነ እያለ ኮላሴና ያልኩአችሁ ምክትል አዘጋጁ ማለት ኤርምያስ ልክ እንደተቃጠሩ ሁሉ ፊትና ኋላ ሆነው ተከታትለው ከሆቴሉ ሲወጡ አየሁ:: ቀልቤ ተገፈፈ:: ነፋስ ክላሴሩን ከፍቶ ያቦነናቸው ወረቀቶች ኮላሴ እንደጠራቸው የውሻ ቡችሎች እግር እግሩን ተከተሉት:: ሰላምታ ልለው ሃሳብ አልነበረኝም እና ግን ይሄ ችግር ሲደርስብኝ አቶ ኮላሴ እንዲረዳኝ 'አቶ ኮላሴ!' 'አቶ ኮላሴ!' እያልኩ ተጣራሁ:: አልሰማኝም:: ከመሃል ምክትል አዘጋጁ ደርሶልኝ ከፊሉን ወረቀት ሲለቃቅም አቶ ኮላሴ ሁለት ወረቀቶችን

---

ሲያነሳ በዐይኔ ቂጥ አየሁት:: አንስቶ ይሰጠኛል ብዬ ስጠብቅ ቅጠሎቹን በግራ እጁ ጨምድዶ ይዞ መኪናው ውስጥ ገባ:: ኤርሚ ግራ በመጋባት አየኝ:: *ይሄ ሰውዬ ምን ሆነ?* አልኩና ሞተሯ ወደተነሳው የኮላሴ መኪና መሮጥ ስጀምር፣ አዘጋጁ በተረጋጋ አንደበት 'ሃኒ አያስፈልግም፣ የሆነ ንድፍ ነገር ነው:: ንፁህ ኮፒ አለኝ አትቸገሪ!' ብሎ አዘዘኝ:: ቢሆንም ተበሳጭቼአለሁ:: የኮላሴን ስም በመጥራቴ ግን ኮላሴን በግል የማውቀው ስላስመሰለኝ ዶክመንቱ ጠቃሚ ቢሆን ኖሮ በዱለታ ወረቀቶቹን የሰረቅሁ ይመስልብኝ ነበር:: ያን ቀን ኤርምያስ የሚከአፕ ስራዬን ጨርሼ እስከሄድ ድረስ በጥንቃቄ ይከታተለኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል:: በአገራችን የፊልም ስራ አካባቢ የስክሪፕት መሰራረቅ ስላለ ቢጠራጠረኝ አልፈርድበትም::'

ከዚህ መልሷ ቀጥሎ ፊት ለፊቷ የተቀመጠው ኢንስፔክተር ('ወንድሙ' የሚባል) ስልኩን ከፍቶ ከሆነ ሰርጀንት ጋር የሚከተለውን አጭር የቃል ልውውጥ አደረገ:

'እነዛ ወረቀቶች አሉ?'

'አዎ......ወረቀቶቹ'

አንድ አምስት ደቂቃ ያህል ከወዲያ በኩል የሚነገረውን ነገር ካዳመጠ በኋላ ስልኩን ዘግቶ በትልቁ አፋሸከ (የፖሊሶች አፍ ሁሉ እንዲህ ሰፊ ነው?):: ሳል ሳለና ዐይኖቹን ዐይኖቿ ላይ ተክሎ:

'እንዳልሽው መኪናው ውስጥ ሁለት የተጨማደዱ ትንሽ ጭቃ የነካካቸው ወረቀቶች አግኝተናል:: ወረቀቶቹ ላይ ምን እንደተጻፈ ግን ትዝ ይልሻል? ለማመሳከር እንዲመቸን ነው:: አንቺ እውነትሽን እንደተናገርሽ ማረጋገጥ አለብን'

ሃና ትንሽ አሰበችና በተረጋጋ አንደበት አልፎ አልፎ ገጽዋ ላይ ፈገግታ እየተነበበ ይህን መለሰችለት:

'የተበተኑት ወረቀቶች ቁጥር አምስት ነበር:: ከነዚህ ሁለቱን ነው ኮላሴ ለቅሞ የወሰዳቸው:: ምን እንዳለባቸው በትክክል ማለቴ ሙሉ በሙሉ አላውቅም:: የሻይዬን (ሳውዲ ሰው ቤት ስሰራ የለመድኩት ነገር ሻይ በጣም መጠጣት ነው) ፔርሙዝ ሳስቀምጥ መጀመሪያ ላይ ያሉት ሁለት ወረቀቶች ትንሽ ተዛንቀው ስለተቀመጡ

ዶኪመንቱ የተሸፈነበትን የክላሴር ሽፋኑን ገልጬ እነሱን ሳስተካክል የመጀመሪያውን በትንሹ፣ ቀጥሎ ከስሩ ደሞ ካለው በከፊል የሚገቡኝንና የማይገቡኝን መስመሮች አንብቤአለሁ:: የመጀመሪያው ወረቀት ላይ የተጻፈው በዛን ቀን የምንሰራው ነገር ነው:: እንደውም በኋላ ኤርምያስ እንደነገረኝ የስራችን ድራፍት ወይም ረቂቅ ነበር:: ተይው ያለኝ ቀደም ሲል እንደነገርኩህ ንፁህ የምንሰራበት ኮፒ ስላለው ነው:: ማለት የመጨረሻው ትዕይንት ያለበት ነው:: የመጨረሻው ሦስተኛ ገቢር ነው:: ገቢሮቻችንን በቁጥር ሳይሆን የምንከፋፍለው በሆሄ ስያሜ ነው:: ሀ ለ ሐ ስንል ሦስተኛው እንዳያምታታ 'ገቢር ሐመሩ' እንላለን:: ስክሪፕት ጸሐፊያችን ልዘንጥ ይላል:: ትዕይንትን የምንከፋፍለው ግን በቁጥር ነው:: እሱ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ማስታወሻዎች በየመሃሉ ተጽፈዋል:: ሁለተኛው ወረቀት ጫፍ ላይ የእኔ ስልክ ቁጥር እንደነበረ ትዝ ይለኛል:: ይቅርታ ከአዘጋጁ ጋር በግል ደረጃ ምንም አይነት ግኑኝነት የለንም:: ማለት ትንሽ ጉራ አለበት እንጂ ደስ የሚል ልጅ ነው:: ወረቀቱ ሳይበታተን በፊት ያሳሰበኝ ያው ማለት በልቤ በፔርሙሱ ክብደት አረንጓዴው ክላሴር ላይ የተሰራው ክብ ሰርጓዳ ነበር:: ግን ኤርምያስ ወረቀቱን ከሰበሰበ በኋላ 'ለፋይሌ ዲምፕል ሰራሽለት' ብሎ ሊያስቀኝ ሞከረ:: ስራዬ ቢያበሳጨውም እኔን ከመነጭነጭ ይልቅ ሁኔታውን ቀልድ አደረገው:: አውቃለሁ በቀልደኛነቱ ጉራ ይነፋል:: ሂሂ:: ውሸቴን አይደለም:: አዲስአባ ውስጥ ቀያይ መኪናዎች አሉ፣ ከሁሉ የሚያምረው ቀይ መኪና የእኔ ብቻ ነው ይላል:: እንደውም መኪናዬ ቀይ ሊፕስቲክ የተቀባች ውብ ከንፈር ትመስላለች ብሎ ይጎርራል:: ግድ እንደሚስጠን ሁሉ:: ከፕሮጀክቱ ላለመባረር በሰበብ የውሸታቸውን ግድ የሚሰጣቸው አክተሮች መአት ናቸው:: ሲያሳዝኑ:: ማለት እንጀራ ነው:: ቆዮታ አይተን አናውቅም እንዴ? በደቃቃ ነገር ሊያስቀን እንደሚሞክረው ሁሉ፣ ደቃቃ ስህተት ፈልጎ በመታዘብና በመተቸት ብሩህ መሆኑን ጠዋትና ማታ ይነግረናል:: ያለፈው አመት አቶ ውድነህ የሰራውን ስህተት እስከ ሃያ አመት ውድነህን በመተቸት ሊጠቀምበት ይችላል:: ይቅርታ ከጉዳያችን ያልገጠመ ነገር አነሳሁ'

ሃና ለአፍታ ቆም አለችና አሰበች። ወረቀቱ ተበታትኖ ሲሰበሰብ የተጋለጠው የመጨረሻው ገፅ ላይ አንድ እንግዳ የሆነባት ፎቶ አይታለች። ይሄን ፎቶ (የምር ፎቶ ነው) ከሁለት ቀናት በፊት አንዳንድ ሰዎች እየተቀባበሉ እያዩት ሲስቁ ነበር። እዚህ ፎቶ ላይ ቀያይ ጸጉር ያላቸው ሁለት ሴትና ወንድ ጨጨ ዝንጀሮዎች (የእኛ አገር አይነቶች አይደሉም) አፋቸውን እስከመጨረሻው ከፍተው ሲሳሳሙ ይታያል። አሳሳማቸው *ፍሬንች ኪስ* የሚሉት አይነት ነው። ሃና አፏ አላርፍ ብሎ 'በእርግጥ እየተሳሳሙ ነው? ወይስ መሳሳም የመሰለ ግን ሌላ መልዕክት የሚያስተላልፍ የመገናኛ ምልክት ነው? ለምሳሌ *ከንፈሮቼን ተባይ በላኝ* ለማለት ቢሆንና እየተሳሳሙ ሳይሆን እከካቸውን እየተታከኩ እንደሆነስ' አለች። ጠዋትና ማታ መሞገስ የሚፈልገው አዘጋጅ፣ የመሞገስ ሱሱን ሃና የተጋፋችው ስለመሰለው በግልፅ ደሙ ፈላ። አዘጋጁ የዝንጀሮዎቹ መሳሳም እንደመገናኛ ምልክትነት ማለት እንደ ቴሌፎን፣ እንደ ቴሌግራምና እንደ ፖስታ አይነት ሆኖ ተለጥጦ እንዲተረጎምበት አልፈለገም። የአዘጋጁ አላማ የዝንጀሮዎቹ የአፍ እሩካቤ ፍቺው ሳይለጠጥ ወሲብ ላይ ፈዞ እንዲቀር፣ ቢቻል ማተኮሩ ገኖና ጠብቆ ምስሉ ፅላት እንዲሆን ነው። ዝንጀሮዎቹ ቢያደርጉትም ይሄ ሃይለኛ የመሳሳም ግኑኝነታቸው የተፈጥሮን የዝርያ ወሰን ተሻግሮ የሰብ ትኩረትን እንደሚቀሰቅስ ይገባዋል። ሆነ አልሆነ እሱ የፈለገው የመሳሳም ድርጊት በዝንጀሮዎቹ ይደረጋል የሚለው መረጃ ትክክል እንዲሆን ብቻ ነው። በሆነ መልክ የዝንጀሮዎች ስድ መሆን ወሲባዊ ድርጊትን ጥልቅ ተፈጥሮአዊ ፋይዳ ይሰጠውና በሆነ በተዛነቀ ስልት የሰዎችም ብልግና (አዘጋጁን ጨምሮ) ማንም የማይጠይቀው ስህተት የሌለበት የማይተች ሕጋዊ ድርጊት ይሆናል። የአገራችን ሲኒማ ከተፈጥሮ የተጣላ መሳሳም እንክዋን የማይፈቅድ አክተሮችን ከዝንጀሮ አሳንሶ የሚያይ ነው ብሎ መከራከር ይችላል። ያኔ ስሟ ያገኝ ይሆናል። ደሞም ያገኛል።

ሃና ስለዚህ ፎቶ መንገር አስፈላጊ አልመሰላትም። ብልጭ ያለ የማስታወስ ጥረቷን በደረቅ ፈገግታ ተካችና፡

'የማውቀው ይሄንን ነው። ሌላ ጥያቄ ካለህ?' አለች

---

ፖሊሱ ከሸሚዙ የደረት ኪስ ድንክ ማስታወሻና ጭቃ ቀለም አወጣና የሚጽፈውን መጻፍ ጀመረ:: ሃና ከተቀመጠችበት እርቀት ማንበብ እንደምትችል ሁሉ ማስታወሻውን፣ የሰውዬውን እጅ፣ ጣቶቹን፣ ብዕሩንና የጣቶቹን ንቅናቄ ስታይ ቆየች:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቀና አለና:

'በጣም አመሰግናለሁ ወይዘሮ ሃና:: ጥያቄዬን ጨርሼአለሁ:: ምናልባት ወደፊት ከፈለግንሽ ብቅ እንል ይሆናል:: አንድ ነገር ልጠይቅሽ እንዲሁ ለማወቅ ነው:: የአዲስአባ ልጅ ነኝ:: ስለአውሬዎች ምንም አላውቅም:: ለመሆኑ ዝንጀሮ ሰው ይበላል? ሰው ሊገል ይችላል? ይገላል? ገሎ ሊበላ ይችላል? የአካባቢው ገበሬዎች በዚህ አያምኑም:: ግን ገበሬ እህሉንና ላሙን ካልበሉበት ሊገባው አይችልም::'

ሃና ግራ በመጋባት አየችውና ለምን ጠየቅሽኝ አይነት የምታስብ መስላ:

'ኧረ የማውቀው ነገር የለም:: ዝንጀሮ በቲቪና በስዕል ነው ያየሁት:: የምር:: የጥይት ፋብሪካ ልጅ ነኝ ደሞ:: ሂሂ'

'የኮላሴን የተቀዳደደ ልብስ ዝንጀሮዎች የሚኖሩበት አካባቢ ትልቅ ዛፍ ጫፍ ላይ ምናምን አገኘን:: ላንቺ ነው ይሄንን የምነግርሽ:: እና ትንሽ ግራ ያጋባል:: አሁን ስለዝንጀሮ የሚያውቁ ሰዎችን ፈልገን ኮላሴ የጠፋበት አካባቢ እንዲመጡ ልንጋብዝ ነው:: አንቺ ጥሩ ተባብረሻል:: በነገራችን ላይ እዚህ አካባቢ ጥሩ ቡና አለ?'

'እ......አዎ ወደ ቀኝ በዚህ በኩል ታጥፈህ እም አንድ ሁለት ደቂቃ ከሄድክ ሶሲ ካፌ የሚባል አለ:: ሁሉ ነገር አላቸው:: ቡናቸው ቶሞካን ያስከነዳል::'

'የዘመድሽ ቤት ነው እንዴ? በጣም ፕሮፓጋንዳ አደረግሽ ሃሃ'

'ሰፈሬ ነው ሂሂ::'

ፖሊሱ እጁን ለሰላምታ ዘረጋና ሃናን ከጨበጣት በኋላ ከፀጉር ቤቱ ወጣ:: መንገድ ዳር ቆሞ ግራና ቀኝ እያየ ጀርባውን ለፀጉር ቤቱና ለሃና ሰጥቶ ቆመ:: ሃና ሽርጧን እየለበሰች ታየዋለች:: ማስታወሻ ካልያዘበት ደረት ኪሱ ጠፍጣፋ የሆነች ሰማያዊ የኒያላ ፓኮ አውጥቶ

ሲጋራ በአፉ አስገባ:: ፓኮውን ኪሱ መልሶ ዞር ብሎ ወደ ፀጉሩ ቤት አየ:: የሚያየው ጨለማ ነው:: ሃና ሰማያዊ ሸርጧን ለብሳ ከመስታወቱ ጀርባ ብትቆምም አያያትም:: ፊቱን ወደ መንገዱ አዞሮ ሲጋራውን ለኮሰና መንገዱን ቀጠለ:: ወደ ግራው:: ስለሶሲ ሰምቷል:: ሶሲ ካፌ የሚሰበሰበው ገንዘብ ያለው ጉረኛ ነው:: ሒልተን ሆቴል አልጋ የያዘ ሳጅን በአለም ላይ አለ? እንደዛ::

## ሁለቱ ወረቀቶች

ፖሊሶች 'ሁለቱ ወረቀቶች' እያሉ የሚጠሯቸው ኮላሴ መኪና ውስጥ የተገኙት የአራት ገጽ ወረቀቶች ይዘታቸው ይህ ነበር::

### ገቢር ሐመሩ
### (ትዕይንት: 3)

ቦታ:

(እውጭ ታቦት ማደሪያ/ ወለቴ ሱቅ:: አስፋልት ዳር:: ጨለማው ይቀጥላል በፍጥነት ያልፋል ታይም ላፕስ:24 ሲነጋ:: ካሜራው ይቆማል (medium shot) ~~(ሜሾ)~~ሜድየም ሾት (ሜሾ):: ካሜራ ~~ዶሊ ዙም ያደርጋል~~ እጅግ በቀስታ ዙም እያደረገ ወደ ዋሽንቷ ይጠጋል:: ፀሐይ እንደወጣች:: ዋሽንቷን ከእርቅት እናያለን:: ቢጫ የመሰለ ቀለም ስላላት ከአስፋልቱ ጥቁረት ጋር በንፅፅር ጎልታ ትታያለች::)

(closeup)[25] ክሎዝ አፕ (ክአ) (በቅርብ) (ቅ)

ካሜራው በትንሽ ከባቢ ውስጥ ማታ ላይ ዋሽንቷ በወደቀችበት ስልት:: አጠገቧ ያለ ሳር በነፋስ ይነቃንቃል

(extreme closeup)[26] ኤክስትሪም ክሎዝ አፕ (ኤክአ) (እጅግ በጣም በርቅብ)(እበቅ)

(ካሜራ ዋሽንቷን በተለይ ቀዳዳዎቹን ወይም የዋሽንቱን አፎች ያለ አውድ ያሳያል:: የጠዋት ነፋስ ገኖ ይሰማል:: በቀዳዳዎቹ ነፋስ ሲያልፍ ይሰማል:: 'ዳንቴል' የተባለው የፉጨት ድርሰት እዚህ ይገባል:: ወፎች ይንጫጫሉ:: የሰው ድምፅ ይሰማል:: የጠዋት ሬድዮ ከሩቅ ይሰማል:: የመኪና ድምፅ ይሰማል:: የሚነዳ/ የሚሽከረከር የብስክሌት የፊት ጎማ ይመጣና ዋሽንቷ

---

24 ወንድሜ ኤርምያስ እዛና እዚህ ለሚያጋጥሙህ የእንግሊዘኛ ቃላት እስኪ አማርኛ ምትክ ፈልግላቸው::

25 ዝኒ. ከማሁ

26 ዝኒ. ከማሁ

አጠገብ ሲደርስ ይቆማል። በፍጥነት ፍሬን የያዘ የብስክሌት የፊት ጎማ ዋሸንቱ አጠገብ ይቆማል። ተሳፋሪዋ ሚዛኗ ከባድ ስላልሆነ ጎማው ብዙ አልተደፈጠጠም። ጋላቢዋ ትወርዳለች። የሚታየው ጥቁር ታይትና ቀይ ስኒከር ጫማ ብቻ ነው። ዋሸንቷን ስታነሳ ጣቶቿና ጥፍሮቿ ይታያሉ። ጥፍሮቿ ሰማያዊ ቀለም ተቀብተዋል። ለተመልካች ሴት መሆኗ ይታወቃል[27]

---

[27] የብስክሌት ጋላቢውን ፆታ በሚመለከት ከኢሳያስ ~~አዘጋጁ~~ ጋር ትንሽ ተነታርከናል። እኔ ሴት እንድትሆን ነው የፈለኩት። ይሄም በሁለት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ፊልሙ ሲጀመር ዋሸንቷ የተሰራችው ለአንዷት *ሕይወት* ለተባለች ልጃገረድ ነበር። ሲጀመር ለሕይወት የተዘጋጀው ስጦታ ለሕይወት እንኳን ባይደርሳት በፊልሙ መጨረሻ ሌላ ሴት እጅ እንዲገባ በማድረግ ሚዛን ለመፍጠር በማሰብ ነው። ሁለተኛው ምክንያቴ ግላዊ ነው። እዚህ ፊልም ውስጥ በትንሹም ቢሆን ስርጋ እንድትገባ የምፈልጋት በእውን የማውቃት ልጅ አለች። ፊልሙ ላይ ተዋንይዋ እንድትለብሰው የፈለኩት አለባበስ የዚህች የማውቃት ልጅ አለባበስ ነበር። አለባበሷ ሁልጊዜ የጥጥ ታይትና ቀላል የበጋ *ትሬንች ኮት* ነው። ከዘነጠች ደሞ ይሄንን አይነት ልብስ ለብሳ ግን ጫማዋን ከስኒከር ወደ ባለ አጭር ተረከዝ *ኪትን ሂል* ትለውጣለች። የጥፍር ቀለሟ ሁልጊዜ ሰማያዊ ነው። ሁልጊዜ ባክ ፓክ ትይዛለች። የሴት ቦርሳ አይደለም። አሁን ልጅቷ በምትማርበት ዩንቨርሲቲ ሰቃይ ከሚባሉት አንዷ ነች። ~~ይሄንን ገልበቅ ለመስጠት ከአምስቱ የፋጨት ድርሰቶች አንደኛው ሴገራችን ሁሉ የእምቢይ ካብ የእምቢይ ካብ' የሚለው ወደዚህ የሚጠቀም ነው።~~ ዳይሬክተሩ ኢያታዊ አጨራረስ እንዲኖረው የፈለገው አጨራረሱ አጠቃላይ ሰፊ የሆነ ማሕበራዊ ፍቺ ላይ ብቻ እንዲያተኩርለት መሰለኝ። ለእኔ አጨራረሱ የዋሸንትና የሰው ነው። መቼ ዕለት ነው ክርክሬን ባበዛበትና ~~ቅንጅ~~ ቢመረው ለመሆኑ *ይህቺ ልጅ ምንህ ናት?* ብሎ ጠየቀኝ። ምኔም አይደለችም። ለመሆኑ ያ ተራራ ምኔ ነው? ያ ወንዝ ምኔ ነው? ያ ድንጋይስ? አንድ ነገር እዚህች ምድርና አገር ላይ ስላለ ብቻ የመወደስ ወይም የመነቀፍ ወይም የመጠራት መብት አለው። <u>መጠራት</u> ስል ~~ሚልኬ እንደሉ~~ በዚህ ምድር ላይ እንዳለ በዐይኖቻችን እንደተመዘገበ መጠቆም ማለቴ ነው። የአገራችን ዋናው ጣጣ በግልፅ የሚታየውን ነገር ሙልጭ አድርጎ የመካድ የኮግኒቲቭ ቀውስ (cognitive crisis) ነው። ልጅቷ ከሰፈር ዐይን እርቃለች ግን ይሄው ላወራላት ነው። ለዚህም ነው አጨራረሱ ላይ የሚመጣው ፉጨት የላሎ ሽፍሪን ሳይሆን የፈሽታ ~~ዩዶሴቃ~~ መሆን አለበት ያልኩት። ጋሺዎች ግን አንስማም አሉ።

ፊልሙን ሹት (ለዚህ ቃል እኩያ ፍቺ ቢኖር እወድ ነበር። በቀጥታ ተርጓሚ 'መተኮስ' ልበለው? ጦርነት ያስመስልብኛል) ስናደርግ ያወራነው ሁሉ ሳይለወጥ የፊልሙ አርታኢ ~~ቅሬእሙ~~ አክብሮ መፈፀም አለበት። ምናልባት ለአፕራስዮን ሆስፒታል ስለምመለስ ~~ሌሙልስ~~

ካሜራው አለበት ይቆማል[28] ብስክሌቱ ለዐይን እየራቀ ይሄዳል:: አብሮትም ደማቅ ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ

---

~~ስልሞችል~~ ድንገት ስራ ላይ ባልገኝ ~~ባልኖር~~ እንኳን ይሄ አቋሜ እንዲከበር እፈልጋለሁ:: የአዘጋጁ ችግር ሁሉን ፍልስፍና የማድረግ ነው:: ማለት *ሜታፎራይዜሽን* (ልዋጭ መስራት) ፍልስፍና ከሆነ:: እኔ የፈለኩት ዋሽንቱ በፍሰት የሰው ታሪክ ውስጥ፣ የሰው ታሪክ በፍሰት ዋሽንቱ ታሪክ ውስጥ *እንዲገባቡና* ዋሽንቱ ለሰው እናም ሰው ለዋሽንቱ፣ የተራዘመ ሕልውና በውበት ሃሳብ እንዲሰጣጡ ነው:: ~~ውበት እንደ ሃሳብ ማለቴ ነው::~~ ማሕበራዊ መልዕክት በእኔ መበደል ወይም መደሰት ላይ ተደግፎ እንዲተላለፍ አልፈልግም:: ይሄን ስለው ዋናው አዘጋጅ ስቆ ነበር:: *ኪነጥበብ የአገራችን ችግር እንዲፈታ ሃሳብ መስጠትና መፍትሄውን መጠቆም አለበት አለኝ::* አገራችን ከባድ ችግር የለባትም:: በተጨማሪም እኔን ለአዳኝነት የመረጠኝ የለም:: የአገራችን ሰዎች ራሳቸው ችግር ፈጥረው ራሳቸውን ካላመሱ በስተቀር አገሪቷ ውስጥ አፍ የሚያካፍት ኪነትን ለእርዳታ የሚያስጠራ ችግር የለም:: ራሳቸው ላይ ችግር ፈጥረው በትንሹም በትልቁም ራሳቸውን የሚያምሱና ስራ የሚፈቱ ሕዝቦች በየትኛውም ሂሳብ እዚህ ምድር ላይ የመኖር መብታቸውን ለብልጦች አሳልፈው ሰጥተዋልና በእኔ አንድ ምስኪን ፊልም ፕሮዲዩሰር ምክር ይቅርና በአላህ ትእዛዝም ከምድረ ገጽ ከመጥፋት አያመልጡም:: ኢምፔሪያሊዝም ገና ከቤቱ ሳይነሳ እዚሁ በዚሁ ራሳችንን ለማጥፋት የሚበቃ የደደብነት ማዕድን በውስጣችን አለ:: እሱም ወይ ደማችን ውስጥ ነው፣ ወይ ቋንቋችን ውስጥ ነው:: በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሁሉም የተመኘውን ያግኝ:: እንደ ድመት እርስ በእርስ ተቦጫጭራችሁ ዐይናችሁ ታውሮ ፊልሜን ማየት ባትችሉ ግድየለኝም:: የምሰራው ለደደቦች አይደለም (አቡ እንዲህ እንደሚል ተስፋ አደርጋለሁ):: ስለዚህ ወንድሜ ፊልሙን ተውልኝ::

በነገራችን ላይ ይሄ ፊልም ቀጣይ ክፍል አለው:: የቀጣዩን ክፍል ስክሪፕት ~~ድራፍት~~ ቢጋር አይተነዋል:: ይሄ የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ሁለተኛው ክፍል የሚበቅልባቸው ዐይኖች ስላሉ እንዳይጠፉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ለፊልሙ አርታኢ ደጋግሜ አስታውሱት:: ምክንያቱም ~~ጓጠፎ~~ ዐይኖቹ ለቅብብል የተሰሩ ላይመስሉት ይችላሉ:: ይሄ ፊልም የራሱ አጨራረስ ቢኖረውም የሚቀጥለው ፊልም የሚጀምርበትን ጥሬ ሃብት ተሸክሞ ይመጣል:: ቀላል ምሳሌ ልውሰድና፡ ዋሽንቱን ከወደቀበት ማን አነሳው? ከዛስ? ይሄ አጨራረስ ራሱን የቻለ ጉጥ ወይም ዐይን ነው:: ድርስቱ ገላ ውስጥም ትንሽ ቢኮረኮሩ የሚፈኩ ዐይኖች አሉ::

---

*የእምባይ ካብ* የተባለው የፉጨት ድርሰት ይገባል:: መንገዱ ላይ ከብስክሌቱና ከጋላቢው በስተቀር ምንም የሚንቀሳቀስ ፍጡር መታየት የለበትም:: ብስክሌቱና ጋላቢዋ አድማስ ውስጥ ከመጥፋታቸው በፊት ፍሪዝ ያደርጋሉ:: *ሆይሼ ሆይሻ* የሚለው የፉጨት ዜማ እዚህ ይከተላል::

ከዚህ ቀጥሎ[29]:

ስክሪን ወደ ነጭ ይሚሚል (*ዲዞልቭ ያደርጋል*)

(እኔ 'ይሚሚል' ብዬዋለሁ:: እናንተ ተነጋግራችሁ የሚመጥነውን ቃል ወይም ደስ ያላችሁን ተኩ)

ከዚህ ቀጥሎ (ከታች ወደ ላይ እንደ ጥብጣብ በሚጎተት ጽሑፍ)

**አዘጋጅ** (ኢሳያስ)

**ምክትል አዘጋጅ** (ኤርሚ)

**ፕሮዲዩሰር** (ባካፉ መዝገቡ)

**ስክሪፕት ጸሐፊ:** (ባካፉ መዝገቡና መሰበወርቅ ይልማ)

ከዛ በሁዋላ ማስታወሻ የተደረገላቸው ሰዎች ይገባሉ::

- አዲስ ብስክሌት አያስፈልገንም (ቢቻል ብንከራይ ጥሩ ነው)
- ጥቁርና ነጭ እናንሳው የሚለው ክርክር የሞተ ነው:: ምክንያቱም ዋሽንቱ አልጠፋም:: ዋሽንቱ ቦታ ነው የለወጠው:: ከመተከል እዚህ ታቦት ማደሪያ:: ዘመኑ አንድ ነው:: የተሰራና የጠፋበት ዘመን አንድ ነው::
- *ዶሊ ዙም* አልፈልግም:: በጣም ድራማቲክ ያደርገዋል

---

28 *ኢሳያስ ~~ዋናው አዘጋጅ~~ ከኤርሚ ~~ምክትል አዘጋጅ~~ ጋር በትራኪንግ ሾት ይሰራ እያለ የሚነዘንዘኝን በማርያም ተው በሉልኝ::*

29 ይሄ በነ.ያላ ፎንት እንዲሰራ አኒሜተርስ ሃሳብ ሰጥተውኛል:: ደስ አላለኝም:: ስንት ቦታ ስለ ኒያላ እንስማ:: በአገሩ ሌላ እንስሳ የለም እንዴ? 'ብርቅዬ' የሚል ደባሪ ቃል ተጠቅማችሁ ልትደልሉኝ አይቻላችሁም:: ከቃሉ ማለት ከብርቅዬ ማምለጥ ካልሆነላችሁ ሌላ እንስሳ አሞራም ይሁን ፈልጉ:: ለመሆኑ በሌላ እንስሳ ስም የተሰየመ ፎንት አታገኙም? አልተሰራም? (ያው የፈረደበት አንበሳ ካልሆነ):: ዋሽራ ሊሆን ይችላል፣ ጅረት ሊሆን ይችላል:: ተራራም:: ብቻ ሌላ ሞክሩ::

---

ሰዎቹ እነዚህ ናቸው:

ሊዲያ ፍስሐ

ገነት ፍስሐ

መዝገቡ ዱባለ

ራሚሱ (አቡ)

ገለታ (ዲምፕል)

ጌርሳሞት (ጌርሳ)

ለምሳ የሚሆን
ወጪ
16 ጥብስ
2 ቀይ ወጥ
4 ክትፎ
11 አምቦ
6 ቢራ
ጠቅላላ
ውጪ በግምት
2200 ብር
ነሐሴ 21

አጃቢና የሴማ ሙዚቃ ሆነው የተሰሩት አምስቱም የፉጨት ድርሰቶች ቀደም ሲል በተነጋገርነበት መልክ ብቻ እንዲገቡ ይሁን:: ሌላ አይቻልም ፉጨት ብቻ::

(ሙዚቃ ድርሰት፡ በአቦምሳ ከበደ:: በፉጨት ተርጓሚ፡ ዘሪሁን)

"ዳንቴል"

"ሆይሼ ሆይሻ"

"ልቤን ያያችሁ ሰዎች ንገሩኝ፣ አፎን ስመለከት ጠፋብኝ"

"እረኛው ለዘላለም ይኑር!"

"ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ የእምቧይ ካብ"

ሃና
090406131

---

(ለፊልም ዳይሬክተሩ ማስታወሻ እንዲሆን በፍጥነት ተሰርቶ የቀረበ ገቢር ሐመሩን ለማጠናቀቅ የሚረዱ ሃሳቦች)

ባካፋ መዝገቡ

*

'መለየት ክፉ እጣ'፡ አምና ጀማምራትና በዚህ በያዝነው አመት ታቦት ማደሪያ በድሮ ዘፈን ፍቅር ሰክራለች። ያለፈውን ዘመን ኪነት አፍቃሪ ያለፈውን ዘመን ፖለቲካ እንደ አፈቀረ ይቆጠራል? ክራር የጋራ፣ ትርጉም ለየቅል ነው ይላሉ የወጨጫ ነፋስ የነካቸው የጠስኝ ሻይ የሚያገሱ የታቦት ማደሪያ ዜጎች። የድሮ ዜማዎችና ግጥሞች እያዳመጡ እዚህ ግባ በማይባል ዛሬን በማይገልፅ ጥልቀቱ መመሰጥና ከንፈር መምጠጥ ደንብ ሆኗል። ፀፀትና ፀፀተኛ። አርፎ መርሳት የከበደው ወደ ኋላ ተንሸራታችና ለምቦጭ ጣይ። ወጣቶችም አዛውንትም ተቀምጠው ወደ ሚመዘምዛቸው ትናንት ሄደዋል። እነሱ እንዳሉት ዘመን ስለማይሽረው ዘመን። የራሱን ባክቴርያ የተከተበ ባክቴርያ። ታማኝ ትናንትና። የዘመናይነትን ውበት ያላወቁ። የጥንት ታዋቂና ታታሪ አዝማሪዎች ዜጋውን አጡዘውታል። *አያ ማሩ እሸቴ......አካል የእኔ አበባ......ቦጌ ኢልካን አናኒ......ወለሌ......ማን ነበር የአላንቺ......ኸረ ምን ይሻለኛል.....ሳባ ሳቢና......ስንቱን ጋራ ዞረሽ......ስንቱን ጋራ ዞሬ......ትዝታ አያረጅም......ምንድነው ሰው ማሰብ ምንድነው ትዝታ.....ሰው እንዴት ባለፈው በትናንት ይኖራል......መለየት ክፉ እጣ.....*ወዘተ ወዘተ[30]

---

30 (ከነዛ ሁሉ አንጻ)። ጠባብ ድንጋይ የተነጠፈ ግቢያቸው ውስጥ መግደላዊት ከሰራተኛዋ ጋር እዛና እዛ ሆነው በላ አንሶላ ላይ ለድርቆሽ የሚሆን የተቆራረሰ ነጭ እንጀራ በዝምታ ያሰጣሉ። የግቢው ልብስ መስቀያ ላይ ከጻር እጻር የጌርሳሞት ልብሶች ተዘርግተዋል። ዝርዝር፡ ሱሪ ሱሪ ሱሪ ውስጥሱሪ ውስጥሱሪ ውስጥሱሪ ውስጥሱሪ ካናቴራ ቀሚስ ካናቴራ ቀሚስ ውስጥሱሪ ሹራብ ሹራብ ሱሪ። መግደላዊትን ያለ ኮላሴ ከሶስት ወር በላይ መኖሯ እንደጎዳት ገጽዋ ላይ ተጽፎአል። ይሙት ይኑር ፖሊስ መርምሮ ባይደርስበትም ተስፋ ቆርጣ ሲሞት ነው ብላ እንደኛውኑ ጥቁር ቀሚስ ለብሳለች፣ ጥቁር ሻሽ አስራለች። ኮልፌን አልረሳሁትም፣ ለማለት መኪናው ተበላሽታ የቆመችበት አካባቢ ወንዝ ዳር የተገኘውን መስታወቱ የተሰበረ የማይሰራ ካሲዮ ኤሌክትሮኒክስ የእጅ ሰአቱን በቀኝ እጇ ላይ አስራለች። ጌርሳሞት ደሞ ዓለምን እንዳኮረፈች ሁሉ አሞድሙዳ በረንዳ ላይ ለትምህርት ቤት የምታዘጋጀውን ባግፓክ ውስጡን በእርጥብ ጨርቅ ትጠርጋለች። የሚታይ የመሰለ ዝምታ

ከመሃላቸው አለ: ይሄውና:: አጠገቧ ከፍ ብሎ ካልተከፈተ ሲ.ዲ. ማጫወቻ የበዛ ወርቅን የትዝታ ዘፈን ትሰማለች::

በተሰጣው የልብስ አይነትና በሙዚቃው ጉዳይ በጌርሳሞትና በእናቷ በመግደላዊት መሃል አለመግባባት ተፈጥሮ የማይመች ፀጥታ በግቢው ነግሦአል:: ዝምታው የዚህ ርዕዮተ አለም ግጭት ውጤት ነው:: *የትዝታ ወሰን አይገኝ ድንበሩ፣ ያርፉ እንደሆን እንጂ ወድቀው ሲሰበሩ::* ጌርሳሞት ካበጠና ከቆሰለ በቅባት ከሚያብለጨልጭ አፏ ላይ ለማረፍ እየተንዛዛ የሚያስቸግራትን ትንኝና ዝንብ አልፎ አልፎ እሽ ትላለች:: መግደላዊት በትዝብትና በቁጣ ጌርሳሞትን ቀና ብላ ታያለች:: ጌርሳሞት ከነገ ወዲያ ወደ አዋሳ ዩንቨርሲቲ ለመሄድ በሻንጣዋ ከምትከተው ልብስ አንድ እንኳን ጥቁር የለበትም:: መግደላዊት እህል እያሰጣች ለብቻዋ ግን ደሞ ሌሎች እንዲሰሙ አድርጋ ታወራለች: 'አሁን ይሄ የቻይና ቅራቅንቦሽን ሰብስበሽ ሄድሽና.....'ይገርማል......' 'እባክሽ አንቺ ልጅ ሰውም አታከብሪ ይሄን ዘፈን ዝጊልኝ' 'በየትም አገር ወላጅ ይከበራል እኔ ቤት ብቻ እንጂ፣ ኮላሴ ብቅ ቢልስ አንድ ቀን' 'ፎርቱና ባለቤትሽ ኮላሴ እንደ ልጄ ነው የጠፋው አለችኝ:: እውነት እኮ ነው:: እሷ ገለታን እየጠበቀችው ነው ድንገት ቢመጣ ብላ:: እኔስ ኩልዬን አልጠብቅም?'

የግቢው የብረት በር ተንኳኳ:: ድምፁ በብረቱ ስፋት ስለተዋጠ ስድስት የሚሆኑ የ 'ቋ' የ 'ጓ' እና የ 'ኳ' ተለዋዋጭ ድምፆች ጀርባ ለጀርባ ሆነው ወደ 'እም' ነት ይሻገራሉ:: የግቢው በር ሲንኳኳ ሁልጊዜ እንደሚሆነው የመግደላዊት ልብ አልደነገጠም:: እስከ ቅርብ ጊዜ እንደሚሆነው ልቧ ትር ትር አላለም:: በዚህ ቸልታዋ በኮላሴ መገኘት ነገር ተስፋ እንደቆረጠች ያስታውቃል:: 'ተስፋ ቆርጫለሁ' ባትልም ፊቷ ላይ የማይታይ ከመደበርዋ ስር የሚርመሰመስ ስሜት እንደሆነ ያጤናት ሰው ሁሉ ይገባዋል::

--ማነው? እስኪ ጌርስዬ? ክፈቺ እስኪ አለችና የምትሰራው ከልቧ ባይሆንም፣ ቁጢጥ ብላ በእጇ ፀሐይ እንዲያገኘው የተሰጣውን እንጀራው አገላበጠች:: በሙቀቱ ወይም በልስላሴው እንደተገረመች ሁሉ ጣቶቿን አተኩራ ዐይታ እንደገና ማገላበጥዋን ቀጠለች:: ጌርሳሞት ሄዳ በር ስትከፍት፣ ጠና ያለ ዕድሜው በግምት አርባ የሚሆን አንድ ጎልማሳ ሰውዬ፣ በተገረበበው በር ወደ ውስጥ ለማየት የምትለፋ ቀልቀል የሚያደርጋት መልከመልካም ወጣት ሴትና ዕድሜአቸው በሃምሳና በስድሳ መሃል የሚሆን የሚያብለጨልጭ ጥቁር ድርያ የለበሱ አሮጊት ሴትዮ ጀርባና ፊት ሆነው ቆመው አየች::

--ማን ልበል?

---

ጌርሳሞት ፊት ላይ መረበሽ አለ፣ ያው እሷም ችላ እያለች ብትመጣም፣ ከውስጧ ስለ አባቷ የሆነ ወሬ ትጠብቃለች፡፡

--ወይዘሮ መግደላዊትን ለማነጋገር ነበር አለ ጎልማሳው ረጋ ብሎ፡፡

--ምንድነው? አለች

--ጥሩ ወሬ ይዤ መጥቼአለሁ አለ ሰውዬው ፈገግ ብሎ

ጌርሳሞት በቀኝ እጇ አስፍታ የከፈተችውን በር ሳትለቅ:

--እማ የሆኑ ሰዎች ሊያነጋግሩሽ ይፈልጋሉ አለችና በሩን ለእንግዶቹ ከፈት አደረገችላቸው፡፡

--ግቡ በያቸዋ ሰው አታቁሚ ከመስሪያ ቤት ይሆን?

--አይ አይደሉም አለች ወጣቷን ልጅ እያየች፡፡ የልጅቷን ቁንጅና አይታ የራሷ ነገር ትዝ ብሏት የታመመ አፏን ለመጋረድ ሞከረች፡፡ ታይታ ስለጨረሰች የተሳካላት አይመስልም፡፡ በቀስታ እየተራመደች እንግዶቹን አስከትላ ተመለሰች፡፡ ከልጅቷ በስተቀር የቀሩት ሰዎች የሚረግጡትን እንደፈሩ ሁሉ በዝግታ ወደ ግቢው ሲገቡ መግደላዊት ቀና ብላ አየቻቸው፡፡ ማናቸውንም እንደማታውቅ ከሁኔታዋ ግልጽ ነው፡፡ ቁጢጥ ካለችበት ተነስታ:

--ማን ልበል? አለች

ሰውዬው ከአሮጊቷና ከልጅቷ ፈጠንና ቀልጠፍ ብሎ:

--ወይዘሮ መግደላዊት ጳውሎስ ነሽ? አይደለም?

--አዎ ምነው? ኮላሴ ተገኘ እንዳትሉኝ አለች ደንገጥ ብላ

--አይ እትዬ አይደለም፡፡ ተቀምጠን እናውራ ጥሩ ወሬ ነው፡፡

--ምንድነው ደሞ የሚያስቀምጥ?

ምንም ቆሻሻ ባይኖርባቸውም የእጆቿን መዳፎች ሱሪዋ ላይ እያጸዳች ወደ ሰዎቹ ቀረበች፡፡

--እዚሁ ንገረኝ

--ለመሆኑ ሰላማዊት የምትባል እናት ነበረሽ?

በዚህ አባባሉ መግደላዊት ብቻ ሳትሆን አካባቢው፣ የቤቱ ግድግዳ፣ ጣሪያው፣ ታቦት ማደሪያ፣ ታቦት ማደሪያ የበቀሉት ዛፎችና ቅጠሎቻቸው ጸጥ ያሉ መሰለ፡፡ የታቦት ማደሪያ ነፋስም፡፡ መግደላዊት ሰውዬውን አተኩራ እያየች:

--እና? አለች

ሰውዬው ወደ ኋላ ዞሮ ቀኝ እጁን ድርያ ወደ ለበሱት ሴትዮ እያሳየ:

--እናትሽን ወይዘሮ ሰላማዊትን አገኘሁዋቸው አለ፡፡

መግደላዊት አፏን ከፍታ ሰላማዊት የተባሉትን ሴትዮ አፍጣ ማየት ጀመረች፡፡ አትናገርም፡፡ አሮጊቷ በከፊል ፊታቸውን የጋረዱበትን ድርያ አውርደው አቅም ያነሳቸው አይነት ከቆሙበት በቀስታ ቁጭ አሉና ማልቀስ ጀመሩ፡፡ ከመናፈጥ ድምፅና በጉንጫቸው ላይ ከሚንዠቀዠቅ ዕንባ

---

ሌላ ሴትዮዋ የድርያ ክምር ሆኑ:: መግደላዊትና ጌርሳሞት የተነገራቸውን መረጃና ጠቅላላ ያሉበትን አለም እንደፈሩ ሁሉ ተጠጋግተው ቆሙ:: መግደላዊት ዐይኖች ውስጥ ከመደንገጥ ምልክት በስተቀር ዕንባ የለም:: እቤቷ ለመግባት እንዳሰበች ሁሉ የልጅዋን እጅ እየጎተተች ወደ በረንዳው በቀስታ ወጥታ ዞር ብላ 'ሰላማዊት' የተባሉትን ሴትዮ አየች:: በረንዳ ላይ ወጥታ የጌርሳሞትን እጅ ለቀቀችና ጭንቅላቷን በሁለት እጆቿ ያዘች:: ከሰላማዊት ጋር የመጣችው ልጅ ቀልቀል ባለ ድምፅ መሬት ላይ ተቀምጣ በድርያዋ ተከናንባ ወደ ምታለቅሰው ሴትዮ ጎንበስ ብላ:

--ሄደሽ እቀፊያት እንጂ አንቺን ትመስል የለ:: አፋልጊኝ ብላ ጨቅጭቃኝ ትጋገርብኛለች:: *ክሬዚ* አሮጊት::

ሰውዬው ዞር ብሎ ገላመጣት::

--በዴቢ ሞት *ጆክ* ነው::

አሮጊቷ ፊታቸውን በሚብለጨለጭ ድሪያቸው እየጠረጉ፣ በከፊል ጉልበታቸውን እየተደገፉ፣ ቁጢጥ ካሉበት እያማጡ ተነሱና በቀስታ እየተራመዱ በረንዳው ላይ ወጡ:: መግደላዊትን ሊያቅፏትና ሊስሟት እጃቸውን ዘረጉ:: መግደላዊት እያለቀሰች፣ የሚፈስ ዕንባዋን እየጠረገች፣ ደሞ አሮጊቷን እንደፈራቻቸው ሁሉ ሸሸት እያለች፣ በሚንቀጠቀጡና በሚቆራረጡ ቃላት:

--ምምን አደረኩሽ እሜሜሜዳ የተውሽኝ? እ? ከሞትኩ በሁዋላ ምን ትሰሪኛለሽ? አለች

ከአርባ አመታት በላይ ተለያይቶ መገናኘት ለማንም ከባድ ነው:: መግደላዊት የማታውቃቸው ብዙ ዘመዶችና ዘመድ አስተኔዎች አንዱ ለአንዱ እየተቀባበሉ ያደገችበት የልጅነት ጊዜ ነው:: በዚህ ጉዞ ሴትነቷ እንዴት እንደተበጠበጠ ማስታወስም ይከብዳታል:: እናቷን በማትፈልግበት፣ ሁለት ወልዳ መከራዋን በዘለቀችበት ጊዜ መምጣቷ የእግዜር ምፀት ሳይመስላት አይቀርም:: ብዙዎች ሲጫወቱባት 'ችፍ' ልትልላት የመጣች እናት አልነበራትም:: እናቷም እንደሚባለው ጥሩ ስም አልነበራትም:: ሉጫ ሽበቷ ከድርዪዋ ያለቁጥጥር ተዘርግፎ የወጣ፣ ግድየለሽ የመሰለች አሮጊት፣ ነፍስ ማጥፋት የምትችል አይመስልም:: ስትነቃነቅ የምትተወው የጠረን ጳና ሽቶ፣ ጫትና ሲጋራ ነው:: ቀኝ የእጇ መዳፍ በእንሶስላ ቀልሟል:: መግደላዊት ሰላማዊትን ሳታቅፋት ፊቷን አተኩራ አየችው:: ያለፈው ዘመን እየተንደረደረ ሲጠጋት ማምለጥ የምትችልበት አቅም አልነበራትም:: የገጽዋ መልክ የዛ ፎቶ ኮፒ ነው:: ስነምግባርን ዕጣ ፈንታን ዘረመል ይሰርዛታል? ሂሳቡ አልከበዳትም:: (ምሳሌ: እናንት ዝንጉርጉር የኢትዮጵያ እናቶች ስትወልዱ ራሳችሁን የመሰለ ውለዱ፤ የሚሆነው አይታወቅምና) እሷን ሳያሰልስ ያስቃያት ይህቺ አገር የሰፈረችበት የሉል ክፍል ኮይራ ኮይራ የምትሸት ምስኪን እናቷን

አንድ ነገር እንዳደረጋት ትገምታለች፡፡ ሱስ ይተዋል? እሷን ያበላሿት ሲያወሩላት የነበረችው ዘመነኛ ምሁራን የተሻሙባት የናዝሬት ስኩል ተማሪ ሳትሆን የተሳካላት የመርካቶ ሳንቡሳና ባለአበባ ቀሚስ ሽቃይ ትመስላለች፡፡

--እኔ አይደለሁም፡፡ ጳውሎስ ሰርቆሽ ጠፉ፡፡ ብዙ ብዙ ነገር ነው ልጄ፡፡ ተወርቶ አያልቅም እያለች እጆቿን ሳታወርድ ተጠጋቻት፡፡ ራቅ ብሎ ከበረንዳው ታች አንጋጦ ሲያየቸው የነበረው ሰውዬ በግራ ብብቱ ከያዘው ቀጭን የቆዳ ቦርሳ የተጨመዳደደ፣ ካኪ ቀለም ያለው የወረቀት ቀረጢት በፍጥነት አወጣና የሚቀበለው ፍለጋ ዘረጋው፡፡ የሚቀበለው ሲያጣ:

--ቹቹ እኔ ልሂድ ስራዬ አልቋል፡፡ ውሰጂና ስጪልኝ አለ፡፡ ቹቹ የተባለችው እያለቀሰችና እየተናፈጠች ክላሴሩን ተቀበለችውና:

--ገንዘቡን እዚህ አልሰጥህም፡፡ ሻገር ና

--የተወራረድነውን አትርሺ

--ይልቁን ቆይና ሊፍት ልስጥህ

--ከቻልሽ ዋናው መንገድ ድረስ አውጪኝ፡፡ ደሞ ጉዳይ አለኝ፡፡ በ1968 የጠፉች ልጅ ሲአይኤ እንኳን ፈልጎ አያገኝም፡፡ ለእኔ ለቆራጡ አንድ መፅሐፈ ዶሮ ሳይሆን መኪናሽን መሸለም ነበረብሽ፡፡ በነገራችን ላይ እዛ ውስጥ ሁሉ አይነት ፎቶ፣ የት የት እና ማንን እንደጠየቅሁ፣ ቀኖቹ፣ ደብዳቤዎች በሙሉ እንዳሉ ታውቂያለሽ፡፡ መዘረዘር አያስፈልግም፡፡ ለመሆኑ መቼ ነው አንቺን የመሰለች ልጅ የምትወልጂው? ሂሂ

--ደሞ እኔን የመሰለች ልጅ ተወልዳ ምስራቅ አፍሪካ በጦርነት ይታመስ?

ሰውዬው እየሳቀና ራሱን እየነቀነቀ ዞር ብሎ አየ፡፡ መግደላዊትና እናት ተቃቅፈው በዝምታ እየተደባበሱ ቆመዋል፡፡ ቹቹ ከሰውዬው የተቀበለችውን የወረቀት ቀረጢት ቶሎ ሂዳ ለጌርሳሞት ሰጠቻት፡፡ ጌርሳሞት ተቀብላ እንደ ጅል አየቻት፡፡

--ሁሉ ነገር እዛ ውስጥ አለ፡፡ የመግደላዊት ልጅ ነሽ አደል?

ጌርሳሞት ጭንቅላቷን በአወንታ ነቀነቀች

--የእናትሽ የልጅነት ፎቶ ምናምን ሁሉ አለበት፡፡ እንኩዋን ደስ አለሽ፡፡ ኮንግራ፡፡ ሰውዬውን እሸኘውና እመለሳለሁ፡፡ ሰላም እዚህ ትንሽ ትቆይ፡፡ ከሰላም ጋር አብረን ነው የምንሰራው፡፡ እንዴት ጥሩ ሴት መሰለችሽ፡፡ ጥዝጠዛ እንዳይመስልሽ አለቻትና ሰውዬውን ተከትላ ከግቢው ወጣች፡፡

---

# የድርሰቱ ቅርፅ

## (የቅልልቦሽ ግማሽ ጨዋታ)

1 የድርሰቱ ቅርፅ የተቀዳው ከባለ አምስት ጠጠር ቅልልቦሽ ጨዋታ ነው:: ቅልልቦሽ ጨዋታ የሚደረገው በአምስት ወይም በሰባት ጠጠሮች ነው:: እነዚህ ቁጥሮች የተወሰኑት ምቹነት ስላለው ይሁን ወይም ከጀርባው የተለየ ታሪክ ወይም ስነ-ተረት ስለነበረው አላውቅም::

2 ጨዋታው ሲጀመር አምስት ጠጠሮች ወለልታ ቦታ ላይ በ 'ጉች' ይቀመጣሉ:: ከነዚህ ጠጠሮች ቀልባችን ያረፈባትን ወይም ለመያዝ የምትመቸንን አንድዋን እናነሳታለን:: ይህቺ 'መቅለቢያ' ትባላለች:: እንዲህ ስናደርግ 'ወለል' ላይ አራት ይቀሩናል:: ቀጥሎ በእጃችን የያዝናትን መቅለቢያ ጠጠር ወደ ላይ አጉነን ከጎነችበት ወርዳ የዘረጋንላት እጃችን/መዳፋችን/ ውስጥ ከመግባቷ በፊት 'መሬት' ላይ ካሉት ጠጠሮች አንድዋን በፍጥነት በዛው የመጀመሪያዋን በወረወርንበት እጃችን እናነሳለን:: በዚህ ዓይነት ተራ በተራ አራቱንም ጠጠሮች እንለቅማለን:: (በዚህ ሂደት ውስጥ በመጀመሪያ ላይ 'መቅለቢያ' ብለን ያነሳናት ጠጠር 'መቅለቢያነቷ'ን ልታጣ ትችላለች) ቀለባው ሲያልቅ በእጃችን ውስጥ አምስት ጠጠሮች ይኖሩናል:: በዚህ የመቅለብ ሂደት ውስጥ መቅለቢያችን ወይም የምንቀልባት ጠጠር ከእጃችን አምልጣ ከወደቀች እንደተሸናፊ እንቆጠርና ተራው ለተፎካካሪያችን ይተላለፋል:: *ይሄ አንድ ጨዋታ ነው::*

3 ቀንቶን ወይም ችለንበት በእጃችን አምስቱን ጠጠሮች ይዘናል እንበል:: ቀጥለን የምናደርገው ነገር ምደባ ነው:: ይህ ማለት አንድ ጠጠር ወደ ላይ እንወረውርና በእጃችን ውስጥ ያሉትን አራቱን ብቻ መሬት ላይ እናስቀምጣለን:: *መመደብ* ያጎናትን ጠጠር መልሰን ሳንቀልባት በፊት የቀሩትን አራቱን ከጭብጣችን ለቀን ወለል ላይ ማስቀመጥ ማለት ነው:: ይሄን ካደረግን በኋላ የጎነችውን ጠጠር ሳትወድቅብን መቅለብ ይኖርብናል:: አጉነን የቀለብናት ብቻ መዳፋችን መሀል ስትቀር የቀሩት ማለት አራቱ ጠጠሮች ወለል ላይ ይሆናሉ:: የሚቀጥለው የጨዋታ ደረጃ ቀደም ሲል አንዳንዶቹን ጠጠሮች ለየብቻቸው ከወለል ላይ ነቅለን እንዳነሳናቸው ሁሉ አሁን ግን ሁለት ሁለቱን ተራ በተራ እናነሳለን:: ሁሉም ጠጠሮች ከተለቀሙ በሁዋላ ጨዋታውን አሸንፌአለሁ ይባላል:: ካልተሳካልኝ ግን አብሮኝ ለሚጫወተው ተራው ይዞራል:: *ይሄ ሁለተኛ ጨዋታ ነው::*

4 ሦስተኛው ጨዋታ አራቱን ጠጠሮች መድቦ አራቱንም ጠጠሮች አንዱም ከጭብጣችን ሾልኮ ሳያመልጥ መዝገን ነው:: ይሄ ልብወለድ የሚመስለው በአንደኛው ጨዋታ ነው:: ሁለተኛውን ወደ ልብወለድ መለወጥ አስቸጋሪ ነው:: በአምስት ጠጠሮች ብቻ ሆን ብዬ መጠቀሜም ከዚህ ጋር ይያያዛል:: የዚህ ልብወለድ አወቃቀር እቅድ አለበት:: ቅልልቦሽ ጨዋታው ውስጥ እቅድ ባይኖርም በተወሰኑ ሕጎች የተደነገገና ቀድመን የምናውቀው ደንብ አለ:: ከዛ ደንብ ውጭ ግን እቅድ የለም:: ለምሳሌ ጨዋታውን ገና ስንጀምር ይሄን ጠጠር እመድባለሁ ያንን መቅለቢያ አደርገዋለሁ ብዬ አይደለም:: በነሲብ ነው:: ነሲብነትን አሰራሬ ውስጥ ካስገባሁ የድርሰቱ ስፋት የትየለሌ ይሆናል:: ምክንያቱም የእያንዳንዱ ጠጠር የተመዳቢነትና የቀላቢነት ድቡል መብቱ ቢከበር የሚኖሩት ምዕራፎች ብዛት አምስት ፋክቶርል (5!) ማለት 5 ሲባዛ በ4 ሲባዛ በ3 ሲባዛ በ2 ሲባዛ በ1 ይሆናል:: ውጤቱም 120 ነው፣ ወደ ድርሰቱ ሲተረጎም መቶ ሃያ ምዕራፎች ማለት ነው::

እዚያ ድረስ መሄድ ከባድ ነው:: ቢሰራበት እንኳን ቅርፁን አሳስፈላጊ ወደሆነ አሰልቺ መጠን መንዳት ይሆናል:: ስለዚህ ከውስብስብነት ይገላግለኛል ብዬ የገመትኩት ግማሽ ጨዋታ መጠቀምን ነው:: ግማሽ ጨዋታ ማለት በተራ ቁጥር ሁለት ላይ የተጠቀሰው ዓይነት ማለት ነው::

በዚህ ድርሰት ውስጥ አምስት ጠጠሮች እንደ ገፀባህርያት ቢመስሉ የመቅለቡ ሂደት ደሞ ምዕራፍ ይሆናል:: የመቀ'ለቡ ወይም ቀላቢ የመሆኑ ሂደት ግን ገጠመኝ ነው:: ሕይወት አይመስልም? አንድ ሰፈር ውስጥ ብንወለድ እኛ መርጠን ነው? ት/ቤት መርጠን ብንገባ ክፍላችን ውስጥ ያሉት አይነት ተማሪዎች ያጋጥሙናል ብለን አስበናል? ዴስኩስ? ዳስተሩስ? ያ ቀጫጫ አስተማሪስ? ያቺስ ደስ የምትል እዛ ጋ ያለችው ልጅስ? ባላችንን የተዋወቅንበትን ሰአትና ደቂቃ ሆን ብለን ያሰብነው ነበር? ሶስት ልጆች እንወልዳለን ከነዚህም ሁለቱ ሴቶች ይሆናሉ ብለን ጠብቀናል? ታክሲ ውስጥ ገብተን ስንቀመጥ ጥግ ብቻዋን የተቀመጠችው እርጉዝ ሴትዮ ትኖራለች ብለን ገምተናል? ግን ወልደናል:: አግብተናል:: ተምረናል:: በመጓጓዣ ተጉዘናል::


በአምስት ጠጠሮች እንድጠቀም ተስማምተናል:: አራቱ ነጫጭ ሲሆኑ አንድዋ ጥቁር ናት:: ጥቁርዋ እንደ ቋሚ ቀላቢ ተደርጋለች—ሲጀመር በእጅ የምትያዘው (በድርሰቱ ውስጥ ጌርሳሞት):: ነጮቹ ተቀላቢ ናቸው:: የመጀመሪያው ድርጊት ወለል ላይ ያሉትን ጠጠሮች በዐይኖቻችን ወይም በስሜት ሕዋሶቻችን መገምገም ነው……

# ኅዳግ ማስታወሻ

1 Carnouba wax (ካርኑባ ሰም: )
2 Steady (ቋሚ)
3 transcendental (በረቂቅነቱ ከሁሉ ሃሳብና ቁስ የበላይ )
4 Produce (ማምረት)
5 Brain (አንጎል)
6 Subset (ሰብሴት: ንዑስ ክፍል)
7 Feng shui (ፌን ሹዌ: የቻይናውያን ኪነታዊ ሜታፊዚክስ:: በቀጥታ ትርጉሙ ነፋስ ውሃ ማለት ነው:: እነዚህን ሁለት ባህርያት በመጠቀም ተፈጥሮን ወይም ዓለምን መረዳትና የሰዎችን ሕይወት በዛ ስልት ውስጥ መተርጎም:: ከተፈጥሮ ጋር መስማማትን ደግ አድርገን ብንወስድም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣው እምነት ግን ኢሳይንሳዊ ያደርገዋል)
8 Baby (ሞሳ)
9 Nice (ጥሩ)
10 Golden ratio (ጎልደን ሬሽዮ: ወርቃማ ሚዛን)
11 Flaneur (ዘናጭ የሆኑ የከተማ አውደልዳዮች/ ፈረንሳይ)
12 Date (ቀጠሮ)
13 (የዚህች ሬስቶራንት ስም የሊሊሳ ግርማ 'ኤጭ' የተባለች አጭር ታሪክ ውስጥ ስሟ (ሬስቶራንት ተብላ ባይሆንም) ሰፍሯል::)
14 Headset (አናት ላይ ተደርጎ በጆሮ ማዳመጫ)
15 Skirt (ቀሚስ)
16 Bitch (ትርቡት)
17 Hi (የሰላምታ አጠራር)
18 Bug(የኮምፒዩተር ስራ አደናቃፊ ፕሮግራሞች)
19 Weekend (ቅዳሜና እሁድ)
20 I am intelligent (ብሩህ ነኝ)
21 Package (እሽግ)
22 Surprise (ድንገተኛ በመሆኑ አስደንጋጭ)
23 Successful (የተሳካ)
24 Neodarwinism, The tao of physics and No Logo
25 Save (ያዝ)
26 Culinary (ኩሊናሪ=ምግብን ማድቤትን የሚመለከት)
27 Culinary adventure is my name (የምግብ መብላት ጀብድ ስሜ ነው)
28 Highway (ሰፊ በፍጥነት ብቻ የሚነዳበት ጎዳና)
29 ከቀናስ አድማሱ ግጥም
30 Homeopathist (ሆሚዮፓቲስት)
31 Aesthetics (ስነውበት)
32 Breaking News (ሰበርዜና)
33 GArl friend (የሴት ጓደኛ)
34 Prozac(ማስታገሻ የመድሃኒት አይነት)
35 My dear friend (ውድ ጓደኛዬ)
36 BiologAcal weapon (ተፈጥሮን የሚያውረገርግ መርዛም የጦር መሳሪያ)
37 Mannequin (ማኒኪን=የልብስ ሺያጮች አሻንጉሊት)
38 Foreign Investment (የውጭ መዋዕለ ንዋይ)
39 ሃዳሪ ዘይቤ
40 ልክ እንደ መሳሪያ ከንፈሮቿን በእኔ አቅጣጫ አሞጠሞጠች

———

41 boomerang
42 ስምጥ ሸለቆ
43 ሃምሳ አለቃ
44 ፒን (ደረት ልብስ ላይ የሚሰካ ጌጥ ወይም ምልክት)
45 Dikgat (በአፍሪካነር ቀበሌኛ በጣም ወፍራም:: በቀጥታ ትርጉም ቦርጫም:: ዲክ=ወፍራም፣ ጋት=ሆድ)
46 ልፋካቤ ብቻ የተሰራች
47 Dispatch (አሰማራ)





ሮሆቦት አታሚዎች ስልክ 011 4 169027

ዋጋ 80 ብር